
ዕጭርተኞች

ክማሞ ውድነህ




t.me/OLDBOOKSPDF

ዕድርተኞች

ከ

ማሞ ውድነህ



ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

፲፱፻፹፭

t.me/OLDBOOKSPDF

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
KURAZ PUBLISHING AGENCY

ስልክ
TEL. 11 27 19

መ. ሣ. ቁ.
P. O. B. 30933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

የሽፋን ስዕል — ሉታስ አማረ

t.me/OLDBOOKSPDF

በግራኑዋ ሥር

ግራኑዋ፣ በሦስት ቅርንጫፎች ተከፋፍላ እድጋለች ። የተከፋፈሉት ቅርንጫፎች ደግሞ፣ አንደኛዉ ወደ ሰሜን፣ ሁለተኛዉ ወደ ደቡብ ምሥራቅ፣ ሦስተኛዉ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫዎች አጋድለው፣ እንደ ገና እነርሱም ብዙ ቅርንጫፎች ወልደው፣ የውላጅ ውላጅ፣ የቅጥያ ቅጥያ፣ የመንትያ መንትያ፣ የጭራሮ ጭራሮ አባዝተው ትውልደ ትውልዳቸውን እንሰራፍተው፣ የግመል ቁመት ያህል ከመጠቁ በኋላ፣ እንደገና ተገጣጥመው ችፍግ ብለው ከግራኑዋ ሥር ዝናብ ጠብ እንዳይል የፀሐይም ጨረር እንዳይደርስ ዳስ ሠርተው የወፍ ጐጆዎችም አንጠልጥለዋል ።

የሠፈሩ አዛውንትና ተሳላፊ መንገደኞች፣ ዐረፍ እያሉ የግራኑዋን ሥር መሬት አለስልሰውታል ። የሠፈሩ እንስሳትም ፀሐይ ወይም ዝናብ ሲበረታባቸው ተሰባስበው ይጠለሉባታል ። ባካባቢዋ የእርሷን ያህል የዕድሜ ጌቶች አይሁኑ እንጂ፣ እምስት ባሕር ዛፎችና አንድ ሌላ ባሕረ-መጥ ዛፍም ይገኛሉ ። ያች ግራር ረዘም ያለ ዕድሜ እንዳላት፣ የዕድሜ ጌቶች የነበሩ እየመሰከሩላት ዐልፈዋል ።

እምዬ ምኒልክ፣ በጹርና በአራዊት ተጠቅጥቃ የነበረችውን አዲስ አበባን 'ከነሰውሀ ሰፈርባት' እያሉ፣ ለመኳንንቱና ለየጦር አበጋዙ ሲያቀራምቷት፣ ያች ግራር የበቀለችባት ቦታም የእንዱ ራስ ሠፈር ሆነች ። በዚያም የተነሣ ስለዚያች ግራር ብቻ ሳይሆን፣ በሠፈሩ ስለሆነው ነገር በቃል የወረሱትን ታሪክ የሚናገሩ አዛውንት ሊገኙ ቻሉ ።

በ1940 በመስከረም ወር መጨረሻ ላይ ፣ በዚያች ግራር ሥር ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ከሠፈሩ ነዋሪዎች ጥቂቶቹ ተሰብስበውባታል ፣ ዕለቱ እሑድ ነበር። ሁሉም ከየቤተክርስቲያኑ ተመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ልሶ አፉን አሟሽቶ ፣ በዚያች ዕለት የመሬቱ ባላባት እንዚያን ሰዎች የሰበሰቡበትን ምክንያት ለማወቅ ጢሰኛዉ ሁሉ በጉጉት ይመለከታል ። በስብሰባዉ የተገኙትም በሠፈሩ የሚኖሩት ጢሰኞች ነበሩ ።

በዚያን ዕለት ወጥታ የነበረችው ፀሐይ ደግሞ ፣ በመሬት ላይ በተለይም በዚያች ሠፈር ከተንጠለጠለችበት ሕዋ ሊያ ወርዳት የሚተናኰላት ጠላት እንዳላትና ፣ ያንን ጠላቷን ለማታ ጠል ስትል ፣ ያለ የሌለ ኃይሏን አሰባስባ የወረወረችው ይመስል ፣ የግራሩዋ ቅርንጫፎች እንኳ ሊቋቋሙት ያልቻሉትን ሙቀት መርጨት ጀምራለች ።

በሦስት አግዳሚ ወንበሮች ከሁቀመጡት ከኻያ የማይበልጡ ፣ በዕድሜ ከሠላሳ እስከ ስድሳ የሚደርሱ ተሰብሳቢዎች መካከል ፣ ሰባቱ ሴቶች ነበሩ ።

ከአግዳሚዎቹ ወንበሮች ፈንጠር ብሎ ፣ አንድ ማለፊያና አንድ መናኛ ታጣፊ የዕንጨት ወንበሮች ተመቻችተው ፣ እግሮቻቸው እንዳይንሸራተቱ ሆነው ተተክለው ፣ ጉብ ጉብ የሚሉ ባቸውን ሰብሳቢዎች ይጠብቃሉ ።

"'የምትሰጡኝን ድርሻ ጨምሬአለሁ' ሊሉን ይሆን ዛሬ የሰበሰቡን ?" አሉና ፣ እንዱ ተሰብሳቢ ከአጠገባቸው ለነበሩት ሹክ አሉዋቸው ።

"የት ይቀራል ብለው ? ብዙዎቹ ባላባቶች ሥራዬ ብለው ይህን ነገር ተያይዘውታል" ብለው መለሱላቸው — ጓደኛቸዉ ።

"የመሬት 'ኪራይ ጨምሬያለሁ' ለማለት ታዲያ መች ሰብስበውን ያውቃሉ ?" አሉ ፣ ሦስተኛዉ አዛውንት ።

"ምናልባት ዛሬ ሊያሰፈር ሙን ወይም ሊያስለቅቁን እንደ ሆንስ ?" አሉ የመጀመሪያዉ ሹክ ባይ ። ያ ሥጋት ፣ እንኳን በግራሩዋ ሥር በሠፈሩም በየዕለቱ የሚያንገበግብ ነበር ።

ምንም እንኳን ወጤ ምኒልክ ፣ 'ከነሰውዩ ሰፈርበት' እያሉ ለመኳንንቶቻቸው ቢሰጡም ፣ ከእርሳቸውና ከመኳንንቶቻቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

በኋላ የተተኩት የየመኳንንቱና የየጦር አበጋዙ ወራሾች ፣ ያን ሰፋፊውን ሰፈር ወርሰው የፈለጉትን ያህል ፣ በፈለጉት ዋጋ እየሸጡ ዘመናዊ ኑሮ ሊጀምሩበት ፣ የማይቋረጥ የዓመት ገቢ ለማግኘት ሲሉም ገሚሱን ጢሰኞች አስፈረውበታል ። ታዲያ ግራሩዋና አካባቢዉ ልጅ አድባሩ ለተባሉ ወራሽ ደርሶ ፣ እር ሳቸውም እንደ ቤተ ዘመዶቻቸው በቤታቸው ዙሪያ ጢሰኞች አስፍረዋል ።

ልጅ አድባሩ ፣ በጥዋት የታረደችውን ጠቦት ፣ ዱለትና ጥብስ ተቋድሰው ፣ ማታዉን በማር እሽት ተልሶ ባደረ ጠጅ አወራ ርደው ፣ ከቤታቸው እስቲወጡ ድረስ ፣ ጢሰኞቻቸው በግራሩዋ ሥር ሆነው በሐሳብ ሲዋልሉ ፣ ሠፈርተኞቹም በየልባቸው ልጅ አድባሩን ሲማጠኑ ወደ እኩለ ቀን ተቃረቡ ።

ቅዳሜ ማታ ፣ የልጅ አድባሩ አሽከሮች በየቤታቸው እየ ሔዱ ፣ 'ለነገ ጥዋት ከቤተ ክርስቲያን መልስ በግራሩዋ እንድ ንገናኝ ፤ ጉዳይ ስላለኝ እንዳትቀሩ ፤ ወደ ሌላም እንዳትሔዱ ብለዋል' እያሉ ያስጠነቀቁዋቸው ተሰብሳቢዎች ፣ ከቤተ ክርስ ቲያን መልስ በየቤታቸው ገባ-ገባ ቢሉም ለሰብሰባው ተቻኩ ለው ወጡ ።

ስለዚህ የከረረው የረፋዱ ፀሐይ ፣ ሐሳብ ፣ ሥጋትና ከየ ሆዱ ጩኸት ጋር ተባብረው ቁጭ ብድግ ያሰኙዋቸው ጀመር።

ቅዳሜ ማታ ፣ የልጅ አድባሩን ትእዛዝ ለተሰብሳቢዎቹ ከነ ገሩት የቤት አሽከሮች አንዱ ፣ ሁለት ጊዜ ተመላልሶ የጭሰኞ ቹን መሰብሰብ ተመልክቶ ለጌታው ነገረና ፣ ልጅ አድባሩ ከቤታ ቸው ወጥተው ወደ ግራሩዋ አመሩ ።

ቤታቸው ብዙም ሩቅ አልነበረም ። ዐሥር ደቂቃ እንኳን አይወስድም ። የእርሳቸውን ብቅታ የተመለከቱት ተሰብሳቢ ዎች መቁነጥነጥ ጀመሩ ። 'የመሬት ኪራይ ጭማሪ ይሆን ? ወይስ ቦታውን ስለ ሸጥኩት ልቀቁ ይሆን ?' ጢሰኞቹ በዚህ ሐሳብ ላይ እንዳሉ ፣ ልጅ አድባሩ ወደ ግራሩዋ ተቃረቡ ። በዚህ ጊዜ ጢሰኞቹም ተነሡና ቆሙ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ልጅ አድባሩ ፣ ሰልከከ ያለ መልክ ፣ መካከለኛ ቁመትና ውፋሬ ያላቸው ናቸው ። በአለባበሳቸውም ዘመናዊነታቸውን ለማስመስከርና ከመሰሎቻቸውም አንሰው ላለመታዬት ሆን ብለው ተጠንቅቀውበታል ። በዕድሜ ከወርባ ዓመት የደረሱ ነበሩ ። ከኢጣሊያ በፊትና በኢጣሊያም ጊዜ የነበረውን 'ትም ህርት' ቀሥመዋል ። ሠፈሩ የአያታቸው ነው ። ስለዚህም በሠፋሪው ዘንድ የተፈሩ ናቸው ። መሬት እየለኩ እንደ ዐቅሙ የሚ ያከፋፍሉ ፣ ለወደዱት የመሬት ኪራይ የሚቀንሱ ፣ ከፈለጉም 'ምሕ ረት' የሚያደርጉ ፣ ካልመሰላቸውም ጢሰኛውን ከነኮተቱ የሚ ያባርሩ ናቸው ። በወርባ ዓመት ዕድሜያቸው ሁለት ጊዜ ተድ ረው ፣ ሁለቱንም ሁለትና ሦስት አስወልደው አባረዋል ። ሦስ ተኛም አጭተው ሊዳሩ መደገስ ይዘዋል ። ቢያንስ የዓመትና የሁለት ዓመት ጠጅ ማቅረብ ስለ ነበረባቸው ድግሱ ከተጀመረ ቆይቷል ። እስከዚያውም ማዝገሚያ ዕቁባቶቹ በሠፈሩ ውስጥ ቦታ በነጻ እየተሰጣቸውና ቤት እየተሠራላቸው ተቀምጠዋል ።

ወደ ግራሩዋ ሲቃረቡ ፣ ከተሰብሳቢዎቹ ጢሰኞቻቸው አም ስቱ እዛውንቶች ከነበሩበት ወደ እርሳቸው ሔደው ፣ በእጆቻቸው መሬት እየነኩ እጅ ነሡዋቸውና አጅበው ወደ ግራሩዋ ወሰዱ ዋቸው ።

ልጅ አድባሩ ከወንበራቸው ሲቀመጡ ፣ ተሰብሳቢዎቹም እንዲቀመጡ የቤት አሽከራቸው በእጆቹ ምልክት አሳየ ። ከልጅ አድባሩ ወንበር አጠገብ የነበረችውን ተራ ወንበር አሽከራቸው ሳብ አድርጎ ፣ ከወደ ኋላቸው አስቀመጠና የልጅ አድባሩ ነገረ ፈጅና ጢሰኛ አስገባሪ የሆኑት ፣ አቶ አርጋው እንዲቀመጡበት ምልክት ሰጠ ። አርጋው ጠየም ያሉ ፣ ፊተ ሞላላ ፣ ቁመተ ረዥም ናቸው ። ትውልዳቸውና ዕድገታቸው በአድባሩ እናት ቤት ነበር ። እመቤታቸው ከሞቱ በኋላ ግን ፣ የልጅ አድባሩ አሽከር ሆነው የርስታቸውና የንብረታቸው ወኪል እስከ መሆን በቅተዋል ። ከጌታቸው ልዩ ልዩ ገቢም ላይ እየቀነጣጠቡ በሚ ያገኙት ገቢ ፣ በጉን እህልና ቆዳ እየነገዱና እያስነገዱ ፣ የጌታ ቸውን ፊት እንጂ ፣ እጅ ሳያዩ ለመተዳደር ችለዋል ።

"የተጠሩት ሁሉም መጥተዋል ?" አሉና ልጅ አድባሩ በሰ ተኋላቸው የተቀመጡትን አቶ አርጋውን ጠየቁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እርሳቸውም ፣ ከሳሪያን ኮታቸው ኪስ ወረቀት አውጥተው እየተመለከቱ ፣ ወደ ተሰብሳቢዎቹም ዐይኖቻቸውን እየወረወሩ ሲያስተያዩ ቆዩና ፣ "ሦስት አልመጡም" አሉ ።

"ማለፊያ ነው ፣ ከተገኙት ጋር ጉዳዩን እንነጋገርበታለን" አሉና ልጅ አድባሩ ጉረሮአቸውን አለስልሰው ተሰብሳቢዎቹን ንም ገለማምጠው ፣ "ጉዳዩ እንዲህ ነው" ብለው ንግግር ሲጀ ምሩ ፣ ተሰብሳቢዎቹም ዐይኖቻቸውን ወደ እርሳቸው መወርወር ጀመሩ ።

"ሁላችሁም እንደምታውቁት ፣ አዲስ አበባ የሁሉም አገር ፣ የሁሉም ቤት ናት ። አማራዉ ፣ ትግሬዉ ፣ ጉራጌዉ ፣ ሻንቅ ላዉ ፣ ዶርዜዉ ፣ ሱማሌዉ ፣ ፈረንጅና ዓረቡ ፣ ሁሉም በአ ንድነት በጉርብትና ፣ በጋብቻ ፣ በጥቅም ተሳስሮ ይኖርባታል ። ይሁን እንጂ ፣ ሁሉም የየራሱ ልምድ ፣ ወግ ፣ ሥርዓት ስላለው ፣ እንደየባሕርዩ እየተጋገዘ ይኖራል ። በዚህም መሠረት የአ ዲስ አበባ ነዋሪ ሁሉ የየጐሣውን ፣ የየቀዬውን ልምድና ወግ አምጥቶ መሥርቶታል ። በዚህ ረገድ በመርካቶ ፣ በተክለ ሃይማ ኖትና በሌሎችም ሠፈሮች ከሚታዩት ልማዶች እንደ ዕድርና ዕቁብ የመሳሰሉት ሕዝቡን በብዙ ነገር ሲጠቅሙት ይታያሉ ።

"የጉራጌ ተወላጆች የሆኑ ሁሉ ፣ዕድርና ዕቁብ አቋቁመው ይረዳዳሉ ፤ ይቀባበራሉ ። ያውም ለመሰብሰብና ለመነጋገር የጣ ሊያናኝን ቁጥጥር ፈርተው ፣ ይገናኙና ይነጋገሩ የነበሩት በድ ብቅና በዕዋ ስም ፣ በጊዮርጊስና በተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲ ያናት ፣ በየጠጁና በየጠላዉ ቤት ነበር ። ይህን ሁላችንም የምናው ቀውና ያየነው ነገር ነው ። በጣሊያን ጊዜ የነበረውን የምታስ ታውሱት ነው ። ሕዝብ በብዛት መሰብሰብና መነጋገር አይቻ ለውም ነበር ። በየቤተ ክርስቲያናቱ እንኳ ለቀብር ፣ ለጸሎት ፣ ለጥምቀት ሕዝቡ ሲሰበሰብ የነበረውን የፊርማቶሪ ብዛትና የወ ታደር ከበባ የምታውቁት ነው ። ያ ጊዜ ዐልፎ ነጻነታችንን ካገ ኘን ወዲህ ደግሞ ፣ ይኸውና በየመንደሩና በየቀዬው ዕድር መቋ ቋም ጀምሯል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"በጣሊያን ጊዜ፣ በፅዋ ማኅበር ስም መረዳጃና መጠያየቂያ ካድሬዎችና ቀዬዎችና ሠፈሮች መካከል የኛ አንዱ ነበር። ጣሊያን በገባ በሦስተኛዉ ዓመት ነበር፣ በሠፈራችን የሚገኘውን የፅዋ ማኅበር አባቶቻችንና እናቶቻችን አቋቁመው ሲረዳዱበትና ሲደጋገፉበት የነበረው። የተቸገሩትን በመርዳት፣ የሞቱትን በመቅበር፣ ያዘኑትን በማጽናናት የፅዋ ማኅበራችን የሚገባውን ሥራ ሁሉ አድርጓል።

"ምንም እንኳን አባቶቻችን 'ሲሞቱ ገመድ፣ ሲሾሙ ዘመድ አይታጣም' የሚል ምሳሌ ቢኖራቸውም፣ በከተማችን ቀባሪ እያጡ በየቤታቸው ሬሳቸው እየሸተተ የተገኙ ብዙ ናቸው።

"እንግዲህ ወደ ፍሬ ነገሩ ስንገባ፣ እስከ ዛሬ ድረስ በፅዋ ማኅበር የቆየውን የሠፈራችንን ማኅበር ወደ ዕድር እንድንለውጠው የሚቻለውንና የሚገባውን ሁሉ፣ ሁላችንም ተመካክረን እገሌ ተገሌ ሳንል ባንድነት ተወያይተንበት፣ በሌሎች ሠፈሮች እንደሚደረገው ሁሉ እኛም እንድናቋቁም ነው። ጉዳዩ የሁላችንም ስለሆነ ነእዚህ የተገኛችሁት መክራችሁበት፣ ሰዎችም መርጠንበት እንድንረዳዳበትና እንድንቀባበርበት ማድረግ ይገባናል" አሉና መሐረባቸውን አውጥተው ግንባራቸውን ወለወሉ።

በተሰብሳቢዎቹ ላይ ሰፍኖ የነበረው ጭንቀት፣ሐሳብና ሰመመን ቀስ በቀስ መግፈፍ ጀመረ። ግን፣ ያን እፎይታ ሠፈርተኞቹ አልሰሙም ነበርና፣ ከግራኑዋ ሥር የተገፈፈው ጭንቀት በሠፈሩ ነዋሪዎች ላይ ገና እንዳጥበበ ነበር።

የልጅ አድባሩ ንግግር ሲያበቃ፣ የተሰማ የደስታ ጭብጨባ ወይም እልልታ አልነበረም። ይህም በመሆኑ ነበር፣ ሠፈርተኛዉ በየቤቱ መስኮትና በራፍ ብቅ ጥልቅ እያለ፣ ስብሰባውን ሲቃኝና መጨረሻውን በጉጉት ሲጠባበቅ የነበረው።

ከመጠነኛ ዝምታና መተሻሸት በኋላ፣ መጠነኛ ሹክሹክታ ፈገግታና ጉሸሚያ ሆነ። ልጅ አድባሩም የተሰብሳቢዎቹን እፎይታ፣ ሹክሹክታና ገጽታ ተራ በተራ ተመለካከቱ። ከእርሳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቸው ንግግር በፊት በተሰብሳቢዎቹ ላይ የነበረውን ጭንቀት ባይረዱትም ፣ ከንግግራቸው በኋላ በታየው ስሜት ሐሳባቸው ተቀባይነት እንዳገኘላቸው ሊገምቱበት ስለ ቻሉ ፣ ቅጭም ብሎ የነበረው ገጽታቸው ወደ ፈገግታ ተለወጠ ።

የልጅ አድባሩን ሐሳብ ለማሞገስና እርሳቸውንም ለማመ ስገንና ለመመረቅ የቸኮለ ተሰብሳቢ አልነበረም ። ሁላቸውም ከአደቀቃቸው ሰመመን ገና አልወጡም ነበር ። እፎይታቸው በግዙፍ አካላቸው ፣ በረቂቅ ሕሊናቸው ሠርፆ ገና ልቦናቸውን አልመለሰላቸውም ነበር ።

በዚህ ጊዜ ፣ አቶ አርጋው ተነሡና ጉሮሮአቸውን አለስል ሰው ከልጅ አድባሩ ፈቀቅ ብለው ፣ "አንድ ጊዜ አዳምጡኝ ፣ እንደማመጥ" አሉ ፤ "የዛሬዋ ዕለት የተባረከች ናት ። ሰማችሁ ወንድሞቼና እኅቶቼ ! በሌሎች ሠፈሮች ያሉ ባላባቶች ገባሮቻ ቸውንም ሆነ ጢሰኞቻቸውን ፣ 'ስጠኝ ፣ እርዳኝ ፣ ታዘዘኝ ፣ ቀና ብለህ አትየኝ' ከማለት በቀር እንደዚህ በአንድነት ሰብስበው 'እንተባበር ፣ እንረዳዳ ፣ የተቸገረን እንርዳ ፣ የሞተን እንቅበር' ብለው እንደማያውቁ ሁላችንም እናውቃለን ። ከቡር ጌታችንና ወንድማችን ልጅ አድባሩ ግን ፣ ይኸውና እስከ ዛሬ በወረዳችን ቀርቶ በየትም ተሰምቶ የማያውቅ አዲስ ሐሳብ አመንጭተው እንደዚህ ያለ አስገራሚ ግጎበር እናቋቁም ማለታቸው ለኛ በአ ርሳቸው ጥማ ፣ በእርሳቸው ጥላ ለምንገኘው አስበውና ተጨን ቀውልን እንጂ ፣ እርሳቸውማ ምን የሚጐድላቸውና ምን የሚ ቸግራቸው ሆኖ ነው ? አሁንም ይህን የተቀደሰ ሐሳባቸውን ተቀ ብለን እንጠቀምበታለን ብለን ስለ ተማመንበት ፣ በሠፈሩ የታ መቃችሁትን ፣ ነገር ይገባችኋል ፣ ነዋሪውን ሕዝብ ትመከሩታ ላችሁ ብለን የተማመንባችሁን ነው የጠራናችሁና ምክሩበት ፤ ዝከሩበት ። ሌሎች ባለጢሰኞች 'የመሬት ኪራይ ጨምረናል' እያሉ ጢሰኛውን በሚያስጨንቁበት በዛሬው ጊዜ ፣ የኛ ጌታና ወንድም ግን" ... ብለው ንግግራቸውን ሳይገቱ ፣ ልጅ አድባሩ ዘወር ብለው ጠቀሱዋቸውና ፣ አቶ አርጋው ጠጋ ሲሉአቸው ፣ "የመሬት ኪራይ ጭማሪ ጉዳይ ወደፊት የማስብበት ነውና አሁን ማንሣት አያ ስፈልግም ። ስለ ሌላው ስለ ሌላው እንደ ጀመርከው ተናገር" አሉ ዋቸው ፣ በሹክሹክታ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አቶ አርጋው ቆመው ሲደሰኩሩበት ወደ ነበረው ቦታ ተመ
ለሱ ። ደመ - ነፍሳቸውን ተገትረው ፣ ቀጥለው የሚናገሩት ጠፉ
ቸውና ፣ ልጅ አድባሩን ሊያስደስትላቸው የሚችለውን ፍሬ ነገር
የግራርዋ ቅርንጫፎች የሚያቀብሏቸው ይመስል ፣ ወደ ላይ እን
ጋጠው ሲማጠኑ ቆይተው ፣ እንደገና ተሰብሳቢዎቹን እየተመ
ለከቱ ፣

"ዕለቷም ብሩክት ፣ ጌታችንም ብሩክና ቅዱስ ናቸው ።
ከዚህ የበለጠ የጥድቅ ሥራ በየትም ፣ መቸም ታይቶና ተሰምቶ
አይታወቅም" አሉና ተቀመጡ ።

"በሉ እንግዲህ ፣ እንምከርበትና የሚሆን የሚሆነውን እና
ድርግ" አሉ ልጅ አድባሩ ፣ ተሰብሳቢዎቹን ተራ በተራ እየቃኙ ።

ቀደም ብሉ ሲንሾካሾኩ ከነበሩት እንዱ ተነሡ ። "እር
ጅና ብቻህን ና" የሚባለው ምሳሌ የሠመረላቸው ይመስላሉ ።
ጸጉራቸው የግራዋ አበባ የረገፈበት ከመምሰሉ በቀር ጤናማ
ናቸው ። ቁም ነገር በቀልድ አዋሕደው በመተቸት ረገድ በሠ
ፈሩ ስመ - ጥር ናቸው ። ይህን የሚያውቁላቸው ተሰብሳቢዎ
ችም ከአንደበታቸው የሚፈልቁትን ቃላት ለመልቀምና ለመ
ተርጉም ሽቅብ ይመለከቷቸው ጀመር ።

"መቸም ጌታዬ ፣ እኛ እንኳን ተሰብስቡ ስንባል የጠረጠ
ርነው ሌላ ነበር ። መኳንንቱና ባላባቱ ሁሉ ፣ የመሬት ኪራይ
በነጋ በጠባ እየጨመረ ጢሰኛውን ሁሉ ማነቆ ስለ ጣለበት ፣
የኛም ተራ የደረሰ መስሉን ወይኖቻችን ግርሽጥ መምሰል
ጀምረው ነበር ። 'ማታ በማሩ የተከማቸ ገንዘብ ቀን ሲናድ
ይውላል' ተብሉ እንደ ተነገረው ፣ ምንም እንኳን በጢሰኛዉ
ላይ ኪራይ እየጨመሩ በገንዘብ ላይ ገንዘብ ቢያነባብሩበትም
ቁምነገር ሲሠሩበት አናይም ። በየአራዳው ሥርቻ ነው የሚበ
ተነው" ብለው እንደ ተናገሩ ልጅ አድባሩ አቋረጡአቸውና ፣

"ሰሙ ወይ አቶ እንደሻው ፣ የተሰበሰብነው ለሌላ ፣ እርስዎ
የሚናገሩት ሌላ ። 'ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ' እንዳይሆ
ንብዎ ስለምናቋቁመው ዕድር ሐሳብዎን ቢናገሩ አይሻልም ?"
አሉዋቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እውነት ነው ፣ እውነት ነው ። ያልተጠየቁትን መለፍ ለፍ ምን ያደርጋል ?" አሉ አቶ አርጋውም ።

"ይሁን ማለፊያ ነው ፣ ወደ ሥረ ነገሩ ልገባ ነኝ" አሉና አቶ እንደሻው ፣ ልጅ አድባሩን ጐንበስ ብለው ይቅርታ ጠይቀው ፣ አቶ አርጋው ላይ እንደ ማፍጠጥ አሉና ንግግራቸውን ቀጠሉ ።

"ቀደም ሲል አባቶችም የመሠረቱት የፅዋ ማኅበር የተ ቸገረን በመርዳት ፣ ያዘነን በማጽናናት ፣ የተጣላን በማስታረቅ ብዙ ብዙ ሥራ ሠርቷል ። አሁንም ዕድር ተቋቁሞ እንረዳዳ ፣ በተሻሻለ አኳኋን እንሥራ ማለትዎ ፣ ለሠፈሩ ፣ ለኛ አስበው ነው እንጂ እርስዎማ ምን ጐደለዎ ? የሰይጣን ጆሮ እይስማውና ፣ በቤትዎ ክፉ ቢደርስ መላው አዲስ አበባ ከዳር እስከ ዳር ወገ ንዎ ፣ ዘመድዎ ፣ ታዛሾዎ ነው ። ምን ይቸግረዎታል ? ምንስ ይከፋዎታል ?

"የዛሬው ሐሳብዎ ለሠፈራችን ቀርቶ ለመላው አዲስ አበባ ለድፍን አገሩ የሚበጅ ፣ የሚወደድና የሚከበር ስለሆነ ፣ በኛ በኩል ቅሬታ ሳይሆን ደስታ ፈጥሯልና በሥራ እንድናውለው የሚገባው ነገር ሁሉ በቶሎ ቢደረግ እንፈቅዳለን" ብለው ተቀ መጡ ።

ልጅ አድባሩ ተፍነከነኩ ። "እዩ አንደበት ! እዩ አነጋገር !" ብለውም አሞገሱዋቸውና ቀጠል አድርገው ፣

"ፍሬ ነገሩን ደርሰውበታል ። ባባቶቼ ሠፈር የሞቱ ሰው ቀባሪ እንዳያጣ ዋናው ምኞቴ ነው ። ሠፈራችንን ደግሞ መን ከባከብ አለብን ። እያደር የሚለማ ሠፈር ፣ በየቀኑም መሬት ዎራን የሚለው ሕዝብ እንደ ጐረፈ ነው ። ታዲያ ነዋሪው እየ በዛ ሲሔድ ፣ የሚረዳዳበትንም ሥራ ሁሉ አብሮ ማየት ይገ ባል ። እንግዲህ በጉዳዩ ካመናችሁበት ሕዝቡን የሚያስተባብሩ የሚቆጣጠሩ ፣ ማንኛውንም ነገር ሁሉ የሚሠሩ ከዚሁ ከእና ንተ መካከል ሰዎች ምረጡና ሥራው እንዲጀመር " አሉ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሁላችንንም የሚያውቁን እርስዎ ነዎት ። ከመካከላችን የሚተማመኑባቸውን ቢመርጡልን አይሻልም ?" አሉ አቶ እንደሻው ።

"ማለፊያ ሐሳብ ነው ፣ ይስማማናል" አሉ አንዱ ተሰብ ሳቢ ።

"ይሁን ፣ ይሁን ፣ የሚበጀው ይሽው ነው" አሉ ሌሎችም ተሰብሳቢዎች ።

ልጅ አድባሩ ፣ አቶ አርጋውና አቶ እንደሻውን ጠቀሱና ከተንሾካሾኩ በኋላ ፣ "እንግዲያው በኔ በኩል መምሬ በዕውቀቱ ፣ አቶ አርጋው ፣ አቶ እንደሻው ፣ አቶ ግዛው ፣ ወይዘሮ ፈትለወርቅ ፣ የ፯/አለቃ ከበደ ፈቃዳቸው ቢሆንና ቢሠሩ የሚሻል ይመስለኛል ። እናንተስ ምን ታስባላችሁ ?" ብለው ተሰብሳቢዎቹን ተመለከቱዋቸው ። 'ይሁን ፣ ይሁን' አሉ ተሰብሳቢዎቹ ።

"እንግዲህ ደንቡን አዘጋጅተን ፣ እያንዳንዱ ዕድርተኛ የሚከፍለውን ወስነን ፣ በዳኝነት ፣ በጸሐፊነትና በገንዘብ ያገር ነት የሚመደቡትንም መርጠን ስናበቃ እናስታውቃችሁና ሥራው ይጀመራል" አሉ ልጅ አድባሩ ።

"ጌታዬ! እንድ ነገር ላስታውስ ፣ ይፈቀድልኝ" አሉ አቶ እንደሻው ።

"ስለምን ነበር ?" አሉ ልጅ አድባሩ ።

"ጌታዬ እንደሚያውቁት ፣ ድሮ ጐላ ሠፈር እኖር ነበር ። ታዲያ በሠፈራችን ነዋሪ የነበረ ፈረንጅ ፣ የሚላላከው አሽከር ነበረው ። ቀልጣፋ ፣ ንቁ ፣ ለሁላችንም ታዛዥ ነበር ። የሚሯሯጥባትም ብስክሌታ ነበረችው ። ከዕለታት አንድ ቀን በብስክሌታው ሲሮጥ ከመኪና ጋር ተጋጭቶ ወዲያውኑ ሞተ ። እኛም እንደ ሰማን ተሯሩጠን ሬሳውን ለመውሰድ ስንሔድ የሙሴ ተራስ ሠፈር ነዋሪዎች ሬሳውን አንስተም ይሉናል ። ምክንያቱን ብንጠይቅ ፣ 'ሟቹ ዕድርተኛችን ስለሆነ የምንቀብረው እኛ ነን' ብለው እምቢ አሉን ። 'ዕድር ማለትሳ ምንድን ነው ?'

t.me/OLDBOOKSPDF

ብለን ብንጠይቃቸው ፣ ምንነቱን ሥርዓቱን ነገሩን ። ከዚያ በኋላ እኛም በጐላ ሠፈር ዕድር አቋቁመን ፣ ዳኛም ገንዘብ ያዢም መረጥንና 'ቸንቶ ቸንቶ ሊሬ' እያዋጣን ማስቀመጥ ጀመርን ። ገን ዘብ ያዣችን የነበሩትም አዛውንት ነገሩ የገባቸው ነበሩና የጣ ሊያኑን ሊሬ በጥሬ ብር እየለወጡ ያስቀምጡ ነበር ። በመካከሉ ታመሙና ሞቱ ። ለካ በኑዛዜያቸው ፣ 'ዕድርተኞች ያዋጡትን ሰማንያ ብር ከገንዘቤ ጋር አስቀምጫለሁና ከፈሉልኝ ፣ እደራ ፣ በወዲያኛው ቤት እንዳታስጠይቁኝ' ብለው ኑሮ ፣ ወራሾቻቸው ያዋጣነውን ገንዘብ ሰጡን ። ወዲያው ሌላ ገንዘብ ያዥ መረ ጥን ። መምሬ ኃይሌ ይባላሉ ። እንደ ጀመርነው 'ቸንቶ ቸንቶ ሊሬ' ስንከፍል ቆዩን ። ወዲያው ጦርነት ሆነ ። ጣሊያን ተሸንፎ ሲወጣ ሊሬው ዋጋ አጣ ፤ ወዲያው ረከሰ ። መንገዱ ሁሉ ሊሬ ሆነ ። እኒያ መምሬ ኃይሌም ከኛ ሰፈር ሲለቁ ገንዘባችንን ይሰጡን ብንላቸው ፣ ያን ሊሬ ሰብስበው ሰጡንና ጥሬ ብራችንን አስቀሩ ብን ። እኛም ፣ 'የሺ ሀብቱን ፣ ያንድ ሚስቱን' እንዲሉ ፣ ተስ ብስበን ተንጫጭተን ቀረን እንጂ ፣ ሌላ አላነሣንም አልከሰስ ንም ። አሁንም የሆነ እንደሆነ ...'' ብለው ተናግረው ሳያ በቁ ፣

''አሁንም መምሬ በዕውቀቱን ለገንዘብ ያዢነት እንዳት መርጡ ነው የሚሉት ?'' አሉ ልጅ አድባሩ እየሣቁ ።

''አላልኩም ፣ አልወጣኝም ። ሌላ ሰው ከምንመርጥ እር ስዎ ለምን አገሌ ይሁን ብለው የሚያምኑትን ሰው አይመርጡ ልንም ማለቴ ነኝ'' አሉ አቶ እንደሻው ።

''የዕዋ ማኅበራችንን ገንዘብ ሲያስቀምጡልን የኖሩት ጌታ ችን እርስዎ አይደሉም ? የዕድሩንስ ገንዘብ ቢይዙልን ምናለ ?'' አሉ መምሬ በዕውቀቱም ።

''ማለፊያ ሐሳብ ነው'' አሉ አቶ እንደሻው ፣ ''ድፍረት ይሆ ናል ብዬ ነው እንጂ በዚህ ነገር ከጌታችን ሌላ መቸም ፣ ሌላ መቸም ማንንም እንደማናገኝ ተረድቸዋለሁ ። በገዛ ርስትዎ ፣ በገዛ ጢሰኛዎ ፣ በገዛ ዕድርዎ ሌላ ማን ሊመጣ ነው ? ለኛ ብለው የጀመሩት ነገር ስለሆነ ፣ መሠረቱን አሳምረው ያስቀምጡልን እንጂ ።''

t.me/OLDBOOKSPDF

"ግዴለም ፣ ይህ እያወዛግበንም ። አስቤ የተነሣሁበት ጉዳይ ስለሆነ አብሬያችሁ እሠራለሁ ። ብቻ የሠፈሩ ሕዝብ በጉዳዩ አምናበት ዕድርተኛ እንዲሆን ማግባባትና ማስረዳት ያስፈል ጋል ። ባንድ ሰው ትከሻ ላይ ጭኖ ዝም የሚባልበት ጉዳይ ያለ መሆኑን ተረዱልኝ" አሉ ልጅ አድባሩ ።

"ይኸማ ከእንግዲህ የእርስዎ ሥራ ብቻ መች ይሆናል ?" አሉ አቶ እንደሻው ። "የየአንዳንዳችን ጉዳይና ኃላፊነት ነው ኮ ! ደግሞስ በሠፈራችን ፣ በመካከላችን እየኖረ ማነው በዚህ ነገር የሚያንገራግር ? ምን ቢቆርጠው ዕድር አልገባም ይላል ?"

"ማለፊያ ነው ፣ እንዳሉት ይሁን ። ግን እያንዳንዱ ዕድር ተኛ የሚያዋጣውስ ስንት ቢሆን ይሻላል ?" አሉ ልጅ አድ ባሩ ።

"ለፅዋ ማኅበራችን የምናዋጣው የሚቀር ከሆነ ፣ በወር ሽልንግ ሽልንግ ብናዋጣስ ?" ብለው ወይዘሮ ፈትለወርቅ ጠየቁ ።

"በነበረው ይቀጥል" አሉ አቶ አርጋው ።

"እይሆንም ፣ ይበዛል" አሉ አቶ እንደሻው ። "ባይሆን ለመጀመሪያ ጊዜ በወር ሰሙኒ ሰሙኒ እየጣልን ፣ ሰው ሲሞት ደግሞ ዐሥር ዐሥር ሣንቲም እያዋጣን ለቀብር ማስፈጸሚያ ብንመድብ ይሻላል ።"

"ሰው እንዳይማረር ለመጀመሪያ ጊዜ የወር ክፍያውንም መዋጮውንም ዐሥር ዐሥር ሣንቲም ብናደርገውስ ?" አሉ መምሬ በዕውቀቱ ።

"አይከፋም ፤ ለጊዜው በዚሁ እንጀምረውና ፣ ሰው ሲለ ምደውና ሲፈቅደው ይለወጣል" ብለው ልጅ አድባሩ አጸደቁት ።

አቶ እንደሻው ተነሥተው ፣ "እንግዲህ ሥራውን እንከፋ ፈለውና ሰው ይመደብበት ። በሌሎች ዕድሮች እንደሚሠራው በኛም እንዲሠራበት ለማድረግ ፣ የሚሆን የሚሆን ሰው እንዲ, መረጥ ማድረግ አስፈላጊ ነው ። ስለዚህ አሁኑኑ ጌታዬ ባሉበት ...' ብለው እንደ ተናገሩ ድንገተኛ ጩኸት አቋረጣቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"አሄሄ! ጌታው እድባሩ፣ ደግሞ ምን ውለዱ ትላቸዋለህ? እነርሱስ ካልጠፉ ባላባት ያንተ ጢሰኞች ይሁኑ? ፈርዶባቸው ነው፣ ፈጣሪያቸው ረግሟቸው ነው። እስካጥንታቸው ድረስ ሊፋቁ ካንተ የተጠኑ ያሳዝኑኛል። መንግሥት ቢሾምህ የድሀ ዶሮና ሠንጋ ጨረስክ። እሁን ደግሞ የጢሰኞችህን ልብስ ልትገፍ ነው?" እያለ እየለፈለፈ አንድ መካከለኛ ዕድሜ ያለው እንደ ነገሩ የሰበሰ ሰው ወደ ተሰብሳቢዎቹ ቀረበ።

"ደባልቀው፣ ከዚህ ግድም አትጠፉም? ያለዚያ አስራ ከበርሜል ውሃ ነው የምጨምርህ። ምስህን ታውቃት የለም?" አሉ አቶ እርጋው፣ ሊያባርሩት ወደ እርሱ እየሔዱ።

"ኧከከከከ! የመኳንንቱ አቃጣሪ ፈትለወርቅም መጥታ ለችና!" ብሎ ሲናገር፣ አቶ እርጋው ሊይዙት ሲጠጉት፣ ድንጋይ አነሣና ፈንጠር ብሎ፣ "እንዱ አቃጣሪስ አንተ አይደለህም? የመሬት፣ የሴት፣ የጉቦ አቃጣሪ" አለና ሲሸሽ ሲል፣ አቶ እርጋው ድንጋይ አነሡበት።

ደባልቀው በሠፈሩ የታወቀ ወፈፌ ነው። በርስት ሙግት ከቤቱ እንደ ወጣ ዐብዶ እንደ ቀረ ይነገርለታል። ሲነሣበት ሲነሣበት የባለርስቶቹንና የባለጸጋዎቹን ነውር ሁሉ ይለፈልፋል።

"'ዕብድና ገር የታየውን ይናገራል' ተብሏልና ይተዉት፣ ልማዱ ነው ይለፍልፍ" አሉ አቶ እንደሻው ለመገላገል ብለው።

በደባልቀው አነጋገር የበገኑት ወይዘሮ ፈትለወርቅ ግን፣ 'የዕብድ ገላጋይ ድንጋይ ያቀብላል' የሚባለው በእርስዎ ደረሰ። እንደዚህ በየአደባባዩ ስማችንን እያብጠለጠለ ምኑን ነው ይተውት የሚሉት? ይዞ እንደ ልማዱ መውቃት ነው እንጂ" አሉ።

"ጥራው ወዲህ! ደባልቀው፣ ና! የጠጅ መጠጫ አይደለም የፈለግኸው?" አሉ ልጅ እድባሩ።

"ማታ ፈትለወርቅ ቤት በጓሮ በር ስትገባ እመጣለሁ" አለ ደባልቀው፣ በአቶ እርጋው ላይ ያነሣባቸውን ድንጋይ እየጣለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"አንተ ምናምንቴ እትሔድም ከዚህ!" አሉ አቶ አርጋው ከቆሙበት ሳይነቃነቁ ።

"አርጋው ፣ ሚስትህንኮ ፈትለ ወርቅ ለጌታህ እቃጥራልን ለች" አለና ደባልቀው ሲሮጥ ፣ አቶ አርጋው ድንጋይ ሲመ ረውሩበት ፣

"ይዘህ እታመጣልኝም ነበር ፣ አንጀቴን የማርስውን" አሉ ልጅ አድባሩ ።

"ይኸ ቀባጣሪ አውደልዳይ ፣ ሥራ ጠልቶ ፣ እያታለለ መኖር የለመደ" እያሉ ወደ መቀመጫቸው ተመለሱ—አቶ አርጋው ።

"በሉ እንግዲህ ፣ ይህ ቦታ መስብሰቢያችን ይሆናልና የግራሩዎ ዙሪያ እንዲታጠር ፣ ጽዳቱ እንዲጠበቅ" ብለው ልጅ አድባሩ ትዕዛዝ ሰጡና ፣ ሊሔዱ ተነሡ ።

* * *

'የልጅ አድባሩ ሠፈር ዕድር' የመቋቋሙ ዜና ከሠፈሩ ዐልፎ ከወረዳው ማስተጋባት ጀመረ ። በተለይ ደግሞ በቤተ ዘመዶቻቸው ዘንድ ቅናትና እልህ ፈጠረ ። የአያታቸውን ሠፈር ከተቀራመቱት ወራሾች ፣ ኩታ-ገጠም የነበረውን ሠፈር የወረሱት እጉታቸው ፈታውራሪ እርገጣቸው በይበልጥ ጮኩ!

'እንዴት እኔ እያለሁ እኔን ሳያማክር! ምን ቢያስብ ነው ሕዝብ ሰብስቦ ፣ "ዕድር እቋቁሜያለሁ" የሚለው? ታምሜ በእግዜር እጅ ተይዤ ለሳምንት ብተኛ ፣ የሞትኩ መስለውና ነው ይህን ያህል ድፍረት የደፈረኝ? እኮ ምን ቢመኝ ነው?' ይህን ሲያወጡና ሲያወርዱ የባሰውን ሕመማቸው እየጠናባቸው ሔደ ።

እያደር ደግሞ ፣ የልጅ አድባሩ ሠፈር የዕድር ሹሞች እነ አቶ አርጋው ፣ እነ እቶ እንደሻውና ወይዘሮ ፈትለወርቅ የወ ረዳውን ነዋሪ ሕዝብ ሁሉ እየሰበኩ በዕድራቸው ውስጥ አሰ ገቡት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ፊታውራሪ እርገጣቸው፣ በፋሽሽት ወረራ ጊዜ ኮረም ድረስ ሔደው፣ ማይጨው ሳይደርሱ ተመልሰው፣ ከዚያም በትውልድ ወረዳቸው ተደብቀው ቆይተው የተመለሱ ናቸው። በጦርነቱም ሆነ በአርበኝነቱ የፈጸሙት ጀብዱ ባለመኖሩ፣ እንደ ሌላው ባለውለተኛ አፋቸውን ሞልተው የሚናገሩ አልነበሩም።

እንዲያውም ተደብቀው ይኖሩበት በነበረው ቀበሌ የአርበኞችን እንቅስቃሴ እያሽሟጠጡ፣ ''ጊዜ ያመጣውን ጊዜ አስቲመልሰው መቻል፣ መታገሥ ነው። የመጣው ጠላት እኛ የምንችለው፣ እኛ የምናስወጣው አይደለም' እያሉ ከመናገራቸውም በላይ፣ 'የሮማ ብርሃን' በሚል አርዕስት ሲታተም የነበረውን የፋሽሽቶች መጽሔት ከአዲስ አበባ እያስወሰዱ ለአካባቢያቸው ሽማግሌዎች በንባብ ሲያሰሙ ነበር'' የሚል ገመና ስለ ነበረባቸው፣ ከአባታቸው ሙያና ታዋቂነት ሌላ በእርሳቸው በኩል የሚነሣ አንድም ምልክት አልነበራቸውም። ታዲያ ከድል በኋላም ቢሆን፣ እንኳን ቤተ መንግሥቱን አደባባዩንም ሸሽተው እንደ መደበቅ ብለው ነበር የሚኖሩት።

ልጅ አድባሩ እንኳ፣ ፊታቸውን ወደ ማይጨው ባያዞሩም፣ በአምስቱ ዓመታት 'በውስጥ አርበኝነት አገልግያለሁ' ብለው አስመስክረዋል።

የፊታውራሪ አባት፣ የልጅ አድባሩ አያት የነበሩት ራስ— በሞት ከተለዩ በኋላ፣ ርስታቸውንና ንብረታቸውን ወራሾቻቸው የተከፋፈሉት በብዙ ሙግት፣ ጥልና ሽምግልና ስለ ነበረ፣ በቤተዘመድ መካከል የነበረው የዝምድናና የቤተሰብ መቀራረብ የሻከረና የጐደፈ ነበር።

'እርሱ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅና ተሞጋሽ ሲሆን? በኔ ላይ ያለበው ተንኮል አለ' እያሉ በሐሳብና በብስጭት ሲዳክሩ የነበሩት ፊታውራሪ፣ የልጅ አድባሩን ዕድር ሊበታትኑ የሚችሉበትን ዘዴ ለማግኘት ማውጠንጠን ጀመሩ።

ፊታውራሪ የደረሳቸው የመሬት ስፋት ላቅ ያለ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ብዙ ጢሰኛ አላሠፈሩበትም። የልጅ አድባሩ ድርሻ

t.me/OLDBOOKSPDF

ግን መጠነኛ ሆኖ ፣ በርካታ ጢሰኛ ችምችም ያለ መንደር ቆር ቁርበታል ።

ቁጥሩ ብዙ አይሁን እንጂ ፣ በፌታውራሪ ርስት ላይ የሠፈረው ጢሰኛም ቢሆን ለፌታውራሪ ታማኝና ጥገትም ነበር ። እና ፣ 'የልብ ታማኞቹ' የሚሉዋቸውን አምስት ጢሰኞቻቸውን በቤታቸው በረንዳ ሰብስበው ፣ የልጅ እድባሩን ዕድር እንዲበታትኑላቸው ምክክር ጀመሩ ።

"የርሱን ተንኮል ደርሼበታለሁ ። ማደሪያ ያሳጣውና ፣ 'ዕድር ዕድር' የሚለው በኔም በናንተም ላይ አሳድሞ ፣ ይህን ዐይኑን የጣለ በትን መሬት ባዶ ነውና እንሥራበት ለማለኝት ነው ። ስለዚህ በዚሁ በዕድሩ ውስጥ ያስገባቸውን ሰዎች እሺ ቢሉ በውዴታ ፣ እምቢ ካሉ በማስፈራራት ከዕድሩ እንዲወጡ ካላደረጋችሁልኝ ራሴ የማደርገውን አደርጋለሁ" ብለው ዛቱ ጌታ ፌታውራሪ ።

ከጢሰኞቻቸውና ከታማኞቻቸው አንዱ ፣ "ጌታዬ አልሰሙ እንደሆነ እንጂ ፣ በልጅ እድባሩ ዕድር ጢሰኞቻቸው ብቻ ሳይ ሆኑ የኛም ሠፈር ነዋሪዎች ፣ የወዲያኛውም መንደር ነዋሪዎች ፣ እንዲያውም ከአባትዎ ርስት ባሻገር ያሉ ሠፈርተኞች ፣ አብዛ ኛዎቹ ገብተዋል ። የዕድርተኛው ቁጥር በጣም በዝቷል" አሉዋቸው ።

ፌታውራሪ ከምር ጠፉ ። ዐይናቸው መፍጠጥ ፣ እጆቻ ቸው መንቀጥቀጥ ጀመሩ ።

"ታዲያ ምኑን ቆሚያለሁ? እድግውን ተንኮሉን የጀመረው ከዚሁ ከእጥሬ ጥግ ከታዛዙ ነቀ ! ሞቻለኋ ! እንግዲህ ነምታ ደርጉት ነገር ካለ ንገሩኝ ፣ ያለዚያ የማደርገውን እኔ ዐውቃለሁ ። እኔ ከተነሣሁ ደግሞ ማንም በጤና ሊኖር አይቻለውም" አሉ ።

ፌታውራሪ ፣ እንኳን እንደዚያ ያለ ከቤታቸው ውጭ የሆነ ከበድ ያለ ጉዳይ ቀርቶ በቤታቸው ውስጥ እንኳ ከቤት ሠራተ ኞቻቸውም ሆነ ከባለቤታቸው ጋር ሲነጋገሩ ፣ 'ይህ ካልሆነ የማ ደርገውን እኔ ዐውቃለሁ' ማለት ልማዳቸው ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ግዴለም ጌታዬ! አያናድድም። የእርስዎን ጢሰኞች እን ደሆነ መከረን ተቆጥተን እንመልሳቸዋለን" አሉ አንዱ ባለሟል፣ የፊታውራሪን ንዴት ለማብረድ ብለው።

"ምከሩበት፤ ያለዚያ የማደርገውን እኔ ዐውቃለሁ" አሉና ከተቀመጡበት ተነሥተው በረንዳውን ወርደው፣ መንሮራደድ ጀመሩ። ባለሟሎቻቸውም ከበረንዳው ወርደው ከጥጉ ላይ ቁመው ይመለከታሉ።

"የተቆጣች ነብር ሆኑ አይደል?" አሉ አንደኛዉ ባለሟል።
"ለአንበሳነቱስ ምን ያንሳቸዋል?" አሉ ሁለተኛዉ ባለ ሟል።

አጠር፣ መጠን፣ ቀጠን ያሉት ጠይሙ ፊታውራሪ በሚና ደዱበት ሰዓት የታችኛው ከንፈራቸውን እየገለጡ፣ አንገታቸ ውን ወደፊት እየወረወሩ፣ እጆቻቸውን ማፍተልተል ይቀናቸ ዋል። እንደዚያ እያሉ ቆዩና፣ ፈቀቅ ብሎ ከአጥሩ ጥግ ከነበ ረው ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው እግሮቻቸውን ማጋጨት ጀመሩ። 'ጥራኝ ዱሩ?' ብለው ለማቅራራት የከጀላቸው መሰሉ።

"'ምቀኛ ሰው የሚጣላው ቢያጣ፣ እጁንና እግሩን ሳያጋጭ አይውልም' የሚባለው ለካ ያለነገር አይደለም። እስቲ አሁን ምን ቀረብኝ ብለው ነው እንደዚህ የሚጠፉት?" አሉና አንደ ኛዉ ባለሟል ለጓደኛቸው ሹክ አሉዋቸው።

"'ምክር ተቀባይ ሲያጣ፣ ተመልሶ ወደ ባለቤቱ ይመጣ' እንደሚባለው ሆኖ ነው እንጂ፣ ይህን ባዶ መሬታቸውን ለጢ ሰኛ ይስጡ ብለን መከርን። እምቢ አሉ፤ ምክራችንን ይዘን ከቤታችን ተቀመጥን። አሁን ደግሞ ምክር አምጡ አይደል የሚሉት? የዛሬው ምክራችንም ይኸው ነው። መሬቱን ለጢ ሰኛ ይምሩና እንደ እጎታቸው ልጅ እርሳቸውም ዕድር ያቋቁሙ፤ ሌላ ነገር የለም፤ የምንሰጠው ምክር ይኸው ነው" አሉ ሦስተ ኛዉ ባለሟል።

"አይሆንም። አሁን እንደዚህ ሆነው በተቆጡበት ሰዓት መሬት ለጢሰኛ ይምሩ ብንላቸው፣ ከኛው ጋር ነው ጥላቸው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለዚህ በመጀመሪያ በሠፈራችን የሚኖሩትን ጢሰኞቻቸውን ከገቡበት ዕድር ለማስወጣት እንሞክር ። ይህንኑ ነግረናቸው ብንሔድ ነው የሚሻል'' አሉ አራተኛዉ ባለሟል ።

ክምር እንዳፈረሰ ገመሬ ዝንጀሮ ፣ ለብቻቸው ተጐብረው የነበሩት ፊታውራሪ ፣ ከተቀመጡበት ተነሥተው እጆቻቸውን እያወናጨፉ ወደ ባለሟሎቻቸው ጠጋ አሉና ፣ ''ታዲያ ምን ይታሰባችኋል ?'' ብለው ጠየቁ ።

''ጌታዬ ! መቸም 'ማሽላና ነገር ካንገት ካንገቱ ነው' ይባላልና ፣ ይኸ ጉዳይ ሥር ሰዶ ጢሰኞችዎን ሁሉ ላይመርዝብዎ በቶሎ ብንከላከለው እይከፋም'' አሉ አንዱ ባለሟል ።

''ስማህ አቶ ፍጡር !'' አሉ ፊታውራሪ ፣ አመልካች ጣታቸውን ከጢሰኞቻቸው ሁሉ እጅግ በሚያምኑዋቸውና በሚያቀርቡዋቸው አማቻቸውም በሆኑት ፣ በአቶ ፍጡር ላይ ቀስረው ፣ ''ከሁሉም ከሁሉም ይህን ጥቃት ትመክትልኛለህ ብዬ የተማመንኩት ባንተ ነው ። ይህ መሠሪ የጀመረው ተንኮል ሁላችንንም ለመንቀል ነው ። ሠፈርተኛ ሰብኮ ፣ አታሎና አስገድዶ ባዶ መሬት ስለሆነ እንሥፈርበት ለማሰኘት ነው ። ስለዚህ ይህ ተንኮሉ ሥር መስደድ የለበትም ። እናንተ የምታደርጉት ከሌለ እኔ የማደርገውን ዐውቃለሁ'' አሉና ወደ በረንዳቸው ወጥተው ተጐበሩ ። ባለሟሎቻቸውም ወደ በረንዳው ወጡና አንዳንዶቹ ሲቀመጡ ፣ አንዳንዶቹ የበረንዳውን አጥር እንደ ተደገፉ ቆሙ ።

'''ካላበደ በቀር ዱባ ቅል አይጥልም' ይባላል ። እንዲያው እንደኛውን ሕሊናቸውን ካልሳቱ በቀር እንዴት እንዲህ ያለ ሥራ ልጅ አድባሩ ይሠራሉ ተብሎ ይታመናል !'' አሉ አቶ ፍጡር ፊታውራሪን ለማለዘብ እየተጣጣሩ ።

ፍጡር ገጸ ሾጣጣ ፣ ሰውነቱ ሙሉ ፣ ቁመቱ ደልዳላ ፣ የቀይ ዳማ ናቸው ። በአመለካከታቸው ተጠራጣሪ ፣ በአነጋገራቸው ቀልጣፋ ፣ እልህና ንቀት የሚያጠቃቸው ሲሆኑ ፣ በፊታውራሪ እርገጣቸው ቀርቶ በሠፈሩ ነዋሪ ንብረትም ላይ የሚያተኩሩ ናቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ስነግርህ ! ይኸው ነው ። ዕብደቱንም ተንኮሉንም ከእነዚያው ዕንቁላል ሊያቀርብላቸው ከነበሩት ፋሺሽት ጌቶቹ ተምሮታል ። ይልቁንስ ጥርጣሬውን ተዉትና የምታደርጉትን አድርጉ ። ያለዚያ የማደርገውን እኔ ዐውቃለሁ" አሉ ፊታውራሪ ፣ እጆቻቸውን እያፍተለተሉና እግሮቻቸውን እያማቱ ።

"እርስዎ አይናደዱ ! እኛ የሚሆነውን ሁሉ እናደርጋለን ፤ መቸስ እኛ እያለን የርስዎ ርስት አይደፈርም ። አባትዎ ያቆዩዎትን ርስት የልጅ ልጅ እንዴት ይደፍራል ?" አሉ ፍጡር ።

"ለመሆኑስ እነማንን ይዞ ነው ይህን ተንኮል የጀመረው?" አሉ ፊታውራሪ ፣ ጠላቶቻቸውን አንድ ባንድ ለመነጠል ፣ የሚያደርጉትን ሊያደርጉና ሊያነጣጥሩባቸው ብለው ።

"እንዴ ሰማነው እነመምሬ በዕውቀቱ ፣ እነ አቶ እርጋው እነወይዘሮ ፈትለወርቅ ፣ እነ..." ብለው ሳይጨርሱ ፣ ፊታውራሪ እንደገና ቱማ አሉና ፣

"አዩ ጉድ ፣ የኛ ቄስ ! ዳሩ እሱስ አብሮት የፋሽስቶች ዕንቁላል አቅራቢ አልነበረም ? እሱን ብሎ ቄስ ! እንዲህ አድርጉም ቅስና የለ ! ፈትለወርቅም ገብታበታለች ? እርሷማ መቸም የርሱዉ ቀኝ እጅ ናት ። ጢሰኛዉና ሴት አቅራቢዉ አይደለች ? እርሷን ሳይዝማ መሥራት ቀርቶ መናገርም አይችል ። አርጋውማ መቸስ ውሻው አይደል ? ምን ያድርማ ? ብቻ ያም ሆነ ይህ ፣ ዕድሩን ማፍረስ አለባችሁ ። አለዚያ የማደርገውን ዐውቃለሁ" አሉና ወደ ቤታቸው ገቡ .....

...አንድ ቀን ፣ የልጅ አድባሩ ሠፈር የዕድር ኃላፊዎች ነዋሪዎችን በማራሩዋ ሥር ሰብስበው በንግግር ላይ እንዳሉ ፣ የፊታውራሪ ጢሰኞች የነበሩ ጐረምሶች ከስብሰባው መካከል ገብተው ከአንዲት ሴት ጋር ውዝግብ ተነሣና ድብድብ ሆነ ። ተሰብሳቢዎቹም ተበታተኑ ። ከዚያ በኋላ የሠፈሩ ነዋሪዎች በሆነ ባልሆነው ምክንያት መደባደቡን የዕለት ተግባራቸው አደረጉት ። ከዚያች ዕለት ጀምሮ በሠፈሩ የጠላና ጠጅ ቤቶች ትርምስ ማለታጋባት ጀመረ ። በየምሽቱ እራትና እምስት ሰዎች መፈነ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከከት ጀመሩ ። እንዲያውም ከመጠጥ ቤቶችም ዐልፎ በየመን ገዶቹ አምባጓሮ ሆነ ። የድንጋይ እሩምታ መንገደኛዉን ቀርቶ መስኮቶችና በራፎችን መደብደብ ጀመረ ። በዚህም የተነሣ ሦስት ሰዎች ክፉኛ እየቆሰሉ ሆስፒታል ገቡ ። አምቧጓሮዉ ከሁለቱ ባለርስቶች ሠፈር ድንበርተኛ በሆኑት ሠፈሮች ሁሉ መዳረስ ጀመረ ። በተለይም የሦስት ባለሥልጣኖች መኪኖች በተባራሪ ደንጋይ ተመትተው መስታወታቸው እንከትክቱ ከወጣ ወዲህ ፣ በሁኔታው ላይ ፖሊሶችም ማተኮር ጀመሩ ።

ፊታውራሪ ኃይላቸውን ለማጠንከር ፣ የአሽናፊነቱን ዕዋ ለመጨበጥ ሲሉ ፣ ጢሰኞቻቸውን ሰብስበው ዕድር አቋቋሙ። የልጅ አድባሩ ጢሰኞች ቁጥር በርከት ያለ ስለ ነበረ ፣ የዕድርተኛውም ቁጥር የዚያኑ ያህል ሆነ ። የፊታውራሪ ባለሟሎችም ነገሩን ተመለከቱና የዕድርተኞቻቸውን ቁጥር ለማብዛት ሲሉ ባዶ በነበረው በፊታውራሪ ርስት ላይ ጢሰኞች እንዲሠፍሩበት አደረጉ ።

የሁለቱ ባለርስቶች ዕድሮች በሁለቱ ወገን ባለሟሎች ይመሩ ጀመር ። የልጅ አድባሩን ሠፈር ዕድር አቶ አርጋው ፣ የፊታውራሪ እርገጣቸውን ሠፈር ዕድር አቶ ፍጡር ማስተዳደር ጀመሩ። ለስሙ ያህል ዕድሮች ይቋቋሙ እንጂ ፣ ዋናው ዓላማቸው ግን የዕድርተኛው ጉዳይ አልነበረም ። የሁለቱ ባለርስቶች ገናና ክብር የሚጠበቅበትን ፣ አንዱ ከሌላዉ የሚበልጥበትን ፣ የአንዱን ሠፈር ዕድር አንዱ የሚያፈርስበትን ዘዴ ማሰላሰልና በተግባር ለማዋል መታገል ነበር ።

በዚያን ወቅት በሕመም ለሚሞቱ ይቅርና ፣ የሁለቱ ዕድር ተሟች ተፋላሚዎች ባስነሡት ግጭት ለሚወድቀው ሰው እንኳን ግድ ያለው የዕድር ኃላፊ አልነበረም ። አድባሩም ሆኑ እርገጣቸው ፣ ያሠለፉዋቸው ምርጥ ምርጥ የዕድር ኃላፊዎች እንዲያሸንፉላቸው ብቻ ገንዘብ ማጉረስ ፣ መሣሪያም ማዶል እንጂ ስለ ችግረኞች ፣ ስለ ሕመምተኛና ስለ መርዶኛ ቀርቶ ፣ ስለሚሞቱ ጢሰኞቻቸው እንኳን ደንታ አልነበራቸውም ። ሠፈርተኛዉ ቀርቶ ተላላፊ መንገደኛ እንኳ ፣ ጊዜው ለዐይን መያዝ ከጀመረ በዚያ ሠፈር ለመዘዋወር የማይደፍር ሆነ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠላ ቤቶችና ጠጅ ቤቶች ደንበኞቻቸውን መናፈቅ ጀመሩ። ዱላ፣ ጩቤ፣ የብረት ቦክስ፣ ሽጉጥ ከሠፈርተኛው እጅ የማይ ለዩ ሆኑ።

'ማነህ?'

'እንተስ ማነህ?'

'የማን ዕድርተኛ ነህ?'

'እንተስ የማነኛዉ ነህ?'

እነዚህ ቃላት የተለመዱ ነበሩ። ወንዱ ብቻ ሳይሆን ቤቱም በትርምሱ ውስጥ ገብቶ በየጉልቱ፣ በየውሃ መቅጃው፣ በየወ ፍጮ ቤቱ በየመንገዱ መሰዳደቡን፣ መዛዛቱን አዘወትረው።

ከሁሉም አስቸጋሪ የሆነው፣ በሠፈሩ ውስጥ በምትገኘው ወንዝ ዳርቻ ተዘርግታ በነበረችው የዕንጨት ድልድይ የመሸጋ ገሩ ጉዳይ ነበረ። ያችን ድልድይ በመጀመሪያ ያሠሩዋት ፈታ ውራሪ ነበሩ። ጥሎ ከተነሣ በኋላ፣ የልጅ አድባሩ ሠፈር ዕድር ተኞች እንዳይሸጋገሩባት የፈታውራሪ ሠፈር ዕድርተኞች ዘጉ ዋት። የልጅ አድባሩ ሠፈር ዕድርተኞችም ማዶ ለማዶ ሆነው ድንጋይ እየወረወሩ መማታት በማዘውተራቸው ነገሩ እየባሰ ሔደ። ሠፈሩ በዚህ ሁኔታ ወራት አሳለፈ።

አንድ ቀን፣ የልጅ አድባሩ ሠፈር ዕድርተኛ የሆኑ ሴት ልጃ ቸውን ሲድሩ ዲል አድርገው ደግሰው፣ ዕድርተኞቻቸውንና ልጅ አድባሩን ለምሳ አደሙዋቸው። ይህን ያወቁት ፈታውራሪ በድልድይዋ ሥርና ማዶ ታማኞቻቸውን አሠልፈው፣ ራሳቸውም ዕርድ ሠርተው፣ ከአባታቸው በውርስ የደረሳቸውንና በጦርነቱ ጊዜ ኮረም ድረስ ታጅበውበት ሔደው አምስት ዓመት ሙሉ ባገር ቤት ጉድጓድ ቀብረውት የነበረውን አሮጌ መትረየሳቸ ውን ጠምደው፣ 'ዛሬ በዚህች መንገድ ትደርስና የማደርገውን እኔ ዐውቃለሁ' ብለው ላኩባቸው።

'የማናውቀው ወንድነት ዛሬ ከየት መጣ?' አሉ ልጅ አድ ባሩም፣ መልእክቱ ሲደርሳቸው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሠርግ የደገሱት ሴት ደግሞ ፣ የልጅ አድባሩ የምር ወዳጅና የውስጥ አርበኝነታቸውን ከመለከሩላቸው ምስጢረኞቻቸው አን ዱዋ ስለ ነበሩ ፣ ወደ ሠርጉ ቤት የመሔዳቸው ነገር ቁርጥ ነበር።

'እስቲ የእርሱ እጅ ቃታ ሰቦ ጥይት ተኩሶ እኔን ሲገድል አያለሁ' ብለው አድባሩ ፣ ታማኞች ጢሰኞቻቸውን እሠለፉ። ሠፈሩ ከጭንቀት ላይ ወደቀ ። ገሚሱ ፊታውራሪን ፣ ገሚሱ ልጅ አድባሩን ይወቅሳል ፤ ይተቻል ። የሠርጉ ቤትም የጎዘን ጥላ ወደቀበት ።

ሠፈርተኛው እንደዚያ በሚዋልልበት ሰዓት ያ 'አያ እንዶ ልቡ' ፣ ደባልቃቸው ከሠርጉ ቤት ጠላና ጠጁን ሲለጋ ቆይቶ ወጣና ከድልድዩ ማዶ ሆኖ ፣

"'ዕድሜ ያልመከረው ሽማግሌ ፣ ከውሃ የገባ አሞሌ' የተባ ልከው እንተ አይደለህም ወይ ፣ እርገጣቸው ? ምነው ያኔ ያባትህ ጠላት መጥቶልህ ሳለ ይህን ሁሉ ወንድነት የት ደብቀኸው ነበር ? ዛሬ በውሽማህ ሠርግ ወንድነትህን ልታሳይ ነው ? በርሷ የተነሣ ከስንቱ ጋር ስትፋጅ ልትኖር ነው ? በርሷ ምክንያት ደጅ ስትጠናበት የኖርከውን ሹመት አጣህ ፤ ዛሬ ደግሞ ከእ ኅትህ ልጅ ጋር ልትታኮስ ነው ?!" እያለ አዋረዳቸው ።

"ሒድና ይዘህ አምጣው ፤ እምቢ ካለም ከነመረቁ ጋተው' ብለው ጋሻ ጃግሬያቸውን አዘዙ — ፊታውራሪ ።

ጋሻ ጃግሬያቸው ፣ እንግቴን እንደ ተሸከመ ከቆደበበት ተ ነሥቶ በድልድዩዋ ላይ ሊሻገር ሲያመራ ፣ "እስቲ ትነካውና! ተመ ለስ" የሚል ማስጠንቀቂያ ሰማና ፣ ከድልድይዋ ጫፍ ላይ ቆመ። ተናጋሪዉ የት እንደሆነ ፣ ማን እንደሆነ አልታወቀም ።

"እርገጣቸው ፣ ትጥቅህንና ድግንህን ለውሽሞችህ ልታሳይ ነው የተሰለፍከው ?" አለ ደባልቀው ።

"ሒድና ያዘው ነውኮ እምልህ" አሉ ፊታውራሪ ።

"ትነታነቅና እነጥፍሃለው" አለ ያልተከሠተው ሰውዬ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ፈርተህ ነው ? ወንድ አሰዳቢ !አትሔድም ?" አሉ ፊታውራሪ ።

"ያንተ አሽከር ሆኖ ቢፈራስ ?" አለ ደባልቀው ።

"ትነቃነቅና ትበላሻለህ" አለ ማስጠንቀቂያዉ ።

"አንት ሲታ ቤት" ብለው ፊታውራሪ ከቆይቡበት ብድግ ሲሉ ፣ ከኋላቸው የእርሳቸውን ጢሰኞች መስለው ተሰልፈው የነበሩት ሦስት ጠብደሎች ሩጠው ከእርዳቸው ገቡና መትረየሳቸውን አፈፍ አድርገው ፣ ሽጉጣቸውን ከወገባቸው አውልቀው፣ "ጌታዬ እንዳይነቃነቁ ፤ በከበሬታ ወደ ቤትዎ ይግቡ ። የመንግሥት ወታደሮች ነን" አሉና እየደጋገፉ ወደ ቤታቸው አስገቡዋቸው ።

ምንም እንኳን ፣ ከልጅ አድባሩ ጢሰኞች ምርጥ ባለሟላቸው ቢሆንም ፣ የዐሥር አለቃ ከበደ የፖሊስነት ግዳጁን ችላ የሚል አልነበረም ። ሁኔታውን ሲከታተል ቆይቶ በዚያች ዕለትም ፣ ልጅ አድባሩን ከቤታቸው እንዳይወጡ አድርጎ ፊታውራሪውን በጭፍሮቹ አስከብቦ ያዛቸው ።

ፊታውራሪ ወደ ቤታቸው ከገቡ በኋላ ፣ በወረዳው የታወቁ አዛውንቶችና ቀሳውስት ተሰብስበው ወደ ፊታውራሪ ቤት ሔደው ልመና ጀመሩ ። በተለይም በወረዳው ከታወቁት ሰዎች አቶ ሕዝቅኤል በትምህርትም በአነጋገርም ላቅ ያሉ ስለ ነበሩ ፣ ሁለቱን ተፎካካሪዎች ወደ ቤታቸው መስደው በዘመኑ እጅግ ብርቅና ድንቅ የነበረውን የእንግሊዞች መጠጥ እየጋበዙ ፣ እየወቀሱና እየመከሩ አስታረቁ ።

ከዚያ በኋላ ፣ በሠፈሩ ውስጥ በሁለት ባላባቶች ሥር ተመሥርተው የነበሩትና ፣ በከፍተኛ ትርምስ ላይ ወድቀው የከረሙት ሁለት ዕድሮች እንዲዋሃዱና ፣ ፊታውራሪ የበላይ ጠባቂ ፣ ልጅ አድባሩ አስተዳዳሪ እንዲሆኑ ከተስማሙ በኋላ ፣ ከልጅ አድባሩ ሰዎች አቶ አርጋው ጠቅላይ ጸሐፊ ፣ ከፊታውራሪ ሰዎች አቶ ፍጡር ገንዘብ ያዥ ሆነው እንዲሠሩ ፣ ዕድሩ በተውጣጡ ጥምር ኃላፊዎች እንዲተዳደር ተወሰነ ። ቀጥሎም ከሁለቱም

t.me/OLDBOOKSPDF

ወገን ሦስት ሦስት ዕድርተኞች ተመርጠው ፣ በዕድሩ ውስጥ በልዩ ልዩ ዘርፍ እንዲመደቡ ስምምነት ተደረገና ፣ ከፊታው ራሪ በኩል አቶ ቡልቻ ፣ አቶ ንጉሤ ፣ ወይዘሮ ይታክቱ ፣ ከልጅ አድባሩም በኩል ፣ መምሬ በዕውቀቱ ፣ የኧ/አለቃ ከበደ ፣ አቶ ይመር ተመረጡ ።

በሠፈሩ ሰላም ወርዶ ፣ ሠፈርተኛው እፎይ ብሎ በመረጋጋቱ ፣ የዕድሩ ተመራጮች ፣ በጠቅላይ ጸሐፊዉ ሰብሳቢነት በግራሩዋ ሥር የመጀመሪያውን ስብሰባ አደረጉ ።

ምንም እንኳን ዕርቅና ሰላም ሆነ ቢባልም ፣ ከሁለቱ ባለ ርስቶች የተወከሉት ባለሟሎች በየልባቸው ቀርጸውት የነበረው ጥላቻ ገና ከየልባቸው አልሻረ ኖሮ ፣ ከልባቸውም ለመነጋገር አልቻሉም ነበር ። በግራሩዋ ሥር እንደ ተሰበሰቡ አቀማመጣቸው በየወገን በየወገናቸው ሆነ ። መተያየት ፣ መገለማመጥና መንሾካሾክ ቀጠለ ።

ጠቅላይ ጸሐፊዉ ፣ ማታውኑ የልጅ አድባሩ ጠጅ አጐርን ናባቸው ያደረውን ድምፃቸውን ደጋግመው አሰሳለሱና ፣ ‘‘ለበጐ ነገር ተብሎ የታሰበው ጉዳይ ትርጉሙን ስቶ ለያጋድለን ተቃርቦ አሁን በመብረዱና እርስ በርሳችን እንድንረዳዳ ፣ በአንድነት ለመሰብሰብ በመብቃታችን ምስጋና ለፈጣሪያችንና ለአዛውንቶቻችን ልናቀርብ ይገባናል ። እንግዲህ ፍሬ ነገሩ በዕድር ተሳስረን ፣ ስንቸገር ልንረዳዳ ፣ ስንታመም ልንጠያየቅ ፣ በሞትም ጊዜ ልንቀባበር ነው ። መከራም ሆነ ደስታ ለብቻ አያምርም ። አባቶቻችን ‘ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት’ ብለው የመሰሉት ያለ ምክንያት አይደለም ። ሠፈራችን የሰላም ፣ የፍቅር የመረዳጃ ምሳሌ እንዲሆንልን ፣ ባለርስቶቹንም እንዳናስወቅስ እንድንትና ጎብረትን ማስፋፋት አለብን ። አሁንም እዚህ ያለነው ደንቡን አዘጋጅተን ፣ ሥራውን ተከፋፍለን ለልጅ አድባሩ እንድናቀርብ ስለ ጉዳዩ የታያችሁንና የታሰባችሁን እንድንነጋገርበት ያስፈልጋል’’ አሉ ።

ለጥቂት ጊዜ መተሻሸትና መጐሻሸም ከሆነ በኋላ ፣ የኧ አለቃ ከበደ ፣ ‘‘ለምንድነው ወይዘሮ ፈትለ ወርቅና አቶ እንደሻው በስብሰባችን ያልተገኙት ?’’ ብሎ ጠየቀ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

''እነርሱ መጡስ ቀሩስ ፣ ምን ፋይዳ አላቸው ?'' አሉ አቶ ፍጡር ።

''እንደዚህ የመሳሰለው ነገርኮ ነው ነገር ያበላሸው'' አለ የ፲ አለቃ ፡ ''በእውነቱ ፣ ባለፈው ጊዜ ነፍስ ጠፍቶ ቢሆን ኑሮ ጥፋተኞቹ እኛው ነበርን ። እንዳንዶቻችን ለባለርስቶቹ ታማኞች ና ባለሟሎች ለመሆን ስንል የሆነ ያልሆነውን ፣ የሚረባ የማ ይረባውን እየነገርናቸው ነው ፣ በመካከላቸው ንትርክና ትንቅ ንት የፈጠርንባቸው ። እኛ ጢሰኞች እንጂ ፣ የርስት ተካፋዮች አይደለንም ። በጢሰኝነታችን የወሰኑብንን ኪራይ መክፈል እንጂ ፣ በነርሱ የግል ጉዳይ ምን ያገባናል ?

''እስቲ ተመልከቱት ! እስቲ ፍረዱት ! በሌላው ሠፈር ዕድር ተቋቋሞ ሕዝቡ እየተረዳዳና እየተባበረ ሲኖር ፣ በኛ ሠፈር ፣ ይህ ሁሉ ትንቅንቅ መፈጠሩ አያሳዝንም ? አሁንም የሚያስፈልጉን ከሆነ ፣ ቅድም የተጠቀሱትንም ሆነ ሌሎች ሰዎች በመካከላችን እንዲገኙ ፣ ሥራውንም አብረን እንድናከና ውን ማድረግ ይገባል እንጂ ፣ መናናቅና ማጥላላት ተገቢ አይ መስለኝም ። ተሳስቻም ከሆነ እርመኝ ።''

ከአጭር ዝምታ በኋላ አቶ ይመር ፣ ''በመካከላችንኮ የመ ሬት ኪራይ እንዲቀነስላቸው ፣ ወይም ምሕረት እንዲደረግላቸው፣ ወይም ተጨማሪ መሬት እንዲሰጣቸውና ሌላ ቤት ሠርተው ለማከራዩት የሚጮሙ ምልተዋል ። እነርሱ ናቸው ሠፈሩን ጤና የነሡት'' አሉ ።

''አሁን ነገር መመላለሱ ይብቃና የመጣንበትን ጉዳይ እንጨርስ'' አሉ መምሬ በዕውቀቱ ፣ በሁለቱ ባለርስቶች መካ ከል ተነሥቶ የነበረው ጣጣ ፣ ዳግመኛ እንዳይነሣ በመሥጋት ።

''ቀደም ብለን የመጣነው በሚገባ እንተዋወቃለን ፣ የፅዋ ማኅበርም አቋቁመን በፍቅርና በሰላም ኑረናል ። አሁን የመጡት ናቸው የማናውቀውን ትርምስ የፈጠሩብን'' አሉ አቶ ፍጡር ፣ አቶ አርጋውን በሸወርኒ እየተመለከቱ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለው ጠባዩ ነው እንጂ የሚታየው ፣ በፊት መጣ በኋላ መጣ ምን ፋይዳ አለው ?" አሉ አቶ አርጋው ፣ ሁለቱን እጆቻቸውን እያናነፉ ። "በኋላ የመጣነውም ብንሆን በየነበርን በት ሠፈር የታወቅን ፣ በአንደበታችንም ሆነ በሥራችን ማንንም አላዝነን ይቅር ምንተ እግዚአብሔር ተባብለን የማናውቅ ነን ። ቀደም ብላችሁ የሠፈራችሁት ናችሁ ሥር የሰደዱ ነገር ያቆያ ችሁን" አሉ ።

"ነገረተኛውን ለይተው ይናገሩ" አሉ አቶ ፍጡር ፣ ኮስተር ብለው ።

"ሁላችሁም ያው ናችሁ ! ምን እገሌ ተገሌ ያሠኛል ? እባ ክዎ ይተዉኝ እያናግሩኝ" አሉ አቶ አርጋው ፣ ንቀትና ጥላቻ እየተናነቃቸው ።

"ሁለታችሁንም ልገዝት ነኝ" አሉ መምሬ ፣ የያዙትን መስ ቀል እንደ ዱላ በሁለቱ ተናጋሪዎች ላይ በየተራ ቀስረው ።

"እንግዲህ እንደዚህ ከሆነ እኔ የለሁበትም ። ለባለርስቶች ነግሬ ከስብሰባችሁም ሁለተኛ አልገኝ" አለና የፒ አለቃ ብድግ አለ ።

"ያሥራ ለቃ ፣ ልገዝትሥ ነኝ" አሉ መምሬ ። ሁሉም ከየተ ቀመጡበት እየተነሡ የዐሥር አለቃን ተማፀኑ ።

"ሁለታቸው ፣ ሁለተኛ አንጃ ግራንጃ ላይነጋገሩ ይፈጠሙ ልኝና ልቀመጥ ። ያለዚያ መሔዴ ነው" አለ የዐሥር አለቃ ።

"አስፈጥማቸዋለሁ ፣ ወርፈው ይቀመጡ" አሉ መምሬ ፣ በመስቀላቸው እያስፈራሩ —

"አውሮፕላ መ'ቶ ሰማይ ሰማይ ሳይ

የወገቤን ጥይት ለቀመው ተባይ"

እያለ እያጉረመረመ ደባልቀው መጣ ። ደባልቀው ያን አካባቢ ያዘወትረዋል ። በዚያ በኩል አድርጎ ወደ ብዙዎቹ ሠፈሮች

t.me/OLDBOOKSPDF

ይመላለሳል ። እንጀራና ቅራሪ የሚሰጡት አዛኞቹ የሚበዙት በዚያ ሠፈር ነውና ፣ ቢያንስ በቀን ሦስት ጊዜ ያህል ብቅ ጥልቅ ሳይልበት አይውልም ።

በዚያ ዘመን መንገዱ ሁሉ በሕፃናት ፣ በጐረምሶችና በኮረዳዎች አልተጣበበም ነበርና ፣ ደባልቃቸው ችግር አልነበረበትም። ከኋላ ኋላው እየተከተለ ፣ በአጥር ቀዳዳ ብቅ እያለ የሚቀልድበት ፣ የሚያናድደውና ወፈፌነቱን የሚገፋፋበት ማንም አልነበረም ። ሠፈርተኞቹም የሚበላው ፍርፋሪ ሰጥተውት ከመሸኘት በስተቀር ፣ ከእርሱ ጋር የሚጫወቱና የሚጣሉ አልነበሩም ። እርሱም ጥሉ ከባለርስቶቹና ከባለጸጋዎቹ ጋር እንጂ ፣ ከጠቅላላው ነዋሪ ጋር አልነበረም ። የባለርስቶቹና የባለጸጋዎቹ አጥር ዘወትር ዝግ ነው ። አስገብተው አጉርሰውት ወይም ዕላቂያቸውን ወርውረውለት አያውቁም ። ታዲያ ስለነርሱ በየመሸታው ቤት የሰማውን ይናገራል ።

እነ አቶ አርጋው ፣ ገና ከሩቁ ድምፁን ሲሰሙ የአውሬ ጩኸት እንደ ሰሙ የቤት እንስሳት እርስ በርሳቸው ተያዩ ። በየልባቸው ተጣጣቁ ። አቶ አርጋው ብቻ ቆጣ ብለው ፣ "ይህን ምናምንቴ ማን ባባረረልን ? እንዲያው ከዚህ ሠፈር እርሱን የሚያስወጣ ነገር ጠፋ ?" አሉና አጉረመረሙ ።

"እሱ ምን አጠፋ ? 'እንዲህ እንዲህ እያልህ እነእገሌን ተሳደብ' እያሉ የሚልኩት ናቸው እንጂ ተንኮለኞቹ" አሉ ወይዘሮ ይታከቱ ፣ ደባልቀው ስለ እርሳቸው የሚናገረው ቢኖር ፣ ተንኮለኞችና ምቀኞች የሚያስወሩባቸው መሆኑን አስቀድመው ለማስረዳት ብለው ።

"ግዴለም ፣ እርሱን እኔ አባርረዋለሁ" ብሎ የፒ አለቃዉ ወደ ደባልቃቸው ሲሔድ ፣

"ከብዬ ፣ የነፍሴ ጌታ ! አንተ ባትኖርኮ ያ ሴታ ሴት ነፍሴን አሰናብቷት ነበር ። ሰማሽ ይታከቱ ፣ ይህን የአዲስ አበባን ሴት ሁላ እያመጣሽ የምታቃጥሪውን ጌታሽን አትገላግይኝም" እያለ ደባልቀው ሲጠጋ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"በቃህ በቃህ ፣ ሥራ ይዘናል ተመለስ ። እንዳንጣላ ተመ ለስ" አለ የ፤ አለቃ ።

"የትልቁ ስትመጣ ፣ የትንሹ አቃጣሪስ ምነው ቀረች" አለ ደባልቀው ፣ ከ፤ አለቃ ፈቀቅ ብሎ እንደ ቆመ ።

"እንግዲህ ከኔ ጋር መጣላትህ ነው ። በቃህ ብያለሁ ኮ' !" አለ የ፤ አለቃ ፣ በሆዱ ግን እየሣቀ ።

"እስቲ ከብዬ ፣ ያንድ ጣሳ መግዣ ጣይልኝ ፣ ጠምቶኛል" አለ ደባልቀው ፣ እጁን በሩቁ ዘርግቶ ።

"ይስጠትና ይሒድልን ፣ እባክዎ" አሉ አቶ አርጋው ፣ ያን የጭቃ ጅራፍ የሆነባቸውን ስድቡን ፈርተው ።

"እንተና ጌታህማ እጃችሁንም ቢመቷችሁ አይወድቃች ሁም" አለ ደባልቀው ።

የ፤ አለቃ ከበደም የተጠየቀውን ሣንቲም ወረወረለትና ፣

"በል ጥፋ! ወደ ማታ ደግሞ ጠጅ እገዛልሃለሁ ። አሁን አታስቸግረን ፣ ዘወር በልልን" አለው ።

"ከብዬ ! ዋና ዋናዎቹን ባለሟሎችና አቃጣሪዎች የሰበ ሰብሺው ስለ ውለታሽ እነእርገጣቸው የገጠር መራት እንዲሰ ጡሽ ለመለመን ነው ?" አለ ደባልቀው ፣ የተወረወረለትን ሣንቲም እንሥቶ መንገዱን አሳብሮ እየገሠገሠ ።

"እንት ምናምንቴ ! ቆይ ከዚህ ሠፈር ባላጠፋህ !" አሉ አቶ አርጋው ፣ የግላቸውን ነገር ሳይናገርባቸው በመመለሱ እፎ ይታ እየተሰማቸው ።

"የሚስትህን አቃጣሪ ፈትለ ወርቅንና የሚስትህን ውሽማ እን ደሻውን አባረርካቸው እንዴ ? ጐብዘሃል !" እያለ ሮጠ ደባል ቀው ። የ፤ አለቃም በሣንቲም ጉርሻ ደልሎ ፣ በፖሊስነቱ አስ ፈራርቶ ደባልቀውን በማባረሩ የልብ ኩራት ተሰምቶት ወደ መቀመጫው ተመለሰና ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"ቅድም እንዳሳሰብኩት ፣ እነ ወይዘሮ ፈትለወርቅን ማስጠ
ራትስ አያስፈልግም ?" ብሎ ጥያቄውን አደሰው ።

"ምን ያጠያይቃል ! በሠፈራችን የኖሩ ፣ ሠፈርተኛውን የሚያውቁ ፣ በየቀኑው የሚያረገውን ሁሉ የሚከታተሉ ፣ ሁላችንም የምናውቃቸው ናቸው ። እነርሱው አይደሉም የፅዋ ማኅ በራችንንስ ሲረዱትና ሲያስፋፉት የኖሩ ! አሁንም መጠራት አለባቸው" አሉ መምሬ ።

"እነርሱ እንዲጠሩ ከተፈለገ ፣ ከኛም ወገን የምንጠራቸው ሰዎች አሉን" አሉ አቶ ፍጡር ።

"እናንተ እንማን ናችሁና ነው ወገን የለያችሁት ?" አለ የኟ አለቃ ተቆጥቶ ።

"ከኛ ከፊታውራሪ እርገጣቸው ወገን ነዋ !" አሉ አቶ ፍጡር ።

"ፊታውራሪስ የማን ወገን ናቸው ?" አለ የኟ አለቃ ደገመና ።

"የኛ ወገን ናቸዋ !" አሉ ፍጡር ።

"ፊታውራሪም ፣ ልጅ አድባሩም ፣ ሁላችንም አንድ ወገኖች ነን " አለ የኟ አለቃ ፣ አቶ ፍጡር ላይ አፍጥጠ ። "እንደ ጠላት ተከፋፍለን 'የኛ ወገን ፣ የዚያ ወገን' የምንባባል አይደለንም ። ሁላችንም ያንድ አገር ዜጐች ያንዲት አገር ልጆች ነን ። ከጥንት ጀምሮ በጠላት የተፈተን ፣ ለትናንትናውም ፋሽስት የአንድነትና የጀግንነት ከንዳችንን ያሳየን ፣ አንድ ወገን የሆን ጀግኖች ነን ። ስለዚህ በመንደር ፣ በሠፈር ፣ በቀዬና በባላባቶች ልዩነት ፣ በጠላትነት መለያየት የሌለብን መሆናችንን በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል ። በሠፈራችን ውስጥም ለምናቋቁመው ዕድር ሊረዱንና ሊያገለግሉን የሚችሉት ሰዎች ካሉ ፣ የእገሌ ጠሰኛ ፣ የእገሌ ባለሚል ናቸው ሳንል ወደ ስብሰባችን እንዲመጡና አብረን እንድንሠራ ያስፈልጋል ። "

ሌሎቹ ተሰብሳቢዎች ፣ አቶ ፍጡርንና የኟ አለቃን ተራ በተራ መመልከት ጀመሩ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የ፤ አለቃ ንግግሩን ቀጠለና ፣ "በሉ እንግዲህ ፣ በሠፈራችን ውስጥ ለምናቋቁመው ዕድር ያስፈልጋሉ ፣ ሕዝቡን ያስተባብራሉ ፣ ሕዝቡም ያምናቸዋል የምትሉዋቸውን ሰዎች ስም ተናገሩና እንጥራቸው" አለ ።

የ፤ አለቃ ከበደ ፣ በሠፈሩ የታወቀ ቀልጣፋ ሰው ነው ። ልጅ አድባሩም ያቀርቡታል ። በርስታቸው ላይ በጢስኝነት ካሠፈሩዋቸው ቀደምቶች አንዱ ነው ። ከተወለደበት ከደብረ ብርሃን ተማ አዲስ አበባ የገባው ለጌታ ለማደር ነበር ።ግን ሐሳቡን ከውጦ በፖሊስነት ተቀጠረ ።

በኃይለማርያም ማሞ የጀግንነት ሥራ እጅግ ይኮራበታል ። የቤተ ክህነት ትምህርት ቀመስ ስለ ነበረ ፣ የፖሊስነቱን ሥራ ከተማረ በኋላ የተደለደለው በጽሕፈት ሥራ ነበረና በአስተሳሰቡና በኑሮው ከሠፈሩ ለወጥ ያለ ሆነ ።

በዚያች ዕለት በተደረገው ስብሰባ ለዕድሩ ሥራ ይበጃሉ፣ ያግዛሉ የተባሉ ነዋሪዎች እየተመረጡ ተጻፉ ። ቀጥሎም አቶ አርጋው ፣ አቶ ፍጡርና የ፤ አለቃ ከበደ የዕድሩን መተዳደሪያ ደንብ እንዲያወጡና በሚቀጥለው ሳምንት ስብሰባ ተደርጎ ፣ አስፈላጊዎቹ ሰዎች ሁሉ እንዲገኙ እንዲነገራቸው ስምምነት ተደርጎ ስብሰባው አበቃ ።

* * *

በመጀመሪያ ቦተመረጡት ስምንት የዕድር ኃላፊዎች ላይ አራት ሠፈርተኞች ተጨምረው ፣ በሳምንቱ ስብሰባው ተጀመረ ። ክርክር የተደረገባቸው አቶ እንደሻውና ወይዘሮ ፈትለ ወርቅም ተገኝተዋል ። ከፊታውራሪ ጢሰኞች አቶ ገብረ ሚካኤልና አቶ ሺበሺ የተባሉ በሠፈሩ የታወቁ ነዋሪዎች ተጨምረዋል ።

የስብሰባው ዕለት እሑድ በተለመደው ሰዓት ነበር ። የሰዓቱም ፀሐይ እንደ ተለመደው ኃይለኛ ሙቀት መርጨት ጀምራለች ። ያች ግራር ግን ተሰብሳቢዎቿን ከፀሐይዋ ግለት ትከልላለች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ባለፈው ሳምንት ተደርጎ በነበረው ስብሰባ የተመረጡት እነ አቶ አርጋው፣ ፍጡርና የኔ አለቃ ከበደ ከግራኙዋ ሥር ፈቀቅ ብለው ስላረቀቁት ደንብ ሲወያዩ ቆይተው፣ወደ ተሰብሳቢዎቹ ለመቀላቀል ሲነሡ፣ ተቀምጠውባቸው የነበሩትንም ወንበሮች እያንጠለጠሉ ወሰዱና ከተሰብሳቢዎቹ ፊት ለፊት እያስቀመጡ ጠቅላይ ጸሐፊው በመካከል፣ የኔ አለቃ በቀኝ፣ ፍጡር በግራ ሆነው ተቀመጡ።

"እንግዲህ መሰንበቻውን ያረቀቅነውን ደንብ እናሰማችኋለን" አሉና አቶ አርጋው ንግግር ጀመሩ።

"አስቲ አንድ ጊዜ ልናገር። እኔ ባልነበርኩበት ስብሰባ የተነጋገራችሁትን ነገር አሁን እንዴት ሰማ እባላለሁ? በመጀመሪያ ፍሬ ነገሩ ሊነገረን አይገባም?" አሉ አቶ እንደሻው።

"እናንተ ስትመረጡ አታስፈልጉም ተብለን ከቀረን በኋላ፣ ዛሬ ያስፈለግንበት ምክንያት ለምን አይነገረንም?" አሉ ወይዘሮ ፈትለ ወርቅም።

"እኛንስ የመረጠን ማነው? እንደ ሰማነው ከሆነ፣ ሁላችሁንም የመረጡዋችሁ ባርለስቶቹ ናቸው ይባላል። እኛን ግን ዛሬ እንድንገኝ የነገሩን አቶ አርጋው ናቸው። ነገሩ ቅር አሰኝቶናል። እኛ ከባለርስቶቹ ፊት የቀረብን እንደሆነ፣ ምናችን የሚያሳፍር ሆኖ ነው?" አሉ፣ እነአቶ ባልቻም።

በጥያቄዎቹ ሁሉም ተያዩባቸው፣ ለመልሶቹ ዋቢ የሚሆን አልነበረም። የኔ አለቃ ከበደ ግን ከንፈሩን እየሸለጠ፣ እጆቹን እያነጋገረ፣ የጥያቄዎቹን መልሶች ማምሰልሰል ጀመረ። ከሁለቱም አቅጣጫዎች የተወረወሩት ጥያቄዎች በእርሱ ዘንድ ክብደት ያልነበራቸው፣ መልሶቻቸውም የማያስቸግሩ እንደሆኑ እድርጎ ይተነትናቸዋል።

ተሰብሳቢዎቹ፣ መልሶቹን ከጠቅላይ ጸሐፊው ይጠባበቁ ጀመር። ጠቅላይ ጸሐፊው ደግሞ ክብዱቸዋል። ቢችግራቸው ወደ የኔ አለቃ ጠጋ አሉና፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን ልበላቸው! ችግርኮ ሆነብኝ" ብለው ሹክ አሉት፣

"ምንድነው የሚቸግርዎት?"

"እስቲ ለብቻ እንነጋገርበት" አሉና የኔ አለቃን ይዘው ብድግ አሉ። ወደ ተሰብሳቢዎቹ መለስ ብለው ይግሞ፣

"እስቲ ቆዩን፣ ለብቻ የምንወያይበት ነገር ስላለን ነው" አሉዋቸው።

"እየህ ጌታዬ፣ ወንድሜ!" አሉ አቶ አርጋው፣ ለኔ አለቃ ምስጢራቸውን ሲያካፍሉት።

"ማንኛውም ሰው ሚስቱን ከአገቡበት፣ አባቱን ከሰይቡበት፣ ርስቱን ከወሰዱበት፣ ዐመሉን ካወቁበት እንዲጣላ የታወቀ ነው። ልጅ አድባሩና አቶ እንደሻው ቀደም ብለው ይተዋወቃሉ። ታዲያ በዚህ የተነሣ፣ አቶ እንደሻው ሲናገሩ ደፈር ደፈር ይላሉ። የልጅ አድባሩን ሐሳብ ብዙ ጊዜ ይጋፉታል። ባለፈው በመጀመሪያው ስብሰባ እንኳ፣ እኔ ነኝ አቶ እንደሻውን እንዲጠሩና በመካከላችን እንዲገኙ ያደረግሁ እንጂ ልጅ አድባሩስ አልፈለጉዋቸውም ነበር። በምርጫው ጊዜ እንዳይመረጡ የከለከሉም እርሳቸው ናቸው። ከወይዘሮ ፈትለ ወርቅም ጋር እንደዚሁ ነው፤ ይተዋወቃሉ። መናናቅም አለ። እሳቸውንም በመጀመሪያው ስብሰባ እንዲገኙ ያደረግሁ እኔ ነኝ። ከምርጫው የቀሩትም በልጅ አድባሩ ትእዛዝ ነው እንጂ፣ በመምሬ በዕውቀቱና በአቶ ይመር ፈንታ፣ ሁለቱ እንዲመረጡ አሳስቢያቸው ነበር። አይሆንም ብለው ከለከሉኝ። ዛሬም በዚህ ስብሰባችን እንዲገኙ እኛ መስማማታችንን አልነገርኳቸውም። የእነዚያኞቹ ጉዳይ እንኳ ይህን ያህል አስቸጋሪ አይደለም። አቶ ፍጡር የሚመልሰው ይሆናል። ታዲያ ምን ትመክረኛለህ!" አሉ።

"ቀላል ነው፣ አይጨነቁበት" አለ የኔ አለቃ፣ "የሚፈቅዱ ከሆነ መልስ ልሰጥበት።"

"ምን ከፍቶኝ! ብቻ ይህችን አሁን ያጫወትኩህን ምስጢር በልብህ ያዝልኝ እንጂ ምን ችግሮኝ፣ ደስ ይለኛል።"

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለቱም ወደ ቦታቸው ተመልሰው ገና ሳይቀመጡ ፣

"እኛ ከእናንተኮ አይደለም መልሱን የምንፈልገው ። ከባ ለርስቶቹ ጋር መነጋገር ነው የምንፈልገው ። እናንተማ እንደ ኛው ናችሁ" አሉ አቶ እንደሻው ፣ በንቀት አመለካከት እያዩ ዋቸው ።

"እኛ እንደ እናንተ ምንድኖች ነን ?" አለና የፒ እለቃ ጠየቃቸው ።

"ጢሰኞች!"

"ታዲያኮ ጢሰኞችም ብንሆን ፣ ለሠፈራችንና ለየራሳችን የሚበጀውን ተመካክረን ለመሥራት የሚከለክለን የለም ። በጉዳ ዩም ባለርስቶቹ ተስማምተውበታል ። በመላው አዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው ነዋሪ ሁሉ ዕድር አቋቁሟል ። ባለርስት የሚ ያገባው ነገር አይደለም—"ብሎ ተናግሮ ሳያበቃ ፣

"የሚያገባቸውና የሚመለከታቸውማ ሆኖ ነው ሰብስበውን የነበረው" አሉ ፣ አቶ እንደሻው ።

"የፅዋ ማኅበራችንን ያቋቋምነው በባለርስቶች ፈቃድና ትእ ዛዝ ነው ?" አሉ አቶ አርጋውም ምርር ብለው ፣ "እኛ ራሳችን በየቤተ ክርስቲያንና በየመሸታው ቤት በየራሳችን ቤት እየተገና ኘን ፣ እየተመካከርን አይደለም የመሠረትነው ? በዚያ በክፉው ቀን እንደዚያ ስንተባበር እንዳልነበር ሁሉ ፣ ዛሬ ይኸ ሁሉ በነ ገር መወጋጋት ምን ያደርጋል ? እግዜር የማይወደው ሥራ ምን ያደርጋል ?" አሉ ።

"እርግጥ ነው ! በፊት ስንረዳዳና ስንጠያየቅ ፣ እንተ ትብስ ፣ አንች ትብሽ ስንባባል ነበር" አሉ አቶ እንደሻው ፣ "ታዲያ ምን ያደርጋል ? አሁን አበላሻችሁታ! በመካከላችን የነበረውን ፍቅርና ሰላም ፣ የድሃ ገበሬ አውድማ በማታከል መሬት ለወጣችሁታ ! የጢሰኞች ባለሚሎች ፍቅራችንን መረ ዛችሁታ ! ባለፉት ወራት የመላው አዲስ አበባ ሕዝብ መዘበቻ የሆንነው እኛ አይደለንም ? ስንቱ ሰው ነው የተደባደበው

t.me/OLDBOOKSPDF

ስንቱ ነው ቂስለኛ የሆነው? ይህን ሁሉ የጠነሰሰው ማን ሆኖ ነው፣ አሁን በደለኛ ፍለጋ የመረረ ነገር የሚያሰሙት?''

''እንግዲህ ይኸው ነው'' አለ፣ የፓ አለቃ ከበደ፣ አጠቃላይ ሐሳቡን ሲያሰማ፣ ''በዚህ ነገር የሆነ ያልሆነ ምክንያት እየፈጠርን ለዕድሩ መሰናክሎች መሆን የለብንም። እነ አቶ እንደሻው ባለፈው ስብሰባ ሳትገኙ የቀራችሁት በኔ ስሕተት ነው'' ብሎ ውሸቱን ገና ተንፍሶ ሳያበቃ፣ አቶ እንደሻው አቋረጡትና፣

''ባንተ ስሕተት አይደለም፣ ስሕተተኛውን ዐውቄዋለሁ። በዚህ ሠፈር ቦታ እንዳልመራ፣ ቤት እንዳልሠራ፣ ከልጅ አድባሩም ጋር እንድጣላ ሌት ተቀን የሚደክሙ ሰዎች አሉ። እኔ ግን—'' ብለው እርሳቸውም ተናግረው ሳያበቁ፣ወይዘሮ ፈትለ ወርቅ ጣልቃ ገቡና፣

''የኔም ጉዳይ እንደዚሁ ነው እንጂ፣ 'ጌቶቹማ ሴቶቹን ትረጅልኛለሽ፣ ዕድርተኛ ታስገቢያለሽ፣ እንኳን በሠፈራችን በአካባቢያችን፣ እንዲያውም ከወንዝ ወዲያ ባለው ሠፈር ሁሉ ያሉትን ነዋሪዎች ታስገቢልኛለሽ' ብለውኝ ነበር። ግን በዚህ ነገር የተመቀኙኝ ሰዎች ስላሉ፣ እነርሱው ናቸው በስብሰባው እንዳልገኝ ውስጥ ውስጡን ተንኮል የሚሠሩብኝ'' አሉ፣ ወደ አቶ አርጋው ዐይኖቻቸውንና እጆቻቸውን እየወረወሩ።

''ያም ሆነ ይህ፣ ዛሬ ተጠርታችሁ መጥታችኋልና ያለፈውን ነገር እርሱት። ይህ ዕድር በየአንዳንዱ ምክንያት—'' ብሎ የፓ አለቃ ተናግሮ ሳያበቃ፣ ከሠፈሩ ሰዎች አንዱ እየሮጠ ሔደና በጥድፊያ፣

''አቶ ዘርጋው ሙቷልና ድረሱልን ይላሉ'' ብሎ አረዳቸው።

''የቱ ናቸው ዘርጋው?'' አለ የፓ አለቃ፣ ግር ብሎት።

''አዬ ጉድ! አዬ ጉድ ወዳጄን! ዘርጋው ሞተ?'' አሉ አቶ አርጋው።

''ምን ሆነው ነው?'' አለ የፓ አለቃ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኒያ ባለፈው ጊዜ በነፈታውራሪ ምክንያት ተደባድበው በጩቤ ተወግተው ከነበሩት ከሦስቱ አንደኛዉ ነውኮ!" አሉ አርጋው ።

"እንዴ! ወደ ሆስፒታል ተወስደው አልነበረም እንዴ!?" አለ ፤ አለቃ ።

"ሆስፒታል የገባ ሁሉ አይሞትም ያለህ ማነው? " አሉ አቶ አርጋው ፣ በሽሙጥ አስተያየት ጭምር ።

"የቀሩትም መትረፋቸውን እንጂ ፣ በጠና ነው የተጐዱት!" አሉ አቶ እንደሻው ፣ አቶ አርጋውን እየተመለከቱ ።

"ያሳዝናል ። እስቲ ድሀዉ ምን በበደለ ይሙት?" አለ የ፤ አለቃ ። "በባለርስቶች ፉክክር ድሆቹ መጋደላቸው ምን ይባ ላል? በዚህ ነገር እንግዲህ ተጠቂየው ማን ነው?"

"ጠያቂውስ ማን ነው?" አሉ አቶ እንደሻው ፣ በአሽሙር አስተያየት አቶ አርጋውን እየተመለከቱ ።

"ያም ሆነ ይህ ፣ አሁን ወደ ተጠራንበት መሔድ አለብን" አሉና አቶ አርጋው ብድግ አሉ ፣ ወዲያውም ከተነሣው ውዝ ግብ ለመራቅ ብለው ።

"እንዴ! ምን ሆኑብኝ? ዋናዉ ጉዳይኮ አሁኑኑ እልባት ማግኘት አለበት" አለ የ፤ አለቃ ፣ ቆጣ ብሎ ።

"ሰዎቹ ለሙግት እንጂ ፣ ለሥራ የመጡ አይመስሉምና ይህነኑ ለባለርስቶቹ ነግረን የሚሆነውን ያድርጉ እንጂ ፣ እኛማ ምን ልናደርግ ይቻለናል ብለው ነው?" አሉ አቶ አርጋው ።

"በፍጹም አይሆንም ። ይህ ጉዳይ ዛሬውኑ አንድ እልባት መያዝ አለበት ። የሆነ ያልሆነውን ለባርስቶች እያቀረብን ፣ ነገርን ነገር እያዋለድን ማጉተት የለብንም ። አሁንም እናንተም ያነሣችሁት ጥያቄ መልካም ነው ፣ ወደፊት እንነጋገርበታለን ። ለዛሬ ግን ከኛ ጋር ተባብራችሁ እንድትሠሩ የፈለግናችሁ እኛ ስለሆን እሺ በሉን ። በሠፈር ውስጥ ለሚጠቅም ለሕዝብ ጠቀሜታ ለሚሆን ሥራ ፣ ምክንያት እየፈጠሩ ፈቃደኛ ያለ መሆን ደግሞ ፣ በመንግ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሥትም በኩል ቢሆን ሊያሳዝንና ቅር ሊያሰኝ ይችላል። እኛም እምቢተኞችን በዝምታ ማየት አይቻለንም'' አለ የፓ አለቃ በማስፈራራት ጭምር።

''ላንተ ለወንድማችንና ለሠፈሩ ነዋሪ ስንል ቅሬታችንን ችላ ብለን አብረን እንሠራለን፤ ግዴለም። የየግላችን ቅሬታ እያደር ይሻራል'' አሉ አቶ እንደሻው፣ ሌሎችንም መሰሎቻቸውን እየተመለከቱና በርሳቸው አነጋገር እንዲስማሙላቸው በሐሳባቸው እየተማፀኑ።

እንግዲህ፣ ''ነገሩ እልባት አግኝቷልና ወደ ልቅሶው እን ሒድ'' አሉ አቶ አርጋው።

''ይቆዩኝ አይቸኩሉ፤ ሟቹም ለቅሶውም ሞልቷል። የነበረ ነው፤ ይኖራል። ይልቁንስ አሁን እንግዲህ እነርሱም ልመናች ንን ከተቀበሉት፣ አሁን ሥራ ሥራችንን ዕንወቅና ለሚቀጥለው ስብሰባችን ለሠራተኛው አሳውቀን፣ ለዕድሩ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እንድናሟላ'' አለ ከበደ።

አቶ አርጋውም ቃሉን ሊጥሱ አልደፈሩምና፣ በሐሳቡ ተስማምተው እንደ ገና ተቀመጡ።

ከዚህ በኋላ የሥራ ክፍፍሉ ተደረገ። ከጠቅላይ ጸሐፊውና ከገንዘብ ያገቡ ቀጥሎ አቶ እንደሻው የሠፈር ሹም፣ አቶ ቡልቻ የዕቃ ቤት፣ የፓ አለቃ ከበደ ተቆጣጣሪ እንዲሆኑ ተስማሙ። ቀጥሎም ቡታ ነጋሪ ወይም ቱልቱላ ነፊ፣ መቃብር አስቆፋሪ፣ ድንኳን ተካይ የሚሆኑ ሰዎች እንዲመረጡ ከተወሰነ በኋላ፣ ዕድርተኛ የሆኑ ሁሉ በወር ኻያ አምስት ሣንቲም መዋጮና ቱል ቱላ ሲነፋ ሲነፋ ደግሞ፣ ሀሥር ሣንቲም እንዲከፈል ከሰ ምምነት ላይ ደረሱ። ከተቀሩት ተሰብሳቢዎች ደግሞ፣

1ኛ. የተጣሉ የሚያስታርቁ፣ 2ኛ. ዕድር ያልገቡትን የሚ ያስገቡ ኃላፊዎች እንዲመደቡ ተደርጎ፣ መምሬ በዕውቀቱ፣ ወይ ዘሮ ፈትለወርቅ፣ አቶ ይመር፣ ወይዘሮ ይታክቱ፣ አቶ ንጉሤ ተመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ረጡ ። የተቀሩት አባሎች ግን ፣ ዕድሩ እየሠፋና እያደገ ሲሔድ እንደ አስፈላጊነቱ የሚደላደሉ በመሆናቸው በአባልነትና በተ ጠባቂነት እንዲቆዩ ተወሰነ ።

"በጣም ተገዛዛ ። የዚህ ሁሉ ሰው ጋጋታ ምን ያስፈልግ ነበር?" አሉ አቶ አርጋው ፣ ከስብሰባው ተነሥተው ወደ ለቅ ሶው ሲሔዱ — የ፤ አለቃ ከበደን ሲተቹት ።

"ግዴለምትም ይሁን ። በሌላው ሠፈር ዕድርም የሚሠራው በዚህ ዐይነት ነው" አለ ።

"መቼም እንደሻው ንትርኩ ፣ ትችቱ አያድርስ ነው" አሉ አቶ አርጋው ፣ የሰውን ብዛት የጠሉበት ዋናው ምክን ያት በአቶ እንደሻው የተነሣ መሆኑን የ፤ አለቃው እንዳያ ውቅባቸው እየሠጉ ።

አቶ ዘርጋው ፣ ቀደም ካሉት ጢሰኞች ሠፋሪዎች አንዱ ነው ። ጢሰኝነቱም የልጅ አድባሩ ነበር ። ሁለቱ ባለርስቶች ጢሰኞቻቸውን እየሰበሰቡ በየፊናቸው 'የአድባሩ ሠፈር ዕድር' 'የእርገጣቸው ሠፈር ዕድር' እያሉ ባቋቋሙበት ሰሞን ፣ ዘርጋው ውና ጓደኞቹም በመጠጥ ቤቶች ውስጥ ተነሥቶ በነበረው አም ባጓሮ ተደባድበውና በጩቤ ተወግተው ፣ ቆስለው ፣ በሆስፒታል ዕርዳታ ከተደረገላቸው በኋላ ፣ በየቤታቸው ከተኙት አንዱ ነበረ ። ሁለት ልጆቹን ፣ አሮጊት እናቱንና ሚስቱን ያለዋቢ ጥሎ ፣ ለልጅ አድባሩ ፍቅርና ክብር ሲል ሞተ! ከእርሱ ጋር የቆሰሉትም በቂ ሕክምናና ምግብ ባለማግኘታቸው እየደከሙ ሔደዋል ።

ዕድሩ ገና በመቋቋም ላይ በመሆኑና ተቀማጭ ገንዘብ ስላ ልነበረው ፣ ከጽዋ ማኅበሩ ሒሳብ ላይ ኻያ ብር ተነሥቶ ፈቃደ ኞች ከሆኑ ላይም ዐሥር ዐሥር ሣንቲም ተዋጥቶ ለቀብሩ ማስፈ ጻሚያ ተሰጠለት ። አቶ አርጋውም በልጅ አድባሩ ስም ሁለት ብር ፣ በራሳቸው ስም ሃምሳ ሳንቲም ከፍለዋል ።

በዚህ የትርምስ ወቅት የተጐዱትም የዘርጋው ቢጤዎች ነበሩ ። ለፈታውራሪ እርገጣቸውና ለልጅ አድባሩ ስም ፣ ዝናና ክብር ሲሉ በፍልሚያው ወደቁላቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አዲሱ የዕድር ደንብ ለአድባሩ ቀርቦ ከተስማሙበት በኋላ ፣ በተረቀቀው ደንብ ላይ ፊታውራሪ የሚከተሉትን ነጥቦች ጨመሩበት ፡

1ኛ. ማንኛውም ዕድርተኛ የወር ሙዋጮ ቢከፍልም ፣ እከል ሲደርስበት ገንዘብ የሚወስደው የዓመቱን የመሬት ኪራይ ለባለርስቱ መክፈሉን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ሲያቀርብ ፡

2ኛ. ባለርስቶቹ በሚያከራዩት ቤት የሚኖር ከሆነ ፣ የቤት ኪራዩን በየወሩ ለመክፈሉ የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ሲያቀርብ ፡

3ኛ. ከባለርስቶቹ ገንዘብ ተበድሮ ከሆነ የከፈለ መሆኑ ሲረጋገጥ ፡

4ኛ. ከባለርስቶቹ ጋር በፍትሐ ብሔርም ሆነ በመንጀል ጉዳይ ክርክር ያላነሣ መሆኑን ማስረጃ ሲያቀርብ ብቻ ፣ የዕድሩ ገንዘብ ይከፈለዋል ።

በእነዚህ ተጨማሪ ደንቦች ልጅ አድባሩ ቅር ስለተሰኙባቸው ፣ ከአጐታቸው ጋር ለመመካከር ሲሉ ወደ ቤታቸው ሔዱ ።

''ነገሩ ትንሽ ከበድ ብሎኛል ። መቸስ አዲስ አበባ ውስጥ ተቀምጠን እንዲህ ያለ ደንብ ስናወጣ ፣ በመንግሥት በኩል የተሰማብን እንደሆነ ያስነቅፈን ይሆናል ብዬ ነው'' ሲሉ ሐሳባቸውን ሰነዘሩ ።

ፊታውራሪ ፣ የዕድሩን መቋቋም እንደዚያ ዕለት አድርገው ወደውት አያውቁም ። ያም ምክንያት ሆኖ ፣ ያም የበላይነትን ሰጥቷቸው እንደዚያ ሲያንጓጥጧቸው የኖሩት የእጎታቸው ልጅ እንኳ ፣ የበታችነታቸውን አምነው ምክር ሊጠይቁ እስከ ቤታቸው በመሔዳቸው ፊታውራሪን የልብ-ልብ ሰጣቸው ።

''እየሀ የኔ አድባር?'' አሉ ፊታውራሪ ፡

''እየሀ ልጄ ! በዚህ ርስታችን ላይ የፈለግነውን ብንተክል ፣ ብንነቅል ማናባቱ ነው ጠያቂ ? እኛስ በዋናው በንጉሡ ከተማ ላይ ወርቅ ሊያሳቅፍ የሚችል መሬት መርተን ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ስንቱ ባላባትና ባለርስት ነው ጠፍ በሆነ የዝንጀሮ መዋያ መሬት ላይ ያሠፈረውን ገባር ጢሰኛ ነፍስህን ጭምር ስጠኝ ብሎ የሚጠይቀው መሰለህ? በዚሁ በከተማችንስ ቢሆን? ኧረ ከዚህ ከአቅራቢያችን የሚገኙት ባለርስቶች ጢሰኞቸውን ሁሉ ስንትና ስንት ይጠይቁትና ያስገብሩት መሰለህ? ለመሆኑስ የቱ አንቀጽ ነው ነውር ሆኖ የታየህ?'' ብለው አንገታቸውን እያወዛወዙ ጠየቋቸው ።

ልጅ አድባሩም ፣ ፊታውራሪ የጨመሩትን ደንብ እንደገና ሊመለከቱት ቆዩና ፣

''የኛ ገንዘብ ፣ እንደ ዋና ግዴታ ሆኖ በዕድርተኛው ደንብ ላይ መሥፈሩ በጠቅላላው ከበድ ብሎብኛል'' አሉና ፣ አጐታቸውን ትክ ብለው ተመለከቱዋቸው ።

''አይከበድህ ፣ ሠፈሩ ርስታችን ፣ በላዩ ላይ የሠፈረው ጢሰኛችን ፣ ዕድሩ መጠሪያችን ነው ። ታዲያ በምንገብርበት ርስታችን ላይ ያሠፈርነው ጢሰኛ የመሬት ግብርና የቤት ኪራይ አልከፍል እያለ ሲያስቸግር ከርሱ ጋር ልሟገት ነው? ስንትና ስንት ገንዘብ ከጢሰኛው ላይ አለኝ መሰለህ? እንዲሁ ከሥረህ ቅር ነው የምትለኝ?''

''የፍትሐ ብሔሩና የወንጀል ክሱ ጉዳይስ እዚህ ውስጥ ለምን ገባ? እኛ በሁለቱስ ጉዳይ ምን ያገናኘናል?'' አሉ አድባሩ ።

''ምን ሆንክብኝ ልጄ! ያገባናል እንጂ ። የመሬትም ሆነ የቤት ኪራይ አንከፍልም የሚሉትን በምን ታስከፍላቸዋለህ? ዙሮ ዙሮ መክሰስህ ይቀራል? አንድ አንድ ባለጌ በዚህ ምክንያት ክብርህን የሚነካ ፣ አጥንትህን የሚሰብር ፣ ዝናህን የሚያረክስ ቃል ቢናገርህ ፣ ልጆችህን ፣ ቤተሰቦችህን ቢደፍርብህ ፣ ክብቴን ለቆ አትክልትህን ቢያስጠፋብህ በምን ትከሰዋለህ? በጅህ አትካስ ነገር ። እኮ ንገረኝ ፣ ምን ታደርገዋለህ? መካሰስህ ይቀራል? ግዴለህም ፣ ቅር አትሰኝበት ፣ ከእንደኛው በየርስታቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

ዕድር ካቋቋሙ ጋር ተመካክሬ ያስገባሁት ሐሳብ ነው ፤ አትክ
ፋበት'' አሉ ፊታውራሪ ፣ እግሮቻቸውን አነባብረው እያስጨፈሩ።

ፍሬ ነገሩ እንደማይከፋ ፣ ልጅ አድባሩም ተረዱት ። የአጐ
ታቸውን ትንተና እንገታቸውን ወደፊትና ወደ ኋላ እየወረወሩ
ከተቀበሉ በኋላ ፣ ተስማሙበትና ለዕድሩ ኃላፊዎች ተሰጠ ።

በተለመደው ዕለት ፣ ሰዓትና ቦታ የተለመደው የዕድር ተመ
ራጮች ስብሰባ ሲደረግ ፣ አቶ አርጋውም አዲስ የተጨመሩትን
ደንቦች ወስደው በንባብ አሰሙ ። ተሰብሳቢዎቹ ፣ ተስፋ በቆ
ረጠ ስሜት ሲቀበሉ ፣ የ፤ አለቃ ከበደና አቶ እንደሻው ብቻ
ቅሬታቸውን አሳዩ ።

''እኔ በበኩሌ ይህ ነገር የተመከረበትና የታሰበበት አይመ
ስለኝም'' አለ የ፤ አለቃ ።

''በእርግጥ ባለርስቶቹ ዐውቀውና ፈቅደውት የተጨመረ
ደንብ መሆኑንም ማወቅ ይገባ ይመስለኛል'' አሉ አቶ እንደ
ሻውም ፣ አቶ አርጋውንና አቶ ፍጡርን የጐራጥ እያዩ ።

''ከፈለጋችሁት ፣ እኔን ካላመናችሁኝ ፣ ባለርስቶቹን ሔዳ
ችሁ ልትጠይቁዋቸው ትችላላችሁ'' አሉ አቶ አርጋው ፣ 'ከደሙ
ንጹሕ ነኝ' እንደ ማለት ያህል ።

''የሆነ ሆኖ ፣ ለዕድራችን መቋቋም ይህ እንቅፋት ሊሆን
አይችልም'' አለ የ፤ አለቃ ፣ ''ባንድ በኩልም የባለርስቶቹ ገን
ዘብ መሰብሰብ ይኖርበታል ። ጢስኞችም ደግሞ የዘወትር ባለ
ዕዳ ሆነው ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ ዕዳ ከሚሸከሙ ያለባቸውን
ክፍያ በወቅቱ እንዲከፍሉ ይረዳቸዋል ።''

''ይሁን እንግዲህ ፣ መቸስ ምን ይደረጋል ? እነርሱም ቢሆኑ
ተቸግረው ነው ። እወደድ ባይ ፣ እበላ ባይ ያቀበላቸውን ላለመ
መለስ ሲሉ ነው'' አሉ አቶ እንደሻውም ፣ አቶ አርጋውንና አቶ
ፍጡርን ተራ በተራ እየተመለከቱ ።

የሁለቱ ንግግር በተሰብሳቢዎቹ ተቀባይነት አገኘ ። ሁሉም
የተስማሙ መሆናቸውን በእጅ ውርወራና ፣ በአንገት ንቅነቃ
አመለከቱዋቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ዕድራችን እንደ ሌሎች ዕድሮች ሁሉ የሚያስፈልጉትን ዕቃዎች እንዲያዘጋጅ ለማድረግ እንዲቻልና ገንዘብ እንድናዋጣ፣ ወይም ደግሞ ሌሎች ዕድሮች እንደሚያደርጉት ከነፈታውራሪ መበደር እንችል እንደሆነ እንድንመካከር ለሳምንት ብንገናኝስ?" ብሎ የፒ አለቃ ከበደ ፣ ሐሳብ ሰነዘረ ።

"በእውነቱ ፣ ዕድሩ የሚያስፈልገውን ሁሉ ፣ ከፈታውራሪ ለማግኘት እንችላለን ። በሌሎች ሠፈሮች ያሉ ባለርስቶች የሚያደርጉትን ሁሉ ፈታውራሪም አይነፍጉንም" አሉ አቶ ፍጡር ።

"የእርገጤ መትረየስ ባለወርቅ ድሪ

የእርገጤ መትረየስ ባለግምጃ ሱሪ

ለጠላት ዐይን ዐፈር ፣ ሠፈር አሸባሪ"

እያለ ጮክ ብሎ እየዘፈነ ፣ ደባልቃቸው ወደ ተሰብሳቢዎቹ ሔደ።

ከበደና አቶ አርጋው ዐይን-ለዐይን ተያዩና እንደመሣቅም ቃጣቸው ። አቶ ፍጡር አንገታቸውን ደፉ ። ሌሎችም ተጠቃቀሱ ፣ ተጐሻሸሙ ።

"ትውልዱ የጠራ በጠባዩ ኩሩ

የጣሊያን ባለሟል የኛ ልጅ አድባሩ"

አለ ደባልቀው ፣ ቆም ብሎ ።

"ይኸ ምናምንቴ ደግሞ ዛሬስ ብሶበታል" አሉ አቶ አርጋው ፣ ተረኛው ተሰዳቢ መሆናቸውን በማመን ።

"ምን ያድርግ ? ጥፋቱ'ኮ የርሱ አይደለም ። እንዲያ እያልክ ዝፈን እያሉ በቅራሪና በአምቡላ እየሸነገሉት ነው" አሉ ፈትለ ወርቅም ሲከላከሉ ።

"ዛሬስ አለቅህም ፤ ዐሰሬ ነው ከበርሜል ውሃ የምጨምርህ ። አትሔድም ከዚህ ?" አለ ከበደ ፣ ወደ ደባልቀው ለመሔድ እየቃጣው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እሺ ከብዮ ! ዐፈር ልብላልሽ ። የሠፈሩ አንበሳ እንች እይደለሺ ? እሽ አሔድልሻለሁ" አለ ደባልቀው ፣ ሁሪቱን ለመቀ ጠል እያዘገመ ።

"ሁለተኛ ወደዚህ ብቅ ትልና አለቅህም" አለ ከበደ ድንጋይ እንሥቶ ሊወረውርበት እየፈለገ ።

"ከብዮ ! ምነው ዱሮ አዛኝ ነበርሽ ። ከዋና ዋናዎቹ ባለሟ ሎችና አቃጣሪዎች ጋር ስትውይ ጊዜ ጥጋብ ተሰማሽ ?" አለና ሮጠ ደ ባልቀው ።

"ይኸ ምናምንቴ ! ቆይ ግዴለም ፣ ከዚህ ሠፈር ባላጠፋው" እሱና አቶ አርጋው ዛቱ ።

በ፲ አለቃ ከበደ ጥረት ፣ ተሰብሳቢዎቹ ከስምምነት ላይ ደረሱና የዕድሩ መቋቋም ጸደቀ ። ስሙም 'የራስ አብተው ሠፈር ዕድር' ተባለ ። ከዚህ በኋላ አስፈላጊዎቹ ዕቃዎች ፣ ማለት እን ድንኳን ፣ እነወንበር ፣ እነሰሐን ፣ እነብርጭቆ ፣ እንጥሩንባ ፣ እነ አግዳሚ ፣ እነመዝገብ እንዲገዙ ተወሰነና ሠፈረተኛው የዐቅ ሙን ያህል እንዲረዳ ተመራጮቹ ተስማሙ ። ይህንኑ ሐሳብ ባለርስቶቹም ስለ ደገፉትና አርአያ እንዲሆኑ የተቻላቸውን ያህል እንዲለግሡ ፊታውራሪ እርገጣቸውን በመጀመሪያ እንዲጠይቁ አቶ አርጋው ፣ የ፲ አለቃ ከበደ ፣ ወይዘሮ ይታክቱ ፣ አቶ ፍጡር ተመርጠው ወደ ቤታቸው ሔዱ ።

ፊታውራሪ ፣ እንደ ተለመደው በቤታቸው በረንዳ ሆነው ተቀ በሉዋቸውና ሲያነጋግሩዋቸው ፣ የሚገዙትን ዕቃዎች ዝርዝርና የሚያስፈልገውንም ገንዘብ ብዛት አቶ አርጋው አስረዱ ።

"ጌታህስ ምን ያህል ከፍሏል ?" አሉ ፊታውራሪ ።

"ገና በጌታዬ ልንጀምር ነው" አሉ አርጋው ።

ፊታውራሪ ፣ ከንፈራቸውን ዠላለጡና አቶ ፍጡርን ጠቀስ አድርገው ፣ "እኮ ምን ያህል ልስጥ" ብለው በጆሮአቸው ሹክ አሉዋቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ጌታዬ መቸም የታየዎትን ፣ የተቻለዎትን ያህል ነው እንጂ" አሉ ፍጡርም በሹክታ ።

"መቸም ቤታችንን ታውቀዋለህ ። አንድ አምስት ብር ያህል ብሰጣቸውስ ?" አሉ ፊታውራሪ ።

"ባይሆን ባይሆን ለሌሎችም ምሳሌ እንዲሆን አንድ ሃምሳ ብር እከፍላለሁ ይበሉና ፣ ሁሉም ከፍሎ ሲጨርስ ቀስ ብለው ይሰጧቸዋል" አሉ አቶ ፍጡር ፣ የፊታውራሪን ስስት ሌሎቹ እንዳያውቁባቸው ሠግተው ።

"ማለፊያ ነው" አሉ ፊታውራሪ ፣ "መቸም የዐቅማችንን ነገር ሁላችሁም ታውቃላችሁ ። ከአባቶቻችን የቆየንን ሁሉ ፋሽስትና ባንዳ ተጫውቶበታል ፤ ዘርፎታል ። ባዶ መሬት ፣ ቆዳ መሬት ነው የተረፈልን ። የሆነ ሆኖ ፣ የተጠየቀውን ርዳታ በአቶ ፍጡር በኩል እልካለሁ" ተወካዮቹም ከአንገታቸው ሳንበስ እያሉ ተመለሱና ቀጥለው ወደ ልጅ አድባሩ ቤት ሔዱ ።

"ግዴለም ፣ ይህስ አይቸግርም ። እንኳን ከስምምነት ላይ ደረሳችሁ እንጂ የገንዘቡ ነገር አሳሳቢ አይደለም" አሉ ልጅ አድባሩ ፣ "ከሕዝቡ ሰብስቡና የጐደለውን ንገሩኝ" ሲሉዋቸው ተወካዮቹ ለፊታውራሪ የነፈጉትን ለጥ እያሉ እጅ ነሡ ።

ከዚህ አከታትለው ፣ የዕድሩ ተመራጮች ወደ ልዩ ልዩ ሰዎች እየሔዱ ፣ የገንዘብ እርዳታ እየጠየቁ ለዕድሩ ያስፈልጋሉ የተባሉትን ዕቃዎች እየገዙ ማሟላት ጀመሩ ። ዕቃዎቹ መሟላት ሲጀምሩ የዕድርተኛው ብዛት ፣ የመዋጮውም ሒሳብ ከፍ እያለ መጣ ። ከዚህ በኋላ ጎዘን ለሚደርስበት ዕድርተኛ ፣

1ኛ. ዕድርተኛ ሲሞት(ስትሞት)

2ኛ. ከዕድርተኛዉ ቤት ሬሳ የወጣ እንደሆነ

3ኛ. ዕድርተኛዉ የተረዳ እንደሆነ

4ኛ. የቅርብ ዘመድ ሙቶባቸው አገር ቤት ሔደው ቀብረው ሲመለሱ ፣ ገንዘብ እንዲከፈል በደንቡ ተወሰነ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እነዚህ የዕድርተኛዉ መብቶች ሲሆኑ ፣ ግዴታዎቹ ደግሞ ፣ ጥሩንባ ከተነፋበት ሰዓት ጀምሮ ማንኛውም ዕድርተኛ ጎዘን በደረሰበት ቤት ተገኝቶ ዕቃ ማጓጓዝ ፣ ድንኳን መትከል መቀመጫ መደርደር ፣ ራሳ መሸከም ፣ መቃብር መቆፈር ፣ የተወ ሰነውን ዐሥር ዐሥር ሳንቲምና የወሩን ሒሳብ ማሟላት ፣ ለጎዘ ንተኞቹ እንጀራ ፣ ወጥና ጠላ መስጠት ናቸው ። እነዚህን ግዴ ታዎች የማያሟላውን ዕድርተኛ ፣ ዳኛው እንደ መሰለው እንዲቀጣ ሥልጣን ይሰጣል ። ከዚሁ ይንብም ጋር ፣ 'ማንኛውም የሠፈሩ ነዋሪ ዕድርተኛ መሆን አለበት ። ያለዚያ በሚደርስበት አከል ሁሉ ዕድሩና የሠፈሩ ነዋሪዎችም ምንም በያነት ዕርዳታ ሊያደ ርጉለት አይችሉም' የሚል ቁርጥ ያለ ማስጠንቀቂያም አብሮ ተወሰነ ።

ከዚህ በኋላ ዕድሩና ሠፈሩ ፣ ለጥቂት ዓመታት በመጠነኛ ቅራኔና ፉክክር ሲተዳደሩ ቆይተው ፣ ወደ ሁለተኛዉ ምዕራፍ ተሸጋገሩ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መዘዘኛዋ ሴትዮ

ዕድሩ ፡ በተመረጡት ኃላፊዎችና እነርሱ ባወጡት ደንብ በመተዳደር ላይ እንዳለ ፡ በተመረጡት ኃላፊዎች መካከል የተፈጠሩት ያለ መግባባቶች ከሁለተኛ ዙር ትርምስ ውስጥ ከተቱት ።

ከተመረጡት አባላት ወይዘሮ ይታክቱ ሁለት ዐይነት ጠላ ፡ ማለት ጉሽና ፊልተር እየጠመቁ በመሸጥ የሚኖሩ ናቸው ። በተለይም ፊልተር ጠላቸው በባለርስቶቹ ዘንድ ተወዳጅነት ስላ ስገኘላቸው ፡ እርሳቸውንም ከባለርስቶቹ ጋር አስተዋወቃቸው ።

ፊልተር ጠላ ፡ በዚያን ዘመን እጅግ ተወዳጅና ስሙ የገነነ ነበር ። ምንም እንኳን ፊልተር ጠላ ከአዜ ምኒልክ ጊዜ ጀምሮ አዲስ አበባ ቢጠመቅም ፡ ወደ መሸታነት ደረጃ ቀልጥፎ አልወረደም ነበር ። ጣሊያን ከመጣ በኋላ ግን ፡ የባለሙያ ሴቶች መተዳደሪያ ሆነ ። ቢሆንም ለተራዉ ጠጭ ዋጋዉ ቀላል አልነበረም ።

የወይዘሮ ይታክቱን ፊልተር ጠላ ከለመዱት ሠፈርተኞች ፡ አቶ አርጋው ፡ አቶ እንደሻው ፡ አቶ ፍጡር ፡ አቶ ንጉሤ ዋናዎቹ ነበሩ ። ታዲያ እንደ አለመታደል ሆኖባቸው ፡ ወይም የሥራቸው ጠባይ ሆኖ ፡ ወይዘሮ ይታክቱ ከእነዚህኞቹ ደንበኞቻቸው ዐልፈው ተርፈው በነፃታውራሪም ይታማሉ ። በተለይ ከአቶ አርጋውና ከአቶ ፍጡር ጋር የነበራቸው ግንኙነትም ከወዳጅነት ዐልፎ ፡ 'ሊጋቡ ነው' እስተባለ ይታመበት ነበር ።

ዕድሩ ፡ ሙሉ ለሙሉ ሥራዉን ጀምሮ ለኃዘንተኞች ገነ ዘብ መክፈል ከጀመረ በኋላ ፡ በአቶ አርጋውና በአቶ ፍጡር መካከል የነበረው ያለመጣጣም እየተካረረ ሔደ ። ሁለቱ ሰዎች ለሁለቱ ባለርስቶች ወኪሎች በመሆናቸው ፡ በባለርስቶቹ መካ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከል ተነሥቶ በነበረው ትንቅንቅ እነርሱም አብረው ተወዛግበ ዋል ። ከዚያ ሌላ ደግሞ ፣ በወይዘሮ ይታነቱ ምክንያት ፉክክር ያዙ ። በዕድሩ ውስጥ ፣ ነበራቸው ሥልጣን ያጣም በዕድርተኛዉ ላይ ያልታሰበ ጣጣ ወለደ ።

ዕድርተኛዉ ፣ ኃዘ/ ደርሶበት በደንቡ የተወሰነለትን ገንዘብ ሲጠይቅ ፣ በአቶ አርጋውና በአቶ ፍጡር መካከል የተጀመረው ንትርክ አብሮ ያንከራትተው ጀመር ። 'ጢሰኝነትህ የማነው ?' የሚለውን ጥያቄ ሁለቱም የዕድር ባለሥልጣኖች ፣ማያዘ ወትሩት ሆነ ።

'የፊታሙራሪ ነኝ' ለሚለው አቶ ፍጡር ገንዘቡን ለመስጠት ፈቃደኛ ሲሆኑ ፣ አቶ አርጋው ደግሞ 'ይከፈል' ብለው ለማዘገዝና ለመፈረም የሚከብዳቸው ሆኑ ።

'የልጅ አድባሩ ነኝ' የሚለውም ችግር ተመሳሳይ ሆነ ። 'የሁለቱም ነኝ' የሚሉም ጥቂቶች ነበሩ ። ከሁለቱም ባለርስ ቶች ቦታ ተመርተው ሥጆ ቀላልሰው ፣ ባንደኛው ራሳቸው እየ ኖሩ ፣ እንደኛውን የሚያከራዩ ናቸው ። እንደነርሱ ላሉት ደግሞ ፣ ይሰነዘርባቸው የነበረው ጥያቄ ፣ 'መኖሪያህስ?' የሚል ነበር ። ተደማሚነት የሚያስገኘውና ገንዘብ የሚያስከፍለውም ይኸው ነበር ። በዚያ ዘመን በዚያ ሠፈር ፣ ዕድርተኛ ሲሞት በቅ ድሚያ የሚነገረው ለቦታ ነጋሪው ነበርና ፣ ገና በማለዳ ቱልቱላ ሲነፋ የማንኛው ጢሰኛ እንደ ሞተ ሁለቱም ባለሥልጣኖች ይጠ ይቁና ከሠፈር ይሰወራሉ ። ኃዘንተኛውም የቀብር ሥነ ሥርዓ ቱን ከፈጸመ በኋላ ፣ የዕድሩ ደንብ የደነገገለትን ገንዘብ ለማግ ኘት ደጅ ጥናት ይጀምራል ።

''ይህ ነገር እንዲህ ሆኖ እንዴት ይዘለቃል !?'' አሉ አንድ የልጅ አደባሩ ጢሰኛ የነበሩ ዕድርተኛ ፣ ብሶታቸውን ለፒ አለቃ ሲያካፍሉት ፣ ''በዕድራችን ገንዘብ እነርሱ ሠልጥነውበት ፣ እነ ርሱ ተለምነውበት ፣ እነርሱ ጉቦ እየበሉበት እስከ መቼ ይገፋል?'' ዕድርተኛው ከትራሳቸው የነበረውን ሽጉጣቸውን የዐሥር ዓመት ልጃቸው እንሥቶ ሲጫወትበት ፣ ከውስጡ የነበረች እንዲት ጥይት ባርቃ ገድላባቸው ፣ በመረረ ኃዘን ተውጠው የነበሩ ናቸው።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን ይደረግ ይላሉ? ሠፈሩ የተረገመ ነው፤ ይለፍልህ ያላለው ሠፈር ነው። ለቆ ከመሔድ ሌላ ምንም ማድረግ አልተቻለም" አለ የኀ አለቃም ተስፋ በቆረጠ መንፈስ።

"ሰማህ የኀ አለቃ" አሉ እኒያ ጎዘንተኛ፣ ወሬውን እንዳገና ሲቀሰቅሱት። "ሰማኸኝ ወንድሜ፣ አንተ ካሰብክበትና ችግራችንን ከተረዳኸው፣ እንኳንስ እነዚህን ተልካሾች ይቅርና ፊታውራሪ እርገጣቸውን ያህል ሰው እንኳ በጥበብህ ያዘሃቸዋል። አገሩ ሠፈሩ ተያንቀጠቀጠልህ። አሁንም እነዚህን ማጋጣምች ሥርዓት አስይዘልን፣ ሠፈሩ አይበላሽ።"

የኀ አለቃ ነገሩን በልቡ ያዙ እኒያን ጎዘንተኛ፣ "...ግዴለም ትም፣ ገንዘብም እንዲያገኙ አደርጋለሁ። ለወደፊቱም አሪድ ዕልባት ይደረግበታል" ብሎ አጽናናቸው።

የሁለቱ ባለርስቶች እንደራሴዎች ፉከከር እየባሰበት የሔደው በወያዘር ይታከቱ ንዳና ፊልተር ጠላ ብቻ አልነበረም። የዕድርተኞቹ ጢሰኝነትና ተቀማጭነት ብቻም አልነበረም። ደንቡ ራሱ እነርሱ ለሚያነጣጥሩበት ጠላት አመች ሆኖላቸውም ነበር።

አቶ አርጋው፣ የፊታውራሪን ጢሰኛ፣ 'ድንኳን ተክላው ላይ አላየሁህም' ብለው ሲቆጡ፣ አቶ ፍጡር ደግሞ፣ የልጅ ኦድባሩን ጢሰኛ፣ 'ሬሳ አልተሸከምክም' ብለው ይቀጣሉ። 'የመቃብር ጉድጓድ አልቆፈርክም' ሲሉ አርጋው፣ 'ከቀብር መልስ ከጎዘኑ ቤት አልደረሳችሁም' ሲሉ ፍጡር፣ 'ድንኳኑ ሲነቀልና ዕቃው ሲመለስ አልተገኘህም' ይላሉ-አርጋው። 'ዐፈር ሳትመልስ ነው የተመለስክው' የሚለውም ዕድርተኛን ለመቅጣትና ጎዘን ሲደርስበት ድርሻውን ለመከልከል ምክንያት ነበር። ዕድርተኛ ሲሞት የሚከፈለውን ዐሥር ሣንቲም ዐውሎ ባሳደረም ላይ ቅጣቱን የሚወስኑት እንደ ጢሰኛው ማንነት ሆነ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለቱ የሠፈሩ፣ የባለርስቶቹና የዕድሩ 'አፈ ንጉሦች' የወይዘሮ ይታነቱን ጓዳና ፈለ.ተር በማዘውተራቸው ፣ ሌሎቹ ደንበኞች መሸሽ ጀመሩ ። ባንድ ወገን የባለርስቶች እንደራሴዎች በመሆናቸው መሬት ይመራሉ ፣ ግብርና የቤት ከራያም ይሰበሰባሉ ። በሌላ ወገን ደግሞ ፣ የዕድሩ ተሿሚዎች ሆነው ገደብና ይግባኝ የሌለው ውሳኔ በዕድርተኛው ላይ ያሳልፋሉ ። ታዲያ ሁለት ሁለት ሥልጣን ከያዙ ሰዎች ጋር በጠላ ቤት ጓዳ መሳጠጡን የጠሉት የይታነቱ ደንበኞች እየራቁ ፣ ሁለቱ ብቻ በጓዳ መሳጠጥ ጀመሩ ።

ይታነቱ ፣ በሁለቱ ሰዎች መሳጠጥ እየሠጉበት ሔዱ ። በእርሳቸው ፍቅርና በእርሳቸው ፈለ.ተር የሁለቱም ደም ፈልቶ ፣ የሁለቱም እጅ ሽጉጥ ልጦ ሁለቱም ሲዋደቁ ይታያቸው ጀመር ። ይህ ሥዕል በአእምሮአቸው በተቀረፀ ቁጥር ደግሞ የተፈጠሩበትን ዕለት ፣ አዲስ አበባም ገብተው እዚያ ሠፈር ጉጅ የሠሩበትን ዕለት ፣ ፈለ.ተር ጠላ መጥመቅ የጀመሩበትን ዕለት ፣ ሁለቱም በጓዳቸው መግባት የጀመሩበትን ዕለት ፣ ለሁለቱም ፈሊ.ተር ጠላ የሰጡበትን ዕለት ፣ ከሁለቱም ጋር የተጫወቱበትን ዕለት ከአንጀታቸውም ባይሆን በአሳቸው ያማርሩታል ።

ቦታውን ለነተው በጤሰኝነት ጉጅ እንዲቀልሱ የረዱዋቸው የፊታውራሪ እርገጣቸው ወኪሎች ናቸው ። በዚያ የተነሣም ከፊታውራሪ ጋር የምስጢር ሙውውት አላቸው እየተባሉ ይታማሉ ።

ወይዘሮ ይታነቱ ፣ በፊታውራሪ ርስት ላይ ጤሰኝነት ሲመሩ አቶ ፍጡር አልነበሩም ፣ በሌላ ሠፈር ነበሩ ። ይታነቱ ጉጅ ከተለሱ በኋላ ነበር ፣ ፍጡር ወደዚያ ሠፈር የገቡትና የፊታውራሪ ወኪል ለመሆን የቻሉት ። ፍጡር የፊታውራሪ ሚስት ወንድም ስለሆኑ ፣ በፊታውራሪ ርስት ጤሰኛ ሆነው የሠፈሩት በነጻ ከመሆኑም በላይ ፣ በቤተሰብነታቸው ምክንያትም የእንደራሴነት ሥልጣን ጨብጠዋል ። የፊታውራሪም ሚስት ፍጡርን ለዚያ ሠፈርና ለዚያ ሥልጣን ያደረሱበት ምክንያት ፣ ፊታው

t.me/OLDBOOKSPDF

ራሪንና የወር ገቢያቸውን እንዲቆጣጠሩላቸው ነበር ። በእርግጥም ዘዴው ሠርቷል ። ፍጡር እዚያ ከሠፈሩ በኋላ ፣ የፈታው ራሪና የይታክቱ ምስጢራዊ ጭውውት ተገትቷል ።

አቶ ፍጡር ፣ ከአቶ አርጋው ጋር መፋጠጡን ለመግታት ሲሉ ፣ "ከእንግዲህ ወዲያ ፣ ኃላፊ በሆንሁበት በጌታዬ ርስት ላይ ጊዜ ያለጊዜ የሚመጣ ሰው ወዮለት ! ውርድ ከራሴ ! ይብላሻል" ብለው ለይታክቱ ማስጠንቀቂያ ሰጡ ።

"ታዲያ እኛ ኑሮአችን በንግድ ነው ፣ እንዴት እንተዳደራለን ?" አሉ ይታክቱ ፣ በማስተዛዘን ።

"ብቻ ውርድ ከራሴ!" አሉ ፍጡር ።

"ይህ ቃል በኔ ብቻ ነው በሁሉም ላይ ነው ?" አሉ ይታክቱ ።

"እኔ በምጠራጠርበት አካባቢ ሁሉ የሚጸና ነው" አሉ ፍጡር ።

"እኔ ምን እንዳላደርግ እጠረጠራለሁ ?"

"በጌታዬ ርስት ፣ በጌታዬ ሠፈር ምንም ዐይነት ጉድለት እንዲገኝ ፣ ነውር ነገር እንዲሰማ አልፈቅድምና ፣ ነግሬያለሁ" አሉና ፍጡር ፣ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያዉን አጠናከሩ ።

ጉዳዩ ለአቶ አርጋው መርዶ ነበር ። ወደ ይታክቱ ቤት ብቅ ሲሉ የነበሩት ማታ ማታ ነበር ። እንዳይታዩና ወሬው ከቤታቸው እንዳይገባ ይጠነቀቁም ነበር ።

"እንዲህ ብሎ ዛተ ?" አሉ አቶ አርጋው ፣ የአቶ ፍጡርን ማስጠንቀቂያ ከይታክቱ እንደ ሰሙ ።

"አዎን !"

"ታዲያ አንችስ ምን ታስቢያለሽ ?"

"እኔማ ምን ዐውቄ ?"

"ግዴለም እኔ ዐውቃለሁ!"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እዬ ዕድሌ!" አሉና ይታነቡ ጉንጮቻቸውን በዕንባ ማረሻዎች ተለተሉ . . . . . .

የፋሽሽት ኢጣሊያ ጦር፣ የኢትዮጵያን አርበኞች ለመደምሰስ ሲያግተለትለው ከነበረው ሠራዊቱ፣ ሩቡ ክፍል ሠፍሮባት የነበረችው ደብረ ብርሃን ነበረች። ከአዲስ አበባ ቀጥሎ ከፍተኛው ሠራዊት የተከማቸባት ደብረ ብርሃን እየሠፋች መሔድ ጀምራለች። የፋሽሽት ጦር ከደብረ ብርሃን እየተነሣ አካባቢውን ያስስና ያተራምስ በነበረበትም ወቅት በካፒታኖ ሮቤርቶ ይታዘዝ የነበረ ጦር በጫጫ አካባቢ ሠፍሮ ሰንብቷል።

ካፒታኖ ከሠፈሩ ወጥቶ ከአንዲት ጉብታ ላይ ሆኖ፣ የረፋድ ፀሐይ እየሞቀ ራቅ ብለው የነበሩትን ቤቶች ሲመለከት፣ ጥቂት ቤቶች ውሃ ከወንዝ ቀድተው ሲሔዱ፣ ወይኖቹ ሩዝዝ ብለው ማየት ይጀምራሉ። ማታውን ያደነዘዘው ቪኖ የጦዋት ፀይኖቹን እንደ ፈለገ ለማዘዝ አስችሟቸታል። መዲያው ከሜሩ ሮቹ እንዱን ጠርቶ፣ 'መነጽሩን እምጣ' ብሎ አዘዘውና፣ መነጽሩን ሲሰጠው፣ በእነዚያ እንስራና ገንቦ በተሸከሙ ሴቶች ላይ አነጣጠረው። ወለል ብለው ተከሠቱለት። ያሁን እንጂ፣ ወይን ሕሊናውም፣ ቀልቡም ተባብረው በእንደኛዋ ሴት ላይ ወረፉ።

ጠይም ለግላጋ፣ አካላተ ሙሉ ነች። የጦዋቱ ፀሐይ በተለይ የእርስዋን ውበት ለካፒታኖ ለማሳየት ጎብረ ቀለሟን እየለዋወጠች የምታንጸባርቅ ይመስል፣ ከደረቷ ላይ እያረፈች ውበቷን የምትፈነጥቅ ሆናለች። ካፒታኖ በመነጽሩ ተመለከተና፣ ትርጁማኑን አስጠርቶ ትእዛዝ ሰጠው።

ፀሐይ ስትቀዘቅዝ፣ ትርጁማኑ ወደ መንደሮቹ ሔደ ሜታ ሹሙን አስጠርቶ የካፒታኖን ትእዛዝ ነገረ።

"ጀታቤ! በእግዝትን ማርያም ይሁንብዎ! የባለሥልጣን ሚስት ናት። ከጉድ ያውጡኝ" አሉት። ሜቃ ሹሙም ቢዉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ንቀው አቶ ይርዳውን አማከረ ። እሳቸውም የፍየል ሙክቶች ለትርጁማኑ ይዘው ቀረቡ ።

"ማን የሚሉት ባለሥልጣን ነው ?" አለ አስተርጓሚዉ ።

"መምሬ ታደሰ ይባላሉ ።"

"መምሬ ምን ሥልጣን አላቸው ?"

"ሥልጣነ ክህነት የተቀበሉ ናቸው ።"

"ታዲያ ምን አለበት ? ጥዋት ትመለሳለች ።"

"እንዴት ተደርጎ ? የቄስ [ሚስት አንድ ጊዜ ከወሰለተች በኋላ ፣ ተመልሳ አትገባም ኮ ! ነውር ነው ፣ ኃጢአት ነው!"

"ግዴለም በምስጢር የሚሆን ነው ። ማንም አያያትም ። ይህን ነገር የምናውቀው እኛ ብቻ ነን ። እኔ ፣ እርስዎ ፣ ጭቃ ሹም ፣ ሴትዮዋና ካፒታኖ ብቻ ነን ፤ ሌላ ሰው አያይም ። አይ ሰማም ።"

"ኧረ እንዲህም አይደል ! የቄስ ሚስት ናትኮ ነው የም ለው ። አንድ ጊዜ ከረከሰች—" ብለው አቶ ይርዳው ተናግረው ሳይጨርሱ ፣

"ከካፒታኖ ጋር ማደር መርከስ ይባላል ?" አለ ትርጁማኑ ፣ ቆጣ ብሎ ።

"ከማንም ወንድ ጋር ቢሆን ከተነካካች 'ረከሰች' ማለት ነው ። ሥርዓቱ ፣ ደንቡ ይኸው ነው ማለቱ ነኝ እንጂ ፣ ጌታዮ ካፒታኖማ ከመላእክት ወገን ናቸው ፤ ርኩሰት የለባቸውም ፣ ክንፍ ቀረሽ ምድራዊ መላክ ናቸው" አሉ አቶ ይርዳው እየ ራዱ ።

"ቄሱ የታሉ ?"

"የለሞን ተረኛ ሆነው ለቅዳሴ ወደ ቆላው ወርደዋል ።"

"መች ይመለሳሉ ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ከሁለት ሳምንት በኋላ ።"

"ግዴለም ፤ ሁለት ሳምንት ቀርቶ ሁለት ቀንም አትቆይም። ጥዋት ራሴ አመጣታለሁ ። እኔ ከዚህ ያሉ መስሎኝ ነው እንጂ ፣ ቁሱ ሽርሽር ከሔዱማ እርሷም መደሰት አለባት ።"

አቶ ይርዳው ፣ ከትርጁማኑ ጫማ ወደቁ ። ሁለት እግሮቹን ጥርቅም አድርገው ያዙና ፣ "ጌታዬ ፣ ባይሆን ሌላ ሴት ልፈልግ ፣ ለርስዎም ጭምር ። እርሷን ግን በጌታችን በመሶሎኒ ሞት ይማሩልኝ" ብለው እያለቀሱ ለመኑት ።

"መሶሎኒ ይሙት ነው የሚሉ ?" አለ ትርጁማኑ ፣ በእግሩ እየገፋቸው ።

"ኧረ ! ኧረ አልወጣኝም ። እሳቸውማ ለዘለዓለም ይኑሩ እንጂ ። በእርሳቸው ይሁንብዎ ፣ በእርሳቸው ተማፅኛዎታለሁ ማለቴ ነኝ እንጂ ፣ እርሳቸውማ ምን በወጣቸው ይሞታሉ ? ገና ሺህ ዓመት የሚኖሩ ናቸው ። በሕልሜም አሳይቶኛል ፣ ገና የልጅ ልጃቸው ዓለምን ይገዛል" አሉ አቶ ይርዳው ፣ ከመሬት ላይ እንደ ወደቁ ።

"ሌላ ሴት ከየት ያመጣሉ ?"

"እንዲያው ከየመንደሩ ልፈልጋ ! ልለምን ።"

"በርስዎ ቤት ሴት የለም ?"

"ባለቤቴ ብቻ ናት ።"

"ቆንጆ ናት ! ልጅ ናት ?"

"ቆርፋዳ አሮጊት ናት ፣ ጌታዬ !"

"ለካፒታኖ አትሆንም ?"

"ኧረ ! ኧረ ! ወይኔ እያዩ እንዴት ?" አሉና ብድግ አሉ አቶ ይርዳው ፣ ቆጣ ብለው ።

"ይበሉ ሌላ ሴት ይፈልጉ ፤ ያለዚያ ወይ የቁሱን ፣ ወይ የርስዎን ሚስት መውሰዴ ነው !"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እሺ ፣ ለነገ ጥዋት ይገር እመጣለሁ ።"

"ጌታ ካፒታኖ ዛሬ ብቻቸውን ሊያድሩ ማለት ? እንዴት ይቀልዳሉ !"

"ለሠርግ የመጡ ሴቶች አይጠቅምና ከየቤቱ እንፈልጋ ለን" አሉ ጭቃ ሹሙ ።

"እንግዲህ ለካፒታኖም ፣ ለቲለ.ንቲም ፣ ለሌላ ሰውም የሚ ሆኑ አምስት ያህል ሴቶች ፈልጉ ።"

"ለርስዎስ ?" አለ ጭቃ ሹሙ ጠጋ ብሎ ።

"ያውም ቆንጆዋን መርጠህ ነዋ !" አለ ትርጁማኑ ።

ጭቃ ሹሙና አቶ ይርዳው ፣ ትርጁማኑን እጅ እየነሡት ሔዱ ። ከተበታተኑት መንደሮች በአንደኛዋ ሠርግ ስለነበረ ፣ ወደዚያው በጨለማ ሔዱ ። አስተርጓሚውም ሙክቶቹን እያ ስነዳ ወደ ሠፈሩ ተመለሰ ። ካፒታኖ በጉጉት ይጠባበቅ ነበርና ወዲያው አስጠሩት ፣

"የታለች" ብሎ ጠየቀው ።

"ውሃ ተሙቆ ሰውነቷን ታጥባ ፣ ንጹሕ ልብስ ለብሳ ትመ ጣለች" አለ ትርጁማኑ ።

"ብራቮ ! ብራቮ ! ብራቮ ! " አለ ካፒታኖ ።

ምሽቱ እየገፋ ሲሔድ ፣ ካፒታኖ ቪኖውን እየደጋገመ ሲጠጣ ትርጁማኑ ወታደሮች አስከትሎ ወደ መንደሩዋ ወረደና ከአቶ ይርዳው ቤት ገብቶ ሲጠባበቅ ፣ ጭቃ ሹሙና አቶ ይርዳው ሦስት እንደ ነገሩ የሆኑ ሴቶች ይዘው ገቡ ።

ትርጁማኑ ፣ የቀረበለትን ሴቶች ተረክቦ ከሁለት ወታደሮች ጋር ወደ ሠፈር እንዲሔዱ አዘዘና ፣

"የእርስዎ ሚስትም ቆንጆ ናቸው ! ግን እስቲ የቄሱን ሚስት ጥሩዋት " አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴ ምን ሆኑብኝ ፥ ጀታዮ ! እንደዚህ በጨለማ መድ ከሜኮ እርሱዋን ለማዳን ነበር ። የቄስ ሚስት ናት ፥ እትደፈ ርም ነውኮ እምለው ።"

"አልወስዳትም ፤ ትምጣና ልያት" አለ ትርጁማኑ ።

"አረ እባክዎ በሥላሴዎች ይሁንብዎ ! ምነው እርስዎስ ወን ድማችን ፥ ዘጋችን አይደሉም ? እንዴት የቄስ ሚስት ትርከስ ይላሉ ?" አሉ አቶ ይርዳው ።

"እሺ ፥ የርስዎን ሚስት ?" አለ ትርጁማኑ ፥ የክፋቱ ክፋት ፥ የትዕቢቱ ትዕቢት ወጥሮት ።

"እንዴት ? እንዴት ? በዐይኔ እያየሁ ? እንዴት ይሆናል ? ግፍ አይሆንባችሁም ?" አሉ አቶ ይርዳው ።

"ግፍ ? የምን ግፍ ? ለእናንተ ጸጥታ ፥ ለእናንተ ልማት ተሠ ልፈን እዚህ ድረስ መጥተን ሠፍረን ፥ ሴት ስጡን ባልን ግፍ ነው ትላለህ ? ምነው የናንተ ባላባቶች ሚስቶቻችሁን እየቀሙ ሲወስዱባችሁ አልነበረም ? አሁን እኛ ምን ግፍ ነው የሠራ ነው ? ግፈኞች እናንተ ናችሁ ፥ ባሏ ሽርሽር የሔደ ሴት አትን ኩብን የምትሉ ፤ ቤቷን አሳየኝ አለና ቱርጁማኑ ሞቃ ሹመን ይዞ ወጣ ። ወዲያው ትሊንቴው ጥቂት ወታደሮች አስከትሎ ባትሪ እያበሩ ወደ መንደሩ ሲገቡ ፥ ትርጁማኑና ሞቃ ሹሙ በሩቁ ተመለከቱ ። አቶ ይርዳው ወደ ኋላ ቀረት አሉ ። ከቤታ ቸው በስተጓሮ ወደ ነበረው ጐተራቸው ሔደው ልብስ ለዋወ ጡና ባለቤታቸውን ይዘው ወደ ቄስ ታደሰ ቤት እየሮጡ ሔደው ፥ ያችን ሴት ያችኑ ጣጠኛ ሴት ቢያስጠሩ ጠፋችባቸው ። ሚስታ ቸውን በጓሮ በኩል ደበቁና እርሳቸው ጨለማን ተገን አድርገው ከዲብ ሥር አደፈጡ ። ቲሌንቲ ፥ ትርጁማኑና ሞቃ ሹሙ ወደ ቄሱ ቤት ሲያመሩ ፥ "ድም ! ድም ! ድም !" ብለው ሦስት ጥይቶች ተከታትለው ተተኮሱ ።

ቲሌንቲ ፥ ትርጁማኑና ሞቃ ሹሙ ሲወድቁ ፥ ወታደሮቹ ሸሹ ። ወዲያው ተኳሹ ሩጦ ከወደቁት ሰዎች ላይ ሁለት ሽጉ ጥና አንድ ባትሪ አንሥቶ ሮጠ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ካፒታኖ ፣ ያችን መንደር አስከብቦዋት አደረ። በዚያች ሌሊት በዚያች መንደር የነበሩት ነዋሪዎች የቻሉት እየሸለኩ ሲወጡ ያልሆነላቸው በየጓሮው ፣ በየአጥሩ ጥግ ፍርሃትና ውርጭ ሲያር በደብዳቸው አደሩ ። ጎህ ሲቀድ ካፒታኖ ከመንደርዋ ራቅ ብሎ መንደርዋን በመነጽሩ እየተመለከተ ፣ በመጀመሪያ በወታደሮች አስፈተሻት ። ቀጥሎ እሳት አስለቀቀባት ።

በፍተሻው የተያዙት ሕፃናት ፣ ሽማግሌዎችና ሴቶችም ተነ ድተው ወደ ሠፈሩ ተወስደው ታሰሩ ። የቤት እንስሳቱም ተወ ረሱ ። አቶ ይርዳውና ሚስታቸው ግን አልተገኙም ።

ለዚያች መንደር መጥፋት ምክንያት የሆነችው ሴት ደግሞ ፣ በዚያ ጨለማ የባለቤቷን ጐልማሳ ወንድም አስከትላ ከመ ንደሩዋ ወጥታ ጠፋች ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ፣ ገበያተኛ መስላ ደብረ ብርሃን ከተማ ስትገባ ፣ ያው ጣጠኛው ውበቷ ሌላ ተመ ልካች አስነሣባትና ፣ ጠልፎ ወደ ቤቱ አስገባት ።

ሰውዬው ፣ ፋሽሽቶች በፊርማቶሪነት ያስቀመጡትና የፈ ለገውን መያዝና መግደል የሚችል ባለሥልጣን ነበር ። ከእር ሱም ባመቱ ወንድ ልጅ ወለደች ። ፋሽስት ጣሊያን ከኢትዮ ጵያ ተጠራርጋ ስትወጣ ፣ ያ ፊርማቶሪ ያችን ሴት ወደ አዲስ አበባ ሰደዳትና እርሱ እጁን ሰጠ ።

ሴትዮዋ አዲስ አበባ ገብታ ፣ ቦታ ተመርታ ፣ ጎጆ ቀልሳ የፊታውራሪ እርገጣቸው ጢሰኛ ሆና ፣ ከውበቷ ሌላ ፊልተር ጠላዋ ባለዝና ያደረጋት ወይዘሮ ይታክቱ ነበረች .....

"አዬ ዕድሌ !" ብላ ያለቀሰችውም አቶ አርጋውና አቶ ፍጡር በርሷ ምክንያት የሚጋደሉባት መስሏት ነበር ። አቶ ይር ዳው ፣ እነዚያን ፋሽስቶች ለሽልሸው እንደ ሸፈቱ ሁሉ ፣ አቶ አርጋውም ፍጡርን ዘርረው የሚሸፍቱባት መስሏት ነበር ፣ ዕድ ሉዋን ያማረረችው ።

የአቶ አርጋው ልብ በወይዘሮ ይታክቱ ፍቅር መደንዘዙን ፣ የአቶ አርጋው ስም በወይዘሮ ይታክቱ ምክንያት በሠፈሩ መነ ሣቱን ፣ ባለቤታቸውና የሁለት ልጆቻቸው እናት የነበሩት ወይዘሮ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዘነቡ ካረጋገጡ በኋላ ፣ ጓዝ ምንጓዛቸውን ጠቅልለው ከቤታ ቸው በመውጣታቸው ፣ አርጋውም ወይዘሮ ይታከቱን ለጊዜው ከዚያ ሠፈር አውጥተው ፣ ቤት ተከራይተው አስቀመጡ ።

ከወይዘሮ ዘነቡ ጋር የነበራቸውን የጋብቻ ውል ቀድደው ከጣሉ በኋላ ፣ ይታከቱን ከቤታቸው አስገቡ ። ፊታውራሪ እር ገጣቸውም አርጋውን ጠምደው ያዙ ።

'እኔ የቀጣሁትን ዕድርተኛ ፣ አንተ ለምን ማርከው ?'

'አንተስ እኔ ሳላውቅ አዲስ ዕድርተኛ ለምንድን ነው የመ ዘገብከው ?'

'አንተስ ዕድርተኛ ላልሆነ ሰው ለምንድን ነው ዕቃ ያዋ ስከው ?'

'የቦታና የቤት ኪራይ ላልከፈለው ዕድርተኛ ፣ ለምንድን ነው ገንዘብ የከፈልኸው ?'

'አንተ ራስህሳ ለምንድነው ፣ ቀብር ሳትመጣ የቀረኸው ?'

አቶ አርጋውና አቶ ፍጡር ፣ በየዕለቱ የሚለዋወጡዋቸውና ጹሳ የሚማዘቡባቸው ጉዳዮች ነበሩ ። ሁለቱ ተፎካካሪዎች በዚህ ላይ እንዳሉ ፣ ዕድሩም መላ ቅጡ ጠፍቶ በመዋለል ላይ እንዳለ አቶ አርጋውን ከነበራቸው ውክልና እንዲያወርዱዋቸው ፊታ ውራሪ አርገጣቸው ልጅ አደባሩን መወትወት ጀመሩ ።

'ጌታ ቅር ተሰኝተዋል ፣ ምን ነውር ነገር ሠርተዋል ? ምን ክፉ ተናግረዋል ?' ብለው ልጅ አደባሩ ወኪላቸውን ደጋግ መው ስለ ጠየቋቸው ፣ ከነበሩበት የውክልና ሥልጣን ሳለመው ረድ ሲሉ ፣ አቶ አርጋው ወይዘሮ ይታከቱን ከቤታቸው አው ጥተው በጐላ ሠፈር ቤት ተከራይተው አስቀመጡ ።

አቶ ፍጡር ደግሞ ፣ ከጌታቸው ከፊታውራሪ ርስት ለአ ምስት ጢሰኛ የሚሆን ቦታ በወይዘሮ ይታከቱ ስም ተመሩላ ቸውና ፣ በዚህ አባብለው ይታከቱን ጠልፈው ፣ ከሴላ ሠፈር ቤት ተከራይተው አስቀመጡ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሠፈሩ ነዋሪ ፣ የፍጡርን ጠላፊነት ሳይሰማ ውሎ ዐደረ ። ሰንባብቶ ግን ፣ የአቶ አርጋውና የአቶ ፍጡር ጥል ከድብብቆሽ ይፋ ወጣና ፣ የሠፈሩ መዘባበቻ ሆነ ።

በመካከሉ ደግሞ ፣ የአጋጣሚ ነገር ሆነና በሌላ ሠፈር ይኖሩ የነበሩ የአቶ አርጋው እኅት ልጅ ዐውቆ ዐበድ ሲያባርረው ከመኪና ጋር ተላትሞ ይሞታል ። በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ ልጅ አድባሩ ሲገኙ ፣ ፈታውራሪ ግን ፣ ማታ ከንዘኑ ቤት ደረስ ብለው ተመለሱ ። አቶ ፍጡርማ እንኳን ለቅሶ ሊደርሱ ፣ 'የእኅቱ ልጅ የሞተው ሠርቆ ሲሮጥ ነው ። ለምን ደግሞ ራሱ አያደገምም ! እርሱስ አንድ ሴባ አይደለም ?' እያሉ መናገራቸውን አቶ አርጋው ሰሙ ።

ሠፈሩን ታዘቡት ። እንኳን ከፈታውራሪ ጢሰኞች ፣ አራሳቸው እንደራሴ በሆኑበት ሠፈርም ከሚኖሩት ዕድርተኞች 'እማዜር ያጥናዎ' ያሉዋቸው በመጠኑ ነበሩ ። አርጋው ኃዘናቸውን ሲጨርሱ ፣ በደንቡ መሠረት ገንዘብ እንዲሰጣቸው ዕድራቸውን ይጠይቃሉ ። የዕድሩን ተመራጮች አቶ ፍጡር መስበክ ፣ ማታ ለልና መደለል ይጀምራሉ ። ነገሩን ለመወሰን የዕድሩ ኃላፊዎች ባደረጉት ስብሰባ ሁለቱ እንደራሴዎች የመረረ ሙግት አደረጉ ።

"እኅትህ ራሷን ችላ በሌላ ሠፈር የምትኖር ናት ። ከራሷ ዕድርም ገንዘብ በልታለች ። ስለዚህ የኛ ዕድር ላንተ ገንዘብ ሊከፍል አይገባውም" ብለው አቶ ፍጡር ፣ ሙግታቸውን አጠነከሩ ።

"የዕድራችን ደንብ አራተኛው አንቀጽ ይደግፈኛልና ሊከፈለኝ ይገባል" ብለው አቶ አርጋው ተከራከሩ ።

"አራተኛው አንቀጽም ቢሆን ፣ አገር ቤት ሔደው ቀብረው የተመለሱትን ነው የሚደግፍ እንጂ ፣ በአዲስ አበባ ውስጥ ዘመድ ለሚሞትባቸው አይደግፍምና ፣ አይገባህም" ብለው አቶ ፍጡር መልስ ይሰጣሉ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምነው ከአምስት ወራት በፊት የጌታህ ሚስት ዘመድ ከዚሁ ከከተማው ውስጥ ሙታ ፣ ለጌታህ ገንዘብ ተሰጥቶ የለም?" ብለው አቶ አርጋውም ይመልሳሉ ።

"'ዶሮ ጭራ ጭራ ታወጣለች ካራ' የሚባለው ተረት እን ዳይደርስብህ እንደበትህን አርመህ ብትናገር ይሻልሃል" አሉና ፍጡር አፈጠጡ ።

"ያንተ ጌታ በካራ ቀርቶ በመትረየሱም አልሠራበት፤ ደርሶ መኮፈስ!" አሉ አቶ አርጋው ፣ ስብስባውን ረግጠው ሊሔዱ እየቃጣቸው ።

"በሉ በቃችሁ ፣ በቃችሁ ። ንግግራችሁን ሰማንላችሁ" አሉ አቶ እንደሻው ፣ ግራ ቀኙን እየገላመጡ ፣ "አሁን ትርፍ ትርፉን ነገር ትተን ስለ ዋናው ጉዳይ እንነጋገር ። አቶ ፍጡር ያነሡት ነጥብ ፣ ትልቁ ጭብጥ እዚያ ላይ ነው ። ፍሬ ነገርዎን አልሳተም" ብለው ገና አስተያየታቸውን ሳያጠቃልሉ ፣

አቶ አርጋው ከተቀመጡበት ብድግ ብለው ፣ "እኮ እንተም አይገባህም አይደል እምትለኝ?" ብለው እየተቆናጠሩ ሔዱላ ቸው ።

"ዕድሩን እንዳይጐዱት መጠነኛም ቢሆን ብንከፍላቸው አይሻልም?" ኦሉ መምሬ ዘዕውቀቱ ።

"ነገር ነገሩ እውነትዎን ነው" አሉ አቶ እንደሻው ።

"የወጣውና ሠፈር ያወቀው ደንብ ይፍረስ ነው የምትሉት?" አሉና አቶ ፍጡር አፈጠጡባቸው ።

"ዕድሩ እንዳይጐዳ' ኮ ብለን ነው" አሉ መምሬ ።

"በምኑ ነው የሚጐዳው? ይህ ዕድር እንደሆነ የባለርስቶቹ ነው ፤ እነርሱ እያሉ በዚህ ዕድር ላይ ማንም ጉዳት ሊያመጣ አይቻለውም" አሉ ፍጡር ፣ እያንዳንዱን ዳኛ በጥያቄያዊ አስ ተያየት እየተመለከቱ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንግዲህ ለዚህ የሚበጀው" አሉ አቶ እንደሻው፣ የመጨረሻ ሐሳብ ሲያሰሙ። "ለዚህ መድኃኒት ቶሎ ብለን ነገሩን ለልጅ አድባሩ ማመልከትና፣ እርሳቸው አቶ አርጋውን እንዲቆጧቸው ማድረግ ብቻ ነው። ሌላ ማቃለያ የለውም።"

"ያሥር አለቃኮ ዛሬ ቢገኝ ኑሮ፣ ነገሩ ባጭሩ ተቆርጦ ነበር። እንዲያው ያለሱ ላይሆን!" አሉ መምሬ በዕውቀቱ።

ከበደ፣ ለአስቸኳይ ሥራ ከአዲስ አበባ ውጭ ሔዶ ስለነበረ፣ በዚያ ስብሰባ አልተገኘም ነበርና፣ በዳኝነቱ ላይ ተቀምጠው የነበሩት አቶ እንደሻው ባቀረቡት ሐሳብ የቀሩትም ተሰብሳቢዎች ስለ ተስማሙበት፣ መሰብሰቢያቸው ከነበረችው ግራር ሥር ሊነሡ ሲሉ፣

"ነርገጤና ፍጡር ጥናቱን ይስጣችሁ
ይታከቱን ተሻምቶ አርጋው ነጠቃችሁ"

እያለ ደባልቀው ሔደባቸው። የዋለ ያደረ ግጥም ነበር።

"እቡ ጉድ! የከበደ ያለመኖር ዛሬ ጉድ አመጣ" አሉ መምሬ በዕውቀቱ፣ ደባልቀውን አስፈራርቶም ሆነ አባብሎ የሚመልሰው ሌላ ሰው ከመካከላቸው እንደሌለ በማመን።

"ራሱ ነው፣ አርጋው ነው፣ እንዲህ ብለህ ተሳደብ ብሎ የላከው። ሌላ አይምሰላችሁ" አሉ አቶ ፍጡርም።

"የርገጤን ውሽማ፣ የፍጡርን ቁባት
አርጋው ነጥቆ አገባት"

አለ ደባልቀው፣ ጮክ ብሎ እያቅራራ። ፍጡር ጠልፈው መውሰዳቸውንና መደበቃቸውን ቢያውቅም፣ ፍጡርን ለማናደድ ነበር።

"የወላዲተ አምላክ ያለህ! ዛሬስ ምኑን ያናግረው ጀመር? እቡ ጉድ!" አሉና መምሬ በዕውቀቱ፣ አንገታቸውን አቀረቀሩ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ራሱ እርጋው እኮ ነው የላከው። ምን ያድርግ? እሁን ደባልቀው ነፍስ ዐውቆ ይህን ሁሉ ይናገራል ብለው ነው፣ አባቴ! ሙያ መስሎት ተናገር ብሎ የላከው ኮ ራሱ ነው" አሉና እቶ ፍጡር ፣ ወደ ደባልቀው እያዘገመ ሔዱ።

"ፍጡር ጉድህ ወጣ! ከጌታህና ከአማችህ ከአርገጣቸው ዕቁባቱን እየሠረቅህ ኑረህ ፣ ጉድህ ፣ ገመናህ ወጣ" አሰ ደባልቀው እየገሠገሠ።

እቶ ፍጡር፣ "ዛሬ ውለህ ያደርክ እንደሆነ ታዘበኝ" አሉና ድንጋይ አነሡበት።

"ያንተ ጠጠር ቀርቶ የጌታህን መትረየስም አልፈራ" አለና ደባልቀው ድንጋይ አነሣ።

"እባክዎ ይመለሱ። ከርሱ ጋር አፍ ይካፈታሉ?" አሉ መምሬ በዕውቀቱ።

"እርስዎስ ከምድረ አቃጣሪ ጋር ምን ያደርጋሉ፣ አባቴ?" አለ ደባልቀው።

"አውጣኝ ፈጣሪ! ምን ሊያሰማኝ ነው?" አሉ መምሬ በሁለት እጆቻው ራሳቸውን ይዘው።

"አትሔድም ከዚህ?" አሉና ፍጡር ያነሡትን ድንጋይ ወረ ወሩበት። እርሱም ወረወረባቸውና ሮጠ።

"በሉ እንግዲህ ፣ ወደ ልጅ አድባሩ ዘንድ እንሒድና ነገሩ እልባት ያግኝ" አሉ እንደሻው።

እቶ ፍጡርም ደባልቀውን አባረው ተመለሱና ፣ ተሰብሳቢ ዎቹን በዐይኖቻቸው ሙሉ ለማየት እየተቅለሰለሱ ፣

"እንግዲህ በደለኛውንና ጥጋበኛውን ተመልክታችኋል ፣ እናንተን ረግጦ ፣ እናንተን ንቆ አይደለም ተነሥቶ የሔደው! በሉ ፍረዱ" አሉና ተቀመጡ።

"እኛ ተችተን እኛ ፈርደን ፋይዳም የለውና ፣ ለልጅ አድባሩ መንገሩ ፣ ጉዳዩ ሳያንካካን ማብረዱ ነው የሚሻለው" ብለው

t.me/OLDBOOKSPDF

አቶ እንደሻው አሳሰቡ ። ተሰብሳቢዎቹም ተስማሙበትና ወደ ልጅ አድባሩ ቤት ሔዱ ።

በዚያ ሰዓት ደግሞ ፣ ልጅ አድባሩ በቤታቸው ሰላልነበሩ፣ በሌላ ቀን ሔደው ጉዳዩን ለማስረዳት ተስማምተው ተሰብሳቢ ዎቹ ወደየቤታቸው ተበተኑ ።

የዕድሩን ተመራጮች በሥራ ላይ ሥራ ፣ በጉዳይ ላይ ጉዳይ እያጋጠማቸው ፣ በተቃጠሩበት ዕለት ተገናኙተው ፣ ወደ ልጅ አድባሩ ፈጥነው ከመሔድ ውለው አደሩ ።

አቶ አርጋው ግን ፣ የዕድሩን ተመራጮች ሰበሰቡና ፣

"ፍጡርን ከዕድርተኛነቱ ሠርዤዋለሁና እንድታውቁት" ብለው አስታወቁ ።

"በምን የተነሣ ?" አሉ አቶ እንደሻው ።

"የሚሠራውን ሥራ ሁሉ እያያችሁት?! የማታውቁት ምን ነገር አለና ነው አሁን የሚጠይቁኝ ?" አሉ አቶ አርጋው ፣ አቶ እንደሻውን በትዝብት እየተመለከቱ ።

"ቢሆንስ ፣ እንዴት ከዕድሩ ያስወጧቸዋል ?"

"ከሠፈሩም ገና አባርረዋለሁ !!"

"እስቲ ለማንኛውም ፣ የፓ አለቃ ከበደ ከሔደበት ይም ጣና ፣ ሌሎችም ሰዎች ታክለው ጉዳያችሁን እናየዋለን ። አሁን አይቸኩሉ" አሉ አቶ እንደሻው ።

"ለማንኛውም ፣ እስቲ ለጊዜው እኛ እንመካከርበት ፣ እርስዎ ይቆዩን" አሉ መምሬ በዕውቀቱ ።

"ምን ከፋኝ ፣ ምከሩበት" አሉና አቶ አርጋው ፣ ራመድ ራመድ ብለው ሲሔዱ ፣

"የሆነ ሆኖ እንዳይርቁን" አሉ መምሬ ።

በዚያ ዕለትና ሰዓት የተገኙት አቶ እንደሻው ፣ መምሬ በዕውቀቱ ፣ አቶ ይመርና አቶ ቡልቻ በሁለቱ እንደራሴዎች መካ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከል የተፈጠረውን ያለመግባባት እያንዳንዳቸው እጣርተውና እፍረተርጠው የማያውቁት ቢሆንም ቅሉ፣ ከመዋደቅና ዕድሩን ከመፀጥፀጥ፣ ሠፈሩንም ከማተራመስ እንዳይደርሱ ሲሉ፣ ሁለቱንም ለማስታረቅ መከራ ለማድረግ ነበር — ውይይቱ።

''መቸም፣ በያለኛው እገሌ ነው ብሎ ለመፍረድከ ያስቸግራል'' አሉ አቶ እንደሻው፣ በውይይቱ መጀመሪያ ላይ።

'''እንተ በዳያ ነህ፣ እርሱ ተበዳይ ነው፣ ይህን ያህል ካሠው' ለማለት ይቸግራል። እንዲያው በደፈናው ግን ለኛ ስትሉ፣ ለዕድርተኛውና ለሠፈሩ ስትሉ ታረቁልን ብሎ መለመኑ ነው የሚሻለው'' አሉ መምራም።

''መቸም፣ የተባባሱት በሴትዮዋ ምክንያት ነውና፣ ታዲያ ከዚህ ነገር ምን ማድረግ እንችላለን?'' አሉ አቶ ይመር።

''ሴትዮዋን ቀድሞ የያዘ ማነው?'' አሉ አቶ ቡልቻ።

''መቸም፣ ይህን እንኳ ለይቶ ለማወቅ ይቸግራል። ሁላችንም የጠላ ደንበኞች ነበርን። ታዲያ 'ቀዳሚው እገሌ ነው' ለማለት፣ እንኳን እኛ ራሳቸው ባለጉዳዮቹም የሚያውቁት አይመስለኝም'' አሉ አቶ እንደሻው።

''ሁሮ ሁሮ እኮ ሴትዮዋን 'በመጀመሪያ ያወቀ እገሌ ነውና' እገሌ ይካስ' ማለት ይቸግራል። ስለዚህ ቀዳሚውንና ተከታዩን ለማወቅ ከመድከም፣ እንዲሁ ታረቁልን ብሎ መለመኑ ነው የሚያዋጣው'' አሉ መምራ በዕውቀቱ።

''እውነት እንነጋገር ከተባለ፣ የተበደሉት አቶ አርጋው ይመስሉኛል'' ኦሉ አቶ ቡልቻ።

''ምክንያቱስ?'' አሉ አቶ እንደሻው።

''ምክንያቱማ፣ ሴትዮዋን ከጠላ ቤታቸው አውጥተው ከቤታቸው ያስገቡ አቶ አርጋው ናቸው። ስለዚህ...'' ብለው ቡልቻ ተናግረው ሳያበቁ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"ከዚህ ቀደም እንኳ ፣ አቶ ፍጡርም ለሴትዮዋ ቦታ ሰሑ ተው ፣ ቤት ሠርተው እስቀምጠዋል ይመስለኛል" ኦሉ አቶ እንደሻው ።

"እንደርሱ አይደለም ። ሴትዮዋ የመጡት ቀድመው ነው ። ፍጡር የመጡት በኋላ ። የትናየት ተገናኝተው ?" አሉ ይመር ።

"ቆይኝማ ፣ የሰውን ሥራ ፣ የሰውን ገመና መናገር ተገቢ አይሆንም እንጂ ፣ አቶ ፍጡር ገና ከዚህ ሠፈር ሳይመጡ ፣ ሴት ዮዋን አምጥተው ፣ ከፊታውራሪ ጋር አስተዋውቀው ፣ ቦታ ሰጥተው ፣ ቤት ሠርተውከ ያስቀመጡ ናቸው ይላላል" አሉ አቶ እንደሻው ።

"እኔ እንግዲህ ይህን ሁሉ አላወቅሁም" አሉ ይመር ።

"ቀዳሚውንና ተከታዩን እናጣራ ፣ በዳዩንና ተበዳዩን እን መዝን ካልን ይጓተታል ፣ እንዲያውም ያባብሳል ፣ ስለዚህ የል ባቸውን በልባቸው እንደያዙ እንዲታረቁልን መለመኑ ነው የሚያዋጣን" አሉ መምሬ ፣ ጣጣውን በአጭሩ ለመቅጨት እየ ቸኮሉ ።

"እሺ ካሉን እኔ ምን ከፋኝ ? 'ቂም ይዞ ዕርቅ ፣ ተመልሶ ልብ ድርቅ' እንዳይሆን ብዬ ነው እንጂ" አሉ አቶ እንደሻውም ።

"እስቲ ለማንኛውም ግራና ቀኙን ጠርተን ብናነጋግራ ቸውስ" አሉ አቶ ይመኒ ።

"ማለፊያ ነው ፣ ይሁን" አሉ መምሬ ።

ከሽማግሌዎቹ ራቅ ብለው ፣ ከባሕር ዛፉ ሥር ከነበረች ድንጋይ ላይ ተቀምጠው የነበሩትን አቶ አርጋውን ፣ አቶ ይመር ጠቀሱዋቸውና መጡ ።

"ነዎር! ነዎር ! እስቲ ዐረፍ ይበሉ" አሉና መምሬ ፣ መቀ መጫ አመለከቱዋቸው ።

"መቸም የግራ ቀኙችሁን ጉዳይ ተረድተነዋል ። የሆነ ሆኖ ፣ ደግሞ እርስዎም 'የሚያሳስቡት ነገር ካለዎት እንስማው' ብለን ነው የጠራንዎ" አሉ መምሬ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"የኔና የርሱ ነገር እንዲህ በዋዛ የሚታይ አይደለም፣ በድሎኛል ። የሠራውንም ተንኮል ሁላችሁም የምታውቁት ነው ። 'የዕድር ክፍያ አይገባህም' ብሎ የተሟገተኝ እርሱ አይደለም ፤ አሁንም ፣ ይህ አልበቃው ብሎ የሠራኝን ሥራ ያው ታውቁታላችሁ ። ምን ያደርጋል ሁሉን መናገር ?" አሉና አቶ አርጋው ፣ ፊታቸውን ቅጭም አደረጉ ።

"የዕድሩን ገንዘብ እናቆየውና ፣ ሌላው በደልዎስ ምንድን ነው ?" አሉ መምሬ ።

"እዩ አባቴ ! እርስዎ አያወቁት ይሆናል እንጂ ፣ የሠራኝን ሥራ ሁላቸውም ያውቁታል ኮ" አሉና ፣ በእግራቸው መሬቱን ይጠበጥቡት ጀመር ።

"እኛ የምናውቀው ቢኖርም እርስዎ ቢናገሩት ያምራልና በደልዎን ቢነግሩን አይከፋም" አሉ አቶ እንደሻው ።

"አሄሄ አጣችሁትና ነው ? ከቤት ያስገባኋትን ሴት አባ ብሎ ከቤቴ አውጥቶ ወስዶ ፣ ደብቋት የለም ?" አሉ አቶ አርጋው ፣ ሆድ በባሰው አንጋገር ።

"ሌላስ?" አሉ እንደሻው ።

"እስቲ ለዚሁ ፍርድ ስጡኝ" አሉ አርጋው ።

"እንግዲህ በደልዎን ከነገሩን ፣ በጉዳዩ እንድንመካከርበት አንድ ጊዜ እናስቸግሪዎ ?" አሉ መምሬ በዕውቀቱ ።

አቶ አርጋውም ፣ የነፍስ ዋጋ እንደሚከፈላቸው ሁሉ የሽማግሌዎቹን ፍርድ ለመጠባበቅ ወደ ባሕር ዛፍ ሥር ሔደው ሸብረክ አሉ ።

"ብሶታቸውን ሰማን ፤ ታዲያ ምን ይመስላችኋል ?" አሉ መምሬ በዕውቀቱ ።

"ሌላ ውጣ ውረድ አያስፈልግም ። ሴትዮዋን እናስመልስ ላቸው" አሉ አቶ እንደሻው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሴትዮዋን ብቻ?" አሉ ይመር።

"ታዲያ ደግሞ ምራቂ ያስፈልጋል?" አሉ እንደሻው።

"እንዴ! እንዲያው ያለ ካሣ?" አሉ ይመር።

"ሴትዮዋን ከመለሱላቸው ይበቃል" አሉ እንደሻው።

"እጥፈው ሳይታወቅ፣ ሳናካክስማ እንዴት ይሆናል!" አሉ ይመር

"እስቲ ለማንኛውም የዚያኛውን ምላሽ ደግሞ ብንሰማ አይሻልም?" አሉ መምሬ።

"እኔ ሔጂ ልጥራቸው" አሉ አቶ ይመር።

"እራሳቸው ሔደው ይጥሩ" አሉ አቶ እንደሻው።

"እንዴ፣ በሚዳ ላያ ቢሳደቡስ?" አሉ መምሬ።

"ውሽታቸውን ነው፤ አይነካኩም። ታዲያ ወንድነቱ ካለ አብረው ባንድ ሠፈር አይደል የሚኖሩት?" አሉ አቶ እንደሻው።

"ወንድሜ፣ ለሽምግልና ተቀምጠን 'ዱላ ተማዘዙ' አንልምና፣ ልጅ ፈልጌ ላስጠራቸው" ብለው አቶ ይመር ሔዱ።

"ካሣ ይፈልጉ እንደሁ፣ ወይም 'ሴትዮዋን ከመለስልኝ ይበቃኛል' ይሉ እንደሁ፣ እኒያኛው እስቲመጡ እኒህኛውን ብንጠይቃቸውስ?" አሉ መምሬ።

"ሴትዮዋ ትመለስልዎ ማለትምኮ ይቸግራል፤ እንዲያው ደስ አይልምኮ" አሉ እንደሻው፣ ነገሩ እየቀፈፋቸው።

"ለምን?" አሉ መምሬ።

"አዩ፣አባቴ! ደስ አይልም። ሴት ልጅ ከቤቷ ወጥታ የሰው ጠረን፣ የሰው ጉያ ከለመደች በኋላ፣ 'እንደገና ወደ ቤቷ ትመለስ' ቢባል ለተቀባዩስ መች ደስ ይላል?" አሉ እንደሻው።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ግን ኮ ፣ እኒህ ሴት የአቶ አርጋው የመጀመሪያ ሚስት አልነበሩም ። ሁለቱም ያገኙዋቸው ከመሸታ ቤት ነው ። ይሁንና አቶ አርጋው ቀድመው ከቤታቸው ቢያስገቡዋቸውም ሰማኒያ የላቸውም ። እልህ ይዟቸው ነው ከቤታቸው ያስገቡዋቸው" አሉ አቶ ቡልቻ ።

"ተበዳዩ ፣ ባለጉዳዩ የሚቀበሉዋቸው ከሆነ እኛ ምን ተዳኝን ? ሴትዮዋም ከቤታቸው ገብተው ለመቀመጥ ፈቃደኛ ከሆኑከ ነገሩ አለቀ ማለት ነበር" አሉ መምሬ ።

"ለማንኛውም ሐሳባቸውን ቢነግሩን አይሻልም ?" አሉ ቡልቻ ።

"እስቲ ይጥቀሷቸው ፣ እንስማቸው" አሉና አቶ እንደሻው አቶ ቡልቻን በአንገት ጥቅሻ አዘዙዋቸው ።

አቶ አርጋው ፣ የተፈጸመባቸውን በደል እያሰላሰሉ ፣ ሠፈሩ መላው አገሩ ፣ እንዲያው በጠቅላላው ዓለሙ ራሱ በእርሳቸው ላይ ዐድሞ ከምድረ ገጽ ሊያጠፋቸው የተነሣባቸው መስሎዋቸው ፣ መድረሻም ጠፍቷቸው ሰማይና ምድርን ሲማጠኑበት ከነበረው ባሕር ዛፍ ሥር ተነሥተው ፣ ወደ ግራሩዋ ሥር ሔደው ከተሰብሳቢዎቹ ጋር ሲቀላቀሉ ፣

"ነዎር! ነዎር! ነዎር!" እያሉ እነ መምሩ ሲነሡላቸው ፣ እርሳቸውም ፣

"አይሆንም ! አይሆንም ! እንዴት ይሆናል !?" እያሉ ተቀመጡ ።

"አንድ ጨዋታ አስታወሱኝ" አሉ አቶ እንደሻው ፣ እኒያን ኃዘንተኛ ያጽናኑ መስሏቸው ።

"እንዴት ያል ጨዋታ ?" ብለው ጠየቁ አርጋው ።

"የአጤ ምኒልክ መኳንንት ሁሉ የጦር አበጋዝነቱን ሹመት ይመኙ ነበርና ይህንኑ ያወቁት ምኒልክም ያችን ሹመት ለፊታውራሪ ሀብቱ ጊዮርጊስ ይሰጣሉ ። ታዲያ በቅሎዋቸው የወርቅ መረ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሽት ተጭና ከአዳራሹ በር ድረስ ቀርባላቸው ፣ ሀብተ ጊዮርጊስም የምኒልክን ጫማ ስመው ወጡና ከበቅሎዋቸው ላይ ሊወጡ ሲሉ ፣ ከመኳንንቱ መካከል ራስ አባተ ሮጥ ብለው የበቅሎዋን ርካብ ያዝ ሲያደርጉላቸው ፣

"'እይሆንም ! አይሆንም ! እንዴት ይሆናል' ብለው ሀብተ ጊዮርጊስ ሲግደረደሩ ፣ 'እንዴ ሲሆንማ እያየነው' ብለው ራስ አባተ መለሱላቸው ይባላል ። አሁንም የእርስዎም እንደዚያው ነው" ብለው አቶ እንደሻው ንግግራቸን ሳይደመድሙ ፣

"ታዲያኮ እኔ ተዋረድኩ እንጂ አልተሾምኩም" አሉ አቶ አርጋው ።

"ሹመትዎን የነካ ፣ የደፈረ የለም ። የልጅ አድባሩ ወኪል ነትዎን ፣ የሠፈራችን ዕድር ጸሐፊነትዎን የነካ የለም ። ይቸ የወንድማማቾች ያለመግባባት ነውና አያምሩበት" አሉ አቶ እንደሻው ።

"አሁን የፈለግነው ሐሳብዎን እንዲነግሩን ነው ። አቶ ፍጡር ስሕተታቸውን ቢያምኑ ምን እንቅጣቸው ? ምን እናስክስዎ?" አሉ መምሬ ።

"ከዕድሩ ይውጣ ፤ ሠፈሩንም ይልቀቅልኝ" አሉ አቶ አርጋው ፣ ሆድ በባሰው አንጋገር ።

"ሴትዮዋን ቢመልሱልዎትና በዚህ ብትታረቁስ ?" አሉ አቶ እንደሻው ።

"አሄሄ! ምን ሆኑብኝ! እርሱ በዚህ ሠፈር ካለ እንኳን ይታክቱን ሌላም ሴት ባመጣ ያው ነው ፤ ስብኮና አባብሎ ትዳሬን ማፍረሱ አይፋርም ። ስለዚህ ባጭሩ ፣ ከዕድሩ ይውጣ ! ሠፈሩንም ይልቀቅልኝ ፤ ይኸው ነው ፣ ሌላ የምለው የለም" አሉ ።

"ሴትዮዋን ከመለሱልዎ ፣ ሁለተኛ ከአጠገባቸው እንዳይ ደርሱ ዋስ ብናስጠራልዎና ብናስፈጥምልዎስ ?" አሉ አቶ እንደሻው።

t.me/OLDBOOKSPDF

''ይተዉኝ ፣ እባክዎ ይተዉኝ! ዋስ ቀረቶ እስር ቤትም ቢገባ ክርሲ አይለያም ፣ እርሷን እይቶ በጤናው ከቤት አይገባም። መድኃኒቱ ሠፈሩን መልቀቅ ነው'' አሉ አርጋው ።

በግራሩዋ ሥር የተዘረጋው ችሎት በዚያ መንፈስ ላይ በነ በረበት ሰዓት አቶ ፍጡርና አቶ ይመር ወደዚያው ተቃረቡ ።

''እስቲ አንድ ጊዜ እናስቸግረዎ ፡ የእርሳቸውንም ሐሳብ እንስማው ?'' አሉ መምሬ ። አቶ አርጋውም የልባቸውን ምስ ጢር ወደሚያጫውቱት ባሕር ዛፍ ሥር ሔዱ ።

''ነዎር ነዎር ! እስቲ ዐረፍ ይበሉ'' ተብለው አቶ ፍጡር ቀጠሙ ።

''የሁለታችሁን ጉዳይ አዳምጠንና መርምረን እንድትታረቁልን ለመለመን ነውና የጠራንዎ ፣ እስቲ ቅሬታዎን ይንገሩን?'' አሉ መምሬ ።

አቶ ፍጡር ተቁነጠነጡ ። ዘወር ዞወር እያሉም እኒያኑ ጣውንታቸውን ተመለከቱና ፣ ''ለማይሆን ነገር ለምን እናንቱ ተቸግራችሁ ሰው ታስቸግራላችሁ?'' አሉ ።

''እንዴ ምነው ? እንዲህ አይበሉ ። በአባት ርስትና በዘር ደም አልተገናኛችሁ ። የተጣላችሁበትን ምክንያት እንደሆነ ደርሰንበታል ። ታዲያ በዚህ አልታረቅም ነው የሚሉ?'' አሉ አቶ እንደሻው ።

''እርሱ የሚለውን ሁሉ አልቀበልማ!'' አሉ ፍጡር ።

''እርሳቸው ምን እንደሚሉ ሰምተዋል?'' አሉ መምሬ ።

''አምን ከዚህ በፊት ሽማግሌ ልኩብኛል ።''

''ምን ብለው ?''

''ሚስቴን መልስልኝ ብሎ ።''

ሽማግሌዎች እርስ በርሳቸው ተያዩ ፣ እንበለ ቃል በየልቦ ናቸው ተነጋገሩ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ታዲያ ይመልሱላቸዋ !! እርስዎ በቤትዎም ሴት አለዎት አይደለም ?" አሉ እንደሻው ።

"ከቤት ያለችው በጭን ግርድና የገባች ናት ። ከይታክቱ ጋር ግን ፣ በሰማንያ ለመጋባት ነው የተስማማነውና አለቅሰትም ፣ ደግሞ እርሱን አትወደውም ። እኔም ብዙ ገንዘብ አውጥቼባታለሁ" ብለው ፍጡር ተናግረው ሳያበቁ ፣

"ሴትዮዋን እስቲ እኛ እናነጋግራቸው ፣ ፈቃድም ቢሆን?" አሉ ይመር ።

"እሷንም ብታነጋግሩዋት እኔ አለቃትም ። ብዙ ገንዘብ አውጥቻባታለሁ" አሉ ፍጡር ።

"ወደ ቤቱ ልመለስ እፈቅዳለሁ ቢሉስ ሴትዮዋ ፣ እርስዎ አይሰማሙልንም ?" አሉ እንደሻው ።

"ብዙ ገንዘብ አውጥቻባታለሁኮ ነው እምለው ?"

"የምን ገንዘብ ነው ያወጡባቸው?"

"ለቦታ መመሪያ ፣ ለቤት መሥሪያ ፣ ለሌላም በርካታ ገን ዘብ አውጥቻለሁ!"

"ያወጡትን ገንዘብ መልሰውልዎ ፣ የሴትዮዋን እጅ አስ ረክበኝ ቢሉዎስ ?" አሉ ይመር ።

"ምንም ነገር ቢሆን አይቻለኝም !!"

"ምነዎ ሞኝ ነው ? አሁን ገንዘብዎን ይቀበሉና ሴትዮዋን ይመልሱ ። ሴትዮዋ ከአቶ አርጋው ጋር ካልተስማሙም ተመል ሰው ከቤትዎ ይገባሉ" አሉዋቸው አቶ እንደሻው ።

"ይኸማ እንደ እርሱው መሆኔ ነው ። ከርሱ ቤት ከገባች በኋላ የርሱ ከንድ ያቀፋትን ሴት መልሼ አላቅፍም" አሉ ፍጡር ።

"ሁለታችሁስ ስትናጠቁዋቸው አይደለም የኖራችሁት? እርስዎስ በመጨረሻ ከእርሳቸው ቤት አውጥተው አያደለም

t.me/OLDBOOKSPDF

የወሰዷቸው ? ከንዱ አላቀፋቸውም ፣ አላንተራሳቸውም ማለትዎ ነው ? እንዲያውም ጥፋት በእርስዎ አይተናልና ፣ ሴትዮዋ እሺ እገባለሁ ካሉ ፣ እሳቸውም እሽ ትምጣ እቀበላታለሁ ካሉ ፣ ነገሩ አለቀ ማለት ነውና ይመለሱ'' አሉ እንደሻው ጮክ ብለው ፣ ንዴት እየተናነቃቸው ።

አቶ አርጋው በነበሩበት ሆነው ፣ ''ይመለሱ'' ብለው አቶ እንደሻው ጮኸው ሲናገሩ ሰምተዋቸው ኑሮ ፣

'እንድ ጊዜ ከጂ በገባች እንጂ ፣ እንኳን እግሩ ሀያኑም ከማይደርስበት ቦታ ነው ወስጂ የምደብቃት' እያሉ ያስላስላሉ ።

''የመጣው ይምጣ እንጂ ፣ ከጂ የገባች ሴት መልሼ አልሰጥም ። በዚህ ነገር ሁለተኛ አትጠይቁኝ ። ከፈለገ ለርሱ ገን ዘብ እከፍለዋለሁ'' አሉ ፍጡር ።

''ሴትዮዋኮ በግጒር የሚዘዋወሩ አይደሉም ። አፈቅራታለሁ ሌላ ነገር ነው ። ገንዘብ እሰጣለሁ ማለት ተገቢ አይደለም '' አሉ አቶ እንደሻው ።

''ሴትዮዋን ካልመለሱኮ ከዕድሩ ይወጣሉ'' አሉ አቶ ይመርም ፣ ራሳቸውን እያስደነሱ ።

''እኔ ለይታክቱ ስል ፣ እንኳን ከዕድሩ ከሠፈሩም ብወጣ ቅር አይለኝም'' አሉና ፍጡር ከተቀመጡበት ተነሥተው እየተቆናጠሩ ሔዱ ።

''አቦ ጉድ! ጉድ ነው! ባንዲት ሴት የተነሣ ደግሞ ፣ ይህ ሠፈር ሊተራመስ ነው?'' አሉ መምሬ ፣ ፍዝዝ ብለው ከባሕር ዛፍ ሥር የተቀመጡትንና ፣ ተቆጥተው ወደ ቤታቸው በመሔድ ላይ የነበሩትን የይታክቱን 'ባሎች' ተራ በተራ እያነጻጸሩ ።

''እንግዲህ ለየጌቶቻቸው እንንገርና ፣ የሚበጀውን እነርሱው ያድርጉ እንጂ ፣ ሌላ ምን ይደረጋል?'' አሉ አቶ እንደሻው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚያች ዕለት ፣ አቶ እንደልቡ ደባልቀው ወደ ግራሩዋ ሥር ብቅ አላለምና ፣ ተሰብሳቢዎቹ በሰላም ከችሎቱ ተነሡ ።

* * *

የዕድሩ ሽማግሌዎች ሁለቱን ጣውንቶች ለማስታረቅ ጥረው ነበር ። በእነሱ በኩል አልሳካላቸው በማለቱ በመጀመሪያ ለልጅ አድባሩ ሐደው ነገሩ ።

"ከዚህኛው ቤት አስኮብልሎኮ ነው ወስዶ የደበቃት" አሉ ልጅ አድባሩ ፣ ሽማግሌዎቹን ሲያነጋግሩ ። "የተበደለውኮ ይኸኛው ነው ። እንደዚህ ያለ ከሠዲ እንዴት ዕድርተኛ ሆኖ ከኛ ጋር ሊቀመጥ ይገባዋል ትላላችሁ ?አቶ አርጋው አላጠፉም። ፍጡር ግን እንኳን ከዕድሩ ከሠፈሩም መውጣት ሲያንሰው ነው!"

"ቢሆንም ፣ ያንድ ጊዜ ስሕተት ነው ። ከቤቷ ያስኮበለሉዋትን ሴት እንዲመልሱ ለጌታ ፊታውራሪ ቢነግሩዋቸውኮ ብለን ነበር አመጣጣችን" አሉ እንደሻውም ።

"እንዴት ያለ ተሰምቶ የማይታወቅ ሽምግልና ነው የያዛችሁት ? ፍጡር ቢመልሳትስ አርጋው እሺ ብለው ከቤታቸው ያስገቡ ይመስላችኋል ?" አሉ ልጅ አድባሩ ፣ በወኪላቸው ሐሞቱ ከስታራነት ኮርተው ።

"እሺ ብለውናል ኮ" ኦሉ እንደሻው ።

"ምን ብለው ነው እሺ ያሉዋችሁ?"

"ከመለሳት እቀበላለሁ ብለው!"

"ሴትዮዋን እንደገና እቀበላለሁ አሉ ?"

"አዎን!"

'ኤዲያልኝ ኤዲያ ! የተጨማለቀ ነገር ነው ! ተዉኝ እዚያው ይጨመላለቁበት ፤ ሁለተኛ ይህን ነገር ወደኔ አታምጡብኝ ፤ እዚያው ጨርሱት ። ግን ሴትዮዋ ተመለሰችም አልተመለሰች ፣ ፍጡር ከዕድሩ መውጣት አለበት" አሉና ልጅ አድባሩ ፣ የመጨረሻውን ቃላቸውን ሰጡ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሽማግሌዎቹም ከልጅ አድባሩ ቀጥሎ ወደ ፊታውራሪ እር ኀጣቸው ሔደው ፣ጉዳዩን አስረድተው ፣ የተጋጋለውን ትኩሳት ለማብረድ ጥረታቸውን ለመቀጠል ቀን መስነው ተለያዩ ።

መምሬ በዕውቀቱና እቶ እንደሻው ወደ ቤታቸው ሲሔዱ ፣ "እህ! አሁንስ ቅጡ ጠፋኝ ። ይህችው ሴትዮ ፣ 'የፊታውራሪ ቅምጥ ናት' እየተባለ ይወራ የለም ? ታዲያ እቶ ፍጡር እንዴት እንደዚያ ያለ ነውር ነገር ይሠራሉ ?" ብለው መምሬ በዕውቀቱ እቶ እንደሻውን ጠየቋቸው ።

"እዩ መምሬ ፣ ድሮውንም ኮ 'ሲከበሩ የደፈሩ ጥንትም ነበሩ' ተብሏል ። ፍጡሬ ኮ የደፈረው ሾርጋውን ብቻ አይደለም ፣ ጌታውንም ጭምር ነው ። ምስጢሩን እነግዲህ ላውጋዎ ። ሴትዮዋን ትወልድልሃለችና ቦታ ሰጥተህ ቤት ሠርተህ አስቀምጣት ብለው ከፊታውራሪ ጋር ያገናኙ የፊታውራሪ ዘመዶች ነበሩ ። ፊታውራሪም ደስ ብሏቸው ፣ ለሴትዮዋ ቦታ እንዲሰጥና ቤት እንዲሠራላቸው አደርገዋል ይባላል ። ሴትዮዋ ግን ፣ ቤቱን ራሴ በጥረቴ ነው የሠራሁት ባይ ናቸው ።የሆነ ሆኖ ነገሩን የፊታውራሪ ሚስት ይሰማሉ ።

"ወዲያው ይህን ወንድማቸውን ፍጡርን ከነበረበት ሠፈር ያመጡና ፣ ቦታ አሰጥተው ፣ ቤት ሠርተው ፣ ባላቸውን እንዲጠብቅላቸው ያደርጋሉ ። ከዚያ በኋላ ፍጡር ሴትዮዋን መዳፈር ይጀምራሉ ። በመካከላቸውም ፍቅር የሚሉት ነገር ጉላ ብሎ ይታይና ምስጢሩን ይፋ ያወጣባቸዋል ። ፊታውራሪና ሴትዮዋም ይራራቃሉ ። ቢሆንም ፣ ፊታውራሪ አንዳንድ ጊዜ ሴትዮዋን ወደ ዘመድ ቤት እያስጠሰዱ መገናኘቱን አልተዉም ። ይኸውና ፊታውራሪ አንጀታቸው እያረረ ከፍጡር ጋር ይኖራሉ ። ምስጢሩና ታሪኩ ይኸው ነው" አሉ አቶ እንደሻው ።

"እንዴ ፣ ፊታውራሪ ከቤት ልጅ የላቸውም እንዴ ?"

"ሚስታቸው አንድ ልጅ ብቻ ወለዱላቸውና ማሕፀናቸው ደረቀ ፤ ይኸው ስምንት ዓመት ዐለፋቸው ። በኃዘን የተነሣ ሆዳቸው አረረና ቀረ" አሉ እንደሻው . . . . . .

t.me/OLDBOOKSPDF

"ያው አንዱ ልጅ ሞተ!" አሉ መምሬ።

"አይደለም፤ እሱስ አለ። ቤትዮዋ ይህንኑ ልጅ እንደ ወለዱ፥ ሁለት የወለዱላቸው የመጀመሪያ ባላቸው ይሞታሉ። ከልብ ይዋደዱ ነበርና፥ ምርር ብለው ቅጥ አጥተው አዘኑ። ከዚያ በኋላ ነው ማሕፀናቸው የደረቀው ይባላል" አሉ እንደሻው።

"ከተዋደዱ ለምን ተፋቱ?"

"ያፋቷቸው የቤትዮዋ አባት ናቸው። ያኛው ባል መናጢ ድኃ ነበር፤ ፈታውራሪ፥ ይህችን ቤት ድንገት ያዩና የሙጥኝ አፋቱልኝ ይላሉ። እነያሚያዩት ባለርስት ናቸው። ከአባታቸውና ከእናታቸው የወረሱት በአዲስ አበባ ሰፋፊ ቦታ አለ። በሸዋ፥ በአሩሲ፥ በወሎ ስንትና ስንት ጋሻ መሬት አለ። ታዲያ የሚስታቸው አባት በልጃቸው በኩል ገብተው፥ የዚህ ሁሉ ርስት ተካፋይ ለመሆን ብለው፥ ልጃቸውን ከድኃው ባላቸው አፋትተው ለፈታውራሪ ሰጡ። ፈታውራሪ ደግሞ፥ እርስታቸውንና ሀብታቸውን ወራሽ፥ ቤት ሙሉ ልጅ ፈላጊ ናቸው። ይታ ከቱንም በጉን አስቀመጡ። ግን በመካከሉ እንዲህ ሆነው ጉድ ተሠሩ!"

"አዬ ጉድ! ይኸ ባላባትነት፥ ይኸ ባለርስትነት እንደዚህ ግፍ የሚያሠራና እንደዚህ የሚያካክድ ይሁን? ታዲያ ቅምጣቸውን መቀማታቸውንስ ፈታውራሪ ያውቁ ይሆን?"

"አሳምረው ያውቃሉ እንጂ!" አሉ እንደሻው።

"ታዲያ እንዴት የቤት ኪራይ ሰብሳቢና ለጢስኞች ርስት አከፋፋይ አድርገው ፍጡሮን አስቀመጡዋችሁ?"

"መቸ ወደው ሆነ? ፍጡሮን ከመኪልነቱ ቢሽሩ፥ ወይም ከሠፈሩ ቢያባርሩ ሚስታቸው ጓዛቸውን ጠቅልለው፥ ድርሻዬን ያካፍሉኝ ብለው ብድግ ይሉባቸዋል። የእሳቸው እንጀት እያረረ፥ የሚስታቸው ቅቤ እየጠጣ ይኸውልዎ ይኖራሉ!" አሉ እንደሻው.....

t.me/OLDBOOKSPDF

በተባለበት ቀን ፣ የዕድሩ ሽማግሌዎች ወደ ፊታውራሪ ቤት ሔዱ ። እንደ ደረሱም ወይዘሮ ላቀች ተቀበሉዋቸውና ፣ "ምነው ደኅና መጣችሁ?" ብለው ጠየቁዋቸው። "ከጌቶች ዘንድ ጉዳይ ነበረን" አሉ እንደሻው ።

"ውይ እኔኮ ሰምታችሁ የመጣችሁ መስሎኝ ነበር ። ትላንት ድንገት አሟቸው ሆስፒታል ወስደናቸዋል" አሉ ላቀች ።

በነገሩ ሽማግሌዎቹ ማዘናቸውን ከገለጹ በኋላ ፣ "የመጣንበት ጉዳይ ፣ በአቶ አርጋውና በአቶ ፍጡር መካከል የተነሣውን ያለመግባባት ለጌታ ፊታውራሪ ነግሪን ፣ ግራ ቀኙንም ተቆጥተው እንዲያስታርቋቸውና ፣ ሠፈሩና ዕድሩ እንዳይበጣበጥ ብለን ነበር" አሉና አቶ እንደሻው ነገሩን ጀመሩ ።

ወይዘሮ ላቀች ፣ "በደል በማን ላይ ኦያችሁ?" አሉና ጠየቁ።

"ንገሌ በድኗል ፣ እገሌ ተበድኗል ብለን ነገሩን ከምናት ተው ፣ እንደዚሁ ፊታውራሪ ተቆጥተው እንዲያስታርቁልን ብለን ነው" አሉ መምሬ በዕውቀቱ ።

"እዩ አባቴ! ሽማግሌ የግራ ቀኙን ሰምቶ ፣ በዳዩን ተቆጥቶና ቀጥቶ ሲያስታርቅ ነበር የሚያምረው ። እናንተ ግን ራሳችሁ የፈራችሁትን ነገር ከፊታውራሪ ላይ ለመጣል ነው ያሰባችሁት ይመስለኛል ። ፊታውራሪም ጉዳዩን ሰምተውታል ። አንዳንድ ሰዎችም ፣ ራሴም ሞምር እንዲያስታርቋቸው ብለን ጠይቀናቸው ነበር ። እርሳቸው ግን ፣ ሴትዮዋ ዱሮም የፍጡር መሆንዋን ስለሚያውቁ ፣ አሁንም በቁርባን እንዲጋቡ ስለ ፈለጉ ፣ አቶ አርጋው በፈጸሙት ተንኮል በጣም አዝነዋልና ይህ ነገር በእናንተ በኩል ቢነሣባቸው ፣ በእናንተ ከማዘንና እናንተን ከመታዘብ በቀር ፣ በነገሩ እንደማይስማሙበት የታመነበት ጉዳይ ነው ። አሁን ሆስፒታል ተኝተዋልና ፣ ወደ ቤታቸው ሲመጡ እንነጋገርበታለን ።"

ሽማግሌዎቹ ተስፋ ቆርጠው ተመለሱ ።

የፊታውራሪ ሕመም እየቀጠለ በመሔዱ ፣ ሽማግሌዎቹም የዕድሩን ጉዳይ የሚያስወስኑበት ዳኛም ሆነ ሽማግሌ ሳያገኙ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዕድርተኛው ጋር መዋለል ጀመሩ ። ከልጅ አድባሩ ጢሰኞች ነዋሪ የሞተ እንደሆነ ፣ ወይም የተረዳ እንደሆነ ፣ ወይም በሌላ አካባቢና ሠፈር ዘመድ የሞተበት እንደሆነ ፣ የመሬትና የቤት ኪራዩን የከፈለ መሆኑን ካረጋጋጠ ፣ ወዲያውኑ የሚገባውን ክፍያ ከአቶ አርጋው ይቀበላል ። ገንዘብ ወዲያው ከዕድርተኛው ሰብስበው ይከፍላሉ ። ፣ዕድሩን ሥልጣን በጃቸው አስገቡ ። የሠፈሩ ነዋሪ ብዛት የሚያመዝነውም ፣ በልጅ አድባሩ ርስት ላይ ስለ ነቦረ ፣ የአቶ አርጋው ደጋፊ ነበር አመዛኙ ።

በፊታውራሪ ጢሰኞች ላይ ለሚደርስው ኃዘን ግን ፣ የገን ዘብ ክፍያ ቀርቶ የዕድሩን ዕቃ እንኳ ለማግኘት ችግር እየሆነ ባቸው ሔደ ። አቶ ፍጡርም ይታከቱዋቸውን ይዘው በዕድር ስብሰባና በለቅሶ መገኘቱን ጠሉት ። እነደዚያ ሆነው እየተሠ ወሩ በሔዱ መጠን ደግሞ ፣ የፊታውራሪ ጢሰኞች እርስ በርሳ ቸው እየተመካከሩ ፣ ከአቶ አርጋው ጋር መስማማት የሚሻላቸው መሆኑን እያመኑበት ነበርና ፣ እያሳሰባቸው ሔደ ።

"እየሀ ፣ ወንድሜ ነህ!" አሉ ፊታውራሪ ፣ ከአቶ ፍጡር ጋር ስለ ሁኔታው ሲመካከሩ ፣ "ስማኝማ ! ከዕድሩ ውስጥ እጃችን ከወጣ ፣ ያ ቀጣፊ የእጎቴ ልጅ ሠፈርተኛውን ሰብስቦ የመሬትና የቤት ኪራዩን ሊያስከለክለኝ ይችላል ። እንዲያውም ውሉ ዐድሮ ቦታ ዬን 'ባዶ ነው ፤ ሰው አልያዘውም' አሠኙቶ ሊያስወስድብኝ ይችላልና ፣ የኛ ጢሰኛ የሆነ ሁሉ ለብቻው እንዲሆንና የሪሱን ዕድር በሠፈሩ እንዲያቋቁም ማድረግ ያስፈልጋል" አሉ ።

"የኔም ሐሳብ ይኸው ነበር ፤ ግን ሌላ ችግር ያማም አለ በት" አሉ አቶ ፍጡር ።

"እንደምን ያለ ችግር ?"

"እሁን ጢሰኞቻችንን ሰብስበን ሌላ ዕድር ብናቋቁም ድን ኳን ፣ ወንበር ፣ ሰሐን ፣ ብርጭቆና ሌላም ዕቃ ሁሉ መግዛት ሊኖርብንኮ ነው!"

t.me/OLDBOOKSPDF

"አሁን ካለው ዕድር ውስጥ የከፈልነውን መልሰው አይስ ጡንም ?" አሉ ፊታውራሪ ።

"አሄሄ! ይህማ አይቻልም ። ምናልባት ለልጅ አድባሩ ቢነ ግሩዋቸው ይሻል እንያሁ አላውቅም እንጂ ፣ እነ አርጋው እን ደሆኑ አንዲት ብርጭቆም አይሰጡን ።"

"ሌላ ዕድር ልናቋቁም ነውና ፣ ከዚህ በፊት 'ያዋጣነውን ገንዘብ መልሱልን ፤ ወይም ከተገዛው ንብረት አካፍሉን' ብንል ፣ ያ ሸረኛ የኔ እኅት ልጅ በጅ ይሳል ብለህ ታስባለህ ?" አሉ ፊውታራሪ ፣ ከነበሩበት በረንዳ ወርደው ቀስ እያሉ እየተንጐ ራደዱ ። ለዱሮው እንደዚያ ያለ የደም ግፊታቸውን የሚያባ ብስ ጉዳይ ሲያጋጥማቸው በግቢያቸው ውስጥ የሚያሳዩት መወራጨት የውሃ ዋና ውድድር የገጠሙ ያስመስላቸው ነበር ። በዚያ ዕለት ግን ሕመም ደቋቁሶአቸው ፣ የሆስፒታሉ ጣጣ ተጫጭኗቸው ሰለ ነበር ፣ በሐኪሙ ምክር ከብስጭትና ከብርቱ ሐሳብ ለመሸሽ ጥረት እያደረጉ ነበር ።

"ባይሆን በሽግግሌ ቢያስጠይቋቸውስ ?" አሉ ፍጡር ።

"ማንን ?" አሉ ፊውታራሪ ።

"ልጅ አድባሩን ።"

"ምን ብዬ ?"

"የዕድሩን ዕቃ እንዲያካፍሉን ፤ ወይም ያዋጣነውን ገንዘብ እንዲመልሱልን ።"

"አሄሄ ! የኔ እኅት ልጅ ነው ፣ እንደዚህ ያለ ቅንነትና ደግ ሥራ የሚያውቀው ? እንዲያው ምክሬን አልተቀበልክም እንጂ ትለኝ መቸም ሰው ፊልጌ እልክበታለሁ ። ግን በሠፈራችን የራ ሳችንን ዕድር እንድናቋቁም ለዕቃ መግዣ የሚበቃውን ገንዘብ አስልተህ ንገረኝ" አሉና ፊታውራሪ ፣ መንጐራደድ ሰለ ታከታ ቸው ወደ በረንዳ ወጥተው ተጐበሩ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እርሳቸው እሺም ቢሉ እምቢም ቢሉ ፣ እኔ መቸም ጢፅ ኛቻችንን ስብስቤ ሌላ ዕድር ለማቋቋም እጥርበታለሁ ። ለስ ድሩ የሚያስፈልጉትንም ዕቃዎች እንደ ተለመደው ዕድርተኛው የተቻለውን ያህል እንዲያዋጣ አደርጋለሁ" አሉ ፍጡር ።

"ግፋበት ። በጐደለም እኔ እሞላለሁ" አሉ ፊታውራሪ ። የዕድሩ ሽማግሌዎች ከሆስፒታል ወጥተው ሰው ማነጋገር መጀመራቸውን ከአረጋገጡ በኋላ ፣ በሠፈሩና በዕድሩ ላይ የደረሰውን ምስቅልቅል ሁኔታ ለማስረዳትና ሁለቱን እንደ ራሴዎች ለማስታረቅ የጀመሩትን ጥረት ለመቀጠል እንደገና ወደ ፊታውራሪ ቤት ሔዱ ።

"እንኳን ለቤትዎ ያበቃዎ ! እኛስ ደንግጠን ነበር" አሉ አቶ እንደሻው ፣ እጅ እየነሡ ።

"ለዚህ ነበራ ሩጣችሁ ሐኪም ቤት መጥታችሁ የጠየቃ ችሁኝ ፤ በሉ ተቀመጡ" አሉና ፊታውራሪ ፣ ከበረንዳቸው የተደረደሩትን ወንበሮች አመለከቱዋቸው ። በዚያ ሰሞን ፊታው ራሪን "እንኳን የማረዎ ፣ እንኳን ቀላል አደረገልዎ ! እን ኳን ለቤትዎ አበቃዎ" ለማለት ወደ ቤታቸው ይሔዱ የነበሩት ጠያቂዎች በርከት ያሉ ስለ ነበሩ ፣ የቤታቸው ወንበሮችም ከጥ ዋት ጀምረው ከበረንዳው ላይ ተደርድረው እየዋሉ ፣ ፀሐይ ስት ጠልቅና ትንኞች ፊታውራሪንና ጠያቂዎቻቸውን ማጥቃት ሲጀ ምሩ ነበር ፣ ወንበሮቹና ፊታውራሪ ከነጠያቂዎቹ ወደ ቤት የሚገቡ ።

"እኔማ ከወዳጅዎችዎ ከነአለቃ ምሕረቱ ጋር ሐኪም ቤት መጥቼ ፣ ደክሟቸዋል ፣ ሰው አይገባም ብለውን ነው የተመለ ስነው" አሉ መምሬ በዕውቀቱ ፣ ፊታውራሪ በዓመት አንድ ቀን ከሚደግሱት ፀበል ፀዲቅ እንዳይሠርዟቸው በሐሳባቸው እየ ተማፀኑ ።

"አዎ ፣ አዎ ፣ እንዲያው ለጨዋታ ስል ነው እንጂ ፣ ጠን ቶብኝ ስለነበረ ሐኪሞቹ ሰው እንዳይገባ ብለው ነበር" አሉ ፊታውራሪ ፣ እንዳልተቀየሙ በሚያሳምን አኳኋን ። "የሆነ ሆኖ ፣ ዛሬም መምጣታችሁ ማለፊያ ነው ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"የዛሬው እመጣጣችን ለሌላም ጉዳይ ጭምር ነው" አሉ አቶ እንደሻው ።

"መች አጣሁት ? የፍጡርና የእርጋው ጉዳይ እንዳሳሰባችሁ ላቀች ነግራኛለች ። በጉዳዩ እኔም ተቸግሬበታለሁ ። ስለ ዚህ እናንተስ ሐሳባችሁ ምንድን ነው ?" አሉና ሽማግሌዎቹን ተራ በተራ ተመለከቱዋቸው ።

ሽማግሌዎቹ እርስ በእርሳቸው ተያዩና ፣ ፍሬ ነገሩን አቶ እንደሻው እንዲያስረዱ በጥቅሻ መወከላቸውን ገለጡላቸው ። አቶ እንደሻው ቆመው ሊናገሩ ሲነሡ ፊታውራሪ ተቆጥ ተው ካስቀመጡዋቸው በኋላ ፣ "መቸም ጌታዮ ! የሁለቱን ጠብ ጌታችን ሳይደርሱበት አልቀሩም ። በአባትና በዘር ርስት ወይም በአባት ደም ያልተገናኙ ሰዎች ፣ ብማይረባ ነገር እስከ ዚህ መዳረሳቸውና ፣ የእነርሱ እንሶ ደግሞ ዕድሩንና ሠፈሩን ማወ ካቸው ሁላችንንም አሳዝኖናል ። ስለዚህ ግራ ቀኙንም እርስዎ ተቆጥተው እንዲያስታርቋቸው ነው የመጣነው ። አገር አይጣቅ ፣ ሕዝቡም በነርሱ ምክንያት አይበጥበጥ" አሉ አቶ እንደሻው ።

"መቸም ጥፋተኛው እርጋው ነው ። ከቤቷ ዐርፋ ተቀምጣ የነበረች ሴት ንግዱን አስጥሎ ፣ ሚስቱን አባርሮ ፣ ይችን በማግባቱ ተሳስቷል ። ሁለት ሦስት ጊዜ እጥፍቷል ። ሁለት ሰው አስቀይሟል" አሉ ፊታውራሪ ፣ እንደ መዛትዎ እየቃጣ ቹ ።

"አቶ ፍጡርስ ቢሆኑ ፣ ሴትዮዋን ከአቶ እርጋው ቤት አባ ብለው መውሰድ ይገባቸው ኑሯል ጌታዮ ?" አሉ እንደሻው ።

"እሱስ ቢሆን መች ያርፋል ብላችሁ ? ለመሆኑ ወስዶ የት አስቀምጧት ይሆን ? ከቤቱ እንደሁ አላስገባትም ። እርሱም ቢደብቀኝ በሌላ ሰው አጣርቻለሁ ። ግን ይታክቱዎን የት እንደ ደበቃት ነው የሚነግረኝ ያጣሁ" አሉ ፊታውራሪ ። ወይዘሮ ይታክቱን አፋቸውን አዳልጦት በቁልምጫ በመጥራታቸው ሽማግሌዎቹ እንደሚታዘቡዋቸው በማመት ስቅጥጥ አሉ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"መቸም ጌታዬ ከተቆጡዋቸው ፣ ሴትዮዋንም ቢሆን ከደ በቁበት መልሰው እምጥተው ያስረክባሉ" አሉ እንደሻው ።

"ለማን ሊያስረክባት ?" አሉ ፊታውራሪ ፣ ነቃ ብለው ።

"ለአቶ አርጋው ።"

"እንዴ ! እንዴ ! አርጋው በጅ ብሎ ያስገባታል ?"

"እዎ ከመጣች እቀበላታለሁ ብለዋልኮ!"

"አርጋው ይታክቱን እንደገና ከቤቱ ሊያስገባ ?"

"አዎን ፣ እሺ ብለውናል ።"

"ኤዲያልኝ ኤዲያ ! ተዉኝ ኤዲያ !" አሉና ፊታውራሪ ፣ ከንፈራቸውን ዝልጠው አቶ አርጋውን በስሜታዊ ጥላቻና ንቀት ሲያስቡ ቆዩና ፣ "ኤዲያ ! የዘመኑ ወንድነት እንዲህ መሆኑ ነው ! አያችሁ ፣ ወይፈን ወደ ተቀጠቀጠበት ቦታ አይደርስም ። ወደዚያ ቢነዱት እንኳ ፣ ወደ ኋላው እየረገጠ ይሸሻል ወይም ይሮጣል ። ውሻ ግን ፣ ወገቡ እስኪቆረጥ በዱላ ቢወቁት ተመ ልሶ ነው ይላል ። 'ውሻ ወደ ትፋቱ ይመለሳል' የሚባለውስ ለዚህ አይደል ? ከቤቱ ወጥታ ፣ ከውሽማዋ ጋር ከርማ ፣ ፍቅርዋን የጨረሰች ሴት 'አገባለሁ ፣ ትምጣልኝ' ማለቱ የውሻውን ምሳሌ መከተሉ አይደለም ?" አሉ ፊታቸውን ቅጭም አድርገው ።

"እርስም እንደዚህ ካሉማ ነገሩ መባባሉ ነው" አሉ መምሬ በዕውቀቱ ።

"ቢብስ ቢቀጣጠል ፣ ምን እንዳያመጣ !? ኤዲያ !" አሉ ፊታውራሪ ።

"እንዴ ቢጋደሉስ ?" አሉ አቶ እንደሻው ።

"ኤዲያልኝ ኤዲያ ! ወንድነቱ የታለና ? ወንድነቱ ካለ እስ ተዛሬስ እየተደባበቁ ከመናጠቅ አይለይላቸውም ነበር ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"አይሆንም ጌታዬ! ሁለቱም በጣም ተናደዋልና፣ ማባባስ ሳይሆን መቆጣቱ ነው የሚበጀው" አሉ እንደሻው።

"ከተናደደ ታዲያ እሱ በሶ ጨብጦ ኑሩዋል!"

"እስከ ዛሬ ሰይጣን ሳያስታቸው ቆይተው፣ ከእንግዲህ ወዲያማ..." ብለው መምሬ ተናግረው ሳይጨርሱ፣

"አሁን ሌላዉን ጣጣ ተዉትና፣ ፍጡር ሴትዮዋን ከያዘቀበት እንዲያመጣ፣ አርጋው ከቤቱ እንዳያስገባ፣ ሴትዮዋ ከቤቷ እንድትቀመጥ፣ ሁለቱም ከደሃቷ እንዳይደርሱ አድርጋችሁ አስታርቁ" አሉ ፊታውራሪ።

"እንግዲህ፣ አርስዎና ልጅ አድባሩ ሁለቱንም ከተቆጣችኋቸው፣ አሁን ጌታዬ እንዳሉት ሴትዮዋ ወደ ቤታቸው ተመልሰው በሰላም ሊኖሩና፣ የሚያፈቅሩትን ሊይዙ ይችላሉ" አሉ አቶ እንደሻው።

"ለመሆኑ ያ የኔ እጎት ልጅ በዚህ ጉዳይ ምን አላችሁ?",

"ሴትዮዋ ወደ አቶ አርጋው ቤት ተመልሳ መግባት የለባትም ነው የሚሉት" አሉ አቶ እንደሻው።

"እንዲህ ነዋ! የኔ እጎት ልጅኮ ሐሞተ ኮስታራ ነው። ፍርድም አይሰትም። እውነቱን ነው፤ ሴትዮዋ እቤቷ ትመለስና አርፋ ትቀመጥ። እናንተም በዚሁ ነው መጨረስ ያለባችሁ" አሉ ፊታውራሪ፣ ወይዘሮ ይታክቱ ከቤታቸው ገብተውላቸው፣ ሁለቱ እንደራሴዎች ደጃፋቸውን እርም ብለው ትተውላቸው፣ አርሳቸው እንደ ጹሮው ልጅ እየላኩ፣ ጨለምለም ሲል ኩታ ተከናንበው፣ አጥር ሾልከው ሲገቡ፣ ወይም ወደ ዘመዳቸው ቤት አስወስደው ከይታክቱ ጋር ሲቃበጡና ሲዝናኑ በሐሳባቸው እየታያቸው። ወዲያው አንድ ሰው፣ የውጭው በር ተከፍቶለት ገባና ለጥ ብሎ እጅ ሲነሣ፣

"ነዎር! ነዎር! ወዳጄ ረዳ፣ እንዴት ሰንብተሃል? ና ወደ ዚህ!" አሉና ፊታውራሪ፣ የጅ ሰላምታ ሰጥተው መቀመጫ

t.me/OLDBOOKSPDF

እመልከተውት ፣ "ይኸውላችሁ ፣ ዘመኑ ያመጣውን መቀበል ይበጃል ብዬ ፣ ትምህርት ጀምሬያለሁ" አሉ ።

"ድጓና ጸመ ድጓ ነው ? ወይስ ሰማኒያ አሐዱ መጽሐፍ ?" አሉ መምሬ በዕውቀቱ ።

"አሄሄ ! እሱንማ ለእናንተው ትተናል ፣ አሁን መኪና ነው የምማር ።"

"መኪና ስለት ?" አሉ እንደሻው ።

"ተዉኮ ! እንዴት እንዴት ! መኪና መንዳት እየተማርኩ ነው ። አስተማሪዬም ይኸውና ፣ ወዳጄ አቶ ረዳ ነው ።"

"ምነው ጌታዬ ! ሳያጡ ፣ ሞልቶ ተርፎ ፣ ሎሌ ሞልቶ እንዴን መርጠው እያሠለጥኑትም ?" አሉ መምሬ ።

"ለወጉማ የተቀጠረ ሾፈርስ አለኝ አይደል ? የልብ እያ ደርስም ፣ ድርቀት ነው ። እኔን ቤተክርስቲያን አድርሶ ፣ ወይም ከማብሣ ቤት ፣ ወይም ከሐኪም ቤት ፣ ያለዚያም ከዘመድ ቤት ወርውሮ ፣ መጠበቅ የለ ፣ ከተማዉን እንዲያው አገር ምድሩን ሲዞር ውሎ ቤንዚናውን ሙጥጥ አድርጎ ጨርሶ ይመጣል ። መኪናዬን በየመሸታው ቤት በር ላይ እየገተረ ከተማዉ ተሣለቀ ብኝ ። የላኩት እንደሁ የልብ እያደርስ ። ምስጢር መቻል የለ ! ጥዋት ቤተክርስቲያን በሰዓቱ እያደርስ ። ሰክሮ አድሮ አሞኛል ይላል ። ታዲያ ተቸገርኩ ። ለዚህ መድኃኒቱ ራስ መማር ፣ መሠልጠን ነው ።"

"መልካም አድርገዋል ። መኳንንቱ ሁሉ መኪናውን ራሱ እያገላበጠ ፣ ምስጢሩን ሾፈርና አሽከር ሳያውቅበት እንደ ልቡ ሆኖየለ ? ደግ አድርገዋል እንጂ" አሉ እንደሻው ።

"ትክክል ነው ፤ ሐሳቤ ገብቶሃል ። የዘመኑንም ሥልጣ ኔና ፍላጐት ተረድተኸዋል ። በሉ እንግዲህ አሁን ከአሠል ጣኜ ፣ ከወዳጄ ከአቶ ረዳ ጋር መኪናዬን ልማር ነውና . . ." ብለው ተናግረው ሳያባቁ ፣

"እግዴት ? እንዲህ እያመመዎ ?" ኦሉ እንደሻው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እይ ደግና ነኝ ። ምን አለው መሰለህ ? መኪና መንዳትኩ እንዲያው በሩቁ ከባድ ይመስላል እንጂ ሲይዙት ቀላል ነው ፤ እያስቸገርም ።"

"እንግዲህ ጌታዬ የዕድራችን ዕድል በእርስዎ ላይ ነውና ይቸገሩለት ። አሁን እንሒድ" ብለው አቶ እንደሻው ብድግ ሲሉ ፣ ሌሎችም ተነሡ ።

"አዎ ! ግዴለም ! ዋናው ነገር ይታክቱ እቤቷ ገብታ በዚያ በሴትነቷ ሙያዋ ብቻዋን ለመተዳደር እንድትስማማ ማድረጉ ነውና ፣ በርቱበት" አሉ ፊታውራሪ ፣ በግቢያቸው ውስጥ ከቆመ መኪና ገብተው ስለ መኪና ዘዋሪነት ለመማር ቸኩለው ።

አቶ ረዳ ፣ በፊታውራሪ ርስት ላይ ቦታ ተመርቶ ቤት ሥራ ጀምሮዋል ። ታዲያ ፊታውራሪ ፣ "ይኸን መኪና መንዳት አስ ተምረኝ እንጂ ፣ ለከፍያው አታስብበት" ብለውት ነበርና ፣ ጥገቱ አድርጓቸዋል ። ቀኑን ሙሉ የራሳቸውን መኪና ከግቢያቸው ውስጥ አቁሞ ፣ ሳያንቀሳቅስ ስለ ማርሽ አገባብ ፣ ስለ ፍሬን እያያዝ ፣ ስለ ሞተር አነሣሥ ፣ ስለ መብራት አበራር ፣ ስለ መሪ እያያዝ ፣ ስለ መስታዋት አከፋፈት ሲያስተምራቸው ይውላል ። ትምህርቱን ከጀመሩ ከአምስት ወራት በኋላ ፣ ወደ ሰበታ መን ገድ ወስዶ ስለ አንዳዱ ሲያስጠናቸው ፣

"ጐማ ሲተነፍስብዎ ደግሞ ፣ ስለ አለዋወጡ ላሳይዎ" አላቸው ።

"አሄሄ ወዳጄ ረዳ ፣ ኧረ ባክህ ! ለእሱ አትቸገር ፣ አሽከር እይዛለሁ" አሉት ።

"አሽከሩስ ካልሠለጠነ እንዴት ይለውጠዋል ?"

"አሠልጥነዋ ! ሌላ ነገር እንዳይነካካ አድርገህ አስተምረዋ !"

"ሒሳቡኮ ታዲያ !"

"ምን ያህል ጊዜ ይጠይቃል ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንድ ሁለት ወር ይፈልጋል።"

"ትዚህ ሁሉ የማይተነፍሰውን ጉማ መርጠህ ብትገዛል ኛስ ?"

"እዱ ጌታዱ ! ጉማ ምንጊዜም ይተነፍሳል ። አላዩም የመ ኳንንቱ ጉማ ሁሉ ሲተነፍስ ?"

"ታዲያ አሽከሬን እስክታስተምረው ሁለት ወር ልጠብቅ።"

"ግዴለም ሌላውን ሥራዱን ሁሉ ትቼ አስተምርልዎታለሁ ። ያው ሥራዱ ፣ ምንጊዜም መተዳደሪያዱ ነው ብዱ ነው ።"

"ሥራህን ትተህ እሱን ብቻ ብታስተምር ፣ በወር እታሥ ለጥነውም ?"

"እሺ ጌታዱ ፣ ይበቃል ።"

"እንግዲያው አሠልጥነህልኝ ፣ ዋጋህን ጨምሬ እከፍል ሃለሁ ።"

ፊታውራሪ ከስድስት ወራት በኋላ ፣ የራሳቸውን እርዲታ መኪና እየነዱ ቤተክርስቲያን ደርሰው መመለስ ጀመሩ ። አሽ ከራቸው ረጋሳም በሳምንት አንዳንዱን ጉማ እየፈታና እየገጠመ በወር አራቱንም ጉማዎች ፈትቶ መግጠም ቻለ ።

ከዚያ በኋላ ፣ ፊታውራሪ ሚስታቸውን በጉናቸው ፣ አሽ ከራቸውን በስተኋላቸው እያስቀመጡ ወደ ድግስ ፣ ወደ ለቅሶና ወደ ቤተ ክርስቲያን መመላለስ ጀመሩ ።

ወደ ቤተመንግሥት ሲሔዱም ረጋሳ ከኋላው ወንበር ተኮ ፍሶ ይቀመጣል ። ፊታውራሪ መኪናቸውን አንገሚግጪው ሲያ ቆሙ ፣ ረጋሳ ከእግሩ ሥር አስቀምጦ ይዞት የሚዞረውን ታኮ አውጥቶ ከጉማው ሥር ይወትፍና ፣ በመሪው በኩል ያለውን በር ከፍቶ ፊታውራሪን ያስወጣና ፣ ካፖርት ያለብስና ባርኔጣ ቸውን ተቀብሎ ከጉማው ሥር ይቀመጣል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዶ ፊታውራሪ ፣ እጅ ለመንሣት ወዶ ቤተመንግሥት የሚሔዱ መኳንንት ሾፌሮች በአንድነት እጅብ ብለው ወይም ካንዶኛው መኪና ውስጥ ገብተው ሲያወሩ ፣ የእነርሱን የሾፌርነት ታላቅነት ላለመድፈር ሲል ፣ ረጋሳ በሩቅ ከማየት በቀር አይጠጋም ። ፊታውራሪ እጅ ነሥተው ከመለሱ ቻቸው ጋር እያወጉ ሲመለሱም ፣ ሮጥ ብሎ ባርኔጣቸውን ሰጥቶ ፣ የመኪና በር ከፍቶ አስገብቶ ፣ ሞተር ሲያስነሡ ታኩውን እንሥቶ ታቅፎ ይገባና ፣ ከኋላው ወንበር ይጐበራል ። ፊታውራሪ መኪና ይዘው ወጣ ገባ ማለት በመጀመራቸው ወይዘሮ ላቀችም ልባቸው እየተሰቀለባቸው በመሔዱ ፣ ረጋሳን ማጉራረስና ማለባበስ ጀመሩ ።

ፊውታራሪ ደግሞ ፣ ረጋሳን ጭኖ መዞሩ እየከበዳቸው ሔደ። ግን ያ ጣጠኛ ጉማ ካጉል ቦታ ቢተነፍስስ ? የግድ ረጋሳን መሜን ነበረባቸው ። ረጋሳ እየቆየ መኪናዩቱን መተናኮል ጀመረ ። መነካካት ፣ ሞተር ማስነሣት ፣ ማንኳቀቅ ተላመደና ፣ እንድ ቀን ከግቢው ውስጥ ከግንብ ጋር አላትሟት እንደ ወጣ ቀረ ። ፊታውራሪ ጉማ የመለወጡ ጉዳይ ቀላል ሥራ መሆኑን ከተረዱ በኋላ ፣ ባለፈው ምኝነታቸው እየተጸጸቱ መኪናቸውን ያለ እኽቢ ይዘው መውጣት ጀመሩ ።

እቶ ፍጡር ፣ የፊታውራሪን ጢሰኞች በየቤታቸው እየዞሩ ሰብከው ፣ ከዋናው ዕድር ተገንጥለው ፣ 'የእርገጣቸው ሠፈር ዕድር' ብለው አቋቋሙና ፣ ዳኛና ገንዘብ ያዥ ራሳቸው ሆኑ ። ፊታውራሪም ለዕድሩ ዕቃ መግዣ ፍጡር የጠየቁቸውን ገንዘብ ከፈሉ ።

ከዚያ በኋላ ፣ በሠፈሩ እንዶገና ብርቱ ትርምስ ተቀሰቀሰ ። የሁለቱ ባለርስቶች ባለሟሎችና ጢሰኞችም የየዕድራቸውን አባል የማብዛት ፉክክር ገጠሙ ። እንዲያውም ከሠፈራቸው አካባቢዎች በነበሩት ነዋሪዎችም ላይ ሰብክት ጀመሩ ።

'የእርገጣቸው ዕድር' እንድ ዕድርተኛ ሲሞት መቶ ብር ፣ የቤተሰብ ሬሳ ከቤቱ ሲወጣ ሰባ አምስት ብር ፣ መርዶ ሲሆን

t.me/OLDBOOKSPDF

ሃምሳ ብር ይከፍላል'' እያሉ የአቶ ፍጡር ምልምሎች ሲሰብኩ፣ የአቶ አርጋው ሰባኪዎች ደግሞ ከዚህ እጥፍ እንደሚከፍሉ ማወጅ ጀመሩ ። የልጅ አድባሩ ሠፈር ዕድር አባል ብዛት እየጨመረ የሚሔድ እንጂ የሚቀንስ አልሆነም ።

ልጅ አድባሩ በክፍያ በደረሳቸው መሬት ላይ በሙሉ ጢስኛ ሲያሠፍሩበት ፣ ፈታውራሪ ግን ፣ 'የጨዋ ልጅና መሬት እያደር ይመደዳል' የሚል ዘዬ ስለ ነበራቸው ፣ በገሚሱ እንኳ አላሠፈሩበትም ነበር ።

''ታዲያ ስለ ሁኔታው ከአቶ ፍጡር ጋር ሲመካከሩ፣ ''የእጎትዎን ልጅ ተንኮል ዛሬ ነው ልደርስበት የቻልኩት ። በዚህ በበዶው መሬትዎ ላይ አትኩረውበታልና የሚሆነውን ቀልጥፈው ያድርጉ'' አሉዋቸው ።

''እኮ ምን ይደረግ ?'' አሉ ፈታውራሪ ፣ ተደናግሩዋቸው ።

''እንዴ ! 'ቦታ እንመራ ፣ የፈታውራሪ ጢስኞች እንሁን ደግ ጌታ ናቸው ። ከሌላው መኳንንት የተሻሉ ፣ ለክፉ ቀን ዋስ የሚሆኑ ናቸው ፤ እኛም በጉልበታችን እናገልግላቸው ፤ በዙሪ ያቸው እንሁን' የሚሉ ሞልተዋል ። ደግሞ የዕድራችንን ማጎበርተኞች ቁጥር ለማብዛት ከዚህ የተሻለ የለም ። የደንቡን እያስከፈልንና እያስፈረምን ብንራመድ ይሻላል ።''

''ማለፊያ ነዋ ! እስቲ ከሳቁች ጋር እንምከርበት '' አሉ ፈታውራሪ ።

''ደግሞምኮ'' አሉ አቶ ፍጡር ፣ የፈታውራሪን ልብ በይ በልጥ ሲፈለቅቁት ፣ ''ደግሞም እኮ ጌታዬ ! ዛሬ በአዲስ አበባ የተያዘው እሽቅድድም ፣ 'እገሌ ምን ያህል ጢስኛና ገባር አለው? ምን ያህል ቤት ያከራያል ? ምን ያህል ጋሻ መሬት አለው ?' እየተባለ ነው ። በክተማዉ ቦታ ጢስኛ ማስፈር ፣ ከባንክ ተበድሮ ቤት ሠርቶ ማከራዬት ፣ የገጠር ርስት መግዛትና ገባር ማስፈር በመኳንንቱ ዘንድ የተያዘ እሽቅድድም ነው ። ስለዚህ ፣ ሳይውሉ ሳያድሩ ጢስኞች ማስፈርና ፣ የቦታውን ካርታ አስይዘው ከባ

t.me/OLDBOOKSPDF

ንክ ተበድረው ፣ ለኪራይ የሚሆኑ ቤቶች በብዛት ማሠራት ነው ። ምነው ፣ ቤተመንግሥት ይሔዳሉ ፣ ሁሉን ነገር ያውቃሉ ። ታዲያ ዝምታው እስከ መቸ ነው ? እኔ የታየኝን የአሽከርነቴን ነግሬያለሁ ” ብለው ፍጡር ሐሳብ ሲያቀርቡ ፣ ፊታውራሪም ከጉጉትና ከሐሳብ ሰመመናቸው ነቁና ፣

“ይባርከህ ወዳጄ ! ይባርከህ ። በል ፣ ከዛሬ ጀምረህ ይህንኑ ነገር አከናውንልኝ ። ጢሰኛ ከመጣም ሰውነቱን እያየህ ምራልኝ ። ግን ያች ያባቴ ወንበር ይዘረጋባት የነበረችውን አጤ ምኒልክ ‘ትከላት’ ብለው የሰጡኝ ባሕር ዛፍ የምትገኝባትን ቦታዬን ለማንም አትስጥብኝ ። እንዲያውም የመጀመሪያይቱ የአጤ ምኒልክ ባሕር ዛፍ ናትና ፣ አደራህን እንዳትነካብኝ ። ያን እካ ባቢ ከልሰህ ፣ አጥረህ ፣ ሴላዉን ምራበት” አሉ ።

“እንዴ ጌታዬ ! ከዚህ ላይ ጌታዬ” ብለው ፍጡር በአመልካች ጣት ራሳቸውን እየቆረቆረሩ ቆዩና ፣

“ጌታዬ ! አሁን እንዳሉት ፣ እነዚህ ትልልቅ ባሕር ዛፎች አጤ ምኒልክ ትከሉ ብለው ለአባትም ልከውላቸው በመጀመሪያ የተተከሉ ናቸው ብለው ሰዎች ሲያወሩ ፣ ባልሳሳት አቶ ንጉሤ ይመስሉኛል ‘የለም የመጀመሪያዎቹ ባሕር ዛፎች እነዚህ አይደሉም ። የመጀመሪያዎቹ ባሕር ዛፎች የተተከሉትና ዛሬም ድረስ የሚገኙት በጪቦና ጉራጌ ፣ ቱሉቦሎ ወረዳ ፣ ጉማ ኪዳነ ምሕረት ፣ በተለይ ሴዴሬ በተባለች መንደር ነው’ ብለው ቢናገሩ ፣ በዚሁ የተነሣ ተወራርደው አቶ ንጉሤ ረትተዋልና ፣ አጤ ምኒልክ በመጀመሪያ ያስተከሉዋቸው ባሕር ዛፎች እነዚህ አይመስሉኝም” አሉ ።

“እም ! ይህን ታሪክ እኔም ገና ድሮ ሰምቻለሁ ፣ ዘንግቸው ነው እንጂ ። ይሁንና ፣ እነዚህኞቹም በተለይ ከመካከላቸው ያለው ትልቁ ባሕር ዛፍ ፣ ያው ከቀደምቶቹ አንዱ ነውና ጠብቅልኝ ። እንዲያውም ለዕድሩ መሰብሰቢያ አድርገው ። ሴላውን ግን እያስቆረጥክ ሽጠው ። ቦታውንም ለደጎና ለያጎና ሰዎች ምራው” አሉዋቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አቶ ፍጡር ፣ ለፈታውራሪ ባቀረቡት ሐሳብ መሠረት ፣ ወፈር ወፈር ያለ ጉቦ ለከፈላቸው ደጎና ደጎናውን ቦታ እየሸነሸኑ መምራት ፣ ኪራይ መቀበል ፣ ባሕር ዛፉንና ጥዱን እያስቆረጡ መሸጥ ፣ ፈታውራሪ ካርታ እያስያዙ ደጋግመው ከባንክ እየተበደሩ ለኪራይ ቤቶች ማሠሪያ ከሰጡዋቸው ገንዘብ ላይ እየቆነጣጠቡ ራሳቸውም በሌላ ሠፈር ቤቶች ሠርተው ማከራየት ጀመሩ ።

ፈታውራሪ መኪና መንዳት ከቻሉ በኋላ ስለ ሠፈሩ ፣ ስለ ርስቱ ፣ ስለ ኪራዩ ስለ ዕድሩ ደንታ ቢስ ሆኑ ። ሁሉንም ጠቅልለው ከአቶ ፍጡር ላይ ቆለሉትና እርሳቸው አዲስ አበባንና አካባቢዋን ማጣጣም ያዙ ።

በሁለቱ ባለርስቶች ሠፈር የተቋቋሙት ሁለት ዕድሮችም ከነምስቅልቅላቸውና ከነትርምስምሳቸው ማዝገም ቀጠሉ ። በፈታውራሪ እርገጣቸው ዕድር በኩል ፣ ከአቶ ፍጡር ቀጥሎ እነ አቶ ይጥና ፣ አቶ ንጉሤ ፣ አቶ ቡልቻ ፣ አቶ ሺበሺ ፣ አቶ ረዳ ሲሰለፉ ፣ በልጅ አድባሩ ዕድር በኩል ደግሞ ፣ ከአቶ አርጋው ቀጥሎ እነ መምሬ በዕውቀቱ ፣ አቶ እንደሻው ፣ አቶ ግዛው ፣ የኔ አለቃ ከበደ ፣ ወይዘሮ ፈትለወርቅ ፣ አቶ ይመር ሆነው ትግሉን ቀጥለዋል ።

ፈታውራሪ ደጋግመው የሰነዘሩትን ሐሳብ ፣ አቶ ፍጡር ባለመቀበላቸው ይታከቱ ብቻ ከሠፈሩና ከዕድሩ እንደወጡ ቀር ተዋል ።

የዕድርተኛ ቁጥር ለማብዛት እንጂ ፣ ደንቡን ለማሻሻል እና በሥርዓት ለማስተዳደር ፣ በሁለቱም የዕድር ኃላፊዎች በኩል የሚቈረቈር ስላልነበረ ፣ የማታለልና የመደለል ተግባሮችም ሥር እየሰደዱ መጡ ።

"አገር ቤት ይኖሩ የነበሩ አያቴ ፣ አባቴ ፣ እናቴ ፣ አክስቴ ፣ አጐቴ ፣ አጎቴ ፣ ወንድሜ ፣ ሙተው ተረድቻለሁ" እያሉ በየቤታቸው እየጐዘጐዙ መቀመጥና የሆነውን ያህል ዕርዳታ መቀበል እየተለመደ ሔደ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

'እውነት ነው ሐሰት ?' ብሎ መጠየቅ አይታሰብም ነበ
ርና ፣ ዘዴዉ ከሁለቱ ዕድሮች ወልፎ በጐረቤት ዕድሮች እየ
ተለመደ ሔደ ።

የልጅ እድባሩ የዕጮኛቸው ቤት አያት በመሞታቸው
ዓመት ያህል ፣ እንደገናም አጐትየው በመደገማቸው ስድስት
ወራት ያህል አሳልፈው ድግሱን ሲጀምሩ ፣ በእናታቸው ኃዘን
ተቆራምደው የነበሩት የሙሽራዪቱ እናትም ወደሌላው ዓለም
በመሔዳቸው ፣ ለሁለት ዓመታት ያህል ከባድና ቀላል ኃዘን ተደ
ርጎ ጋብ ካለ በኋላ ፣ የልጅ እድባሩ ሦስተኛው ዙር የሠርግ
ድግስ ተጀመረ ። ካለፉት ሁለት ሠርጎች ላቅና ሞቅ ያለ እን
ዲሆን ከልብ ታስቦበታል ። 'ቢያንስ ቢያንስ ለእንድ ሺህ ሰው
የምሳ ግብዣ ፣ ለሦስት መቶ ያህል ራት እንዲዘጋጅ ያስፈልጋል'
ብለው ልጅ እድባሩ መስነዋል ። ሙሽራዪቱ እንደ እርሳቸው
'ያጥንት ሐረግ ፣ የደም ጥልቀት' ከነበራቸው ቤተሰቦች የተ
ገኘች ነበረች ። ከዚያ ሌላ ደግሞ ልጅ እድባሩ ከአያታቸው
ግዛት ሩብ ያህል ተስጥቷቸው ወረዳ ገዢ ሆነዋል ። የደረሱበት
የሀብት ሚዛንና ደረጃም ማንነታቸውን ለማሳወቅ ዲል አድ
ርገው እንዲደግሱ ገፋፍቷቸዋል ።

የእርሳቸው ኃዘን ኃዘናቸው ፣ የእርሳቸው ዓለም ፣ ዓለማቸው
እንዲሆን በልዩ ልዩ ሥልትና ዘዴ የተገፈትትና የተገደዱት የክ
ተማ ጢሰኞቻቸውና የገጠር ገባሮቻቸው ደግሞ ፣ የድግሱ ተካፋ
ዮች እንዲሆኑ እነ አቶ እርጋውና መምሬ በዕውቀቱ ስለጣሩበት
የመጀመሪያውን ስብሰባ በዚያችው በግራሩዋ ሥር አደረጉ ።
በስብሰባውም ላይ ዕድርተኞቹ ብቻ ሳይሆኑ ፣ ከልጅ እድባሩ
ርስት በገባሮቻቸው በኩል ተመርጠው የተላኩት ወኪሎች
ነበሩ ። የጎብረት ስብሰባ የተደረገውም በገባሮቹና በጢሰኞቹ
በኩል ምን ምን ዕርዳታ ሊደረግ እንደሚገባው ለመወሰንና
ለማቀናጀት ተብሎ ነበር ።

"የዛሬው ስብሰባችን የተባረከና ለሌሎችም ሁሉ ታላቅ
እርአያ የሚሆነው" አሉ መምሬ በዕውቀቱ ፣ ንግግሩን ባርከው
ሲከፍቱ ፣ "ጌታችንና ወንድማችን ልጅ እድባሩ ፣ ለኛ ለከተሜ

t.me/OLDBOOKSPDF

ምቹም ሆነ ለገጠሬዎቹ ከእያቶቻቸውና ከእባቶቻቸው ሲወርድ ሲዋረድ የደረሳቸውን ርስት ለዘመዱ ለወዳጁ ሳይሉ ፣ ለሁላችን ስማያውቁን አንድ ቀን ላልጠየቅናቸው ሁሉ ፣እንደየፍላጎታችን እንደየችሎታችን አከፋፍለውናል። በእርሳቸው ቸርነትም ይኸውና ከተሜዎቹ ቤት ሠርተን ፣ ገጠሬውቹ እርሻ አርሰን በደስታ እንኖራለን ።

"ምንም እንኳን ፣ በልዩ ልዩ ምክንያት ደጋግሞ ትዳራቸው ቢፈርስም ፣ ዛሬ ቢጤአቸውንና መሰላቸውን አጋጥሟቸው ፣ ትዳር ሊመሠርቱ ሲነሡ መቸም ጉዳዩ ጉዳያችን ነውና እንደሚሆን እንደሚሆን አድርገን እንረዳዳበት" አሉና ተቀመጡ።

በተሰብሳቢዎቹ መካከል መተያየትና መጉሻሸም በመካሔድ ላይ እንዳለም ፣ "አዎ ! ይኸው ነው ። ሁሉንም በሚገባ አባታችን ተናግረውታል ፤ ሌላ የምጨምረው የለኝም ። እንግዲህ ጢሰኛው ስንት ስንት ፣ ገባሩ ስንት ስንት ማውጣት እንደሚገባው ሐሳባችሁን እንወቀውና እንስማማበት" አሉ አቶ አርጋው ። የተሰብሳቢዎቹ መተያየትና መጉሻሸም አልተገታም ።

"እንግዲህ በመጀመሪያ ፣ እኛ የከተማው ጢሰኞቻቸው ስንት ስንት እንደምናዋጣ ከተነጋገርንበትና ከተስማማንበት በኋላ ፣ ቀጥለን ደግሞ ገባሮቻቸው ስንት ስንት ማዋጣት እንደሚገባቸው እንወስናለን ። ለነገሩ መጀመሪያ ይኸው ይሻል ይመስለኛል" አሉ አቶ እንደሻው ።

"በሉዋ ንገሩን ፣ በጢስ ስንት ይጣል?" አሉ አቶ አርጋው ።

"መቸም የዕድርተኛውን ዐቅም ገምቶ መጣል ያስፈልጋል ፣ ያለ ዐቅሙ እንዳይሆንበት" አሉ ይመር ።

"ከወርቅና ከዕንቁ የበለጠ መሬት ለሰጠ ጌታ ፣ ያለውን ያፈራውን የማይሰጥ ጢሰኛና ገባር መቸም በመካከላችን ቢኖር የሚወገዝ እንጂ ፣ የሚያመጥና የሚደገፍ አይሆንም" አሉ አቶ አርጋው ።

"በጢስ ስንት ይጣል ?" አሉ አቶ እንደሻውም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለመሆኑ ፣ ገንዘቡን ነው የምንሰጣቸው ወይስ ዕቃ ሊገዛ ላቸው ነው ?" አሉ ይመር ።

"እዎ ፣ ይህም ቢለይልን እይከፋም" አሉ እንደሻው ።

"መቸም ጠጁ ከተጣለ ቆይቷል" አሉ አቶ አርጋው ፣ "ጠላውም ተጀምሩዋል ። ቅቤዉም ፣ በርበሬዉም ፣ ጤፉም ከያ ግሩ መጥቷል ። አሁን የሚቀረው የፈረንጁ መጠጥና ሠንጋዉ ነው ። እኛም መቻል ያለብን ይህንኑ ነው ።"

"ማለፊያ ነው ። ታዲያ ምን ያህል ሠንጋ ፣ ምን ያህል የፈ ረንጅ መጠጥ እንደሚያስፈልግ ታውቋል?" አሉ እንደሻው።

"መቸም ፣ የፈረንጁን መጠጥ ልኩን ማወቅ ያጻጋታል ። ሠንጋዉ እንኳ ዐሥራ ዐምስት ያህል ይበቃ ይመስለኛል ። የተጠራው ሕዝብ እጅግ ብዙ ነውና ፣ መቸም አስቡት" አሉ አቶ አርጋው ።

"ማለፊያ ነው" አሉ እንደሻው። "ሠንጋውንም ሆነ መጠ ጡን በሙሉ ዕድርተኛው ይግዛ ለማለት ያስቸግረናል ። ከዚሁ ከተባለው ውስጥ የተቻለንን ያህል ለመግዛት ተመኑን ብናው ቀው እይከፋም ።"

"የመጠጡ ልክ እንኳ ባይታወቅ ፣ ሠንጋዎችን ግን በሙሉ ጢስኛው መግዛት ይገባዋል" አሉ አቶ አዐጋው ፣ ፊታቸውን ቅጭም አድርገው ።

"እንዴ! የዐሥራ ዐምስቱ ሠንጋ ዋጋ ተደምሮ ለእያንዳ ንዱ ጢስኛ ሊመደብኮ ይበዛበት ይሆናል ብዬ ነኝ" አሉ እንደ ሻው ፣ ለዘብ ብለው ።

"እንዴ ፣ ምን ሆኑብኝ ? መፍረድኮ ያለብዎ ጢስኞቹም ሆኑ ገባሮቹ የያዙትን መሬት ልክና ዐይነት ነው ። ከዚያ ሌላ ደግሞ ፣ እንደ ሌሎቹ ባለርስቶች በየወሩ ኪራይ ጨምረው አያውቁም ና..." ብለው አርጋው ተናግረው ሳይጨርሱ ፣

"ይሆን እንኳ ይርሱት" አሉ አቶ እንደሻው ። "እኔ ራሴ ከዚህ ከመጣሁ በዐምስት ዓመት ውስጥ ሦስት ጊዜ ኪራይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጨምሩዋል ። በመጀመሪያም መሬቱን ስንመራ የከፈልነው ገን ዘብ ከሌሎቹ ሠፈርተኞች የተለየ ነው ። ብቻ ግን አሁን መቸም አንድ ጊዜ የተጀመረ ጉዳይ ነውና ተረዳድተን እንቻለው እንጂ፣ የኪራዩ ውድነት እንኳ ላቅ ያለ ነው ።"

"አባቶቼ ጌቶቼ! እንድም ዐሥርም ሠንጋ ቢገዛ ጢሰኛዉንና ገባሩን አግባብተንና ለምነን ነው እንጂ፣ በማስገደድ የሚሆን ነገር ያለ አይመስለኝም . . ." ብሎ የፃ አለቃ ተናግሮ ሳያበቃ፣ አቶ እንደሻው አቋረጡትና፣

"አይደለም ፣ አይሆንም ፣ እንዲህም አይደል ። እንተ በቤት ኪራይ ስለምትኖር ሐቅ ነው ፣ ግዴታው አይመለከትህም ይሆ ናል ። ጢሰኛዉን ግን ይመለከተዋል ። እንዴት ብትለኝ ፣ ቦታውን ተመርቶ ቤቱን ሲሠራ ፣ ባለርስቱ ልቀቅ ባለው ወቅት ቤቱን አፍርሶ ለቆ ሊሔድ ነው የፈረመውና ፣ ከኋላው መዘዝ እንደ ምንም ብሎ ተበድሮና ተለቅቶ የተፈለገውን ሠንጋ ዛሬ ቢገዛ ይሻለዋል" አሉ ።

"እንዴ ፣ ምን ሆኑብኝ! እኔምኮ ጢሰኛ ነኝ ።"

"ሆነሃል እንዴ? እኔኮ በኪራይ መግባትህን ነው የማውቀው ። ጢሰኛ ከሆንክ ታዲያ የፈረምከውን ውለታ ትረሳለህ?"

"ረስቸው ሳይሆን ፣ በዚህ ምክንያት ተጣልተውን ቤታችሁን አፍርሳችሁ ልቀቁልኝ አይሉንም ብዬ ነው ።"

"እከድ እከድዬ! የባለርስቶችን ዐመል ገና አላወቅሽውማ!" አሉ እንደሻው ።

"እያንዳንዱ ጢሰኛና ገባር የዐቅም የዐቅሙን ያህል እንዲ ያዋጣ ፣ በውዴታው የቻለውን ያህል እንዲከፍል ቢደረግ አይሻልም?" አሉ አቶ ይመር ።

"አሄሄ! አቶ ይመር ፣ ሲቀልዱ ነው? ወደስ ከሙሪዎ ነው?" አሉ አቶ አርጋው ፣ በንቀት እስተያየትና በጥላቻ ስሜት ፤ "አሁንማን ይሙት የኛ ሠፈር ነዋሪ ነው ፣ በውዴታው ለመ ንጋ መግዣ የሚበቃ ገንዘብ የሚያወጣው?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ታዲያ እንዴት እናስከፍል ?" አሉ ይመር ፣ ምርር ብለው።

"እንደየገቢው ነዋ ! ባለጀመወዙንና ባለንግዱን እየለየን ይህን ያህል ከፈል ብንለው ነው የሚያዋጣን" አሉ አርጋው ።

"እንዴ! በንግድም ሆነ በመኪና የሚተዳደረውም ቢሆን ሁሉም እኩል አይታደም ። በባለመኪናው በኩል ተሳላ ኪም ድሌክተርም በሠፈራችን ጢሰኛችም ዕድርተኛችም ናቸው። በነጋዴው በኩል ተሆነ ደግሞ ፣ ጠላና ጠጅ አረቄ ፣ ዕንጨት ከሰል ፣ እህል የሚሸጡና ከባሕር ማዶም የሚመጣ ሸቀጥ የሚ ነግዱ አሉ ። ታዲያ መደዳውን በስመ ይሞዝና በስመ ንግድ ሁሉንም በአንድ ዐይን እንዳንመለከታቸው ማሰብ የግድ ያስፈ ልጋል" አሉ አቶ እንደሻው ፣ ተሰብሳቢዎቹን ተራ በተራ በማ ስተዛዘን እየተመለከቱ ፣ "መቸም ባለጀመወዙም ሆነ ባለንግዱ ሁሉም ሳንድነት አይመዘንም ። አሁን እንደ ተባለው ይለያያል። ዝቅ ያለው ከፍ ካለው ጋር እኩል ክፈል አይባልም ። አሁንም የሚበጀው እኛው እንደ መሰለን በየጢሰኛዉና በየዕድርተኛዉ ላይ የሚከፈለውን እንጣልበት ።"

"አሁንኮ በሠፈራችን በጢሰኝነት ቤት የሠሩና ቤት ተከ ራይተውም የሚኖሩ አሉ" አለ ፣ በቅርቡ የሟ እልቅና ማዕረግ ያገኘው ከበደ ። "ታዲያ ክፍያው ባንድነት በሁለቱም ላይ ነው የሚጣለው ፣ ወይስ በጢሰኞቹ ላይ ብቻ ?"

"ጢሰኛ ፣ ኪራይተኛ የሚባል ነገር የለም ፣ ሁሉም መነ ፈል ያለበት በዕድርተኛነቱ ነው" አሉ አቶ አርጋው ፣ እንደ መቆጣት ብለው ።

"ጢሰኛውንስ ማስገደድ የሚቻልበት መንገድ ገባኝ ።ቤት ተከራይቶ የሚኖረውስ አልከፍልም ቢል ምን ይደረጋል ?" አለና የሟ አለቃ ከበደ ፣ አቶ አርጋውን ጠየቃቸው ።

"ቤት ያከራየው ከቤቱ ፣ የዕድሩ ዳኛ ከዕድሩ ያስወጡታላ" አሉት አርጋው ።

"ይኽ ነገር ታዲያኮ በሕግ በኩል" ብሎ ተናግሮ ሳያበቃ ፣ አቶ እንደሻው አቋረጡትና ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

‘ወንድሜ ፣ ወዳጄ ፣ ስማኝ! ይህን ነገር እዚሁ ተመካክረን ነዋሪውም እንዳይጐዳ አድርገን ከዚሁ እንጨርሰው እንጂ ሕግና ዳኛ ፍለጋ ሰማይ እንቧጥጥም ። ሁሉንም እናውቀዋለን ። እነኳንስ ከርስታቸው ላይ የሠፈረን ጢሰኛና ኪራይተኛ ማባረር ይቅርና ፣ ርስቱን ከነንብረቱ ሲቀሙት ‘ምነው ? ለምን ነው?’ ብሎ የጠየቃቸው የለም ። ስለዚህ ፣ አሁን ሙግቱን ትተን ሰሞኑን እየተገናኘን ባያንዳንዱ ዕድርተኛ ላይ የሚጣለውን ክፍያ እንወስንና እናስከፍል” አሉ ።

“ማለፊያ ነው” አሉ አርጋው ፣ “ሰሞኑን ሳይሆን ነገና ተነገ ወዲያ ብንጨርስ ነው የሚሻል ። ሠርጉኮ ተቃርቧል ። ታዲያ ሠንጋዎቹም ከወዲሁ ተገዝተው ፣ ደማቸው እንዲረጋና ሥጋው ጠፈፍ እንዲል ሣር መብላት አለባቸው ።”

“እሞ ፣ ይሽው ይሻላል ። በሉ ፣ እኔም ጉዳይ አለብኝና ለዛሬ ይበቃናል” አሉ መምሬ ።

“በተጨማሪ ደግሞ ፣ዳስ የሚጣልበትን ቦታ የመጠራረጉና ዙሪያውን የማሳመሩስ ነገር እንዴት እንዴት...” ብለው አርጋው ተናግረው ሳያበቁ ፣ አንድ ልጅ እግር ሲሮጥ ሔደና ፣

“የአቶ ጣሰው ልጅ ሙቷልና ድረሱልን ይላሉ” ብሎ ተና ገረ ።

“ምን ሆኖ ?” አሉ አርጋው ።

“ከቤት ተቀምጦ የነበረ መድኃኒት ትላንት ማታ ጠጥቶ ታሞ ዐድሮ ነበር ፤ አሁን ሞተ ።”

“እዱ ጉድ ፣ ወንድሜን ! እንዴት ተጐዳ ! እዱ ጉድ” አሉ አርጋው ።

“ትልቅ ልጅ ኑረዋል ?” አሉ መምሬ ።

“ገና ሕፃን ነው ፤ ኧረ ሦስት ዓመት ቢሆነው ነው” አሉ አርጋው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እባክህ ካቶ ገብሬ ዘንድ ሩጠህ ሒደና ፣ ድንኳንና መንበር እንዲወስዱ ንገራቸው" አሉት ፣ መርዶ ያመጣውን ልጅ ።

"እሳቸውም መጥተዋል ፣ እዚያው ናቸው" አለ ልጁ ።

"ወዲያው ፣ መጣን ብለዋል በል" አሉት ።

"እንግዲህ ፣ ምን ቀረን?" አሉ መምሬ ።

"አንዲት ትንሽ ጉዳይ ደግሞ አለች" አሉ አቶ አርጋው። "ቀኛዝማች ሰይፉ የልጃቸው ባል አስቸግሯቸው ፣ 'እባካችሁ ምክሩልኝ ፣ ተቆጡልኝ ፣ እንዳልከሰው የወዳጄ የአብሮ አደጌ ልጅ ሆናብኝ ተቸገርኩ' ብለው ነግረውኝ ፣ ለዛሬ እናንተ ባላችሁበት ልጁን እንድንቆጣው ፣ እሳቸውንም እሱንም ቀጥሬያቸው ይጠብቁናልና ፣ አንድ ጊዜ ሳስጠራቸውና ጉዳዩን ሰምተን እንድንነጋገርበት" አሉ ።

"ብዙ የሚያቆየን እንዳይሆን!" ኦሉ መምሩ ።

"አይ ልጁን ጠርተን ነውሩን ነግረን ለመቆጣት ነው፤ አያቆየንም" አሉ አርጋው ።

"እሳቸው ይቆዩና ልጁን በቶሎ ያስጠሩታ!" ሉ እንደ ሻው ፣

አቶ አርጋው ፣ አቶ ቡልቻን ተከሳሹን እንዲጠሩላቸው ሰደዱዋቸውና ፣

"እንዲያው ያሳዝናል አሉ ! ይህ ልጅ አባቱ ትልቅ እስ ተዋይና ጨዋ ሰው ነበሩ ። ታዲያ የቀኛዝማችን ልጅ ለማግባት ሲጠይቅ ፣ ሁላችንም ደስ ብሎን ቀኛዝማችን አስቸግረን ፣ 'እባካችሁ ትማር ትቆይ' ሲሉን ፣ 'ሴት ልጅ ተማረችስ አልተማረችስ ምንድነው ትርፉ፣ ትዳር መያሂ ላይቀር ምን ያደርጋል? ዕድሜ ማስቆጠር?' ብለን ገፋፍተን ያጋባን እኛ ነን ። ታዲያ ዛሬ..." ብለው አርጋው ተናግረው ሳይጨርሱ ፣

"ታዲያ ዛሬ ፣ የተማረችውን ፣ ደሞዝ ያላትን ፍለጋ ሔዳ!" ብለው እንደሻው አቋረጡ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እዱ፣ መች እንደሱ ሆነ? ይህማ ያባት ነው። ውጭልኝ፣ በቃሽኽኮ አላለም።"

"ታዲያ ምን አላት?"

"እንዲያው እንደ ወደል አለሌ ቤቱን ጥሎ እየጠፋ ነው ያስቸገራት" ብለው አርጋው ሲናገሩ፣

ተከላሹ ቀረበና ለጥ ብሎ እጅ ነሥቶ ቆመ።

"ና ወደዚህ፣ ቀረብ በል" አሉና አርጋው፣ ቀጠል አርገውም፣ "ቀኛዝማች 'አስቸገረኝ፣ ቤቱን ጥሎ ሳምንትና ሁለት ሳምንት እየጠፋ ልጄን አሳዝኗታል፣ አባሳጭቷታልና ምክንያቱን ጠይቃችሁ ተቆጡልኝ' ብለው ስለ ጠየቁን ነው የጠራንህ። ወደ ለቅሶ ለመሔድ ቸኩለናልና ምክንያቱን ንገረን" አሉት።

ደምሴ ተቅለሰለሰ። ትዳር ከያዘ ገና አምስት ዓመቱ ነው። ከቀኛዝማች ሰይፉ ልጅም ሁለት ልጆች፣ ሴትና ወንድ ወልዷል። በአምስት ዓመቱ የትዳር ጉዞው ውስጥ፣ ተከሶ ከዕድር ሽማግሌዎች ዘንድ ገና መቅረቡ ነበር።

"እርግጥ ነው፣ ለሥራ ጉዳይ ብዙ ጊዜ ወደ ውጭ እሔዳለሁ። በዚህ ምክንያት ነው የምጠፋው" አለና ዝም አለ፣ እየተቅለሰለሰ።

"አሄሄ! አትቀልድብን" አሉ አርጋው፣ እያፈጠጡበት፣ "እንኳን ይህን ሌላም ብዙ ብዙ ነገር እናውቃለን። እዚህ አዲስ አበባ ሆነህ፣ ከቤት ውለህ ማታ ውልቅ ብለህ በዚያው ታድራለህ፣ ትሰነብታለህ፣ ያለ ጥርጥር ሌላ ቤት ለምደህ ወደሃል። ከሌላ ቤት ፍቅር የያዘህ መሆኑን አረጋግጫለሁ። ይህን ትክደኛለህ?"

"ታዲያ ምን አለ እንግዲህ?" አለና ደምሴ አካባቢዉን ቃኝቶ ወደ ሽማግሌዎቹ ዘወር አለና፣ "ከመምሬ በቀር፣ ከኔ ባለ ቤት አባት ጀምሮ፣ ከዚህ ካላችሁት መካከል እንደኔ ያልሠረቀ እኔ የሠራሁትን ያልሠራ ካለ ይፍረድብኝ!" አለ፣ ሁሉም ላይ ዐይኖቹን ተራ በተራ እየተከለና እየነቀለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ጉድ ፈላ! 'ዶሮ ጭራ ጭራ ታወጣለች ካራ' የሚባለው እንጋገር አሁን መጣ" አሉ መምሬ ፣ በሆዳቸው እየሣቁ ። የዕድሩ ሽማግሌዎችም እርስ በርሳቸው እየተያዩ ተጉሻሸሙ ።

"ሙግቱንማ ተከናችሁት የለም፣ ለቅሥፈትኮ ነው የተፈጠራችሁት ፤ አሳዳጊ በድኃችሁኮ ነው" እያሉ አርጋው ሲቀባጥሩ ፣

"ይልቁንስ የባለቤቴን አባት አማልዱኝ" አላቸው እንደቆመ ፤ "ባለቤቴን ይመልሱልኝ ። ወንድማቸው ትልቋን ልጃቸውን ከድሃ ባሏ አፋትተው ለሀብታም ዲሬክተር እንደሰጡት ሁሉ ፣ እኒህኛውም ከኔ አፋትተው ለአንዱ ባለሥልጣን ከመሰጠታቸው በፊት ሚስቴን ይመልሱልኝ ። እኔና እርሷ ልብ ለልብ እንተዋወቃለን ፤ እንፋቀራለንና ፣ የአገር መሣቂያ እንዳይሆኑ ለምኑልኝ!"

"ዋናው ፍሬ ነገር ቅድም ያልከው ነው" አሉ እንደሻው፣ ሽማግሌዎቹ ሁሉ በሐሳባቸው እንዲስማሙላቸው በአስተያየታቸው እየተለማመኑ ፣ "'እኔ የሠራሁትን ከመካከላችሁ ያልሠራ ይፍረድብኝ' ያልከው ነው ነገሩን የሚያካትተው ። የኛን ደግሞ ሴቶቻችን ሳይሰሙ ፣ ያንተን ምስጢር በየልቦናችን ይዘን ቤትህ ትዳርህ እንዳይፈታ እናደርጋለንና ፣ አንተም ፣ 'እንድ ጊዜ ተናዝኛለሁ ፣ ታውቆልኛል ፣ ከሽማግሌዎቹ እንደኔው መሰል ሞልቷል' ብለህ ልቅ እንዳትሆን ዋስ ጥራልን ።"

"መልካም ብለዋል ። ይሽሙ ነው ማታለያው" አሉ መምሬ ።

"እሺ እስማማለሁ ። ዋስ እጠራለሁ ፤ ያላችሁኝን እፈጥማለሁ" አለ ተከሻሹ ።

"እንግዲያው ነገ አንዳፍታ ወደ ቀኛዝማች ሰይፉ ቤት እንሒዳ?" ብለው አቶ አርጋው ሐሳብ አቀረቡና ፣ ሽማግሌዎቹ ከተመካከሩበት በኋላ በዚሁ ተወሰነ ።

"የጢሰኛዉና የዕድርተኛዉስ ዕዳ ታወቀ ። ገባሮቹስ ስንት ስንት ነው የሚያዋጡት ? አልተወሰነም ኮ" አለ ከበደ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"በዚያ በኩል ችግር የለም ። ከዚህ ቀደምም ለምደውታልኮ! ልጅ እድባሩ ቤት ሲሠሩ በፊትም ለሁለተኛዋ ሚስታቸው ሠርግ ያዋጡትን ያውቁታል..." ብለው እቶ አርጋው ቱና ግረው ሳያበቁ ፣ የፃ አለቃ ከበደ እቋረጣቸውና ፣

"ለመጀመሪያው ሠርጋቸውስ አላዋጡም ነበር ?" ብሎ ጠየቀ ።

"ያን ጊዜ እንኳ ጣሊያን ነበረና ሠርጉም እንደ ነገሩ ነበር። ባላገሩንም መጠየቅ አላመቸም ነበር ።"

"በእናንተስ በኩል ያለባችሁን ችግር አትናገሩም እንዴ?" አለና ከበደ ፣ ከአገር ቤት የመጡትን የገባር ተወካዮች ጠየቀ ።

'ባላገር ደግሞ ምን ችግር አለበት ። የሌለባቸውን ችግር እትጥራባቸው ? ካረሱበት ፣ ከደከሙበት ዕጥፍ ድርብ ምርት የሚዝቁበት መሬትኮ ነው ፣ ጌታቸው የሰጡዋቸው" አሉ አርጋው ፣ የገባሮቹን ብሶት ተወካዮቹ እንዳይናገሩ ሲከላከሉ ።

"ችግራቸውን ተናግረው ፣ እኛም አመዛዝነን ይሀን ይሆን ሳያሀል ከፈሉ ብለን ላንወስንባቸው ታዲያ ለምን መጡ? እዚህስ ለምን ተቀመጡ?" ከበደ ለአቶ አርጋው የሰነዘረው ጥያቄ ነበር ።

"ካገር ቤት ድረስ የመጡትማ ልኪባቸው ነው ፤ የሚጉ ድሰውንና የሚያስፈልገውን ዐውቀው ሔደው ከገባሩ ጋር ተመ ካክረው የምንጠይቃቸውን ሁሉ እንዲልኩ ነው ። ዛሬም ከመ ካከሳችን የተገኙት ጉዳዩ በጣም የታሰበበትና ከተሜው ሞምር ጉዳዬ ብሎ የያዘው መሆኑን እንዲረዱት በማለት ነው" አሉ አርጋው ።

"ታዲያ አሁንስ መች ነገርናቸው ? ይሀን ያህል እዋጭ ብለንኮ አልነገርናቸውም" አለ ፣ ከበደ ።

"ያውቁታል ። እነርሱ የሚያዋጡትን መች አጡትና ?" አሉ አርጋው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴን ነገር ስንደጋግመው ብንውል ምን ያደርጋል?" አለ ከበደ ፣ ቁጣ እየተናነቀው ፤ "ዐሥራ አምስት ሠንጋ የከተማው ጢሰኞችና የገጠር ገባሮች ሆነን እነድንገዛ ተፈርዶ ብናል ። ታዲያ ጢሰኞቹ በአጠቃላይ ስንት ስንት ፣ ገባሮቹም እንደዚሁ ስንት ስንት እንደምናዋጣ ለመወሰን ነበር ዛሬ የተሰበሰብነው ። አሁን ነገሩን ውል አላጡት ። እኛም ሆን ገባሮቹ ዕዳችንን በትክክል አላወቅነውም ። ያኛው እነኳ ነገና ተነገ ወዲያ ሊወሰን ይችላል ። የገባሮቹስ መች ሊወሰን ነው? ወይስ እነርሱ ተነጋግረው እንደየበትማቸው አዋጥተው ሊያመጡ ነው? ለምን ቁርጥ ያለ ውሳኔ አይነገራቸውም?

"ምናልባት ጢሰኞች የሚያዋጡትን ገባሮች እንዳያውቁ ፣ ገባሮች የሚያዋጡትንም ጢሰኞች እንዳያውቁ የታሰበ ጉዳይ እንደ አለበት?" አለ የሷ አለቃ ከበደ ።

"እሽ በሉ እንግዲህ ነገሩን ላሳጥረው ። ገባሮቹ በጢስ ሐያ ሐያ ብር ይክፈሉ" ብለው አርጋው ፣ የገባሮቹን ተወካዮች ተመለከቷቸው ።

"ምን ያህል ገባሮች አሉዋችሁ?" አለ ከበደ ፣ ከኪሱ መረቀትና እርሳስ እያወጣ ።

"ይህንማ የሚያውቁ ራሳቸው ጌቶቹ ናቸው ። በያገሩ ያላቸውን ርስት ቆጥሬ አልያዝኩትም ። እንኳን በመላው አገር ያለውን ገባር ፣ በዕድሩ ውስጥ እንኳ ያለውን ጢሰኛ ብዛቱን በቃሌ አልያዝኩትም" አሉ አርጋው እያገነገኑ ።

"እሺ ቅድም እንደ ነገሩን ፣ በሁለተኛው ሠርጋቸው ባላገሩን ስንት ስንት አስከፈላችሁ?"

"እርሱንማ እኔ አላውቀውም ። እንደዚሁ ከየገባሩ እህሉ ፣ ማሩ ፣ ቅቤዉ ፣ ሠንጋዉ ፣ ሙክቱ ፣ ሽሀሩ ፣ ብሩ ምኑ ቅጡ በያይነቱ ገባ እንጂ! ይህን ያህል ይክፈል አልተባለም ነበር ። እኔም አልያዝኩትም ። ምናልባት ጌቶቹ ናቸው የሚያውቁት" አሉ አቶ አርጋው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ይበሉ አሁንም ፣ ገባሮቹ የሚከፍሉትን እዚያው ባለር ስቶቹ ይወስኑ ። እኛ ዕድርተኛዉ ሊከፍል የሚገባውን ነገና ተነገ ወዲያ እየተገናኘን እንወሰን” ብሎ ከበደ ብድግ ሲል ፣

“እኛም እንጂ የምንናገረው ነበረን ፣ እናንተም ብትሰሙ ልን በወደድነ ነበር” ብለው ከገባሮቹ ተወካዮች አንዱ ተነሡ ፤

“እንዴ እንዴ ! ምን ሊሉ ነው ? ይቀመጡ ፤ እቤት ለጌ ቶቹ ያመለክታሉ” አሉ አርጋው ፣ ተቆጥተው ።

“ቢናገሩ ምን አለበት ?”

“ዝም በል የፃ አለቃ ፤ አንተም ዝም በል ። እኛ እንዳን ሰማው የሚደረግ ምስጢር ይኖራል” አሉ እንደሻው ።

“ጥዋትኮ ወደዚህ የመጣነው ፣ ‘እዚያው ሐዳችሁ ሁላ ችሁም በአንድነት ተመካክራችሁ የሚሆን የሚሆነውን አድ ርጉ ብለው ጌቶቹ ነግረውን ነው የመጣነው” አሉ የገባሮቹ ተወካይ ።

“አቶ አርጋው” አለ ከበደ ፣ ቆፍጠን ብሎ ።

“እቤት !” አሉ አርጋውም ተኮሳትረው ።

“ይህ ነገር እነዴት ነው ፣ መላው ጠፋሳ!”

“በቃ በቃ ተወት ! የገባሮቹን ክፍያ ጌቶቹ ባሉበት ተመ ካክረን እንጨርሳለን ፤ እዚህ መነታረክ አያስፈልገውም” አሉና ኦርጋው ነገሩን ያመዳሙት ።

“በሉ እንግዲህ ፣ ነገሩን ቀላል ያድርግላችሁ” አለ ከበደ፣ እነዚያን የገባር ተወካዮች በኃዘኔታ እየተመለከተ ። እነዚያ ገባሮች የሚጫንባቸውን ፡ሠርግ መዋጮ ካልከፈሉ ከሠ ፈሩበት መንደር ሲባረሩ ፣ ተሰብስበው በእስር ቤት ሲታጉሩ በዐይነ ሕሊናዉ ተመለከታቸው ።

ሽማግሌዎቹ፣ በየዕለቱ እየተገናኙና እየተመካከሩ ፣ እያን ዳንዱ ዕድርተኛና ጭሰኛ ለባለርስቱ ሠርግ ሠንጋ መግዣ ሊያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዋጣ የሚገባውን ለመወሰንና ለማስከፈል ከተስማሙ በኋላ ፣ ችሎቱ ተነሥቶ ወደየቤታቸው ሔዱ ፤ አቶ እንደሻውና ከበደም አብረው እየተጨዋወቱ ወደ ቤታቸው ሲያዘግሙ ፡

"ምስጢሩ አልገባኝም ፤ ለምንድን ነው ባላገሮቹ እንዳይ ናገሩ አቶ አርጋው የከለከሉዋቸው ?" ብሎ ፣ ከበደ አቶ እንደ ሻውን ጠየቃቸው ።

"እንዴት ሊገባህ ይችላል ፣ ልጄ ? የአርጋው ተንኮል ፣ የአርጋው ጥልፍልፍ መች እንዲህ በዋዛ ቁሞ ይታያል ? ውስጥ ውስጡን ነው እንጂ የሚገዘግዝ ። አየህ ፣ ጌታው ካገር ቤት የመጡትን የገባር ወኪሎችና እኛ ጢሰኞች ተመካክረን የተወሰነ ገንዘብ እንድናዋጣ አዘው ነበር ፣ ባላገሮቹን የላኳቸው ። እርሱ ግን እኛም ሆን ጌታው ሳናውቅና ሳንወስን ባላገሮቹን የፈለገ ውን ያህል ያስከፍልና ፣ ቢፈልግ ገሚሱን ፣ ካልፈለገም ሲሶዉን ለጌታው ይሰጥና ፣ በቀረው ገንዘብ ባንዱ ሠፈር ጢሰኝነት ተመርቶ ወይም ቦታ ገዝቶ ቤት ያከራያል ማለት ነው ። ምስጢሩ ይኸው ነው ። ባላገሮቹ እንዳይናገሩና እኛም ይህን ያህል ክፈሉ ብለን እንዳንወስን ፣ ሽንጡን ገትሮ የተሟገተው እርሱ የፈለገውን ሊቈጥባቸው ፊልጎ ነው ፤ ገባህ ?" አሉት ።

"እስከ መቸ ድረስ በዚህ መንገድ ይዘልቃሉ ?"

"ምን እንዳይሆን ብለህ ?"

"እንዲያው አንድ ቀን ቢያዙስ ?"

"ማነው የሚነካው ? አድባሩ እንደሆኑ እንደምታያቸው ናቸው ። በከተማው ያለችውን ሴትና ወሬ ሲለቅሙ ነው የሚ ውሉት እንጂ ፣ 'ከጢሰኛ ምን ያህል ፣ ከገባር ምን ያህል ገባ' ብለው ተናግረው አያውቁም ። የሰጣቸውን ነው የሚቀበሉ ፤ ያጐረሳቸውን ነው የሚበሉ ፤ ሌላ ነገር የለም ። ደግሞስ እሱ ብቻ መስለህ የቤተ መንግሥቱ ፣ የመሳፍንቱ ፣ የመኳንንቱና የባለርስቱ ወኪል የሆነ ሁሉ ነው የሚያጋፍፈው ። ማን ነክቷቸው ፣ ማን ጠይቋቸው ያውቃል ? ስንትና ስንት ጉድ ፣ ስንትና ስንት

t.me/OLDBOOKSPDF

ግፍ ሞልቷል መሰለህ ?'' አሉና ፥ ትክዝ ብለው ተመለከቱት ።

ሽማግሌዎቹ ፥ ከሰኞ ጀምረው በየዕድርተኛዉ ቤት እየዞሩ፥ 'ይህን ያህል ጥለንብሃል ፤ ይህን ያህል ጥለንብሻል' እያሉ ሲወስኑ ሰነበቱ ። በእያንዳንዱ ዕድርተኛ ላይ የሚጣለውን ከፍያ አቶ አርጋው ይመዘግባሉ ። ከዕድርተኛዉም ለሚሰነዘረው ቅሬታ አቶ አርጋው ይመልሳሉ ፤ ይከራከራሉ .....

'እንደ መንግሥት ግብር ለባለርስት ሠርግ ዕዳ ትጥሉብን ?'

'በአዲስ አበባ ባለርስቶች ጥጋብና ግፍ ከሚመጣው መዓት ይሠውረን !'

'ጌቶቼ ፥ በጉልት ችርቻሮ ነው የምኖረው ። ይህን ሁሉ ገንዘብ ከየት አመጣለሁ ?'

'ዕንጨት ተሸክሜ የምኖር ነኝ ። በምን ዐቅሜ ነው ይህን ያህል የምከፍለው ?'

'ቤት ሙሉ ልጆች አሉኝ ። አስተያየት አድርጉልኝ ።'

'ደመወዜ የምታውቁት ነው ? እንዴት ይህን ያህል ትጠ ይቁኛላችሁ ?'

'ኃዘን ላይ ተቀምጠን እንዴት ለሠርግ መደገሻ እንጠ የቃለን ? ግፍ አይሆንም ?'

'ጢሰኛ ጢሰኛውን አስከፍሉት እንጂ ፥ በቤት ኪራይ የም ንኖረው ምን በወጣን ?'

'ብቻ ከመሬቱ ኪራይ ጋር ደምራችሁ ቀዋሚ ግብር እን ዳታደርጉብን እንጂ ፥ ለአንድ ጊዜ ብቻ ከሆነስ እንችለዋለን ።'

'ለሠርጉስ ይሁን እንከፈል ። ደግሞ ለክርስትና እንዳት ጠይቁን እንጂ !'

'እሁን ዕለት ሌባ ያለኝ የሌለኝን ዘርፎኝ ፥ ከየት አባቴ አምጥቼ እከፍላለሁ ?'

t.me/OLDBOOKSPDF

'በቤት ሥራ ጣጣ ተወጥረን ፣ ለእናንተ ሠርግ መደገሻ ገንዘብ ከየት ሊመጣላችሁ ነው ?'

'ለሐኪም ቤት ተበድሬ የከፈልኩት ዕዳ ከላዬ ላይ ተከ ምሮ ፣ የእናንተን ሠርግ መዋጮ ደግሞ በምን ጉዴ ልሸከመው ነው ?'

'ከቻላችሁ ራሳችሁን ችላችሁ ብትደግሱ ፣ ያለዚያ ቢቀር ምን አለበት ? የመብራትና የውሃ የምከፍለው ችግሮኛል ፤ ደግሞ እናንተ ለሠርግ ትላላችሁ ።'

'በአገር ቤት የሚኖሩ ዘመዶቻችን ፣ 'ከብቶቻችን በበ ሽታ አለቁ ፣ ላምና በሬ ገደል ገቡ ፣ አህያችንን ጅብ በላብን ፣ የመሬት ግብር የምንከፍለው ተቸገርን ፣ ለአቤቱታ መጥተን ስንቅ አለቀብን ፣ ጉቦ እምንከፍለው ቸገረን' እያሉ ያስቸግሩ ናል ። እናንተ ደግሞ የኛ ዘበናዮች ለሠርግ አዋጡ ትሉናላችሁ!'

'ወቸ ጉድ ! ሰው ለአገሩ ልማት ፣ ለሕዝብ ጥቅም ለሚውል ተግባር ቢያዋጣ ያምራል ፤ ያስከብራል ፤ ያኮራል ። እንዴት ለባለርስት ዘበናዮች መደነሻ አዋጡ ይባላል! መንግሥት የለም! እያይም ? አይሰማም ? ወይንስ ሕዝቡን ጭምር ነው ለባለሬ ስቶቹ የሰጠው '.....

ዕድሮተኞቹ ፣ ይህንና ይህን ነመላለሰውን ሮሮ ቢያለሙም እቶ አርጋው በዕድር ኃላፊነታቸውና በወኪልነታቸው ሥል ጣን እያስፈራሩ ማስከፈላቸውን ቀጠሉ ። አንዳንዶቹ ፣ የባሰ ባቸው ፣ ልጅ አድባሩን ከቤታቸው ሲወጡና ሲገቡ እየጠ በቁ ችግራቸውን ሲያመለክቱ ፣ 'እሺ ፣ ግዴለም ፣ ለአቶ አርጋው እነግራለሁ' እያሉ በጠገበ ኦቶሞቢላቸው ይፈተለ ካሉ ። እና ነገሩን ችላ ይሉታል ፤ ወይም ይረሱታል ።

ለሰሙ ያህል ወደ ወረዳ ግዛታቸው ብቅ ብለው ፣ በዚያ ውለው አድረው ፣ ከተዘጋጁ ማዘጋጆች ላይ ፊርማቸውን አኑ ረው ፣ ወደ አዲስ አበባቸው ከተፍ ስለሚሉ ፣ የዕድርተኞቹ እቤ ቱታ በመካከሉ ይረሳል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የዕድሩ ሽማግሌዎች ፣ በየቤቱ እየተዘዋወሩ ፀየእንዳንዱ ዕድርተኛ ላይ የጣሱበትን ሒሳብ እቶ አርጋው ከሰበሰቡ በኋላ ፣ ስለ ሁኔታዉ ለመወያየት ደግሞ እንደገና በተለመደው ቦታና ሰዓት ተገናኙ.....

እሀል ውሃ የማያሠኝ ጹላ ይዞ ፣ ከወገቡ በላይ ራቁቱን ሆኖ ፣ ሻሽ ቢጤ ጠምጥም ፣ ድንጋይ እያነሣ እየወረወረ ፣ እየ ለፈለፈ አንድ ሰው ወደነርሱ ሲመጣ ፣ ቀበሮ እንደ መጣባቸው ፍየሎች ሆነው ሲመለከቱት ፣ ሰውዬው እየቀረባቸው መጣና ፣

"ያድባሩ ዕድርተኛ መረደበት ፍዳ

ቤት ንብረቱን ሽጦ እንዲያቀርብ ፍረዳ

አርጋው እንቆ ያዘው ደርሶ በማለዳ"
ብሎ ሲዘፍን ፣

"አትሒድም ፣ አንተ ምናምንቴ ?" አሉ አርጋው ።

"አሄሄ ! ዛሬስ ብሶበታል" አሉ መምሬ ።

"ይበል ይበል የሚያሰኝ ቅኔ ነው" አሉ እንደሻው ።

"አሄሄ ያ ከበደ እንኳ የለ ። እንግዲህ ማን ሊመልሰው ይሆን ?" አሉ መምሬ ።

"ወደ ጌትዮው ቤት ነበር እንጂ መሰደድ ። እዚህ ምን ይፈጥራል ?" አሉ እንደሻው ።

"አትሒድም ተዚህ ፣ አንተ ምናምንቴ !" ብለው አርጋው ወደ ርሱ ሔዱ ።

"አንተ ወራዳ ፣ ና ትግል እንግጠም" አለ ደባልቀው አንፈራጦ ቆሞ ።

"አሄሄ ! ዛሬስ ብሶበታል" አሉ መምሬ ፣ እንገታቸውን እቀርቅረው ።

"ከጌትዮው ጋር ነበር እንጂ ግጋጠም" አሉ እንደሻው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንካ ፣ የጠላ መጠጫ አያደል እምትፈልገው ?" አሉና አርጋው ተኪሳቸው ሳንቲም አውጥተው ወረወሩለት ።

"ለጌታህ ሠርግ ደግስባት ፣ አሁን የመጣሁ ተ ካንተ ጋር ትግል ልገጥም ነው" አላቸው ፣ ዝም ሲሉ ጊዜ ። "ፈትለ ወርቅ ነይ ትግል እንግጠም" አለ ደገመና ።

"ምን ያደርጋ አርሱ ፣ እንዲህ ብለህ ተናገር ኮብሎ አይ ያል ፣ እሱማ በሽተኛ ነው" አሉ ፈትለ ወርቅ ፣ አንገታቸውን ያፍተለ ።

"በል ና ወዲህ ፣ ብር እጨምሬ ልሃለሁ" አሉና አርጋው ባለ ጉዳታቸው የደረት ኪስ የነበረ ጥቅል ብር አወጡ ።

"እንተና ፍጡር በጌታህ ሠርግ እያመካኛችሁ ሕዝቡን ትቦጠቡጣላችሁ ። ይልቅስ ሰማ ። ይታከቱ ያለችበትን ልንገርህ! ትላንት እንተን ፍለጋ ነው መሰለኝ ፣ እዚህ መጥታ አግኝቻታለሁ ። ፍጡርም ለጌታህ ሠርግ የሠንጋ መግዣ ከባላገር ሊጋ ፍፍ ወደ ጌታው ርስት ሔዶልሃልና ፣ ቶሎ ሒድላት ። እርገጣ ቸው ሳይቀድምህ ። ፈትለ ወርቅ ፣ ማታ እመጣልሻለሁ ጠብቂኝ" አለና ፣ እየዘፈነ ጉዞውን ቀጠለ ።

"ቆይ ፣ አንት ምናምንቴ! ቆይ! ከዚህ ሠፈር ሳላጠፋህ ብቀር እውነት እኔ አይደለሁም" እያሉ አቶ አርጋው ወደ ችሎቱ ሲመለሱ ፣ "አሁን የተናገረው የምሥራችም ነው" አሉ እን ደሻው ፣ ሲያባጩባቸው ።

"ምኑ ነው የምሥራቹ!" አሉ አርጋው እየተቀመጡ ።

"ሴትዮዪቱ ብቻዋን መሆንዋን መናገሩ ።"

"ኤዲያ! እርስዎ ደግሞ የዕብድ ገላጋይ!"

"እሄሄ! ደባልቀው ነው ያበደ ? ያበዳችሁስ እናንተ ነበራችሁ" ብለው እንደሻው መለሱላቸው ።

"አሁን እንግዲህ ወደ ዋናው ጉዳይ እንመለስና..." ብለው መምሬ ተናግረው ሳያጨርሱት ፣ አነዲት ሴት እያለቀሰች ወደ እነርሱ ሔደች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ያሀች ልማያኛ ነገናዛ ፥ ደግሞ መጣች ! ሠፈር ያሰለቸች" አሉ አርጋው ። ሴትዮዋ ከነርሱ ዘ፡ድ ደረሰችና ፥

"እርስዎ ነዎት የሚያስደበድቡኝ! 'ይሰሩልኝ ፥ ይያዙልኝ ይዳኙኝ ብለዎት ፥ እሺ እቆጣዋለሁ ፤ ሁለተኛ ከደጅሽም አይደርስም' እያሉ ፥ በነጋ በጠባ የሚያስደበድቡኝ እርስዎ ነዎት። ማታ ከጮሪቤት ተደብቄ ተረፍኩ ። አሁን መጥቶ ይሽውና እጄን ጠምዝዞ ፥ ገንዘቤን ቀምቶ ፥ በአጠና ቀጥቅጦኝ ሔደ ። ይሽውና ሰውነቴ ፥ ጀርባዬን እዩት" ብላ ፥ ነጠላዋን አንሥታ ቀሚሱዋን ልታወልቅ ስትል ፥ ወይዘሮ ፈትለ ወርቅ ተነሥተው ያዙዋትና፥

"በኋላ ከቤት ታሳይናለሽ ፤ ምች ይመታሻል" አሉዋት ፥ ነጠላዋን እያለበሱ ።

"ምን ሁና ነው ?" አሉና እንደሻው ፥ ጠየቁ ።

"ወንድሜ የእነርሱ ነገር በጣም አስቸግሮናል ። ባሉዋ የነበረ ሰው የኛ ሠፈር ነዋሪ ነው ፤ እርሷ የፊታውራሪ ሠፈር ነዋሪ ናት ። ጧት ማታ እየሔደ እየተደባደበ አስቸገረ ። እርሷም አታርፍም ፤ ምናምኑን ቆጥ ባለች ቀን ፥ ብቅ ብላ ትሰድበዋለች ። ሠፈሩን ያስቸገሩ ናቸው" አሉ አርጋው ።

"ሠፈሩንማ ያስቸገሩ ምን እነርሱ ብቻ ናቸው ? ባለርስቱ ፥ ወኪሉ ፥ ሴቱ ፥ ዕብዱ..." እያሉ ፥ እንደሻው ሠፈር ያስቸገረ ያስቸገረውን ሲቆጥሩ ፥

"ኤዲያ! እርስዎ ደግሞ በቁም ነገር ላይ ቀልድ ያበዛሉ' አሉና አርጋው አጉረመረሙ ።

"አሁን ከተናገርኩት አንድ ቀልድ ካለበት ልቀጣ" አሉ እንደሻው ።

"እሪ እባካችሁ ፤ የኔን ጉዳይ እንድ በሉኝ" አለች ሴትዮዋ ።
"አሁን ታዲያ ምን እናደርጋለን ?" አሉ አርጋው ።
"ተደብድቤ ፥ በዚያ ላይ ገንዘቤን ተቀምቼ ልቅር ?"

"ከዚህ እንደ ተነሣን እቤቱ ሔጄ እይዝልሻለሁ ። ገንዘብሽን አሰጥሻለሁ ። አሁን ሒጅና ከኔ ቤት ጠብቂኝ መጣን" ብለው አርጋው መለሷት .....

t.me/OLDBOOKSPDF

አርጋው ፣ ወደ መምሬ መለስ ብለው ፣ "እንግዲህ ወደ ዋናው ጉዳይ እንመለስና ፣ አብዛኛው ዕድርተኛ ገንዘቡን ከፍ ሏል ። የቀሩት በዚሁ ሳምንት ውስጥ ይከፍላሉ ። አሁን በጀ ሦስት ሺህ ብር ይገኛል ። በአገር ቤት በኩል ግን እስካሁን የመጣ የለም ። የማይሆን ከሆነ እንግዲህ ከሰሞኑ እኔዉ ሔጄ የሚሆነውን አድርጌ እመለሳለሁ" ብለው ተሰብሳ ቢዎቹን ተመለከቱዋቸው ፣ ወደ አገር ቤት ርስት ሔደው ከገ ባሩ ሁሉ በትርፍ ለሚቀበሉት ገንዘብ የቸኮሉ መሆናቸውን ያወቁባቸው መስሏቸው ።

"እንዴ ፣ አገር ቤት ሔዳችሁ ደግሞ እዚያ እንዳትገናኙ" ብለው የአሸሙር ጥያቄ ሠነዘሩ እንደሻው ።

"ከማን ጋር እንዳንገናኝ?"

"ከፍጡር ጋር ?"

"እርሱ ከዚያ ምን ሊሠራ ይሔዳል ?"

"ቅድም ደባልቀው ሲለፈልፍ አልነበረም ?"

"እርስዎ ደግሞ ፣ የዕብድ ነገር ሰምተው ?"

"ለነገሩማ ፤ ለእናንተ ጌታ ሠርግ መደገሻ ላመጣ ወደ ፊታ ውራሪ ርስት እሔዳለሁ" ሲሉ ነበር አሉ ፣ ወይዘሮ ፈትለ ወርቅ ጣልቃ ገብተው ።

"ይሄዋ ! ደባልቀው ዕብደት የለበትም ! እውነቱን ነው' አሉ እንደሻው ፣ በቃለ አጋኖ ።

"ብሔድስ ፣ የርሱ ጌታ ርስት ወዲያ ፣ የኛዉ ወዲህ ነው ! ምን ያገናኘናል ?" አሉ አርጋው ።

"አይ! ደግሞ እንደዚሁ እንደ ከተማው ኩታ ገጠም እንደ ሆነ ብዬ ነው" አሉ እንደሻው ።

"ኩታ ገጠም ቢሆንስ ምን ያገናኘናል ?"

"እዚህ ያገናኛችሁ ፣ እዚያም እንዳያገናችሁ ብዬ ነዋ!" አሉ እንደሻው ፣ አቶ አርጋውን እየተመለከቱዋቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ኤዲያ! እርሰዎ ደግሞ በቁም ነገር ላይ ቀልድ ያበዛሉ" አሉ አርጋው ኮስተር ብለው ።

"እኔንኮ አዘገያችሁኝ" አሉ መምሬ ፣ በዕለቱ ተጠርተው በት የነበረው ስንበቴ ትዝ ብሏቸው ።

"ጐሽ ፣ ጐሽ! የ፤ አለቃ ከበደ ያውና መጣ" አሉ እንደሻው በሩቅ እየተመለከቱት ።

"አሁንኮ የገንዘቡን አወጣጥ ነገር ጨርሰነዋል" አሉ አር ጋው ፣ "የሚቀረን የዳስ ሥራው ጉዳይ ነው ። ቦታውን ማዘጋ ጀት ፣ ዕንጨት ማቀራረብ ፣ ቆርቆሮ መግዛት ፣ ሠራተኞች መቅጠር በዕድርተኛው ሁሉ ላይ የተጣለ አደራ ነው ።"

"ለመሆኑ ሠርጉስ መቸ ነው ?" አሉ መምሬ ።

"እንዴ ፣ የወዲያኛው እሑድ ነዋ ! ሁለት ሳምንትኮ ነው የቀረው ። ረሱት እንዴ ?" አሉ አርጋው ፫

በቅርብ ርቀት ያዩት ከበደ ከሽማግሌዎቹ ዘንድ ደረሰና ፣ ሰላምታ ሰጥቶ ፣ እንደ ተለመደው ወንበሩን ጠጋ አድርጐ ከአቶ እንደሻው ጐን ተቀመጠ ። ሁለቱ በሐሳብም በአነጋገርም ይደጋገፉሉና ፣ በስብሰባም መለያየት አይወዱም ።

"ምነው እስካሁን አረፈድከ ?" አሉ እንደሻው ።

"የሠፈራችን ጉድ ነዋ ያስረፈደኝ!" አለ የጉድ ከረጢቱን ቋጠሮ ለመፍታት እየቸኰለ ።

"የሠፈራችን ጉድ በረፋድ ጊዜ ብቻ ከለቀቀህም ራሱ ጉድ ነው" አሉት አርጋው ፣ እያባጩበት ።

"እሄሄ! ቅድምኮ ልጄ ፣ ያ ልቡን የነሣው ሰው መጥቶብን ፣ እንተ የለህ ፣ እንዲያው የሆነ ያልሆነውን እየለፈለ ፈብን አስቸግሮን" ብለው መምሬ ክሰና ስሞታቸውን ገና እነብንበው ሳያበቁ ፣ ስለማን እንደሚናገሩ የገባው ከበደ አቋረጣ ቸውና ፣ "አባቴ ፣ እዚህ ሠፈር ልቡን የነሣው ሌላ ሞልቶልዎ ታል ። ደባልቀውማ ጤነኛ ነው ። ቢሰሙ ስንት ጉድ አለ መሰ ለዎ ?" አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ዐውቄብሃለሁ ፣ አርጋውን፣ ጌታውን ልትወቅስ ብለህ ነው" አሉ እንደሻው ።

"ምን እነርሱ ብቻ ! ስንት ጉደኛ ሞልቷል መሰለዎ ? ጆሮ ያልሰማው ስንት ጉድ ተወለደ መሰለዎ ? ሠፈሩ ጉደኛ ሠፈር ነው" አለ የፃ አለቃ ከበደ ፣ ሣቅ እየፈታተነው ።

"በሠፈራችን እንግዳ ጉድ ምን ተገኘበት ?" አሉ ፈትለ ወርቅ ።

"ላንቱ እንግዳ ሆኖ አስካሁን ያስረፈደሀን ጉድ ታዲያ እትነግረንም ? ሌላ ጉድ አስቲወለድና አስቲራባ ድረስ ነው የም ትጠብቀው ?" አሉ አርጋው ፣ ከኪሳቸው ያወጡትን የጢስኛ ችና ዕድረተኞች ስም የተጻፈቦትን ወረቀት በርሳስ እየጨነቋ ቆሩ ።

"ለዚህ ለጣጠኛ ሠርግ የሚሆን ገንዘብና ሠንጋ እንዲያመ ጡላቸው ፣ ፊታውራሪ አቶ ፍጡርን ከትላንት ወዲያ ወደ አገር ቤት እንዲሔዱ አዘዋቸው ኑሮ ፣ እርሳቸውም ትላንትና ጥዋት ተነሥተው ዕቃ በጫን መኪና ጉዞ ይጀምራሉ ። ያ መኪና ከመ ንገድ ሲበላሽባቸው ጊዜ ፣ ወደፊት ለመሔድም ሌላ መኪና ሲያጡ ጊዜ ፣ ከዚሁ ከአዲስ አበባ በአውቶብስ ተጣፍረው ለመ ሔድ ትላንት ኮምሽቱ ላይ ወደዚህ ይመለሱና ፣ በቀጥታ ወይ ዘሮ ይታክቱን ደብቀው ወዳስቀመጡበት ቤት ይሔዳሉ ።

በር ሲቆረቁሩ አንዲት ልጅ ትከፍትላቸውና ሲገቡ ፣ "እረ እንግዳ ገብቷል" ትላቸዋለች ። በዚህ ጊዜ እርሳቸውም ይናደ ዱና በሩን በእርግጫ በርግደው ወደ መኝታ ክፍል ሲገቡ ሴትዮዋን ካንድ ሰው ጋር ያገኙዋቸዋል ፤ ወዲያው በያዙት ዱላ ሁለቱንም ይጨረጋግዷቸዋል ። በዚህ ጊዜ ሴትዮዋ ይን ሡና "'እረ ነግሬያለሁ ፣ ውርድ ከራሴ ፣ ነው ፣ ጌቶች ናቸው !' እያሉ ይጮሃሉ" ብሎ ሳይጨርስ ፣

"የትኛው ጌቶች ?" አሉ እንደሻው ።

"ፊታውራሪ !" አለ ከበደ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ፊታውራሪ እርገጣቸው!?"

"የጉድ ጉድ ነው፣ ብልግና!" አሉ እንደሻው፣ "'ፊቴን ለግላየት የሚኮራ ውሎ አድሮ ምኑን ያሳያል ነው' የሚባለው ገና አሁን ደረሰ። አዩ ፊታውራሪ! ምን ቀን ጣላቸው በል?"

"እኮ መጨረሻውስ ምን ሆነ?" አሉ ፈትለ ወርቅም።

"በሩን የከፈተችው ልጅ እሪ ስትል ጉረቤት ደረሰ። እንዳ ጋጣሚ ሆኖ በዚያው ግድም ፖሊሶች ተገኙተው፣ ሁሉንም ጣቢያ መስደዋቸዋል።"

"እና ፊታውራሪ ጣቢያ ናቸው?"

"እርሳቸውማ ራሳቸውን ስለ ተመቱ፣ ይታከሙ ተብለው ግታውን በዋስ ተለቀዋል።"

"ለይታከቱ ዋስ የሚሆንስ አልተገኘም?" አሉ እንደሻው፣ አርጋውን እየተመለከቱ።

"ዋስ ቢገኝም ምርመራው አላለቀም። እኔም ነገሩን ትላን ትና ግታ ሰምቼ ነበረና፣ ጥዋት ሔጀ ሳይባባስ በቶሎ እንዲያ ልቅ ብዬ ነበረ። የጣቢያው ሹም አይገቡም ስለተባለ፣ ሁለቴን ብቻ አነጋግሬ መጣሁ" አለ የኔ አለቃዉ።

"ፍጡርስ ቢሆን መኪናቸውን ሲያይ ቢመለስ ምን ነበር?" አሉ እንደሻው።

"መኪናቸውንማ በሌላ ሠዋራ ቦታ ላይ እቁመው ጋቢ ለብሰው፣ አልባሌ መስለው ኑሩዋል የሔዱት" አለ ከበደ።

"አረ እንኳን መግሪያ ያልያዙ። ያበላሹት ነበር" አሉ እንደሻው።

"የሳቸው መግሪያ ደግሞ ማንን አበላሽቶ ያውቃል?" አሉ አርጋው፣ ከንፈራቸውን እየለጠጡ።

"እንዲያው ለነገሩ ተጉድተው ይሆን?" አሉ እንደሻው።

t.me/OLDBOOKSPDF

"በመጀመሪያ የመታቸው ወገባቸውን ነበር ። ቀጥሎ የሙ ነዘረው ደግሞ አናታቸውን ነው ያገኛቸው ። እንደ ሰማሁት ብዙ ደም ፈሷቸዋል ።"

"እንደዚያ የነረታቸው እንደተኙ ነው ?" አሉ እንደሻው ።

"አዎ እንደተኙ ነበሩ ።"

"እንዲያው ያሠጋቸው ይሆን ?" አሉ መምሬ ።

"አይ ለክፉስ አይሰጣቸውም ። ደግሞ ካልደገማቸው በስተ ቀር ።"

"ሌትየዋስ ተጐድተው ይሆ ን?" አሉ እንደሻው ፣ አርጋውን እየተመለከቱ ።

"አርሳቸው እ'ነኳ ወገባቸውንና ሽንጣቸውን ነው የጎመቱት ደጎና ናቸው ።"

"እከድ እከድዬ! ዋና ዋናውን ክፍል ነው ያገኘው" አሉ እንደሻው ፣ አርጋውን የጐሪጥ እያዩ ።

"እንዲያው ለመሆኑ ይህን የጉድ ጉድ ባለቤታቸውስ ሰም ተው ይሆን ?" አሉ መምሬ ።

"አዩ የርሶዎ ነገር ! ከእንግዲህማ ከጽ!ፍ እስከ ጽንፍ ያስ ተጋባል እንጂ ። ሌላው ቢቀር ደባልቀውስ ለዚሄ ነገር ይተኛ ለታል ብለው ነው ?" አሉ እንደሻው ።

"ይህን ጊዜማ ግጥሙ ሁሉ ተገጥሞ ለደባልቀው እየተነ ገረ ይሆናል እንጂ ፣ አባቴ ። ሠፈራችንን እያወቁት ። እንኳን የሆነውን ገና ያልታሰበውን ፈጥሮ የሚያወራኩ ነው" አሉ ፈት ለወርቅም ፣ በደረሰው 'ጉድ' ደንግጠው በሁለት እጆቻቸው ሁለት ጆሮዎቻቸውን ይዘው ።

"እንኳን በዚሁ ያለፈላቸው እንጂ ፣ ሌላ ምን ይባላል ?" አሉ እንደሻው በማባጨት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ኤዲያ! እርስዎ ደግሞ በሆነ ባልሆነው መቀለድ ምንድ ነው፤ የገዛ እሽከራቸው በዱላ ሲወቃቸው፥ ከዚህ ሌላ ምን ሊደ ርስባቸው ኑሮዋል?" አሉ አርጋው፥ የውስጥ ደስታቸው ፈነቃ ቅሎ እንዳይወጣባቸው እየታገሉ ።

"እንዴ፥ አቶ ፍጡር ሽጉጥ ይዘው ቢሆን ኑሮኮ ሊገድሉ ዋቸው ይችሉ ነበር" አሉ እንደሻው ።

"ኤዲያ! በየትኛው ወንድነት?" አሉ አርጋው ።

"ይታከቱን ከእርስዎ በነጠቁበት ወንድነት!"
"ደሞ እዚህም እሳት ሊለኩሱ ነው፤ በቃ ወደ ዋናው ጉዳ ያችን እንግባ፤ እባካችሁ እኔም ቀጠሮ አለብኝ" አሉ መምሬ።

"ስርቆ ነው የወሰዳት ። አታሎ፥ አባብሎ ነው የወሰዳት። 'ሌባውን ሌባ ቢሰርቀው ምን ይደንቅው' ይባል የለም? ይሽ ውና መለከረበት" አሉ አርጋው፥ በጣውንታቸው መጋለጥ ተደስተው ።

"እንግዲህ እኔ ልሒድላችሁ" አሉና መምሬ ብድግ አሉ ።

"እንዴ! ሁላችንም እንሒድ እንጂ ። ቁስለኛ የምንጠይቅኮ እንጠፋም ፥ ሌባው ከተያዘ" አሉና እንደሻው ተነሡ ፥ አቶ አርጋውን በሽሙጥ እያዩዋቸው ። ሌሎቹም ተነሡ፥ አርጋ ውን እየተመለካከቱ ።

"ኤዲያ! ምን ያደርጋል አጉል ጨዋታ?" አሉ አርጋውም፥ ተነሥተው ሁሉንም እየገረመሙ ።

"ለመሆኑ ምን የቀረን ነገር አለ? የሠርጉን ጣጣ፥ የተጣሉ ትን ዕድርተኞች ጉዳይ አዳምጠናል ። የደባልቀውንም ስድብ ቀምሰናል ። የይታከቱንም መቅረት ሰምተናል" አሉ እን ደሻው እየተንጠራሩ ።

"ኤዲያ! ምን ያደርጋል ቀልድ፤ በቁም ነገር ላይ ቀልድ ምን ይባላል?" አሉ አርጋው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንግዲህ ፣ ያም ሆነ ይህ ፣ ፍሬ ነገሩ መቸም አልቋል ፣ አይደል ? ምን ቀረን?" አሉ መምሬ ።

"ፍሬዉም ገለባዉም ይኸው ነው ፤ አልቋል ። የቀረው እንግዲህ ቁስለኛ ማስታመም ነው" አሉ እንደሻው ፣ በአርጋው ላይ እያሾፉ ።

"የዳሉ ጉዳይኮ ገና ነው ። የዳስ ሥራውምኮ የዕድርተኛው ጉዳይ ነው" አሉ አርጋው ፣ የእንደሻው አሽሙር ለልችታቸው ለመሔድ ቸኩለው ።

"ስለ ሁሉም ነገሪ ዕድርተኛውን ማስቸገር አይገባም ። የወደደ እንደዚሁ ይርዳ ፤ ለዳሉ ሥራ የሚሆኑ ሠራተኞች መቅጠር ያስፈልገናል" አለ ከበደ ፣ አርጋውን ትክ ብሎ እየተመለከተና እነደ መቆጣትም እየከጀለው ።

"የቸገረም ቢኖር ሰሞኑን ተመካከሩበት ። የተረፈውንም ያው እሑድ እንነጋገርበታለን" አሉ መምሬ ።

የዕለቱ ስብሰባ በዚሁ አበቃና ፣ እነደ ተለመደው ሽማግሌ ዎቹ ሁለት ሁለት እየሆኑ ወደየቤታቸው ሲያዘግሙ ፣ የአቶ አርጋው የቤት ሠራተኛም መነሣታቸውን ሲጠባበቅ ነበርና ፣ ወደ ግራሩዋ ሔዶ ወንበሮቹን ወደ ቤት መውሰድ ጀመረ ።

"እንዲያው ሠፈራችን ከሚያሳፍር ነገር ላይ ወደቀ" አለና የፃ አለቃ ከበደ ጨዋታ ጀመረ ፣ ከአቶ እንደሻው ጋር ጉን ለጉን እየተጨዋወቱ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ።

"ሠፈሩ ምን ይዋረዳል ?" አሉ እንደሻው ፣ ቆም ብለው ሠፈራቸውን በጉጉት እየተመለከቱ ። "እነርሱው በተዋረዱ ሠፈሩ ምን ይሆናል ? እንዲያውም በተደባደቡና በለየላቸው ።"

"እነዚህኞቹማ ቢምን የተነሣ ሊደባደቡ ይችላሉ ብለው ነው ! ሁለቱን የምታገናኝ ሴት የለች" አለ ከበደ ፣ ርምጃውን እየቆጠረ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሴት ባያገኙ ፣ በገንዘብ ሳያጋደሉ ይቀራሉ ብለህ ነው?"

"በገንዘብ እንዴት ይጣላሉ ብለው ነው?" አለ ከበደ ።

"የአድባሩ ርስትና ቤት ገንዘብ ስብሳቢ ወኪል እርጋው ነው ። እየቆነጣጠበ ፣ እየሰረቀ ቤቶች እየሠራ ማከራየት ጀምሮ ዋል ። ከሠርጉ መዋጮ ደግሞ ሁለትና ሦስት ቤት የሚሠራበት ይሰርቃል ። ታዲያ ጌታው የነቃበት እንደሆነ ጉሮሮውን ነው የሚ ያንቀው ። መቸም ይህ እንደሚደርስ አትጠራጠር ፣ ከዚያ በኋላ ሠፈሩም ባይሆን ዕድሩ ነጻ ሆኖ ፣ እንደ ሌሎች ዕድሮች ራሱን ችሎ ሊተዳደር ይችል ነበር ። እንዲያው ለዚህ ባበቃቸው እንጂ ፣ ነገሩስ አይከፋም ነበር" አሉ እንደሻው ፣ ቁጭትና ጉጉት እየተናነቁዋቸው ።

"እውነትዎን ነው ፣ መቸም እንድ ቀን አይቀርም ። በተ ለይ ደግሞ ሴት ከገባች በኋላ ቁጥጥሩን ራስዋ መያዟ አይቀር ምና..."

"እም! ከዚያ በኋላማ አርጋውም 'መጥባት የለመደ ጥጃ ሲይ ዙት ያጓራል' እንደ ተባለው ይሆናል ።"

"ለመሆኑ ፣ እስከዛሬ ለሠርጉ መደገሻ ምን ያህል ገንዘብ ተዋጣ?" አለ የፃ አለቃ ከበደ ።

"እንግዲህ አርጋው ነው የሚያውቀው ። እኛ ተምነን ለታል ። እርሱ እየዞረ ይቀበላል ። ተዚያ የፈለገውን ያህል ቀንጫጭቦ የተረፈውን ይሰጣል ። ተቆጣጣሪ የለበት ! ማን ያውቃል?" ኦሉ እንደሻው ።

"እንዴ! ዕድርተኛው ያዋጣውንኮ እኛም ማወቅና ለሰው ዱው ማስታወቅ አለብን ። ያለዚያማ መና መቅረቱ ነው"አለ የፃ አለቃ ፣ ቆጣ ብሎ ።

"ገንዘቡኮ ምን ጊዜም መና የቀረ ነው ። ከአድባሩ እጅ ገብቶ ሠርግ ቢደገስበትም ፣ ከአርጋው ኪስ ቢገባም ያው መና

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው ። ለሰውዬው ቢነገር ፣ ባይነገር ከቁም ነገሪ እይቈጥሩትም ። ምን አለፋን ? ለልማት ሥራ ፣ ለሠፈሩ ነዋሪ ጥቅም የሚውል ቢሆን የተዋጣውን መቈጣጠር በተገባን ነበር ። ባለርስቶችና ወኪል ለሚቀራመቱት ገንዘብ ምን ያደክመናል ብለህ ነው ?''

ከለሚ ጀምሮ አርጋው ሥራ በዝቶባቸው ሰንበተ ። አጣና፣ ቆርቆሮ ፣ ምስማር ፣ ገመድ እና ሌላም ለዳሱ ሥራ የሚያስፈል ገውን ዕቃ ሁሉ እያስገዙ በልጅ አድባሩ ግቢ ሲያከማቹ ሰን በቱ ። ከሠፈሩ ነዋሪዎችም እየተመረጡ ለቁፋሮ ፣ ለሸክም ፣ ለጠባቂነትና ለመሳለሉት ሥራዎች ተመደቡ ። ገሚስ ከፍለው ገሚስ ከቀረባቸውም እየዙሩ መቀበሉ አድከሚቸው ነበር ። በአገር ቤት በኩልም መዋጮው እንዲፋጠንና ገንዘቡ እንዲላክ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ልከው ነበርና ፣ ሽሀሮችና ሠንጋዎች መግባት ጀምረዋል ። ከልጅ አድባሩ ቤት በውጭ በኩል ጊዜያዊ ማረፊያ ተሠርቶላቸዋል ። የሠፈሩ ነዋሪ ከነበሩት ሴቶ ችም እንደዚሁ እየተመረጡ ለድፍርስ ፣ ለፊልተር ጠላ ፣ ለመና ኛና ለማለፊያ ጠጅ ሥራ ፣ ለቀይና ለአልጫ ወጥ ፣ ለጥቁርና ለነጭ ጤፍ እንጀራ እየተመደቡ ሥራቸውን ያጣድፋሉ ።በክ ትማና በገጠር የሚኖረው የአድባሩ ቤተ ዘመድ መክተት ጀመ ሩዋል ። እንደዚህ ሆኖ በተሟሟቀው የልጅ አድባሩ ሠርግ ድግስ ሰሞን ላይ የተፈጠረው የፊታውራሪ መደብደብ ደግሞ የተሟሟቀ ሹክሹክታ ፈጥሩዋል ።

'ፍል ውሃ ሲታጠቡ አዳልጧቸው ወድቀው ተኝተዋል' ተብሎ የተወራላቸውን ሽፋን ፣ የፍጡር ዱላ እየጣሰው ወጥ ቷል ። ፍጡርም ጌታቸው መሆናቸውን ባለማወቅ በሰነዘሩት ዱላ ተይዘው ጣቢያ ቆይተዋል ። ወይዘሮ ላቀችም የባላቸውን መፈንከትና የወንድማቸውን መታሰር እንዳይሰሙ ታላቅ ጥን ቃቄ ተደርጎ ስለነበረ ፣ ወደ ሠርጉ ቤት በሐዱ ቁጥር ሴቱ ሁሉ የሚጠቃቀስባቸው ጉድ ሆነው ይታዩ ነበር ። ፊታውራሪ እንደ ተደበደቡ ወደ ዘመዶቻቸው ሠፈር ሔደው ፣ 'ከፍል ውሃ ስታ ጠብ ወደቅሁ' ብለው ምክንያት ከሰጡ በኋላ ነበር ወደ ቤታቸው የገቡት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ታዲያ ትልቁ ጥሬታ ይደረግ የነበረው ወፈፌው ደባልቀው ወደ እድባሩ ቤት አካባቢ እንዳይደርስ ነበር ። በሠፈሩ ከነበሩት ሰዎች እንዳንድ ቀልደኞች ግጥም እየገጠሙ እርሱን እያስጠኑ እንደሚልኩት የታወቀ ነበርና ፣ በፊታውራሪ እርገጣቸው ላይ ስለ ደረሰው ዱብ ዕዳ እንደ ልማዳቸው ቅኔያቸውን ዘርፈው እንዳይነግሩትና ፣ ምስጢር ወጥቶ ከወይዘሮ ላቀች ጆሮ ደርሶ ሴትዮዋ ጓዛቸውን ጠቅልለው እንዳይወጡና ሠርጉ እንዳይበጠበጥ ፣ አገርም እንዳይሥቅ ጥንቃቄ ይደረግ ነበር ።

በመካከሉም ፣ አርጋው ተራቸውን ወደ ወይዘሮ ይታክቱ ቤት ጉራ ለማለት ፣ እመቺ አጋጣሚ ለማግኘት ችለው ነበር ።

ከሰኞ እስከ ዓርብ በነበሩት ቀናት ፣ እቶ አርጋው ሥራ በዝቶባቸው ይውሉና ፣ ማታ ማታ ደግሞ ሹልክ ብለው ወደ ወይዘሮ ይታክቱ ቤት ማመሻሸት ጀምረዋል ። በመጀመሪያው ቀን ፣ 'ለቁስልሽ ማድረቂያ' ብለው አንድ ብልት ሥጋ ይዘው ሔደው እመቹ ። ከዚያ በኋላ ፣ 'ያስፈልግሽ እንደሁ' እያሉ የማይወስዱት ነገር አልነበረም ። ይታክቱም በደስታ እየተቀበሉ ማስተናገድ ሥራቸው ሆነ ። ፊታውራሪም ምንም እንኳን በቤታቸው ቢተኙም ፣ ሐሳባቸውና ልቦናቸው ወይዘሮ ይታክቱ ጓዳ የሚንሳፈፍ ነበርና ፣ የይታክቱን ቤት እየቃኘ የሚነግራቸው ታማኝ መድበዋል ።

ቅዳሜ ወደ ማታ ፣ ጨለምለም ሲልላቸው ፣ 'እስቲ ከደጃዝማች ለቅሶ ደረስ ብዬ ልምጣ' ብለው ወጡ ። ያን ሰሞን፣ ወዳጃቸው የሆኑ ደጃዝማች ይጥና እናታቸውን ተረድተው ነበር ። ታዲያ ፊታውራሪ ፣ 'ታመው ተኙተዋል' ስለተ ባለላቸው ፣ ከወዳጃቸው ኃዘን ሳይደርሱ ነበር ውለው ያደሩት ። በዚያች ዕለት ማታ ራሳቸውን በሻሽ አስረው ፣ ጥቁር ቆብ ደፍተው ፣ ጋቢ ደርበው ወጡና ፣ ወደ ዘመዶቻቸው ሠፈር ሔደው ይታክቱን እንዲጠብቁላቸው አደራ ያሉትን ጉረምሳ በመኪናቸው ጭነው ይታክቱ ወደሚኖሩበት ሠፈር ሔዱና ፣ መኪናቸውን ራቅ አድርገው አቁመው ደፈጣ ጀመሩ ።

ራሳቸው ባንድ በኩል ፣ ታማኞቻቸው በሌላ በኩል እደፈጡና የይታክቱን ቤት የፊት ለፊትና የጓሮ በር ወጠሩት ። እዚያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሆነው ሲያያቡ ፣ በነጠላ ላይ ካፖርት የደረበ ፣ ቡሽ ባርኔጣ የደፋ ሰው ወደ ይታክቱ ቤት ገባና በሩ ሲዘጋ ፣ ፊታውራሪ ከነረዳታቸው ተከትለው ገቡ ።

"ንቅንቅ ትልና ትበላሻለህ" አሉ ፊታውራሪ ፣ ፊሽሌ ሽጉጣቸውን ደግነው ።

"ጌታዬ የዛሬን ! ሁለተኛ ኦኳደርስም ። ለኔም ለጌታዬም አይበጅም ፣ ይማሩኝ የዛሬን ፣ በሚያምኑት ታበት ይዝምታለሁ" ብለው አርጋው ሶመኗቸው ።

"ያዝልኝ ፣ ንሣ ያዘው!" ብለው ፊታውራሪ እንዳዘዙ ፣ ታማኛቸው አርጋውን ፈጠረታቸው ።

"ጌታዬ የዛሬን ለኔ ሲሉ ፣ ሁለተኛ እይለምደኝም" አሉ ይታክቱም ሊፈተለኩ በር በሩን እያዩ ።

"በል በያዝከው ገመድ እጁን እሰርልኝ ።"

የአርጋው እጆችና እግሮች ታሰሩ ። ፊታውራሪ በርግጫ በቡጢ ብለው ፣ አልጠቅም ሲላቸው ፣ በጥርስ ነክሰው ነክሰው ቁጭታቸውን ከተወጡ በኋላ ፣

"በል ፣ አንተ ደግሞ ውቀጥልኝ ፣ ቀጥቅጥልኝ" አሉና ፣ አሲዘውት በነበረው ብረት የአርጋውን ፍሬ አስቀጠቀጡት ። አርጋው ሥቃይ ሲበዛባቸው ጮኹ ።

የልባቸውን ንዴት ተወጡና ፣ ፊታውራሪና ታማኛቸው ወጥተው ሔዱ ። ወይዘሮ ይታክቱም ቅጥቅጣቸውን ታቅፈው ቀሩ ።

ያን ዕለት ፊታውራሪ ሲገላበጡ አደሩ ። እንቅልፍ ባይ ናቸው መዞሩን ጠብ እርግፍ አድርጉ ትቶታል ። 'ያ ቅጥቅጥ' ይታክቱዋቸውን ዐቅፎ ሲተኛ ይታያቸው ጀመር ። ከንጋቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት ከመኝታቸው ተነሡ ።

ወይዘሮ ላቀችም ተነሡና ፣ "እንዴ ፣ ምነው ፀሌሊት ምን መጣ" አሉዋቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ዕለቱ ሰንበት ነው ፤ የቅዳሴው ሰዓት መዳረሱ ነው ፤ ቅዳሴ ሳይገቡ ልደርስ ነዋ!" አሉ ።

"ተመስገን ፥ ዛሬስ ተመስገን ! እንኳን ልቦናውን የሰጠዎ! ታዲያ አብረን እንሒዳ ?" አሱና ላቀችም ብድግ አሉ ።

ፊታውራሪ ያልጠበቁት ዱብ ዕዳ ሆነባቸው ። ለዘወትሩ እርሳቸውም ሲረፍድ ፥ ቅዳሴጪ ሊያበቃ አቅራቢያ ነበር የሚ ሔዱት ። ወይዘሮ ላቀችም እንደዚያ ናቸው ። ሁለቱም ቢሆኑ የጥዋቱን ብርድ ይፈሩታል ፤ ቅዳሴው ሲጋመስ ነበር ቤተ ክር ስቲያን የሚታዩት ።

በዚያ ዕለት ፥ ሁለቱም ለባበሱና በመኪናቸው ቤተ ክርስ ቲያን ሔዱ ። ከንጋቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ደረሱና ፥ ወይ ዘሮ ላቀች በሴቶች በር በኩል ሲገቡ ፥ ፊታውራሪ ፥ በወንዶች በር በኩል ገብተው ለደቂቃዎች ያህል ቆይተው ወጡና ፥ መኪ ናቸውን አስነሥተው ሲያባንናቸው ወደ አደረው ቤት ሔዱ ።

ወይዘሮ ይታክቱንም ቤተ ክርስቲያን ሊሔዱ ሲለባብሱ አገ ኙዋቸውና ፥ "ወገቤን በሙቅ ውሃ ታሽኛለሽና ነይ እንሒድ" ብለው ይዘዋቸው ሔዱ ። በዚያ ዘመን በፍል ውሃ ውስጥ የን በሩት የግል መታጠቢያ ቤቶች ጥቂቶች ስለነበሩ ፥ ለመሳፍንቱና እነርሱ ለሚፈቅዱላቸው ባለሟሎች ካልሆነ በስተቀር ለማነ ኛውም ሰው የግል መታጠቢያ አይገኝም ነበር ። ፊታውራሪ 'ብርድ አሞኛል' ብለው መሰንበቻቸውን አስፈቅደው ሲመ ላለሱ ነበር ።

የልጅ አድባሩ ሠርግ ሳምንት ቀርቶታል ። የመጨረሻውን ጉዳይ በመጨረሻው ሳምንት ለመነጋገር የአድባሩ ዕድር ሽማ ግሌዎች ከረፋዱ ላይ እንደ ተለመደው ተሰቦሰቡ ። መምሬ በዕ ውቀቱ ፥ አቶ እንደሻው ፥ አቶ ይመር ፥ አቶ ቡልቻ ፥ ወደዘሮ ፈትለ ወርቅ ተገኝተዋል ።

"የሟ አለቃ እንኳን ማርፈድ ፥ እንዲሁም ሲል መቅረት ልማዱ ነው ። የዋናው ባለጉዳይ የአቶ አርጋው መቅረትስ ምን ይሉታል ?" አሉ መምሬ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"የሷ አለቃ ከበደምኮ መቅረቱ ይሻላል እንጂ፣ አርፍዶ ሲመጣ ብቻውን አይመጣም። ጉድ ይዞ ነው የሚመጣ" አሉ እንደሻው ፣ በሩቁ የሚያዩት ይመስል መንገዱን ትከ ብለው እያዩ።

"እረ በስማም ይብሉ፣ ሌላ ጉድስ አያምጣብን! ምን አድርገነው ፈጣሪያችን?" አሉ ፈትለ ወርቅ።

በመካከሉ አንድ ልጅ እግር መጣና እጅ ነሥቶ ቆመ።

"ምነው ማንን ትፈልጋለህ?" አሉት አቶ ይመር።

"ተልኬ ነው" አለ ወጣቱ።

"ማነው የላከህ?"

"ጋሼ ከበደ፣ ዛሬ አትጠብቁኝ፤ ብርቱ ሥራ ስለ አጋጠመኝ ለመምጣት አልችልም ብሏል" አለና ሔዶ።

"እርሱስ እሺ፣ ሥራ አጋጠመው። ዋናው ባለጉዳይ፣ እቶ አርጋውስ ምን ሆኑ?" አሉ መምሬ።

"እርሳቸውምኮ ይህን ሰሞን ሥራ ያጣድፋቸዋል። ሩጫው ሲል አድርጉ ይሏቸዋል" አሉ ይመር።

"ታዲያ ቁርጡን እንወቀዋ! ይመጣሉ አይመጡም? 'እመጣለሁ ጠብቁኝ፤ አልመጣም አትጠብቁኝ' ማለትምኮ ያስፈልጋል። ወይ የቅድሙን ልጅ አልሰደድነባቸው፤ ወይ አሳቸው አልላኩብን ምን ይሻላል?" አሉ እንደሻው ፣ ምርር ብለው።

"እስቲ ልጅ ልላክባቸው?" አሉና ይመር የሚልኩት ልጅ ፍለጋ ሔዱ።

"ንቀት እኮ ነው፤ ተንቀን ነው እንጅ፣ እንዴት እስካሁን ልጅ አይልኩብንም?" አሉ እንደሻው።

"ይተዉ ክፉ አይናገሩ። ባይመቻቸው ይሆናል። እንኳን የሠርግ፣ የከርስትና ድግስስ ልብ ያጠፉ የለም? ባያመች ይሆናል" አሉ መምሬም ፣ ያስታራቂነት ምክራቸውን ሲለግሱ።

"አይምሰልዎት አባቴ ንቀት ነው፤ ጥጋብ ነው። ሁላችን ንንም የሚቆጥሩን እንደ አቶ ፍጡር አድርገው ነው፤ ሁላችንም

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍጡርን መስለን ነው የምንታያቸው" አሉ እንደሻው ፣ እየተ ወራጩ ።

"አይገባም አይማረሩ ፣ ክፉም አይናገሩ ፣ ያለወትሮዎ ። ምነው ? ሥራ ባይበዛባቸውኮ አይጠፉም ነበር" አሉ መምሬ ።

"ከይታክቱ አልጋ እርገጤ ተኛቶ
ፍጡር ወቃው አሉ ድንገት ዘሎ ገብቶ"

እያለ ፣ ዘፈንና ቀረርቶ እያቀላቀለ ደባልቀው መጣ ። ሦስቱ እንገታቸውን ሲያቀረቅሩ ፣ እንደሻው እንደ መነሣትም እየቃጣ ቸው ፣

"እንዴት እንዴት አልክ ? እስቲ ድገመው" አሉት ጮክ ብለው ።

መምሬ ቀና ብለው ተመለከቱዋቸውና ፣ "እንዴ ፣ ኧረ አይ በጅም ! ምን ሆነዋል ዛሬ ? ደግሞ ብለው ብለው የዕብድ አጨ ብጫቢ ሊሆኑ ነው ?" አሉዋቸው ።

"ዕብዶትስ እኛ ! ደባልቀው ምኑ ዕብድ ነው ? ሲያልፍም አይነካው ። ለመኳንንት ሠርግ መፈንጠጥ ገንዘብ አምጡ ብለን ምድረ ድሃ የምናስለቅስ እኛ ነን እንጂ ዕብዶች" አሉ እንደ ሻው ፣ ደባልቀው ሲጠጋቸው ደግሞ ፣ "እስቲ ድገመው ፣ጥ ሙን ?" አሉት ።

"ስማ እንደሻው ፣ ፍጡር ታስሮልህ የለም ? ለምን የእር ገጤ ወኪል ለመሆን ደጅ አትጠናም ? ፍጡር መቸም አይመለስ" አለ ደባልቀው ።

"እከደ እከድዬ ! እውነትም ዐብዷልና" አሉ እንደሻው ፣ ከንፈራቸውን እየለጠጡ ።

"አርጋው የታለ ? እርሱም ከጌታው ጋር ተደብድቦ ታሰረ እንዴ ?" አለ ደባልቀው ።

"አዬ እንደ አፍህ ባደረገው !" አሉ እንደሻው ።

"ከብዬ የለችም እንዴ ? እስቲ ፈትለወርቅ ፣ የጠላ መጠጫ ጣይልኝ ? ዳሩ ያነች እጅ የሚፈታው ለጉሪምሶች ነው ። የጉ ሪምሳ ጥገት.." ሲል ደባልቀው ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"እሄሄ ! ዛሬስ ብሶበታል" አሉ መምሬ ፥ ፈትለ ወርቅን እየተመለከቱ ።

"እስቲ የቅድሙን ግጥም ድገመው ። ዛሬስ እኔ ነኝ የምሰጥህ" አሉና እንደሻው ብር መዘው አሳዩት ።

"ከቄስ አጠገብ አልቀርብም ፤ ቄስ አልወድም ። አምጣና ስጠኝ" አለ ደባልቀው ።

"እሄሄ ! ኧረ እባክዎ እንዳይሰድበኝ ! በሊቀ መላኩ ይሁንብዎ ፥ ይስጡትና ያባሩልኝ" አሉ መምሬ ፥ አንገታቸውን ደፍተው ፥ እንደሻውን እየተለማመጡ ።

"የዛሬው ግጥምህ ጠጅ ጭምር ያስጠጣሃል" አሉና እንደሻው ፥ የመዘዙትን ብር ወስደው ሰጡት ።

"እሄሄ ? እርስዎስ ከርሱ ምን ይሻላሉ ?" አሉ መምሬ ቀስ ብለው ።

"ለሰጭ ይስጠው ፤ ለንቀጣ ልብ ይስጠው" እያለ ደባልቀው ሲነጉድ ፥

"ለአርጋውም ልብ ይስጠው" እያሉ እንደሻው ፥ ወደ መቀመጫቸው ተመለሱ ።

ወዲያው አንዱ ዕድርተኛ ቀረብ ብለው እጅ ሲነሡ ፥ "ነዎር ነዎር !" ተባሉ ። ሰውዬው በኑሮዋቸው ጉስቁላ መሆናቸው ካለባበሳቸው ያስታውቃል ።

"ምነው ደኅና መጡ ?" አሉ እንደሻው ።

"ደኅናስ ደኅና ነኝ ። ትንሽ ጉዳይ ነበረችኝና ፥ ለአቶ አርጋው ነግሬያቸው ፥ ዛሬ ሽማግሌዎቹ ሲሰበሰቡ ብቅ በልና እናይል ሃለን ብለውኝ ነበር" አሉ ዕድርተኛው ።

"ሽማግሌዎቹማ ይኸውና ተገኝተን ነበር ። አቶ አርጋው ጉርምሰው ጠፉብን እንጂ" አሉ እንደሻው ።

"እባክዎ ይተዉ ፤ ከፉ ቃል አይናገሩ" አሉና መምሬ ፥ እንደሻውን ገላምጠው ወደ ዕድርተኛው መለስ ብለው ደግሞ ፥ "ምን ነበረ ችግርዎ ? ለኛ ሊነግሩን ይፈቅዳሉ ?" ብለው ጠየቋቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እኒያ ዕድርተኛም ጉሮሮአቸውን አለሳለሱና ፥ ዐይናቻቸውን ወዲያና ወዲህ መራውረው መለሱዋቸውና ፥

"የባለቤቴ ወንድም ከሰው ጋር ተጋጭቶ ሞተ ። ታዲያ በዕድራችን ደንብ መሠረት ሊሰጠን የሚገባውን ገንዘብ አቶ እር ጋውን ጠይቀናቸው ፥ 'የእናንተ ጉዳይ ለሽማግሌዎቹ የማሰረዳው አለኝና አንተም እንድትገኝ' ብለውኝ ነበር" አሉ ።

"ሰውዬው የሞተው እዚሁ ከሠፈራችን ነው ?" ብለው እንደሻው ጠየቁ ።

"የለም በሌላ ሠፈር ነበር ።"
"እዚሁ አዲስ አበባ ነው ?"
"አዎ ፤ እሱስ እዚሁ ነበረ ፥"
"የት ሠፈር ?"
"መርካቶ"

"ታዲያ እኛ ለምን አልሰማንም ? እለቅሶ እንድንደርስ ለምን አልነገሩንም ? ምን ያህል ጊዜ ሆኖታል ?"

"ተወር በሳይ ነው !"
"ቀብሩስ እዚሁ ነበር ?"
"አይ በአገር ቤት ነበር ።"
"ኃዘን እዚሁ ተቀምጣችሁ ነበር ?"
"እዚያው ጨርሰን ነበር የመጣነው ።"
"ታዲያ ገንዘባችሁን ለምን ከለከሉ ?"
"ብቻ ከሽማግሌዎቹ ጋር ልመካከርበት እያሉ ነው ።"

"ታዲያ አሁን እንደሚያዩት እርሳቸው የሉም ። እንግዲህ ከመጡ ሰውዬውን እንጠይቃቸዋለንና ፥ እስተዚያው እርስዎም የሚሔዱበት ካለዎት ዘወር ዘወር ብለው ይመለሱ" አሉ እንደሻው ።

"እሺ ፥ እንግዲህ እደራ" አሉና ዕድርተኛው ሲመለሱ ፥ ወይዘሮ ፈትለ ወርቅ በትዝብት አስተያየት ተመለከቱዋቸውና ፥

"ጉድ ነው ኃፍረት ማጣት" ብለው አጉረመረሙ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምነው የሰሙት ነገር አለ ? ጉዳዩን ያውቁታል ?" አሉና እንደሻው ጠየቁዋቸው ።

"እረ ጉድ ነው እቴ ! ሰዉ ይሉኝታውን ሽጦታል" አሉ ራሳቸውን እያነጋገሩ ።

"ምንድን ነው ምክንያቱ ? አልሞተባቸውም ?" አሉ እንደሻው ።

"መሞትስ ሙቶባቸዋል ፣ ግን..."

"ታዲያ ተመልሶ ተነሣ ?"

"እሚሞቱ ደሰ አይልም ።"

"ድሮስ ሰው ሲሞት ምን ደስ ይላል ?"

"አይ የዚህኛው ሌላ ነው ፣ ደስ አይልም ።"

"ወይ የሚያውቁት ነገር ካለ ይንገሩን ። ለርሱ ብቻ የተለየ መልክ ያለው ሞት አልመጣበትም" አሉ እንደሻው ።

"ሰውዬው የሞተው ከሰው ቤት ገብቶ ተገኝቶ ፣ ተደብድቦ ነው ።"

"ከሰው ሴት ላይ ተገኝቶ ነው ?" አሉ እንደሻው ።

"እረ የሱስ አሳፋሪ ነው ፣ እርሱማ የወንድ ሥራ ነበር ?" አሉ ፈትለ ወርቅ ።

"ምነው ? ከነፊታውራሪ ጋር አይመሳሰልም ?" አሉ እንደሻው ።

"ይኸኛው የተዘጋ ቤት ከፍቶ ፣ ዕቃ ተሸክሞ ሲወጣ ተገኝቶ ነው ፣ ተደብድቦ የሞተው ።"

"ታዲያ ፊታውራሪስ ሲሠርቁ አይደል የተገኙት ? ሙትው ቢሆን ኑሮ የዕድር ገንዘብ ሊከለከሉ ነበር ?" ሲሉ እንደሻው ፣

"እሄሄ ! የርስዎ ነገር ምኑን ተምን አገናኙት ?" አሉ መምሬ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሌባውን ተሌባ !"

"ይተዉ እባክዎ ፣ ክፉ አይናገሩ !"

"እሁን የተናገርኩት በመጽሐፍ ቅዱሱ ፣ በወንጌሉ ፣ በሰማኒያ አሐዱ ፣ በፍትሐ ነገሥቱ ታይቶ የሚያስነውር ከሆነ በሰማዩና በምድሩ ሕግ ልቀጣበት" አሉ እንደሻው ፣ ሽንጣቸውን ገትረው ሲሟገቱ ፣

በመካከሉ አቶ ይመር ከሐዱበት ተመለሱና ፣

"አቶ አርጋው ከቤታቸው የሉም" ብለው ተቀመጡ ።

"ከጌታው ቤት ይሆናል እንጂ ! ይህን ሰሞንማ እርሱስ መዳሩ አይደል ?" አሉ እንደሻው ።

"እዚያም የሚገኙ አይመስለኝም ። ብቻ እስቲ ወደዚያው ልጅ ልኬያለሁ" አሉ ይመር ፣ በገነገነ ስሜት ተረብሸው ።

"ምነው ? የሰሙት ነገር አለ እንዴ ?" አሉ ወይዘሮ ፈትለ ወርቅም ወደ አቶ ይመር ጠጋ ብለው ፣ በለሆሳስ አነጋገር ። ቀደም ሲል ከነበራቸው ሁናቴ የተለየ ድንጉጥኛ ነገር የተሰማቸው መሆናቸውን አይተዋል ።

"አይ እስቲ ለማንኛውም የላክሁት ልጅ ይመለስ" አሉ ይመር ፣ የሰሙት ነገር ቢኖርም በይበልጥ ማጣራት ተገቢ መሆኑን በሚያስታውቅ እኳኋን ።

"ወይም ወደ ሠርጉ ቤት እንሒድና ሥራም እየረዳን ብን ነጋገርስ ? አይሻልም ?" ብለው መምሬ ሐሳብ አቀረቡ ።

"እርሱማ የማይቀር ነው ። ድንገት የኛን ሽምግልና የሚፈልጉ እንዳሉ መጥተው እንዳያጡን ትንሽ እንጠብቅ እንደሆነ ብዬ ነው እንጂ ፣ ወደዚያው መሔዳችንማ የማይቀር ነው ። ደግሞስ አቶ አርጋው እዚያ ከሆኑ ለምን አይልኩብንም ?" አሉ እንደሻው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እዚያም የሚገኙ አይመስለኝም ። ብቻ እስቲ እንጠብቃቸው ፣" አሉ ይመር በገነገነ ስሜት ተውጠው ።

"ከቤታቸውና ከጌታቸው ቤት ከጠፉማ ወይ ወደ አገር ቤት ሔደው ገባሩን ሁሉ ሰብስበው ያንጫጫሉ ፣ ወይም ከይ ታክቱ ቤት አድፍጠው ይሆናል" አሉ እንደሻው ።

"ትላንትናኮ ወደ ማታ አይቻቸዋለሁ ። ምን ጊዜ ወደ አገር ቤት ይሔዳሉ ?" አሉ ይመር ።

"ዛሬ በሌሊት ተነሥተው ሔደውስ እንደሆነ ? ማታስ ወደ ይታክቱ ቤት ሔደው እንደሆነ ?" አሉ እንደሻው ።

"እንዴ ምነው ? ከቤትኮ ሴት አላቸው" አሉ ፈትለ ወርቅ ።

"እኒያኛቹስ አልነበራቸውምና ነው ፣ ሲሠራረቁ የተደባ ደቡት ?" አሉ እንደሻው ።

"አሄሄ ! እባክም በቃዎት ፣ ከቱ አይናገሩ !"

"እሁን የተናገርኩት ከቱ ቃል ከሆነ ፣ በመሬት ላይ ያለው ሽማግሌ ሁሉ ይፍረድብኛ !"

የላኩት ልጅ እየነሠገሠ ሲመጣ በቅርብ ርቀት ላይ አዩ ትና አቶ ይመር ወደ ርሱ ሔዱ ። ልጁም ከገሥጋሽነት ወደ ሩዋጭነት ፣ ወይም ከሁለተኛ ወደ ሦስተኛ ማርሽ ፍጥነት ጨመረና ወደ ርሳቸው ቀረበ ።

"እንዲያው ከምላሴ ጸጉር ትነቀል ፣ አርጋው ከጌታው ቤት የተገኘ እንደሆነ" አሉ እንደሻው ፣ የአቶ ይመርንና የልጁን ፍጌታ እየተመለከቱ ።

"ምናልባት ወደ ገበያምኮ ሔደው ይሆናል" አሉ ፈትለ ወርቅም ፣ በልጅ አድባሩ ቤትም ባይኖሩ ፣ ወደ ሌላ ነውር ቦታ ቢሔዱም ፣ ገመናቸውን ለመከላከል በቆረጠ ሁኔታ ።

አቶ ይመር ፣ ከልጁ ጋር ተነጋግረው ወደ ሽማግሌዎቹ ሲመለሱ ፣ ድንጋይ እደናቀፋቸውና ባፍጢማቸው ሊደፉ ሲሉ ተፍ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገምግመው ተነሡና ፣ እንደገና ተመልሰው ያን ድንጋይ ከመን ገዱ ላይ አንሥተው ለመጣል ሲታገሉ ፣

"ይተዉት ፤ በዚህ ሠፈርኮ ያለው እንቅፋት እርሱ ብቻ አይደለም ። ባለርስቶቹም ወኪሎቻቸውም እንቅፋቶች ናቸው። ካነሡ ሁሉንም ነው ማንሣት" ኦሉ እንደሻው በማባጨት ፤

"እሄሄ! እባክዎ ክፉ አይናገሩ!"

ድንጋዩ ገሚሱ መሬት የነከሰ ነበርና ፣ በቀላሉ የማይነቀል ላላቸው መሆኑን የተረዱት አቶ ይመር ሌላ ድንጋይ አንሥተው ከላዩ ላይ አስቀመጡበት ፤ በጉጉት ሲጠብቋቸው ወደ ነበሩት ሽማግሌዎች ሔዱና ፣ ከወንበራቸው ላይ ተቀምጠው ሽማግሌዎቹ ሲመለከቱዋቸው ፣ እርሳቸውም ትከ እያሉ እያዩዋቸው ቆዩና ፣

"እረ ደኅናም አይመስሉኝ ። በሠርጉም ቤት የሉም" አሉና ተነፈሱ ።

"ዳሩ እኛ ምን አስጨነቀን ? ባለጉዳዮቹ እነርሱ ናቸው ፤ ሠርገኞቹ ፣ዕድርተኛ አስገባሪዎቹ እነርሱ ናቸው ፤ እኛ እንደሆነ አራጋቢዎች ፣ አጨብጫቢዎች ነን ፤ ሲፈልጉን እንሔዳለን ፤ ሲደበቁን እንመለሳለን ። ይኸው መጥቶን ስንጉላላ ውለናል ፤ ከተደበቁበት ወጥተው ሲጠሩን እንመጣለን ፤ አሁን ወደ ቤታችን እንሒድ" አሉና እንደሻው ብድግ አሉ ።

"ዛሬስ በደኅናቸውም አልመሰለኝም" አሉ ይመር ።

"ምን ቀን ደኅና ሆነው ያውቃሉ?" አሉ እንደሻው ፣ለመሔድ እየቃጣቸው ።

"እህ? የሰሙት ነገር ካለ አይነግሩንም ?" አሉ መምሬ ።

"ማታ ከሰው ጋር ተጣልተው ነበር ፤ የት እንዳሉ ገና እላጣራንም ብሉ ልጁ ነግሮኛል ። እና" ብለው ይመር ተናግረው ሳይጨርሱ ፣ እንደሻው አቋረጧቸውና ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን ዐይነት እነጋገር ነው ? ወይ ከሰው ጋር ተጣልተው ጣቢያ ተወስደዋል ፤ ወይ ሆስፒታል ገብተዋል ፤ ወይ ከቤት ተኝተዋል ። ያለያም ሸፍተዋል ፤ ወይ ሙተዋል..."

"እባክዎ ከፉ አይናገሩ!"

እንደሻው ለመሔድ እንዳቆበቆቡ ፥ ሌሎች ደግሞ ከተቀመጡበት ሆነው እንደሻውን በመመልከት ላይ እንዳሉ ፥ የሟ አለቃን ከቅርብ ርቀት ተመለከቱና ፥

"ዛሬ ሌላ ጉድ ደግሞ ሳንሰማ እንቀርም ፤ ከበዶ ያውና ወደኛ ይገሠግሣል" አሉና እንደሻው ፥ መልሰው ተቀመጡ ።

"ማታ ከሰው ጋር ተጣልተው ሳይጐዱኮ የቀሩ አልመሰለኝም ። ብቻ አላጣራሁም እንጂ" አሉ ይመር ፥ የሰሙትን ነገር የሟ አለቃ ሳይቀድማቸው ለማውራት ዳር ዳር እያሉ ።

"እሁንማ እንግዲህ ከዋናዉ ከጐተራው ሊወጣ አይደል ፥ የደረሰባቸው ነገር ካለማ ?" አሉ መምሬ ።

"የሟ አለቃ ፥ አርፍዶ ከመጣ መቸም ጉድ አይጠፋምና እና ዳምጥ !" ኦሉ እንደሻው ። "አቶ አርጋው እንኳ ወደ ጣቢያ የሔዱም አይመስለኝ ፤ ብቻ ግን እነዲያው ለምናልባቱ..." ብለው ይመርም አጉረመረሙና ዝም አሉ ።

"ጣቢያስ ባይደርስ ፥ የአርጋውን ምስጢር ፖሊስ ፈልፍሎ ለማወቅ ምን ይቸገረዋል ?" አሉና እነደሻው የሟ አለቃን መድረስ በችኮላ አመለካከት ጠበቁት ።

የሟ አለቃ ከበዶ ፥ እፎይታና ቅሬታ የሚፈራረቁበት ገጽታ ይታይበታል ። የሠፈሩ ነዋሪዎች ፥ በሁለት ባለርስቶች ሽኩቻ መካከል ገብተው ያሳለፉዋቸው ሁኔታዎች በዚያች ዕለት ከተፈጸሙበት ድርጊቶች ጋር እየተጋጨበትና የወደፊቱም ሁኔታ እየተደበላለቀበት ገጽታውንና አረማመዱን ይቈጣጠሩበት ጀምረዋል ። የሠፈሩን ፥ በተለይም የዕድሩን መጥፎ መጥፎ ጉዳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዮች ተከላከሉ መልካሞቹን ይዞታዎች ለማቅረብና ለማዋሐድ ሲልም ፣ እጆቹን ወዲያና ወዲህ እያወራጨ ወደ ሽማግሌዎቹ ሲሔድ ፣ ትርፉንና ኪሳራውን የሚያስላ የሲራራ ነጋዴ ይመስል ነበር ።

በዕድሩና በዕድርተኞቹ ላይ የደረሱትን ውዝግቦች ፣ በምን ምክንያት እንደ ተነሡ ፣ እነማን እንደ ጀመሩዋቸውና እንደምን እያደረጉ እንደሚያብሱዋቸው እየተነተነ ለአለቆቹ ሳያስረዳ አልቀረም ነበር ። ግን እነዚያ ባለርስቶች ደግሞ ፣ ሥረ ብዙዎች ነበሩና በገዛ ርስታቸው ያፈቀዳቸውን ቢሠሩ ቀና ብሎ የሚያያቸው ባለመኖሩ፣ ''እርፈሀ ተቀመጥ'' ከሚል ምክር በቀር ያተረፈው ነገር አልነበረም ። ታዲያ አቶ እንደሻው ያጫወቱት ነገር ትዝ ሲለው ፣ ''እውነታቸውኮ ነው'' እያለ ፣ በልቡ የሠረፀውን ብቀላውን ይወጣዋል ። ''እነዚህ ባለርስቶችና ወኪሎቻቸው እያሉ ዕድሩም ሆነ ሠፈሩ ጤና የሚያድሩ አይምሰልህ'' አቶ እንደሻው በየጊዜው እያነሡ የሚጥሉት የጨዋታቸው መደምደሚያ ነበር ።

ሁለቱ ባለርስቶች ከነወኪሎቻቸው ፣ ከዚያ ሠፈር በሆነው ሁሉ ምክንያት ቢነሡለት ወይም ቢጠፉለትስ ? ዕድርተኛውን አስማምቶና አስተባብሮ በሚገባ ለማደራጀትና ለመምራት ይቻል ይሆን ? እርስ በርሱ የተነካከሰ ነዋሪ ፣ ለባለርስቶች ዝናና ደም የተፋሰሰና የተበጣበጠ ነዋሪ የነበረ ፣ ስሕተቱን እርሞ በሁለት እግሮቹ ቀጥ ብሎ ቁሞ ወደ ትክክለኛው የመረዳዳት ዓላማው ይሻገር ይሆን ?

ዕድርተኛዉ በጪለኝነቱ የውል ግዴታ ጭምር እየታነቀ ለስብሰባ ፣ ለቀብርና ለመሳሰሉት ግዴታዎች እንደሚወጣና የባለርስቶቹ ወኪሎችም የሚያዙትን ሁሉ ሳያመነታ እንደሚፈጽም የሚ አለቃ ያውቃል ። ታዲያ እነዚያ ባለርስቶችና ወኪሎቻቸው ከዚያ ሠፈር ቢነሡ ወይም ቢጠፉ ፣ ዕድርተኛዉ ሁሉ በዕድሩ ደንብ አስገዳጅነት ብቻ ይታዘዛል ? ይህንና ይህን የመሳሰሉትን ከአረማመዱ ጋር እያነጣ እየረገጠ ፣ ከግራሩዋ ሥር ተቀምጠው የእርሱን መድረስ እንደ በልግ ዝናብ በጉጉት ሲጠባበቁ ከነበሩት አዛውንቶች ዘንድ ደረሰና ፣ቀጥ ብሎ ቆሞ ፈገግታው

t.me/OLDBOOKSPDF

ንና ወታደራዊ ሰላምታውን አቀረበላቸው ። እንዴ ተለመደውም የመምሬን መስቀል ተሳለመና ፣ በመጀመሪያ ላቶ እንደሻው የእጅ ሰላምታ ሰጠ ። አጨባበጡም ጠበቅ ያለ ነበር ፣ የልብ ደስታውን በሰላምታው ለመግለጽ ብሎም ይመስላል ።

"ድንገተኛ ሥራ ተገኝቶ ወደዚያው ሔጂ ነው ያረፈድኩት፣ እኔን ነበር የምትጠብቁ?" አለና ተቀመጠ ።

"እንዳልተመቸህና ሥራ ላይ መሆንህንማ የላከኸው ልጅ ነግሮናል ። ዛሬስ የጠፋኸው እንተ ብቻም አይደለህ ! እንደ ራሴውም ጭምር ናቸው የገቡበትን ያጣነው ። ለመሆኑ ዛሬስ ዘግይተህ የመጣኸው ጉድ ቢኖር ነው?" አሉት እንደሻው ።

"የዛሬውማ ከጉድ ያለፈ ጉድ ነው ። ለመሆኑ እናንተስ እስካሁን ያልሰማችሁ ሁናችሁ ነው?" አለና ፣ ሽማግሌዎቹን እንድ ባንድ ተመለከታቸው ።

"እሄሄ! ምን ጉድ ልታሰማን ይሆን?" ኦሱና መምሬ አቀረቀሩ ።

"የምሥራችም ይሆን ይሆናል" አሉ እንደሻው ፣ ከበያን እያዩ ።

"እግዴት እስካሁን አልሰማችሁም ! እቤታቸውኮ ለቅሶ ተጀምሩዋል !"

"እማን ቤት ? ከአቶ አርጋው ቤት ?" አሉ እንደሻው ።

"የምን አርጋው ! እርሳቸው ምን ሆኑና ! ለክቶም አይሰጣቸው ። ሐኪሞችም ምንም አይሆኑም ብለዋል ። ቢበዛ ዐሥራ አምስት ቀን ቢተኙ ነው ።"

"ምንድነው ያመጣኸው ጉድ ? ደግሞ በተራቸው ሁለቱ ተደባደቡ" አሉ እንደሻው ፣ ከት ከት ብለው ሊሥቁ ቸኩለው ።

"እረ ጉዳዩ ከባድ ነው ። ሙተዋልኮ !"
"አርጋው ሞቱ?" አሉ መምሬ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"አርጋውስ ምንም አይሆኑም ፣ ተርፈዋል ። ግን እስካሁን እንዴት አልሰማችሁም ?

"ታዲያ አድባሩ ሞቱ ?" አሉ እንደሻው ።

"እሳቸውም አይደሉም ።"

"ታዲያ የሞተው ማነው ?"

"ፊታውራሪ ።"

"የኛው ፊታውራሪ ?"

"አዎ ፣ የናንተው ፊታውራሪ ።"

"ምን አገኛቸው ? ምን መዓት መጣባቸው ? ምን የጉድ ጉድ ነው የምታሰማን ?" አሉ መምሬ ።

"ምን ጉድ ነው ይኸ ?" አሉ እንደሻው ።

"እሄሄ እባክዎ ክፉ አይናገሩ ?"

"እስቲ ታሪኩን ንገረን እንጂ ፣ ከጀመርከው" አሉ እንደሻው።

"ትላንትና ማታ ፊታውራሪ ፣ ወደ ወይዘሮ ይታከቱ ቤተ ሲሔዱ ፣ አቶ አርጋውን ያገኙዋቸውና በእሽከራቸው ያስቀጠቅ ጧቸዋል ።

"እንዴ ፣ ያስቀጠቀጡዋቸው ከሴትዮዋ ፊት ነው ?" አሉና እንደሻው ጠየቁ ፡ሣቅ እየታገላቸው ።

"ይቆዩማ ! እስቲ ፍሬ ነገሩን እንስማው" አሉ መምሬ ።

የሁለቱን ንትርክ ፣ ሌሎቹም የሰለቹት መሆናቸውን በሁ ናቴያቸው መግለጽ ሲጀምሩ ፣ የግ አለቃ ንግግሩን ቀጠለ ፣

"ማታ አቶ አርጋውን ደብድበው ከሔዱ በኋላ ፣ ሲነጋጋ ደግሞ ወደ ወይዘሮ ይታከቱ ቤት ተመልሰው በመኪናቸው ጭነው ወደ ፍልውሃ ሲሮጡ ከፊት ለፊታቸው ሲመጣ ከነበረ መኪና ጋር ተጋጭተው ሞቱ ።"

"ሴትዬዋስ ?" አሉ እንደሻው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እሳቸውማ ለጉድ የፈጠራቸው አይደሉ? ተርፈዋል፣ምንም አልሆኑም ።" አለ የፃ አለቃ ።

"እንግዲህ ሠፈሩም ባይሆን ዕድሩ ነጻ ሊወጣ እንድ ቀረው" አሉ እንደሻው ።

"እሄሄ! እባክዎ ክፉ አይናገሩ" አሉ መምሬ ።

"የዛሬው የምሥራችህ አረቄ ያስጨብጣል ። በል ና እን ሒድ" አሉና እንደሻው ብድግ ሲሉ፣

"እንዴ የተሰበሰብንበቱ ጉዳይስ?" አሉ፣ ፈትለ ወርቅ ።

"እንድ ዕልባት እናድርግለት እንጂ!" አሉ መምሬም ።

"ጉሩም የሆነ ዕልባት ነው ያደረግንለት ። ከተስካሩና ከሠ ርጉ በኋላ እንቀጥላለን" አሉ እንደሻው ።

* * *

ሰኞ ጥዋት ፣ በሠፈሩ ውስጥ የሚገኙት ሁለት ዕድሮች ጥሩ ንባ እያስነፉ መርዶውን ማሰማት ጀመሩ ።

'ፊታውራሪ እርገጣቸው ዐርፈዋልና እቃብሩኝ ይላሉ ባለ ቤታቸው!' እየተባለ በፊታውራሪ ዕድር ሲለፈፍ፣ በልጅ አድ ባሩ ዕድር ደግሞ፣

'የልጅ አድባሩ እጮት ፣ ፊታውራሪ እርገጣቸው ዐርፈዋ ልና አቃብሩኝ ይላሉ!' እየተባለ ተለፈፈ ።

"አንተ አይዋ ተፈሪ ፣ እንደምን አድረሃል? ምነድነው ይኸ ቱልቱላ? ምን ኦድርጉ ነው የሚለው?" ብለው የቤቱን ባለቤት ጠየቁ፣ አንድ ጐንደሬ ለአቤቱታ መጥተው፣ ከዐረፉ በት ከዘመዳቸው ቤት በጥዋት ወጥተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊሔዱ ሲሉ ቱልቱላውን ሰምተው ።

"ፊታውራሪ እርገጣቸው የተባሉ የሠፈሩ ባለርስት ሙትው ነው" አሉዋቸው አቶ ተፈሪም ፣ ከመኝታ ክፍላቸው መጥ ተው ከሳሎኑ በር ላይ ቁመው ።

"እርበኝነታውስ በየት በየት ነበር?" አሉ ጐንደሬው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እርበኝነትስ የላቸውም ።"

"ታዲያ ቀሚሱን እንዴት አገኙት ?"

"ከጣሊያን በፊት ነበር የተሰጣቸው !"

ታዲያ ከጠላት በፊት ባለቀሚስ የሆኑ ፣ ሰው በአምስቱ ዓመት አልሠሩበትም ማለት ነው ?"

"ባገር ቤት እድፍጠው ነው አምስቱን ዓመት ያሳለፉት ።"

"ታዲያ ዱሮውን እንዴት ቀሚሱ ተሰጣቸው ?"

"እባታቸው ራስ ነበሩዋ ! በዚሁ ምክንያት ነበር ቀሚሱ የተሰጣቸው ።"

"እሀ ፣ የራስ ልጅ ሆነው ቀሚስ ለብሰው እንዴት አም ስት ዓመት ሳይዋጉ ቀሩ ? በኋላስ እንዴት ዝም ተባሉ ?" አሉ ጐንደሬው ።

"ማንም አልጠየቃቸው ፣ ምንም አልተደረጉ ።"

"እሀ ፣ ታዲያ ዛሬስ ቱልቱላ እንዲነፋላቸው እንዴት ተፈ ቀደላቸው ? ቱልቱላ የሚነፋለትኮ በጀግንነቱ ፣ በአርበኝነቱ ፣ በባለቀሚስነቱ የታወቀ ሰው ነው" አሉ ጐንደሬው ፣ ወጋ ወግ እያስታወሱ ።

"ዛሬኮ ቱልቱላውን ያስነፋላቸው ዕድር ነው ።"

"ይኸው ዕድር የሚሉትላ ማነው ?"

የጐንደሬው እንግዳ ጥያቄ ፣ ማለቂያ የሌለው የሆነባቸው የቤቱ ባለቤት አቶ ተፈሪ ስለ ዕድር ምንነት ሲያነበንቡላቸው ቆዩና ፣

"ዕድርተኛው ሁሉ ወጥቶ እንዲቀብራቸው ነው ቱልቱላ የተነፋው" አሉዋቸው ።

"እንዴት እንዴት ? ሰው ሙቷልና ውጡና ቅብሩ ተብሎ እንዴት ዐዋጅ ይነገራል ? ያውም ባለቀሚስ ፣ የፊታውራሪነትን

t.me/OLDBOOKSPDF

ያህል ቅሚስ የለበሰ ሰው፣ በዚያውም ላይ ባላባትና ባለርስት!" አሉ ጐንደሬው።

"ይኸው ነው፤ ያዲስ አበባ ደንብ ነው። ዕድርተኛ የሆነ ሰው ሲሞት፣ ሁሉም በጥሩንባ ወጥቶ ይቀብራል፤ ካልወጣም ይቀጣል" አሉ አቶ ተፈሪ፣ የዘመዳቸው ጥያቄ በዚያው እንዲ ያበቃላቸው በመመኘት።

"እቤት፣ እቤት! እንዴት ያለው አገር ነው በል? እንዴት ሰው ሲሞት በግድ ውጡና ቅበሩ ይባላል? ቡታ መንገሩ ብቻ አይበቃም? ሰውን ያህል ነገር ሲሞት በድንጋጤና በኃዘን ተወጥቶ ይለቀሳል፣ ይታዘናል፣ እንደ ማንነቱ ይቀበራል እንጂ፣ እንዴት በሮድና በቅጣት ቅበሩ ይባላል? እዩ አገር! እዩ ጉድ ምነው የኛን አገር መጥተው ባዩት" አሉ ጐንደሬው፣ እየተገረሙ።

"እየሀ አይዋ ቸኩል፣ ያዲስ አበባ ነዋሪ ከየትም የመጣ ነው። ከየአገሩ የተጠራቀመ ነው። በዚህም የተነሣ ከተማዪቱ እንደ ቀራጭ አቅማዳ ትመስላለች። ቀራጭ በገበያ እየዞረ ጥራጥሬውን፣ ጤፉን ጥጡን፣ በርበሬውን፣ በአንድ አቅማዳ አይደል የሚሰበስበው? አዲስ አበባም እንደዚያው ናት። የየአገሩን፣ የየነገዱን ተወላጅ ሁሉ ነው የሰበሰበችው። ስለዚህ ሁሉም አይዛመድም፤ አይተዋወቅም፤ አይጠያየቅም፤ ጥዋት ወጥቶ ከዋለበት ሙሉ ማታ ይገባል። ሁሉም ቤቱን ዙሪያውን አጥሮ፣ በሩን ዘግቶ ነው ለየራሱ የሚኖር። ታዲያ ሁሉም የየቅየውን፣ የየነገዱን ወግና ሥርዓት ይዞ መጥቶ፣ ለየ ሠፈሩ ያስታዋውቃል፤ በየሠፈሩ ይሠራበታል። ዕድርንም ለአዲስ አበባ ነዋሪ ያስተዋወቁ ወይም ያስለመዱ ጉራጌዎች ናቸው ይባላል። ጠቃሚ ነገር በመሆኑም ሁሉም በነሠፈሩ አቋቁሞታል" አሉ አቶ ተፈሪ፣ የመጨረሻ ማብራሪያቸው እንደሚሆን በመገመት።

"እንዲያው ለመሆኑስ እንድ ሰው በዚሁ ዕድር ነው፣ ማኅበር ባልከው ቤት ባይገባና ቢሞት ወይም ሰው ቢሞትበት፣ ቁልቁላውስ ላይነፋለት ነው?" አሉ ጐንደሬው።

t.me/OLDBOOKSPDF

"በዕደሩ ውስጥ ካልገባ ራሱም ሲሞት ፣ ከቤቱም ቢሞትበት ፣ ወይም መርዶ ቢመጣበት ማንም የሚያርስላት፣ የሚረዳው ፣ የሚያቃብረው የለም ። ጣጣውን ራሱ ይችላል እንጂ ለችግሩ የሚያርስለት ማንም አይኖርም" አሉ ።

"ጉግዠ! አዬ አገር! አዬ ወግ! እንዴት እንዲህ ይደረጋል? አዬ የከተመኛ ኑሮ! ለመሆኑ አንተሳ አለህበት ?" አሉ ጐንደሬው ፣ በዘመዳቸው ወይም ቦአርሳቸው ላይ ክፉ ነገር ድንገት ቢያርሰ ቀባሪ እንዳያጡ ሠግተው ።

"ገና ድሮ ነዋ! ዕድር ካልገባሁኮ መኖር አይቻልም ። ዕድር መግባት የአብሮ መኖር ግዴታ ነው ።"

"ለመሆኑ እኒሁ ፊታውራሪያችሁ አሟሟታቸው እንዴት ነው ? ታመው ኑረዋል ?"

"አሟሟታቸውማ ፣ ውሽማቸውን በመኪናቸው ጭነው ሲሔዱ ፣ ከመኪና ጋር ተጋጭተው ነው ይባላል" ሲሉዋቸው ፣ ጐንደሬው ራሳቸውን በሁለት እጆቻቸው ይዘው ፣

"አዬ የዘንድሮ ፊታውራሪ እንዴት ጉድ ሆኑ !! ውሽማ ይዞ ከመኪና ጋር ተጋጭተው ሲሞቱ በአዋጅ መቀበር...ጉድ ነው—የጉድ ጉድ !" አሉ..... ዐይኖቻቸውን በልጥጠው ።

ፊታውራሪ እርገጣቸው የሞቱት ፣ የልጅ አድባሩ ሠርግ የሳምንት ዕድሜ ሲቀረው ስለ ነበረ ፣ ለሠርግ የተደገሰው ለታዘን ሆነ ። የሠፈሩ ነዋሪና የገጠሩ ገበሬ አፍንጫ ተጉሮሮ እየተያዘ ያዋጣው ገንዘብ ገሚሱ ሠንጋ ተገዝቶበት ነበር ። ገሚሱንም አቶ አርጋው እንደ ታቀፉት ተቀጠቀጡና ፣ 'እኔን ደብድበው ዘርፈውታል' ብለው የቻሉትን ያህል አስቀርተውለታል ። የተገዙት ሠንጋዎች ፣ ሽሀሮችና ሙክቶች እየተቀለቡ ይቆዩና ፣ ባይሆን የፊታውራሪ መንፈቅ ከወጣ በኋላ ቤተ ዘመድ ብቻ የሚገኝበት ራት ተዘጋጅቶ የልጅ አድባሩ ጋብቻ ይፈጸማል ተብሎ ታስቦ ነበርና ፣ እንስሳቱ በደኅና ውኔታ እንዲያዙ ተደረገ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ግን ወዲያው በንጉሡ ዘንድ ሐዘን ደረሰ ስለተባለ ፣ ልጅ አድባሩ ለሠርጋቸው ያሰቡት ለቤተ መንግሥት 'እንግዳ መቀበያ' እንዲሆን ወደዚያ ተላከ ።

ከዚያ በኋላ በሁለቱ ባሶርስቶች ሠፈር የነበሩትንና ተከፋፍለው የብጥብጥና የትርምስ ምንጭ ሆነው የቆዩትን ዕድሮች ለማዋሐድ ከሁለቱ ዕድሮች የተውጣጡ ሽማግሌዎች ደግሞ ጥረት ጀመሩ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዕድሮቹን ለማዋሐድ

ሁለቱን ዕድሮች አንድ ለማድረግ ፣ ከፍተኛ ጥረት ካደረጉት የሠፈሩ ነዋሪዎች ጥቂቶቹ በዚያ ዕለት ተገኝተዋል ። ቦታውም ሰዓቱም ያው የተለመደው ነበር ። ሁለቱ ዕድሮች ተጠቃለው አንድ እንዲሆኑ ልጅ አድባሩ ፈቃደኛ ቢሆኑም ፣ የፊታውራሪ ባለቤት ወይዘሮ ላቀች ግን አልተደሰቱበትም ነበርና ፣ ነገሩ እየ ተንዛዛ በመሔዱ ፣ የመቶ አለቃ ከበደ ፣ አቶ እንደሻው ፣ አቶ ንጉሤና ሌሎችም የሁለቱ ዕድሮች አባሎች የነበሩ ጥቂቶች ስለ ተጣጣሩበት ፣ የመጀመሪያው አስታራቂ ቡድን ሊሰበሰብ ቻለ ።

የመቶ አለቃ ከበደ ለተሰበሰቡት ሽማግሌዎች ፣ "እስከ ዛሬ ድረስ እርስ በርሳችን እንደ ተወዛገብን ቆየን ። ከኛ በኋላ ዕድር ያቋቋሙ ሠፈሮች ዛሬ ከሚያስደስት ይዞታ ላይ ደርሰዋል። በርካታ ዕድሊተኛና ደጎና ተቀማጭ ገንዘብ አላቸው ። ደንባቸውን እያሻሻሉ ፣ በችግራቸው እየተረዳዱ ፣ በሠፈራቸው ልማት እየሠሩ ይገኛሉ ። የኛ ዕድር ግን በዕድሜው አንጋፋ ሆኖ በሥራው የልጅ ሥራ ነው ሲሠራየኖረው ። ከፅዋ ማኅበር ወደ ዕድር ተሸጋግሯል ከተባለ ይኸውና ዘጠኝ ዓመት ሊሞላው ነው ። ግን ይህን ሁሉ ጊዜ ያሳለፍነው በሚያሳዝን ታሪክ ነው ። ሁሉንም የምታውቁት ስለሆነ አሁን ብዘረዝረው ዋጋ የለውም ።

"ስለዚህ ዛሬ የተሰባሰብነው እስከዛሬ የቆዩትን ችግሮች እስወግደን ፣ ሁለቱን ዕድሮች አንድ አድርገን እንድንመሠርት ስለሆነ ፣ ሁላችሁም እንድታስቡበት አደራ እላለሁ" አለና ተቀመጠ ።

አቶ እንደሻውም ተነሡና ፣ "ባለርስቶቹና ወኪሎቻቸው በሴት የተነሣ ይህን ሠፈር ሲጫወቱበት መኖራቸውን ታውቃላችሁ ። ስንትና ስንት አዛውንት ያለበት ሠፈር እንዲህ ሆኖ ተበክሎ ኖረ ። መንግሥት አይቈጣጠራቸው ፣ ሽማግሌ አይመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከራቸው ፣ የነፍስ አባት አይገሥጻቸው ፣ ዕድሜ አይመክራቸው ፣ የዕድርተኛው ችግር አይሰማቸው ፣ ሕሊናቸው አይወቅሳቸው ፣ እንዲያው በዘፈቀደ የኖሩ ሰዎች ሁላችንንም ያለፈቃዳችን ፣ ያለ ሐሳባችን ፣ ያለ ውሎአችን ሊያውሉን ኖረዋል ። አሁንም እንግዲህ ፣ 'ያለፈው ቅሪና ነው ፣ የሚመጣው ምጫኛ ነው' እንዲሉ ፣ ያለፈው ዐልፏልና ለወደፊቱ መነጣጠሉ መነታረኩ ቀርቶ ፣ እንድ ዕድር ሆኖ ሌሎቹ ዕድሮች ከደረሱበት ደረጃ እንድንደርስ መጣር አለብን " አሉና ተቀመጡ ።

በዚያ ስብሰባ ከሁለቱም ዕድሮች የተውጣጡ ዐሥራ አምስት ወንዶችና ሴቶች ዕድርተኞች ተገኝተው ነበር ። እነዚያንም ዕድርተኞች ለመሰብሰብ የቻለው የመቶ አለቃ ከበደ ነበር ። በሠፈሩ ውስጥ ሴባና ወሰላታ በመቈጣጠር ረገድ በሚፈጸመው ጥበቃና ክትትል በማዕረግም እያደገ በመሔዱ ፣ በሠፈሩ ነዋሪዘንድ የሚወደድና የሚከበር ለመሆን ስለ ቻለ ፣ የመጀመሪያዉን አስታራቂ ኮሚቴ ሊሰበስብ ችሏል ።

አቶ እንደሻው በልባቸው ሲጉላላ የኖረውን ቂማቸውን በንግግር ከተወጡት በኋላ ፣ ተሰብሳቢዎቹም ተራ በተራ እየተነሡ የየልባቸውን እንዲናገሩ ጋበዙ ።

በሁለቱ እንደራሴዎች ፉክክር የተነሣ ፣ ለዕድርተኞች ሊከፈል የሚገባው ብዙ ገንዘብ መባከኑን ፣ ሁለቱ እንደራሴዎች ተቈጣጣሪ ስለሌለባቸው ፣ የዕድሩን ገንዘብ ማባከናቸውን ፣ ሴላው ቀርቶ ፣ ድንኳን ሞምር መሸጣቸውንና ዕድርተኛውን እዋጣ ብለው ሌላ ድንኳን መግዛታቸውን ፣ ሁለቱ እንደራሴዎች የዕድሩን ገንዘብ በወለድ አግድና በአራጣ ሲያበድሩት መኖራቸውን ፣ ለአድባሩ ሠርግና ለፈታውራሪ ዝክር መደገሻ እየተባለ ሠፈር ተኞቹ ያዋጡት ገንዘብ በየእንደራሴዎቹ ኪስ ገብቶ መቅረቱን እየዘረዘሩ ከሁለቱም ዕድሮች እየተነሡ የታመቀ ብሶታቸውን ተነፈሱ ።

ከብሶቱ ንግግር በኋላ ፣ የተሰብሳቢዎቹ አጠቃላይ ሐሳብ በእንድነቱ ላይ ያተኮረ ሆኖ ታይቶ ፣ ሁሉም ተደሰቶ ሳለ ፣ ከፌ ታውራሪ ዕድር ከተመረጡት ሽማግሌዎች እንደኛዉ ተነሡና ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

‘የቸገረው ዱቄት ከነፋስ ይጠጋል’ እንዲሉ ፣ እኛም መውደቂያ ብናጣ ፣ ቢቸግረን እነዚህን ባለርስቶች ተጠግተን ፣ ‘አምጡ’ ያሉንን ሁሉ እየከፈልን ኖርን ። አሁንም ከመዳፋቸው አልወጣንም ። እዚህ እንኳ እንዳንመጣ ወይዘሮ ላቀች አስጠንቅቀውናል ። ‘በገዛ ርስቴ ፣ በገዛ ዕድሬ መጠቃቀሳችሁና ዱለታችሁ ምንድን ለመሆን ነው ? ’ እያሉ ሲዝቱብን ነበር ። ራሳቸው እቶ ፍጡርም ቢሆኑ ፣ ምንም እንኳን ከሠፈሩ ዘወር ቢሉም ፣ የፊታውራሪን ቤት እንደሆነ በይበልጥ የሚያዙበት ሆነዋል ። በወዲህኛውም ዕድር ቢሆን ልጅ አድባሩ ምንም እንኳን በሹመት ወደ ሌላ ጠቅላይ ግዛት ቢዛወሩም ፣ ሁልጊዜም ከዚሁ ናቸው ፤ አልተለዩንም ። ታዲያ ከዚህ ላይ እያለን ፣ ይህን ዘንግተን ዕድሮቹን አንድ እናድርግ ብንል ይሆናል ? በዚህ ረገድስ መከራችሁበታል ?’’ ብለው ሲናገሩ ፣ ሁሉም እርስ በርሳቸው መተያየትና መጉሻሸም ጀመሩ ።

የመቶ አለቃ ከበደ ፣ ፊቱን አኮሳትሮ የሽማግሌውን እሮሮ ሲያዳምጥ ቆየና ፣ ‘‘የኛ ዕድር የእነርሱን መሬት ሊቀማ የተቋቋመ አይደለም ። በጤሰኝነታችን በገባነው ውል መሠረት ተገቢውን ኪራይ እንከፍላቸዋለን እንጂ ፣ ዕድሩንና ዕድርተኛውን ሁሉ በእሽከርነት ሊመለከቱት አይችሉም ። የወይዘሮ ላቀችን አልሰማሁም እንጂ ፣ ልጅ አድባሩ ግን ጠይቀናቸው ፣ ‘ምን ከፋኝ ? ድሮውንስ አስበበት አልነበረም ወይ ? አሁንም ተመካከሩበትና አንድ አድርጉት’ ብለውናል ። ስለዚህ የኛ ስምምነት ፣ የኛ አንድነት አስፈላጊ ስለሆነ ፣ ከእንግዲህ ወዲህ በአጉል ምክንያትና ይሉኝታ ዕድሮች ተለያይተው መቅረት የለባቸውም’’ አለና ፣ ሽማግሌዎቹን አንድ ባንድ ተመለከታቸው ።

ከዚያ በኋላ ንግግሩ በእንባት ፣ በከንፈር ፣ በእጅ ፣ በዐይንና ግንባር እንጂ በቃል አልነበረም ። በጥቅሻው ንግግርም ቢሆን የመቶ አለቃን የተቃወመ አልነበረም ። የሁሉንም ሐሳብ ከፊታቸው ላይ ካነበበ በኋላ ፣

‘‘አሁን እንግዲህ በዕድሮቹ አንድነት ሁላችንም ተስማምተናል ?’’ አለና ፣ ፊቱን ቅጭም አድርጎ ተመለከታቸው ፤ ቀጠል አድርጎም ፣ ‘‘እንግዲህ የዕድር ዳኛ ፣ ምክትል ዳኛ ፣ ጸሐፊ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ገንዘብ ያገኘ ፣ የሒሳብ ሹም ፣ ተቋጣጣሪ የሚሆኑ እንደ በፊቱ እንምረጥ ። በብዙዎቹ ዕድሮች የሚሠራው በዚህ መልክ ነውና ፣ ሐሳብ ስጠበት ” አለ ።

“አዎ ፤ ማለፊያ ነው” አሉ እንደሻው ። “አሁን እንግዲህ ለጊዜው ዕድሩ አንድ ሆኖ ማነኛውም ነገር እስቲዋሐድ ድረስ ከሁለቱም ዕድሮች ሁነኛ ሰዎች ይመረጡበት ። በዚሁ ብናደርገው አይሻልም ?”

“ይሻላል ፤ እስማማበታለሁ” አለ እርሱም ።

“እንግዲህ ከኛ በኩል መቶ አለቃ ፣ እኔ ራሴ ፣ አቶ ይመር ፣ ወይዘሮ ፈትለወርቅ አለን ። ከዚያኛው በኩል ደግሞ አምጡ” አሉ እንደሻው ።

“ከዚያም በኩል ያሉትንኮ ሁላችንም እናውቃቸዋለን አይደለም ? ስም ብጠራ ቅር ይላችኋል ?” አሉና ፣ ናመቶ አለቃ ጠየቁ ።

“ይሁን ፤ ይምረጡ ይሻላል” የሚሉ ቃላት ሰማና ፣

“እንግዲያው አቶ ንጉሤን ፣ ኦቶ ይጥናን ፣ አቶ ሽበሺን በበኩሌ መርጫቸዋለሁ ። እናንተስ አትስማሙልኝም ? ግን ከሴቶቹ አንደኛዋ ፈቃዳቸው ከሆነ አብረውን ቢሠሩ ምን ይመስላችኋል ?”

“እባክህ ከዚያ ሠፈር የምትመጣ ሴት ትቅርብን” አሉና ፣ እንደሻው አሽሟጠጡ ።

“ከእናንተም በኩል መምሬ ቢገቡ ይሻላል” አሉ አቶ ይጥና ።

“እሺ ፤ ከኛ አንድ ቄስ ፣ ከእናንተ አንዲት ሴት እናስገባለን” አለ የመቶ አለቃ ።

በጉዳዩ ላይ ሌሎቹም ሽማግሌዎች የየበኩላቸውን እስተያየት ለመሰንዘር እርስ በርሳቸው እየተያዩና ከሐሳባቸው ጋር እየዋለሉ ሳሉ ፣ ያ ነገረኛ ያ እንደ ፈለገውና እንደ ነገሩት የሚናገር ፣ በሠፈሩ ውስጥ የሆነችውን ማነኛዋንም እያነፈነፈ ፣ በየ

t.me/OLDBOOKSPDF

መሸታው ቤት እየዞረ በዘፈንና በእንጉርጉሮ የሚያስተጋባው ደባልቀው ፣ እያቅራራና እየዘፈነ ብቅ ሲል ፣ ሁሉም አንገቱን አቀረቀረ ። የመቶ አለቃ ከበደም ፣ የፈለገውን ይናገር ብሎ ነው መሰል ፣ እንደ ዱሮው ፊጥኖ ተነሥቶ አልሔደበትም ።

''እስቲ ዛሬስ በሠፈራችን ምን ተብሎ ተገጥሞ ይሆን ? እንስማዋ !'' አሉ እንደሻውም ፣ በለሆሳስ ።

''አንዱን አስተጥቅጣ ፣ አንዱን አስናብታ
ይታክቱ ዐረፈች ፣ ፍጡርን አማብታ
የፊታውራሪ ጦር የተራከተባት
የፍጡር እመቤት ይታክቱ እንደምን ናት !''

አለ ደባልቀው ፣ በቀረርቶና በዘፈን ከማራርዋ አልፍ ብሎ ፣ ይዞት የነበረውን አጠና ተያግፎ ።

''እከክ ! የዛሬውማ ይበል ይበል የሚያሰኝ ነው'' ኦሉ እንደሻው ፣ ደባልቀውን በፈገግታ እየተመለከቱ ።

''በል በቃህ ፣ ሒድልን ሥራ አለብን'' አለ የመቶ አለቃ ።

''የመቶዬ ፣ ምነው እጅሽ ራቀኝ ? እስቲ ለጠላ መጠጫዬ ጣል አድርጊብኝ ። አይዞሽ ሻምበል ትሆኛለሽ ። ያን ጊዜ ደግሞ አረቄ ትገዣለሽ ? ፈትለ ወርቅ ፣ አንችስ አድባሩንና የመቶዬን የምታ ደባድቢው መች ነው ?'' ብሎ ፣ ጉዞውን ቀጠለ ።

''ምድረ ሚረሳኝ ያግሞ ፣ ምን ሚርት ያስወሩብኛል ? ግዴለም ፤ ጠላቱቹን ዐውቄአቸዋለሁ'' አሉ ፈትለ ወርቅ ፣ እን ገታቸውን እንዳቀረቀሩ ።

''አያ ጉላ ማለት ነው'' የርሱን ነገር ሰምተው አደበሳጩ ። ያውቁት ፖለም ?'' አሉ እንደሻው ።

''እሱማ ምን ያድርግ ? የነገሩትን ነው ፡ሚለፈልፍ!''

''በሠፈራችን ውስጥ መቸስ የሰው ስም ለማጥፉት ፣ እርስ በርሳችን ለማጣላት ሆን ብለው የተሠለፉ ምቀኞች እንዳሉብን

t.me/OLDBOOKSPDF

የተረጋገጠ ነው ። ግን የየግላችንን ንጽሕና የሚያውቅ ያውቃ ዋል" አለ የመቶ አለቃ ፣ ቆጣ ቆጣ እያለ ፣ ደባልቀው የበከ ለውን ስሙን ራሱ ለማደስ ብሎ ።

"ይህን ይህንማ ችላ ማለት ነው እንጂ ፣ ሁላችንንስ ያብጠ ለጥለን የለም ? ሽረኞች እየላኩትኮ ነው ። በአንድ አንድ መስላቶች ተንኮል መበሳጨት አይገባም" አሉ ይመርም ፣ የመቶ አለቃን ለማጥናናት ብለው ።

"ግዴለም ፤ እኔ በዚህ የምበሳጭና የማዝን አይደለሁም ። ተንኮለኞቹ ግን ፣ እኛን ለማጋጨትና ዕድሩን ለመበታተን ነው ይህን ሁሉ የሚያስወሩት" አለና የመቶ አለቃ ፣ ሽማግሌዎቹን ተመለካከቶ ንግግሩን በመቀጠል ፣ "እንግዲህ የዕድሩን አዲስ ደንብ ስምኑን ማርቀቅ ስላለብን መቸ እንገናኝ ?" አለ ።

"የዕድሩ ደንብ ምን አዲስ ነገር ያስፈልገዋል ? ያነኑ በፊት የወጣውን ለምን አንሠራበትም ?" አሉ ይመር ።

"የፊተኛው ደንብማ መለወጥ ይኖርበታል" አለ መቶ አለቃ፤ "የመሬትና የቤት ኪራይ ክፍያ ጉዳይ ከዕድሩ ደንብ ውስጥ መሠ ረዝ አለበት ። ባለርስቶቹ ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ በዕድራችን ደንብ ውስጥ ያስገቡትን ግዴታ መሻር አለብን ።"

"ነውና ፤ ያለዚያማ ምኑን ዕድር ተባለ ? የባለ ሪስቶች አሽ ከሮችኮ አይደለንም ። ዕድሩም የእነርሱ በረት መሆኑ ነለበትም" አሉ እንደሻውም ።

"ጉድ ፈላ!" ለሉና እኒያ ከፊታውራሪ ዕድር ፣መጡት አቶ ይጥና ፣ ሽማግሌዎቹን ፣ በተለይም አቶ እንደሻውንና ፣መቶ አለቃን ተመለካከተው ፣ ንግግራቸውን በመቀጠል ፣ "እንዴት ነው ነገሩ ? ወይ በዕድራችን ደንብ ላይ ባለርስቶቹ የጨመሩትን ደንብ እንዲሠርዙልን ለመንግሥት እናመልክት ። ያለዚያ በሰው ርስት ላይ ሠፍረን እንዳለ ያለ ጥጋብ ያዋጣናል !" አሉ ።

"ማነኛው የመንግሥት ባለሥልጣን ነው ባለርስቶቹ የደ ነገጉትን ደንብና ውል የሚሠርዝልዎ ?" ብለው እንደሻው ጠየ ቋቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ታያዲነገ ጥዋት ከርስታችን ላይ ተነሡ ቢሉንስ ማነው የሚያስጥለን ?" ብለው መለሱላቸው ።

"እኛ ለዕድራችን እያስፈልግም ፣ አይጠቅመንም የምን" ውን ደንብ እንሠርዛለን ። በዚህ የተነሣ ከርስታችን ላይተነሡ ሲሉን ደግሞ ፣ ጉዳዩን ለመንግሥት አቅርበን እንከራከራለንለ አለ መቶ አለቃ ፣ በሕግ ላይ የነበረውን ጽኑ እምነት በሚያረጋ ግጥ አኳኋን ።

"እሁን ማን ይሙት እነርሱን እኛ እንሞግታለን ?" አሉ ከፊታውራሪ ዕድር የተመረጡት አቶ ንጉሤ ፣ "እሁን ማን ይሙት እነርሱ ከሚገቡበት እኛ እንደርሳለን ? ምንስ ፊታውራሪ ቢሞቱ የሚስትየዋ ዘመዶችና ልጅ አድባሩ የሚደፈሩ ሰዎች ናቸው ? ምናለ የሚሆን የሚሆነውን ብናደርግ ? ያለ ዐቅማችን ባንንጠራራ ምናለበት ? እነዲያው ለነገሩስ ዛሬውኑ 'ቤታችሁን አፍርሳችሁ ፣ ንዛትሁን አነሥታችሁ ከርስታችን ላይ ተነሡ' ቢሉን ማነው የሚያስጥለን ? የትኛው ባለሥልጣን ነው አቤቱታችንን የሚያዳምጠን ?"

በሽማግሌቹ መካከል የሐሳብ መዋለል ሲሰፍን በግልጽ ለመረዳት የቻሉት አቶ እንደሻው ፣ እንደ መነሻት እየቃጣቸው ፣ "ግዴለም ፣ ግዴለም ! ይህ ጉዳይ ሊያሳስበንና ሊያጨቃጭቀን አይገባም ። ባለርስቶቹንም ፣ ዐመላቸውንም ፣ ዕድርተኞቻችንንም፣ ባለሥልጣኖቻችን ንም እናውቃለን ። ደንቡ እንዳለ ይቀመጥላቸው ፣ በዚህ አንጣላም ። እኛ ሁለቱን ዕድሮች አንድ አደርገን ሥራችንን እንቀጥል ። ከእንግዲህ ወዲያ የዕድራችንን ዳኛ ፣ ጸሐፊና ገንዘብ ያዥ ከመካከለችን መርጠን ፣ የዕድሩን ሥራና ኃላፊነት ሁሉ ከባለርስቶቹ ወኪሎች ወስደን እንሠራለን ። በዕድርተኞቻችን ላይ ለሚደርሰው ችግር ገንዘብ የምንከፍለው እኛ ከሆነ ፣ የባለርስቶችን የመሬትና የቤት ኪራይ ከፈለ አልከፈለ ምንተዳችን ? ስለዚህ ተግባባን ፣ ሰይደል ? የመሬትና የቤት ኪራይ ላልከፈለ ዕድርተኛ የኃዘን ገንዘብ ከፍላትኋልና ኑ ተያዙ ፣ ተቀጡ ስንባል ፣ ያን ጊዜ ይሆናል" አሉና የመቶ አለቃን ሲመለከቱት ፣ በነጥቡ እርሱም መስማማቱን አንገቱን እየናጠ አረጋገጠላቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ብቻ በኋላ ማለቂያ ከሌለው ውዝግብ ውስጥ እንዳንገባ፣ ጢስኛ እናድናለን ብለን በራሳችን ላይ ያልታሰበ ዕዳ እንዳና መጣ ይታሰብበት" አሉ እኒያ የፊታውራሪ ሠፈር ዕድርተኛ።

"ግዴላችሁም፣ ዕድሩም እኛም ዕዳ ውስጥ አንገባም። ዕዳስ ባለርስቱ ያወጡትን ደንብ ተሸክሞ መኖር ነው። ከዚህ የበለጠ ዕዳ አይመጣብንም። የሆነ ሆኖ ግን፣ የኛ አንድነትና መፋቀር ነው ዋናው ጉዳይ። ሌላውን በኔ ላይ ጣሉት" አለ የመቶ አለቃ፣ ሰውነቱን አስቆጥቶ።

"እሀ፣ ይህ ሰው ማንን ተማምኖ ነው እንዲህ የሚደነፋው? አይዞህ ያለው ሰው ይኖረው ይሆን?" አሉና አቶ ይመር፣ ለመ ይዘሮ ፈትለወርቅ ሹክ አሉዋቸው።

"እኔ ምን ዐውቅለታለሁ? በባለርስቶቹ ላይ ብዙ ጉድ ሳይ ሰበሰብ የቀረ አልመሰለኝም። 'ባገር ቤት ርስታቸው፣ በከተማ ቦታቸው ባሠፈሩዋቸው ገባሮችና ጢሰኞች ላይ፣ የፈጸሙትን በደል ሁሉ ልቅም አድርጌ ይገባለሁ' እያለ ሲፎክር ነበር" ብለው ፈትለ ወርቅም ሹክ አሉዋቸው መልሰው።

"እንደኔ እንደኔ" አሉ አቶ ይጥና። "ደንቡን ሳትነካኩ ሌላ ሌላውን ሥራ ብትሠሩ ይሻል ይመስለኛል። ደንቡን ለማሻሻል ከመድከማችሁና ባለርስቶቹን ከማስቆጣታችሁ በፊት ግን ዕድርተኛውን ብትጠይቁ ይበጃል። ባለ ርስቶቹ የደነገጉበት ደንብ 'ይሠረዝ' ይል እንደሆነ፣ ወይም 'የለም እንዳለ ይቆይ' ይል እንደ ሆነ ቢጠየቅና ከዚያ በኋላ ብትሠሩ አይሻልም?"

"አሁን ማ ይሙት እነፊታውራሪ ያወጡትን ደንብ ብንሠ ርዝ ዕድርተኛው 'ቀንበሬን ለምን አነሣችሁ፣ ልጓሜን ለምን ፈታችሁ' ብሎ ቅር ይሠኛል ብለው ያስባሉ?" አለና የመቶ አለቃ፣ የታችኛውን ከንፈሩን ይነካከሰው ጀመር።

"ቢሆንም ሕዝብ እንደ ልጅ የሚሆንበት ጊዜ አለ" አሉ ይጥና። "'አቆላምጡኝ፣ ለምኑኝ፣ አትንኩኝ፣ ስጡኝ' ይላልና 'ሐሳብህንና ፈቃድህን ንገረን' ሲሉት ደስ ይለዋል። ስለዚህ፣ ደንቡን እንድናሻሽል ፍቀዱልን ብሎ መጠየቅ አያስነውርም።

t.me/OLDBOOKSPDF

ለነገሩማ ገና ዕድርተኛዉ ተሰብስቦ የዕድሩን ተጠሪዎች ሊመርጥ እይደለም ?''

የአቶ ይጥናን ሐሳብ ካንጠራጠሱ ፥ ነገሩ እንደ ሚበላሽባቸው አቶ እንደሻው ተገነዘቡት ። ይጥና በዕድርተኛዉ ዘንድ የታወቁና ተሰሚነት ያላቸው ናቸው ። ቤቶች ያከራያሉ ፥ መሸታ ያስነግዳሉ ፥ አራጣም ያበድራሉ ይባላሉ ፤ በአማጭነትና በእፋችነትም የታወቁ ናቸው ። ታዲያ በዚህ ምክንያት የሠፈሩ ነዋሪ ዕድርተኛ ቀርቶ ፥ ያካባቢው ሠፈር ዕድርተኞችም ያውቋቸዋል ፤ ቃላቸው ተቀባይነት አለው ።

''ግዴለህም ፤ ይህን ሰው እንዳልክ ይሁንልህ እንበለው ። ያለዚያ ጉድ ይሠራናል'' አሉና እንደሻው ፥ ለመቶ አለቃ ሹክ አሉት ።

''የሠፈሩን ሽረኛና አዋሻኪ ሁሉ እያባበልን እንዴት እንገፋዋለን ? ይዞ መቀፍደድ ነበር ይህን...'' አለ የመቶ አለቃ ከበደ ፥ ከሹክሹክታ ላቅ ባለ አነጋገር ።

''ግዴለህም ፤ እሺ እንበለው ፤ በኋላ የምናደርገውን እናደርጋለን'' አሉ እንደሻው ፥ የመቶ አለቃን ጉሸም አድርገው ፥ እንፈራጠ ረግጦበት የነበረውን ጉልበቱን ጫን ጫን አድርገው ።

''እውነትዎን ነው ፤ ማለፊያ አነጋገር ነው'' አሉ እንደሻው ፥ ''እንግዲህ እናንተም የሠፈራችሁን ዕድርተኛ ሰብስቡ ፤ እኛም እንሰበስባለን ። በዚያን ጊዜ ሐሳባችንን ገልጸን የዕድር ተኛውን ሐሳብ እንጠይቃለን ። ታዲያ ስብሰባው ለመቼ ይሁን ?''

አቶ ይጥና ፥ የቀኝ እጃቸዉን ጣቶችና ከንፈራቸዉን አስ ተባብረው ሲያሰሉ ቆይና ፥ ከዚያች ዕለት ማግሥት ጀምሮ የሚቀጥሉት ቀናት አዝለውት የሚመጡትን ጣጣ ተራ በተራ እያነጻጸሩ ፥

''እንግዲህ መቸም ሰሞኑን የገና በዓል ነው ። ከዚያ ጥምቀት ነው ። ብኛ ዕድር ውስጥም የአንድ ዕድርተኛችን

t.me/OLDBOOKSPDF

የዐርባ ቀን መታሰቢያ አለብን ። ቀጥሎም የፌታውራሪ ተዝ ካር አለ። እንግዲህ እንዲህ እንዲህ እያለ ወደ ሁለቱ ወር መሔዱ ነው ። ከዚያ ወዲህ የሚመችም አይመስለኝም'' አሉ ።

ፈመቶ አለቃ ቀልጥፎ ቀበል አደረገና ፣ ''የገናዉና የጥም ቀቱ በዓላት እንኳ ፣ እሺ ይሁን ። ከዚያ በኋላ የተዝካሩ ጋጋ ታስ ምን ይሉታል ? በዚህ ምክንያት ዕድሮቹ እንደዚሁ እንደ ዋለሉና እንደ ተነጣጠሉ ሊቀሩ ነው ? ምናለ ከጥዋቱ ጀም ረን እስከ አምስትና ስድስት ሰዓት ተሰብስበን ከዚያ በኋላ ወደ ተስካሩ ብንሔድ ?'' አለና ፣ ሁሉንም ጠየቀ ።

''እስከ ዛሬ ቆይተን የለም ? ምናልባት ከእንግዲህ ወዲያኮ ለአንድና ለሁለት ወራት ብንቆይ ምን ያጣድፈናል ? እስተ ዚያው እናንተም ለየዕድርተኞቹ አሰረዱ ፣ እኛም እናሰረዳለን'' አሉ ይጥና ።

''በተዝካር ምክንያት ደግሞ ፣ ሁለት ወር ልንጓተት ነው ?'' አለ መቶ አለቃ ።

''ሁተዝካሩ ድግስኮ ዕድርተኞቹም ተካፋዮች ናቸው ። ታዲያ ማን ፣ ልንሰበሰብ ነው ?'' አሉት ይጥና ።

''ግዴለም ፣ በዚህም እንስማማለን ፣ አይጐዳም'' አሉ እን ደሻው ፣ ኮመቶ አለቃን ጉልበት መታ መታ አድርገው ።

''የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል' እንዲሉ ፣ እስተዛሬ ቆይ ተናል ። ከእንግዲህ ወዲያም ወርና ሁለት ወር መታገሥ ሩቅ አይሆንብንምና ፣ በዚሁ እንስማማበት'' ብለው እንደሻው ፣ ንግግ ራቸውን ሊቀጥሉ ሲሉ ፣

''ወተቱ እንኳ ቅቤ የሚወጣው ተገፍቶ ፣ ተንጠ ነው ፤ ካልተገፋ በቀር ወተት ቅቤ አይወጣውም ። ዕድርተኞችም የእስተዛሬው ግፍ ይበቃቸዋል ብለን ነበር ፤ ግን ገና መገፋት ሊኖርባቸው ነው'' ብሎ መቶ አለቃ እጉረመረመ ።

ምንም እንኳ መቶ አለቃ ከበደ ባይደሰትበትም ፣ በእቶ ይጥና ሐሳብ መሠረት የሁለቱ ዕድሮች አባላት ከበዓላቱና ከተ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዝካራቱ በኋላ እነዲሰበሰቡ ፣ አስተዚያው ድረስ ሽማግሌዎቹ በተቻለ መጠን እየተገናኙ እንዲመካከሩ ፣ ሐሳብ ለሐሳብ እንዲ ለዋወጡ ተስማምተው እቶ ይጥና እየሣቁ ፣ መቶ አለቃ ቆሽቱ እያረረ ከግራኙዋ ሥር ተነሥተው ወደየቤታቸው አመሩ ።

"እየሀ ወዳጄ !" አሉ አቶ እንደሻው ፣ ከመቶ አለቃ ከበደ ጋር ጐን ለጐን እየተራመዱ ፣ "የሠፈሪችን ነዋሪ ዐይነቱ የበዛ ነው ፣ የተሰበሰበውም ከየአቅጣጫው ነው ። ሼዌው ፣ ጐን ዬሬዉ ፣ ጐጃሚዉ ፣ ወሎዬዉ ፣ ትግሬዉ ፣ ወለጌዉ ፣ ጊሚራዉ ሐረርጌዉ ፣ ከፈዉ ፣ ከምባቲዉ ፣ ጉራጌዉ... " ምኑ ቅጡ ! ሞልቷል ። ከየዐይነቱ ነው ፣ መጣውና ታዲያ መልኩም ጠባዩም የተለያየ ፣ የተነጣጠለ ነው ። አንዱ እናልማ ሲል ፣ አንዱ እና ጥፋ የሚለውም ስለዚህ ነው ። መቸም አላዋቂነት ፣ ያለ መሠልጠን ነው ፣ በራሱም ላይ ሆነ በጐረቤት ላይ ጉዳት የሚ ያመጣው ። በትዕግሥት ፣ በልበ ሠፊነት መያዝ ነው ። የፊታውራሪ ዕድርተኞች ያን ያህል የተሻገቱትም ካለመረዳታቸው የተነሣ ነውና ለሠፈሩ ልማት ካሰብን ፣ ሁሉንም በትዕግሥት መቀበሉ ነው ፍሬ ነገሩ ። ግዴለህም ፣ አትናደድ ፣ የሚያሰቸኩለን ደግሞ ምንም ነገር የለም ። ታዲያ ወደ ቤት ገባ ብለህ ቅራሪ ብጤ ኦተ ጠጣም ?" ኦሉት ።

"እንዲያው የዕድራችን ዕድል ግን ያሳዝናል ። የምናዋ ጣው ገንዘብ የሚውልበት አይታወቅ ፣ ዕድርተኛዉ በደንቡ መሠረት የሚገባውን የኃዘን ክፍያ አያገኝ ። አሁን ደግሞ 'እን ድነት እንመሥርት ፣ አንድ እንሁን ፣ እንተባበር ፣ ዕድራችን ይጠፋ!' ስንል ይኸ ሁሉ ሙግትና ንትርክ እያናድድም ?" ኦለ የመቶ አለቃ ።

"አትናደድ ፣ አይሆንም ። ከተበሳጨህና ከተናደድክማ ቶሎ ትረታለህ ። ግዴለህም ፣ ቀስ እያልን ሁሉንም እናስተካክለዋለን ። ታዲያ ወደ ቤት ገባ ብለህ አትወጣም ?" አሉት ደገሙና ፣ ቅራ ሪያቸውን አብረው ሊጐነጩ ቸኩለው ።

"የለም ፣ የለም ፣ እሔዳለሁ ። ለቅሶ አለብኝ" አለ የመቶ አለቃ ፣ ሰዓቴን እያየ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"የት ነው ለቅሶው ?"
"ወደ ቀጨኔ አካባቢ ነው ።"
"ምነው ዘመድ ሙቶህ ነው ?"
"የጓደኛችን ልጅ ሙቶ ፣ ቀብሩ በስድስት ሰዓት ነው ።"
"ታሞበት ኑሯል ?"
"ከቤት የነበረ ካቲካላ ጠጥቶ ነው ።"
"እዬዬ ! ምንኛ ተገመደ! ትልቅ ኑሮዋል ?"
"ሕፃን ነው ። አራት ዓመት ቢሆነው ነው ።"

"ምናለ እንደዚህ የመሳሰለውን አደገኛ ነገር ፣ ልጅ ከማ ይደርስበት ቦታ ቢያስቀምጡት ! እሁንለትም ከዚያ ማዶ ሠፈር ሁለት ሕፃናት ከተከፈተ ጉድጓድ ገብተው ሞቱ ሲባል ሰም ቻለሁ ፤ እንዲያው ሰዉ ማዬለሽ ሆነ ኮ ! በላ እንግዲህ ፣ በኒ ዚም ከተመለስክ እቤት ነኝና ብቅ በል ። ሁሉንም ቀስ እያልን እንጨዋወተዋለን" አሉትና ተለያዩ ።

* * *

በዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ ፣ ከፊታውራሪ ዕድር የተመ ረጡት ሽማግሌዎች በጥዋቱ ስብሰባ ስለ ሆነው ነገር ለወይዘሮ ላቀች ነገሩ ። ፊታውራሪ ከሞቱበት ዕለት ጀምሮ እስከዚያ ዕለት ድረስ ዕድሩን በዳኝነትና በገንዘብ ያገዙበት ሲመሩት የነበሩትም ራሳቸው ወይዘሮ ላቀች ነበሩ ። የምክትል ዳኝነቱንና የጸሐፊነቱን ሥራ ግን ፣ እያቀያየሩ ሲሾሙበትና ሲሽሩበት ቆይተው ነበር ። አንድ ሰሞን አቶ ይጥና ፣ አንድ ሰሞን አቶ ንጉሤ ፣ አንድ ሰሞን አቶ ሽበሺ ፣ እንዲሁም አቶ ቡልቻ እየተለ ዋወጡ ተሹመዋል ። በዚያ ወቅት ግን ተረኛው ምክትል ዳኛ አቶ ይጥና ነበሩ ።

"አዩ ፣ እመቤቴ ! ነገሩን ደርሰንበታል" አሉ ይጥና ፣ በዕ ለቱ ስለ ተደረገው ስብሰባ ለወይዘሮ ላቀች ሲያስረዱ ፣ "ጌቶ ችም ሲፈሩትና ሲጠራጠሩት የነበረ ጉዳይ ነው ዛሬ እ'ደገና ያገረሸው ። በነገሩ ልጅ አድባሩም ሳይኖሩበት የሚቀሩ አይመስ ለኝም ። እርሳቸው ባያውቁትና ባይስማሙበት ኑሮ ፣ መቶ አለ ቃዉና እንደሻው ያን ያህል ባልደነፉም ነበር" ብለው በማጎ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶር አጭቀውት የነበረውን ወረቀት አውጥተው እንደ ማገላበጥ እያደረጉ ንግግራቸውን ገታ አደረጉ ።

"እኮ ፍሬ ነገሩሳ ምንድን ነው ?" ብለው ወይዘሮ ላቀች ጠየቁ ።

"እንደሻውና መቶ አለቃ ፣ የኛንም ዕድር ጭምር ጠቅልለን እንውሰደው እንዘገበት ብለው ተነሥተዋል" አሉና ፣ ሲመለከቱት የነበረውን ማጎደር አስቀመጡት ።

"'ያላረፈ እግር ጉድጓድ ይገባል' የሚባለው ተረት በእኔ ነርሱ ላይ መድረሱ ነው ። እንዴት ነው ይሀን ያስመኛቸው ? ማን አይሂችሁ ቢላቸው ነው ?" አሉ ወይዘሮ ላቀች ።

"ልጅ አድባሩ ናቸዋ !" ብለው መለሱ ይጥና ።

"እንኳን ዐወቅሁት ። ያስ መቶ አለቃዉ ግዴለም ፤ ኩፍ ኩፍ ይበል ፤ በአለቆቹ ተማምኖ ይሆናል ። ያስ እንደሻው የሚሉት ልበ-ገጣባ ምን ልሁን ? የት ልድረስ ብሎ ነው ? ዐርፎ መቀመጥ አቃተው ? ጥጋብ አልቻለው አለ ? ዳሩ ምን ያድርግ እሱ ? ከጌታው ከጣሊያን ያጋፈፈው ብር ነው እንዲህ ያጠገበው ። ዐርፎ ቢቀመጥ ይሻለዋል ። እኔ ላቀች እንደርሱ ላለ ሞሽላቃ ሌባ ቀርቶ ፣ ከደፈሩኝ ፣ ከመጡብኝ ለሌላውም አልመለስ ። ግለፊያ ነው ፤ ግዴለም ። እንኳን ነገራችሁኝ ! ለመሆኑ እናንተስ ዝም አላችኋቸው ?"

"እኛማ ልክ ልካቸውን ነግረናቸዋል ። የኛ ዕድር በነርሱ ዕድር ውስጥ ሊዋጥ እንደማይችል በሚገባ ተከራክረናል" አሉ ይጥና ።

"ግዴለም ! ወንድሜ ባጠገቤ ባይኖርክ ነው እንጂ ፣ ፍጡር ባጠገቤ ቢኖር ኑሮ ፣ ምድረ ምናምንቴ እንደዚህ አይቀናጣብኝም ነበር" አሉና ፣ ከንፈራቸውን ነክሰው አንገታቸውን ነቀነቁ ።

"እሳቸውስ ቢሆኑ ከልጅ አድባሩ ጋር መነጋገር ይችላሉ ? አሁንም የሚሻለው ከእርሳቸው ጋር እርስዎ ቢነጋገሩበት ነው"

t.me/OLDBOOKSPDF

እሱ ይጥና ፣ ድንገት ፍጡር የተመለሱ እንደሆነ በምክትል ዳኛ ነቱ የነበራቸው ሥልጣን እንይዳወስድባቸው አስቀድመው ሲከ ላከሱ ።

"ምን ብሎ ነው ከእርሱ ጋር የሚነጋገረው ?"

"ዕድሮቹ ፣ እስተዛሬ በቆዩበት እንዲናሩ እንጂ ፣ ይቀላ ቀሉ ተብሎ ደግሞ ሌላ ጣጣ እንዳይመጣ ነዋ ! ያለዚያ እኮ ዕድ ርተኛውን ውስጥ ውስጡን ሰብከው ፣ 'አንድ ሆነናል' አሠኝተ ው ሊወስዱት ነው ። በእነርሱ ሥር ከሆነ ደግሞ ፣ የቤትና የመሬት ኪራይ እስከዛሬ እነደ ነበረው መሰብሰቡ ሊያስቸግር ነው" አሉ ይጥና ትክዝ ብለው ።

"ግዴለም ፤ የማደርገውን ዐውቃለሁ ። እንኳን ነገራችሁኝ እንጂ ሁሏንም እሠራላታለሁ ። በሉ ለማንኛውም ቢሆን ዕድር ተኛው እንዳይሰበክ ፣ እንዳይታለል እናንተም በርቱበት ፤ እኔም የማደርገውን አደርጋለሁ" ብለው አሰናበቱዋቸው ።

ዕድርተኞቹ ፣ ከእጃቸው ከወጡ የየወሩ የዕድር መዋ ጮ የቤት ኪራይ ገቢ እንደ ልብ እንደማይሰበሰብላቸው ፣ ቀጥሎም ለታላላቅ ሰዎችና ሹሞች የሚሸጥ ይሆናል" ብለው ፊታው ውራሪ ከልክለው ያስከብሩት ቦታ ተከራካሪ ሊነሣበት ታያ ቸው ። ተከታትሎም የገጠሩን ርስት ሲያጡ ተሰማቸው ። ከዚያ በኋላ የእርሳቸው ኑሮ በጨለማ ውስጥ ሲገባ ታወቃቸው ።

ምንም እንኳን ፣ ፊታውራሪ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ እም ነው የተቀበሉዋቸው ሁለት ልጆች ቢኖሩም ፣ ፊታውራሪ ከሞቱ በኋላ ደግሞ ከሦስት ሴቶች የተወለዱ ሦስት ልጆች ብቅ ብለው ሀብትና ርስት ይገባናል ፤ አካፍሉን ቢሉም ቅሉ ፣ በተራፊው ሀብትና ርስት የተዋጣለት ቀምጣላ ኑሮ ሊኖሩ እንደሚችሉ አም ነውበት ፣ "ከዚህ የባሰ አታምጣ !" እያሉ መጽናናት ጀምረው ነበር ።

የዕድር ገንዘብ ያዢነታቸው እንኳ ብዙም ወጭ ስላልነበ ረበት ጥቅም የሚሰጣቸው ነበር ። እርግጥ ነው ፣ ፊታውራሪ ከሞቱ በኋላ በዕድሩ ውስጥ የሞቱና የተረዱ ዕድርተኞች ነበሩ ። ግን በደንባቸው መሠረት ድንኳንና ዕቃ እንጂ ፣ ገንዘብ ያገ ኙት ሦስት የሚሆኑት ብቻ ነበሩ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እቶ ፍጡር ከሠፈሩ ቢለቁም ቅሉ ፣ ከእኅታቸው ቤት አል ጠፉም ነበርና ፣ 'የርስትና የቤት ኪራይሽን ለመከፈላቸው ፣ በእርግጥ ደግሞ የሩቅ ዘመድ የሞተባቸው ለመሆኑ ሳይጣራ አትክፈይ' እያሉ ሲያማክሩ ስለ ነበር ፣ ወይዘሮ ላቀችም በቤ ታቸው ሁልጊዜ ስለማይገኙና በሚገኙበትም ሰዓት 'ከእንግዳ ጋር ናቸው ፣ እሚቸው ተኝተዋል' ስለሚባልላቸው ፣ ዕድርተ ኞቹ መመላለሱን እየሰለቹ ፣ አንዳንዶቹም ከኃዘኑተኛ ሴት ገን ዘብ መጠየቁን እየጠሉ ፣ የኃዘን ገንዘባቸውን ሳይቀበሉ ይቀ ራሉ ። ይሁን እንጂ ፣ የቦታና የቤት ኪራያቸውን ፣ የዕድር መዋ ጮአቸውን ቀጥ ብለው ነበር የሚከፍሉት ። ምክንያት እየ ፈጠሩ መክፈሉን ቢያቋርጡ ፣ በገቡት ውል መሠረት የዕቁብ አባልነታቸውና የጢሰኛነት ግዴታቸው ከባሰ ዕዳ ላይ እንደሚ ጥላቸው ስለሚያውቁና ስለሚፈሩትም ነበር ። ከዚህ ሌላ ደግሞ ፣ አንዳንዶቹ ዕድርተኞች የፊታውራሪና የወይዘሮ ላቀች ወዳጆች ስለነበሩ ፣ ይህነኑ በማሰብ ተገቢውን ክፍያ በወቅቱ ይከፍላሉ ።

ወይዘሮ ላቀች ፣ ከመጀመሪያ ባላቸው አንድ ፣ ከፊታውራሪ አንድ ልጅ የወለዱ ፣ ገና ከአፍለኛው የዕድሜ ክልል ብዙም ርቀው ያልሔዱ ነበሩ ። የባላቸውን የሙት ዓመት ካወጡ በኋላ እኩያቸውን አግብተው ገና የተቀማጠለ ኑሮ ይመኛሉ ። እንደ ፊታውራሪ ያለ ዘቅዝቆ የሚያያቸውን ሳይሆን ፣ የሚሽቆጠቆ ጥላቸው ፣ ያለዚያ ደግሞ ፣ በእኩልነት የሚያያቸው የትዳር ጓደኛ ፈላጊነታቸው እየጐላ መታየት ጀምሯል ። ባላቸው ከእርሳቸው ሌላ ሴት ወደው ፣ በስተርጅና ሲያብዱና ሲቀናጡ ነው የሞቱት ። ታዲያ ይህ ትዝ ትዝ ስለሚላቸው ፣ ፈጥነው ባል በማግባት ቁጭታቸውን ሊወጡት ነበር የሚቸኩሉት ።

የዕድሩ ሁኔታ ደግሞ ወደዚሁ መንገድ በፍጥነት የሚገ ፋፋቸው ሆነ ። አንድ ማስፈራሪያ ወንድ ካልያዙ በቀር ዕድ ርተኞችም ፣ ቤቶች የተከራዩትም ከመዳፋቸው መውጣታቸው ሆነ ። ከዚያ ጥቃት የሚታደግ ወንድ በአስቸኳይ አስፈላጊ ሆነ ። ያን አስገምግሞ የመጣ ጥቃት ከፍጡር ጋር ብቻ ሊወጡት እንደ ማይችሉ አመኑበት ። ታዲያ ተከራካሪ ፣ አስፈራሪ ፣ አስከባሪና ተቆጣጣሪ ወንድ ፣ ሲሆን ከቤቱ የሚያስገባቸው ፣ ያለዚያ በዕ ቁባትነትም ቢሆን የሚጠብቃቸው ወንድ አስፈለጋቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ካንተ ሌላ በጐኔ የሚቆም እገሌ የሚባል ወንድ ቢኖ ረኝኮ ይህ ሁሉ ድፍረት አይቃጣም ነበር" አሉ ወይዘሮ ላቀች፣ ከፍጡር ጋር ሲጫወቱ ።

"እንች ፈቃድሽ ከሆነ ፣ እንች በይሉንታ የማትታሰሪ ከሆነ ምን ጠፍቶ ? እንዳንች ያለ የተሟላለት ሴት ተፈልጐስ የት ይገኛል ? ይህማ በእውነት ላንችም ፣ ለልጆችሽም ፣ ለን ብረትሽም ፣ ለሁላችንም አስበሻል ማለት ነበር ። የፊታውራሪ ሙት ዓመት ከወጣ በኋላ ፣ እኩያሽን ብትይዢ ምንድን ነው ነውሩ? እንዲያውም 'ሰው ምን ይለናል' ብለን ነው እንጂ ፣ እንደ ፊታ ውራሪ ኦድራጐትማ ቢሆን ኑሮ ከግልስቱ ፣ ግፋ ቢል ከመን ፈቁ በኋላ ብታገቢ ምን ነውር ነበረበት ? ከሌላ ሴት ጋር ሲማግጡ ለሞቱ ሰው ማዘንስ ፣ ሀብትና ርስት ለልጆቻቸው ለማካፈል መስማማትስ መች ይገባሽ ነበር ? አሁንም እንደሆነ—" ብለው ንግግራቸውን ሳይገቱ ላቀች አቋረጧቸው።

"አነሀ ፍጡር ! እሳቸው ከሌላ ሴት ጋር ሲቀብጡ ቢሞ ቱም ፣ መርፌና ክር ሆነውኮ አልተያዙም ። አስቀድመን ተከ ታትለናቸው ቢሆን ኑሮ ፣ ካንተ ጋር የተደባደባችሁ ዕለት ነበር በፖሊስ ማስያዝ ። ነገሩንኮ ከሕግ ዐዋቂ ጋር መከራበት ነበር ፤ ታውቀው የለም ? የማያዋጣ ስለሆነኮ ነው የተውኩት ። ከሴት ዮዋ ጋር በመኪና ሲሔዱ እንጂ ተጋጭተው የሞቱት ፣ ተኝ ተውኮ አይደለምና በሕጉ በኩል አወዛጋቢ ነው ። ደግሞስ ሰው ምን ይላል ? ዘረ ብዙ ናቸውና ከዚያ ሁሉ ዘመድ አዝማድ ጋር መቀያየም አይገባም ብለውኝ ነው ነገሩን ችላ ያልኩት ። ሁሉ ንስ ያው ታውቀው የለም ?" አሉ ።

"እኔኮ ያልኩት እንዲያው በሕሊና በኩል ማለቴ እንጂ ፣ በሕግ ረገድማ አይሆንም ። በሕሊና ፍርድ ከሆነ ግን ፣ ተበድ ለሻልና አንችም የፈለገሽን ወንድ ብትይዢ አያስወቅስሽም ፤ አይፈረድብሽም ማለቴ ነው ። አሁንም ጥሩ አስበሻል ፤ ግፊበት ። ያለዚያ አድባሩን ያህል ከባድ ሰው ብቻሽን አትችይውም ። መሬትሽና ቦታሽ ሳይደፈር ዕወቂበት ። ደግሞስ ገና ልጅ ነሽ ፤ ምኑ ነው የሚያሳፍረው ? እንኳን አንች ገና ሁለት የወለድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሽው ፣ ስምንትና ዐሥር የወለዱትስ እየተሞሸሩ ያገቡ የለም ? እንግዲህ ከኔ የቀረበ ካለሽ ደግሞ ምከሪበት ። እንደኔ ግን ፣ ተከብሮ የሚያስከብርሽን ፣ ተፈርቶ የሚያስፈራሽን ፣ ሀብትሽንና ርስትሽን የሚያስጠብቅልሽን እኩያሽን ንግቢ ፣ ወይም ያገር ፣ ከዚህ የተሻለ ምንም ነገር የለም'' አሉና ፍጡር ፣ የመጨረሻ ምክራቸውን ሰጡ ።

''ነገሩን በኔ ላይ ብቻ ጥለህ ዘወር ማለትኮ አይደለም ። የሚሆነኝን ፣ ንብረቱንና ርስቴን ብቻ ሳይሆን እኔን የሚጠብቀኝን ፣ የሚያስከብረኝንና የሚንከባከበኝን መርጠህ ፣ 'ይህ ይሻላል' ካላልከኝ ፣ እኔ ገበያ ወጥቼ አልሸምተው ? ያደባባይ ሴት አይደለሁም ። እንደ ሌሎቹ ሴቶች አይደለሁም ። እጎትህ ከትት ያልኩ ፣ ያለ ባለቤቴ ሌላ ሰው የማውቅ አይደለሁም ። አንተው የሚሆነኝንና የሚገባኝን መች አጣኸው ? እኔ ብከበር የምትከበሩት ዘመዶቼ ናችሁ ፣ ብዋረድም ውርደቴ ውርደታችሁ ነው ። ሀብቴ ሀብታችሁ ፣ ድህነቴ ድህነታችሁ ነውና አስብበት ። ከሆነ ላይቀር ደግሞ ጊዜ መፍጀት የለብንም''አሉ ላቀች፡ ከአፍለኛነት ዕልፍ ያለው ዕድሜያቸው የጠየቀውን ወንድ ለማግኘት ጓጉተው ።

''እኔማ መቸስ ፣ እስከ ዛሬ ሳላስብበት ቀረሁ ብለሽ ነው ? እንችን መጠየቁን ፈርቸሽ ነው እንጂ ?'' አሉ ፍጡር ።

''አስቀድመህ ካስብክበትማ ከእንግዲህ ወዲህ ብዙም አትቸገርበት ፣ ያሰብከው ሰውም ይኖርሃል'' አሉና ፣ ላቀች ፈገግ አሉ ።

''እርሱማ የት ይጠፋል ? ሚስቱ የሞተችበት ፣ የተፋታ ፣ ገና ያላገባ ፣ ስንቱ ሞልቷል መሰለሽ ?'' አሉ ፍጡርም ፣ ሣቅ ሣቅ እያሉ ።

''አይ ! ሚስቱ የሞተችበትስ ጣጣው ብዙ ነው ። ልጆች ይኖሩታል ፣ ወይም ይወዳት ኑሮ ይሆናል ። ወዮም ከዘመዶቹ ጋር ሌላ ጣጣ ይኖርበት ይሆናል ። እንዲያውም ገዱም ራሱ እኔ እንጂ ፣ ያላገባውም ደግሞ መቅኖ ቢስ ነው ። ሲንዘላዘል

t.me/OLDBOOKSPDF

የኖረ ፣ በዋለበት የሚያድር ፣ ዲቃላ በዲቃላ የሆነ ፣ ንብረት የሌለው ፣ ገና ያልተፈተነ ነውና ያስቸግራል ። ፈቱ እንኳን አይከፋም ። የተፋታበት ምክንያት ግን መታወቅ ይኖርባታል ። በቅናት ፣ ልጅ ባለመውለድ ፣ ገንዘብ በማባከን ፣ በሴትነት ሙያ አለመቻል ባልና ሚስት ይፋታሉ ። እኔ እጎትህ ያጣሞ ትዳር አከባሪ ፣ እግዚአብሔርን ፈሪ ነኝ ። ፊታውራሪ ያነ ያህል ሲማ ግጡብኝ እያየሁ እንዳላየሁ ፣ ሰምቼ እንዳልሰማሁ ነበር የቻልኳቸው ። በመውለዱም ሆነ በሀብቱ በኩልም ቢሆን የምታየውና የምታውቀው ጉዳይ ነው ። ስለዚህ ፈቱ ከተገኘና ምክንያቱ ከታወቀ እርሱ ይሻላል'' አሉ ወይዘሮ ላቀች ፣ እየተሽኮረመሙና ስሜታቸው ተነሣሥቶ 'አሁን አሁን' እያለባቸው ።

''እንዲያው ለነገሩ አልኩሽ እንጂ ፣ አንችኮ አማረጠሽ ፣ ተለምነሽ የምታገቢ እንጂ ፣ ማንም አስገድዶሽና አታሎሽ ከቤትሽ የምትወጭ አይደለሽም ። በመላው አዲስ አበባ ካለው ሕዝብ ራስሽ ለመምረጥ የምትችይ ነሽ ። በዕድሜሽ ገና አበባ ነሽ ። በመልክሽ ከዚህ ቀረሽ የማትባይ ፣ በራስሽም ሆነ በልጆችሽ ሀብት አገር ማስተዳደር የምትችይ ነሽ ። እንዳንች ያለች ሴትኮ በከተማው ውስጥ ብርቅ ናት ፤ አትግኝም ። ስለዚህ መርጠሽ እንጂ ተመርጠሽ አይደለም የምታገቢው'' ብለው ፍጡር ሲናገሩ ፣ ወይዘሮ ላቀችም ከሁሉም በላይ እየሣቁ ፣ እየበለጡ ፣ እየናሩ ሲሔዱ ተሰማቸው ።

''እኔ እንግዲህ መቸስ'' አሉ ላቀች እየተሽኮረመሙ ፣ የወንድ ሠራዊት በእንሜዳ ጥቅጥቅ ብሎ ተሠልፎ ፣ ለመምረጥ ተለምነው እየተጓደዱ ሲሔዱ በምኞት እየታያቸው ። ''እኔ እንግዲህ መቸም ፣ ሁሉንም ነገር ነግሬሃለሁ ። እኔ መቸም መምረጡን አላውቅበትም ፤ ባንተው ላይ ጥየዋለሁ ። 'ለእጎቴ ፣ ለክብሩዋ ፣ ለውበቷ ፣ ለንብረቷ ይኸ ይሻላታል' የምትለውን ምረጥልኝ እንጂ ፣ እኔማ እኔ አይደለሁ ? የምታውቀኝ አይደለሁ ?''

''ግዴለሽም እንግዲህ ፣ ለኔ ተይው'' አሉና ፍጡር ቀጠል አድርገው ደግሞ ፣ ''መኪና ፣ መንዳቴንስ ትምህርት ፣ ተውሽው ወይስ ገፍተሽበታል ?'' ብለው ጠየቁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ስውዬው መች የሚጠመድ ሆነ ? እንዳየኸው ፣ ሲያመ ቸው ሲያመቸው ብቅ ይልና ፣ 'ይህን ጨብጭ፣ ይህን እርገጭ' እያለ ሲያደከመኝ ውሎ ፣ 'ነገና ተነገ ወዲያ እመጣለሁ' ብሎ ፣ ሒሳቡን ይዞ ውልቅ ይላል ። በዚያው ጠፍቶ ከርሞ ደግሞ ብቅ ይላል ። ደግሞ ! ፍጡራ አይ ያለው ጣጣ ! እግሩና ውሃ አይተዋወቁም ። ግማቱ እንዳንድ ቀንማ ሊያስታውከኝ ሲል ፣ 'ጠብቀኝ መጣሁ ፣ ውሃ ልጠጣ' ብየው እቤት እገባና ፣ ሽቶ በመሐረም ዘፍዝፌ እመለሳለሁ ። አያድርስብህ ! እንዲያውም ከባልየው በፊት ፣ ንጽሕናውን የሚጠብቅ አስዘዋሪ ፈልግልኝ እባክህ ?" አሉ ምርር ብለው ።

"እንኳን የነገርሽኝ ። የኔ ጐረቤት የሆነ አገር ግዛት የሚ ሠራ ማለፊያ ሾፌር አለ ፣ አመጣውና እሱ ያስተምርሻል ። በጣም የተመሰገነ ሹፌር ነው ። ሹማምንቶቹ ወደ ውጭ ሲወጡ እሱን ካልያዙ ንቅንቅ አይሉም ። የታወቀና የተመሰገነ ሾፌር ነው ።"

"ነገሩስ ባልከፋ ። ከሥራው ጋር ይመቸዋል ?"

"አይ ምንም አይደል ። ቅዳሜና እሑድ ሁለት ሁለት ሰዓት ቢያስተምርሽ በቂ ነው ። ደግሞም ዋናው ሥራው ሹማምንቱ ወደ ውጭ ሲሔዱ ይዞ መሔድ ስለሆነ ፣ ከተማው ውስጥ ሥራ አይበዛበትምና ፣ ግድ የለሽም ፤ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊያስተም ርሽ ይችላል ።"

"በል እንግዲህ ቶሎ አምጣልኝ ። መኪና እቤት ተገትሮ ፣ እኔ እቤት ታሥራ ፣ ዐይን ዐይኑን እያየሁ ዕድሜዬን ልገ ፋው ?" አሉ እየቆጫቸው ።

"ምነው ሾፌሩን አባረርሽው እንዴ ?"

"ቢባረር ይሻላል ። ጥጋቡኮ ቅጥ ያጣ ነው ። ጥዋት ተነ ሥቶ ፣ ከዋለበት ውሎ ፣ ማታ ብቅ ይላል ። ደግሞ የሚናገ ረው ንግግር ደም ያስቀምጣል ። የርሱን ነገር ተወኝ ! ልጆቼማ እንደ ሚነግሩኝ ፣ 'ሌላ ሥራም ይዟል' ብለውኛል ። በፊት ድንገት ተነሥቶ ፣ ሳይሰናበተኝ ጠፍቶ ፣ ሦስት ወር ሙሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከኖረበት ኑሮ መጣ ። ያው ሁላችሁም ሃያ ሃያ ! ብላችሁ ገባ ። ከዚያ ወዲህማ ተወኝ ። የሚሠራው ሥራ ተወርቶም ማለቂያ የለው ። በወር ቢበዛ ቢበዛ ዐሥር ቀን ያህል ነው የሚያገለግ ለኝ ። እኔ የርሱን ጥጋብ ሰንቱን ችየው ? ብቻ ይህንኑ አስተማሪ ቱሱ አምጣልኝ ።''

''ሲሆን ሲሆን ዛሬ ፣ ያለዚያ ነገ ወዲ ማታ ይገርው እመ ጣለሁ'' ብለው ፍጡር ሊሔዱ ተነሡ ።

''በል እስቲ ፣ ሰው ሆኜ ከሰዎች ጋር እኩል እንድሆንልህ ሁሉንም ጉዳይ በርታበት'' አሉ ላቀች ።

''ግዴለሽም ሁሉንም በኔ ጣይው ። በአጭር ጊዜ ነው መኪ ናሽን ይዘሽ ፈልሰስ እምትይው ። ያ ፊታውራሪን ያስተማራ ቸው አቶ ረዳ ቢኖርኮ ፣ ይሀን ጊዜ መኪናሽን ራስሽ ይዘሽ ጉዳይሽን ሁሉ ራስሽ ታከናውኚ ነበር ። አሁንም ግዴለም'' ብለው ፍጡር ወጡ ።

* * *

አቶ ሽዋንግዛው በራሳቸው የትውልድ ሐረግ ፣ በጊዜው ቀስመውትም በነበረው ትምህርት ተደጋግፈው ከዋና ዲሬክ ተርነት ማዕረግ ላይ ከደረሱ በኋላ ፣ የሁለት ልጆቻቸው እናት የሆነችውንና የመጀመሪያ ሚስታቸውን ፈትተው ፣ በዘመኑ እጅግ ተፈላጊ የነበረውን የከፍተኛ ቤተሰብ ተወላጅነት ያላትን ፣ የዘ መኑን ትምህርት እፍታ እፍታውን ፉት ፉት ያለችውን ፣ እንደ እርሷው ከታወቁ ቤተሰቦች አብራክ የተገኙትን ወጣቶች ስታ ደባድብ የነበረችውን ፣ ወጣቶች የትልቅ ቤተሰብ ተወላጅ በመ ሆኑዋ ፣ የዘር ሐረግ ብጤዎቿም በጠባዩዋና በሁለንተናዋ የተ ነሣ ፣ ለሠርግና ለፓርቲ አጃቢነት እንጂ ፣ ለትዳር ማንም የማይ ፈልጋትን አስቴርን ባገቡ በስድስት ወራቸው ከምክትል ሚኒ ስትርነት ደረጃ ላይ ወጡ ። ከዚያ አክታትሎም ያምስት ቦርዶች አባል ሆኑ ። የየቦርዱ ስብሰባ በተካሔደ ቁጥር ከሁለት መቶ ሃምሳ እስከ ሦስት መቶ ብር ያገኙ ስለ ነበረ ፣ ከወላጆቻቸው ከወ

t.me/OLDBOOKSPDF

ረሱት የገጠርና የከተማ ርስት ጋር ፣ እነዲሁም ከአስቴር ወላጆች ላመተዳደሪያ ከተሰጣቸው የገጠር ጋሻ መሬትና የቤት ኪራይ ጋር ተደምሮ የወር ገቢያቸውን አናረው ። እና ከተሟላለት ኑሮ ላይ ወጡ ። በእኗኗራቸውም ለሰውና ለፈጣሪያቸው ነግረው የናጠጡ ሆኑ ።

የአስቴር ወላጆች ፣ በልጃቸው ማጋጣነት ና ቁም—ቀርነት እጅግ አፍረውና አዝነው ቤተ መንግሥቱ በትዕዛዝ ላንዱ ታማኝ እንዲድርላቸው ደጅ ጥናት በጀመሩበት ወቅት ፣ አቶ ሸዋንግዛው ከአንድ ሠርግ ቤት አግኝተዋት አብረው ሲጠቃቀሱና ሲጐራረሱ ውለው ፣ ማታም ተቃቅፈው ሲደንሱ ካመሹና አብረውም ካደሩ በኋላ ተጣጣሙና ሲጠቃለሉ ፣ የያስ ደሱን በእጥፍ አድርገው ከፈሉ ። ወዲያውም የደጅ ጥናቱን መሥመር ይለውጡና ፣ ለአማቻቸው የማዕረግ ዕድገት ሲሉ ወዳጅ ዘመድ መጣጠን ጀመሩ ። ልፋታቸው ተቆጥሮላቸው አማቻቸውን ለምክትል ሚኒስትርነት ደረጃ አደረሱ ። ምክትል ሚኒስትሩም ሚስታቸውን ለወፍራም ደመወዝ ሥራ አበቁ ።

ዳሩ ግን ፡ በሸዋንግዛውና በአስቴር መካከል መተማመን የሚባል ነገር ከቢታቸው ቀርቶ ፣ ከውጭው በር እንኳን አልደፈስ እያለ በየበኩላቸው መደፋፋጥ ጀመሩ ። በየቢሮአቸው ምክንያት እየፈጠሩ ስልክ ይደዋወላሉ ። ሸዋንግዛው "ለቦርድ ስብሰባ ሔደዋል" ከተባለም ፣ አስቴር "ስብሰባ አለ" ወደ ተባለበት መሥሪያ ቤት ስልክ ደውላ ብቻ ሳይሆን ፣ መኪናቸውን አይታ ማረጋገጥ አለባት ። ሸዋንግዛው ወደ አስቴር ቢሮ ስልክ ደውሎ ካጡዋት፡ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኛና ማኅደር ሁሉ ትርምስ ምሱ ይወጣል ። ሁለቱ ሲገናኙ ግን ስለ ጥርጣሬያቸው አይነጋገሩም ። 'የት ሔደህ ነበር ?' የሚሉ ነገር ከአስቴር አንደበት ወጥቶ አያውቅም ። "በዚህ ሰዓት ስልክ ደውዬ አጣሁሽ ፣ የት ነበርሽ ?" የሚል ቃልም ሸዋንግዛው ተንፍሰው የት ሊገቡ!

እንዲህ ሲሉ እንዲህ ሲሉ ፣ ሲጠባበቁ ሲጠባበቁ ፣ ሲደፋፈጡ ፣ ሲጠማመዱ ሲጠማመዱ ፣ ሲጠላለፉ ሲጠላለፉ ፣ አንድ ዕለት ከዘጠኝ ሰዓት በኋላ ፣ ሸዋንግዛውንም አንዷ በአቶሞቢሏ ጭና ፣ አስቴርንም አንዱ የቆዩ የከንፈር ወዳጅዋ የነበረ ባለትዳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ርና ባለታላቅ ሹመት ጭኗት ሲጋልቡ፣ መንገድ አስተላላፊው ፖሊስ ይገታቸውና፣ ጐን ለጐን መቆም፣ መቸም የስበት ኃይል አለውና ሁለቱም ከየጐናቸው ወደ ቆመው መኪና ዘወር ዘወር ሲሉ፣ ዐይን ለዐይን ግጥምጥም!!

በዚያ ዕለት፣ ሁለቱም ወደጋራ ቤታቸው አልገቡም፣ በማ ግሥቱም አልደረሱም፣ በሣልስቱም በአካባቢው አልታዩም። አስቴር የደረሰባትን በደል፣ የተፈጸመባትን የግፍ ሥራ ለወላ ጅዎቿ እንባዋን እያጕረፈች መናገር። ወዲያው ጉዳዩ ወደቤተ መንግሥት መተላለፍ። ከዚያ ፍች መከተል። አቶ ሸዋንግዛ ውም የምክትል ሚኒስትርነቱ ደረጃ እንደ ተጠበቀና ወደፊት ግን፣ ዕድገት እንዳይጨምሩ ሆኖ በአገር ግዛት ሚኒስቴር በክፍል ሹም ሥራ እንዲመደቡ ተዛወሩና የሠራተኛ ማስተዳደሪያ ሹም ሆኑ። ታዲያ በማዘጋጆች ላይ "ሸዋንግዛው ድፋባቸው፣ በም/ሚኒስትር ማዕረግ የሠራተኛ ጉዳይ ሹም" እያሉ ስለሚፈርሙ ፈርማቸው ክብደት ነበረው።

* * *

አቶ ፍጡር፣ ጐረቤታቸው የሆኑትን አቶ ገብረሥላሴን ከወይዘሮ ላቀች ዘንድ ወስደው ካስተዋወቁና ካዋዋሉ በኋላ፣ ላቀች የመኪና መንዳት ትምህርቱን ቀጠሉ። በግቢያቸው ውስጥ በራሳቸው መኪና የሚያደርጉትን ልምምድ ካጠናቀቁ በኋላ፣ በከተማው ውስጥ እነዴት እንደሚነዳ ለማሳየት ሲሉ ገብረሥላሴ ወይዘሮ ላቀችንና መኪናቸውን እየያዙ መውጣት ጀመሩ። በሳምንት ሁለት ቀን ከሰዓት በኋላ ከሥራቸው እየወጡ ወደ ወይዘሮ ላቀች ቤት በመሔድ ማስተማሩን ይዘዋል።

ከዕለታት አንድ ቀን፣ ለዘመዳቸው ሠርግ እንዲያድሉ የተ ሰጣቸውን ኑጥሪ ወረቀት ከሚነዱት የመሥሪያ ቤት መኪና ውስጥ ረስተው ኑሮ፣ ወይዘሮ ላቀችን በመኪናቸው እንደ ጫኑ እግረ መንገዳቸውን ወደ መ/ቤቱ ይገባሉ። ሰዓቱም ከዐሥራ ሁለት ሰዓት ጥቂት ዐለፍ ብሎ ነበር። የጥሪውን ወረቀት ከሚ ነዱት የመሥሪያ ቤት መኪና ውስጥ አውጥተው፣ ሾፌርነት ወደ ሚያስተምሩበት መኪና ሲሔዱ፣ አቶ ሸዋንግዛው ከቢሮአቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

ወጥተው ባለጉዳዮች ሲያነጋግሩ ቆይተው ከመኪናቸው ሊገቡ ሲሉ ፡ ፊት ለፊት ይገናኙና ፡ ገብረ ሥላሴ እጅ ነሥተው ፡እጅ በው ፡ በር ከፍተው ሸዋንግዛውን ከመኪናቸው አስገብተው ይመለሳሉ ። ሸዋንግዛው ግን ፡ ባለጉዳዮች እያነጋገሩ ወይዘሮ ላቀችንና መኪናቸውን እያነጣጠሩ ሲቃኙዋቸው ነበርና ፡ ከላቁ ጋር የዐይን ጠርነት ገጥመው ነበር ።

"ምንድን ናቸው እኒህ ሰው ?" አሉ ላቀች ፡ ገብረሥላሴ ከመኪናው ገብተው ሞተር ሲያስነሡ ፡ የላቁም የስሜት ሞተር አብሮ እየተነሣ ።

"ትልቅ ባለሥልጣን ናቸው" ኦሉ ገብረሥላሴ ።
"ሹመታቸው ምን የሚሉት ነው ?"
"ምክትል ናቸው ።"
"የማን ምክትል?"
"የሚኒስትሩ ።"
"እንዴ ! ትልቅ ሰው ናቸዋ !"
"እንዴታ !"
"ደግሞ ያለመኩራታቸውን ያዝልኝ ።"
"እንዴት ዐወቁ ?"

"እህ! እያየኋቸው ? ባርኔጣቸውን አንሥተው ፡ እጅ ነሥ ተው ፡ እጃቸውን ዘርግተው ላንተ ሰላምታ ሲሰጡህ እያየሁ ? ዛሬ ጊዜ የሚኒስቴር ምክትል የሆነ ሰው ይህን ያህል ትሕትናና ሰላምተኛነት የሚገርም አይደለም ? ሌሎቹንማ እያየናቸው ፡ መሬት ለመርገጥ ሲጠየፉ ?" አሉ ወይዘሮ ላቀች ! ሸዋንግዛው ከመኪናቸው ከመግባታቸው በፊት እርሳቸውንም ገርምመዋ ቸው ሲያልፉ የደነገጠውን ልባቸውን እየታዘቡት ።

"አዩ እመቤቴ ! እርስዎ በሰላምታው ነው የሚደነቁት ? አዩ ፍርድ ዐዋቂነታቸው ! አዩ ቸርነታቸው ! ተነግሮ ተወስቶ አያልቅምኮ" አሉ ገብረሥላሴ ።

"ነውና ! ያለ አንድ ምክንያት ከእንዲህ ያለ ታላቅ ሹመትና አደራ የደረሱ ይመስልሃል ? ተመርጠውኮ ነው ። ለመሆኑስ ማን ይባላሉ ?"

"አቶ ሸዋንግዛው ይባላሉ ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ወይ ግሩም! ስም ከጠባይ መስማማቱ" ብለው እንገታ ቸውን ሲወረውሩ ቆዩና፣ "የማን ዘር መሆናቸው ነው?" ብለው ጠየቁ።

"በእባታቸው የቢትወደድ ኃይሉ፣ በእናታቸው የራስ ሚካ ኤል ዘር ናቸው ሲባል ሰምቻለሁ።"

"ቢሆን ነው እንጂ! ያለ አንድ ምክንያት ከዚህ ታላቅ እደራ ላይ ይቀመጣሉ?" አሉና ላቀች፣ ቀጠል አደርገውም፣ "መቸም ባለትዳር ይሆናሉ። ባለቤታቸውስ የማን ዘር መሆናቸው ነው?" አሉ፣ የምሥራች ወይም መርዶ ለመስማት ቸኩለው።

"ለጊዜው እንኳን——" ብለው ገብረ ሥላሴ ተናግረው ሳይ ጨርሱ፣ በርከት ያሉ በጐች እየተንጋጉ ከመኪናው መንገድ ገቡባቸውና፣ እነርሱን ለማዳን ሲታገሉ እንደኖውን በግ ገጭ ተው ጣሉትና፣ ከመኪናው ሁለቱም ወጥተው ሁለቱም ከባለ በጉ ጋር ሙግት ገጠሙ። ወዲያው በጉ መንፈራፈር ሲጀምር፣ ገብረ ሥላሴ ወይዘሮ ላቀችን ከመኪናቸው አስገብተው፣ ከመን ገዱ ዳር ወደ ነበሩት ቤቶች ሩጠው ሔዱና፣ ካራ ተውሰው በጉን፣ 'መቸም አይድን' አሉና ባረኩት። ወዲያውም ባለበ ጉን እያሰፈራሩ፣ 'ትፈልግ እንደሁ አምስት ብር ልስጥህ እሜቴ ሳይሰሙ፣ እና ልውሰደው። ያለዚያ የታላቅ ባለሥልጣን መኪና አስገጭተህ ጉድ ይፈላብሃል' አሉት።

ያ ከአገር ቤት የመጣ ባለበግም፣ በነገሩ ተስማማና ብሩን ተቀብሎ ሲሔድ፣ ገብረ ሥላሴም በጋቸውን ከመኪናው ኋላ ጭነው ጉዞ ሲጀምሩ፣ ከግጭቱ በፊት ጀምረውት የነበረው ጨዋታ የወይዘሮ ላቀችን ልብ እንዲ ሰቀለው ቆይቶ ኑሮ፣

"ደንቃራ የሆነ ሰው! የቁም ነገር ጨዋታችንነኩ እደናቀ ፈው። በጀ፣ ታዲያ ባለቤታቸውስ የነማን ልጅ መሆናቸው ነው?" ብለው፣ ተንጠልጥሎ የቆየውን ጨዋታ ወደ ልባቸው ለማስገባት እንደገና ጀመሩት።

"አይ፣ እመቤቴ!" አሉ ገብረ ሥላሴ፣ እቅጩዋን ተናግረው የወይዘሮ ላቀችን ልብ እንዳያሳርፉት፣ በይበልጥ ለማንጠልጠል ብለው ነገር ሲያራዝሙ፣ "አዬ እመቤቴ! ሴቶቹ ሁሉ እንደርስም ትዳራቸውንና ቤታቸውን አክባሪ አይደሉም። አንዳንዶቹ ሴቶች

t.me/OLDBOOKSPDF

በባሎቻቸው ላይ ሌላ ወንድ እየለመዱ ትዳራቸውን ያበላሻሉ። እንዳንዶቹ ደግሞ ጌጥ የማይጠግቡ፣ ገንዘባቸውን ለዚሁ የሚጨርሱ፣ በዚህም የተነሣ ከባሎቻቸው ጋር ዘወትር የሚፋጁ ናቸው። እና ታዲያ...'' ብለው የመኪናውን ማርሽ ለውጠው ፍጥነት ሲጨምሩ፣ ከአቋራጭ መንገድ የወጣ መኪና ሩጦ ከፊታቸው ሲገባ፣ እርሳቸውም ከመሥመራቸው ወጥተው፣ አንዱን እግረኛ ገፍትረው እንደገና ወደ ዋናው መንገድ ገብተው ፍሬን ሲይዙ፣ ወይዘሮ ላቀች ከመስታወቱ ጋር ተጋጩ።

አቶ ገብረ ሥላሴ መኪናውን አቁመው፣ የወይዘሮ ላቀችን ግንባር እንዳያብጥ ደሙን ለመበቱን ሲያሻሹላቸው፣ የተገፈተረው ሰውዬ ከወደቀበት ተነሥቶ፣ ''ቆርቆሮ የያዝክ እንደሁ የኔ ገሥክ መሰለህ? አሮጊት የጫንክ እንደሆነ አገሩን የምትገዛ መሰለህ? ወንድ ከሆንክ እስቲ ከቆርቆሮው ውጣና ይለይልን፣ወንዱ ይታያል'' እያለ መፎግላት ጀመረ።

''እንሒድ አቶ ገብረ ሥላሴ፣ እንሒድ፣ የዛሬው ቀን ደግሞ የጀመሩትን ጨዋታ የሚያደናቅፍ ነው የሆነው'' አሉ ላቀች፣ በመሐረማቸው ጭምር ግንባራቸውን እያሻሹ።

''እሜቴን ባልይዝ ኑሮ አሳይህ ነበር። ወንድ መሳይ!'' እለያ ተገፍትሮ የተነሣ ሰውዬም፣ የገብረ ሥላሴን ትዕግሥት በሚቴ ወሮታ ሊያቻችለው ብሎ።

አቶ ገብረ ሥላሴ፣ ከተገፈተረው ሰውዬ ጋር መነታረኩን አልፈለጉትም። ያን ግፍተራ የፈጠሩት እርሳቸው ያለመሆናቸውን ለዚያ ተገፍታሪ አስረድተው ለማሳመን እንደማይቻል ስለተገነዘቡት፣ ሞተሩ ሳይጠፋ ሲንተከተክ የነበረውን አውስቲን አቶሞቢል ማርሹን አስገብተው ተፈተለኩ።

''ስለ ሰው ትዳር፣ ስለ ሴትዮይቱ ዘር ለማወቅ ምን አሳሰበሽ?' ብሎ ነው መሰለኝ ያልታሰበ ነገር ደጋግሞ የላከብኝ'' አሉ ወይዘሮ ላቀች፣ ግንባራቸው ላይ ከደረሰው የመስታዋት ቡጢ ይልቅ፣ የአቶ ሽዋንግዛው ትዳር ወሬ መቋረጥ እያንገበገባቸው።

''እረ የዚያኛውስ ቀላል ነው። ዋናው ነገር የግንባርዎ ጉዳይ ነው። እውንስ እንዴት ያደርግዎታል፤ ሊያብጥብዎ ይሆን?'' አሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገብረ ሥላሴ ፣ የወይዘሮ ላቀችን ግንባር ለማየት ሲሞክሩ ፣ ከመን ገዱ ሊወጣባቸው የነበረውን አቶሞቢል ወደ መሥመሩ ለመመ ለስ እየታገሉ ።

"እዎ ትንሽ መቆጣት መጀመሩ ነው መሰለኝ ። አበጥ ሊል ነው መሰለኝ" አሉ ላቁ ግንባራቸውን እየዳሰሱ ።

"ይኸውልዎ! ቅድም እንዳነጣሁት ፣ የዛሬ ሴቶች አስቸጋ ሪዎች ናቸው ። ሁላችንስ በየቤታችን አሉን አይደለም ? አሁን ለምሳሌ የኔ ባለቤት እመቤቴን እየያዝኩ እንደዚህ በከተማው ውስጥ መዘዋወሬን ብታይ ወይም ብትሰማ——"

"እረ እስቲ ያንተዪቱን ተዋትና ፣ የእርሳቸውን ሚስት ታሪክ እጫውተኝ" አሉ ላቁ ፣ የገብረ ሥላሴን መንጠራራት አሸቀንጥ ረው ሲወረውሩት ።

"ሴትዬዋ የትልቅ ሰው ዘር ነበሩ ። ታዲያ ምን ያደርጋል! ሰውዬውን መከታተል ፣ ማሳደድ ሆነ ሥራቸው ። ሰውዬውም ክትትሉና ቁጥጥሩ ሲበዛባቸው ጊዜ ነው መሰለኝ ፣ በቃሽኝ ብለው ፣ እነሆ በጸሎት ተወስነው ብቻቸውን ይኖራሉ።"

"ኤዲያ! የሴት ቀናተኛ ምን ያደርጋል ? ለነገሩ ሰውዬውም የሚቀናባቸው ናቸው ? ቢሆንስ ፣ 'የት ገባህ ? የት ወጣህ ? ማን እየችህ ?' ተብሎ ወንድ ልጅ አይጠየቅም ። ወንድን ችላ ሲሉት ራሱ እርር ድብን ይላል ። ልብን ከከፈቱለትማ ይብሳል" አሉና እያበጠ የሔደውን ግንባራቸውን እሽት እሽት አደረጉ ፤ "ወይ ጉድ! ታዲያ አሁን የሚኖሩት ብቻቸውን መሆኑ ነው ?" ብለው የመጨረሻዉን የማረጋገጫ ጥያቄ ሠነዘሩ ።

"እዎ ብቻቸውን ነው ። እንዲያውም ሁለተኛ ሴት ቤታቸ ውን የምትረግጥባቸውም አይመስሉ ። እንዲያው ሴት በዞረች በት የሚያር ሱም አይመስሉ ።"

"ብዙ ልጆች ወልደው ኑረዋል ?" አሉ ላቀች ፣ የሸዋንግ ዛውን ሚስት ወላጆች ስም ማወቁን ችላ ብለው ፣ ወደ ቤታቸው ሕይወት አትኩረው ።

"እረ ብቻቸውን ናቸው ። ከቤት ካሉት ሠራተኞች በቀር ልጅ የሚሉ ነገር የለም" አሉ ገብረ ሥላሴ ፣ የሸዋንግዛውን የመ ጀመሪያ ሚስትና ልጆች ታሪክ ዋጥ አድርገው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ወይ አለመገጣጠም!" ብለው ላቀች ተነፈሱና፣ "እንዲህ ያለው መኳንንት ብቻውን ይኖራል። ስንቷ ትዳር የጠማት ወይዘሮ ደግሞ ብቻዋን ትኖራለች" አሉና እንደ መዝናናት ቃጣቸው።

በዚያች ምሽት የመኪና መንዳቱ ጉዳይ ችላ ተብሎ፣ሁሉቱም በጋራ አንድ ዐይነት አነጋገር፣ በየልባቸው ደግሞ መንታ መንታውን እያወጡ እያወረዱ ከቤት ደረሱ። ወይዘሮ ላቀች ከመኪናቸው ወጥተው የቤታቸውን በረንዳ ሲወጡ፣ "አቶ ገብረ ሥላሴ፣ ግባ እፈልግሃለሁ" ብለው ገቡና፣ ከመኝታ ክፍላቸው ገብተው በቁም ሳጥናቸው መስታወት ቁመናቸውን ሲመለከቱት፣ የግንባራቸው እብጠት የሾላ ፍሬ አክሎ አዩት። ወደ እንግዳ ማረፊያው ክፍል ተመለሱና፣ ከበረንዳው ላይ ቁመው የነበሩትን፣ ገብረ ሥላሴን ጠርተው፣

"ስለ ሰው ትዳር፣ ስለ ሰው ሚስት ታሪክ ለማወቅ ምን አገባሽ ብሎ የፈረደብኝን ቅጣት?" ብለው አሳዩዋቸው።

"እንዴ፣ እንዴ፣ እመቤቴ! ተጐድተዋልና? ሐኪም ቤት እንሒድ እንዴ?" አሉ ገብረ ሥላሴ።

"አይ ምነው ለሆነ ላልሆነው ሐኪም ቤት ሩጫ? ግዴለህም በሙቅ ውሃ አሸዋለሁ። ባይሆን ነገን አይቼ ከባሰበት እሔዳለሁ በል እንግዲህ፣ የተነጋገርነውን በልብህ ያዘው። አሁን ራትህን ብላና ሒድ" አሉና፣ ገብረ ሥላሴን ከእንግዳ መቀበያው አስቀምጠው ራትና ጠርሙስ ጠጅ ላኩላቸው። ጠጅ ቀርቶ ራት ሲጋብዙ እንኳ ያ ዕለት የመጀመሪያቸው ስለ ነበረ፣ ገብረ ሥላሴ ነገሩ ገብቷቸዋል። 'ከሸዋንግዛው ጋር አስተዋውቀኝ ማለታቸው ነው' እያሉ፣ ራታቸውንና ጠጃቸውን ጥርቅም አድርገው ወደ ቤታቸው ሊሔዱ ሲሰናበቱ፣

"በል እስቲ ለዘመድህ ሠርግ እርዳታ ቢሆንህ" ብለው ሃምሳ ብር አስጨበጡዋቸው። ከመኪናው በስተኋላ የሜኑ ትንም በማ አሸክመው ሔዱ።

በማግሥቱ ጥዋት በሦስት ሰዓት፣ የአቶ ሸዋንግዛው ተላላኪ የመሥሪያ ቤቱን ምድረ ግቢ ሲያስስ፣ አቶ ገብረ ሥላሴ እገር አማን ነው ብለው እየተቆነጉ ገና ከዋናው በር እንኳ ሳይደርሱ ተላላኪው በሩቁ አይቷቸው፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሮጥ ሮጥ ይበሉ ፥ ይፈለጋሉ!" አላቸው ፥ በእጁ ጭምር እየጠራቸው ።

"ማንን ነው?" አሉ ገብረ ሥላሴ ።

"እርስዎን ነው ፤ ይፈለጋሉ ።"

መኪና እንኳ እሩጠው በማያውቁት ፍጥነት እየሮጡ ሔዱና ከአቶ ሽዋንግዛው ቢሮ ገብተው ለጥ ብለው እጅ ነሥተው ሲቆሙ፥

"ጤና ይስጥልኝ! እንዴት አደሩ ፤ እባክዎ አሁን የፈለግ ሁዎት ላሥራ ጉዳይ ወደ ውጭ ልልክዎ አስቤ ነው ። ቅርብ ነው ፤ ከጥቂት ቀናት በኋላ ይመለሳሉ ። ሌላ ሥራ አለብዎት?" አሉና ሽዋንግዛው ጠየቁ ።

"እንዴት ጌታዬ! ሥራ ከሆነማ ሥራ ነው ። የግል ጉዳይ ቢኖርብኝም እንጂራ የምበላበት ሥራ ይበልጣል ።"

"ለመሆኑ ምን ጉዳይ አለብዎ?"

"አይ ፥ የአነዲት እኅቴ ልጅ ሠርግ ነው እንጂ የሌላ አይ ይለም ።"

"መች ነው ሠርጉ ።"

"እሑድ ነው ።"

"የመቸው እሑድ?"

"የነገው ሳምንት ።"

"እኅትዎ ትላንት አብሮዎት የነበሩት መሆናቸው ነው?" አሉ ሽዋንግዛው ።

"አረ! አረ! ሆ!ሆይ!" አሉና ገብረ ሥላሴ ራሳቸውን እያ ሻሹ ተቅለሰለሱ ።

"ምነው?"

"እንዴ ፥ ጌታዬ! የትላንትናዋማ ፥ ጌታዬ!" አሉና ተቅ ለሰለሱ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እህ ?"

"እንዴ ፣ የትላንትናዋማ ! ጌታዬ ! የትልቅ ሰው ሚስት የነበሩ ናቸው ፣ መኪና መንዳት እያሳየኋቸው ነው ።"

"ይበሉ እስቲ ይቀመጡማ አንድ ጊዜ" አሉና ደጋግመው ስልክ ሲደዋውሉ ቆዩና ፣ ስለ ወይዘሮ ላቀች ታሪክ ሲሰሙ አረፈዱ ።

በዚያኑ ዕለት ወደ ማታ ፣ አቶ ገብረ ሥላሴ እንደ ተለመደው ወደ ወይዘሮ ላቀች ቤት ቢሔዱ ፣ ወይዘሮ ላቀች ግንባራቸው ወደፊት አሞልሙሎ ፣ ከመካከሉ ላይ የሎሚ ያህል አፍጥጦ አገኙዋቸው ።

"እንዴ ፣ እሚትዱ ! እንዴ ! ወይ ጉዴ ዘንድሮ ! ታዲያ ሐኪም ቤት ልውሰድዎት እንዴ !" አሉ ፣ ከልባቸው የደነገጡ በመምሰል ።

"ሐኪም ቤትማ ቀን ሔድኩኝከ ። ይኸውልህ ፣ ይኸን ክኒንና ይኸን ቅባት ሰጠኝ ። 'ኪኒናውን በቀን ሦስት ጊዜ ዋጭ ፣ ቅባቱን ደግሞ ማታ ስትተኚ ፣ ሌሊትና ሊነጋጋ ሲል ታሺው' ብሎኛል ። ታዲያ ችግሩ ፣ ማታስ ልጆች ሳይተኙ ያሹልኛል ፤ ሊነጋጋ ሲልስ ማን ይሽልኝ ? የዛሬ ልጅ እንደሁ እስከ ቆምን ጤና እስከሆን እንጂ ፣ ካልጋ ላይ ከተኛን የማንነሣ ፣ ነፍሳችን የወጣች ነው የሚመስለው ። ይኸውልህ ፣ ከአጠገቤ ሰው የለኝ ፤ ችግር ሆነ ። ለመሆኑ ፣ እኒያ አለቃህ አልተቆጡህም ?" ብለው የጉጉት ጨዋታ ጀመሩ ።

"እንዴ ምን ብለው ይቆጣሉ ?"

"እንዴ ከመሥሪያ ቤታችን ድረስ የምን ሴት ጭነህብን መጣህ ብለው ?"

"እረ እሳቸውስ የጠየቁኝ ሌላ ነው ።"

"ምን ጠየቁህ ልጄ ?" አሉና ላቀች ፣ ቀና ብለው ቁጭ አሉ ። ቆመው የነበሩትን ገብረ ሥላሴንም ፣ "እስቲከ ከሳሎኑ ወን

t.me/OLDBOOKSPDF

በር አምጣና ተቀመጥ'' አሉና ፣ ከትራስጌያቸው የነበረውን ደወል አታጨሉት ። ሠራተኛ ሩጣ ስትገባ ፣ ''እስቲኮ ለገብረ ሥላሴ መቀመጫም ጠጅም አምጪለት'' አሉና ቁጣ የተዋሳቀለበት ትእዛዝ አስተላለፉ ።

አቶ ገብረ ሥላሴ ፣ ጠጃቸውን እየሳቡ የላቁን ልበ-ልቡና በሸዋንግዛው ወሬ እያለቡ ቆዩና ፣ ሊወጡ ሲነሡ ፣

''እንግዲህ መቸም ሁሉንም በልብ መያዝ ነው ። 'የሆድ ምቀኛው አፍ ነው' ተብሎ የለ ? ባነጋገርህ ዕወቅበት'' ብለው አሰናበቱዋቸው ።

''ዛሬስ ማስተማርምን ይቀጥላሉ ?'' ብለው አቶ ሸዋንግ ዛው ገብረ ሥላሴን ጠየቁዋቸው ፣ በማጣፊቱ ጥዋት ሲያነጋግሩዋቸው ።

''እዮ ፣ ጌታዬ ! ዛሬስ አሟቸው ተኝተዋል ።''

''እንደ ፣ ምን አገኛቸው ? የሰው ዐይን በላቸው እንደ !''

''ምንኮ የሲቶች ነገር'' ብለው ነገሩን አድበሰበሱት ፤ እውነቱን ያወጡ እንደሆነ ሹፌርነታቸው እንዳይነወርባቸው ሠግቶው ።

''እንግዲያው እስቲ በዚህች ፍራፍሬ ገዝተው ያድርሱልኝ ። ለርስዎ ደግሞ የተረፈው ለአንድ ጉዳይ ቢሆንዎ ?'' ብለው መኮብር አውጥተው ሰጡ ።

''ዛሬውኑ ልውሰድላቸው ?''

''እንደ በኔ መኪና እሮኑኑ ያድርሱላቸው ።''

አቶ ገብረ ሥላሴ ፣ ከዚያ በፊት እንኳን እርሳቸው ሊምክሩት በከተማው ውስጥ አይተውት በማያውቁት ፍጥነት እየጋለቡ ወደ አትክልት ተራ ሔደው ፣ አትክልት የተባለውን ሁሉ አግበስብሰው ወሰዱና ለወይዘሮ ላቀች አስረከቡ ።

''አሉቱ ! ያትክልት ችግርኮ የለብኝም ። ካከበሩኝ ራሳቸው መጥተው አይጠይቁኝም ነበር ? ከማን የማንስ መስልኳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ችው ! መቸስ ምን ይደረግ ፡ በኔ በኩል ደግሞ ሴትነቴን ፡ እጄን እንዲቀምሱት ከደረቁ ጠጅ ውሰድልኝ'' አሏቸውና ሠራተኛቸውን በደወላቸው ጠርተው ፡ ''በይ እስቲ ፡ በትንሽዋ ገንቦ ከደረቁ ጠጅ ከመኪናው ውስጥ አስገቢ'' አሉዋት ።

''ከማን መኪና ፡ ከኛው መኪና ነው ?'' አለች ሠራተኛዋ ።

''ልባውልት ! ከኛ መኪና የምታስገቢው ውሽማሽን ልት ግችው ነው ?'' ሲሉ ዘለፏት ፡ ከሾፌራቸው ጋር የምታደርገውን መግገጥ በአግቦ ሲነግሩዋት ።

በማግሥቱ ወደ ማታ ፡ በገብረ ሥላሴ ሾፌርነት አቶ ሸዋን ግዛው ከኋላ ተጭበረው ከወይዘሮ ላቀች ቤት ደረሱና ፡ ወደ እንግዳ ማረፊያው ክፍል ገብቱው ተቀመጡ ።

ወይዘሮ ላቀች ፡ ከመኝታ ቤታቸው ሆነው ሠራተኛዋን በደ ወላቸው ጠሩና ፡ ''እንቺ ማነው የመጣው ?'' ብለው ጠየቋት ።

''አቶ ገብረ ሥላሴና —''

''ብቻውን ነው ?'' አሉ ላቀች ቸኩለው ፡

''አይ ከአንድ ትልቅ ሰው ጋር ናቸው ።''

''ውይ ፡ በሞትኩት ! እዬ የሱ ነገር ! እስቲ ጥሪው ።''

ገብረ ሥላሴ ገብተው እጅ ነሥተው ቆሙ ።

''አንተ ፡ አንተ ታሪከኛ ! እኒያን ትልቅ ሰው እኒያን ከሰ ማይና ከመሬት የከበዱ ሰው ይዘህብኝ መጣህ እንዴ ?'' አሉ ካልጋቸው ላይ እንደሆኑ ፡ ከወገባቸው ቀና ብለው ፡ በግራ ጉና ቸው ዙረው ፡ ዐይኖቻቸውን እያንከባለሉ ፡ ቀኝ እግራቸውን ዕጥፍ ዘርጋ እያደረጉ ።

''እንዲያው 'ሳላያቸው አላድርም' ሲሉኝ ጊዜ ፡ ምን ላድ ርግ ?''

''ጉድ ሠራኸኝ ። ሳልዘጋጅ ትልቅ ባለሥልጣን ይዘህብኝ ትመጣ ! በል እንግዲያው ፡ ልነሣና ልለባብስ'' አሉ ፡ በስሜ ታቸውና በአነጋገራቸው ተቻኩለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"አይ ለምን እመቤቴ ! ለምን እዚሁ እንደሆኑ እርሳቸው ይግቡ እንጂ ! ሳይቀር ነገር ። የመጡበት ጉዳይ አይደለም ?" አሉ ገብረሥላሴ ።

"በል ካልህማ ይሁና ! እንግዲያው ልጅቱን እስክልክብህ እዚያው ቆዩ" አሉና ፣ ገብረሥላሴ ሲወጡላቸው ላቀች ካል ጋቸው ተነሡ ። ከቁም ሳጥናቸው ሰስ የውስጥ ልብስ አውጥ ተው ፣ የገላ ልብስ አውልቀው ቀየሩና ፣ ሽቶ በላያቸው ቱሽ ቱሽ አድርገው ፣ ግንባራቸውን በደበላ ሻሽ ሸብ አድርገው ፣ ከሽቶው በክፍሉ አርከፍክፈው ፣ የአልጋቸውን ልብስና ትራ ሶቹን አስተካክለው ፣ ተመልሰው ካልጋቸው ውስጥ ገብተው ፣ በደወላቸው ሠራተኛቸውን ጠሩና ፣

"ስሚ እንች ልባውልቅ ፣ ዛሬ ነግሬሻለሁ ! ሰው እዚህ ከፍል ድርስ ይልና ወዮልሽ ! በይ አሁን ያን የፊታውራሪ የነበረውን ወንበር እዚህ አስገቢና ፣ እንግዳውን እንዲያስገባቸው ለገብረ ሥላሴ ንገሪው" አሉዋት ።

ሠራተኛዋ ፣ እንደ ታዘዘችው ሥራዋን አቁላጥፋ ስታቢቃ ፣ አቶ ሸዋንግዛው በአቶ ገብረ ሥላሴ አጋፋሪነት ሲገቡ ፣ ወይዘሮ ላቀች ካንገታቸው ቀና ብለው እጅ ነሡ ።

"ምነው ምን አገኘዎ ፤ በበቀደም ደኅና አልነበሩም ?" አሉ ሸዋንግዛው ፣ ከወይዘሮ ላቀች አልጋ ጐን ከተዘረጋው የመዝ ናኛ ወንበር እየተቀመጡ ።

"አረ እባክዎ ፣ የዚያን ቀን ጉድ ስንቱ ተነግሮ ?" ብለው ከፊት ለፊታቸው ተገትረው የነበሩትን ገብረ ሥላሴን ሲመለከቱ ዋቸው ፣ እሳቸውም በእጃቸው ምልክት እያሳዩ የግንባራቸውን ዕብጠት እንዳያሳዩ ተማፀኑዋቸው ። "እንዲያው አታድርስ ነው እንጂ ፣ ደኅና ከቤት የወጣሁ ሰው እንዲያው በድንገት አሞኝ መጣሁ" አሉና ፣ ደወላቸውን ሲያቃጭሉ ፣ ሠራተኛዋ ገባች ። ወደ እርሳቸው አስጠግተው የጠጁን መኖር ጠየቋት ። ወዲያው ወደ ሸዋን ግዛው ዘወር ብለው "ምን ታምጣ ? ማለፊያ ጠጅ አለ ። የፈረንጅም መጠጥ ይፈቀድ እንደሁ ይቅረብ" አሉ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ጠጁን እመርጣለሁ" አሉ ሸዋንግዛው ።

ሠራተኛዋ ፣ በጠርሙስ ጠጅና ብርጭቆ ይዛ ገባች ፤ ቀድታ ከወይዘሮ ላቀች ኮመዲኖ ላይ አስቀምጣ ወጣች.....

• • •

የመቶ አለቃ ከበደ ፣ ለሥራ ከሔደበት ቦታ ሰንባብቶ ከተመለሰ በኋላ ፣ የሁለቱን ዕድሮች ብቻ ሳይሆን ፣ በአካባቢው የነበሩትንም ዕድሮች ኃላፊዎችና ዕውቅ አዛውንቶች በየቤታቸው እየሔዱ ስለተጀመረው የዕድሮቹ እንድነት ጉዳይ በሰፈው ማነጋገር ጀምሯል ። ከሁለቱ ዕድሮች ጋር ሌሎች የአካባቢ ዕድሮችንም በእንድነት ለማዋሐድና ለሁሉም የሚሆን ደንብ ለማውጣት ፣ ከሌሎች ዕድሮች አንዳንድ ደንቦችን ወስዶ በርሱም ዕድር ውስጥ እንዲሠራባቸው ለማድረግ ይጣጣራል ።

በዚሁ መሠረት ፣ በየቤታቸው እየዞረ ካነጋገራቸው ተባባሪዎቹ ጋር ለመገናኘትና ለመነጋገር እንደ ተለመደው እሑድ በግራርዋ ሥር ለመገናኘት ተስማምተው ነበርና ፣ የልጅ አድባሩ ዕድር ሽማግሌዎችና የጉረቤት ዕድሮች ተወካዮች ሲገናኙ መምሬ በዕውቀቱ ብቻ አልተገኙም ። በተቀጣጠሩበት ዕለት ከረፋዱ ላይ በግራርዋ ሥር እንደ ተቀመጡ ፣ የመቶ አለቃ ከበደ ተነሣና ፣

"አባቶቼና ወንድሞቼ" ብሎ ጀመረ ፤ "በዚህ ወረዳ ቁጥራቸው ከዐሥራ ሰባት በላይ የሚሆኑ ዕድሮች አሉ ። ግን በየአንዳንዱ ዕድር ያለው ዕድርተኛ ብዛት በጣም ጥቂት ነው ። በአንዳንዶቹ ዕድሮች እስከ ሁለት መቶ ሲደርስ ፣ በአንዳንዶቹ ደግሞ ከሰድሳና ከሰማኒያ ሰው አይበልጥም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"በዚህ በኛ ሠፈር እንኳ ከአምስት መቶ ለማይበልጥ ነዋሪ አራት ዕድሮች ተቋቁመዋል። ለምሳሌ በልጅ አድባሩ ቦታ ላይ ሁለት መቶ የማይሞሉ ነዋሪዎች ሲገኙ፣ በፊታውራሪ ዕድር ሥን ያሉት ዕድርተኞች ከመቶ በታች ናቸው። ታዲያ የዕድር ከፍያውም በዚሁ ልክ እንሰተኛ ነው።

"በሌሎቹ ወረዳዎች ያሉት ዕድሮች ግን በጣም የተሻሉ ናቸው። የዕድርተኛቸው ብዛት ላቅ ያለ ነው። አብዛኛዎቹ ዕድሮች የዕድርተኛቸው ብዛት ከሁለት መቶ በላይ ስለሆነ ፣ ለኃዘን ተኛም ሆነ ለልማት የሚያዋጡት ገንዘብ ከፍ ያለ ነው።

"የኛ ሠፈር ፣ በተለይም የሁለቱ ዕድሮቻችንን ነዋሪ ግን ፣ እንስተኛነቱ ብቻ ሳይሆን ስምምነት ማጣቱ በጣም ፣ እጅግ በጣም ጐድቶታል። የሁለቱን ዕድሮቻችንን ታሪክ ስለምታውቁት መዘርዘር አያስፈልግም።

"የዛሬው ስብሰባችን ዋናው ጉዳይም ፣ ዕድሮቻችንን እቀ ላቅለን በሠፈራችን የልማት ሥራዎች እንድናከናውን እንድን ጥርበት ነው። ከዚህ ቀደም ባደረግናቸው ውይይቶች መሠረት ሁለቱ ዕድሮች አንድ እንዲሆኑ የሚታመን ስለሆነ ፣ በዚህ በአ ካባቢያችን ካሉት ዕድሮች ጋር አንድ ለመሆን እንድንችል ነው ከአራቱ ዕድሮች ተወጣጥተን እዚህ እንድንገናኝ የተስማማነው። ስለዚህ ፣ ከጥቂቶቻችሁ ጋር ሆነን ሰሞኑን ያረቀቅነውን ደንብ ፣ ፈቃዳችሁ ከሆነ ላንብብላችሁ" ብሎ ፣ በማጎደር ይዘት ከንበረው ወረቀት ማውጣት ሲጀምር ፣

"በኛ በኩል ኮ ችግር ተንሥቶብናል" አሉ የፊታውራሪ 'ዕድርተኛ አቶ ንጉሤ ፣ 'ሰሞኑንኮ ተቸግረን ነው የሰነበትነው። ዛሬም እዚህ የመጣሁት እኔ ብቻ ነኝ። ሌሎቹ ፈርተው ቀር ተዋል። ወይዘሮ ላቀች ፣ እኔ 'ሳልስማማበት ፣ እኔ ሳልጠየቅ በምታደርጉት ስብሰባና ስምምነት አልስማማም ፣ ዐርፋችሁ በየ ቤታችሁ የማትቀመጡ ከሆነ ፣ በውላችን መሠረት ርስቴን ትለ ቃላችሁ' እያሉ እየዛቱብን ናቸው።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"አዎ ፤ እሳቸውማ እንኳን ጢሰኖቻቸውን እኛንም ማስፈራራት ጀምረዋል ። ብቻ ዐቅ ፂቱ የለችም እንጂ" አሉ አቶ እንደሻው ።

"የተከፋፈሉ ዕድሮቻችንን እንድ እናደርጋለን ብለን በተነሣን ከርስቴ ተነሡ የሚሉበት ምክንያት ሊኖር አይገባውም ፤ ለማስፈራራቱማ ለኔም ተልኮብኛል ። እስቲ የሚያደርጉትን እናያለን እንጂ ። ፊታውራሪ ነበሩ የሚያስቸግሩን እንጂ ፣ የቤትዋ ዛቻና ፉከራ እንኳ እንዲያው ነው ። ይልቁንስ አሁን ስለ ተሰበሰብንበት ጉዳይ እንነጋገርበትና ሥራችንን እንቀጥል" አለ የመቶ አለቃ ፣ የወይዘሮ ላቀችን ድንፋታ እያቃለለው ።

"የተማመኑት ሰው ላያገኙ እንደዚህ አይዝቱብንምና ፣ በጉዳዩ ብንመካከርበት አይከፋም" አሉ ንጉሤ ፣ የመቶ አለቃንና አቶ እንደሻውን በጥያቄያዊ አስተያየት እየተመለከቱዋቸው ።

"ግዴለዎትም ፤ የርሳቸውን ድንፋታ መመከት አያቅተንም" ብሎ መቶ አለቃ ተናግሮ ላያጠቃልል ፣

አቶ ንጉሤ አቋረጡትና ፣ "'ጌታዬ ነህ ፤ ስማኝማ ! ነገ ጥዋት ከርስቴ ከቦታዬ ተነሡ' ብንባል የሚያድነን ላይኖር ፣ ዛሬ እዚህ መታየት የለብኝም ። የመጣሁትም ይህንኑ ልንገራችሁ ብዬ ነው እንጂ ፣ ሌሎቹማ ፣ ብልጦቹማ ከየቤታቸውም አልወጡ ። በየቤታቸው መስኮት ሆነው እኛን እያዩ ይሣሣቃሉ ፤ ከወይዘሮ ላቀች ጋር ተመካክራችሁ ካላስፈቀዳችሁልን ዳግመኛ እዚህ አንደርስም" አሉና ብድግ ሲሉ ፣

"ግዴለዎትም ፤ ምንም አያደርጉዎት ፤ ነገም ከርስቴ ላይ ተነሥ ቢባሉ ከኔ ቤት ይገባሉ" አሉ አቶ እንደሻው ፣ አቶ ንጉሤን ሲያጥናኑና ሲያበረታቱ ።

"ምንም አይደርስብዎትም ፤ እኔ አለሁ" አሉና የመቶ አለቃ አቶ ንጉሤን ሊያስቀምጣቸው ሲሞክር ፣

"እሀ ! ተውዋቸው እንጂ ይሒዱ ። ችግራቸውን እየተናገሩ እንዴት እንጫናቸዋለን ? ባለርስቶች የሚሠሩትን ሥራ ታውቁት የለም ?" አሉ ከጐረቤት ዕድር የሔዱት አዛውንት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሌሎች ሽማግሌዎች ስለ ተሰማሙበት ፡ አቶ ንዑሜ እንዲ ሔዱ ተፈቀደላቸው ። የመቶ አለቃና አቶ እንደሻው እርስ በር ሳቸው ተያይተው መተከዝ ሲጀምሩ ፣

''እንደኤት ነው ነገሩ ? በዚህ ጉዳይ ላይ ባለርስቶች የማይ ስማሙበት ከሆነማ እኛምኮ የሠፈርነው በሰው ርስት ላይ ነው ። ያውም የኛው ባለርስትማ መቶ አለቃ የምትፈታተኑኛችውም አይ ደሉም ፡ ጀነራል ናቸው ። በትንፋሻቸው ብቻ መሬት የሚያ ንቀጠቅጡ'' አሉ ሌላው ተዋራቢች ዕድርተኛ ፣ ለመተቸትና ለማሸሟጠጥ ብለው ።

''አባቶቹ ፣ ጌቶቹ ! መላዋ አዲስ አበባ የባላባቶች የባለ ሟሉችና የባለርስቶች ከተማ ናትኮ ! ይህን አላጣነውም ። ግን ዕድሮችን አንድ ለማድረግና መንደሩን ለማልማት የሚቃወሙ እይመስለኝም ። የዚህ ዓላማ ተቃዋሚዎች ያሉት በኛ ሠፈር እና ዕድር ውስጥ ብቻ ነው ። ያውም ሁሉም ሳይሆኑ አንድ ሰው ናቸው'' አለና መቶ አለቃ ፣ ትንሽ ተከዝ ብሎ ደግሞ ፣ ''ሰውዬው እንኳ መተዋል ፡ ተገላግለናል ። ሚስታቸው ናቸው ደግሞ የሚያሰቸግሩን'' አለ ።

''ሴት የምታመጣውኮ ነው መዘዘኛው ። ሴትን ነው መፍ ራት እንጂ ፣ ለወንዱማ እንደ ወንድነትህ ትመክታለህ'' አሉ ከጄ ኔራሉ ዕድር የሔዱት አዛውንት ፣ እንደ መቀለድ እያሉ ።

''እሱስ እውነትዎን ነው ። ሠፈራችንና ዕድራችንም የተበ ጠበጠው ባንዲት ሴት የተነሣ ነው'' አለ መቶ አለቃ ።

''እሱነስ እንኳ ማለት አይቻልም'' አሉ ከጄኔራሉ ሠፈር ዕድር የሔዱት አቶ ገብረመልድ ፡ ''ሴትዮዋ የመጡ በኋላ ፣ሠፈ ራችሁና ዕድራችሁ የተበጣበጡት ቀደም ብሎ በባለርስቶች መካከል በተነሣ ሙግት ነው ። ሦስኛው ነው ጥፋተኛ ፣ ሴትዮዋ ብቻም አይደሉም ። ምነው ? በመካከላችንኮ ያለው ኑሯራ መንገድ ብቻ ነው ፡ ወንዝና ተራራ አይጋርደንም ፡ ሠፈሩንም ሰዉንም እናውቀዋለን ።''

''ጢሰኛው ምን አጠፉ ? ምን ማድረግ ይችላል ?'' አለ መቶ አለቃ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴት ምን አጠፋ ትላለህ ! እልም አድርጉ አጥፍቷል እንጂ" አሉ ፣ ገብረወልድ ።

"እኮ ምንድን ነው ጥፋቱ !" አሉ እንደሻውም ግር ብሏ ቸው ።

"ከዕድሩ ደንብ ውስጥ የባለርስቶች የግል ጥቅም ማስከበ ሪያ ደንብ ሲደነገግበት ፣ ለምን አሜን ብሎ ተቀበለ ?" አሉ ፣ ገብረወልድ ።

"ምን ማድረግ ይቻለው ኦሮዋል ! ከሰው ርስት ላይ ሠፍሮ አምቢ ቢል እየነቀሉ ይወረውሩታል ። ምን ዋቢ አለው ? ለምን ሜዳ ላይ አልወደቀም ነው የሚሉት ?" አሉ እንደሻው ፣ እንደ መቆጣት ብለው ።

"ባገር የሌለ ድንጋጌ ሲጣልበት ፣ አልቀበልም ብሎ ሜዳ ላይ ቢሠፍር አይሻልም ነበር !"

"ምነው ! አሁን ካንጀትም ነው የሚናገሩት ? በራስም በደ ርስብም የማይችሉትን ነገር ለምን ይናገራሉ !" አሉ እንደሻው ራሳቸውን ግራ ቀኝ እያሉ ።

"ደርቧል እንጂ ፣ ለምን ቢደርስብም" ይላሉ ! የኛ ሠፈር ባለር ስት ሠፈሩን ለኤምባሲ ሲሸጡ ውስጥ ውስጡን ተስማምተው ኦሮ ፣ "ልቀቁልኝ" ማለት ሲጀምሩ ፣ ሕዝብ ባንድነት ሆኖ "ይህን ሠፈር አባትም የተቀበሉት ፣ 'ከነወታደርህ ሥፈርበት ተብለው ነው ። የኛ አባቶችና ወንድሞችም ዓድዋና ማይጨው ዘምተው በታል ፤ በአርበኝነት ተዋግተውበታል ፤ በኋላም ወደ አጋዬን ታዘው ሔደዋል ። እኛም ቤት ሠርተን ፣ ንብረት መሥርተን ፣ ከተቀመጥንበት እንዴት እንነሣለን ? ለፈረንጅ ለመሸጥ እኛን እንዴት ያባርሩናል ? እንተላለቃለን እንጂ አንላቀቅም' ብለን ቁርጥ ያለ መልስ ስለ ሰጠናቸው ፣ ቦታውን እንደ ይዞታችን በየ ወሩ ለመክፈል ሸጠውልናል ። ለመግዛት የማይችለውንም ደግሞ እስከ ዕድሜ ልኩ ተቀምጠ ሲሞት ፣ ለልጁ ወይም ለዘመዱ ላያ ወርስ በሞስኝነቱ እንዲኖርበት ለማድረግ ችለናል ። ታዲያ ይህ ቀላል ነገር ነው ? እናንተም የሞስኝነቱና ፣ቤቱ ኪራይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማስገደጃ ድንጋጌ ከዕድሩ ደንብ ሲጨመርበት ትንሽ እንኳ አላን ገራገራችሁም ። አሜን ብላችሁ በመቀበላችሁ ነው የባለርስቶቹና የወኪሎቻችው መጫወቻ የሆናችሁት ። አሁንም ዕድርተኞቻችሁን ሰብስባችሁ ፣ የተጣለባችሁን የዘበናዮች ድንጋጌ አስወግዱና ፣ ከዚያ በኋላ ከኛ ዕድር ጋር አንድ ለመሆን ደግሞ እንጥራለን'' አሉና አቶ ገብረወልድ ብድግ አሉ ።

''እንደ ይቅዩ እንጂ ። ስለ ዕድራችሁ ደንብ እኮ አንዳንድ ነጥብ እንዲነግሩን እንፈልጋለን'' አለ መቶ አለቃ ።

''የኛ ዕድር ደንብ ጠበቅ ያለ ነው ፣ የዋዛ ወይም የይስሙላ አይደለም ። ብዙ ዐዋቂዎችና ሽማግሌዎች መክረውና ዘክረው ያወጡት ፣ የወረዳው ገዥ የተስማሙበት ነው ። ባለርስቶች የበ ከሉትኮ አይደለም'' አሉ እንደ ቆሙ ።

''እኛምኮ ይህንኑ ሰምተን ነው ፣ ከኛው ጋር እንድናስተያየ ውና ልዩነቱን ለማወቅ የፈለግነው ። ታዲያ ይቀመጡና በቅጡ ይንገሩን እንጂ! ሲሆን ሲሆን ባንድነት የምንተባበርበትን ደንብ እናወጣለን ፤ ካልሆነም የኛው የሚሻሻልበትን ነጥብ እንወስዳ ለን'' አለ መቶ አለቃ ።

''የእናንተውኮ ችግሩ ወይም ልዩነቱ ሌላ አይደለም ፣ የባለ ርስቶች ማነቆ ነው አሰቸጋሪው ። እሱን ካስወገዳችሁ ሌላው እንደ ነገርከኝ አያሳስባችሁም ። ለምሳሌ ስለ ቀብር ደንብ ያወ ጣነው ከእናንተም ሆነ ከሌሎች ዕድሮች ጋር አንድ ዐይነት ነው ። ግን የኛው ደንብ አንዳንድ ሁኔታዎችን ጠበቅ ያደርጋል ። ለምሳሌ ፣ ዕድርተኞች የሆኑ ባልና ሚስት ቢፋቱ ፣ ሁለቱም ከዕድሩ አባሎች ጋር አይጋቡም ። ሲትዮዋም ከዕድሩ ውጭ የሆነ ባል ፣ ወንድዬውም ከዕድሩ ውጭ የሆነች ሴት ነው የሚያገ ቡት ። ሌላው ደግሞ ፣ በሠፈራችን ውስጥ እየኖረ ዕድር ያል ገባ ሰው ኃዘን ቢደርስበት ፣ ምንም ዐይነት ርዳታ አይደረግለትም። ሌላው ቀርቶ ከእርሱ ኃዘን የደረሰ ፣ ከቤቱ የገባ ወይም እርሱን ወደ ቤቱ ያስገባ ፣ ድግስ የጠራ ወይም ከእርሱ ድግስ የሔደ ዕድርተኛ ላንድ ጊዜ አምስት ብር ፣ ከደገመ ዐሥር ብር ፣ ካሠ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለሰ ኻያ ብር ይቀጣና ከዕድሩ ይሠረዛል ። እንድ ቀደም ሲል የደረሰ ነገር ልንገራችሀ ።

"የክብር ዘበኛ አባል የሆነ እንድ የዐሥር አለቃ ፣ በሠፈራችን ይኖራል ። ዕድር እንዲገባ ሁላችንም ለመንነው ። 'በሰው ላይ ክፉ አለ ፣ በጉ አለና ፣ ለማንኛውም ነገር እባክህ ከኛ ጋር ሁን ። በዕድራችን ውስጥ እንዳንተ ያሉ ከብር ዘበኞች ፣ ጦረ ሠራዊቶች ፣ ፖሊሶች ፣ ወታደሮችና መኮንኖች ገብተዋልና ፣ አንተስ ከጓደኞችህ ስለምን ትለያለህ ?' እያልን ብንለምነው ፣ ብናስለምነው ፣ 'ኤዲያ! የእናንተ ዕድር' እያለ እምቢ ብሎን ኖረ ። እንዲህ ሲል ሲል ልጁ ትሞታለች ። በዚህ ጊዜ ፣ የኛ ዕድር ኃላፊዎች ይመካከሩና ሦስት ተመልካቾች ኃዘንተኞች አስመስለው ወደ ለቅሶው ቤት ይልካሉ ። እነርሱም ከለቅሶው ቤት ሔደው ከውጭ ይቀመጣሉ ። ጉረቤቶችና የሚያውቁት አንዳንድ ዕድርተኞቻችን ወደ ቤቱ ገባ ሲሉ ፣ እነዚያን የእኛ ተመልካቾች ሆነው የተቀመጡትን እያዩ መለስ ይላሉ ። በመጨረሻ ያ ሰው ወደ መሥሪያ ቤቱ ልጅ ላከና ፣ወታደሮች በመኪና መጥተው ከዋናው መኪና መንገድ ቆመው ፣ 'መጥተናልና ሬሳውን ይዘህ ና' ብለው ላኩበት ። በመኪናቸው እንዳይገቡ መንገድ የለም ። እርሱም 'ሬሳውን የሚሸከምልኝ የለም ብሎ' ላከባቸው ። ወታደሮቹም መጥተው ሬሳውን ተሸከመው ወሰደው ቀበሩለትና ከቤቱ በራፍ አድርሰውት ፣ 'ከቤትህ አንገባም ፣ ሰው አይደለህም ፣ አውሬ ነህ ፣ ከሠፈርህ ሕዝብ ጋር ተስማምተህ ዕድር ገብተህ የማትኖር ሰው ፣ እንኳን ለወታደርነት ለምንም ሥራ ብቁ አትሆንም ። እኛ ሁለተኛ ከደጅህ አንደርስም' ብለውት ተመለሱ ።

"ከዚያ በኋላ ፣ ብዙም ሳይውል ሳያድር ፣ ለዕድር ስብሰባ እንደ ተቀመጥን ያ ሰው ትልቅ ድንጋይ ተሸክሞ መጥቶ ከመካከላችን ወድቆ ፣ 'ማሩኝ ! ተሳስቻለሁ ፣ አጥፍቻለሁ ፣ የፈለጋችሁትን ቅጡኝና ከዕድሩ አስገቡኝ' ብሎ ለመነ ። እኛም ፣ 'እንኳን ልብ የሰጠህ ' ብለን ፣ ቅጣቱን ትተን ፣ የዕድሩን ሒሳብ ብቻ አስከፍለን ፣ ከዕድሩ አስገባነው ። እርሱም በእውነቱ ከሁላችንም የበለጠ ለዕድሩ አሳቢና ተቆርቋሪ ሆኖ ሲኖር ፣ በመካከሉ ሚስቱ በወላጆቿ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሀብት ተመከታ እሱን ትታ ሔደችና ፥ ሴላ ባል ካገባች በኋላ ፥ እር ሱንም በነቂስ ከየኪሳችን ገንዘብ አዋጥተን ፥ እህሉን ፥ ቅቤውን ዕርዱን ራሳችን አዘጋጅተን ፥ አሳምረን ግሩም አድርገን ደግ ሰን ዳርነው ። የኛ ዕድር እንደዚህ ያለና ሌላም ብዙ ብዙ ታሪክ ያለው ነው" አሉ አቶ ገብረወልድ ። ከአንድ ዐይናቸው ላይ የነበረውን የዐይን እር ሊልሱ ሲረባረቡባቸው የነበሩትን ዝን ቦች ዳግመኛ እንዳይደርሱባቸው አድርገው ለማባረር ሲሉ ፥ መሐ ረማቸውን አውጥተው ዐይኖቻቸውን አባበሱ ።

"በኛ ዕድር ውስጥ ድሆችም ሀብታሞችም ሞልተዋል ። ኃዘን ሲደርስባቸው የምንሰጣቸው ርዳታ እኩል ነው ። አንድም ዝንፍ አይልም ። ደግሞም የወሩን መዋጮ ለመክፈል የተቸገረ ዕድርተኛ ፥ ሴት ከሆነች ዕድርተኛው ኃዘን ሲደርስበት ንፍሮ በመቀቀል ፥ ወጥ በመሥራት ፥ ቡና በማፍላት ፥ ዕቃ በማጠብ ፥ በመሳሰለው ትረዳለች ። ወንድ የሆነም እንደሆነ ዕንጨት በመ ፍለጥ ፥ ዕቃ በመሸከም ፥ በመላላክ ያገለግላል ። ይህ በገንዘብ እየተተመነ እንደከፈሉ ይታሰብላቸዋል ።

"በእነርሱ ላይ ኃዘን ሲደርስ በድኅንታቸው የተነሣ ከዕ ድሩ የሚቀርባቸው አንድም ነገር የለም ። ለሀብታሙ ለቅሶ ሙማ ፥ ለድሃው ሽሮ አናቀርብም ። ሁላችንም ተሰብስበን እና ጽናናቸዋለን ፤ ገንዘቡንም በትክክል እናካፍላቸዋለን እንጂ ፥ የባ ለርስቶች የመሬትና የቤት ኪራይ ከፍለዋል አልከፈሉም ? ሩሚ ባል ጣጣ የለባቸውም" አሉ ፥ ፍጹም በሆነ የመንፈስ ኩራት እየተጀነኑ ።

"ማለፊያ ነው ። ታዲያኮ ከኛው ደንብና አሠራር ጋር ለማ ዛመድ እንድንችል—" ብለው አቶ እንደሻው ተናግረው ሳያ በቁ ፥ አቶ ገብረ ወልድ ያቋርጡዋቸውና ፥

"የእናንተ ዕድርኮ ጣጣው ገና ነው መሰለኝ ። ዛሬም እዚህ የተገኘሁት በመካከላችሁ የቆየው ንትርክ ውሳኔ አግኝቶ ፥ ዕርቅ ወርዶ ፥ አንድነቱን መሥርታችሁ ደንብ ለማውጣትና ከኛም ዕድር ጋር ለማዋሐድ የምንችልበትን ጉዳይ ለመነጋገር የተዘ ጋጃችሁ መስሎኝ ነበር ። አሁን እንደምንረዳው ከሆነ ግን ፥ ገና

t.me/OLDBOOKSPDF

ናችሁ ፣ ብዙ ይቀራል ። ስለዚህ አሁንም ዋናው መድኃኒቱ ከዚህ በፊት እንዳደረጋችሁት ዕድርተኛውን ሁሉ ሰብስቡና ፣ ችግሩን ፍርጥርጥ አድርጋችሁ ንገሩትና ፣ ሁለቱን ዕድሮች አንድ ካደረጋችሁ በኋላ እኛን ጥሩንና ተነጋግረን ፣ ደንቡን አገናዝበን ልንቀራረብ የምንችልበትን ነገር ሁሉ እናበጃለን" አሉና ለመሔድ መቸኮላቸውን በሁኔታቸው ማሳየት ጀመሩ ።

"ዕድርተኛውንስ ልንሰበስብ እንችላለን ። ግን በስብሰባው ተገኝተው ምክርዎን ሊለግሡልን ይፈቅዳሉ ?" አለና የመቶ አለቃ ጠየቃቸው ።

"ምን ብዬ ! ምን ዐይነት ምክር ?"

"በእናንተ ዕድር ስላለው ሁኔታ ከባለርስቱ ጋር ያደረጋችሁትን መግባባትና—"

"መች ተሟገትንና ! ማ'ው የሚያሟግተን ! ከየትኛው ችሎት ! ከማነኛው ዳኛ ዘንድ ቀርበን ነው ተሟግተን ፍሬ ልና ገኝ የምንችለው ? ቦታውን ለመሸጥ ውስጥ ውስጡን መነጋገራቸውን ሰምተን ፣ እኛንም ፣ 'ልቀቁልኝ' ማለት ሲጀምሩኮ ነው ፊት ለፊት የተቃወምናቸው" አሉ ገብረ ወልድ ፣ ቁጣቸው እንደገና እየተናነቃቸው ።

"ይህንኑስ ቢያስረዱልን ?" አለ መቶ አለቃ ።

"ሆሆይ ! ሞኝህን ፣ ዝንጉህን ፈልግ ወዳጄ ። ደግሞ ባለርስ ቶቹ ላይ ያሳድማል ፤ ሕዝብ ያነሣሣል ተብዬ የቁም ስቅሌን ልቀበላ ! እናንተው ራሳችሁ እንደ ፍጥርጥራችሁ ጣጣችሁን ጨርሱና ፣ ሁለቱን ዕድሮች አንድ ካደረጋችሁ በኋላ ደንቡንና ሥርዓቱን አብረን እንሠራለን ። እስተዚያው ጤና ይስጥልኝ" ብለው ራመድ ሲሉ ፣ ሌሎችም ከጐረቤት ዕድሮች የሔዱት ሽማግሌዎች ከየመቀመጫቸው ብድግ ብደግ ብለው ለስንብት እጆቻቸውን ሲወራወሩ ፣

"የላይ ሠፈር አቃጣሪዎች ወደዚህ ቦታ ምን አመጣችሁ ? ቦታ ነው ፣ ሴት ፍለጋ የመጣችሁት ?" እያለ ባልተጠራጠሩበት አቅጣጫ ደባልቀው ብቅ አለባቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ይኸ አገር ያሰለቸ ለፍላፊኮ እንዲያው!" አለና መቶ አለቃ ወደፊት ራመድ አለ፣ እንግዶቹን ሰላዋረደበት ደባልቀ ውን ሊበቀለው ።

"የሠፈራችሁ መጠጥ ቤቶች፣ አበጀህ! አበጀህ እያሉ እየጣቀለት ነው እንጂ፣ ምነው ታዲያ በኛ ሠፈር ብቅ አይል? ሠፈራችሁን የባለርስቶችና የዕብድ መጫዎቻ ያደረጋችሁት ራሳ ችሁ ናችሁ ። በኛማ ሠፈር እንኳን እንደዚህ ሊሳደብ ብቅ ብሎ በትም አያውቅ ። እርም ብሎ ቀርቷል" አሉ ገብረ ወልድ ።

"ነብዩ፣ አፈር ስሆንልሽ! እስቲ ለዛሬ መዋያ ያስለመ ድሽኝን ጣይልኝ ። አይዞሽ፣ ሻምበል ልትባይ ነው፣ በሕልሜ ታይቶኛል ። የኔ ሕልም ደግሞ መሬት ጠብ አትልም ። እርገ ጣቸው እንደሚሞት ነግሬሽ አልነበረም? ጠብቂ ደግሞ አድባ ሩም አይቀርለት" አለ ደባልቀው፣ ዱሮ ከሚቆምባት ቦታው ሰልፍ ሳይል ።

"በል ያውልህ፣ ቶሎ ከዚህ ጥፋ፣ ያጥፋህና!" አለና መቶ አለቃ ሳንቲሞች ወረወረለት ።

"ለዚህ ነዋ! ከሠፈራችሁ የማይጠፋው! ስለተሳደበ፣ ሕልም ሰላየ፣ ስላሟረተ ሳንቲም ትጥሉለታላችሁ ። ታዲያ ይህ ሰው ምን አጠፋ? ይህን ሠፈርስ ለቆ የት ይሔድ? እንዲህ ያለ ምቹ ሠፈርና ዕድር፣ እንኳን ዐውቆ ዐበድ፣ የተራቀቀ ተንኮለኛ ዕድርተኛም ቢሆን ዕድሜ የለው፣ ቶሎ ይደረስበታል" አሉ አቶ ገብረወልደ ።

"የዕድርተኛ ተንኮለኛውስ እንደምን ያለው ነው?" አለ የመቶ አለቃ ሲሸኛቸው ።

"ተንኮል የት ይጠፋል ብለህ ነው? ዕድርማ እንዲያው ብዙ አታላዮች የሚረባረቡበት ነው ። በዕድር ውስጥ ዐሥር አያቶች፣ አምስት አባቶች፣ ሦስት እናቶች፣ በኻያና በሠላሳ የሚቆጠሩ እጎትና ወንድሞች የሞቱበት አታላይ፣ መርዶ መጣ ብኝ" እያለ እያዘናጋ የማስተዛዘኛውን ገንዘብ የበላ በየጊዜው ተገኝቷል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"የሚስቱን ውርጃ ፣ ሕፃን ልጅ ሞተብኝ ብሎ የዕድር ጥሩንባ አስነፍቶ ፣ ድንኳን አስተክሎ ፣ 'አስተዛዝኑኝ' ብሎ የተቀመጠውን ዕድርተኛ ፣ ከዚያው ከዕድርተኛው ፊት ገመ ናውን ተናግረን አሳፍረነዋል ። እንደርሱ የመሳሰሉ ለማታለል የሚሞክሩትንም ለመግታት ስንል ፣ ከእናቱ ማሕፀን ወጥቶ ዐርባ ስምንት ሰዓት ድረስ በሕይወት ቆይቶ ለሞተ ብቻ ጥሩንባ እን ዲነፋለት ፣ ድንኳን እንዲተከልለት ፣ የዕርዳታም ገንዘብ እንዲሰ ጠው ደንብ አውጥተን ተገላግለናል ። የሰዉ ተንኮል እየተራቀቀ በመምጣቱ የዕድሩ ሁሉ ደንብ እየጠበቀ ሔደ ። ዛሬ በኛ ዕድር ውልፍት ለማለት አይቻልም" አሉና ተሰነባብተው ሲሔዱ ፣ ንግግራቸውን በታከተ ስሜት ሲያዳምጡላቸው የነበሩት እንደ ሻውም ፣

"ዕድርተኛው ፣ በሚሰበሰብበት ቀን እኒህን ሰው ከዚህ ታደርስና ውርድ ከራሴ ፣ ዕድሩን ከነአካቴው ታስፈርሰዋለህ" አሉት - መቶ አለቃን ።

"እንዴት ? የእርሳቸውን ንግግር ሲሰማ ፣ ወኔው ተቀስቅ ሶበት የባለ ርስቶችን ደንብ እንዳይሽረውና እነርሱም ከርስ ታቸው ላይ እንዳያባርሩት ነው ?" አለና መቶ አለቃ ተምኔታዊ ጥያቄውን ሠነዘረ ።

"አይደለም ፣ ኖኅ ሠፈር ዕድርተኛ እንዲህ ያለ ጥጋብ አይጠ ግብም ። ግን ፣ በስብሰባው ዕለት እኒህን የክተማ ዐርቦኛ ጠርተህ ይደስኩሩ ያልካቸው እንደሆነ ፣ ዲስኩራቸውን ሳያጨርሱ የቡ ናና የቅራሪ ሱስ ያነበዘው ዕድርተኛ እየጣላቸው ነው የማ ሔድልህ ?" አሉት ፣ በገብረ ወልድ ንግግር መጫኛነት መሰ ልቸታቸዉ በአሽሙር ሲነግሩት ።

"ዕድርተኛው በተሰበሰበ እንጂ ፣ የእርሳቸውንስ መጫኛ ዲስኩር በቆረጥኩት ነበረ" አለና መቶ አለቃ ፣ በሩቅ ወደነርሱ ሲገሠግሡ የነበሩ ሽማግሌ ዕድርተኛ ተመልክቶ ፣ "ታዲያ ሁለቱንም ዕድሮች ለመቸ እንዲሰበሰቡ እናድርግ ?" ብሎ አሳሰበ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እህ ምን ሆንክብኝ? የኛውንስ ዕድርተኛ ራሳችን ለም ነን እንሰበሰበዋለን ። የፈውታራሪን—ዛሬማ 'የላቀች' ቢባል ይሻላል—ዕድርተኛስ እንዴት አድርገን እንሰበስበዋለን?" አሉ እንደሻው ።

"ግዴለም ፡ አንድ ሴላ ዘዴ ደግሞ እሞክራለሁ ። 'ዕድሮቹ አንድ ሲሆኑልን እርስም ምክትል ዳኛ ወይም ገንዘብ ያዥ ይሆናሉና ዕድርተኞችም እንዲሰበሰቡልን ይፍቀዱልን' ብዬ ወይዘሮ ላቀችን እለምናቸዋለሁ ።"

"እሽ አይሉህም ፤ አፍህን አታጥፋ ።"

በቅርብ ርቀት የታዩት ሽማግሌው ዕድርተኛ ደረሱና ፡የገረረ ወገባቸውን ወረድ አድርገው ፡ እንደ ቀላዋጭ ውሻ እያስተዛዘኑ ቆሙ ።

"እንደምን ሰነበቱ ፡ አቶ መርጊያ? ደግሞ ዛሬ ምን ደረሰብዎና መጡ" አለ የመቶ አለቃ ፡ ሽማግሌው በየጊዜው ሲያስቸግሩት የኖሩ መሆናቸውን በሚገልጽ ሁኔታ ። በዚያው ሰዓት ፍጥነት ውስጥ ደግሞ ፡ እንዲት ልጅ እግር ሴት ወደ ግራኙዋ ሥር ስትሔድ ፡ ሽማግሌዎቹ ባንድ ላይ ዐይኖቻቸውን እየወረወሩ ተቀበሉዋት ።

"ጌታዬ ልጄ! ችግሬን ፡ ጉዳቴን ፡ ረሃቤን ፡ ጥቃቴን መች አጣኸው? ይኸውና ፡ ያ ርጉም ፡ አፈር አባቱ ይብላና ፡ የወር ቀለቤን ከለከለኝ ። ረሃብ ሊገድለኝ ነው ። ለወረዳውም ባመለክት ፡ 'ለዕድራችሁ ዳኛ ያመልክቱና በዚያው በኩል ይጨርሱ እንጂ ፡ እኔን አሰልችቶኛል' ብለው መለሱኝ ። ሴሊቱን ሲዞር ሲጋት አድሮ አሁን እቤት ገብቶ ተጋድሟልና ፡ አስጠርተህ ጠይቅልኝ ። ረሃብ ልሞትልህ ነው" አሉና ፡ እንደገና የደረቀ ወገባቸውን እያንቃቁ መሬት ላይ ወደቁ ።

"ምነው ከዚህ በፊት በየወሩ ቀለባቸውን አከፍላለሁ ብሎ ከወረዳው ዘንድ ፊርማልዎ አልነበረም!" አሉ አቶ እንደሻው ።

"አዎ ፡ ፊርማ ነበር ። ዛሬ ከለከለኝ ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ስንት ጊዜ ሆነዎት ከተከለከሉ?"

"ሁለት ሳምንት ወለፈው?"

"እባክዎ አቶ ይመር፣ ልጅ ይላኩና ይህንኑ ሰው ያስጠሩት" አለ መቶ አለቃ።

አቶ ይመር፣ በታከተና በሰለቸ ሁኔታ ሽማግሌውን እየተመለከቱ፣"እርሱምኮ ቢጠራ ዋጋ የለውም። ለኔም በበቀደምለት ራሳቸው ነግረውኝ ልጃቸውን ጠይቂው ነበር። እርሱ እሚለው፣ 'ቤት ሰጥቻቸው፣ በሚገባ ይገዟቸው ለመኖር ሙሉ ፈቃደኛ ነኝ። ግዴታዬም ነው። አባቴ ናቸውና መጦር አለብኝ' ብሏል። 'ግን እርሳቸው እየዞሩ መለመኑን ይተዉ፣ አያዋርዱኝ። እርሳቸውን ለመጦር የሚቸግረኝ አይደለሁምና፣ በዚህ ነገር አግልዱኝ። ያለ ዚያ እንድ ቀን የነደደውን እንጀቴን ቅቤ ጠጣዋለሁ' ነው የሚለው። እርስዎ ምናለበት ይህን ልመና ቢተዉ? ማረፊያ ቤት ሳያጡ በልጅዎ ቤት ተከብረው ቢቀመጡ ምን ቸገረዎ?" አሉዋቸው።

"እንደዚህ ያለ ራሱን የቻለ ማለፊያ ልጅ እያለዎ፣ ምናለበት ሠፈሩንም ሆነ ዕድሩን ባያሰድቡ? የልመና ገንዘብ ምን አስወ ደደዎ?" አሉ እንደሻው።

"እኔኮ እምለምነው አያቴ ለተከሉት፣ አባቴ ለተሸሙበት ቤተክርስቲያን ማሳደሻ የሚሆን ዕርዳታ ለማግኘት እንጂ ለሆዴ አይደለም—" ብለው አቶ መርጊያ ተናግረው ሳይጨርሱ፣ አቶ እንደሻው በድንገት ያቋርጧቸውና፣

"የእርስዎ ቤተክርስቲያን የሚታደሰው በመርካቶ ጠጅ ቤት ነው?" ብለው አፈጠጡባቸው።

"እዚያማ እምሔደው ዕቁብ ልጥል ነው። ዕቁብ አለችኝ" አሉና መርጊያ ዐይኖቻቸውን አሰለመለሙ።

"እኛን አይደለም ማታለል! እንተዋወቃለን። እስቲ እውነት ከሆነ የሚታደሰው ቤተክርስቲያን አለቃና ጭቃ ይህንኑ አጋረግጠው ይጸፋልን? እውነት ሆኖ ከተገኘ፣ እኛም ሁላችንም

t.me/OLDBOOKSPDF

ለልመናው አብረንዎት በተሠማራን ! ደግሞስ ስንት ጊዜዎ ነው ልመና ከጀመሩ ? እኛ እንኳ ስናውቅ ይኸው አምስት ዓመት መሆኑ አይደለም ? እና ልጅዎንም እያሳፈሩት ። 'ትዳር ካማረህ አባትህን ከልመና አውጣና እንገባለን' እያሉ ሴቶቹ መላ ቂያ አድርገውኛል እያለ ነው የሚያዝነውና ልመናውን ያቁሙ ። ያለዚያ ለእርስዎም ፣ ለልጅዎም አይበጅም'' አሉ ይመር ፣ በሽማግሌው ልጅና በእርሳቸው ላይ የነደደውን ቁጣ በሽማግሌው ለማኝ ላይ ሊወጡት እየፈለጉ ።

''እኔ ብለምንስ ብቻዬን አልበላው ! እርሱም ቤት እሠራለሁ እያለ የወር ወጪ እየከለከለ ፣ ከወር ወር የሚያርሰው በኔው እጅ ነው'' አሉና አጉረመረሙ ።

''ያም ሆነ ይህ ፣ እኛ ምንም ለማድረግ አንችልም ። ልጅዎ ከኔ ጋር ይሁኑና ልጡረዎ ሲል ፣ እርስዎ እየለመንኩ እኖራለሁ አይደል የሚሉት ?'' አለና መቶ አለቃ ፣ ጥያቄያዊ ትችት ሲሰነዝር ፣

''ከሱ ቤት ገብቼ የነረዶቹና የውሾሞቹ መዘባበቻ አልሆንም ። በገባው ውል መሠረት ቀለቤን ይስጠኝ'' አሉ ድርቅ ብለው ።

''ልመናውን ይተዉና እናሰጠዎታለን'' አለ ፣ መቶ አለቃ ።

''እሺ ፣ አሁን የቤቱን ኪራይ ይክፈልልኝና ይተወው'' አሉ አዛውንቱም ፣ እንደ መቆጣት እያቃጣቸው ።

''ማለፊያ ነው ። እንግዲህ የዕድርተኛው ጠቅላላ ስብሰባ ስለሚደረግ ፣ ያን ጊዜ ይምጡና ፣ ልጅዎንም ከሕዝቡ ፊት አዋርደን ቀለብዎን እናሰጥዎታለን ። እስተዚያው ከለመኑት ገንዘብ ላይ የቤት ኪራይዎን ይክፈሉ'' ብሎ የመቶ አለቃ አሰናበታቸው ።

ወጣቱዋ ሴትም ፣ ቀጥላ ቀረብ አለችና እጅ ነሥታ ቆመች። በአለባበሱዋና በሁኔታዋ ፣ በደኅና ኑሮ ላይ እምትገኝ መሆኑዋን ለማሳየት ሆን ብላ ተጣጥራበት የወጣች ትመስላለች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ወደኛ ነበር የመጣሽው ?" አለ መቶ አለቃ ፣ ዐይናቹን ሰፍጥጦ ።

"አዎ!" አለች እሷም ፣ ዐይናቿን እያስለመለመች ።

"ምን ነበር ጉዳይሽ ?" ከማለቱ ፣ አቶ እንደሻው ንግግራቸውን ጣልቃ ያስገቡና ፣

"እረግ! እረግ! ዘንግቸኩ ነው ። እንደምን ሰነበትሽ ፣ አቴ ወዳጄ! አየሀ መቶ አለቃ ፣ ጉዳዩዋን ችግሩዋን ቀደም ፣ብላ ደጋግማ ነግራኛለች ። ባሏ አስቸግሯት ነው ። በእርግጥም ተበድላለች ። ታዲያ ብቻዬን ጠርቸ እንዳላነጋግረው የሠፈራችን ስም አያምርምና በሌላ ነገር እንዳይተረጉመው ብዬ ነው ፤ ሁላችንም ባለንበት መጥተሽ ጉዳይሽን ተናገሪና ሽማግሌዎቹ ጠርተው ይቆጡልሻል ብያት ነው አመጣጡዋ ። ባሏን ዐወቅኸው? አቶ ግዛው ነው ይኸ አስተማሪው" አሉ ።

"ባልሽ ምን በደለሽ?" አለ ፣ መቶ አለቃ ።

"ሁሉንምኮ ለእርሳቸው ነግሬያቸዋለሁ" አለች ወጣትዋ ሴትዮ አንገትዋን ወደ አቶ እንደሻው እያሰገገች ።

"ግዴለሽም ተናገሪ ። ከሽማግሌ የሚደበቅ ነገር የለም ፤ አይዞሽ ። በደልሽን የምታውቂው እኔች አይደለሽ ?" አሉና እንደሻው ፈቃድ ሰጡዋት ።

"እያመሸ እየጠጣ አስቸግሮኛል ። ከቤቱ እንዳልወጣ ሕፃን ልጅ አለኝ ። ደግሞም ያመጣኝ ከሀገር ቤት ነው ። እዚህ ከተማ ውስጥ ዘመድ እንደሌለኝ ፣ መሐጅ እንደሌለኝ ፣ አገሩን እንደማላውቅ ስለሚያውቅ መጫወቻ ነው ያደረገኝና ፣ 'ለዕድሩ ሽማግሌዎች ዛትናገሪ እነሪሱ ልክ ያስገቡታል' ብለው ጐረቤቶች ስለመከሩኝ ነው የመጣሁት" አለች እንባዋን እያረገፈች ።

"የወር ወጭሽንስ ይሰጥሻል?" አለ ፣ መቶ አለቃ ።

"አዎን! እሱንስ ቀንሶብኝ እንኳ አያውቅም ።"

"ውጭስ ያድራል?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እያ!"

"ሰክሮ መጥቶስ ይመታሻል?"

"እያ! እንኳን መማታት ነፉ ነጣርም አያውቅ።"

"ታዲያ በደሉና ጥፋቱ ከምን ላይ ነው?"

"እህ፣ ከማምሸቱ ላይ ነዋ!"

"ታዲያ የወር ወጪ ካላንያለ፣ በዋለበት ካላደረ፣ ሰክሮ ካልተደባደበ፣ ምን አለበት ከጓደኞቹ ጋር፣ ከዘመድ ጋር ሲጫወት አምሽቶ ከመጣ፣ ምን ችገረሽ?" አላት፣ መቶ አለቃ።

"ለምን ብዬ፣ ለማን ተብሎ! እፍታ እፍታውን የትም እየጨረሰ እየመጣ እኔ በደረቁ እምደርቀው?" አለች፣ ደረቷን በቡጢ እየደቃች።

ሽማግሌዎቹ ዘወር፣ ዘወር ፈገግ፣ ፈገግ ሲሉ፣ መቶ አለቃ ከበደ ሲተናነቀው የነበረውን ሣቅ እየዋጠ ቆዩና፣

"በይ፣ በደልሽን ተረድተነዋል። ባልሽን ጠርተን እንቆጣልሻለን። ከዚያ በኋላ ቢያስቸግርሽ እንቀጣልሻለን። ቅድም እንዳልሽው ልጅሽንና ቤትሽን ነው ማየት። አይዞሽ! ግዴለሽም፣ ሁሉንም ትጠግቢዋለሽ። እረ ትለለችዋለሽ" አላት።

ወጣትዋን አባብሎ ወደ ቤቷ ለመመለስ በመገፋፋት ላይ እንዳለ፣ ሌሎቹ ሽማግሌዎችም ወደየቤታቸው ለመሔድ መንገድ መንገዳቸውን መመልከት ሲጀምሩ፣ መምሬ በዕውቀቱ ጭራቸውንና እግሮቻቸውን እኩል እየወረወሩ ከተፍ አሉ። የመስቀሉና የእጅ ሰላምታው ከተከናወነ በኋላ፣

"ምነው? የዛሬው ድግስ ተስካር ነበር ወይስ ዝክር?" አሉ አቶ እንደሻው፣ ወደ ቤታቸው ለመሔድ የነበራቸው ችኮላ በመምሬ መምጣት በመደናቀፉ ብሽቅ ብለው።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እረ እንደሚሉት አይደለም ። አባትና ልጆች ተጣልተው እቆጣለሁ ብዬ ሔጄ ነገሩ አላልቅ ብሎኝ ነው የዋልኩት" አሉ እየተቀመጡ ።

"ዕድርተኞቻችን ናቸው ?" አለ ፣ መቶ አለቃ ።

"እሀ ፣ ዕድርተኞቻችንማ ቢሆኑ ኑሮ ፣ 'ሩጠው እዚህ ነበር ከቸች እሚሉት" አሉ መምሬ ።

"ታዲያ ፣ አገር ላገር እየዞሩ ማንንም 'አስታርቃለሁ' እያሉ ውለው ፣ አሁን ልንሔድ ስንል መምጣትዎ ለምን ነው ?" አሉ እንደሻው ፣ የዕለቱ ብርጭቆ ትዝ እያላቸው ።

"እንዴ ፣ ዘመድ ወዳጅ ፣ አብ ልጅ ሲቸገር ፣ የሠፈሬ ነዋሪ ዕድርተኛ ካልሆንክ አልመጣም ይባላል ?" አሉ መምሬ ፣ ያካ ባቢውን ዝንብ የሚራ ቄደ እየለቀቁበት ።

"ለመሆኑ አባትና ልጆች በርስት ነው በሀብት የተጣሉት" አለ መቶ አለቃ ፣ ሁለቱን ተነታራኪዎች ለማስታረቅ ብሎ ።

"እረ አያድርስ ነው ፣ ልጄ ! በርስት ፣ በሀብትና በንብረት መጣላትማ የቆዩ ነው ። የእነዚህስ ተሰምቶ የማያውቅ ጉድ ነው ።"

"እሀ ፣ መቶ አለቃ ሲያመጣው ከነበረው ጉድ ይብሳል እንዳይሉን" አሉ እንደሻው ፣ እያባጩ ።

"እንዴ ! ምንና ምን አገናኝቶት ?"

"የርስም ይብሳል ?"

"መቸም ፣ ቄስና ፖሊስ የማይለማው ጉድ የለም ። እስቲ ይንገሩን" አሉ ይመር ።

"እንዲህ ሆነላችሁ" ብለው መምሬ ጉዳቸውን ለማውራት ሲጀምሩ ፣ ሁሉም ከፈዘዙበት ነቃ ነቃ አሉ ።

"አባት ፣ የአምስት ልጆቻቸው እናት የነበሩ የብዙ ዓመታት ባለቤታቸው ይሞታሉ ። ወርባቸውም ከዐሥር ቀን በኋላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው ። ታዲያ ለዐርባቸው መታሰቢያ እንዲሆን ተብሎ የሴት ዮዋ የሕይወት ታሪክና የኃዘን እንባርጉሮ ፣ እንደዚሁም የጥሪ ወረቀት እንዲታተም ሲባል ጊዜ ፣ ሰውዬው 'የኔ ስም ከእን ጉርጉሮውም ላይ ሆነ ከጥሪው ወረቀት ላይ አይገባም ። በራሳ ችሁ ፣ በእጎቶቿና በወንድሞቿ ስም አሳትሙ' ብለው እምቢ ብለው ተቸግረን እርፍደን ነው ።''

''ይህስ እውነትም የጉድ ጉድ ነው ። በምን የተነሣ ነው ? ከሚስቱ ስም ጋር የኔ ስም አይጻፍም የሚሉ ? ትጠራኛለች ብለው ነው'' አሉ ፣ እንደሻው ።

''እርሳቸውማ እሚሉት ፣ ከተጋባን ጊዜ ጀምሮ ጤና ሰጥ ታኝ አታውቅም ፣ እንደ ተነዛነዝን ነው የኖርነው ። በሽማግሌ ዎችና በልጆች አስገዳጅነት ነው የኖርነው ።ከሠላሳ ዓመት ውስጥ በቀን ተሣሥቀን የታየነው ሰዓት ቢቁጠር ሳምንት አይሞላም ። እንዲያውም እርሷ ቀደመችኝ እንጂ ፣ እኔማ ፣ ከመቃብሬ ላይ እንዳትቆም ፣ ንብረቱንና ሀብቱንም ትልቁ ልጄ ተረክቦ በርሱ ኃላፊነት ሁሉም ይተዳደሩ ፣ ድርሻቸውን ፣ የእርሷንም ሞምር እርሱ ያካፍላቸው እንጂ ፣ እርሷ እንዳትደርስባቸው ብዬ ተና ዝሬ ነበር ። አሁንም ቀድማኝ ከሐዲች ፣ 'የእርሷ ስም በተጻፈበት ወረቀት የኔ ስም አይጻፍም' ብለው ነው ያስቸገሩን'' አሉ መምሬ በደከመ ስሜት ።

''ታዲያ መጨረሻውስ ምን ሆነ እሺ አሉ ?''

''እረ አልተነኩም ! እንዲያው ሌሎች ሽማግሌዎች ደግሞ ጨምረን ነገና ከነገ ወዲያ እንሞክራለን ብለን ነው እንጂ እር ሳቸውስ ጸንተዋል ።''

''እስቲ ከሞቱላቸው በኋላ እንኳ ይቅር ቢሉዋቸው ። ምንስ ቢሆን ሠላሳ ዓመት ባንድነት ኑረው ወልደው የለ?'' አሉ እን ደሻው ።

''አይ ፣ እንዲያው ለስሙ ያህል ተጋቡ እንጂ ፣ እኗኗራ ቸውስ ኑሮም አልነበረ ። ሰውዬውም በየጊዜው በሥራ ምክንያት በየአገሩ ሲዞሩ ነው የኖሩ'' አሉ ፣ መምሬም እየተከዙ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ግሩም ነው ! ከኛ ሠፈር የሚበልጥ ጉድ የሚፈላበት የጉድ ሠፈርም አለ ለካ" አለና የመቶ አለቃ ከበደ ፣ ሽማግሌ ምቹን አንድ ባንድ ተመለካከቶ ፣ "እንግዲህ ዕድርተኛውን መች እንሰብስበው ?" ብሎ ጠየቀ ።

"የማነኛውን ዕድር ?" አሉ ፣ አቶ እንደሻው ።

"ያኛውን የወዲያኛውን ፣ ማለት የነወይዘሮ ላቀችን ።"

"ያኛውን ዕድርኮ ለመሰብሰብ አልተቻለም ። እየነገርኩህ ? ምን ማለትህ ነው ? ወይዘሮ ላቀች ካልፈቀዱ ዕድርተኛ መጥራት አንችልምኮ ? ያቶ ንጉሤን ንግግር ከልብህ አላዳመጥ ካቸውም እንዴ ?" አሉት ፣ አቶ እንደሻው ።

"ታዲያ ዕድሮቹ እንደ ተለያዩ ሊኖሩ ነው ?" አለ መቶ አለቃ በምሬት ።

"እንግዲህ ሁለቱ ዕድሮች አንድ ሊሆኑ የሚችሉት ሠፈሩን ፣ እንዲያው ቦታውን ፣ አጠቃሎ አንድ ሰው የያዘው እንደ ሆነ ነው ። ያለዚያ የኛ ድካም ፣ ውሃ ቢወቅጡ እምቦጭ ነው" አሉት እንደሻው ፣ ተስፋ በቆረጠ ስሜት ።

"እንዲያው በእነርሱ የተነሣ ፣ ሠፈሩና ዕድሩ እንደ ተለያየና እንደ ተበጣበጠ ሊኖር ነው ?" ብሎ የመቶ አለቃ ሠፈሩን በጉጉት ሲመለካከት ፣ ወዲያው በሠፈሩ ውስጥ ኡኡታ አስተጋባ ።

"ደግሞ ምን ጉድ ተወልዶ ይሆን ?" አሉ ይመር ።

"አንዱ ሞቅ ብሎት አመሻሽቶ የገባ ፣ በማምሸቱ አኩርፋ ፊቷን አዙራ ፣ ጉልበቷን አቅፋ አድራ ፣ በጥዋት ተነሥታ የሽሮ ፍትፍት ላትሰጠው ቤተክርስቲያን ሐዳ ፣ እግረ መንገድዋን ወደ መንደር ጐራ ብላ ፣ ቡናና ቅራሪ አደባልቃ የተመለሰች ሚስቱን እየነረተ ይሆናላ !" አሉ እንደሻው ።

"እረ ኡኡታው የባልና የሚስት ድብደባ ብቻ አይመስልም" አለ መቶ አለቃም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ወዲያው አንድ ጐረምሳ ከሠፈሩ እየሮጠ ሲወጣ ፣ ሴቶች "አ-አ !" ሲሉ ፣ ወንዶች ፣ "ያዘው ፣ ያዘው ፣ ሰው ገድሏል ያዘው" እያሉ ሲከታተሉት ፣ መቶ አለቃ ከበደም ወደሚሮጠው ሰውዬ ሲሮጥበት ፣ ሌሎች ሰዎችም በየአቅጣጫው ብቅ ብቅ ሲሉበት ፣ ያ ሲሮጥ የነበረ ሰው ካንድ ሰፊ ግቢ ገብቶ በአጥር ዘሎ ሊወጣ ሲሞክር ተያዘ ።

"ምንድን ነው ነገሩ ?" አለና መቶ አለቃ ከአባራሪዎቹ እንዱን ጠየቀ ።

"ሰው ገድሎ ነው ፣ ሰው ገድሎ ።"

"ማንን ነው የገደለው ?"

"ታናሽ ወንድሙን በጩቤ ዘክዝኮ ገደለው ።"

"በምን ምክንያት ተጣሉ ?"

"በሴት ፣ በርስትና በገንዘብ ከተጣሉ ብዙ ጊዜያቸው ነበር ።"

"የባሰ የጉድ ጉድ ተወለደ" አለ መቶ አለቃ ።

በበነጋው ፣ መቶ አለቃ ከበደ ከቤቱ ተጠርቶ ተወሰዶ ፣ ላይመለስ ቀረ ።

ለአንድነታቸውና ለልማታቸው ሲጣርላቸው የነበሩት ዕድሮች ጉዳይ ፣ ውሃ ላይ እንደ ተጣለ ኩበት መዋለል ብቻ እየሆነ ሔደ ። ዕቃዎቹ እያረጁ ፣ እየጠፉና እየተሰባበሩ ፣ ዕድርተኞቹ በሚያርሱባቸው ችግሮች የዕድሮችን ድጋፍ ለማግኘት ባለመቻላቸው በይበልጥ እየተቸገሩ ሔዱ ። ሌላው ቀርቶ ከዕድርተኞቹ መካከል ሲሞት ወይም ሬሳ ከቤቱ ሲወጣ እንኳን ፣ ኃዘኑ ተሞቹን የሚቀበልበት ድንኳን ለማግኘት የማይቻል እየሆነ ሔደ። ድንኳኖቹም ቢሆኑ ከአያያዝ ጉድለት የተነሣ ተቀዳደዋል ። በጥርና በሚያዝያ ወራት ደማሞ ፣ በየሠርጉ ቤት ይጐተታሉ ፣ ለዕድሮቹ ኃላፊዎች የኪራይ ገቢ ያስገኛሉ ፣ በሁለት ቀን ሃምሳ ብርና ከዚያም በላይ ገቢ ቀላል አይደለም ። ሌላዎቹም ዕቃዎች እንደዚሁ ። ታዲያ ፣ ይህ ሁሉ ተደራራቢ ጥፋት የደረሰባቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

ዕድርተኞችም ባለርስቶቹና የዕድሮች ሽማግሌዎች እንዳይነቁ ባችው እየተጠነቀቁ ወደ ጉረቤት ዕድሮች ለመኮብለል ተገደዱ ።

ይሁን እንጂ ፣ የኮበለሉትም ሆኑ ያልኮበለሉት ዕድሮች የየወሩን መዋጮ ቀጥ ብለው ይከፍላሉ ። በተለይማ ወይዘሮ ላቀች በዚህ ጉዳይ በጣም ጠንቃቃ ነበሩ ። የየወሩን መዋጮ ከነመቀጫው ማነኛውንም ዕድርተኛ ጋማውን እንቀው ነበር የሚያስከፍሉት ።

ዕድሮቹ ፣ እንደዚያ ሆነው ተዝረክርከው በነበሩበት ወቅት የአንድ ዕድርተኛ ልጅ ከምሶሶው ሥር ተወታትፎ የነበረ የኤሌክትሪክ ሽቦ ይዞ ሲጐትት ፣ የኤሌክትሪኩ ኃይል አደንዝዞ ገደለውና ፣ ለቀብሩ በቤተ ክርስቲያን በተደረገው ሥነ ሥርዓት ላይ ቄሱ ለማሳረግ ከመካከል ቁመው ሲያጨበጭቡ ፣ አቶ እንደሻው ቄሱን ይቅርታ ጠይቀው ከመካከል ገቡና ፣ "እባካችሁ አንድ ጊዜ አዳምጡኝ" ብለው ደጋግመው ሲጮሁ ፣ የተሰበሰበው ሕዝብ ጸጥታውን ከለገሣቸው በኋላ ፣ "ሰማችሁ ፣ ወንድሞቼ ! ለደስታችንም ለኃዘናችንም ይረዳናል ፣ ይደርስልናል ብለን ያቋቋምነው ዕድር ከምን ደረጃ ላይ እንደ ደረሰ በሚገባ የምታውቁት ጉዳይ ነው ። ከዚህ ቀደም ሁለቱን ዕድሮቻችንን አንድ እንድናደርጋቸው ተስማምተን ፣ እኛም ደንቡን አሻሽለን እንድናቀርብ ተመርጠን ነበር ። ነገር ግን ይህን እንዳናደርግ ተከልክለናል ። 'ሁሉን ቢናገሩ ሆድ ባዶ ይቀራል' እንደሚባለው ነውና ፣ አሁን ጉዳዩን ሁሉ አልዘረዝርም ። በየወሩ የምታዋጡትንም ገንዘብ እነማን እንደሚያዙበት የምታውቁት ነው ። ሁለቱን ዕድሮች አንድ ለማድረግና ለማሻሻል ቀርቶ ፣ እያንዳንዳቸውንም እንደ ነበሩ ማስተዳደር አልተቻለም ። ለሁለቱ ዕድሮች ብቻ ሳይሆን በነጂኔራል ፣ በነቢትወደድና በነደጃዝማች ርስት ላይ የሠፈሩት ዕድርተኞች ጭምር አንድነት እንዲኖረን ከልቡ ሲጥርበት የነበረው ወንድማችን የመቶ አለቃ ከበደም ፣ ያውም እንደ ደረሰበትና ምን እንደሆነ ሁላችሁም ታውቃላችሁ ። የቀረነውም ብንሆን ዕድርተኛውን ለመስብሰብ ቀርቶ ፣ ራሳችን ሽማግሌች የተባልነው እንኳ ለመገናኘትና ለመሰብሰብ አላመቸንም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለዚህ ፣ በጠቅላላው ስለ ዕድራችን ለመነጋገር ፣ ማለት 'እናፍርሰው' ወይም 'እናሻሽለው የምንል እንደሆነ ለመነጋገርና ለመወሰን ከዛሬ የተሻለ አጋጣሚ ስለማናገኝ ፣ አሁን አባታችን ከአሳረጉ በኋላ ፣ እዚሁ ቆይተን ነገሩን ፍርጥርጥ አድርገን እንድን ነጋገርበትና ዕልባት እንድናደርግበት አደራችሁን እላለሁ'' አሉና ተማፀኑ ።

ጸጥ ረጭ ብሎ የነበረው ዕድርተኛ ሁሉ ጉርምርምታውን ሲያስተጋባ ፣ ቁሱም እያጨበጨበ ፣

''በሉ እባካችሁ ጠጥታ ፣ ጠጥ በሉ !'' ሲሉ ፣ ቀባሪው ሁሉ ከአቶ እንደሻው የላቀ ጸጥታ ለጣሳቸው ።

''ይኸ ጨቅላ ፣ ገና በአንድ ፍሬነቱ ፣ ሀሥር ዓመት እንኳ ሳይሞላው የተቀሠፈው በኛ ኃጢአት ነው ፣ በኛ ሥራ የተነሣ ነውና ፣ እባካችሁ ከልባችሁ ተመለሱ ። እኛ የሠራነው ኃጢአት ነው ይህን ጨቅላ የቀሠፈው'' እያሉ ሲሰብኩ ፣ ፈንጠር ብለው በአንድነት ችምችም ብለው ከነበሩት ዕድርተኞች አንዱ ፣ ''እሀ ምን ይላሉ እኒህ ቄስ ? ኤሌክትሪኩን የሠራው ፈረንጅ ፣ ገመዱን እዚህ ድረስ ጐትቶ የዘረጋው መብራት ኃይል ፣ ሽቦውን የጐተተው ራሱ ላጁ ? እኛ ምን አጠፋን ? ደግሞስ ሰው ሁሉ ለሠራው ኃጢአት ይኸ ሟች ልጅ ብቻ የሚተጣበት ምን ምክንያት ይኖራል ?'' ሲል ፣ አብረውት የነበሩት ሰዎች ሳያስቡት ሣቅ ያፈነዳቸውና ፣ ሰው ሁሉ ዘወር ዘወር እያለ ሲያያቸው ፣ ቁሱም ሞጭሚቴ ዐይኖቻቸውን አፍለቁባቸውና ፣

''አሁን ምን እየተነገረ ነው እዚያ እምታሽካኩት ? ይህም ቅሥፈት ነው ፣ ጥጋብ ነው ፣ ልባችሁን ነሥቷችሁ ነው ። ሁላችሁ ብትተነፍሱ እገዝታችኋለሁ'' ብለው አስፈራሩና ፣ የሰዓቱን ሰብከት አሰምተው ሲያሳርጉ ፣

''ዕድሩ የፈለገውን ያህል ይቅጣኝ እንጂ ፣ ሁለተኛ እዚህ አልደርስም'' አለ ፣ ያ ፎታች ዕድርተኛ ።

''ለምን ?'' ብሎ ጠየቀው ጓደኛው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴ ፣ ጨርሶ ሊገናኝ የማይችል ነገር እያገናኙ የሚ ወርፉ ቄስ ካሉበት ቦታ ምን ላደርግ ? ሊሆን ሊሆን ፣ ሊመ ስል ሊመስል የሚችል ስብከት ሊያሰሙን ሲችሉ ፣ እንዲያው የማይቀራረብ ፣ ጨርሶ ሊገናኝ የማይችለውን ነገር የግድ እያላ ተሙ መናገር ምን ያደርጋል ?''

የቀብሩ ሥነ ሥርዓት የተከናወነው እኩለ ቀን ላይ ነበር ። በዚያን ጊዜ በሠፈር ውስጥ ሰው ከሞተ ፣ ከመሥሪያ ቤት ሥራና አለቃ ይልቅ የዕድር ደንብና ዳኛ የኮለበቱበት ወቅት ነበርና ፣ ይህንኑ ምክንያት አድርጐ ሙሉ ቀን ከሥራ መለየት የተዘወተረ ነበር ። ታዲያ ግማሹዋን ቀን ፣ ለግል ጉዳይና ፍላ ጐት ማከናወኛ ለማድረግ ሲባል ፣ ሬሳ አሳድሮ መቅ በር እየተዘወተረ ሔዶ ነበር ። በዚያች ዕለትም ገሚሱን ዕድር ተኛ ተመለከከተው ያሰቡት እንዳልሆነላቸው ተረድተው ፣

''የኛ ዕድር ነዋሪ እናንተ ብቻ ሆናችሁ ? ይሽውና ጉዳዩ ጉዳያችን አይደለም ብሎ ነው ፣ ያ ሁሉ ዕድርተኛ ጥሎን የሔደው ? ይሰማኛል ፣ ዐውቄዋለሁ ፍርሃት ነው ። ባለርስቶች የሰሙብን እንደሆነ ይጣሉናል ተብሎ ተፈርቶ አይደለም ?እን ግዲህ በሉ እሰቲ ፍርድ ሰጡ ። ያንድ ዕድር ሕዝብ የፈራውን ጣጣ እኛስ ምን በወጣን እንጋፈጠዋለን ? በሉኮ ፍርድ ሰጡ! እኔ እንግዲህ የለሁበተም ። ከዛሬ ጀምሮ ሠፈሬን እለውጣለሁ ። ከዕድራችሁም ወጥቻለሁ ። የምገባበት ቤት የሚቸግረኝ አይደ ለሁም'' አሉ ፣ በየወረዳው ቤቶች ኑሚያከራዩ በመሆናቸው ፣አን ዱን ተከራይ አባረው ለመኖሪያት የማይሰናቸው መሆናቸው ፣ በሚ ያረጋግጥ ስሜት ቁምር ታጅበው ።

ዕድርተኞቹ ፣ ትርጉሙ ያልታወቀ ወይም አዝማሚያው ያለየለት ጉርምርምታ በማሰተጋባት መልስ ሰጡዋቸው ። እርሳ ቸውም ሁለት ሦስት ጊዜ አጨብጭበው ሹክሹክታውን ፣ ጉሽ ሚያውንና መተረማመሱን ጉቱትና ፣

''በሉ እንግዲህ ፣ የሚበጀውን አድርጉና ወደየምንሔድበት እንሒድ - ዝናቡ ሳይጥል'' አሉ ፣ የተንጠለጠለውንና የጠቋቆረ ውን ደመና በየአቅጣጫው እየቃኙ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ ጊዜ ፣ የቤተ ክርስቲያኑን ግንብ ተጠግተው ቆመው ከነበሩት መካከል- ያ ፎታች ዕድርተኛ ወደፊት ራመድ አለና ፣

"ዕድርተኛው ቢፈራ አያስወቅሰውም ። እናንተስ በሠፈራችን ውስጥ ለመስብሰብ ባለ ርስቶችን ስለ ፈራችሁ አይደለም እዚህ የያዛችሁን ?" አለ ።

ቀጥሎ ደግሞ ሌላው ዕድርተኛ ፡

"እናንተው ናችሁኮ ዕድርተኛውን ከባለርስቶቹና ከወክ. ሎቻቸው ጋር ያናከሳችሁት" አሳቸው ።

"እናንተው በሴትም በምኑም እርስ በርሳችሁ ያመጣች ሁት ፈተናኮ ነው ፣ ከኛ ላይ ያረፈውና ይህን ሁሉ መዘዝ ያመ ጣብን" አሉ ፣አንዲት ጠና ያሉ ዕድርተኛም ።

አቶ እንደሻው ፣ አቶ ይመርና ሌሎችም ሽማግሌዎች እን ዲህ እያሉ ከዕድርተኞቹ ጋር ሲወዛገቡ ፣ "እምዬ! አናቴ! እኛን ለማን አደራ አልሺን ?— ወይኔ ፍቅሬን ተነጠቅሁ ፣ አብሮ አደ ጌን ተቀማሁ ፣ ዛሬ ተጋለጥኩ !—ልጆችሽንና እኔ ፣ ለማን አደራ አልሺን ? ትዳሬ ፈረሰ ፣ ቤቴ ተዘጋ! "በሚሉ ኃዘተኞች የታጀበ ሬሳ ከተፍ አለ ።

እነ አቶ እንደሻውና ዕድርተኞቻቸውም መሣሪያቸውን ገት ፋው ከየተቀመጡበት ተነሡና ፣ ጉንጭ ጉንጫቸውን በነጠላ በጋቢና ፣ በኩታ ጠርዝ እሽት እሽት አደረጉ ፣ ነጠላ ያልለበሱት ደግሞ በሁለት እጆቻቸው እነክ እነክ እያደረጉና እጅ እንደ መንሣት እያሉ አዲስ ደራሹን ሬሳ ተቀብለው ፣ ለደቂቃዎች ያህል በዝምታ ተሸብበው አሳለፉት ። ወዲያውም ስለ ኃዘንተኞቹ ልጆችና ስለ ሟችቷ ባል የየበኩላቸውን ኃዘን ገለጡና ተቀመጡ ።

"ይኸው ነው መጨረሻችን" አሉ አቶ እንደሻው ፣ "ለዚህ አይደል እምንፋጅው ? እንዲህ ጥለነው ውልቅ ለምንለው ዓለም አይደል ፣ ዘወትር የምንናከሰው ? እስቲ እነዚያ ልጆች አያሳዝ ኑም ? ባልየውስ ቢሆን ? አላያችሁትም በኃዘን ከሰል መስሎ ? እንግዲህ ይኸ ሰውኮ በቃው ፣ ኑሮው ጨለመ ማለት ነው ።የሚ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደርስበትን ሥቃይ እስቲ አስቡት ? 'የእናትና የሚስት ሞት እያ ደር ያንገበግባል' እንደሚባለው ይህ ሰው እንግዲህ ሴላ ሴት ለማግባት ቢያንስ ቢያንስ ሦስትና አራት ዓመት መቆየት ግዴ ታው ነው ። ያውም ደግሞ ያገኘ እንደሆነ ! የተፈቀደለትም እን ደሆነ ። ሚስት በመብራት ትመሰላለች ። መብራት የሌለበት ቤት እንደሚጨልም ሁሉ ፣ ሴት የሌለችበት ቤትም እንደዚያው ነው ። ስለዚህ 'ያንደኛዋ ሬሳ ሲወጣ ፣ ሁለተኛዪቱ ሚስት ፈጥና ትግባ ' እያሉ የሚመስሉ አንድ ዐዋቂ የሆኑ አቶ ዘይኑ የሚባሉ ወዳጅ አሉኝ ። ሁልጊዜ አስታውሰዋለሁ ። ትልቅ አባባል ነው " ብለው አቶ እንደሻው ሲናገሩ ፣ አቶ ይመርም ቀበል አደረጉና ፣

"ሴላም ታሪክ አለልዎት እንጂ ! አንድ አቶ ኑር የሚባሉ ነጋዴ ለንግድ ጉዳይ ወደሴላ አገር ከርመው ወደ ቤታቸው ሲመ ለሱ ፣ ሚስታቸው ሙተው ሲለቀስ ይደርሳሉ ። ታዲያ በዚህ ጊዜ ፣ 'አላህ ሞኝ ብታገኝ ምን ልታደርግ ነበር ? 'ብለው ወደ ሁለተኛዪቱ ሚስት ቀጥታ ሔዱ ይባላል" ብለው ተናገሩ ።

"እንዴ ! እነዚህ ሰዎች ምን ነካቸው ? ከየት ወደየት ነው የሚሔዱ ? የቅድሙን ቄስ አሁን ማን በጠራቸው ?" አለ ያ ፎታች ዕድርተኛም ፣ ቀስ ብሎ ።

"በሉ እንግዲህ ፣ ወደ ጉዳያችን እንመለስና የሚሆነውን አድርጉ" አሉ እንደሻው ።

"እንዴ ! እንዲህ በችኮላ ምን የሚሆን ነገር አለ ? ሴላ ቀን ይለወጥና ዕድርተኛውን በሙሉ ሰብስበን እንነጋገርበት እንጂ" አለ ያ ፎታቹ ዕድርተኛ ።

"አሄሄ ! ዛሬ እዚሁ እየለፈለፍኩ ፣ እየሾለከ የጠፋ ሕዝብ ነው ፣ ሴላ ጊዜ እሺ ብሎ እሚመጣው ? ይልቁንስ ዛሬ የሚሆነውን አድርጉ" አሉ እንደሻው ።

"ዛሬ መቸም የሥራ ቀን ስለሆነ ፣ ሁሉም ጉዳይ ስለማያጣ ነው የሾላለከው ። እሑድ ቀን ሲሆን ግን ፣ ሥራዬ ብሎ ይመ ጣልና ፣ ቀን ይወሰንልን" አሉ አንድ አዛውንት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"በእውነቱ ፣ ሁላችንም በየቤቱ እየዞርን እንነግራለንና ፣ በሌላ ቀን እዚያው ከተለመደው ቦታ እንሰብሰብ" አለ ፣ፎታቼ ዕድርተኛም ።

ጥቂቶቹ ዕድርተኞች ፣ ተመሳሳይ የሆነ ትችት ሲሰነዝሩ እነአቶ እንደሻውም በጥንቃቄ ሲያዳምጡ ቆዩና ፣

"እንተ ወንድሜ ፣ እንደ ፈረንጅ ጠገብህን የከፈልከው ፣ ስምህን ታውሰኛለህ?" አሉ እንደሻው ፣ከግንቡ አጠገብ ቆመው ወደ ነበሩበት ሰዎች አንገታቸውን አስግገው ።

ከተሰገገባቸው ሰዎች መካከልም ጸጉሩን ከፍሎት የነበረው ያ—ትችተኛው ዕድርተኛ ብቻ ነበርና "እኔን ነው?" ብሎ መለሰላቸው ።

"አዎን ፣ አንተን ነው ። ማን ትባላለህ?"

"ሽዋዬ እባላለሁ ።"

"ማለፊያ ። ሽዋዬም ፣ ወሎዬም ፣ ትግርዬም ፣ ጉራግዬም ፣ ጐጅዬም ሁን ብቻ እንደምታውቁት ፣ መቶ አለቃ ስለሌለ ፣ በወረቀት በኩል ተቸግረናል ፣ የሚጽፍልን ፣የሚያቀነባብርልን ተቸግረናልና ፣ ሽዋዬ አብሮን ይሥራ ይርዳን ፣ ሌሎች ሰዎች እስከትመርጡበት ድረስ" ብለው ዕድርተኛውን ጠየቁ ።

"እንዴ ፣ እኔኮ ሥራ ይበዛብኛል" አለ ሽዋዬ ።

"ሥራህ ምንድነው?" አሉ እንደሻው ።

"አስተማሪነት ።"

"እም! አንተማ በስሌትም ጭምር አሳምረህ ትረዳለህ ። እስተዛሬም የነበረን ችግር ይኸው የስሌቱ ጉዳይ ነበር ። ግዴለህም ፣ የኛንም የዕድርተኛውንም ምርቃት ታተርፋለህና እሺ በለን ። ሥራውም አይበዛብህም" ብለው ለመኑት ።

"ዕድርተኛውም ፣ ከእርሳቸው ጋር ተባብሮ ልመናውን ስላስተጋባ ፣ ሽዋዬ ፣ "ከባለርስቶች መቅሠፍት ያውጣኝ እንጂ ፣ በም ችለው ለማገልገል ፈቃደኛ ነኝ" ብሎ እያጉመተመተ ጥያቄውን ተቀበለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ይኸው እንግዲህ ፣ እኛን አላመናችሁን አይደል ! በሉ ሁሉንም ነገር ከዚህ ወንድሜ ትረዱታላችሁ ! ስብሰባውስ ለመች ይሁን ? አሁኑኑ ንገሩኝ" አሉ እንደሻው ።

ከዚያ በኋላ ከዕድርተኛው አንዳንድ ሐሳብ ተሠነዝሮ ፣ ዕድርተኛው ሁሉ በሁለተኛው ሳምንት እሑድ እንዲሰበሰብ ከስ ምምነት ላይ ተደረሰ ።

ዕድርተኞቹ ፣ ስብሰባውን ፈጽመው ወደ የቤታቸው ለመ ሔድ ሲባተኑ ፣ ቀደም ሲል ወደ ቤተክርስቲያኑ የገቡት ለቅ ሰኞች ቀብሩን ፈጽመው ሲወጡ አዩ ። ሆነ ።

አቶ እንደሻው ፣ ከአዲሱ ረዳታቸው ከአቶ ሽዋዬና ከሌሎ ቹም የዕድሩ ሽማግሌዎች ጋር ቆመው ሲነጋገሩ ፣ አንድ አዛ ውንት ቀረብ ብለው ሰላምታ ሰጡዋቸው ።

"ምን እግር ጣለዎ ?" አሉ እንደሻው ።

"ለቀብር መጥቼ ነው ። ቅድም ከሰው መካከል ሆነውብኝ ነው እንጂ አይቸዎታለሁ ።"

"ለቅድሙ ቀብር ነበር የመጡት ? ምነው እስካሁን ቆያ ችሁ ?"

"ሰውን ክፉ ሊሉ የጭንጫ መቃብር ይጭሩ እንደሚባ ለው ሆኖ ፣ ካልሆነ ቦታ ላይ የተጀመረ ቁፋሮ ከፍታቱም ፣ ከሴቱ ችከታም ጋር ሆኖ ትሸሽ ኦቆየን ።"

"ሟችቷ ዕድርተኛዎ ናት ?"

"የለም ፤ የሟች ባል ዘመዶች ጉረቤቶቹ ስለሆኑ አብሬ መጥቼ ነው" አሉ አዛውንቱ ።

"ሟች ምን ሆና ሞተች በወሊድ ነው ?"

"እባክዎ አንድ ያበደ ሐኪም ነው የገደላት ።"

"እሀ ፣ እንዴት እኮ ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ኟች ሆዴን ያመኛል እያለች ስንብታ ፣ ዘመዶቿ ወደ እንጦጦ ነው መሰለኝ ፀበል ወስደዋት ፣ እዚያ ስትጠመቅ ስት ጠጣ ውላ እቤቷ ተመልሳ ትተኛለች ። እና ትደክማለች ። በዚህን ጊዜ ልጆቿ ነገሩን አላወቁ ፣ ወደ ሐኪም ቤት ይዘው ይሔዳሉ ። የተንቀዠቀዠ ፈረንጅ ፣ መቸም ሊማሩብን ነው የመጡ ፣ ሆዷ አብጦ ሲያየው ጊዜ ፣ ' ጉበቷ ውሃ ቋጥሯል ' ብሎ ኦፒራሲዮን ሲያደርጋት ትሞታለች ። የሚያሳዝን ነገር ነው" አሉ ።

"ለመሆኑስ አንጀት ጉበትዋ በደኅና ተገኝቶ አብሮ ተቀብሮ ይሆን ?" አሉ እንደሻው ።

"እህ ፣ ምን እንዳይወስያው ?" አሉ አዛውንቱ ።

"ድንገት ሙሴ ዜርቮስ እንዳደረገው ሆኖ እንደሆነ ብዬ ነው ።"

"እህ ፣ ሙሴ ዜርቮስ አንጀት ጉበት ያስቀር ኑረዋል ?" አሉና አዛውንቱ ፣ የመገረም ጥያቄ ጠየቁ ።

"እህ ፣ አልሰሙም ወይስ ረሱት ? ሙሴ ዜርቮስ እንደዚሁ አንዲት ሴት ኦፒራሲዮን ሲያደርግ ፣ ዕቃ ረስቶ ኑሮ ፣ ያን ዕቃ ውን ካንደኛው ክፍሉ ሲያመጣ ሲሔድ ፣ ድመቷ ኦፕራሲዮን የሆነችውን ሴትዮ አንጀት እየጐተተች ወስዳበት እነበለ ሆድ ዕቃኮ ነው ሬሶ ያስረከበ" አሉ እንደሻው ።

"እህ ፣ እርሱ የሆነው ድሮ ይሆናላ ? ዜርቮስማ ከቤቱ ምን ያልሠራው ግፍ ነበር ? ይህች እንኳ የገባችው ሐኪም ቤት ነው ። ግን ሐኪሙ ገና እንግዳ ነው ፤ እንዲያው ከነፋስ የፈጠነ ቀዝቃዛ ነው" ኦሉና አዛውንቱ ፣ አብረው እየተጫወቱ መሔድ ሲጀምሩ ፣ አንድ ባለ አቶሞቢል ሰውዬ ከፊት ለፊታቸው በኩል ደረሱና የመኪናቸውን ፍጥነት ገታ አድርገው ፣

"ጤና ይስጥልኝ! ቀብሩ ተፈጸመ እንዴ ?" ብለው ጠየቁ ። እኒያ አዛውንት ፣ ጠጋ ብለው ሰላምታ ሰጡዋቸውና ፣

"አዎ ፣ ቀብሩስ ተፈጽሟል ። ኃዘነተኞቹ ግን ፣ ሰው እያ ሰናበቱ ናቸው መሰለኝ ፣ ወደ ኋላ ይመለሱኛል" ሲሉዋቸው ባለ አቶሞቢሉ ወደፊት ተፈተለኩ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኒህን ሰው ያውቋቸዋል?" ብለው አዛውንቱ፣ አቶ እንደ ሻውን ጠየቁዋቸው ።

"ዘነጋኋቸው መሰለኝ" አሉ እንደሻው ።

"እንዴት እርሳቸውን አያውቁም?"

"ሚኒስቴር ናቸው ዲሊክተር?" አሉ እንደሻው ።

"ኧረ አይደሉም ።"

"ታዲያ ምንድን ናቸው?"

"ሚስታቸውን ተቀምተው በሙግት ያስመለሱትኮ ናቸው ።"

"እሀ! እሀ! እኒህ የራስ ያረጋል ልጅ ቀምታቸው ለጃን ሆይ አቤት ብለው ተመለሰችላቸው የሚባሉት ናቸው እ፣ዴ?" አሉ እንደሻው፣ ወደ ኋላቸው ዘወር ብለው እያዩ ።
"እሀ፣ እርሳቸው ናቸው" አሉ አዛውንቱ ።

"ወይ ግሩም ነገር! በየሠፈሩ ስንት ጉድ አለ እባካችሁ!! ታዲያ ዛሬም ከዚያችው በአቤቱታ ከተመለሰችላቸው ሴት ጋር ናቸው?" አሉ እንደሻው ።

"ለጥቂት ጊዜ አብረው እንደ ቆዩ፣ ደግሞ አንዱ የዘመኑ ጉረምሳ አስኮብልሎ ይዟት ጠፍቶ፣ ማፈላለጉና መሟገቱ ሲሰ ለቻቸው ጊዜ ሌላ አግብተው ሲኖሩ —" ብለው አዛውንቱ ተና ግረው ሳይጨርሱ፣

"ደግሞ ሁለተኛዪቱን ተነጠቁ!" አሉ እንደሻው ።

"ኦዎ ያው መነጠቅ ነው ። ደኅና ሚስት አገኘሁ ብለው ደስ ብሏቸው ሲኖሩ፣ 'እንኳን ያችን ማንዘራሽ የወሰደልኝ! ከእ ርሷ ጋር ብሆን ኑሮ የሴትን ፍቅር፣ የሴትን ጣዕም ሳላውቀው እኖር ነበር' እያሉ ሲኖሩ" ብለው አዛውንቱ ወደ ኋላቸው ዘወር ብለው በሩቅ ላሉ ሰዎች ሰላምታ ሲሰጡ፣ ለታሪኩ የቸኮሉት እንደሻውም፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"ታዲያ ይህችኛዋንም ተነጠቁ?" ብለው ጠየቁ ።
"ያው መነጠቅ ነው ። ሞተችባቸው " አሉ አዛውንቱ ።

"ግዴለዎትም ፣ ሦስተኛዋ ተስማሚያቸው ትሆናለች ፣ አይ ጠራጠሩ" አሉ እንደሻው ።

"ኦይ ፣ ማን ያውቃል?" አሉ አዛውንቱ ።

"እሀ ፣ አንድ ምሳሌ ልንገርዎ ? ሰውዬው የመጀመሪያ ሚስቱ ነዝናዛ ፣ ሰነፍ ፣ ሙያ ቢስ ነበረች ። ያለ ቂጣ መጋገር ፣ ያለ ንፍሮ መቀቀል ሙያ አልነበራትም ። ታዲያ ሞተችለት ። እርሱም ከእርሷ ሌላ ሴት አላገኝም ብሎ ሲናር ፣ ዘመድ ወዳጅ ቁስ መነኩሴ ተሰብስቦ መክሮና ተቆጥቶ ሌላ ሴት አገባ ።

"ሁለተኛዪቱ ሚስት ወፍ ጭጭ ሲል ትነሣና ፣ ቁርሱን ሠርታ ፣ ከመኝታው ቀስቅሳ ታጉርሰውና ፣ የእርሻው ቦታ ሩቅ ከሆነ ምሳውን ባገልግል አስይዛ ትሰደዋለች ። የእርሻው ቦታ ቅርብም ከሆነ በሰዓት ላይ ከአገልግልዋ ጋር ዱቃዋን በገንቦ ወይም በቅምጫና ፣ ያለዚያም በኮዳው ይዛለት ትሔድና ፣ እርሱ እስቲመገብ በሬዎቹን እዳሪ እያጋጠች ትቆየዋለች ። ማታም ሲመለስላት የእርሻ መሣሪያውን ትቀበለውና ፣ ለበሬዎቹ ገለባ ወይም ሣር ትሰጥና ፣ እግሩን ኦጥባ ፣ ቆሎውን ወይም ንፍሮውን በቁና ፣ ጠላውን በሽክና ታቀርብለታለች ። እሳቱን ግር እድርጋ አንድዳ ስታሞቀው አምሽታ ፣ ማታ ራቱን አጐራርሳ መደቡን ወይም ቆጡን ደልድላ ከንዲን አንተርሳ አሙቃው ታድራለች ።

ታዲያ ያ የዋህ ሰው ፣ እንደዚያ እድርጋ ስትይዘው ጊዜ የእርሻ መሣሪያውን እየረሳ መሔድ ይጀምርና ፣ ከአፋፍ ላይ ሆኖ እየተጣራ "አቀብይኝ" ማለት ይጀምራል ። እንደዚያ ሆኖ ሲቀማጠል ፣ ኑሮው እንደ ጣፈጠው የተረዱት ዘመዶቹ ወደ ቤቱ ሔደው ፣ "ታዲያ ሴትዮዪቱ ተስማማችህ ወይ?" ይሉታል ።
"እረ እባካችሁ ተዉኝ ፣ አሁንስ ይህችንም በገደለልኝና 'ሦስተኛ ሴት ባገባሁ!' ብሎ መለሰላቸው ይባላል" አሉ እንደሻው።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ታዲያ ፣ ነገሩን እርስዎስ ሞክረውታል?" አሉ አዛውንቱ ።
"እህ ፣ ሥስተኛ ሚስት ባላገባም ሥስት ሴቶች ሳላውቅ አልቀረሁም" አሉና እንደሻው አጉመተመቱ ።

ይህንንና ሌላም ሌላውንም እየተጫወቱ በቀስታ ርምጃ እያዘገሙ ከቤተ ክርስቲያኑ ወረድ ብሉ ከሚገኘው መለያያ መን ገድ ሲደርሱ ፣ እርምጃቸውን ገታ አደረጉና የመለያያ ስንብት ሲጀምሩ ፣ ከቅርብ ርቀት አስከሬን በመኪና ተጭኖ በርከክ ባሉ ሰዎች ታጅቦ ሲመጣ ይመለከቱና ፣

"ወቸው ጉድ! እንዲያው አንድ ሰው ለመቅበር መጥተን ሁለትና ሥስት ሰው መቅበር እየተዘወተረ መሔዱ ነው?" አሉ አቶ እንደሻው ።

"ምን ይደረግ! እንዳንቀር ደግሞ ፣ የዕድሩ ቅጣት አያ ድርስ ነው" ብለው መለሱ አዛውንቱ ።

"እንግዲህ እኔ ልሒዳ?" አለ ሸዋዬ ፣ ሰልቸት ብሎት ።

"እንዴ ፣ ለዕድር ጸሐፊነት እየመረጥህ ሬሳ ተሪምጂ ልሒድ ትላለህ!" አሉ እንደሻው ፣ ሩጦ የሚጠፋባቸው መስ ሏቸው እጁን ያዝ አድርገው ።

"እህ ፣ ታዲያ ይህም እስቲቀበር ልንቆይ ነው!" አለ ሸዋዬ ነጥቆ ለመሮጥ እየከጀለው ።

"እስቲ ለሁሉም ታገሥ ። ሬሳው ይድረስና ሚች ሞን እን ደሆነ ካወቅን በኋላ ቁርጡ ይለያል ። አንተም እንግዲህ የዕድር ጸሐፊ ከሆንክ ገና ብዙ ብዙ ትቀብራለህና ፣ ተለማመደው ።
"ኧረ እምናውቃቸው ሰዎች አሉበት" አሉ አዛውንቱ ፣ አጀቡ ሲቃረብ ።

"እ፡ዴ ፣ እነዴ ኧረ ብዙ የምናውቃቸው ሰዎች አሉ ። እነዴ እንዴ ፣ እንዴ ፣ ብዙ መኳንንት አሉበት ። ማን ይሆን የሞተው?" አሉ እንደሻውም ።

የታጀበው ሬሳ ሲደርስ ፣ እነ አቶ እንደሻው እጅ እንደ መንሣት እያሉ ተቀበሉና ፣ የሚያውቋቸውም ሰዎች ስላገኙ ሰላምታው፣ እንኳን በቅጡ ሳይመላለሱ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"ማነው የሞተው?" ብለው አቶ እነደሻው፣ አንዱን አሽቢ ጠየቁ ።

"ፊታውራሪ አቻምየለህ ናቸው ።"

"እንዴ፣ እንዴ! እኒህ ዳኛው ናቸው?"

"አዎ፣ እሳቸው ናቸው ።"

"እንዴ ምን አገኛቸው?"

"መኪና ገጭቷቸው!"

"መቼ?"

"ከትላንት ወዲያ እሑድ ።"

"እዬ ጉድ! እሳቸው እየነዱ ነው?"

"አረ በእግራቸው በሰበታ መንገድ ሲሔዱ ነው ።"

"በእግራቸው ወደዚያ ምን ወሰዳቸው?"

"እግራቸውንና ሰውነታቸውን ለማፍታታት ብለው፣ መኪናቸውን ከከተማው ወጣ አድርገው፣ በእግራቸው ሲሔዱ ሲሽቀዳደሙ ከነበሩ መኪኖች አንደኛዉ አበላሽቷቸው ሔደ ።"

"እንዴ! እዚሁ አከተማው አይንሸራሸሩትም ነበር? እዚያ ምን ወሰዳቸው?

"አከተማውማ ተቸግረው ነው ። በእግራቸው ሲንሸራሸሩ ባለጉዳይ እየጠበቀና እየከበበ አላስኬዳቸው፣ አላራምዳቸው አለና፣ ከጣጣው ለመሸሽ ሲሉ ነበር ከተማውን የጠሉት ይባላል" ሉ እኒያ አሽቢ ።

"አዬ ጉድ! ዳኝነትን ያህል ሥልጣን ተሸክሞ፣ ነገር መቁረጥ ፈርቶ፣ ባለጉዳይ ተጠልቶ ይዘለቃል? እንግዲህስ እኛም እንቅበር እንጂ፣ ሬሳ ተራምዶን አንሔድ" አሉና እንደሻው አብረዋቸው ከነበሩት ሰዎች ጋር አብረው ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመለሱ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ቅብሩ ከተፈጸመ በኋላ ፣ አራት ሴቶች ከአጃቢዎቻቸው ጋር እየሆኑ ለየብቻ ፈንጠር ፣ ፈንጠር ብለው ቆመው ለቅሶኛውን ሲያሰናብቱ ፣ አቶ እንደሻው ተመለከቱና ፣

"እህ ፣ ይህ ነገር እነዴት ነው ? እነዚህ አራት ሴቶች ምን ምን መሆናቸው ነው ?" ብለው በመጀመሪያ ወሬውን የነገሩ ዋቸውን አዛውንት ጠየቁ ።

"እኚያ በመካከል የቆሙት አሁን ከቤት ያሉት ባለቤታቸው ናቸው ። አልፍ ብለው የቆሙት ሁለት የወለዱላቸው የመጀመ ሪያ ሚስታቸው ናቸው ። በወዲህ በኩል የቆሙት ሁለቱ ደግሞ አንዳንድ የወለዱላቸው ዕቁባቶቻቸው ናቸው " አሉ ።

"ጉድ ነው ፤ በዛሬው ዕለት አራት ሴት ከተሰለፈላቸውማ እንግዲህ ለዐርባቸው ደግሞ ዐሥር ሊሞሉ ነዋ" አሉና እንደ ሻው ቀጠል አድርገውም ።

"አዎ ፤ ሳያልፉስ ይቀራሉ ብለው ነው ? ሰውዬው ከድሮ ጀምሮ በአገረ ገዢነትና በዳኝነት በየጠቅላይ ግዛቱ እየተዘዋወሩ የኖሩ ናቸው ። እንግዲህ በየደረሱበት መቸስ አንዳንድ ያጣሉ ብለው ነው ?" አሉ ።

"እኔ ምን ዐውቅላቸው ? በ፴፯ ዓ.ም ወረዳ ገዢ ሆነው ወደ ሲዳሞ ተልከው ነበር ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ያልደረሱበት አገር የለም ። እኔ እንኳ ሳውቅ ወደ አሩሲ ፣ ጅማ ፣ ወለጋ ፣ ወሎ ፣ ሐረርጌ ፣ ተዘዋውረዋል ። ወደ አዲስ አበባ የመጡት እንግዲህ በ፵፰ ዓ.ም ገደማ ይመስለኛል" አሉ አጃቢው ተጠያቂ ።

"እንግዲህ ፣ በዐሥራ አንዱ ዓመታት ውስጥ ቢያንስ ቢያ ንስ በዓመት ሦስት ሴቶች ቢያውቁ ፣ በድምሩ አዎ ፣ ከሠላሳ በላይ ሴት ቢሔዱ ፣ ከነዚሁ ውስጥ እንዲያው በትንሹ ዐሥሩ ያህል አንዳንድ እንኳ ቢወልዱ ፣ ከ፵፰ ዓ.ም. እስከ ዛሬ ፣ ማለት በአራት ዓመት ውስጥ ደግሞ አዲስ አበባ ውስጥ ዐሥር ያህል ሴት ቢሠርቁ ፣ ያውም በትንሹ ነው ፤ እነርሱም አንዳንድ ቢወል ዱላቸው ፣ ዛሬ ከለቅሶው ላይ ከተገኙት ሴቶች ከተወለዱት ጋር ወደ ሐያ ሊጠጉ ነው ። ከዚያ እንግዲህ በትንሹ ሐያ ያህል ሩይል

t.me/OLDBOOKSPDF

ይከፈትና ፡ በሐያ ጠበቆች መካከል የሚነሣው መግት የምድረ ጻኛን ጭንቅላት እምቧለሱ ያዞረዋል'' አሉ እንደሻው ።

''ያሀማ እንዴት ይደረጋል ! በየደረስበት ሴት ሴት ካሉማ ነገር ይበላሻል'' አሉ አዛውንቱ ፡ የእንደሻውን ግምት ሲያንጠ ራጥቡባቸው ።

''አሄሄ ! ሴትንና ድንጋይን በየደረስበት ነው ማነጣት ይባል የለም ? ባለሥልጣኖችን መገመት የሚያመቸው ደግሞ ፡ወደ ጠቅ ላይ ግዛት ሲሔዱ ነው ። ከመኪና ወርደው ሆቴል ቤት እንደ ገቡ ከሴት ላይ ነው የሚያፈጡ ። ብዙ አይተን ታዝበናል'' አሉና እንደሻው ፡ ከነአጃቢዎቻቸው አራቱንም ሴቶች እጅ እየ ነሡ ወደ ቢታቸው ሲመለሱ ፡ ከእኒያኛው አዛውንት ጋር ተስ ነባበቱና ፡ ''ከእንግዲህ ይኸወልህ ፡ የኛ ጣጣ ብዙ ነው ። ባለብ ንበት ውለን ዐናውቅም ። ለዕድርተኞችን ቀብር መጥተን የጉድ ጉድ ስንሰማ ዋልን አይደል ? አንተም እንግዲህ የዕድራችን ጸሐፊ ከሆንክ ከብዙ ሰው ጋር ትተዋወቅና ፡ የቋሚንም የሟ ችንም ጉድ እየሰማህ መዋሉን ትለምያውና ከሲጃራው ሌላ የወ ራም ባለሱስ ትሆናለህ አሉት'' የሸዋዬን እጅ ይዘው በዝግታ እየተራመዱ ።

''እንግዲህ እዚህ ቆም እንበልና ፡ኦቶቡስ ወይም ጋሪ እን ጠብቅ እንጂ'' አለ ሸዋዬ ፡ የግንቦት ፀሐይ አድብኖት ፡ ባረማ መዱና ባነጋገሩ ትክት ብሎት ።

''አሄሄ! የዘመኑ ወጣት ፡ ከዚህ ፡ ለዚህች አነድ ምዕራፍ ለማትሆን መንገድ ገንዘብ እናውጣ ትላለህ ? ዳሩ ምን ታደርጉ ትንባሆው ፡ መጠጡ ፡ ሴቱ እየተረባረበባችሁ አይደል ሐሞታች ሁን ያፈሰሰባችሁ ? በልኩ ፡ ነቃ ነቃ በልና ወደኔ ቤት ሔደን ቤት ያፈራውን ቀማምሰን ፡ ስለ ኮመረጥክበት ሥራ ጉዳይ እን ነጋገራለን'' አሉ እንደሻው ፡ በቁፍጥንጥነት አነጋገር ።

''እኔማ በጋሪ ወይም በኦቶቡስ መሔድ አለብኝ ። ምክን ያቱም ትምህርት ቤትም ሥራ ስላለብኝና ሔድ ማስተሩ ስለሚ ጠብቀኝ ነው'' አለ ሸዋዬ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምኑ ስለሚጠብቀኝ አልክ?" ብለው ጠየቁት ፣ ቆም ብለው።

"ሔድ ማስተሩ ።"

"ምንድነው እሱ?"

"ሥራ መሪ ነው ።"

"ሥራው ይመራዋል እንጂ ፣ እርሱ ደግሞ ምን ይመራል ? የሆነ ሆኖ ፣ ከቸኮልክ አሁን ሒድና ማታ የኔን ቤት ታውቀው የለም ?— ብቅ በል ። የማሳይህና የማጫውትህ ብዙ ጉዳይ ሞልቷል" አሉትና ፡ ከጋጣ እንደ ተለቀቀች እምቦሳ እየዘለለ መሮጥ ሲጀምር ፣ አቶ እንደሻው ፡ እንዳሞኛቸው ተረዱትና ፣

"ስማህ ወይ ? አንተ— ምንትስዬ ፣ ወንድም ፣ ወንድም!" ብለው ሲጠሩት ፣

"አቤት!" ብሎ ቆመ ።

እንደሻውና አቶ ይመር መገሞቱን ተወት አድርገው ፡ ነጠቅ ነጠቅ አድርገው ተራምደው ደረሱበትና ፣ እንደ በፊቱ አቶ እን ደሻው እጁን ያዝ ሲያደርጉት ፣ ብስጭት መተናነቅ የጀመረው ሽዋዬ ፣

"ስሜን አጡትና ነው ፡ ምንትስዬ ብለው የሚጣሩት ?" አላቸው ፣ ለማምለጫ ቢሆንኝና ብጣላ ብሎ ።

"አላጣሁትም ። እንዴት? ዛሬ ነግረኸኝ ? እንዴት ?" አሉት እንደሻው ፡ ወደፊት እያዘገሙለት ።

"ዛሬ ነግረኸኝ እንዴት እረሳለሁ ነው ? ወይስ ዛሬ ነግረ ኸኝ እንዴት ትዝ ይለኛል ማለትዎ ነው ?" አላቸው ፣ እንደ መቆጣት እያለው ።

"እንዴት ረሳሻለሁ ማለቱ ነው" አሉት ።

"ስሜን ያስታውሱታል ?" ብሎ ደግሞ ጠየቃቸው ።

"እንዴታ!"

t.me/OLDBOOKSPDF

''እሺ ማነው ?'' አለና አፋጠጣቸው ።

''አሃሃ! የአሁኑስ ጥያቄህ አንድ እንዳንተው የመሰለ ሰው ታሪክ አስታወሰኝ'' አሉ እንደሻው ፣ የአረማመዳቸውን ፍጥነት እየጨመሩለት ።

''ምን ትዝ አለዎት ደግሞ የኔን የሚመስል ?''

''ይኸውልህ ፣ አንድ ጊዜ አንድ አዛውንት ፀበል ተጠር ተው እጦረቤት ሔደዋል ። በዚያ ቤትም ካንድ አንዳንተ ካለ ጐበዝ ጋር ይተዋወቃሉ ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ፣ ከዚያው ጐበዝ ጋር በሌላ ቦታ ይገናኙና ፣ እርሱ አልዘነጋቸው ኑሮ ፣ ጠጋ ኦለና ሰላምታ ሰጥቶ ፣ 'እሜቴስ ፣ ልጆችስ ፣ እንዲያው አጥር በመለስ ቤት በጐረስ ያለዎት ሁሉ ደኅና ነው ?' ብሎ ይጠይቃቸዋል ። እርሳቸው ግን ፣ ዘነግተውት ኑሮ ፣ ይደናገሩና ፣ 'ደኅና ናቸው ደኅና ናቸው ደኅና' ብለው ሊያልፉት ሲሉ ፣ 'እርስዎስ ደኅና ነዎት?' ብሎ ደግሞ ጠየቃቸው ።

''ዘመድስ ?'' ብሎ ሦስተኛ ጥያቄ ሠነዘረባቸው ።

''ደኅና'' ይላሉ ፣ ''በዚሁ በያበቃልኝ'' እያሉ እየተመኙ ።

''ለመሆኑ እኔን አስታወሱኝ?'' ብሎ ድርቅ ይላል ።

''አዎ ፣ ኦውቄሃለሁ'' ይላሉ እሳቸውም ።

''እሺ ካስታወሱኝ ስሜ ማን ይባላል?'' ብሎ ያፋጥጣቸዋል ።

''እህ ፣ ችኬ መነቻኬ ነህ !'' ብለውት ሮጡ ይባላል ።

ሽዋዬ ቀበል አደረገና ፣ ''ስለዚህ እኔንም እንደዚያው ነህ ማለትዎ ነው ?'' ብሎ እንደገና ያመርባቸዋል ።

''አልወጣኝም ፣ አላልኩም ፣ አላሰብኩትም ። ግን እንደኔ ያለውን አዛውንት ማፋጠጥ አይገባም ለማለት ነው'' አሉት፣ ስሙን የዘነጉት መሆናቸውን በገደምዳሜ ሲነግሩት ።

''እሺ ፣ አሁን የጠሩኝስ ለምንድነው ?'' አለ ሽዋዬ ፣ እንደገና ከእጃቸው ለመውጣት እየናፈቀ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

''ትዳር ይዘሃል ? ልጅችሽ ወላልደሃል ?''
''እንዲያውም ! ገና ነኝ'' አለ ሸዋዬ ፣ በሰለቸ አነጋገር ።

''ከምኑ ላይ ነው ገና የሆንከው ? ለዐቅመ አዳም አልደረስኩም ማለትህ ነው ?'' አሉት እንደሻው ፣ በአሽሙር ሲገርፉት።

''የምትሆነኝ አላገኘሁም ማለቴ ነው ።''

''ከእንግዲህስ ?''

''ከእንግዲህማ ፣ ከአሁኑዋ ደቂቃ ጀምሮ እፈልጋለሁ ፣ እር ስዎ ከለቀቁኝ ።''

በዚህ ጊዜ እንደሚያባብሉባቸው ተገነዘቡትና ፣ እጁን ለቀው የጠፉጣሩ ፊታቸውን ቆዳ አኩማትረው ፣

''ስማህ እንተዬ'' ብለው ትክዝ ብለው ቆዩና ፣''ስማህ ወዳጄ ነህ ! ዕውቀትን ኩራት ፣ ሹመትን ክፋት ፣ ሴባን ንቃት ፣ ጨለ ማን መብራት ፣ ጅብን ፣ጋት ፣ ጭድን እሳት ፣ ከቀደሙዋቸው ነገር ቀረ'' ሲባል አልሰማህም ? ባንተም ላይ ምሳሌው እንዳይ ደርስ ተግተህ ተከላከለው ። በል እንግዲህ ፣ እሠፈራችን ደርሰ ናልና ፣ ወደ ቸኮልክበት ጉዳይህ ድረስና ፣ ወደ ማታ እቤቴ ብቅ በልልኝ ። ቤቱን ታውቀው የለም ? እቆይሃለሁ'' አሉትና ራመድ ራመድ ሲሉ ፣ አቶ ይመር ከኋላ ኋላ ስንዝሮሽ እግሮቻቸውን እየ ወረወሩ ሲከተሉ ፣ በእንደሻው መለዋወጥ ድንጋጤ የወረረው ሸዋዬም ያን የተቆጣ ገጽታ ወደ ፈገግታ ለመለወጥ ሲል ፣

''ምን ላድርግ ? እጄን ሲይዙኝ ጊዜ ፣ ሽንት ሽንትኮ ብሎኝ ነው'' አለንና ፣ እጅ እንደ መንሣት ብሏቸው ለመገሥገሥ ሲያ ቆበቁብ ፣

''የእጄ ብርታት ነው ወይስ ሚስት የማግኘቱ ጉጉት ፣ ሽንት ሽንት ያሰኘህ ?'' አሉት ፣ እውነትም ፈገግ እያሉለት ።

''ሁለቱም ናቸው'' አለና ፣ ርምጃውን ሲቀጥል ፣

''በል በኋላ እቤት እጠብቅሃለሁ ። ብዙ ብዙ ጉዳይ አጫ ውትሃለሁ ። ለዕድርተኛው የምንሠራው ብዙ ብዙ ሥራ አለብን ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉንም ስትመጣ አጫውትሃለሁ'' አሉት ፣ ሁለቱን ዕድሮች እንድ ለማድረግ ለጀመሩት ጥረት በአያሌው እንደሚረዳቸው በመተማመን በተስፋ እየተመለከቱት ።

''ግዴለምትም ይጠብቁኝ'' አለ ሸዋዬ ፣ ከእጃቸው በማፈ ትለኩ በልቡ ዳንኪራ እየመታ ።

''ቁም ነገረኛ ልጅ ይመስላል ፣ ለዕድራችን የሚጠቅም ሳይሆን አይፋርም'' አሉና ፣ እንደሻው ምኞታዊ አስተያየታች ውን ለአቶ ይመር ሠነዘሩ ።

''እም ፣ ቁም ነገረኛስ ይመስላል ። ብቻ እንዲያው—''ብለው አቶ ይመር ፣ ሐሳባቸውን ለመግለጽ ጀመር አድርገው ዝም አሉ።

''ለመሆኑስ የሠፈራችን ነዋሪ ከሆነ ፣ ምን ያህል ጊዜ ይሆ ነዋል ?'' አሉ እንደሻው ።

''ካመት በላይ ሳይሆነው አይቀርም ።''

''ከዚህ ቀደምስ ?''

''በእቴጌ ትምህርት ቤት ግድም ነበርና ፣ እንደሚባለውማ በዚያ ግድም ሳለ ፣ አገባሻለሁ እያለ ሦስት ልጃገረዶች አማግጦ በፖሊስ ጣቢያም እየታሰረ ብዙ ጊዜ ተጉላልቶ ነበር ይባላል ።''

''በዚህ በሠፈራችንስ? አላማገጠም ?''

''ባይነቃበት ነው እንጂ ፣ መቸም ወደ ቤቱ ገባ ወጣ የሚሉ ልጃገረዶች አይጠፉም ።''

''እህ ፣ እኛስ በጊዜያችን አገር አቋርጠን ፣ ወንዝ ተሻግረን ነበር ጠልፈነ የምንወስድ ። እቤቱ ድረስ ሰተት ብላ 'ያደረግ ኸውን አድርገኝ' ብላ ከመጣችለትማ ምን ያድርግ ? ምንስ የክ ተማ ልጅ ቢሆን ወንድ መሆኑ እንዴት ይረሳል ? እኛ ግን ለዕ ድራችን ሳይጠቅመን አይቀርም ፣ እንደ ገመትኩት ቁም ነገረኛ ልጅ ይመስላል ። እንዲያውም በዚህ ሠፈር በሚገኙት ዕድሮች ላይ ባለርስቶች የሚሠሩትን ግፍ ሁሉ ልቅም አድርጎ ይጽፍል ኛል ።''

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን ሊያደርጉት ነው የሚያጽፉት?" አሉ ይመር።

"ወደ ጃንሆይ ለማቅረብ።"

"ወደ እርሳቸው ለማቅረብኮ ሰው ያስፈልግዎታል። ተሰሚነት ያለው፣ የሚቀርበውን የሚያስፈጽም ባለሥልጣን ከሌለ፣ በእርስዎ ጥረት ብቻ የሚሳካ አይሆንም። እንዲያውም ጠላት ያተርፍብዎታልና ይጠንቀቁበት" አሉ ይመር።

"ግዴለሀም። ለዚህ የሚሆን ሰው አላጣም። በጣሊያን ጊዜ የማውቃቸው፣ ለጣሊያኖቹ በጣም ታማኝና የአርበኛውን እንቅስቃሴ ሁሉ እየተከታተሉ ለጣሊያኖቹ ሲያቀርቡ የነበሩና፣ አሁንም ወደ ቤተ መንግሥቱ እንደ ልባቸው የሚገቡና የሚ ወጡ፣ ሹመትም ሆነ ሽልማት የሚያሰጡ የልብ ወዳጅ አሉኝ። እርሳቸው አቅርነው የዚህን ሠፈር ሥቃይ መፍትሔ ያስገኙለ ታል" አሉ እንደሻው።

ይህንና ይህን የመሳሰለውን እየተጨዋወቱና፣ እያዘገሙ ከሠ ፈራቸው ደርሰው፣ ከአውራ መንገድ ላይ ቆመው ለመለያየት ሲሰነባበቱ፣ በመጠነኛ ፍጥነት ከፊት ለፊታቸው ሲሮጥ የነበረ ሸፍሮሌት አቶመቢል፣ ከአጠገባቸው ሲደርስ ፍጥነቱን ገታ አደረገና እንደ መቆም ሲል፣ እነ አቶ እንደሻው ደንገጥ ደንገጥ ብለው ሲመለከቱ፣ የአቶሞቢሉ መስታወት ወረድ አለና፣

"እንደሻው—" አሉ ወይዘሮ ላቀች፤ "ይህን ሠፈር መበ ጥበጥ፣ ዕድርተኛ ማሳደም፣ ካላቅምህ መንጠራራት፣ የሰው ከብር መዳፈር አትተውም? አይበቃህም? ባስመካርህ አሻፈረኝ ማለትህ ነው? እንዳንተው አገር ሲያስቸግር የነበረው ከበደ ምን እንደ ደረሰበት ታውቅ የለም? እስቲ የሚያስጥልህን ዕያለሁ። ጠብቀኝ!" አሉ።

"ምን አሉኝ፣ እመቤቴ?" ብለው እንደሻው ወደ አቶሞ ቢሉ ጠጋ ሲሉ! "ኡፉፉ! ኧር ኧር ኧር ውው!" ብሎ ሸፍሬሌቱ ተፈተለከ።

ይህ ከሆነ ከሳምንታት በኋላ አቶ እንደሻው ከቤታቸው ተጠ ርተው ተወስደው፣ ሳይመለሱ ቀሩ።

* * *

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚያ ዕለት በኋላ በቀጠሉት ሳምንቶችና ወራቶች ዕድርተኞች ለመሰብሰብ አልሆነላቸውም ነበር ። የሁለቱም ዕድሮች ኃላፊዎች በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሣ ፣ በዕድሮቹና በዕድርተኞቹ ጉዳዮች ላይ ለማተኮር አልሆነላቸውም ነበር ። ከዕድርተኞቹ መካከል በሞት ለሚለዩ ፣ መርዶ ለሚመጣባቸውና ወደ ገጠር ሔደው ቀብረው ለሚመለሱ ሁሉ በዕድሩ ደንብ የተደነገገው መብታቸው በትክክል ሲፈጸምላቸው አልተቻለም ነበር። ይሁን እንጂ ፣ የወር መዋጮና መቀጫ ሳይውልና ሳያድር ይከፈላል ። በዚያ ሁኔታ ወራት ካለፉ በኋላ ፣ በመስከረም ወር አጋማሽ በ፲፱፻፶፱ ዓ. ም. የሁለቱም ዕድሮች አባላት እንዲሰበሰቡ ጥብቅ ዐዋጅ በወረዳው ገዥ ተላለፈና ፣ በተወሰነው ዕለትና ሰዓት ዕድርተኛው ሁሉ የየራሱን ወንበር ፣ እግዳሚ ወንበርና ዱካ እየተሸከመ ወጥቶ ፣ በዚያችው ግራር ሥር ተሰበሰበ ።

በዕለቱ በሰዓቱ ተረኛ የነበረችው ፀሐይ ደግሞ ገንትራለች፤ የግራሩዋ ሥርም የሁለቱን ዕድሮች አባሎች በእንድነት ዐቅፋ ከፀሐይዋ ትኩሳት ለመከላከል አልበቃችም ።

በመጀመሪያ ጊዜ ፣ የሁለቱም ዕድሮች ዕድርተኞች ተቀራርበው በግራሩዋ ሥር ለመቀመጥ የሚችሉ አልነበሩም ። ሁለቱም ወገኖች በየዕድራቸው እንጂ ፣ ተቀላቅለው ለመቀመጥ ተፈራርተዋል ፤ ተናንቀዋል ። ሌላው ችግር ደግሞ የግራሩዋ ባለመብቶች የአድባሩ ዕድርተኞች ስለነበሩ ፣ የፊታውራሪን ዕድርተኞች ላለማስጠጋት በአሸሙር ይተናኩሉዋቸው ስለነበር ፣ እነዚያም ወደ ግራሩዋ ሥር ተጠግተው ለመቀመጥ አልተደሰቱም ነበር ።

በዕድሩ ጉዳይ ፣ ወረዳ ገዢው ገብተው የሰብሰባ ትእዛዝ ማስተላለፋቸው ተሰብሳቢዎቹን ሁሉ ተደናግሩዋቸዋል ። ያልተሰመደ ጉዳይ በመሆኑም ይንሾካሾኩበታል ። በሁለቱ ዕድሮች የሠፈር ሹም ሆነው የተመረጡትም ሽር ጉድ ይላሉ ። የሁለቱንም ዕድሮች መቀመጫዎች እያስጋዙ አስደርድረው ባለመብቃታቸው ፣ ከየቤቱ ማስወሰድም ግድ ሆኖባቸው አርፍዷል። የወረዳ ገዢው ትእዛዝ በመሆኑም ፣ ዕድር ያልገቡ የሁለቱ ዕድሮች

t.me/OLDBOOKSPDF

አዋሳኝ ነዋሪዎችም እንኳ ለወሬው ቂምጠው ሔደዋል። ለመቀ ቀላል ያልያፈሩትም በቅርብ ርቀት እቆብቁበዋል።

"መቸም ታረቁ፣ ተስማሙና አንድ ሁናችሁ ሠፈራትሁን ዐልሙ፣ እንደ ሌሎቹ ዕድሮች ሁኑ" ሊሉን ነው ሲል አንዱ፣ ሌላው ደግሞ፣

"እርግጠኛ ነኝ፣ ባለርስቶች የጫኑባችሁን ቀንበር አንስቶላ ችኋለሁና፣ እንደ ሌሎቹ ዕድሮች በፈለጋችሁት ደንብ ተዳደሩ ሊሉን ነው" ይላል።

ሌላው ደግሞ "የባለርስቶቹን የመሬትና የቤት ኪራይ የከለከ ላችሁ ስላላችሁ፣ 'ዛሬውኑ ባትከፍሉ ሰብስቤ ወደ ጣቢያ እሰዳ ችኋለሁ' ሊሉን ይሆናል" እያለ የፍርሃት ጥርጣሬውን ያስተ ጋባል።

"አዎ፣ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ራሳቸው ወረዳ ገዥ ውም ከወይዘሮ ላቀች ቤት ሲመላለሱ አይቻቸዋለሁ" የሚልም ነበር።

"እንግዲያውማ፣ ማታም ከእርሳቸው ቤት አምሽተው ይሆ ናል፣ ዛሬ በጥዋት መምጣት ያልቻሉት" አሉ አንደኛው ዕድርተኛ፣ የፀሐዩ መግነጥርና የሰዓቱ መርፌድ አንገፍግፏቸው።

ዕድርተኞቹ፣ ይህንና ይህን የመሳሰለውን የየበኩላቸ ውንም ግምታዊ ትንተና እያወጉ በነበረበት ወቅት፣ ወረዳ ገዥው ቀኛዝማች ሣህለማርያም በርከት ባሉ ሰዎች ታጅ በው ወደ ግራሩዋ ሥር ሲያመሩ በቅርብ ርቀት ታዩ። ይበልጥ ትርምስ ሆነ፣ ሽክሽክታው ወደ ጉርምርምታ ተለወጠ። ወረዳ ገዢው ከነአጃቢዎቻቸው ሲቃረቡ ደግሞ፣ የአጃቢዎቹ ማንነት እየጐላ መታየት ጀመረ። የተሰብሳቢዎቹ ጉርምርምታ ከፍ ወደ አለ ንግግር ተሻገረ። የወረዳው ገዥ ገበርዲን ልብስ በሣሪያን ቅድ አሰፍተው፣ ቡናማ የቡሽ በርኔጣ ደፍተዋል። አጠር ወፈር ያሉ የጠይም ዳማ ናቸው።

ከአጃቢዎቻቸውም መካከል አቶ ፍጡርና አስተማሪው ሸዋዬ ከኋላ ኋላቸው ይከተላሉ። የተሰብሳቢዎቹ ጉርምርምታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደናረ ንግግር የተሸጋገረውም ሁለቱን አጃቢዎች በማየታቸው ነበር። በሦስት ፖሊሶችና በወረዳው ውስጥ በታወቁ ነዋሪዎች የታጀቡት ወረዳ ገዥ ከግራኑዋ ሊደርሱ ፣ ሩብ ገደማ ርቀት ሲቀራቸው ፣ ተሰብሳቢዎቹ ሁሉ ከተቀመጡበት ተነሡ ። እርሳቸው ሲደርሱም ፣ ቁም የነበረው ሁሉ ፣ ከፊት ለፊት የነበረው ከወገቡ ፣ በሰተኋላና ፈቀቅ ፈቀቅ ብሎ የነበረው ደግሞ ከእንገቱ ጐንበስ ጐንበስ እያለ እጅ ሲነሣ ፣ የወረዳ ገዥውና የሠፈር ሹሞች ፣" እንዴት አደራችሁ ? እንዴት ሰነበታችሁ?" እያሉ ኮተዘጋጁት ወንበሮች ሲቀመጡ ፣ የቆመው ሁሉ ተቀመጠ ።

የወረዳው ገዥ ፣ ለትንሽ ደቂቃዎች ያህል ተሰብሳቢዎቹን ሲገለማምጡ ቆዩና ፣ በሰተኋላቸው ቆሞ ከነበረው አሽከራቸው ዘወር ብለው ፣ አንድ ማጎዳር ተቀብለው ፣ከውስጡ አንድ ወረቀት አወጡና ፣ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ተመለካክተው ፣ ከተቀመጡበት ተነሡና ፣

"የተከበራችሁ ዕድርተኞች! አባቶቼና ፣ እናቶቼ ፣ ወንድሞቼና እኅቶቼ" ብለው ዙሪያውን ተመለካከቱና ፣ "ልጆቼ" የሚሉት ክፍል ያለመኖሩን አረጋግጠው ዲስኩራቸውን ቀጠለ ፣

"እስከ ዛሬ ድረስ በብዙ ጠቅላይ ግዛቶችና በዚሁ በአዲስ አበባም በልዩ ልዩ ወረዳዎች ሳገለግል ኑሬያለሁ ። ወደዚህ ወረዳም በገጠርነት ተመርጬ ከመጣሁ እነሆኝ ቀላል ጊዜ አይደለም፤ አምስተኛ ወሬን ይዣለሁ ። ታዲያ በዚህ ጊዜ ውስጥ ፣ በወረዳው ውስጥ ባሉት ዕድሮች ሥራ የተደሰትኩበትን ያህል ፣ በእነዚህ ሁለት ዕድሮች ታሪክ ደግሞ በጣም አዝኛለሁ ። እስከ ዛሬ ድረስ አንድነታችሁን መሥርታችሁ ፣ ችግራችሁን ተወጥታችሁ ፣ ሠፈራችሁን እንዳታለሙ ልዩ ልዩ የተራቀቀ ተንኮል ሲሠሩባችሁ የነበሩ እነመቶ አለቃ ከበደ ፣ እነአቶ እንደሻው እነአቶ አርጋው ፣ እነአቶ ይመር ፣ እነወይዘሮ ፈትለ ወርቅ ፣ እነ መምሬ በዕውቀቱና ሌሎችም ተንኮለኞች እንደ ነበሩ ደርሼበታለሁ ።

በተለይም ፣ የመቶ አለቃውና አቶ እንደሻውማ ዕድሮቹ አንድ እንዳይሆኑ በተራቀቀ ዘዴ ከሚሸርቡት ተንኮል ሌላ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙ ብዙ ወንጀሎች ተገኝተውባቸዋል ። ለምሳሌ ፣ ባለፈው ዓመት አንድ የዕድርተኛችሁ ልጅ ሙቶ ቀብር ሔዳችሁ ፣ አቶ እንደሻው የሚባሉት የክርስቲያንን ሃይማኖት እያጥላሉ ሲለፈ ልፉ የነበረውን ሁሉ የሰማችሁት ታውቁታላችሁ ። ስለዚህ እን ደነርሱ የመሳሰሉትን ተንኮለኞች በዝምታ መመልከት የማይ ቻል በመሆኑ ፣ የደረሰባቸውን ሁላችሁም ታውቁታላችሁ ። የእ ነርሱ ግብረአበሮች የነበሩትንም በብርቱ ማስጠንቀቂያ ዐልፈና ቸዋል ። ስለዚህ ፣ ከመካከላችሁ ሆነው ለተንኮልና ለወንጀል ሥራ ሲገፋፉዋችሁ የነበሩትን ከመካከላችሁ ስላወጣንላችሁ ደስ ሊላ ችሁ ይገባል ። ከዛሬ ጀምሮ ግን ፣ ሁለቱን ዕድሮች አንድ አድ ርገው እንዲያስተዳድሩ ለጊዜው አቶ ፍጡርን በዳኝነትና በገ ንዘብ ያዥነት ፣ አቶ ሸዋዬን በጸሐፊነት መርጫቸዋለሁ ። እነ ርሱም ማነኛውንም ነገር ካዘጋጁላትሁና በመካከላችሁ የነበረ ውን ያለመግባባት አስወግደው ካረጋገጉላችሁ በኋላ ፣ እንደዚሁ ተሰብስባችሁ ሌሎች ኃላፊዎች ልትመርጡ ትችላላችሁ ።

በዛሬው ዕለትም ቢሆን ፣ ምክትል ዳኛ ፣ ምክትል ጸሐፊ ፣ የሠፈር ሽሞችና የዕድር ሽማግሌዎችም ልትመርጡ ትችላላችሁ ። ከእንግዲህ ወዲህ ግን ፣ በዚህ ጉዳይ በዚህ ሠፈር ፣ አጉል ነገር ባይና ብሰማ ፣ ዕድሩን አፍርሼ ፣ እንዲያውም ባለርስቶቹ ሌሎች ጢሰኞች እንዲያሠፍሩ ለማድረግ የምገደድ መሆኔን አሳውቃ ለሁ'' ብለው ሲቀመጡ ፣ የፊታውራሪ ዕድርተኞች ሞቅ ያመቅ ያለ ፣ የልጅ አደባሩ ዕድርተኞች እነደ ነገሩ የሆነ ጭብጨባ አበረከቱላቸው ።

''በእውነቱ የዛሬው ፍርድ የሰለሞን ፍርድ ነው ። በወረዳ ችን ቀርቶ በመላው አዲስ አበባም ሰምተን አይተን አናውቅም ። በእውነቱ ፍርድ ብቻም አይደል የተሰጠው ፣ ሕክምናም ጭምር ነው ። የዕድራችን ነቀርሳ ነው የተፈወሰው ። ወረዳችንም እንደ እርስዎ ያለ ጀግንነትን ከነበይነትና ከፍርድ ዐዋቂነት ጋር አጣምሮ የሰጠው ገዢ በማግኘቱ በጣም ፣ እጅግ በጣም ዕድ ለኛ ነው ። እርስዎንም ለዘለዓለም ያኑርልን! ሺህ ዓመት ያስን ዛልን ! እንዲያውም ከነልጅ ልጅም ፣ ከነዘር ማንዘርም'' ብለው አንድ የፊታውራሪ ዕድርተኛ ተናግረው ሳያጨርሱ ፣ ወረዳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገዢው ወደ ጎላቸው የነበረው ፖሊስ ማስታወሻ ሲጽፍ አዩትና ቦመካከል ጣልቃ ገብተው ፣

"ስሙ ጌታዬ ፣ ሐሳብዎ ማለፊያ ነው ። ግን ለዘለዓለም እን ዲኖሩልን ፣ ሺህ ዓመት እንዲነግሡልንም ፣ ዘር—ትውልዳቸው እንዲገዛን መጸለያ የሚኖርበን ለግርማዊነታቸው ብቻ ነው ። እኛ ኃላፊዎች ፣ ነገ ጠራዎች ፣ ነገ በሞትም በሽረትም ከሥልጣን የምንነሣ ነን" ሲሉ ተጨበጨበላቸው ።

"ያስ ሸክላ በየት በኩል ዙሮ እዚያ ተለጠፈ እባካችሁ?" አሉ የአድባሩ ዕድርተኛ ለጓደኛቸው ።

"ማን ?" አሉ እኒያኛውም ።

"ይኸው ሸዋዬ የሚሉት?"

"አሃሃ! እርሱማ የኒያን የዋሀ ፣ የኒያን ገራገር የአቶ እንደ ሻውን ገንዘባቸውን በብድር ስም ወስዶ ሳይመልስ 'የባለርስቶ ችን ግፍ ለመንግሥት አቀርባለሁ' እያሉ የሚያጽፉትን ሁሉ በጐን ለነወይዘሮ ላቀች አቀብሎ ፣ ዛሬማ የእርሳቸው ቤተ—ሰብ ሆኖየል! አሃሃ! እርሱ የማይገባበት ቀዳዳ የት አለና?" አሉ አንደኛውም ።

"ልጅ አድባሩኮ ቢገኙ ኑሮ ይህ ሁሉ ግፍ አይሠራም ነበር" አሉ አንደኛዉ ።

"አወይ ወዲያ! እዚሁ እያሉስ ምን ሠሩ! ታዲያ አጐታ ቸው እንደ ሞቱ ዕድሮቹን አንድ እናድርጋቸው እያልናቸው አል ነበረም? አቅቷቸው ነው? እንኳን ለዕድሩ ጉዳይ ፣ የተሾሙበት ንስ ሥራ ችላ በማለታቸው አይደለም ከአለቆቻቸው ጋር መስ ማማት አቅቷቸው ወደ ጠረፍ የላኩዋቸው? የእርሳቸውንስ ነገር አያንሡብኝ" አሉ ሁለተኛው ተቺ ።

ወረዳ ገዢው ፣ ባቀረቡት ሐሳብ መሠረትም ከፊታውራሪ ዕድርተኞች ምክትል ዳኛ ፣ ጸሐፊ ፣ የሠፈር ሹሞች ፣ የዕቃ ቤቶች ተመረጡ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የፊታውራሪ ዕድርተኞች እየፈነደቁ ፣ የልጅ አድባሩ ዕድርተኞች አንገታቸውን እየደፉ ፣ ከግራሩዋ ሥር እየተነሡ መሔድ ጀመሩ ።

ከዚህ በኋላ ፣ በሁለቱ ዕድሮች የነበሩትን ንብረቶች በፖሊስ አማካይነት አዲሶቹ ሹሞች ተረከቡ ። እየዋለ እያደረም የዕድርተኞቹ አንድነት በመጠኑ መቀራረብ ጀመረ ። የአቶ ፍጡርን ዳኝነት ያልተቀበሉ ጥቂቶች የልጅ አድባሩ ዕድርተኞች በአካባቢ ዕድሮች መግባት በመጀመራቸው ፣ ፍጡርም ጥብቅ ቁጥጥር እያደረጉ በመሔዳቸው ፣ አንዳንዶቹ ሠፈሩን ጭምር እየለቀቁ ሔዱላቸው ። ፍጡርም የእጎታቸው ወኪል ፣ የዕድሮቹ ዳኛና ገንዘብ ቤት ከሆኑና ተቀናቃኞቻቸው ከከሰሙላቸው በኋላ ወይዘሮ ይታከቱን ጠቅልለው ፣ አከራይተውት በነበረው ቤታቸው በሰላም መኖር ጀመሩ ።

ከዚህ በኋላ ፣ ብዙም ሳይቆይ የታጎሣሥ ፲፱፻፶፫ቱ የመፈንቀለ አገዛዝ ሙከራ ተደረገ ይሽም በዕድርተኞች ላይ አዲስ ጣጣ አመጣ.....

ከዕለታት አንድ ቀን እንደዚያ ሆኖ ከተማው መለስተኛ ርኃታ አግኝቶ በነበረበት ወቅት ፣ አንዲት የጎዘን ከል የለበሰች ሴት ሁለት ሕፃናት ይዛ ወደ ወይዘሮ ላቀች ቤት ሔዳ ከጫማቸው ወደ ቀችና ፣ "እመቤቴ ፣ ድሮም እዚህ የመጣነዉ እናንተን ተማምነን ፣ እናንተን ተስፋ አድርገን ነው ። አሁን ባለቤቴ እነዚህን ሕፃናት ጥሎ በእምባጓሮው ጊዜ ሞተብኝ ። አሁን ችግሬም በዛ ፤ እጅና እግሬን አሰረው ። ልጆቹን ይዤ ወደ አገር ቤት ለመሔድ አስቤ ነበር ፤ግን የቤት ኪራይ አልከፈልኩም ፤ የሚቹን ባለቤቴንም ዐርባ አላወጣሁምና የዕድሩን ገንዘብ እንዲሰጡኝ ለአቶ ፍጡር እንዲነግሩልኝ ነው የምለምነው" አለች ፣ እንባዋን እያጮረፈች ። ልጆቿም እርሷን አይተው ማልቀስ ጀመሩ ።

"ባልሽ ምን ሆኖ ሞተ ?" አሉ ላቀች ።

"በእምባጓሮው ምክንያት ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ወታደር ነበር እንዴ?"

"አዎ፣ ክብር ዘበኛ ነበር።"

"ከየትኛው ዕድር ነበር የገባችሁት?"

"ከልጅ አድባሩ።"

"በይ እንግዲህ፣ እንኳን የጥጋብ ዋጋችሁን አገኛችሁ እንጂ፣ ለሕፃናቱ ስንል የሚገባሽን የዕድር ርዳታ እንዲሰጥሽ ለፍጡር እሰጠዋለሁ" አሉዋትና፣ እንባዋን እያባበሰች ተመለሰች።

ከቀናት በኋላ፣ ሸዋንግዛውና ላቀች ወደ ምሽጋቸው እስቲገቡ ድረስ በሚሉናቸው ሆነው ሲዝናኑ፣ እንደ ተለመደው ፍጡር ገብተው እጅ ነሥተው ቆሙ።

"ታዲያስ ፍጡሬ! በሠፈሩ፣ በክተማው ምን ይወራል? የድሃ ልጅ ሁሉ ልክ አልገባም?" ብለው የክተማውን ወሬ ለመስማት የነበራቸውን ጉጉት አስቀደሙና ሲያጨበጭቡ፣ ሠራተኛዋ ሩጣ ገባች።

"ንሺ እባክሽ፣ ለፍጡሬ ብርጭቆ አምጭለት" አሉና፣ ወዲ ፍጡር ዘወር ብለው ደግሞ፣ "ተቀመጥ እስቲ! እንኳን መጣህ። አዎ፣ ሳልረሳው፣ እንዲት ያድባሩ ዕድርተኛ፣ ባሌ ክብር ዘበኛ ነበር። በበቀደሙ እምባንሮ ስለ ሞተብኝ፣ የዕድር ገንዘብ ያሰጡኝ ብላ አስቸግራኛለች። እና ታዲያ" ብለው ተና ግረው ሳያበቁ ፍጡር አቋረጡዋቸውና፣

"ሆ! ሆይ! ደግሞ ከድቶ ለሞተ ወንጀለኛ የዕድር ገንዘብ ሰጥተን በራሳችን ላይ እሳት እናንድድ?" አሉ ቆፍጠን ብለው።

"ልክ ነህ፣ እውነትህን ነው። እንዲያውም ሌሎች ዕድሮች ይከፍሉ እንደሆነ እየዞርክ ጠይቅና በአስቸኳይ ንገረኝ" አሉ ሸዋንግዛውም ቆጣ ብለው፣ ወሬውን ለታቅመው ወደ ቤተ መንግሥት ለመሮጥ እየቃጡ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ይኸውላችሁ የኔን ጅልነት ፣ እግዜር ያሳያችሁ ! የኔን ነገር! እንዲያው ነገሩን አዙሬ ሳላየው ከትልቅ ጉድ ውስጥ ገብቼ ጉዴ ፈልቶ ፣ አንገቴ ታንቆላችሁ ነበር ። ትላንት ከድቶ ጥጋብ አላስችለው ብሎ ለወጋን ወንበዴ ዐርባ መደገሻ ገንዘብ ልስጥ ነበር ማለት ነው ። በል በል አሁን ልጅ ሸዋንግዛው እንዳሉት በአካባቢያችን የሚገኙ ዕድሮች ይከፍሉ እንደሁ አጣርተህ በቶሎ አምጣ ። ነገሩን ቤተ መንግሥት ማወቅ አለበት" አሉ ወይዘሮ ላቀች ።

ከዚያ በኋላ ፣ አቶ ፍጡርና አቶ ሸዋየ አዲስ አበባ በነበሩት ዕድሮች እየተዘዋወሩ በግጭቱ ወቅት በውጊያው ላይ ለሞቱ ክብር ዘበኞችና አንዳንድ የፖሊስ አባሎች ቤተሰቦች የዕድር ገንዘብ የከፈሉትን ዕድሮች ለቅመው ለሸዋንግዛው አቀረቡ ።

ሸዋንግዛውም ፣ በግርግሩ ሰሞን ከብር ዘበኞችን የደገፉትንም ሆነ እርሳቸው የጠሉዋቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር ጨምረው ወደ ቤተ መንግሥት አቀረቡና እጅግ ስለ ተመሰገኑበት ፣ በጉዳዩ እንዲቀጥሉበት በምስጢር ታዘዙ ። ለዚሁ ሥራ የሚያውሉትም ወጭ ተመደበላቸው ። ክትትላቸውንና ጥናታቸውን በሰፊው ከቀጠሉ በኋላ ፣ ወደ ቤተ መንግሥቱ ባቀረቡት ሐሳብ ላይ ፣ "ከከዳተኞቹ ጋር ተሠልፈው ለሞቱ ወታደሮች ቤተሰቦች ገንዘብ የከፈሉ የዕድር ዳኞችም እየያዙ ፣ የከፈሉትን ገንዘብ ከሰጡዋቸው ሰዎች እየተቀበሉ እንዲመልሱ መደረግ ይኖርበታል ። ይህንንም የሚያስፈጽመው ልዩ ክፍል ያስፈልጋል" የሚል ማጠቃለያ ይገኝበታል ። ይህ ሐሳባቸው ሞገስ ስላገኘላቸው ፣ በእርሳቸው ኃላፊነት ከሥራ ላይ እንዲውል ተወሰነላቸው ።

ከዚያ በኋላ ፣ ሸዋንግዛው ሁለቱን ረዳቶቻቸውን ፣ ማለት ፍጡርንና ሸዋዬን ፣ በከተማው አሠማርተው ፣ የከሸፈውን ንቅናቄ የደገፉትን ፣ የንቅናቄውን ሁኔታ የሚያወራውን ሁሉ እየተከታተሉ እንዲጠቁሙ ለተመረጡት ግለሰቦች ዋነኞቹ አስተባባሪዎች አድርገው መደቡ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህም ሥምሪታቸው ስለ ተመሰገኑበት ፣ ሽዋንግዛው በሚ ኒስትር ማዕረግ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ሲሆኑ ፣ አቶ ፍጡር የዕድር ዳኝነታቸውን እንደያዙ የወረዳው ገዢ ፣ አቶ ሽዋዬ የዕድር ጸሐፊነቱን እንደያዙ የትምህርት ቤቱ ሥራ መሪ እንዲሆኑ አሾሙአቸው ።

ከዚያ በኋላ ፣ ሦስቱ ባለሥልጣኖች በከተማዪቱ ውስጥ ባሉት ዕድሮች መካከል ልዩ ተመልካቾች እያስገቡ ፣ የታጎሣሡ ንቅናቄ በሕዝቡ ዘንድ የፊጠረውን ስሜት ማስለቀም ጀመሩ ።

ፍጡር ፣ የወረዳው ገዢ ከሆኑ በኋላ የዕድሩን ጉዳይ ጠብ ርግፍ አድርገው ስለተዉት ፣ ዕድርተኞቹ በየቤታቸውና በየሠፈራቸው የሚያጋጥሙዋቸውን ችግሮች ለማመልከት ወደ ወረዳው ግዛት በነጋ በጠባ መመላለስ ግድ ሆነባቸው ። ፍጡር የማይፈጽሙላቸውንም ችግራቸውን ወይዘሮ ላቀችን መማፀን ዕጣ ፈንታቸው ሆነባቸው ። አንዳንዶቹም ፣ ለምሳሌ የዕድር ክፍያ የተከለከሉ ፣ ወይዘሮ ላቀችንና አቶ ፍጡርን እየዘለሉ ሽዋንግዛው ወደ ወይዘሮ ላቀች ቤት ሲገቡና ሲወጡ እየጠበቁ መማጠን ጀመሩ ። በነገሩ ሽዋንግዛው ስለ ተቸገሩበት ፣ የዕድሩን ጣጣ የሚሸከሙ ሌሎች ሰዎች እንዲመረጡ አዘዙ ።

ላቀችም ሆኑ ፍጡር ፣ ከሽዋንግዛው ውሳኔ የሚወጡ አልነበሩምና ፣ ለዕድሩ ዳኛና ገንዘብ ያዢ እንዲመረጥ ዕድርተኛው በጥሩንባ ተጠርቶ ተሰበሰበ ። ዕድሮቹ ብቻ ሳይሆኑ ፣ ሠፈሩ ብቻ ሳይሆን ፣ ወረዳው ራሱ ከነጓዝ ምንጓዙ በፍጡር መዳፍ ገብቷልና ፣ የፈለጉትን ለማድረግ የሚችሉ ሽዋንግዛውን ያህል ጋሻ መከታ ይዘዋልና ፣ እንኳን የጥሩምባቸውን ጥሪ ችላ ብሎ የሚቀር ቀርቶ ፣ እርሳቸው ባለፉበት መንገድ እንኳ ለመሔድ ሁሉም የሚርድበት ወቅት ነበርና ፣ ጤነኛ ቀርቶ ለልመና ወደየ አቅጣጫው የሚሠማራው ሁሉ ነበር የተሰበሰበው ። እስከዚያች ዕለት ድረስ በዚያች ግራር ሥር ያን ያህል ዕድርተኛ ተሰብስቦባት እንደማያውቅ የዕድሚ ጌቶች ይተርካሉ ። በዕለቱ የነበረው ሕዝቡ ሁሉ ዕድርተኛ አልነበረም ። ብቻ የወረዳው ገዢ ጥሩንባ አስነፍተው "ተሰብሰቡ" ብለዋል ስለተባለ ፣ ዕድር ያል

t.me/OLDBOOKSPDF

ገባውም ሁሉ በዕድርተኛነት ለመመዝገብና ለመታየትም ብሉ ነበር የተከማቸው ። በዚያ ዕለት የተሰበሰበውን ሕዝብ እንደ ዘወትሩ የግራርዋ ሥር ዐቅፎ ሊይዝ አልበቃም ፣ ሜዳዋም ራሱዋ አልበቃችም ነበር ። በዚያች ዕለት ፣ ወንበር ከየቤቱ መውሰድም ከወረዳ ገዢው ጋር እኩል ለመሆን እንደ መንጠራራት የሚያስቆጥር መስሎ ስለታዩ ፣ አብዛኛው ተሰብሳቢ በመስኩ ላይ ነበር የተሰጣው ። ደግነቱ ፣ በዕለቱ ተረኛ የነበረችው ፀሐይ ከደመና ጋር ድብብቆሽ የምትጫወትበት ሰዓት ኑሮ ፣ እንደ ወትሮው አልገነተረችም ነበርና ፣ ተሰብሳቢውም ማማረር ፣መራገምና ማሽሟጠጥ ከመጀመር ተቆጥቧል ።

"ደግሞ ዛሬስ ምን ልንባል ይሆን ?" ብለው የአድባሩ ዕድርተኛ ለጓደኛቸው ሹክ አሉ ።

"እንግዲህማ ምን የማይሉት ይኖራል ? ሠፈሩንና ዕድሩን ቀርቶ ወረዳውን ጨብጠውታል" ብለው መለሱላቸው ጓደኛው ።

"ምናልባት ፣ እቴን ላቀችን ልድር ነውና ለሠርጉ መደገሻ ገንዘብ አዋጡ ሊሉን ይሆን ?" አሉ የመጀመሪያው ነገር አቀንቃኝ ።

"ምናልባት ፣ አዋሻኪያቸውን ሸዋዬን ፣ 'ተቀመጥ በወንበሬ' ተናገር በአንፈሬ' ብዬ የዕድር ዳኝነቱንና ገንዘብ ያዢነቱን ሰጥቸዋለሁና ፣ ከዛሬ ጀምራችሁ ተገዙለት ሊሉንስ እንደሆነ ?" አሉ ሁለተኛዉ ።

"መቸም የእነታቸው አልጋ ወራሽ ናቸውና ፣ የመሬት ኪራይ ጨምሬያለሁ ቢሉስ ?" ሲሉ አንዱ ፤

"እሀ ፣ ታዲያ የልጅ አድባሩን ጢሰኞች ለምን ይሰበስባሉ ?" ብለው መለሱ ሁለተኛዉ ።

"ከእንግዲህ ወዲያ ደግሞ ፣ እንኳን ባድባሩ ርስት በወረዳው በሚኖረው ጢሰኛ ላይ የመሬትና የቤት ኪራይ ጨምሬያለሁ ቢሉስ ማን ይከለክላቸዋል ?" ብለው መለሱ እኒያኛው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ተሰብሳቢዎቹ ፣ ስለ ዕለቱ ስብሰባ የየበኩላቸውን ግምት እያነሡ እየጣሉ ሲወያዩ ፣ አቶ ፍጡር በሠፈሩ በታወቁ አዛውንቶችና በጥቂት ፖሊሶች ታጅበው ብቅ ሲሉ ፣ ረጋ ብሎ ሲጫወት የነበረው ተሰብሳቢ መቋነጥነጥ ጀመረ ።

"እናንት በዚያ በኩል ያላችሁት ወደዚህ ፣ በዚህ በኩል ያላቸሁት በዚያ በኩል ተቀመጡ" ብለው የሥነ ሥርዓት ትእዛዝ ሰጡ ፣ ቱልቱላ ነፈሱ ።

"ጀመሩ እንግዲህ ሰውን ቅጡን ሊያሳጡ" ኦሉ እንዲት ዕድርተኛ ።

"ምን ያድርግ ? እርሱስ ለእንጀራው አይደል ?" አሉ የቱልቱላ ነፊው የጠላ ቤት ጓደኛ ።

ወዲያው አቶ ፍጡር ከነአጃቢዎቻቸው ሲደርሱ ፣ ከተሰብሳቢው ሕዝብ ከግንባር በኩል ተቀምጦ የነበረው ብድግ ሲል ፣ በስተኋላ የነበረው ደግሞ ሸብረክረክ እያለ ተቀበላቸው ።

ከፍጡር አጃቢዎች ጥቂቶቹ ሲቀመጡ ፣ ገሚሶቹ ደግሞ በስተኋላ በኩል ቆሙ ።

" 'ጉድ ሳይሰማ መስክረም አይጠባም' ይባላል ። እንዲህ ተጀንኖ የመጣው ምን ሊናገር ይሆን ?" አሉና የአድባሩ ዕድርተኛ ፣ ለብጤያቸው ሹክ አሉ ።

"መቸም ይህ ሠፈር ለጉድ የፈጠረው ፣ ጉድ የሚፈልቅበት የጉድ አውድማ አይደል ? ጉድን በገሃድ እያየን ጉድ ልንሰማ ነዋ !" ብለው መለሱላቸው — ብጤያቸው ።

ተሰብሳቢዉ ፍጡርንና አጃቢዎቻቸውን አንዳንዱ በንቀት ፣ አንዳንዱ በትዝብት ፣ አንዳንዱ በጥላቻ ፣ አንዳንዱ በሙግሳ ፣ አንዳንዱ በሣቅ ፣ አንዳንዱ በበቀል ዐይን ሲመለከታቸው ፣ እነርሱም እንደዚሁ አፍጥጠባቸው የነበረውን ሕዝብ በንቀትና በጥርጣሬ ሲመለከቱት ፣ ለዐይኖቻቸው ማረፊያ የሚሆኑ ሴቶችንም እንደዚሁ ተራ በተራ በጉጉት ይቃኙዋቸው ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የተሰብሳቢዉና የሰብሳቢዎቹ ገጽታ በዚያ ላይ እንዳለ ፣ ሸዋዬ ተነሣና ይዘት ከነበረው ማጎደር አንድ ወረቀት አውጥቶ ፣

''ዘዛሬው ስብሰባችን የወረዳዉ ገዢና የዕድራችን ዳኛ የሆኑት አቶ ፍጡር ተሰማ በመካከላችን ስለ ተገኙልን እጥፍ ድርብ ደስታ ሊሰማን ይገባል ።

የስብሰባችንም ዋና ዓላማ ፣ የዕድራችንን ጉዳይ በማስመ ልከት በችግሮቹ ላይ ለመነጋገር ፣ ከዚህም ሌላ የወረዳው ገዢ የሚሰጡንን ምክርና ትእዛዝ ለማዳመጥና በሥራም ላይ ለማዋል ነው'' ብሎ ሲቀመጥ ፣

አቶ ፍጡር ቀጠል አድርገው ተነሡና ፣ ''እንደምታውቁት ያለብኝ የሥራ ኃላፊነት ከባድ በመሆኑ የተነሣ ፣ ስለ ዕድራችን ተገናኝተን ለመነጋገር አልተመቸንም ነበር ። ለወደፊቱም ቢሆን የወረዳችን ሕዝብ ብዛትና ችግር ከሌሎቹ ወረዳዎች ለየት ያለ በመሆኑ ፣ ታላላቅ ባለሥልጣኖችም የሚኖሩበትና የሚመላለሱ በት በመሆኑ ፣ ችግሮቹን ለማስወገድና ልማቱን ለማሩጠን ቀን ከሌሊት የሚያደክም ሥራ ስላለበት ፣ እኔም የወረዳ ገዢነ ትን ያህል ኃላፊነት እያለብኝ የዕድሩን ኃላፊነት በብደራቢነት ለመያዝ ስለማያመቸኝ ፣ ቀጥሎ በማቀርበው አኳኋን እንዲሠራ በበኩሌ ወስኛለሁ ።

1ኛ. ዕድሩ ''የወይዘሮ ላቀች ዕድር'' ተብሎ እንዲሠየም ፣

2ኛ. የዕድሩ ዳኛ አቶ ሸዋዬ እንዲሆን ፣

3ኛ. ምክትሉ ዳኛ አቶ ጠና እንዲሆን ፣

4ኛ. ገንዘብ ያዢ ያው አስተዛሬ እንደ ቆየው እሜቴ መይዘር ላቀች እንዲሆኑ ።

''ከዚህ ሌላ ፣ እንደ በፊቱ ስለ ሠፈሩና ዕድሩ የሚቆረቆሩ ፣ የዕድርተኞችን ጉዳይ በቅርብ የሚከታተሉና የሚቈጣጠሩ በሠ ፈራችን ውስጥ የታወቁ ሽማግሌዎች እንድትመርጡ አሳስባ ለሁ'' ብለው ፣ የሺህ ዓመታት ገዢነትንና ዘለዓለማዊ ነዋሪነትን

t.me/OLDBOOKSPDF

ለቤተ መንግሥቱና ለዕድሩ አባላት ተመኝተው ሲቀመጡ ፣ ገሚሱ ለብ ያለ ፣ ገሚሱ ቀዝቀዝ ያለ ጭብጨባ ተቀበላቸው ።

''እህ ፣ ምነው ከሹመቱ ላይ ወይዘሮ ያታነቱን ረሱዋቸው፣ ባይሆን ምክትል ገንዘብ ያገረነቱን አይሰሩዋቸውም ነበር?'' አሉና አንድ ተረበኛ አሽሟጠጡ ።

''ምናልባት እርሳቸውንማ ለምክትል ወረዳ ገዢነቱ አስበዋቸው ይሆናላ'' አሉ ሌላው ተረበኛ ።

ተሰብሳቢዎቹ እርስ በርሳቸው እየተገለማመጡ ፣ እየተገሙሻሸሙና እየተሳሳቁም ደቂቃዎች ከአለፉ በኋላ ፣ ሽዋዬ ተነሣና ፣

''እንግዲህ የወረዳ ገዢውን ሐሳብ መሠረት አድርገን ፣ በጉዳዩ ላይ የየበኩላችንን ሐሳብ እንድንሰነዝር ያስፈልጋልና ፣ ሐሳብ ያላችሁ በሉ ሰንዝሩልን'' አለና ተቀመጠ ።

''ስንት ሽማግሌዎች ነው የምንመርጠው?'' አሉ ጠያቂው ።

''እንደ በፊቱ አምስት ፣ ያለዚያም ሰባት'' አሉ ፍጡር ።

''እንደ በፊቱማ ከሆነ ከሁለቱም ዕድሮች ነው መምረጥ የሚገባን ?'' አሉ ሌላው ጠያቂ ።

''ሁለት የሚባል ዕድር የለም ፡ ቀርቷል። አንድ ዕድር አንድ ሥያሜ ፣ አንድ ዳኛ ብቻ ሆኗል'' አሉ ፍጡር ፣ የወረዳ ገዢነቱ ሥልጣን እየተጫጫናቸው ።

ወዲያው ምርጫው ቀጠለና ፣

፩ኛ. አቶ ይጥና ከምክትል ዳኝነቱ ጋር ሽማግሌም እንዲሆኑ ፤

፪ኛ. አቶ ዘይኑ

፫ኛ. አቶ ቡልቻ

፬ኛ. ወይዘሮ አዛለች

t.me/OLDBOOKSPDF

፭ኛ. ወይዘሮ አልጋነሽ

፮ኛ. አቶ ሥዩም

፯ኛ. አቶ ሺበሺ

፰ኛ. አቶ ንጉሤ ተመረጡ ።

በዚህ ጊዜ ባላምባራስ ሽንቁጥ የተባሉ በሠፈሩ የታወቁ ሽማግሌ ተነሡና ፣

"መቸም የዕድሩን ታሪክ ሁላችንም እናውቃለን ፣ አሁን መዘርዘር አያሻኝም ። ከዚህ ቀደም ሁለቱ ዕድሮች በየበኩላቸው ሽማግሌዎቻቸውን ይምረጡ በተባለበት ጊዜ ፣ መምሬ በዕውቀቱን ሁላችሁም ደስ ብሏችሁ መርጣችኋቸው እንደ ነበር ይታወቃል ። ታዲያ ከእነዚያ ጥሩተኞች ናቸው ከተባሉት ጋር አብረው ተጠልተው ነው መሰለኝ ፣ አሁን ስማቸው ሲነሣ አልሰማሁምና ፣ ጥሩት ሠርተው ከሆነ ይቅርታ ይደረግላቸውና ከሽማግሌዎቹ ጋር ይሥሩልን" ብለው ሲናገሩ ፣ ደመቅመቅ ያለ ጉርምርምታ አስነሣ ።

ባላምባራስ ፣ በልጅ አድባሩ ዕድር ውስጥ ከሚገኙት ማለፊያ ማለፊያ ቤቶች ባንደኛው በቅርብ ጊዜ ተከራይተው የገቡ ፣ በሌሎች አካባቢዎችም ማለፊያ ማለፊያ ቤቶች የሚያከራዩ ፣ ከዚያም ሌላ ትልቁ ልጃቸው የዋና ዲሬክተርነት ሹመት ያለው ፣ ቀጥላ ያለችው ልጃቸው ያንድ ሻለቃ ሚስት የሆነች ፣ ሦስተኛው ልጃቸው በማዘጋጃ ቤት ወፈር ያለ ሹመት ያለውና ፣ ሌሎችም ላቅ ደመቅ ያለ ሹመት ያላቸው ወንድሞችና ወዳጆች ያሉዋቸው የተከበሩ ናቸው ። ወደ ቤተ መንግሥቱም እየገቡ እጅ እንዲነሡ የተፈቀደላቸው ስለ ነበሩ ፣ ተጨማሪ ክብደት ያላቸው ነበሩ ። በእነ አቶ እንደሻውና በእነመቶ አለቃ ከበደ ላይ በተፈጸመው ግፍ የሚያዝኑ ነበሩ ።

የእርሳቸውን ሐሳብ ወረዳ ገዢውም ሆኑ ዕድርተኞቹ ሊያንጠራጥሱት ስላልደፈሩ ፣ የመምሬ በዕውቀቱን አባልነት የሚስማሙበት መሆናቸውን አመኑ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እስታሁን የተመረጡት ሰባት ደርሰዋል ፥ ታዲያ ማን ኛቸውን አስቀርተን መምራን እናስገባለን ?" ብለው ወረዳ ገዢው አስተያየት ጠየቁ ።

"ከሁለቱ ሴቶች አንደኛዋ ትቅርና ፥ መምራ ይተኩ ። የሠ ፈራችን ሴቶች እንደሆኑ አንዱዋ በቃኝ ናት" አሉ ባላምባራስ ።

"እህ ፥ እኒህ ሰው ጤና የላቸውም እንዴ ?" አለና ሽዋዬ አጉረመረመ ። ተሰብሳቢውም እርስ በርሱ ተጉሻሸመ ።

"ታዲያ ከሴቶቹ ማነኛቸው ይቅሩ ?" ሲሉ ፍጡር ፥

"እርስዎ ይምረጡዋ !" አሉ ባላምባራስ ፤ በዚህ ጊዜ ተሰ ብሳቢው ሁሉ ሁለቱን ሴቶች ለማየት አንገት አንገቱን ማስ ገግ ጀመረ ።

"እኮ ሁለቱ ሴቶች የትኞቹ ናቸው ?" ብለው ወረዳ ገዢው ሲጠይቁ ፥

"እስቲ ወይዘሮ አዛለችና ወይዘሮ አልጋነሽ ወደዚህ ቀረብ በሉ" ብሎ ሽዋዬ ትእዛዝ ሰጠ ።

ወይዘሮ አዛለች ቀላ ብለው ረዘም ፥ ቀጠንና ፥ ጠና ያሉ ሲሆኑ ፥ ወይዘሮ አልጋነሽ ደግሞ መካከለኛ ቁመት ፥ ከሙሉ ሰውነት ጋር የተዋሐደ ጠይምነት የነበራቸው ፥ በዕድሜያቸ ውም መለስተኛ የሆኑ ነበሩ ። ሁለቱም ተነሥተው እንደ ቆሙ ወረዳ ገዢውና ሽዋዬ ተመካከሩና ፥

"በኛ በኩል ወይዘሮ አልጋነሽን መርጠናል" ብለው ወረዳ ገዥው ሲናገሩ ፥ ሣቅና ጉርምርምታ አስተጋባ ።

አንድ ጐረምሳ ዕድርተኛ ተነሣና ፥ "ሁለቱ ዕድሮች ከተ መሠረቱና እንደገናም በፊተኛው ወረዳ ገዥ ትእዛዝ አንድ እን ዲሆኑ ከተወሰነ ወዲህ ፥ እስከ ዛሬ ድረስ ሒሳብ ተዶርጐ የግ ንዘባችንን ሁኔታ ሰምተን አናውቅም ። ምን ያህል እንደ ተዋጣ ፥ ምን ያህሉ ለዕድርተኛ እንደ ተከፈለ ፥ በገንዘብ ያገ እጅ ምን ያህል እንደሚገኝ ሰምተን አናውቅም ። በሌሎቹ ዕድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሮች ግን ፣ ይህ ነገር ይሠራበታል ። ራሱን የቻለ የሒሳብ ሠራ ተኛና ተቆጣጣሪም ያላቸው ዕድሮች ሞልተዋል ። ታዲያ ይህ ጉዳይ እስከ መቸ ችላ ተብሎ ይኖራል?" ብሎ ሲናገር ፣ የግራርዋን ቅጠል ሊያራግፍ የሚችል ጭብጨባ ተመረቀለት።

"መልካም ሐሳብ ነው ። እኛም አስበንበታልና ፣ ለወደፊቱ ከእነሽዋዬ ጋር አብረህ እንድትሠራ በበኩሌ መርጨሃለሁ" አሉት ወረዳ ገዢዉ ።

"አይ ! እኔማ በሌላ ወረዳ ቤት ተከራይቼ መሔዴ ነው ። ነገሩን ያነሣሁትም ከመሔዴ በፊት ምን ያህል ገንዘብ እንዳለን ለማወቅ ብዬ ነው" አለ ።

"ታዲያ ሠፈሩን ለቀህ እምትሔድ ከሆንክ የሆነውን ያህል ገንዘብ ቢኖረን ምን ያደርግልሃል ? የሚመለስልህ ሳንቲም እን ደሁ አይኖርም" አሉት የወረዳዉ ገዢ ፣ 'አብረህ ሥራ' ብለው መርጠው ፣ እንደ ሽዋዬ በጥቅም ዐሥረው ፣ በመዳፋቸው ውስጥ ለማግባት ያቀዱት ዘዴ እንደ ከሸፈባቸው ተረድተው በእስተ ያየታቸው እየገረመሙት ።

"እርሱም ለቆ ቢሔድ ሌላ ሒሳብ ዐዋቂ አሁኑኑ እንምረጥና የዕድሩ ገንዘብ ልኩና ቅጡ ቢታወቅ ሁላችንም እንወዳለን ፤ የምንደግፈው ሐሳብ ነው" አሉ ባላምባራስ ሸንቁጥ ።

አቶ ፍጡርና ሽዋዬ ደነዘዙ ። እርስ በርሳቸው ተንሾካሾ ኩና አንገታቸውን ነቃንቀው ፣ "እኛም እንስማማለን ። ቅድም ምኮ ተናግሬያለሁ ። አሁንም የሒሳብ ሥራ ልምድ ያለው ሰው ከመካከላችን እንፈልጋለን" አሉ ወረዳ ገዢው ። "በእውነቱ ሠፈ ሩን ለቅቄ የምሔድ ብሆንም ፣ አንዳንድ ጉዳዮችን ማንሣትና ማሳሰብ ይገባኛልና የዕድሩ ደንብም መለወጥ አለበት ። እስከ መቸ ድረስ ነው ባለርስቶች ያውም ዛሬ ከመካከላችን የሌሉ ሰዎች ባወጡት ደንብ ዕድሩ ታንቆ የሚኖረው ?" ብሎ ያ ጐረምሳ ተናግሮ ገና ትንፋሹን ሳይውጠው ፣ ነጐድጓዳዊ ጭብ ጨባ አስተጋባለት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሞብጨባውና ትርምስምሱ ገና ሳይገታ ፣ ፍጡርና ሽዋ ዮም እንገት ላንገት ገጥመው በመንሾካሾክ ላይ እንዳሉ ፣

''እንዴነሽ እንዴነሽ ! እንዴነሽ ገዳሜ

ዛሬ መሞቱ ነው ፣ ትላንት ታምሜ''

እያለ ደባልቀው ብቅ ሲል ፣ ወረዳ ገዢውም ቅስማቸው ስብር አለና ፣ ከወደ ኋላቸው ከነበሩት ፖሊሶች አንዱን ጠቅሰው ደባል ቀውን እንዲያባርር አዘዙት ። ደባልቀው ግን ፣ እንደ እምቦሳ እየዘለለ ዶረሰና ፣ እንደ ተለመደው ቆም ብሎ ፣

''ፍጡር ይታክቱን ሲነጥቅ ሲቀማ

ወረዳውን ሰጠው የእጎቱ ውሽማ''

ብሎ ሲዘፍን ፣ እርሳቸውም ብድግ ብለው ሲሔዱበት ሲቃጣ ቸው ፣ የተሳከው ፖሊስ ዶረሰና ይዞ ሲያንገላታው ፣

''እይሆንም ! ከባለሥልጣን ፊት ድሃ ማንገላታት ነውር ነው ። በሠፈሩ ፣ በወረዳው የታወቀ ሕመምተኛ ነውና ይለቀቅ'' ብለው ባላምባራስ ሲቆጡ ፣

''እንዴ ፣ ምነው ጌታዬ ? ሰው እያዋረደ ይኑር ነው እንዴ የሚሉት ?'' አለ ሽዋዬ ።

''ታዲያ እንዳይዋረዱ መሆን ነዋ ! ደግሞስ ዕብድ ለፈለፈና ማነው ከቁም ነገር የሚቁጥረው ? ኃላፊነት ያለበት ሰውኮ ሁሉንም ካልቻለ ፣ በየምክንያቱ ያዘው ጥለፈው ካለ ደግ አይሆ ንም ። 'ሹመት ላወቀው ይከብደዋል ፤ ላላወቀው ያሳብደዋል' '' ብለው ሲሚገቱ ፣ ለእርሳቸው ተሚጋችነትና ለደባልቀው ግጥም ሕዝቡ አጨበጨበላቸው ።

''ፍጡር ፣ ትላንትና በእጎትህ ሞን ተሸመህ ፣ ዛሬ እኔን ታስ ደበድበኝ ?'' አለ ደባልቀው ፣ ከያዘው ፖሊስ ጋር እየተናነቀ ።

''እንተም ዝም በል አትለፍልፍ ! የማናውቀውን ነገር መና ገርህ ነው ? ነሁላላ !'' አሉ ባላምባራስ ጮክ ብለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

''ዘል እባክህ ወዲያ አላርልኝ ማያለም ! እነማን እንደ ላኩት በውቂያለው'' አሉ የወረዳው ገዢ ። ፖሊሱም በርግጫና በቡጢ ለኮኮ ለኮኮ እያደረገ አላረረውና ተመለሰ ።

''ዘሉ እንግዲህ ስለሞና ሞናዎቹ ጉዳዮች እንነጋገር'' አሉ ፡ወረዳው ገዥ ፡ ያባልቱው ያወረደባቸው ናዳ መንፈሳቸውን ስላሻከረባቸው የነገሩ ውል ጠፍቷቸው ።

''ሞና ሞናዎቹንማ ጉዳዮች ቅድም ያ ወንድሜ እንሥቲ ቸዋል'' አሉ ባላምባራስ ፡ ''አሁን እንግዲህ የሚቀረን እርስ ምን መርቅን ከዕድር ዳኝነትም ማሰናበትና አዲሶቹ ተሿሚዎች ስለ ዕድሩ ሒሳብና ደንብ መለወጥ ጥረት እንዲያደርጉበት የየ በኩላችንን ሐሳብ መስጠት ነው ።''

''የዕድሩን ደንብ ለመለወጥ እንኳ ሳያስቸግረን የሚቀር ኦደመስለኝም ። ብቻ'' ብለው አቶ ይጥና ተናገረው ሳይጨ ርሱ ''ከምኑ ላይ ነው የሚያስቸግረው ?'' አሉ ባላምባራስ ።

''እንዴ ! ባለርስቶቹኮ እንዳሉ ናቸው ፡ አልተለወጡም ። ርስቱም በይዞታቸው ሥር እንዳለ ነው'' አሉ ይጥና ።

''አድባሩም ኑሮአቸው በጠረፍ ሆኗል ። የፊታውራሪ እርገ ጣቸው ይዞታ የነበረውም እንደሁ ይኸው እየተለወጠ ነው....'' ብለው ባላምባራስም ተናግረው ሳያበቁ ፡

''እንግዲህ ይህን የመሳሰለው አተካራና አሉባልታ ነው አስልችቶን የኖረው ። ከእንግዲህ ወዲያ እንደዚህ የመሳሰለ ንትርክ ለመስማት አንፈልግም ። ያም ሆነ ይህ ፡ ማነኛውንም ነገር ይኸው እንግዲህ የሚወስኑት ዳኞቹ ናቸው ። እኔም ያው መቸም የምኖረው አብሬያችሁ ስለሆነ ፡ በሚቸግራችሁ ሁሉ ምክሬንና ዕርዳታዬን ከማካፈል አልቆጠብም ። ዛሬ ግን ወደ የጉዳያችን ብንሔድ የሚከሩ አይመስለኝም ። ነገሩን የጨረስን ይመስለኛል'' ብለው የወረዳዉ ገዥ ብድግ ሲሉ ፡ አብረው የነበሩትም ተነሡ ።

''አሁን የየወሩን መዋጮ እንድትከፍሉና ፡ ዛሬ የተመረ ጣችሁትም ሳምንት እዚው ቦታ ተገናኝተን እንድንነጋገር አደራ

t.me/OLDBOOKSPDF

እላለሁ'' ብሎ ሸዋዬ ትእዛዘ እንደሰጠ ፣ ሁሉም ወደየቤቱ ማዝገም ጀመረ ።

በሳምንቱ በተደረገው የሽማግሌች ስብሰባ ፣ ራሱ ዳኛው ሸዋዬና ሦስት አባሎች ስላልተገኙ ፣ የተሰበሰቡት አራቱም በዕድሩ ጣጣ ለመነጋገር አልተቻላቸውም ነበርና ተለያዩ ።

የዕድሩ ኃላፊዎችና ሽማግሌዎች ስለ ዕድሩና ዕድርተኛው ደንታ ባይኖራቸውም ፣ በሠፈሩ ውስጥ በልዩ ልዩ ምክንያት እያሳበበ ሞት የሚወስዳቸው ጠይም በየሀገር ቤቱ ከሚኖሩ ዘመዶቻቸው ቤት እየገባ የሚነጥቅባቸው ሰዎች አልጠፉም ነበርና ፣ በደንቡ መሠረት የዕድሩን ገንዘብ ለማግኘት በመቸገራቸው አቤቱታቸውን ለወረዳው ጎሽ ፣ ለእጎትዮዋና ፣ ዐልፎ ዐልፎም ለውሽምዬው ማሰማት ግድ እየሆነባቸው በመሔዱና ፣ እነርሱም በየጊዜው የጎዘንቲኞች ሮሮ መሰማቱ ስለ ሰለቻቸው ፣ እነ ሸዋዬንም መቆጣት ስለ ጀመሩ ፣ ከወራት በኋላ የመጀመሪያውን ስብሰባ አደረጉ ። በዚያ ዕለትም የዕድር ገንዘብ አልተከፈለንም የሚሉ ጎዘንተኞች እየቀረቡ የደረሰባቸውን ጎዘን እንዲያስረዱ የተቀጠሩት ሁሉ በግራርዋ ሥር መከልከል ጀመሩ ።

የዕድሩ ዳኛና ጸሐፊው ፣ እንዲሁም ለገንዘብ ስብሳቢነቱ ወይዘሮ ላቀች የወከሉዋቸው አቶ ንጉሤ ዘግየት ቢሉም ፣ የቀሩት ሽማግሌዎች በሰዓቱ ተገኝተው ባለፉት ወራት እያንዳንዳቸው የሰሙትንና ያዩትን ይጨዋወቱ ነበር ።

''ይህን ዕድር መቸም በየጊዜው የ ጊበጠብጠው አያጣ ። ከመቶ አለቃውና ከአቶ እንደሻው ቀጥሎ ደግሞ ባላምባራስን አዘዘበት'' አሉ አቶ ዘይኑ ፣ ጨዋታ ሲጀምሩ ።

''ምን አዘዘበት ይላሉ ?'' አሉ አቶ ሥዩም ፣ ''አዘዘለት እንጂ ። ያለዚያማ ማን ከጉዳይ ይጥፈን ነበር ብለው ? እኛ እኛማ ስንጫጫ ብንውል ማን ከፋይዳ ይቆጥረልናል ? በተለይ ደግሞ ያ ከአቶ አያሌው ቤት በኪራይ ይኖር የነበረው ወጣት ስሙን ረሳሁት እንጂ ጉዱን ሁሉ ፍርጥርጥ አድርጐት ነው ያወጣው ።ደኅና ተከራካሪ ነበር ። ብቻ ምን ይሆናል? ሠፈር ሊለቅ ነው ።''

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለርሱማ መልቀቁ ነው የሚበጀው" አሉ ዘይኑ ፣ "እን ደዚያ ደፍሮ የተናገረውምኮ ሠፈሩን መልቀቁን ተማምኖ ነው ። ያለዚያማ እዚህ ቢቀመጥ ፣ እሺ ካለ ከጉያቸው ያስገቡታል ፣ ካፈነገጠም ያው ነው ፣ እንደነአቶ እንደሻው ምክንያት ፈጥረውና ለጣጥፈው ያስቀፈድዱታል ።"

"እሪ አሁንም ዘሚሔድበት እግዜር ያውጣው!" አሉ ሥዩም ።

"እኛንስ ምን አድርጉ ፣ ምን ፍጠሩ ሊሉን ነው ?" አሉ ዘይኑም ፣ የተመረጡበትን የዕድር ጣጣ በሚገባ ለመሥራት እንደማይችሉ የነበረባቸውን ጥርጣሬ ሲገልጡ ።

"ሌላ ምን ልንሠራ እንችላለን ?" አሉ ሥዩም ፣ "ደንብ አናሻሽል ፣ የዕድርተኛውን ገንዘብ ገቢ ፣ ወጪና ቀሪ ልናመሳ ክር አንችል ። ያው የተጣላ ማስታረቅና ጎዘን ደርሶብኛል ርዳታ ስጡኝ የሚለውን ፣ የባለርስቶቹን የመሬትና የቤት ኪራይ መክ ፈሉን አጣርተን ማቅረብ ነው ። ዳኛው ዳረጐተኛው ሸዋዬ ፣ ገንዘብ ከሩያዋ ራሳቸው ናቸው ። እነርሱ ካዘኑለት ያገኛል ፣ ከጨከኑበትም ያው ዕንባውን አፍስሶ ይቀራል ። ሌላ ምን ለማ ለት ይቻላል ?"

"እሱስ ይኸው ነው ፣ ሌላ መቸም የሚያረግ ነገር የለም" አሉ ዘይኑ ።

አቶ ይጥና እንደ ያረሱ ሰላምታ ተለዋወጡና ፣

"መምሬ በዕውቀቱ የታሉ ?" ብለው ሲቀመጡ ፣

"ዋናው ዳኛስ መቼ መጡ?" አሉ አቶ ሥዩም ።

"መምሬ እንኳ ፣ አይመቸኝም ፣ ወደ እንጦጦ የምሔድበት ፣ የማልቀርበት ጉዳይ አለኝ ሲሉ ነበር" አሉ አቶ ንጉሤ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ዳኛውም እንደዚሁ ነው ። 'የዛሬን ይቅርታ አድርጉልኝ፣ በመንግሥት በኩል የታዘዝኩት ሥራ ስላለኝ አይመቹኝምና ፣ የዕድርተኞቹን ጉዳይ አዳምጣችሁ ሳምንት ውሳኔ እንሰጥበታለን' ብለዋልና ፣ እንግዲህ ሰዎቹን አነጋግረን እንሸኛቸው" አሉና ይጥና ፣ የያዙትን ማጎደር እንደ ዐውዶ ንባብ ገለጥ አድርገው ፣

"እዎ ፣ የዛሬዎቹ ባለጉዳዮች ዐሥራ አምስት ገንዘብ አል ተከፈለንም የሚሉ ፣ ዐሥር ደግሞ በአንዳንድ ምክንያት የተጣሉ ናቸው ። እንግዲህ ማነጋገሩን እንጀምራለን" አሉ ።

"ለመሆኑ ፣ ጎዘን ደርሶብናል ፣ ገንዘብ ይከፈለን የሚሉት ሰዎች ሁኔታ እውነትነቱ ተመርምሩዋል ?" አሉ አቶ ንጉሤ ፣ ተኰልኩለው የነበሩትን ባለጉዳዮች በጥርጣሬና ተራ በተራ እየ ተመለከቱ ።

"የዚህን ሁሉ ሰው ጉዳይ በዛሬው ዕለት ልንጨርሰው እንችላለን?" ብለው ሥዩም ጠየቁ ።

"መቸም እነግዲህ የቻልነውን ያህል እንደሚሆን አደረግን ። የተረፈውን ደግሞ—" ብለው አቶ ይጥና ሳይጨርሱ ፣

"ጌቶቼ ! ድሃይቱን ለምን ሠርታ በላች ብለው ፣ ወገቤን ሰብረው አናቴን ፈልጠው ፣ ሐኪም መስክሮልኝ ፣ ሐኪም ቤት የምከፍለው እጥፍ—" ብላ አንዲት ኮረዳ ከተቀመጠችበት ተነሥታ ስትጮህ ፣ አቶ ይጥናም በተራቸው ያቋርጧትና ፣

"ማነው የደበደበሽ ?" አሏት ።

"የምሠራባቸው ሰውዬ ባለቤት ።"

"ከማን ቤት ነው እምትሠሪ ?"

"ከአቶ ጌታቸው ዘለቀ ቤት ።"

"ቤትዬዋ ምን ስላጠፋሽ ነው የደበደቡሽ ?"

"ወዬው ! እሳቸውማ እሚሉት ብዙ ነው ። 'እንዳንቺ ያሉት ያልበረደላቸው ናቸው ፣ ወንዱን ሁሉ እያሳሳቱ ዲቃላ እየታቀፉ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚያስቸግሩንና የሚያዋርዱን' እያሉ ጥዋት ማታ እላስቀምጥ ብለውኝ ፣ 'ደመወዜን ይክፈሉኝና ልሒድ' ብላቸው ፣ 'የሰበርሽውና ያጠፋሽው ዕቃ ፣ ፈታድ ሒደሽ ፣ ውለሽ ያደርሽበት ፣ ታመሽ የተኛሽበት ፣ እኔን የገላመጥሽበት' ብለው የሠራሁበትን ሒሳቤን ቢከለክሉኝ ለባልየው ነገርኳቸው ። እሳቸውም ፣ 'ጥሩ ታማኝ ፣ የልብ የምታደርስ ሠራተኛ ናትና ፣ መውጣት አይገባትም ። ምን አደረገችሽ ሁሉን ፣ ነገር ባገዘችሽ ለምን ታስወጫታለሽ?' ብለው ሚስታቸውን ተቆጡ ። እኔም ውዬ አደርኩ ። አሁን ከትላንት ወዲያ ፡ ሰውዬው ወደ ጠቅላይ ግዛት ለሥራ ሲሔዱ፣ ሴትዮዋ የእነታቸውን ልጅ አስጠርተው ለሁለት ይዘው ደበደቡኝ'' ብላ በሰውነቷ ላይ ያረፈውን ስንበር ለማሳየት ወደ ሽማግሌዎቹ ጠጋ ብላ ልብሷን ልታወልቅ ስትሞክር ፣ ''ግዴለም፣ ግዴለም ፣ ሴትዮዋ ልማደኛ ናቸው ። ከዚህ በፊትም እንዳንች የመሳሰሉትን ሴቶች ደብድበዋል ። እኛ አስጠርተን እንጠይቅልሻለን'' ብለዋት ይጥና ፣ ያች ዕድሜዋ ወደ ኻያ አምስት ዓመት የሚሆን የቀይ ዳማ ኮረዳ የዕንባ ዘለላዎቿን በነጠላዋ እየጠራረገች ስትቀመጥ ፣ አቶ ሥዩም ወደ አቶ ይጥና ጠጋ ብለው ፣

''ምክንያቱን ተረድተውታል?'' ብለው ጠየቁዋቸው ።

''የምኑን?''

''የድብደባውን። ''

''ምነው ? የሰሙት ነገር አለ ?''

''አይ ፣ እንዲያውም አንድ ታሪክ ትውስ ብሎኝ ነው'' አሉ ሥዩም ።

''እንደ ምን ያለ ?''

''እንደዚህች ልጅ እመቤት የሆነች ሴት አንድ ዕለት ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ ፣ ሠራተኛዋ አየቻትና የምታለቅስበትን ምክንያት ብትጠይቃት ፡ 'ባለቤቴ ትላንትና ካንዲት ሴት ጋር ውሎ በዚያው ማደሩንና ዛሬም እዚያው መሆኑን ሰማሁ' ብላ ነገረቻት ። ሠራተኛዋም ዕንባዋ እየተናነቃት ፣ ' እርስዎም ለኔ የነገሩኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

እኔን ለማናደድና ለማስለቀስ ብለው አይደለም ፡፡ አለቻት ይባላል ። እውንም የሁለቱ ሴቶች ጠብ ይኸው ላይሆን ይቀራል ብለው ነው ?" ሲሉ ሥዩም ፣

"ይኸማ ምን አንደና ሁለት አለው ?" አሉና አቶ ይጥና ፣ መገዛባቸውን ገለጥ ሲያደርጉ ፣ አንድ ዕድርተኛ ቀረብ ብሎ ፣

"ጌታዬ ! አባቴ መቶ አገር ቤት ወስጄ ቀብሬ ከተመለስኩ ይኸው ኻያ ቀን ሆነኝ ።ለዐርባው እንኳ እንዲሆነኝ በደንቡ መሠረት ዕርዳታውን እባክችሁ ስጡኝ" ብሎ ጠየቀ ።

"አባትህ የት ነበር የሚኖሩት ?" አሉ ይጥና ።

"ባገር ቤት ነበር ።"

"እዚህ ለምን መጥተው ኑረዋል ?"

"ታሞ መጣና ሳሳክመው ሞተብኝ ።"

"ለዚህ ሁሉ ምን ማስረጃ አለህ ?"

"ለምኑ ? አባቱ ለመሆኑ ?"

"አባትህ ለመሆናቸው ፣ ለመሞታቸውም የሚያውቅልህ ሰው ታገኛለህ ?"

"እንዴ ! አስክ ዛሬ ተጠይቆ የማያውቅ ጥያቄ እንዴት ይጠይቁኛል ?" አለና ፣ ዕድርተኛው አቤት ባይ አንገቱን አቀረቀረ ።

"አየህ ወዳጄ !" አሉት ይጥናም ፣ ሽማግሌዎቹንና የተኮለኮሉትን ሰዎች እየቃኙ ፣ "ሰማህ ወዳጄ ! አስመስሎ ፣ አስተዛዝኖ በሐሰት የዕድር ገንዘብ ለመውሰድ ብዙ ብዙ ተንኮል እየተሠራ ነው ። በቫር፡፡ የአንድ ዕድር አባል የሆነ ሰው ፣ አንድ ቀን ጥዋት ይነሣና አብሮት ከነበረ ወንድሙ ጋር ሆኖ አሉታውን ያቀልጠዋል ። ጮሪቤት ፣ ወዳጅ ዘመድና ዕድርተኛ ተሰብስቦ ቢጠይቃቸው ፣ 'ካገር ቤት ታሞ መጥቶ የነበረ ወንድማችን ሉሊት ቦለ ሞተ ፣ ወዳገር ቤት ወስደን ልንቀብረው ነው' ይላሉ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የዕድሩ ገንዘብ ይሰጣቸውና ፣ ሣጥናቸውን ተሸክመው መርካቶ ድረስ ከሔዱ በኋላ ፣ በአውቶቡስ ተሣፍረው ወደ ወሊሶ መንገድ እንደ ጀመሩ ፣ ነገሩ አልታመንላቸው ያሉ ዕድርተኞች ተከታትለው ሔደው ሣጥኑን አስከፍተው ቢያዩት ፣ በውስጡ ሽቀጣ ሽቀጥ ሞልቶበት ይገኛል ። ተዚያ በኋላማ የሆነውን ምኑን እነግርሃለሁ!'' ይሉና ትከ ብለው ሲያዩት ፣ እርሱም ወደ ኋላው ማፈግፈግ ይጀምራል ።

''ይኸውልህ ፣ በየዕድሩ እንደዚህ የመሳሰለ ጉድ ደርሷል ። ስለዚህ ፣ እኛም ለጥንቃቄ ስንል ፣ ለደንቡ ስንል ነው'' ሲሉት አቶ ሥዩም ቀጠል አደረጉና ፣

''ይኸኮ አዲስ ፈሊጥ አይደለም ። በጣሊያን ጊዜም እንደ ዚሁ ነጋዴዎች በሬሳ ሳጥን ጥይት ፣ ቦንብና ጠመንጃ እየሞሉ ፣ ዘመድ ሙቶብን ለመቅበር ወደ አገር ቤት መሔዳችን ነው እያሉ የጣሊያንን ዘብጥያ እያታለሉ ይወጡ ነበር'' አሉና ፣ እርሳቸውም ያን ከፊታቸው ቁሞ ወደ ኋላው ሲመለከት የነበረውን ዕድርተኛ ተመለከቱት ።

''እረ የኔውንስ ብዙ ሰው ያውቃል'' አለ እርሱም ፣ ዐይኖቹን እያቅለሰለሰ ።

''በል እስቲ እንግዲህ ፣ የሚታመን እንደሆነ ነገሩን በውል እናጣራውና እሜቴ ላቀችን ጠይቀን እንዲከፈል ይሆናል'' አሉት ።

''እንዴት እንደዚህ ይላሉ ? የአባቴን መሞት ርሶስ ያውቁ የለም ? እዚህ ያሉት ሁሉስ ያውቁ የለም ?'' አለ ዕድርተኛው ።

''አባትህንኮ በቁመናቸው ፣ በሕይወታቸው እያሉ አላየናቸውም ። ሬሳውን እኛ ገንዘን በሳጥን አላስገባነውም ። ይህ ነው ችግሩ'' አሉት ይጥናም ።

''ይኸ ሁሉ ምን ያደርጋል ? ታመው መጡ ፤ ሲታከሙ ሞቱብኝ ። ተቁጭራ ሠፈር ዘመዶቼን ጠርቼ ፣ ሳጥን ገዝተን ፣ አገር ቤት ወስደን ቀበርን ። ይህን ሁላችሁም ሰምታችኋል'' ሲል ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

''አዎ ሰምተናል ። ግን ተጠራጥረናል'' እንዳሉት ፣ አንዲት አሮጊት ቀረብ ብለው ፣

''የባለቤቱን መሞት እናንተም ፣ እሜቴ ላቀችም ታውቁታላችሁ ፣ አገር ያውቃል ። እንዴት ገንዘቡን አትከፍሉኝም ?'' ብለው አመለከቱ ። አቶ ይጥናም ማጎደራቸውን እያገላበጡ ፣

''አዎ ፣ እናውቃለን ። ባለቤትዎ በመጠጥ ኃይል ተሸንፈው ፣ በጨለማ ወዲያና ወዲህ እያሉ ከመንገድ ዳር ከነበረ ትልቅ ጉድጓድ ገብተው ፣ ወደ ኋላቸው ወድቀው ፣ አናታቸውን ድንጋይ መትቷቸው መሞታቸውን እናውቃለን ። በጎዘነም ዕለት የዕድሩን ድንኳንና ዕቃ ሁሉ ሰጥተንዎታል ፣ አቃብረን ዎታልም ። ግን የዕድሩን መዋጮ 'ችግረኛ ነኝ ፣ ይመወዜን አል ተቀበልኩም ። ልጅ ታሞብኝ ፣ ዘመድ ሞቶብኝ' እያሉ ባለቤትዎ አራት ወር ፀሎ ባለመክፈላቸው ሰርዘናችኋል ። የተዳረገላችሁን ዕርዳታ ከጉዳይ የማትጥፉ ከሆናችሁ የድንኳንና የዕቃ ኪራይ እንጠይቃችኋለን ። በጠቅላላው ግን ፣ የልጅ አድባሩ ጢስኞች በጣም ነው ያስቸገራችሁን ። ተቆጣጣሪ የለባችሁ አይደል ? ሰድ ሁናችኋል ። ከዚህ ሌላ እንግዲህ ስለ ባለቤትዎ ሞት ፣ 'ካሣ ይገባኛል 'የሚሉ እንደሆነ ፣ ከአውራ ጐዳና ላይ ጐተራ የሚያክል ጉድጓዱን መዝጋት አቅቶት መንገደኛውን ሁሉ የሚያጠምደውን ማዘጋጃ ቤቱን ይጠይቁ ። ይኸው ነው'' አሉዋቸው ።

''እኔ መቸስ የዕድሩን መዋጮ ሳይከፍል መቆየቱን የት ሀውቃለሁ ?'' አሉና ሴትዮዋ ተመለሱ ።

ቀጥለውም የሠፈሩ ሹም ቀረቡና ፣ ከነታቸው ኪስ ተጣጥፎ የተቀመጠ ወረቀት አውጥተው ፣ ለአቶ ይጥና ሰጡዋቸው። እርሳቸውም ወረቀቱን ተመለካከቱና ፣

''እንዴ ! እስተዛሬ ይኸ ሁሉ ሰው በሠፈራችን ሲኖር ዕድር ሳይገባ እንዴት ቀረ?'' ብለው የሠፈሩን ሹም መልሰው ጠየቁ ።

''ምን ያህል ሰው አድፍጦ ኑሩዋል ?'' አሉ ሥዩም ፣ በመነከል ጣልቃ ገብተው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እረ ጉድ ነው" አሉ አቶ ይጥና ፣ ሐያ አራት ሴቶችና ሐያ ሁለት ወንዶች በላጤነትና በደባልነት ፣ ዐሥራ ሁለት ባለትዳሮች በሠፈራችን ውስጥ እየኖሩ ዕድር አልገቡም ። ጉድ ነው ! እስቲ እስተዛሬ እደጋ ደርሶባቸው ቢሆን ምን ሊሆኑ ኑሩዋል ? ሠፈር ሊያሰድቡ ነበር ማለት ነው ። እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ ፣ እነዚህን ሰዎች በደባልነት የያዙ ወይም ለእነዚህ ሰዎች ቤት ያከራዩ ሁሉ ፣ በዕድሩ እንዲያስገቡ ጥብቅ ትእዛዝ እንዲነግሩ ። ያለዚያ በእነዚህ ሰዎች ላይ በሚደርሰው አደጋ ብቻ ሳይሆን ፣ በዕድር ያልተመዘገቡ ፣ ዕድሩ ያላወቃቸው ሰዎች በሠፈራችን መገኘታቸውም በኃላፊነት እንደሚያስጠይቃቸው ያስጠንቅቁዋቸው ። እምቢ ካሉም በሰብሰባው ጊዜ በዕድርተኛው ፊት ይጠየቁበታል ።"

የሠፈሩ ሹም ቀጠል አድርገው ፣ "አቶ ጐሽሜ ፣ አቶ ተክሌ፣ አቶ ቢነጋ ፣ ወይዘሮ አያልነሽ የተባሉት ዕድርተኞች ዘወትር እየሰከሩ ጐረቤትና ሠፈር በማስቸገራቸው ፣ ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ተመክረው ነበር ። እስተዛሬ አልሰሙም ፤ ያውናቸው ። ከእንግዲህ ውርድ ከራሴ ብያለሁ" አሉ ።

"የእነርሱን ነገር የወረዳው ገሸም በሚገባ አውቀውታል" አሉ ይጥና ፤ "እንዲያውም ለደባልቀው ግጥም እየነገሩ ሰው የሚያሰድቡ መሆናቸው ታውቋል ። ስለዚህ ፣ ይኸንኑ ሁኔታ ለፖሊስ ጣቢያ ከማስተላለፍ በቀር ሌላ የምናደርገው ነገር የለንምና ፣ ነገ ሰኞ አብረን ሔደን እናመለክታለን ።"

የሠፈሩ ሹም ፣ የዕለቱ ጉዳያቸው አላለቀም ነበርና ፣ እንደገና ከኪሳቸው ወረቀት አቀረቡ ። አቶ ይጥናም ወረቀቱን ተመለካከቱና ፣

"ይህም በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። ዕድርተኞች ሆነው በቀብር ላይ ካልተገኙ ሁልጊዜ በመቀጫ ብቻ መታለፍ የለባቸውም ። እነዚህ ዕድርተኞች ደጋግመው በስብሰባ ላይ ያልተገኙ ፣ በቀብር ላይ ተገኝተው አፈር ያላለበሱ ፣ በጎዘን ቤት እየተገኙ ጎዘንተኛን ያላጽናኑ ፣ በድንኳን ተከላ ያልተሳተፉ ናቸው ። በጠቅላላው በዕድሩ ላይ የታበዩ ናቸው ። ይህንኑ ገመና

t.me/OLDBOOKSPDF

ችውን ለዕድሩ ዳኛና ለዕድርተኛው ሁሉ አሳውቀን የምንሰር ዛቸው መሆኑን እየዞሩ በጥብቅ ያስጠንቅቋቸው ።''

''እነዚህ ሰዎች ደግሞ ፣ ቀን ቀን ከቤት ተኝተው እየዋሉ ፣ ማታ ማታ የትም የሚያድሩ ናቸው ። ምን እንደሚሠሩ ፣ በምን እንደሚተዳደሩ ተጠርተው ይጠየቁ'' ብለው የሠፈሩ ሹም ብጣሽ ወረቀት አቀረቡ ።

አቶ ይጥና ሁለት ዐይኖቻቸውን ጐልጉለው ፣ በዚያች ወረ ቀት ላይ አፍጥጠው ቆዩና ፣ ''ዳኛች ከመረመሩ ፣ ይናገራል ምድሩ'' ይባላልና ፣ ''እስቲ አቶ ሸዋዬ ባለበት ጠርተን እንመረምራቸዋ ለን ። እስተዚያው በሚገባ ተከታተሉዋቸው ። ቀን ቀን እየተኙ ማታ ማታ ጨለማ እየለበሱ ሠፈር እያተራመሱ ፣ እንዴት አብ ረን እንኖራለን ?'' አሉና ፣ ወደ ተከልኳዮቹ ዘወር ብለው ፣

''እንድ ነገር ላስታውሳችሁ ይገባኛል ፤ 'ዕድሩ ገንዘብ ይሰ ጠኝ ፣ ከተጣላሁት ጋር ያስታርቀኝ ፣ ችግሬን ያስወግድልኝ' ማለት ብቻ አይበቃም ። ሠፈሩ በየዕድርተኞቹ ጀርባ ታገለው ከሚመጠበት መንታፊዎች መጠበቅ አለበት ። በየቤታችሁና በየጐረቤታችሁ የሚኖሩትን ሰዎች ጠባይ ፣ ሥራ ፣ አኑዋኑዋር ታውቃላችሁ ። 'እገሌ እንዴት ይኖራል ? ከነማን ጋር ይውላል ? ምን ሠርቶ ምን ያገኛል ?' እያላችሁ መመራመርና እያንዳንዱን ነዋሪ ማወቅ ይገባል ።

''ሠፈራችን በሌባ ተደፍሮ አያውቅም ነበር ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ፣ ከወረዳው ውስጥ ጐላ ብሎ ተጋንኖ የሚጠራበት የቅጽል ስሙ ሆኖለታል ። በዚህ አስነዋሪ ሥራ ከሠፈራችን የተያዙ ወስላቶች እንዳሉም እናውቃለን ። ገና ያልተነቃባቸው ፣ ግበረ አበሮቻቸውን እያመጡና ቤት እየጠቆሙ የሚያስዘርፉ ንም ወራዳዎች በሠፈራችን መኖራቸውን አንጠራጠርም ። ዕድ ርተኛውን ለብስበን እስክናስረዳ ድረስ ሁላችሁም እንድታስ ቡበት አደራ እንላለን ።''

ከተሰብሳቢዎቹ በሌብነት የጠረጠሩት መንትፍ እንዳለ ሁሉ እያንዳንዳቸውን በጥንቃቄ ተመለከቱ ። ከተሰበሰቡት መካ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከል ፣ ሁለቱ እንገት አንገታቸውን ሲደፋላቸው ደግሞ በደበልጥ አፈጠጡባቸውና ፣

"እነኳን ከሠፈራችን ከመካከላችንም ቢሆን ፣ ፫ዚህ አሳፈሪ ምግባር የሚታመና ምናልባትም ለወደፊቱ የሚጠየቁበት ነው ፈሮች እንደማይታጡም አንጠራጠርም" ሲሉ ፣ እነዚያ ሁለት ሰዎች በደበልጥ እየተረተሩላቸው ሔዱ ።

"ባንድ በኩል እጅንና ምግባርን ሳያጠዱ ፣ ባንድ በኩል ደግሞ ጎዘን ደርሶብኛልና ገንዘብ ክፈሉኝ እያሉ ሠፈርተኛን ለመገረፍ መነሣት አንድ ቀን እጅ ያሲዛል ። ዋ ! ያን ዕለት ያን ሰው አያድርገኝ !" ሲሉ ደግሞ ፣ እነዚያ ሁለት ሰዎች እየተነሡ ለመፈርጠጥ ቃጣቸው ።

በዚህ ጊዜ ፣ ወይዘሮ አልጋነሽ ጣልቃ ገቡና ፣

"ሠፈሩ ምን አጠፉ ? ሌቦቹን አስያዘ ። ለወረዳው ፣ ለፖሊስም እያመለከተ ተረዳድቷል ። ስንት ነበሩ የተያዙት ። መልሰው በዋስና አንጀት በማያርስ ቅጣት እየተለቀቁ አይደለም ? ሆዳችን እያወቀ አጥራችን እየተጣሰ ፣ ቤታችን እየተሰረሰረ ፣ መስኮታችን እየተሰበረ ንብረታችን የሚዘረፈው ? 'የም ኮጠረጥሩትን ሰው በምስጢር አመልክቱ' እየተባለ አይደለም ሰዎቹ ከተያዙ በኋላ ውለው ሳያድሩ የተለቀቁት ? እንዲያውም የተረፈን የሌባ ጠላተ ማናቸው ። 'የጠቆመብህ እገሌ ነው ፤ ያስያዘችህ እገሊት ናት' እየተባለ እየተነገራቸው አይደለም ከተለቀቁ በኋላ ንብረታችን የተዘረፈው ? ቤታችን በደንጋይ የሚደበደበው ? እስቲ ነገሩ በውል ይታይ ። ሌባ የጠቆምነው ሰዎች አይደለንም ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተደጋግሞ ቤታችን የተደፈረው ?" አሉ ንዴት እየተናነቃቸው ።

እነዚያ ሁለቱ አንገታቸውን ወደ መሬት ደፍተው የነበሩ ሰዎችም ፣ አልጋነሽን እያጮለቱ ይመለከቱዋቸው ነበር ። አቶ ይጥናም በሦስቱ ዕድርተኞች ሁኔታ ተደናገጡበትና ፣

"መልካም ብለዋል ፤ እውነት ብለዋል ። የሠፈሩ ነዋሪ በመካከሉ ያሉትን እያስያዘ መልሶ እርሱው የሚጠቃ ከሆነ ፣ የምና

t.me/OLDBOOKSPDF

ደርገውን እናደርጋለን ። ሌላ ከያዘው መሣሪያና ወንድነት ያነሰ የለንም!'' አሉና ፣ ተሰብሳቢዎቹን በጥያቄያዊ አመለካከት ሲገ ረምሙዋቸው ቆይተው ፣

''በሉ እንግዲህ ፣ አሁን ወደ ዋናው ጉዳያችን እንመለስና ዛሬ የሁላችሁንም አቤቱታ ለማዳመጥና ውሳኔም ለመስጠት—'' ብለው ወደ ሠፈሩ ዘወር ብለው ሲመለከቱ ፣ የወይዘሮ ላቀች ሾፈር እየገሠገሠ ሲመጣ አዩትና ፣ እንደ ወትሮው ፣ ''ከዕድሩ ገንዘብ ላይ ይህን ያህል በቶሎ ላክልኝ'' የሚባሉ መሆናቸውን ዐውቀው ፣ ቦርሳቸውን አውጥተው የያዙትን ገንዘብ ልክ ሲመ ለከቱ ሾፈሩ ደርሶ እጅ ነሣና ጠጋ ብሎ ፣

''ዛሬ ሌሊት የዕቃ ቤቱ ተሰብሮ ፣ እህሉ ሁሉ ፣ ዕቃዎ ሁሉ ሲዘረፍ ማደሩን አሁን ከረፈደ ወዲህ ስላወቅነው ፣ ለፖሊስ እን ድታመለክቱልኝ ብለዋል'' ብሎ አረዳቸው ።

''ታዲያ ምን እንጠብቃለን ? ተጠርጣሪዎቹን ከዚህ ጀም ረን እንያዝ እንጂ !'' አሉና ይጥና ብድግ ብለው ፣ ''በሉ ያዙ ልኝ !''አሉና ፣ ራሳቸው አንዱን ሲይዙ ፣ የቀሩት ሰዎች ደግሞ አንደኛዉን ያዙላቸው ። እነዚያን አንገታቸውን ደፍተው ለመ ፈርጠጥ ፈራ ተባ እያሉ ፣ በደረሰባቸው ጎዘን ምክንያት የዕድር ዕርዳታ ሲጠይቁ የነበሩ ሁለት ዕድርተኞችን ይዘው ወደ ወይ ዘሮ ላቀች ቤት ሔዱ ።

በቀጠለው ስብሰባ ለመላው የወረዳው ሕዝብ የተላለፈ መን ግሥታዊ ትእዛዝ ስለ ነበረ ፣ የዕድሩ ጉዳይ አልተነሣም ነበር ። በዚያው ዕለት የወረዳው ገዥ አቶ ፍጡር በግዛታቸው ውስጥ በነ በሩት ዕድሮች እየተዘዋወሩ ለማዘጋጃ ቤት አማካሪነት ከየወ ረዳው ሁለት ሁለት አባላት እንዲመረጡ ስለ መፈቀዱ ዝርዝር ማብራሪያ ሲሰጡ ዋሉ ።

በዚያ ጊዜ ፣ በየወረዳው ሁለት ሁለት አባላት በሕዝብ እን ዲመረጡ ፣ ከመንግሥት ሠሥሪያ ቤቶች ደግሞ በጠቅላላ ስም ነት አባላት ተመርጠው እነዲላኩና ፣ የማዘጋጃ ቤቱ አማካሪዎች እንዲሆኑ ተወስኖ ስለነበረ ፣ በ፲፱፻፷፬ ዓ. ም. ላይ ዕድሮች በዚሁ ፖለቲካ ቀመስ ወጋ ወግ ለመሳተፍ በቅተው ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በሳምንት ሁለት ቀን ብቻ ለሚያደርጉትም ስብሰባ በእንድ ስብሰባ ሐያ አምስት ብር እንዲከፈላቸው ደንቡ የሚፈቅድ ስለ ነበረ ፣ በወር ሁለት መቶ ብር ለማግኘት ትንቅንቅና ዕድርተኛ ችንም ማባበል ተጀመረ ። ታዲያ አቶ ፍጡርም ራሳቸውንና ሸዋ ዬን አስመርጠው ሁለቱም የምክር ቤት አባላት ለመሆን ችለ ዋል ። ከዚያ በኋላ የዕድሩ ጉዳይ በምክትሎቹ እጅ ገባና እየቀ ዘቀዘ ሔደ ።

ሁለት ጊዜ በተደረገው ስብሰባ ብዙም ዕድርተኛ ያልወ ጣለትን ያህል ፣ ብርቱ የሚያደርግ እጋጣሚ በመድረሱ ፣ ባልተጠ በቀበት ዕለት የወረዳው ገዥ ትእዛዝ ተጨምሮበት ያስተጋባ የነበረውን ጥሩንባ ዕድርተኛው አዳምጦ ግልብጥ ብሎ ወጣ ። በዚያ ዕለት የተደረገው ጥሪ ለወይዘሮ ላቀች ዕድር ብቻ አልነ በረም ። በወረዳው ውስጥ በነበሩት ሌሎች ዕድሮችም ላይ የጥሪው ቱልቱላ ማታውን ጀምሮ እስከ ረፋዱ ድረስ ያስተጋባ ነበር ።

በዚያ ወረዳ ፣ ከዚያን በፊት ያን ያህል ሕዝብ የወጣለት ስብ ሰባ ተደርጎ አይታወቅም እስከ መባል ደርሷል ። የወረዳው ገዥ አቶ ፍጡር በመጀመሪያ ወደ ወይዘሮ ላቀች ሠፈር ዕድር ሔዱና በተዘጋጀላቸው ወንበር ላይ እንኳ ሳይቀመጡ ፣ከዕድርተኞቹ መካ ከል ልዩ ተመልካች እንዳለባቸው ሁሉ ገጽታቸውን በጎዘንና በቁጣ እየለዋወጡ ፣

''ሁላችሁም እንደምታውቁት ፣ በአገራችን ላይ መሪር ፣ እጅግ መሪር ጎዘን ደርሷል ። በዚህም ምክንያት በርካታ ሕዝብ የጎዘን ተካፋይነቱን ለመግለጽ ከየጠቅላይ ግዛቱና ከመላው ዓለም ወደ አዲስ አበባ መጉረፍ ጀምሯል ። የሚጉርፈውን ጎዘ ንተኛ ቤተ መንግሥቱ ብቻውን መሸከም ስለማይገባውና ፣ ሁላች ንም የጎዘኑ ተካፋዮች መሆናችን የታመነበት በመሆኑ ፣ እያንዳ ንዱ ዕድርተኛም ሆነ ዕድር ያልገባ ሁሉ የሚከፍለውን ገን ዘብ ልክ አሁን የዕድሩ ዳኞች ያስታውቋችኋልና ፣ በዛሬና በነ ገው ቀን እንድትከፍሉና በወረዳችን ስም ለቤተመንግሥቱ እን ድናበረክት ። እኔም ሌሎች ዕድሮች ስለሚጠብቁኝ ወደዚያው መሔዴ ነውና ፣ መዋጮውን ለድዕሩ ዳኞች እንድትከፍሉ'' ብለው ፣ በወይዘሮ ላቀች መኪናና ሾፌር ወደ ሌላው ስብሰባ ሔዱ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የዕድሩ ላኛና ጸሐፊ አንድ ሰፊ ወረቀት ከማኅደር አውጥተው ስም እየጠሩ ፣ የተጣለበትን ዕዳ መናገር ሲጀምሩ ፣ አቶ ሥዩም ነገሩ ስልቸት ብሏቸው ነበርና ፣ ከነበሩበት መቀመጫ እየተቁነጠነጡ የሚያጫውታቸው ወጻጅ ፍለጋ በዐይናቸው ሲማትሩ ፣ አቶ ዘይኑ ሁኔታቸውን ይመለከቱዋቸው ኑሮ ፣ ከነበሩበት አግዳሚ ወንበር ተነሡና ወደፊላቸው ሔደው ከጉናቸው ተቀመጡላቸው ።

"ምነው ? የሚፈልጉት ሰው ነበር እንዴ !" ብለው ዘይኑ ጨዋታ ጀመሩ ።

"እሀ ፣ እሀ ! እርስዎምኮ ጎዘንተኛ መሆንዎ ነው ። ምንስ ቢሆን እርስ ዎስ የየጁ ባላባት አይደሉ !" አሉ ሥዩም ፣ ዘይኑን በአሽሙራዊ አስተያየት እየተመለከቱ ።

"እና ከሚዋጣው ገንዘብ ትጥሉብኛላችሁ ማለት ነዋ !" አሉ ዘይኑም ፣ አሽሙሩን ባሽሙር ሲመልሱ ።

"እኛ መቼም የምናዋጣውን ገንዘብ በድምሩ መሰደን እና ስረከባለን ። በተወላጅነትዎ መጠየቅ የሚገባዎ ራስዎ ነዎት ።"
ሸዋዬ ቀንቶ ፣ "አቶ ሥዩም ገብሩ" ብሎ ተጣራ ።

"አቤት !"

"ሃምሳ ብር !" አለና ጥሪውን ቀጠለ ።

"መቀጫ ጭምር እንደሆነ እንጂ ፣ በዕድርተኛነቴስ የተጣለብኝ ትንሽ ነበር" አሉና ሥዩም እጉረመረሙ ። የዕድሩ ጸሮች የጣሉበትን ሒሳብ ዕድርተኛው ያለምንም ተቃውሞ ከከፈለ በኋላ ፣ ከወረዳው ጠቅላላ ሒሳብ የቀነሱለትን ያህል ቀንሰው ፣ የፈለጉትን ያህል አቶ ፍጡር ለቤተመንግሥቱ ባለሥልጣናች አስረከቡ ።

አቶ ፍጡርም በተመላሳዩ ሁኔታ በወረዳ ግዛታቸው ከነበረው ሕዝብ "የእንግዳ መቀበያ" እያሉ ልኩን እርሳቸው ብቻ የሚያውቁት ገንዘብ ሰብስበው ፣ ለቤተመንግሥቱ ባለሥልጣናች ስላቀበሉ በወረዳ ንጉሠነትና በዕድሮች አስተባባሪነት ያን ያህል ገጸ-በረከት

t.me/OLDBOOKSPDF

ለግቅረብ ከቻሉ ፣ ከፍ ያለ ኃላፊነት ቢሰጣቸው ደግሞ ፣ ገፋ አድርገው ገጸ-በረከት ሊያቀርቡ እንደሚችሉ ያመኑበት ባለ ሥልጣን ከአቶ ሽዋንግዛው ጋር ተመካክረው በአገር ግዛት ሚኒ ስቴር ውስጥ የሞና ዲሬክተርነት ሹመት እንዲሰጣቸው አደረጉ።

ይህም ምክንያት ሆነና ፣ በሽዋዬ እሳላቢነትና አስተባባሪ ነት በወረዳው ውስጥ ከሚገኙት ነዋሪዎች ሻል ሻል ያለ ገቢ ያላቸው ባዋጡት ገንዘብ ፣ በወይዘሮ ላቀች ቤት ዲል ያለ ግብዣ ተደረገላቸው ።

"የሚቀጥለው ዕዳችን ስለምን እንደሚሆን ልንገርዎ ?"አሉ አቶ ሥዩም ፣ በቀጠለው የዕድሩ ስብሰባ ላይ ከአቶ ዘይኑ ጋር ጉን ለጉን ተቀምጠው ሲጨዋወቱ ።

"ለሽዋዬ ሹመት ይሆናል ?" አሉ ዘይኑ ።

"አልደረሱበትም " አሉ ሥዩም ።

"ለወይዘሮ ላቀችና ለአቶ ሽዋንግዛው ጋብቻ ይሆናል" አሉ ዘይኑ ቀጥለው ።

"አልደረሱበትም" አሉ ሥዩም ፣ ዕድርተኛው ወይም የሠፈሩ ነዋሪ ሴላ መዋጮ የሚጠየቅበት ምክንያት እንደ ሐውልት ተገትሮ ይታያቸው ይመስል አሻግረው እየተመለከቱ።

"ርቆብኛል አልደረስኩበትም ፤ ይንገሩኝ ።"

"ለልዑል መኮንን እንዳዋጣነው ሁሉ ፣ ዛሬም ለእቴጌና ለልዑል ማህለ ሥላሴ መታሰቢያ ማሠሪያ ነው የሚሆነው" አሉ ሥዩም ፣ ከዚያ በፊት "ለልዑል መኮንን መታሰቢያ " እየተባለ በመላ ኢትዮጵያ ገንዘብ ሲዋጣ በነበረበት ጊዜ ሲፈጸም የነበረውን ምስቅልቅልና ዝርፊያ በዐይነ ሕሊናቸው እየተመለከቱ።

"እዱ እርሱማ አይሆንም" አሉ ዘይኑ ።

"ለምን አይሆንም ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ዛሬ አባ ሐና የሉማ!" ለልዑል መኮንን መታሰቢያ ግሡ ሪያ የሚሆን መዋጮ ሕዝቡ እንዲያዋጣ ሐሳብ ያቀረቡትና ያን ሁሉ ጣጣ አምጥተውብን የነበሩትኮ እርሳቸው ነበሩ ።"

"እንድ አባ ሐና ቢሞቱ ፣ በመቶ የሚቈጠሩ ሐናዎች መንግሥት ያጣል ብለው ነው?"

"የፊትኛውን አዋጥቶ ሳይጨርስ ፣ ደግሞ ለእቴጌዪቱና ለልዑሉ መታሰቢያማ አዋጡ ከተባለ ፣ የዕድሜ ልክ ዕዳ መሆኑ ነው ።"

"እረ በኛው ዕድሜ ተከፍሎ ያልቃል ብለው አያስቡ ፣ ለልጅ ልጅም ይተላለፋል" አሉ ሥዩም ።

"እኔኮ የራሴ ድርሻ አይደለም የሚያሳስበኝ ። የባላገሩን ሕዝብ ሲያንቁት ፣ እርሱ ደግሞ ወደኛው እየመጣ ሲያለቅስብን ነው የሚታየኝ ።"

ሁለቱ ይህን ሲጨዋወቱ ፣

"እንዲያው የእናንተ ነገርኮ አስቸገረኝ ። የመጣችሁት ለዕድር ስብሰባ ፣ እናንተ እንገት ላንገት ገጥማችሁ የምታወሩት ሌላ ። እስቲ አሁን ምን ተባለ? ምን ተነገረ?" አለና የዕድሩ ዳኛ ሸዋዬ ፣ በመካከል ጣልቃ ገብቶ ጠየቃቸው ።

"እኛምኮ የምናወራው ስለ ዕድሩ ነው" አሉ ሥዩም ።

"ስለ ዕድሩ ምንነት?" አለ ሸዋዬ ።

"በሚቀጥለው ስብሰባ ስለሚጣልበት መዋጮ" አሉት ሥዩም ።

"ይኸ ሠፈር መቼም አንዳንድ ነገር ቆስቋሽ አያጣ!" አለ ሸዋዬ ፣ የመቶ አለቃ ከበደና አቶ እንደሻው ትዝ ብለውት ፣ በዐይነ ሕሊናው ከአቶ ሥዩም ጋር እያስተያያቸው ።

"እየህ ወዳጄ!" አሉ አቶ ሥዩም ፣ አንገታቸውን እያወዛወዙና ሸዋዬን በዋያቄያዊ አስተያየት እያነጣጠሩበት ። "ስማህ

t.me/OLDBOOKSPDF

አቶ ሸዋዬ? ሁላችንም ከመጻሕፍትና ከጋዜጦች እንደምናነበው ከየራዲዮ ጣቢያዎች እንደምንሰማው፣ አንድ አገር፣ አንድ መንደር፣ እንዲያውም አንድ ቤተሰብ ነገር ቀስቃሽ፣ ነገር አመላላሽ፣ ነገር ጠንሳሽ፣ ነገር አነሣሽ፣ ነገር አተራማሽ እኖቶ እያውቅ ምና፣ ሠፈራችን ወይም ዕድራችን እንደዚህ የመሳሰሉትን ሰዎች ቢያፈራ አይገረምህ" አሉት፣ ገጽታቸውን አስቆጥተው።

አቶ ሥዩም፣ በዕድሜና በሥራ ልምድ ከሸዋዬ ላቅ ያሉ ነበሩ። እንዴ እርሱ በዘመናዊ ትምህርት ቤት ገብተው እስከ ከፍተኛ ክፍል ባይደርሱም ቅሉ፣ ለበር መክፈቻ ያህል ቀደም ብለው በቀሰሙት ዘመናዊ ትምህርት በጣሊያንኛ ቋንቋ የሚጻፉትንና የሚነገሩትን ጉዳዮች እዘውትረው የሚከታተሉ ናቸው።

የመቶ አለቃ ከበደንና የአቶ እንደሻውንም ሐሳብና ንግግር የሚያደንቁ፣ የሚደግፉ ከነበሩትም ዕድርተኞች እንዱ ናቸው። በዕድሩ ስብሰባ እዘውትረው ለመገኘት ሳይሳካላቸው ጉረው፣ በሽማግሌዎቹ ችሎት ከተመረጡ በኋላ ነበር ከስብሰባውም ከንትርኩም መሸሽ ያልቻሉት።

ገጽታቸውን እንደዚያ አስቆጥተው የሰነዘሩዋቸው ቃላት ከሬት የመረሩት ሸዋዬ ግን፣ ባልተለመደው ሁናቴያቸው ተደናገረና፣ "በሉ አሁን ያም ሆነ ይህ፣ ወደ ተሰበሰብንበቱ ጉዳያችን እንመለስ" አለና ግለታቸውን አበረደው።

* * *

የዕድሩ ደንቦች ሳይነኩ፣ የዕድርተኞቹም የውስጥ ችግር እንዳለ፣ ፲፱፻፶፬ ዓ.ም ወደ ማለቁ ተዳረሰ። የዕድሩና የዕድርተኞቹ ጉዳይ የሆነውን ያህልም ቢሆን፣ የሠፈሩ፣ እልፍ ብሎም የወረዳው አውታሮች የሆኑት ወይዘሮ ላቀች፣ አቶ ፍጡርና ሸዋዬ፣ በአቶ ሸዋንግዛው ጥላ ከለላነት ጣዕመ ኑሮአቸውን ቀጥለዋል። በአቶ ፍጡር ምትክ የወረዳው ገዥ ሆነው ተሹመው የሔዱትን ግራዝማች ሰይፉንም በከበባቸው ውስጥ አስገብተዋቸው ስለ ነበር፣ የዕድሩን ጉዳይ ቀርቶ የወረዳውንም ሥራ ሁሉ የለቀቁት ለእነርሱው ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

አቶ ሽዋንግዛው ፣ ምንም እንኳን ተጠቃለው ከወይዘሮ ላቀች ቤት ባይገቡም ቅሉ ፣ ከዋናው ቤታቸው ቅድሚያ ትኩረት የሰጡት ለሳቱ ነበር ። ሳቱም ቢሆኑ ሽዋንግዛውን ከጌጣ ጌጥ የወግ ዕቃቸው አስበልጠው ነበር የሚንከባከቡዋቸው ።

ቀደም ሲል ፣ በመሬት ላይ የሚገኘውን ምክንያት እየደረደረ ሲያስቸግር የነበረው ገባር ፣ ጢሰኛና ቤት ተከራይ ሁሉ ሽዋን ግዛውን እየፈራ ሰጥ ለጥ ብሎ መክፈል በመጀመሩ ፣ የላቁ የወር ገቢም ከሚያስተማምን ደረጃ ላይ ወጥቷል ። ከዚያ ላይ ደግሞ ፣ የፋጡር ሹመት ተጨማሪ ክብደት እየሰጠ መጥቷል ።

በሰኔ ወር ፲፱፻፶፬ መጨረሻ ላይ ፣ እንደ ተለመደው የወረዳው ገዥ ትእዛዝ ተጨምሮበት የወረዳው ዕድሮች ስብሰባ ተደረገና ፣ አቶ ፍጡር በየዕድሮቹ እየዞሩ የሰብሰባውን ምክንያት ሲያስረዱ ፣

"ከመካከላችሁ እኔን መርጣችሁ ለማዘጋጃ ቤት አማካሪ ነት እንደ ላካችሁ ሁሉ ፣ እኔም የወረዳው ሕዝብ የሚመሰገን በትንና የሚወደድበትን ሐሳብ ማቅረብና ሥራ ማከናወን ዋናው ግዴታዬ መሆኑን እምናለሁ ። ስለዚህ ፣ በዚህ ዓመት እያከታ ተለ ከባድ ጎዘን የደረሰባቸውን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችንን ማጽናናት ስላለብን ፣ ለልደታቸው መታሰቢያ የሚሆን ገጸ በረከት እንድናቀርብ ፣ እያንዳንዳችን በዕድሩ ዳኞች አማካይነት የሚወሰንብንን ገንዘብ በዚሁ ሳምንት እንድናዋጣ አሳስባችኋ ለሁ" አሉ ፣ በወይዘሮ ላቀች ዕድር በመጀመሪያ ተገኝተው ።

በዕለቱ የነበሩት ተሰብሳቢዎች ፣ እርስ በርሳቸው ከመተ ያየትና ከመጐሻሸም በስተቀር ፣ ሌላ ሐሳብ ፣ ሌላ ጥያቄ ፣ ሌላ ንግግር ማድረግ አልደፈሩም ነበር ። ስለዚህ የተጠየቁትን እያጉረመረሙ ከፈሉና ፣ አቶ ፍጡርና አንዳንድ የዕድር ዳኞች ገንዘቡን ሰብስበው ፣ በዘመኑ የተሻለ ነው ብለው ያመኑበትን ሥዕል አሠርተው ፣ "ለእንግዳ መቀበያም ቢሆን" ብለው ከገ ንዘብ ጋር በንጉሡ ልደት ዋዜማ ወደ ቤተመንግሥቱ ወስደው ለባለሥልጣኖቹ አስረከቡ ።

ዕድሩና ዕድርተኞቹ በዚያ ላይ እንዳሉ ፲፱፻፶፭ ገባ ። በዚሁ ዓመት በወይዘሮ ላቀች ዕድር የደረሰ ለውጥ ቢኖር ፣ ሌላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዕድር ለማቋቋም እንደ ታጎማሥ "ኩዴታ" የተደረገው ሙከራ ነበር ።

በልጅ አድባሩ ሠፈር ከነበሩት ነዋሪዎች አቶ ጸጋዬ የተ ባለ ሰው ቤት ተከራይቶ በገባ በሁለተኛው ወር ፣ እናቱ ሊጠ ይቁት ከአገር ቤት መጥተው አብረውት እንደ ሰነባበቱ ፣ በድን ገት ታመው ይሞታሉ ። አቶ ጸጋዬ ዕድር አልገባም ነበርና ፣ የእናቱን ሬሳ ብቻውን ታቅፎ ሲጮህ ሲያጓራ ይውላል ። ዕድ ርተኛም አልወጣ ። ድንኳንም አልተተከለም ፣ ጥሩንባም አል ተነፋም ፣ ወንበርም የለ ። ለነገሩ ያህል ግን ፣ ከቤቱ ተቀጣጥ ለው ተሠርተው ከነበሩት ክፍሎች የሚኖሩ ዐሥር የማይሞሉ ጐረቤቶቹ ተከልኩለውለታል ። እኩለ ቀን ሆኖ ፣ በሠፈሩ ነዋሪ የነበሩ ዕድርተኞች ያልሆኑ ወታደሮች ከየሥራቸው ሲመለሱ ነገ ሩን ይሰሙና ፣ ከመሥሪያ ቤት መኪና ለምነው ሬሳውንና ታዘንተ ኛውን ከነጐረቤቶቹ ጭነው ፣ ወደ ቤተክርስቲያን ወስደው ፣ ቱድንዱን ራሳቸው ቆፍረው ፣ አስፈላጊ ለነበረው ጣጣ ሁሉ ከየኪሳቸው ገንዘብ አዋጥተው የአቶ ጸጋዬን እናት ቀብር ያስፈጽማሉ ።

ከዚያ መልስም የዐሥር አለቃ ታደሰ ዕድር ያልገቡትን ሲቪ ሎችና ወታደሮች ሰብስቦ ፣ በዚያኑ ዕለት "እንረዳዳ" የሚል ዕድር ይመሠርታሉ ። በሳምንቱ የዕድርተኞቹ ብዛት ወደ ሠላሳ ይደርሳል ።

በሁለተኛው ሳምንት የዐሥር አለቃ ታደሰና ረዳቶቹ ተከሰው ከወረዳው ጽሕፈት ቤት ይቀርባሉ ። በዚህ ጊዜ ከሳሽ የነበረው አቶ ሸዋዬ ፣

"ከጥንት ጀምሮ የተቋቋመውን ዕድር ለመበታተን ፣ በዕ ድር ምክንያት አድርጎ ወታደሮች እንዲሰበሰቡና እንዲነሣሡ ለማድረግ ፣ ከአምና ወዲያ የከሸፈውን ተንኮል እንደገና ለመ ሞከር ሆን ተብሎ የተቋቋመ ዕድር ነውና ፣ በአስቸኳይ መፍረስና መሥራችቹም መቀጣት አለባቸው" ብሎ አስረዳ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የወረዳው ገዥ ግራዝማች ሰይፉም ፣ "የተጠራችሁበት ምክንያት ይኸው ነው ። ይህን ነገር ሠርታችኋል ፣ መይሰ አልሠራችሁም ?" ብለው እንዐሥር አሊቃን ጠየቁ ።

"እርግጥ ነው ፣ ዕድር አቋቁመናል ። ምክንያቱ ግን ከዚህ ቀደም ጉረቤታችን የነበረ ሰው እናቱ ሞተው የሚያቃብረው አጥቶ ሲቸገር ፣ ዕድርተኛም ባይሆን በመጠኑ ዕርዳታና ጎዘኔታ ሊያደርጉለት ሲገባ ፣ ሬሳውን አስታቅፈውት ዝም ስለታቸው እኛ ዕድር ያልገባነው ተሰብስበን ከአቃበርነው በኋላ ፣ እንደ ዐቅማችን ደግሞ ዕድር አቋቁመናል" ብለው መለሱ ።

"ከዋናው ዕድር ለምን አልገባችሁም ?" አሉና ግራዝማች ጠየቁ ።

"ከዋናው ዕድርማ እንዳንገባ 'እስክ ዛሬ የተከፈለውን ሐያ አምስት ፣ ሐያ አምስት ብር የመቃጮና የመመዝገቢያ ሒሳብ በትድሚያ ከፈሉ' ተባልን ። እኛ ደግሞ ይህን ያህል ገንዘብ በአንድ ጊዜ መክፈል ስለ አልቻልን ፣ ዕድር ሳንገባ ቀርን ። አሁንም በዐቅማችን ከብጤዎቻችን ጋር ዕድር አቋቁመናል" ብሉ መለሰ ፣ የወሥር አለቃ ።

"እንግዲህ" አለ ዝምቡ ፣ "ዛሬ እናንተ ይህን ስታቋቁሙ ነገ ደግሞ ሌሎቹ ሌላ ዕድር ይመሠርቱና ፣ የወረዳው ዕድር በሙሉ ብትንትኑ ሊወጣ ነው ። ከዚያ በኋላ ደግሞ እንደገና ለማቋቋምና አንድ ለማድረግ ችግር ውስጥ ልንገባ ነው ማለት ነው ። ስለዚህ ፣ እንደ ምንም ብላችሁ የተጠየቃችሁትን ሒሳብ ከፍላችሁ ከዋናው ዕድር ትገባላችሁ እንጂ ፣ ሌላ ዕድር ልታቋቁሙ አትችሉም ።"

መረዳ ገዥውም ፣ "እኔም በዚሁ እስማማለሁና ፣ ከዛሬ ጀምሮ የአቋቋማችሁትን ዕድር እፍርሱ ፣ ሁለተኛ እንዳትሰበሰቡ" ብለው መሰኑና ፣ ምስተኛው ዕድር ፈረሰ ።

፲፱፻፶፮ ከገባ በኋላ ግን ፣ የአዲስ አበባ ዕድሮች ከዚያ በፊት ያልተለመደ እንቅስቃሴ ያሳዩበት ሁኔታ ተፈጠረ ። በዚያ ጊዜ የራማሌ መታደሮች ጥር ፮ ቀን ፲፱፻፶፮ በዶሮና በፈ

t.me/OLDBOOKSPDF

ርፈር ፣ ቀጥሎም በቶጓጫሌ በኩል ጦርነት መጀመራቸው እንደ ተሰማ ፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር ተቆጣ ። በዚያ ጊዜ ፣ የጀግናች ማኅበር ፣ የሴቶች ማኅበር ፣ የአገር ፍቅር ማኅበር እና ሌሎችም ማኅበሮችና ድርጅቶች ያስተላለፉት የአንድነትና የዕርዳታ ጥሪ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ፈጥኖ መልስ አስገኘ ።

በዚያ ጊዜ ፣ የሀገሪቱ ዳር ድንበር መደፈር እጅግ ያስቆጣቸው አባት ጀግናች በአዲስ አበባ ከተማ በልዩ ልዩ ቦታዎች እየተዘዋወሩ ባደረጉት ንግግር ላይ ከወይዘሮ ላቀች ዕድርተኞችም ጥቂቶቹ እዛውንት ተገኝተው ነበር ።

የዕለቱ ሰብሳቢ የነበሩት እዛውንት አርበኛ ፣ ሱማሌ ሰላ ደረገችው ወረራ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተው ፣ በንግግራቸው መደምደሚያ ላይ ፣

"ወደ ጦርነቱ ቦታ ለመሔድ ፈቃደኞች የሆናችሁትን ሁሉ ከዛሬ ጀምሮ እንመዘግባለን" ሲሉ ፣

"ስሜን ይጻፉት" አሉ ባላምበራስ ሽንቁጥ ቁመው ።

"ግዴለም ፣ እርስዎና እርስዎን የመሳሰላችሁት እንኳ ጸጉ ታችሁና ዕርዳታችሁ ይበቃናል ። ወጣት ሞልቷል ፤ እታስቡ" አሉዋቸው ሰብሳቢው ።

"በእርጅናዬ ምክንያት ነው ?" አሉና ጠየቁ ባላምባራስ ።
"አዎን ።"

"እሄሄ ! መድፍስ ተጉትቶ ተወስዶ አይደለም አገር ምድሩን የሚያጋየው ። እኛን አርጅታችኋል ካላችሁንም የከተማ ወንድ እንዳታዘምቱ" አሉ ባላምባራስ ሽንቁጥ ፣ እኔ ካልዘመትኩ ከተሜ ወንድ አይደለም በሚል ውሳኔ ቁጭታቸውን እየተወጡ ።

በጦርነቱ ግንባር ተሠልፎ ከሶማሌ ወታደሮች ጋር ሲዋጋ ለነበረው ኃይላችን ትኀቢውን ስንቅ ለማቅረብ ሲባል ፣ ዕድሮች

t.me/OLDBOOKSPDF

በሙሉ ፈቃደኝነት መዋጮውንና ዝግጅቱን ቀጠሉ። ባደረጉት እጅግ አስደናቂ ዝግጅት ፣ ጠቅም ያለ ስንቅ በወቅቱ ለመሩ ማቅበል ተቻለ።

ይሁን እንጂ ፣ በዚያው ምክንያትም ዕድርተኛው ካጥጣው ገንዘብ የተቻላቸውን ያህል የቀነጣጠቡ የዕድር ዳኞች አልታ ጡም ፣ እንደዚያ ከመላሰሱት ሰዎች አንዱም አቶ ሸዋዬ ነበር። የማዘጋጃ ምክር ቤት አባል እንዲሆን በሁለተኛነት ከወረዳው የተመረጠና የወይዘሮ ላቀች ዕድር ዳኛም በመሆኑ ፣ ከወረዳው የተውጣጣውን ገንዘብ ከየዕድሮቹ ተቀብሎ ፣ የቻለውን ያህል ቀንሶ ፣ በርከት ያለውን ለራሱ አስቀርቶ ፣ መጠነኛውን ደግሞ ለወይዘሮ ላቀችና ለእቶ ፍጡር አከፋፍሎ ፣ ከሥነታቸው የተረፈውን በጥሬ ገንዘብና በልዩ ልዩ አላቂ ዕቃዎች ሰጠሁ ብሎ አስታወቀ። ለማን እንዴ ተሰጠ ፣ ምን ያህልስ እንዴ ተሰጠ የጠየቀው አልነበረም። ከዚያ መዋጮ ላይ ገንዘብ ቀንሶ ማስቀረቱ የታወቀበት ፣ አዳዲስ የመኝታ ቤትና የሣሎን ዕቃዎች ፣ ልዩ ልዩ ልብሶች እጅ በእጅ ከፍሎ መግዛቱ ከተረጋገጠ በኋላ ነበር።

ፓፀፀፃ በአዲስ አበባ ዕድሮች ላይ ፣ ሌላ የሥራ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች እንዲያተኩሩባቸው መነሻ የሚሆን ምክንያት ደግሞ ተወለደ።

በባለርስትና በጪሰኛ መካከል የነበረውን የይዞታና የጥቅም ጉዳይ የሚመለከት ክርክር በፓርላማ በመነሣቱ ፣ በከተማውም ውስጥ የተጧጧፈ የርስ በርስ ውዝግብ አስነሣ። በተለይም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ፣ "መሬት ላራሹ" የሚል ድምፅ እያሰሙ እስከ ፓርላማዉ ድረስ በሠልፍ በመሔዳቸው ፣ ወሬው እየተባዛ ፣ ክርክሩም እየተንዛዛ ሔደ።

የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ፣ "የመሬት ላራሹን" ጥያቄ ለፓርላማው ሲያሰሙ ፣ እንግበዋቸው ከነበሩት ጽሑፎች መካከል ጉላ ብሎ ይታይ የነበረው ፣ "ልዑል ራስ እምሩ ርስታቸውን ለሕዝብ እንዴ ሰጡ ፣ ሌሎችም ይስጡ" የሚል ስለነበረ ፣ የሕግ መምሪያው ፕሬዝዳንት የነበሩት ተማሪዎቹን ተቀብለው ሲያነጋግሩ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"እያችሁ ይዛችሁት የመጣችሁትን ? በሉ እንግዲህ ፣ እኛ የምናወጣው ሕግ የመብት እንጂ የልመና ስላልሆነ ፣ 'እንደ ዚህ ያለውን ጽሑፍ ወዲያ ጣሉት' ብለው መለሱዋቸው" የሚል ወሬ በማስተጋባቱ ፣ ባለርስት የሆነ ሁሉ ከብርቱ ሠቀቀንና መዋለል ላይ ወደቀ ።

ከዚህ በኋላ ፣ ከፓርላማው እስከ ዕድር የነበሩት ባለ ርስ ቶች በጉዳዩ እንዲተጉበትና የባለርስቶችን እጅ የሚሰበስበው ሕግ እንዳይወጣ ጥረት እንዲደረግበት ባለርስት የሆነ ሁሉ መሯ ሯጥ ጀመረ ።

ወይዘሮ ላቀች ፣ አቶ ሽዋንግዛውና አቶ ፍጡርም በዚሁ ጉዳይ ላይ ምክክር ሲያደርጉ ፣ የሽዋዬንና የሌሎችንም የዕድር ዳኞች ማንነትና ምንነት ማበጠር ግድ ሆነባቸው ። በብጠራው ወቅት ሽዋዬ ከጠቅላይ ግዛት በትምህርት ተመርጦ አዲስ አበባ የገባ ከመሆኑ በስተቀር ፣ የባለርስት ወይም የጪሰኛ ልጅ መሆኑ በሚገባ ስላልታወቀ ፣ በዚያ ወቅትም ከተንጠላጠለበት እርከን ማውረድ ስላስቸገረ ፣ ከወይዘሮ ላቀችና ከአቶ ሽዋንግዛው ሩብ ሩብ የገጠር ርስት በችሮታ ተሰጠው ። እርሱም በአቶ ፍጡር አማካይነት ወደ ወይዘሮ ላቀች ቤት ሔዶ ደስታውን ለሁለቱ ባለውለታዎች ሲገልጽ ፣

"ለስጦታችሁ በፍጹም ልቤ ከማገልገል በቀር በምንም ልመልሰው አልችልም ። የአባቴንና የእናቴን ርስት ፣ ጊዜ ያነ ሣቸው ባለሥልጣኖችና ባላባት ጉልበተኞች ቀምተዋቸው ፣ በጎ ዘንና በችግር ላይ የሚገኙ ነበሩ ። ዛሬ ግን በእናንተ ሰፊ እስ ተዋይነትና ልግሥና ባለርስቶች ለመሆን ስለ በቃን ፣ የእናንተን ባለውለታነት ምን ጊዜም አልረሳውም" ብሎ ነበር ።

ከዚያ በኋላ ፣ አቶ ሽዋንግዛው የተነሣውን የባለርስቶ ችና የጪሰኞች ክርክር ለማከሸፍና የጪሰኞችን ባለመብትነት የሚደነግገው ሕግ እንዳይወጣ ከሚታገሉት ባለርስቶች ከዋና ዋናዎቹ ተከራካሪዎች አንዱ ስለነበሩ ፣ ሽዋዬንም በይበልጥ መሣሪያቸው እንዲሆን ከታላላቅ ባለርስቶች ጋር አስተዋወቁት ። የአንዱን ዘመዳቸውንም ልጅ አጨለት ። ከዚያ በኋላማ እርሱም

t.me/OLDBOOKSPDF

የሾረ ተቆርቋሪያቸው ሆነ ። በፓርላማ ተጀምሮ የነበረው የባለ ርስትና የጪሰኛ ሕግ ክርክር እንደ ተንጠለጠለ ፣ ፓርላማው ፲፱፻፺፯ ጊዜውን ፈጽሞ ተዘጋ ። ባለርስት የነበሩ የምክር ቤቱ አባላት ፣ 'ችግር ያማረው የጪሰኛ ልጅ ያገባል' የሚል አሽሙር በማሰማታቸው ወሬው ከተማውን አላበሰው ።

ያ ሐሳብ ፣ በሕግ ተደንግጎ በሥራ ላይ እንዳይውል ፣ የም ክር ቤቱን አባላት በመከፋፈልና የሐሳቡ ደጋፊዎች የነበሩትን የጪሰኛ ተቆርቋሪዎች በመከታተሉ ረገድ በዕድሮች ውስጥም ከፍተኛው ትንቅንቅ ተደርጐ ነበር ። ዕድሮች በይበልጥ ሲተኩ ርባቸው ደግሞ እንደዚያ የመሰለ ድምፅ ሁለተኛ እንዳይሰማ ለማድረግ ፣ የተጣሪዎቹን ንቅናቄ ለመከታተልና ሲያኮርፉም ከመ ንግሥት ጋር ለማስታረቅ በየሠፈሩ የነበሩ ወታደሮችንም አዝ ማሚያ በሚገባ ለማጤን በአያሌው ሊረዱ እንደሚችሉ ስለታ መነበት ፣ ቀደም ብሎ በአንዳንድ አካባቢዎች ተጀምሮ የነበረ ውን ዕድሮችን የማጠቃለልና የመቈጣጠር ሐሳብ በይበልጥ እየታ መነበት ሔደ ።

ከዚያ በፊት በአንዳንድ ወረዳዎች የነበሩ የዕድር ዳኞች "የሕዝቡን ችግሮች በጎብረት ለማስወገድ ፣ የሠፈር ጸጥታ ለመ ጠበቅ ፣ መንገድ ፣ ትምህርት ቤት ፣ ክሊኒክና የመሳሰሉትን የል ማት ሥራዎች ለማከናወን በወረዳችን የ ሚገኙ ዕድሮችን አንድ አድርገን እናቋቁም" የሚል ሐሳብ እያቀረቡ ፣ 'ይጠናል' እየተ ባሉ ያልቆዩትን ያህል ፣ የዕድሮች መጠቃለል ለየወረዳው ነዋሪ የሚያገለግለውን ያህል ለመንግሥትና ለየግላቸው እምነትና ፍላ ጐት ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም የተረዱት አንዳንድ ባለሥል ጣኖች ደግሞ በ'ይጠና' ላይ የነበረውን ሐሳብ ወደ ሥራ እንዲ ተረጐም ማጣደፍ ጀመሩ ።

በተለይም አቶ ሸዋንግዛው ፣ ከጥቂቶቹ ጓደኞቻቸው ፣ ከወይ ዘሮ ላቀች ፣ ከአቶ ፍጡርና ከአቶ ሸዋዬ ጋር በሰፈው ከተመካ ከሩበት በኋላ ፣ የወረዳ ዕድሮች አጠቃላይ እንዲቋቋም በአንደኛ ቁጥር ተሰለፉበት ።

የዕድር ዳኞችንና ጸሐፊዎችን እየዞሩ በማነጋገር ፣ ሐሳባቸ ውን ከቀሠሙ በኋላ ፣ የዕድሮች አጠቃላይ እንዲመሠረትና በማ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዜጋጃ ቤት ፣ በሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና በአገር ግዛት ሚኒስቴር ሥር እንዲመራ አቶ ሽዋንግዛው ሐሳብ አቀረቡና ተቀባይነት ካገኘላቸው በኋላ ፣ እርሳቸው ወደ አገር ግዛት ሚኒስቴር በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ ተዛውረው የዕድሮችን ጉዳይ እንዲከታተሉ ተመደቡ ።

የዕድሮችን አጠቃላይ ለመመሥረት በተከታታይ በየወረዳው በተደረገው ሰብሰባ መሠረት ፣ አቶ ሽዋንግዛው የመረጡዋቸውና የደገፉዋቸው የብዙዎቹ ዕድሮች ነባር ዳኞች ወደ ዳኝነት ለመመረጥ በቁ ። ከእነርሱም አንዱ ሽዋዬ ነበር ። የራሱን ዳኝነት እንደ ያዘ ፣ ከነበረው የማዘጋጃ ቤት አማካሪነት ሌላ የወረዳው ዕድር ዳኛም ሆኖ በመመረጡ ፣ በመደበኛ ሥራውም ላይ ተመሳሳይ ዕድገት እንዲሰጠው አቶ ሽዋንግዛው ስለ አስታወቁለት ፣ በሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ውስጥ የዋና ዲሬክተርነት ሥልጣን ተሰጠው ። ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ፣ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባላት ምርጫ ስለ ተደረገ ፣ አቶ ፍጡር በወረዳቸው ተመርጠው ለአባልነት በቁ ።

የወይዘሮ ላቀች ሰዎች ፣ እንደዚያ ሆነው በየረድፉ ከተደላደሉ በኋላ ፣ እርሳቸውም በወረዳው ውስጥ ዘውድ-ቀረሽ ንግሥት ሆኑ ። በዚያ ላይ እንዳለም ነበር ፣ በመድኃኒት ሲከላከሉት ቆይተው ከአቶ ሽዋንግዛው ወንድ ልጅ ዱብ ያደረጉት ። ግን ለብዙ ዓመታት የወሰዱት የፅንስ መከላከያ መድኃኒትም ፣ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጎ የተወለደው ልጅ አንድ እጅ የሌለው እግሮቹ የሰለሉ ሆኑ ። ታዲያ ሽዋንግዛውም ዲቃላቸውንና ውሽማቸውን ለማላከም ወደ ፈረንጅ አገር ይዘው ሔዱ ። ምንም እንኳን ሁለቱም የርስትና የገንዘብ ጌቶች ቢሆኑ ፣ የቤተ መንግሥቱ "ችሮታ" እንዳይቀርባቸው ተብሎ ፣ የመጓጓዣውን እንርሱ ሲችሉ ፣ የሆቴሉና የሕክምናው ሒሳብ እንዲከፈልላቸው በጽሕፈት ሚኒስቴር በኩል ጠቅላይ ግምጃ ቤት ታዘዘላቸው ።

ዕድሮች በወረዳ በወረዳ ከተቋቋሙ በኋላ ፣ የመተዳደሪያ ደንቦቻቸው እንዲሻሻሉላቸው አንዳንድ ዕድርተኞች ጥረት ማድረግ ቢጀምሩም ፣ የወይዘሮ ላቀችን ዕድር ጉዳይ የሚነካ ወይም የሚደፍር ጀግና አልተገኘም ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለግዘጋጃ ቤትና ለፓርላማ አማካሪነት የመረጣችሁን እን ደሆነ ፣ በወረዳ በወረዳችሁ ተጠቃላችሁ ዕድር የመሠረታችሁ እንደሆነ ፣ 'ክሊኒክ ፣ ትምህርት ቤት ፣ መንገድ ፣ የገቢያ ቦታ ፣ መጠ ናኛ እናሠራላችኋለን' እያሉ በፀሐይ እያንቃቁ ሲያስጨንቁን ኑረው ፣ እነርሱው ከዶረጃ ወደ ዶረጃ ተሻጋገሩበት እንጂ ለኛ ምን ሠሩልን ? ሌላው ቀርቶ የዕድሩ ደንብ እንኳ አልተሻሻለም። ጎዘንተኛ ገንዘቡን ማግኘት አልቻለም ። የኛስ የሸምግልና ሥራ ምን ውጤት ሰጠ ?" አሉና አቶ ሥዩም እጉረመረሙ ፣ ከአቶ ዘይኑ ጋር በግራሩዋ ሥር ጉን ለጉን ተቀምጠው ፣ ሽማግሌዎቹን እየተጠባበቁ ሲጨዋወቱ ።

በዚያ ዕለት ፣ ሽማግሌዎቹ እንዲሰበሰቡና የቅድርተኞቹን ጉዳይ እንዲያጻምጡ አቶ ይጥና ጥሪ አስተላልፈው ስለነበረ ፣ ከብዙ ወራት በኋላ መሰብሰባቸው ነበር ።

አቶ ሥዩም ለሰነዘሩት ሰሞታ ፣ አቶ ዘይኑ መልስ ከመስ ጠታቸው በፊት ፣ አገር ምድሩን እየተራመሙ ፣ እንዲት የተቦ ጫጨቀ ያገር ልብስ የለበሰች ቆት ከተፍ አለችባቸውና ፣ የስድብ ቋያሞን ለቀቀችባቸው ።

"አቶ ፍጠር ያላዩዋት ደግሞ ከየት መጣች ?" አሉ ዘይኑ ተደናግጠው ።

"ቢያያት አያገባት" አሉ ሥዩም ።

"እንደ ደባልቀው ያስጠፍሩዋት ነበራ !" አሉ ዘይኑ ።

"እርሱንም የሚያግሥሩት ያው ስብሰባ ሲኖርባቸው ነበር። ዛሬማ ከሠፈሩ ቀርቶ ከወረዳው ጭምር አጥፍተውታል ።"

ቤትዮዋ ሚኒቲም እየለመነች የማዳበሪያው ስድብ በእያ ሌው ቀጠለችበት ።

"አልሰሙም እንዴ ? ደባልቀውኮ አስረው መደ ትውልድ መንደሩ ሰደውታል" አሉ ዘይኑ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንደሱ ሆነ እንዴ ? በሠፈራችን ውስጥ ሦስተኛው ግዞ ተኛ መሆኑ ነዋ !" አሉ ሥዩም ።

"ሁለቱ እነማን ናቸው ?"

"መቶ አለቃ ከበደና አቶ እንደሻው ።"

"እህ ፣ አዎ ! ሦስት መሆናቸው ነው ።" አሉ ዘይኑ ።

"ይህች አራተኛ ላትሆን ብትጠፋ ይሻላት ነበር" ሲሉ ሥዩም ፣ ሴትዮዋም ዘፈን አይሉት ቀረርቶ ባለየለት እንጉርጉሮ ፣

"እንዱ ጠረፍ ገብቶ እንዱም ሙቶላት
እስቲ ተመልከቱዋት ላቀች አምሮባት"

ብላ ስትደጋግመው ፣ መምሬ በዕውቀቱና ሌሎች የዕድር ዳኞች እየተከታተሉ መድረስ ጀመሩ ።

"ደባልቀው ሲጠፉ ደግሞ ፣ ደባልቂት ተተካች ?" አሉ መምሬ በዕውቀቱ ፣ መስቀል እያሳለሙ ።

"እንዲህ አርጎም ቅስና የለ! የድሆችን የዕድር ገንዘብ ዳኞች ሲበሉት አብረው እየበሉ ደሞ መስቀል ያሳልማሉ" አለች ሴትዮዋ ።

"አሄሄ! እንዲያው ይሄ ሠፈር ከፉ ተናጋሪ ላያጣ ነው ?" አሉ መምሩ ፣ በሰዓቱ ከነበረችው ፀሐይ ጨረር ጋር ሴትዮዋ ቱባ ብራ የሰነዘረችባቸው ቃል እየለበለባቸው ።

"አከከከ! ይህችንማ ፍጡርና ሸዋዬ ሲመጡ እንድትመጣ መንገር ነበር" አሉ አቶ ሥዩም ።

"በይ በቃሽ! የተላከሽበትን አድርሰሻል ፤ ዘወር በይልን ፤ በቃሽ" አሉ ዘይኑ ፣ ወደ ሴትዮዋ እየሔዱ ፣ ለማስፈራራትም እየቃጣቸው ።

የሽማግሌዎቹን መሰብሰብ ሲጠባበቁ የነበሩ ባለጉዳዮች ዕድርተኞችም ወደ ግራሩዋ ሥር ማምራት ጀመሩ ።

"እስተዛሬ ጠፍተው በመከረምዎ ይቀጣሉ" ሲሉ አቶ ሥዩም ፣ መምሬ በዕውቀቱ ደግሞ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"እስተዛሬ በመጥፋቴም ፣ ለወደፊቱም እዚህ ግድም እንዳ ልደርስም ይኸውና አጋፋሪያችሁኮ ሸንቁጣኛለች" ብለው መለ ሱላቸው ።

አቶ ዘይኑ ፣ ሲትዮዋን አባብለውና አስፈራርተው ወደ ምትሔድበት አባርረው ተመለሱና ፣ "እንዲያው ሠፈራችን የዕብዶች መፈንጫ ሆኖ እሚኖረው እስከ መቼ ነው ?" ብለው ሲቀመጡ ፣ አቶ ሥዩም ቀበል አደረጉና ፣

"እሚቴ ላቀች እስቲጨምቱ" አሉዋቸው ።

የዕድሩ ሽማግሌዎች መሰብሰባቸውን በሩቅ ተመልከተው ካረጋገጡ በኋላ ፣ አቶ ይጥና ወረቀቶቻቸውን በማጎደር አጭቀው ወደዚያው ማዝገም ሲጀምሩ ፣ በመንገድ ሲጠባበቁዋቸው የነ በሩ ባለጉዳዮች ዕድርተኞችም እጀቡዋቸው ።

"ያንተስ ? ያንችስ ? የእርስዎስ ? ጉዳያችሁ ምን ነበር ?" ጥያቄዎች እከታተለው እየወረወሩ ፣ መልሶቹን በቅጡ ሳይሰሙ ፣ ሁሉንም እያለፉለፉ ወደግራሩዋ ሲቃረቡ ፣

"ባለተራው ደግሞ ይጥና መሆናቸው ነው ?" አሉ ሥዩም ።

"የምኑ ባለተራ !" ብለው ጠየቁ ዘይኑ ።

"የወረዳ ጉዳኑቱ !"

"ወረዳውማ እንግዲህ የወይዘሮ ላቀች ጉዳ መሆኑ አይደል! የፈለጋቸውን ይተክላሉ ፣ ያልፈለጉትን ይነቅላሉ" ብለው አቶ ዘይኑ መልስ እንደሰጡ ፣ አቶ ይጥና ከነአጃቢ ባለጉዳዮቻቸው ደረሱና ፣ ከሰላምታው ቀጥሎ ሣቅ ሥላቁ ተካሔደና ፣ አቶ ይጥና የዕለቱን ስብሰባ ምክንያት ሲያስረዱ ፣

"በልዩ ልዩ ምክንያት የቱነሣ ለብዙ ጊዜ ባለመገኘታችን በሠፈራችን ውስጥ የዕድራችንና የኛንም ስም የሚያጠፉ ሰዎች በመብዛታቸው ፣ እርስ በርስ የተጋጩ ሰዎችም ጉዳያቸው በዕ ድሩ በኩል እንዲታይላቸው ከወረዳው ማዛት በመታዘዙ ፣ እንድንነ ጋገርበት ብዬ ነው የጠራኋችሁ" አሉና ወደ መምሬ በዕውቀቱ፣ ጀሮር ብለው ደግሞ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለመሆኑ እርስዎስ የት ገብተው ነው የጠፉት፣ በእርስዎ ምክንያትኮ ዳኛችን ተቸግረን ነው የቆየነው" አሉዋቸው።

"የቅርብ እኅቴ የሆነች ሴት ሙታ ወደዚያው ሔጂ ሰን ብቼ ነበር" አሉ መምሬ።

"ምን አግኝቷቸው ሞቱብዎ?" አሉ ይጥና።

"አረ እንዲያው ለወግ የሚበቃም አይደል፣ ባልሆነ ምክ ንያት ሞተች" አሉ መምሬ።

"በወሊድ ነው፣ በመኪና አደጋ?" አሉ ሥዩም በመምሩ ላይ በደረሰው ኀዘን እንደ መደንገጥ ብለው።

"የፋሲካ ሠንጋ ወግሸቶ ወግቶ ገዳላት" አሉ መምሬ።

"እባካችሁ፣ በስንት ጊዜያችሁ ደግሞ ዛሬ ለመምጣት ከቻ ላችሁ፣ የመጣንበትን ስሙንና እንድ በሉን" አሉ እንድ የራሳ ቸው እንጂ የመምሬ ኀዘን ያልተሰማቸው ዕድርተኛ አዛውንት።

"ምን ነበር ጉዳይዎ?" አሉ አቶ ይጥናም፣ በሚያጽናና ቃል መምሬን ሳይሸነግሉ አቤቱታው በመቅደሙ በሸቀው።

"የባለቤቴ እኅት በድንገት ሙተው፣ ከወር በላይ ከዳኛ ውም ከእርስዎም ቤት ተመላልሼ እስተዛሬ የተደረገልኝ እንድም ነገር የለም። ወይ ዕድሩን አፍርሱት፣ ያለዚያ በሥርዓቱ ያዙት። ምንድነው እንዲህ ያለ መላ ቅጡ የጠፋ ነገር?" አሉ ቁጣና ንቀት እየተፈራረቁባቸው።

"እዎ፣ ነገሩን ከአቶ ሸዋዬ ጋር ተነጋግረንበታል። እንግ ዲህ አንድ ሳምንት ያህል ቢታገሡን እንከፍልዎታለን፣ ለመ ሆኑስ አግትዎ የሞቱት የት ነበር?" አሉ ይጥና።

"እዚሁ አዲስአባ ሠንጋ ተራ።"

"ይሁን እንግዲህ፣ ሳምንት ብቅ ይበሉ" አሉዋቸውና፣ ዕድ ርተኛው እንደ መወራጨት ብለው እያጉረመረሙ ሲሔዱ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"በራሳቸው ጥፋት ነው ሴትዮዋ የሞቱት ። እኛን ምን ፍጠሩ ይሉናል ?" አሉ ዘይኑ ።

"እንዴት ነው ነገሩ ? ሴትዮዋ ታንቀው ነው የሞቱት ?" ብለው ጠየቁ ሥዩም ።

"የልጆቻቸው አባት ሙተው ወደላይ እየዘለሉ ደረታቸውን ሲደቁ ለካ የልብ ድካም ኑሮባቸው ኑሮ ፣ መሬት ሳይ ይዘረጋሉ ፣ ወዲያው ይሞታሉ" አሉ ዘይኑ ።

"አቤት፣ የልጆቻቸውን አባት እንዴት ይወዱዋቸው ኑሩ ዋል !" አሉ ሥዩም ፣ እያባጩ ።

"ከተፋቱኽ ዐሥር ዓመት አልፏቸዋል" አሉ ዘይኑ ።

"ታዲያ ዝላዩን ምን አመጣው ?" አሉ ይጥናም ነገሩ አስገርሟቸው ።

"ባላቸውንና የልጆቻቸውን አባት ሚስት ያስቀኑ መስሏቸው ነበራ !" አሉ ዘይኑ ።

"ሟችቷ ባል ነበራቸው ማለት ነው ?"

"አዎ !"

"የልጆቻቸው አባትስ አግብተው ኑሩዋል ?"

"አዎ !"

"እንግዲህ ቀሪዎቹ ደግሞ ይጋቡዋ !" አሉ ሥዩም ።

ወዲያው እንዲት አሮጊትና አንድ ጠና ያሉ አዛውንት ወደ ሽማግሌዎቹ ችሎት ቀርበው እጅ ነሥተው ቆሙ ።

"የእናንተስ ጉዳይ ምን ነበር ?" ብለው ጠየቁ አቶ ይጥና መዝገባቸውን እያገላበጡ ።

"ከአገር ቤት ከመጣሁ እነሆ ሁለት ወር ሊሞላኝ ነው ። ችግሬን ለእናንተ ለማመልከት ስጠብቅ ሰንቄን ጨረስኩ" አሉና አመለከቱ አሮጊቷ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን ነበር ጉዳዩ?" አሉ ይጥና ።

"ጉዳዩማ ፣ እንደምታውቁት ፣ ልጄ አቶ ይታጠቁ ሲሞት ፣ የዕድርተኝነቱ ገንዘብ ለባለቤቱ ተሰጥቷት ፣ እርሱንም ለኔ ለእናቱ ልትከፍል ሲገባት ፣ በሙሉ በልታው አሁን 'የለኝም' ስላለች እንድትከፍለኝ ላመለክት ብዬ ነው" ሲሉ ሴትዮዋ ፣ ዳኞቹ በመገረምና በመደንገጥ ይመለከቱዋቸው ጀመር ።

"የዕድሩን ገንዘብ እርሷ ልትወስድ አይገባትም ነው የሚሉት?" ብለው ይጥና ጠየቋቸው ።

"አዎን ፣ ልክ ነው!" አሉ አሮጊቷ ።

"በምን ምክንያት? ሚስት አይደለችም?"

"ሚስቱም ብትሆን አልወለደችምና ፣ የዕድሩን ገንዘብ ልትወስድ አይገባትም!"

"ሁለቱም ዕድርተኞቻችን ናቸው ። ባልዮው ሲሞቱ የዕድሩን ገንዘብ ለሚስቲቱ ከፈልን ። እርሷም ለቀብሩ ሥነ ሥርዓትና ለዐርባው ጣጣ አውላዋለች ። አሁን እንዴት አልወለደችምና የዕድር ገንዘብ ትመልስልን ትላላችሁ? ተሰምቶም ታይቶም አይታወቅምና ፣ እንዲህ ያለ ነገር አንሰማም" አሉ አቶ ይጥና ።

"እሺ ፣ የሟች ልጅሽን ገንዘብ ተቀምተሽ ቅሪ ካላችሁ ፣ የፍርዳችሁን ግልባጭ ስጡን" አሉ ሰውዬው ።

"ምን ልታደርጉት?"

"ለፍርድ ቤት እናመለክታለና!"

"ስለዚህ ጉዳይ ብላችሁ ፍርድ ቤት ልትሔዱ ነው?"

"ይህን የመሰለ ግፍ ሲሠራብን እንዴት በዝምታ እንመለከታለን? አቤት እንላለን እንጂ!" አሉ ሰውዬው ።

"እኛ ለዚህ ጉዳይ የፍርድ ግልባጭ አንሰጥም ፣ ሰጥተንም አናውቅም ። ከፈለጋችሁ ለምታመለክቱት አመልክቱና ስንጠ

t.me/OLDBOOKSPDF

የቅ መልስ እንሰጣለን ። አሁን ሥራ ስላለብን ዘወር በሉልን' አሉ አቶ ይጥና ። የሠፈሩ ሹምም ፣ ሁለቱን ሰዎች እንዴ ግባበ ልም እንደ መግፋትም እያደረጉ መለሱዋቸው ።

''ለመሆኑ ፣ አቶ ሽዋዬ የዚህን ዕድር ዳኝነት ትቶታል ማለት ነው ?'' ብለው አቶ ሥዩም ፣ ይጥናን ጠየቁዋቸው ።

''እኔ ምን አቅለታለሁ ? ዛሬ ነገ እያለ ስብሰባ እንዳናደር ግስ የሚጐትተው እርሱ አይደለም ? የሆነ ሆኖ ፣ የአባሎቹን ጉዳይ ተመልክተን የሚሆነውን እናደርጋለን ። ለሚመጣው ስብሰባ መገኘት ይኖርበታል'' አሉ ይጥና ።

''እም ፣ በሚመጣው ስብሰባ መዋጮ የሚጠየቅ ከሆነ መቼም ቀድሞ ከተናገ ይላል'' አሉ ሥዩም ፣ ሁለቱንም በአሽሙር ሊነኩ ዋቸው ፈልገው ።

''እስቲ የመጣንበትን ጉዳይ ቶሎ ቶሎ እንጨርስና እን ሒድ ። ሽምግልና አለብን'' አሉ ይጥና ፣ የተሰነዘረው አሽሙር በዚያው እንደማያበቃ በመገመት ቀልጥፈው ለመሸሽ ብለው ።

''እውነት ነው ፣ እኔም እቸኩል ነበር ። እንደዚሁ የቤተ ዘመድ ሽምግልና አለብኝ'' አሉ መምሬ በዕውቀቱ ፣ የዕለቱ የክርስትና ድግስ ትዝ ትዝ እያላቸው ።

''ነገ ሰኞ ፣ ወደ ደሴ ስለምሔድና ለሁለት ሳምንት ያህል በዚያው ስለምቆይ ፣ በኔ ምክንያት ባለጉዳዮች እንዳይጉላሉ ዛሬ ውኑ ብንጨርስላቸው?'' አሉ ዘይኑም ።

''ሁለት ሳምንት ሙሉ የሚያቆይ ምን ጉዳይ አለዎ ?'' ብለው ጠየቁ ሥዩም ።

''የእንድ ወዳጄ ወንድም ከላውዲ ዐረቢያ መጥቶ ሚስት ሊያገባ ፣ በነገር አባትነት ተመርጫለሁ ።''

''ደግሞ ብለው ብለው የዐረብ አገር አባት ሊሆኑ ነው ?'' አሉ ሥዩም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"የለም ፣ የኛው ሰውነ ነው ። በልጅነቱ ሌቦ እዚያው ኑሮ ፣ ገና ሚስት ሲያገባ ነው ።"

"ስንቱኛዋቱ ሚስት መሆኑም ነው ?" አሉ ሥዩም ።
"ገና የመጀመሪያውም ያልሆነችኛው መሆኑ ነው ።"

"እዘርስትና ጭሪሶች ነው እንዴ የሚያነበንቡ ?" አሉ ሥዩም ።

"አይደለም ፣ ነገሩ ወዲህ ነው ።"

"ወዴ ዮት ?"

"ስለብ ስለሆነ ፣ ሠፊ ኮንና ጉበራቱ የሚወርስ ነው የሚረገውና ፣ እንዴም ትፀቃዋለች ። እርጅውም ሳትሰበት ለጅ ናት ።"

"ታዲያ እንዲህ ከሆነማ በደነት እድርን ቢመሰርቱ ምነለ በት ፣ በዚያው እዝር ለሚሆኑ መንገድ ቢያገኙለት ምነለ ?" ሲሉ ሥዩም ፣

"ዋናው ኦዲያነ ቱረነ" ነሉ መምሬ ። ወዲያው እንዲት ሴት ሀላት ሰዝናት ይዝ ተረብ አሰኙና ፣

"ጌቶች፣ እማዘር ያሳያችሁ ፣ ድሃይቱ ሥርቁ እነኑልሀለ አባ ብሎና አልገድ ሂድስቹን አስታቅርኝ ፣ ቀለብ አልሰጥም ብሎ ክልክሉኝ ፣ ለሠረጻው ባሠልነችም እቅ ሽዋዩ ፣ እኔ እመረረ ላታለው ብለው እታለውኝ ፣ ያዝሠሩ አሱ ነድኛቸው ስለሆነ ፣ በረሃብ እሰኝ ያስገርፉኛል" አለች ።

"የልጅቱ አባት ማን ይባላሉ ?" ሉሉ ደግሞ ።

"ማዘቸው በሰቸው ይሀሴል ።"

"የት ነው ሥሪው ?"

"አስተማሪ ነው ። የአቶ ሽዋዩ ጓደኛ ።"

"እንኳን ናርድ ቢት ሐኪ ፣ ለመረጻው ባመለክትኩ አይደለም አቶ ሽዋዩ የቁም በቅሌን ኢየሠታዮኝ የከረሙ ? እና

t.me/OLDBOOKSPDF

"የለም፣ የኔ ጡቶች እንዲህ አይደሉም፣ ገና ሚስት ሲያገባ ነው።"

"እንኮንጎራ ሚስት መቼ ነው?" አሉ ሥዩም።
"ገና የመጀመሪያው ጉመጮ ሲመጣ ነው።"

"እዚህስ ሳንሥሩ ነው እንጂ የሚያሠራን አሉ ሥዩም።

"እይታህ ነገር ወዳለ ነው።"

"ወይ ዛሬ?"

"በልጣ ለሰዎች ፣ ሠርተውን ጉድፍን የሚደብቅ ነው የሚፈለገው፣ እንጂ ትዝብትን። ወንዶች አልከበቡሽ ልጅ ናት።"

"ታሪኳ እንዲህ ከሆነ በርሱት ሌላን ሲመለከት ምናለ ባት፣ በዚያው አህያ ከሚነዳ መንገድ ጉዳት ነው" ሲሉ ሥዩም፣

"ዋናው ጉዳይ ቁርጥ ነው። ከሚያስጨንቁ ከሚያሠጉ እንዲት ሴት ውለታ ሰጥቶ ያለ ችግር አይገኝ።

"ጎጆዋን እግዚአ ያለእንቁላሉ ያሳያችሁ፣ ያሳያችሁ ሠርቻ እንደሰዘለ አባ ብሎን ትህትና ጴጥሮሳዊ አበው ትምህርትን ቀለብ አልሰጣም ብለው ከልክለሰኝ፣ ለሥራለው ባመሰግኑም ነው ቤተኛ እስ እሠራለሁ ላታለው ብለው አትለመኝ። ይንገሥ ከነ ሁሉም ሰውነት ሰው ሠረሃነ እሰንጋ ያስነድፍሃል" አለች።

"የልጅነት እብት ማነ ይህንን?" አሉ ሥዩም።

"ሚስቱ ሰላቸው ይሰጣል"

"የት ነው ሥራው?"

"እስትማሪ ነው። የእሱ ጽሑፍ ነጋሪ ነው"

"እንኳን ጥርድ ቤት ሰጪ ፣ ሰመረኝው ባመለክትህ አይደለም አቶ ሽጥው የቁም ሰዎችን ሲያሠቃዩኝ የነበረ? እና

t.me/OLDBOOKSPDF

እሁንም —" ብላ ንግግሩዋን ሳትጨርስ አቶ ሥዩም አቋረጡ ዋትና ፥

"ታዲያ ማንኛቸውን ነው የምንጠይቅልሽ ?" አሉዋት ።

"ግዛቸውን ነዋ ! ሌላ ማን ሊጠየቅ ኑረዋል ?"

"እንዴ ፥ ግዛቸው ማለት ይሽ ከመንገዱ በላይ ከነአቶ ንጉሤ ቤት በስተኋላ የፊታውራሪን ቤት ተከራይቶ የሚኖረው ነው ?" አሉ ይጥና ።

"አዎ ፥ እርሱ ነው ጌታዬ !"

"ታዲያ እርሱ ሚስትና ልጆች አሉት አይደለም ? ምንድን ነው እምታወሪው ?"

"እዎን" አለች ።

"ካንቺ ጋር እንዴት ተገናኙችሁ ?"

"በመጀመሪያ በግርድና ገባሁ ። ይህን ትልቁን ልጅ እንዳ ረገዝኩለት እኔን አስወጥቶ ያሁኑዋን ቤት አገባ ። እንደገና ደግሞ 'ሚስቴን ፈትቼ አንቺን ላገባ ነው ?' ብሎ አታሎኝ ፥ ይህች ኖዪቱን አስወለደኝ እንጂ ቤቱን ያቋቋምኩትና ለወግ ለማረግ ያበቃሁት እኔ ነበርኩ" አለችና ፥ ዕንባዋን አጐረፈች ።

"በቃሽ በቃሽ ፥ አታልቅሺ ። ቤቱን ያቋቋምሽ ብቻ ሳይሆን እርሱንም ያሚሸሽ አንች መሆንሽ ነው" አሉ ሥዩም ።

"በይ እንግዲህ በጅ ቢለን ጠርተን እንጠይቅልሻለንና ፥ ላምንት ተመለሺ" አሉ ይጥና ።

"እስተዚያውስ እኒህን ልጆች ምን ላብላቸው ? በባዶ ቤትኮ ነኝ" አለችና ተንሰቀሰቀች ።

"ታዲያ እኛ ከየት እናመጣለን ? የዕድር ዳኞች እንጂ የዲ ቃላ ሰብሳቢዎችኮ አይደለንም" ሲሉዋት ይጥና ፥ አቶ ሥዩም ከጥቁር ቦርሳቸው ሐያ ብር አወጡና ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለዛሬ በዚህች ምናምን ግኽላቸዋ! ምን ይደረጋል!" አሉዋት ።

የእርሳቸው ጅምር ገዱ ያማረ ሆነላት ፤ ሽማግሌዎቹና ባለጉዳዮቹ የችሮታቸውን ያህል ለገሡዋትና ፣ የዕንባ ዘለላዎቿን እየጠረገች ተመለሰች ።

የሠፈሩ ሹም ፣ ከኪሳቸው የሰዎች ሰም የጻፉበትን ወረቀት አውጥተው ለአቶ ይጥና እያሳዩ ፣

"ሐያ የሚሆኑ ባለትዳሮችና በዕድሜ የገፉ ነዋሪዎች በዕድርተኛነት ለመመዝገብ በዛሬው ዕለት ይመጣሉ ። ያስቸገሩት ግን ነጠላዎቹ ናቸው" አሉና ፣ ሪፖርታቸውን አቀረቡ ።

"ዕድር አንገባም ያሉትን ፣ እከል ሲደርስባቸው ብቻ ሳይ ሆን ፣ ማጅራታቸው ቢበጠስ ፣ ቤታቸው ቢሰበር ፣ ንብረታቸው ቢጠፋ ፣ ዕድሩ ቀርቶ ወረዳው እንኳ ፣ ኧረ እንዲያው መንግሥት ኃላፊነት እንደሌለበት ደጋግመው ያስጠንቅቋቸው" ብለው አቶ ይጥና ፣ የሠፈሩ ሹም የሰጡዋቸውን ወረቀት ከማጎደራቸው አስ ገቡ ፤ ቀጠል አደርገውም ፣

"እንግዲህ የዛሬን ባለጉዳዮች እናነጋግርና ፣ ለሚመጣው ሳምንት ደግሞ ጠቅላላ ስብሰባ ስላለ ፣ ለዕድርተኛው የምናቀርበውን ሐሳብ እናዘጋጃለን" ብለው የሌሎቹን አስተያየት ለማዳመጥ ተራ በተራ ሲመለከቱዋቸው ፣ አንድ ወጣት እየሮጠ መጣና ፣ ከወይዘሮ አልጋነሽ ዘንድ ቀረብ ብሎ በጆሮአቸው ሹክ ሲላቸው ፣ እርሳቸውም ደነገጡና "ምን አግኙቶት ነው?" ብለው ጠየቁት ። ልጁም መልሱን እንደገና በሹክታ ነገራቸው ።

"ጌታዬ ፣ የባለቤቴ አክስት ልጅ ከዛፍ ላይ ወድቆ ስለ ሞተ ለቅሶ አለብኝ" ብለው ተደናግጠው ሔዱ ።

"እህ ፣ እኔምኮ አስቸኳይ የማልቀርበት ጉዳይ ነው ያለኝና ባዘቦቴ ቀን ብንነጋገርበት አይቻልም?" አሉ መምሬም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ግለፈኛ ነው ! ንጉሣዊ ሰብለጥዓዮስ እናስረዳችውና ሁላ ችንም ወደ ምክራችን እንሒዳ !" አሉና አቶ ይጥና ፣ ወደ ተሰ በሰቡበት አቡቱኮ አቅራቢያም ዘንድ መለስ ብለው ፣

"እንግዲህ እንደምታዩት ፣ ዋናው የዕድሩ ዳኛም አልመ ጣም ። ሳምንት ግን አያተርም ። እናንተም ብትመጡና ማንኛ ውንም ነገር ሁኔኔ ላይ ሠነን ብንፈርስላችሁ አይሻልም ? 'ጋዘን ይርስብናል' የምትሉ ከሳችሁ ፣ ዛሬ ገንዘብ አልያዝንም ። ቢኖርም ፣ ዋናው ዳኛ ሰላልመጣ መክፈል አንችልምና ምን ይመስሳችኋል ? እሁን ወደ ጉዳያችን ብንሔድ ፣ ሳምንት ዳኛው ባለበት ብንገናኝ ነው የሚሻለው" ብለው ሲናገሩ ፣

"ይኸን ዕድር ብታፈርሱትና ወደ ፊለግንበት ዕድር ብን ገባ ምን አለበት ? እኛን ሚመላለስ ገንዘባችንን እየስበሰባችሁ ወይድ ማበደር ፣ ንግድ ማስነገድ ሆኗል ዋናው ሥራችሁ" አለና አንዲት አሮጊት እየተቆናጠሱ ሔዱ ።

* * *

በቀጠለው ሳምንት ከወረዳው ዕድሮች የተወጣጡ ሽማግ ሌዎችና ዳኞች በወረዳው ማዘት ጽሕፈት ቤት ስብሰባ አደረጉ ። የስብሰባው ዋና ዓላማ ፣ የከተማው ዕድሮች አጠቃላይ ኮሚቴ በመቋቋሙ ፣ የኮሚቴው አባላት የሚሆኑ ፣ እንዲሁም በወረዳው ዕድር ውስጥ ከሞናው ዳኛ ጋር ሆነው የሚሠሩ አባላት ለመም ረጥ ነበር ። በስብሰባውም ላይ አቶ ይጥና ፣ የወረዳው ገቨና አቶ ሽዋዬ ተገኝተዋል ።

የወረዳው ገቨ ፣ የስብሰባውን ፍሬ ነገር አስረድተው እንዳ በቁ ፣ አቶ ይጥናና አቶ ሽዋዬም የየበኩላችውን አስተያየት ከወ ረወሩ በኋላ ፣ ለአጠቃላዩና ለወረዳው ዕድር አባልነት አምስት ሽማግሌዎች ተመረጡ ። ከእነርሱም አንዱ አቶ ሥዩም ነበሩ ።

"በወፈራሹን ባለው ዕድር አንድም ቁም ነገር ሳንሠራበት የወረዳ ተቋቋመ ?" አሉ አቶ ሥዩም፣ "አሁን ደግሞ አጠቃላይ ተደ ገመ ። ሕዝቡም በደለበት ፍርድ አጣን ፣ ትምህርት ቤት ፣ ክሊኒክ መንገድ ሥራልን እያለ ይጠይቃል ። እንደምንረዳው ከሆነ የሕዝቡን ጥያቄና ፍላጎት መንግሥት ሊያሚላለትና ሊፈጽምለት

t.me/OLDBOOKSPDF

አልቻለም ። ታዲያ ለሠፈሩ ዕድር አንድም ነገር ያልሠራው ሰው ምን ብላችሁ ነው መደቢያ ላይ ያንጠለጠላችሁኝ ?'' ብለው ሲናገሩ ፣ አራቱ ሽማግሌዎች እንኳተቸውን እያወዛ ወዙ ንግግራቸውን ሲያደንቁላቸው ፣ ሦስቱ ባለሥልጣናች ደግሞ ከንፈሮቻቸውን እየነካኩ ሲመለከቱዋቸው ሽዋዬ በቁጣ እንደ ሠፈ ፣

''የሚያሳዝነው ጉዳይኩ የዕድሩን ችግር በመረዳ ፣ እንዲያም ሲል በአጠቃላይ ለመፍታት እንደምንችል ያለመረዳትዎ ነው ። በእውነቱ ያለዎት እምነት እንደዚህ ከሆነ ከአባልነቱ ቢቀሩ ይሻላል —'' ብሎ ንግግሩን ሳይጨ ፣

''ከአባልነቱስ መቅረት የለባቸውም ። በእውነቱ ፣ እር ሳቸው የሚቀሩ ከሆነ ሁላችንም እንቀራለን ፣ አስበበት'' ሲሉ አንደኛዉ አባል ፣ የቀሩትም በዚሁ ሐሳብ የሚስማሙበት መሆ ናቸውን በየሁኔታቸው በማሳየታቸው የአቶ ሽዋዬ ተቃውሞ ውድቅ ሆነ ።

* * *

''የዛሬው ሰብሳቢያችንስ ማን ይሆን ?'' አሉ ሥዩም ፣ ሁሉ ቱም የዕድሩ ዳኞች እንደማይገኙ በመጠራጠር ።

''እንዴ ትላንትናኮ አቶ ይጥና እመጣለሁ ብለውኛል ፤ አይ ቀሩም ። 'ለእሚቱ ላቀችም የምናቀርበውን ጉዳይ ሁሉ ነገ እነድ ንጨርስ' ሲለኝ ነበር'' አሉ ዘይኑ ።

መይዘሮ ላቀች ፣ ሽባ ዲቃላቸውን አሳክመው ራሳቸውም ጤነኛ ልጅች ለመውለድ የሚችሉበትን የሐኪም ምክር አዳም ጠው ከተመለሱ ውለው አድረዋል ። ይሁን እንጂ አቶ ሽዋን ግዛው ደግሞ ከቤታቸው መራቅ በመጀመራቸው መይዘሮ ላቀች በሐሳብ መዋለል ጀምረዋል ።

''እንደምን ሰነበታችሁ ? በዚህ ሠፈር የተመሠረተ ዕድርኮ እየደር ጉድ እየወለደ አስቸገረ'' አሉ መምሬ ፣ ገና መስቀላቸውን አሳልመው ሳይቀመጡ ።

''በሌላው ሠፈርም ጉድ ተወልዶልዎታል'' አሉ ሥዩም ፣ ከመቀመጫቸው እየተነሡ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ከዚህ ሠፈር የከፋ ጉድ የሚወለድበት ሠፈር ደግሞ የት ይገኛል ?" አሉ መምሬ ።

"ባለፈው ሳምንት መርካቶ ሔጄ የሰማሁትን ልንገርዎ ?" አሉ ሥዩም ።

"አሄሄ ! መርካቶማ የጉድ መፍለቂያው አይደል ? ምን ያስ ገርማል ?" አሉ መምሬ ።

"የደረሰው ጉድኮ የእናንተው ነው ።"

"በኛ በነማን ?"

"በእናንተ በቄሶች ።"

"ምን ተገኘብን ደግሞ ?"

"በጾም ቀን ፣ ጥዋት በሦስት ሰዓት የዝክር ድግስ ባርከው ሲበሉ ትን ብሏቸው የሞቱትን መነኩሴ ወሬ አልሰሙም ?" ሲሉ ሥዩም ፣ መምሬም ደነገጡና ፣

"እስመሳይ መነኩሴ ነው ። እውነተኛ መነኩሴ ቢሆን ኑሮ በጾም ቀን ሳይቀደስ ጠበል ጠዲቅ አይባርከም ነበር ። ለሆዱ ያደላ አውደልዳይ ነው" አሉ ።

"እባክዎን ይተዉኝ ! እውነተኞች ናቸው የተባሉትስ ያባ ወራ ሚስት እያማገጡ እየተያዙ ፣ በጋዜጣ ጉዳቸው ወጥቶ የለም ? ምን ያደባብቃል ?" ሲሉ ሥዩም ፣

"እባክዎ ክፉ አይናገሩ ። እውነተኞቹን ቀሳውስትና መነ ኮሳት እናውቃቸዋለን" አሉና መምሬ ቀጠል አድርገው ፣ "እንዲያው ቁም ነገር ላንሠራኮ በየጊዜው 'ተሰብሰቡ' እያሉ ሥራ ማስፈታት ልማድ ሆነ" አሉ ፣ ለዕለቱ ድግስ ሰዓቱ እንዳያልፍባቸው በመሥጋት ።

"ምነው ? ዛሬም ይቸኩላሉ ?"

"እም ! የኛ ሰው ያገኘውን በቃኝ አይል ። ጣጣው ብዙ ነው ። እንደዚሁ የወንድሟን ዲቃላ አልቀበልም ብላ ያስቸገ ረች ሴት በሽምግልና ይዘናል ። ቀጠሮው ለዛሬ ነው ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ብዙ ልጆች አሉትና ይበቃሉ ባይ ናት?" አሉ ሥዩም፣ ለታሪኩ ጓጉተው።

"እረ አይደለም! አንድም ልጅ የለውም። አሁን ከሞተ በኋላ አንዱዋ፣ 'ልጄ ነውና ተቀበሉኝ' ብላ መጥታባት ነው።"

"እኅቲቱ ታዲያ የወንድሟን ልጅ ለምን አልቀበልም ትላለች? የማሳድግበት የለኝም ብላ ነው?" አሉ ሥዩም።

"ነገሩማ እንዲህ ነው። የሟች እኅት የምትኖረው አገር ቤት ነበር። ከሁለት ዓመት በፊት፣ ሁለት ዐይኖቿን ታማ መጥታ ወንድሟን አሳክመኝ ትለዋለች። 'ከሐኪም ዘንድም ሳይወስዳት፣ ከሱቅ ጠብታ የሚሉትን ነገር ገዝቶ፣ ገንዘብ የለኝም' ብሎ መልሶ ይሰዳታል። እርሱ ግን፣ እንዲያው ሲፈጥረው ንፉግ አድርጎት ነው እንጂ፣ ከመንግሥት ሠራተኛነቱም ሌላ፣ ንግድ አለው፤ የጦፈ ነጋዴም ነበር። ሚስት የለው! ልጅ የለው! የቅርብ ዘመድ የለው! እንዲያው የገረድ መን ደላቀቂያ ሆኖ ሲኖር፣ በመኪና አደጋ ዘንድሮ ይሞታል። ለካ በባንክ ከዘጠና ሺህ ብር በላይ አስቀምጦ ኑሮ፣ አሁን ያች 'ዐይን ንሽን አላሳከምሽም' ብሎ የመለሳት እኅቱ ተጠርታ መጥታ ገንዘቡን ወረሰች። ታዲያ ያዲሳባ ሴቶች መቼም የማያደርጉት ነገር የለምና፣ አንዱዋ ባለመጠጥ ቤት የተገኘውን ሀብት ከለማች በኋላ፣ አንዱን ከድሃ የወለደችውን ልጅዋን፣ 'የእርሱ ልጅ ነውና ተቀበሉኝ' ብላ ብቅ ስትል፣ ይህችኛዋም 'አልቀበልም' ብላ 'ነገሩን በሽምግልና እዩልን' ብለው ይዘውናል።"

"ታዲያ ይኸ ጉዳይሳ ፍርድ ቤት ደርሷል?" ብለው ጠየቁ ሥዩም።

"ገና ነው። ጠበቆች ግን በሁለቱም ሴቶች በኩል ተሠልፈው፣ 'እስከ ዙፋን ችሎት እናደርሰዋለን' ብለው አለፍ ብለውበታል" አሉ መምሬ።

"አሄሄ! ይኸማ ሙሉ በሙሉ ሲሳይ አይደል? አህያ ሥጋ ተጭና ጅብ አግኝቶ፣ 'አንቺም ሥጋ፣ የተጫንሽውም ሥጋ' እንዳለው መሆኑ አይደል? ሁለት ሴቶች በዚህን ያህል ገንዘብ ተጣልተው፣ ከመካከል ጠበቃ ገብቶ፣ ሲሳይ በሲሳይ ይሏል ይህ ነው! ለመሆኑስ እኅቲቱ ባለትዳር ናት?" አሉ ሥዩም።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ፈጽ ተመለስኖለች ።"

በዚህን ጊዜ የወይዘሮ ላቀች ፕሮፌሉት ሽዋዬንና ይጥናን ሥም እሰከ ግራኒዋ አጠባበቅ ድረስ ከተጥ አለ ።

"እንዲህ ነዋ! ማንኛቸው ደማም ላቀኽን ተጠግተው ይሆን?" አሉ ዘይራ ።

"እንደ ምን ያጠራጥራል? ሽዋዬ ነዋ!" አሉ አቶ ሥዩም ።

መኝታው ሁለቱም ድረስና ለለምታ ተሰዋውጠው ተቀመጡ። ፈንጠር ፈንጠር ብለው የነበሩ ባለጉዳዮች ወዲ ሽማግሌዎቹ ሲቀርቡ ፣ የወይዘሮ ላቀች ሽፈርም ፕሮፌሉቱን አዙሮ ተፈተሉት ። ከባለጉዳዮቹ አንዱ ወደ ሽዋዬ ሲሉድ ሽዋዬም ወደ እር ሱው ሉኤና ፣ ሁለቱ ፈንጠር ብለው ሲነጋገሩ ፣ መምሬ በዕው ቀቱ ወደ አቶ ይጥና ጠጋ ብለው ፣

"ለሞኑን ለያመሻሽ ቀርቶ አልመጣሁም ። የተያዘብኝስ ተማሪዎች ተፈረደባቸው?" ብለው ጠየቁዋቸው ።

"ምን ያደርጋል ብለው? በእነርሱ ላይ ምንስ ነገር ቢፈረድ የተደፈረው ክብራችን ፣ የፈሰሰው ደማችን አይመለስ!" አሉ ይጥና ፣ ራሳቸውን እየነቀነቁ ።

"አይ! ያለማሰን ነው ፣ መቀበል ነው ፣ ትእዛዝ ነው ፣ ከፌ ጣሪ ታዙ ነው" ሲሉ ሙምሩ ።

"እባክዎ ይተዉኝ መምራ! እኛ ለሰላም የቆምነው ሽማግ ሌዎች እንድንታሰብ እማዙር ነው ዘዘ ነው የሚሉት?" አሉና ይጥና ፣ ከንፈራቸውን መንከስ ጀመሩ ።

"እሄዱ ራስ ባሊ የተናገሩትን አልሰሙም?" አሉ መምሬ። "ምን ብለው ኑሬዋል?"

"እዩ ቄሞድሮስ ፣ ግና ደጅች ካጣ እየተባሉ በረሃ ገብተው በነበረ ጊዜ ፣ ራስ ዓሊ ፣ ካሣን እነሱዉጋሳቸው ያዘመቱት ሠራዊት ድል በመመታቱ ከሐያ ሺህ በላይ የሚሆን ሠራዊታቸውን አስከ ትተው ይዘምታሉ ። ደጀች ካጣም ጥቂቶች ወታደሮቹ ይዘው

t.me/OLDBOOKSPDF

ይገጥሙና ራስ ድል ሆነው ሲማረኩ ፣ ‘ይህች ለበት የእግዚአብሔር እንጂ የካሣ አይደለችም’ አሉ ይባላል ። በእናንተም ላይ የደረሰው ይኸው ነው ።”

አቶ ሸዋዬም ከባለጉዳዩ ጋር የነበረውን ቆይታ አብቅቶ ሲመለስ ፣ የሁለቱ ጭውውት ቆመ ።

“በዕለቱ የሽማግሌዎች ስብሰባ እንዲያረግ ያስፈለገበትን ምክንያት አቶ ሸዋዬ ማስረዳት እንደ ጀመረ ፣ የወይዘሮ ላቀች ሾፈር ሾፍሮሌቱን እያሳበደ ፣ መልሶ ወደነሱው ሲመጣ ፣ ሸዋዬም ንግግሩንና ሁለመናውን አቁሞ ሲመለከተው ፣ ሾፈሩ እየተቆናጠረ ወርዶ በተፋጠነ አረማመድ ወደ ግራዋ ሥር ሔዶ በሸዋዬ ጆሮ ሹክ አለው ።

“በሉ እናንተ ቀጥሉ ፣ እሜቴ ፈልገውኝ ነው” ብሉ ብድግ ሲል ፣ አቶ ይጥናም እስክ መኪናው ተከትለውት ፣ የያዛቸውን ማስታወሻዎች እያገላበጠ ሲያነጋግራቸው ፣

“ወይ ጉድ! እኒህ ሴትዮ ይህን ልጅ እንዲህ አድርገው ልቡን ያጥፉት ?” ሲሉ ሥዩም ፣

“እረ እባክዎ ዝም ይበሉ ! ሰው እንዳይሰማ” አሉ ዘይኑ ቀስ ብለው ።

“መቼም የጉድ ሠፈር ዕድር ነው ። አንድ ቀን ደግሞ ፣ ሸዋዬና ሸዋንግዛው ይዋደቃሉ” ሲሉ አቶ ሥዩም፣ አቶ ይጥና ደግሞ ከሸዋዬ ጋር የነበራቸውን ንግግር ፈጽመው ሲመለሱ ፣ ሾፍሮሌቱም ሸዋዬን ተሸክሞ ፣ ‘ይኸ ከተፍ’ እያለ ሸመጠጠ ።

“እባካችሁ ወደ ዋናው ሥራችን እንመለስ ። ጊዜ ውኮ ሮጠብን” አሉ መምሬ ፣ አቶ ይጥና ሲቀመጡ ።

“የዕድሩን ዋና ፣ የሠፈሩ ዋና ጠርተው ሲወስዱት እያዩ ምን ዋና ነገር ይኖራል ብለው ነው ?” አሉ አቶ ሥዩም ፣ ከንፈራቸውን እየለጠጡ ፤

t.me/OLDBOOKSPDF

"እርሱ ቢሔድም ተነጋግረንበታል ። ጎዘን ደርሶባቸው ገን ዘባቸውን ያላገኙ ካሉ ፣ ለወይዘሮ ላቀች አሳውቀን እንዲከፍሉ ይደረጋል ።"

"ምን ማለት ነው ? አድሮ ጥጃ አልሆናችሁም ? ሴትዮዋ ከሽርሽር ከተመለሱ ጅምሮ ፣ አንድም ዕድርተኛ ገንዘቡን አግኝቶ አያውቅም ሁላችሁም የዕድሩን ጉዳይ ትታችሁ ስለ ተማሪ ፣ ስለ ማዘጋጃ ቤትና ስለ ፓርላማ አማካሪ ነው የምትናውዙት ። በየጊዜው እንሰበሰባለን ፣ አንድም ቁም ነገር ሠርተን አናውቅም ። አሁን ዕድርተኛው ሁሉ ዕድሩ ይፍረስና ወደሌላ ዕድር እንግባ ነው የሚለው ። እኔም እስማማለሁ ። ከዛሬም ወዲያ እዚህ ግድም አልገኝም" አሉ ሥዩም ምርር ብለው ።

"ባልተቤትየዋ እንኳን በደኅና የተመለሱ እንጂ ፣ ከእንግዲህስ ወዲያ የዚህን ዕድር ጉዳይ አንድ ነገር ማድረግ አለባቸው። እንዲህ ሆኖ እስከ መቼ ?" አሉ መምሬም ፣ ራሳቸውን በእምቢተኝነት እያወዛወዙ ። አቶ ይጥና ለሁለቱ ንግግር መልስ ከመስጠታቸው በፊት ሽማግሌዎቹን ሲመለከቱ ፣ ሁሉም በሐሳቡ የሚስማሙበት መሆናቸውን አሳወቋቸው ።

"እንግዲያው ፣ሁላችሁም የምትስማሙበት ከሆናችሁ ፣ለምን ለብሰብ ብለን ሔደን እንነግራቸውም ?" በማለት ሐሳብ ጠየቁ።

ሽማግሌዎቹ እርስ በርሳቸው በመተያየት ላይ እንዳሉ ፣ ከአካባቢ ዕድሮች ባንደኛው ቱልቱላ ተነፋ ።

"የየትኛው ዕድር ነው ?" አሉና ይጥና ሁሉንም ጠየቁ ።

"ከቤትወደድ ዕድር ነው" አሉ አንድ ባለጉዳይ ።

"ማን ሙቷል ?"

"እመት አዛለች የሚባሉ ናቸው ።"

"ምን አገኛቸው ?"

"ታመው ብዙ ጊዜ ተኝተው ነበር ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሐኪም አልሔዱም ኑሩዋል ?"

"እንኳን ሐኪም ቤት የሚሔዱበት፣ የሚበሉትም አልነበራቸው። የሚያሳዝኑ ሴት ነበሩ። ልጆቻቸው ፈረንጅ አገር ተመችቷቸው እንደ ልባቸው እየኖሩ፣ እሳቸው ከመኝታቸው እንኳ ቀና አድርጎ ውሃ የሚሰጣቸው ጠፍቶ እንደ ተሠቃዩ ሞቱ" አሉ ወሬ ነጋሪው ባለጉዳይ።

"ሌላም ቀብር አለብንና፣ እባካችሁ የመጣንበትን እዳም ጡን" አሉ፣ ሌላኛ ባለጉዳይ።

አቶ ይጥና መልስ ሊሰጡ ባለጉዳዮችን አንድ ባንድ መቃኘት እንደ ጀመሩ፣ በሠፈሩ ከታወቁት ነዋሪዎች መጠነኛ ሥልጣን የነበራቸው ዕድርተኛቸው በመኪና ደረሱና፣ መኪናቸውን አቁመው፣ እየተቆናጠሩ ቀረብ ብለው፣ እንገታቸውን ጉንበስ ሲያደርጉ፣ ሁሉም ተነሡላቸው።

"በቤቴ እክል ደርሶ ከጥዋት ጀምሮ ብጠብቅ፣ ብጠብቅ ምነው ዝም አላችሁኝ? ቱልቱላውም አልተነፋልኝም? ምነው እንዲህ መደረጉ? ዕድርተኛ መሆኔ ተዘነጋ እንዴ?" ብለው ጠየቁ፣ ቁጣቸው እየጦናነቃቸው።

"እምን፣ እውነት ነው፣ ጥዋት የላኩትም ልጅ አሽከርዎ መሞቱን ነግሮኛል" አሉ አቶ ይጥና "ለአቶ ሽዋዬም ነግሬዋለሁ። እያካድም፣ እርግጥ ነው፣ ዕድርተኛችን ነዎት። የየወሩንም መዋጮ ሊከፍሉ ኑረዋል። ድንኳን፣ ወንበር፣ ሰሐን፣ ሌላውንም ዕቃ ሁሉ ሊወስዱ ይችላሉ። የሚገባዎትንም ገንዘብ እንከፍላለን" ሲሉዋቸው ባለሥልጣኑ በይበልጥ ተናደዱና፣

"እንዴ፣ እናንተ ልታታብሩኝ እትችሉም ማለት ነው?" ብለው ጠየቁ።

"እርስዎ ከማን ቀብር ተገኝተው ያውቃሉ?" አሉዋቸው ይጥና።

"ምን ቀን ነግራችሁኝ ታውቃላችሁ?" ሲሉ ባለሥልጣኑ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኛ ለማንም አንነግርም ። የዕድሩን ቱልቱላ ብቻ ነው የምናሰማው ።"

"ቱልቱላውኮ አይሰማም ። ቱልቱላ ነፊውም የሚናገረው ተሰምቶኝ አያውቅም" ብለው ባለሥልጣኑ ሲቆጡ ፣ ቱልቱላ ነፊው በዳሰ ደግሞ በተራው ተቆጣና ፣

"ለሚን ቱልቱላውን በቱራ በቱራ አኒነፋም ? እርሶዎም ሞኪሩት" አላቸው ።

"እንዴ ፣ ደግሞ ቱልቱላ ንፋ ትሉኛላችሁ ? በዕድሩ ደንብ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል ?"

"ቱልቱላ ነፋም አልነፉ ፣ እርሰዎም ሆኑ ባለቤትዎ ከማ ንም ቀብር ተገኝታችሁ ስለማታውቁ ፣ አንድም ዕድርተኛ ሊመ ጣልዎ አይችልም ። የዕድሩን ዕቃ ግን ተሸክመው ሊወስዱ ይች ላሉ" አሉና አቶ ይጥና ፣ ወደ ሠፈር ሹሙ ዘወር ብለው ደግሞ ፣ "አንድም ዕድርተኛ ከደጃፋቸው እንዳይደርስ ፣ አንድም የዕድር ዕቃ ደግሞ እንዳይቀርባቸው ። የሚፈልጉትን ያህል ይውሰዱ" ብለው ትእዛዝ ሰጡላቸው ።

ሲደነፉ የነበሩት ባለሥልጣን ነገሩን ከተረዱት በኋላ ፣ "አጥፍቻለሁ ፣ ተሳስቻለሁ ፣ ለወደፊቱ ከደንቡ አልወጣም ፣ የዛሬን ብቻ ማሩኝ ። የዛሬን ብቻ ከጉድ አውጡኝ ፣ መምሬ በዕውቀቱ እባክዎ ዝም አይበሉ ፣ ያግልዱኝ እንጂ" ብለው ከሽማግሌዎቹ ፊት አጉነበሱ ።

"ታረቋቸው ፣ ይቅር በሏቸው ። ስሕተታቸውን ከተረዱ ፣ አትጨክኑባቸው" አሉ መምሩ ።

አቶ ይጥናም ከፊታቸው ያጐበደዱትን ባለሥልጣን እያ ስነሡ ፣ "ስሕተትዎን ካመኑ ይቅር ብለናል ። በል በዳሰ ፣ ቱል ቱላውን ንፋላቸው" ብለው ትእዛዝ ሰጡላቸውና ፣ "በሉዋ ሁላ ችንም ወደ ለቅሶው እንሒድ" ብለው ችሎቱን በተኑ ።

አቶ ሥዩም ወደ አቶ ይጥና ቀረብ ብለው ፣ "እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅዎ ? ወይዘሮ ላቀችና ዕድራችን ተያይተው እያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውቁም ። ታዲያ እንድ ቀን እርሳቸው ወይም ሠራተኛቸው ቢሞቱስ ምን ሊባል ነው ?'' አሉዋቸው ።

በዚያ ዕለት ተጀምሮ የነበረው ስብሰባ በደረሰው ኃዘን ምክንያት በመጨናነፉ ፣ የተለመደውን የዕርዳታ ገንዘብ የሚጠይቁና ነገራቸው በሽማግሌዎች እንዲታይላቸው አቤቱታ የሚያቀርቡ የነበሩ ሁሉ ፣ ነፍሱ ከሥጋው የተለየችበትን ምስኪን አሽከር እየረገሙ ተበታተኑ ። ከዚያ በኋላ የዕድሩ ዳኞችና ሽማግሌዎች ተሟልተው የማይገኙ በመሆናቸው ፣ በባለጉዳዮቹ ዕድርተኞች ላይ የሚደርሰውንም ችግር የሚያስተውለው እያጣ ሐዲ ።

በዚያ ዘመን እየተዳከሙ መሔድ የጀመሩ በርካታ ዕድሮች ነበሩ ። ምክንያቱም ፣ ዳኞቻቸውና ጸሐፊዎቻቸው በአቶ ሽዋን ግዛው መዋቅር ውስጥ ገብተው ስለ ነበረ ፣ የተማሪውን እንቅስቃሴ መከታተል ፣ ለፓርላማ ምርጫ መታገል ፣ ለማዘጋጃ ቤት አማካሪነት ፣ ለዕድሮች አጠቃላይ አማካሪነትና ለአባልነት መሯሯጥ ብዙ ጥረት ጠይቆ ስለነበር ፣ የብዙዎቹ ዕድሮች ገንዘብ ያሻዎች ወደ ወለድ አበዳሪነት ተሠማሩ ።

የወይዘሮ ላቀች ዕድርተኞች በየወሩ መጨረሻ ይከፍሉት የነበረው ገንዘብ ሳይሰበሰብ እስከ ሦስት ወራት ድረስ መዘፍ ጀመረ ። ምክንያቱም ፣ የዕድሩ ዳኞች የማይገኙ ከመሆናቸውም በላይ ፣ በዕድርተኞቹ ላይ ለሚደርሰው ኃዘን ተገቢው ርዳታ የማይደረግ እየሆነ በመሔዱ ነበር ።

እንደዚያ ሆነው ዕድርተኞቹና ዳኞቹ ተራርቀው ሳለ ፣ በመካከሉ ለፓርላማው አማካሪነት አቶ ፍጡርና ሌሎችም ተወዳዳሪዎች ስለቀረቡ ፣ የወረዳው ሕዝብ አቶ ፍጡርን እንዲመርጥ ለማድረግ ዕድሮችን እየሰበሰቡ ማስረዳት በማስፈለጉ ፣ የወረዳው ዕድር ዳኞች ዕድርተኛው እንዲሰበሰብ ማድረግ ጀመሩ ።

በአንድ ሰብሰባ ቀን ፣ አቶ ሽዋዬና አቶ ይጥና ቀደም ብለው ተገኝተው ዕድርተኛውን ሲጠባበቁ ፣ እንደ ለመዱት አቶ ሥዩምና አቶ ዘይኑ እያወጉ ከሰብሰባው መጥተው ጉን ለጉን ተቀ

t.me/OLDBOOKSPDF

መጡ ። በዳሳና ሌሎቹ ቱልቱላ ነፈዎች ሠፈሩን ያደነቁራሉ ፤ ዕድርተኛው ግን ከመንጠባጠብ ዐልፎ ግልብጥ ብሎ የማይወጣ ሆነ ።

እኩለ ቀን እየታቃረበ ሔደ ። ሽዋዬ ወደሚሔድበት እየ ሔደ ይመለሳል ። የዕድርተኛው ብዛት ግን ፥ ለዐይናቹ የማይ ሞላ እየሆነበት ተቸግሯል ።

"ምን ይሻላል ? ሕዝቡኮ አልምጥ ሆነ" አለና ወደ አቶ ሥዩም ጠጋ ብሎ ጭንቀቱን ገለጸ ።

"እሀ ፥ ረስቶታልኮ ትቶታል" አሉት ሥዩም ።

"ምኑን ?" አለ ሽዋዬ ።

"ዕድርተኛነቱንም ፥ ስብሰባውንም ።"

"ዕድር እንዴት ይረሳል ?"

"ዳኞቹ ረሳችሁት ፤ ዕድርተኛውም ረሳው ።"

"ታዲያ አሁንስ ምን ይሻላል ? በየቤቱ እየሔድን እናስ ወጣው ? " አሉ ይጥና ፥ ጣልቃ ገቡና ።

"ፍጡርን ለማስመረጥ ዕድርተኛውን ከየቤቱ ልትጐትቱ ነው ?" አሉ ሥዩም ።

"ታዲያ ምን ይሻላል ?" አለ ሽዋዬ ፥ በአቶ ሥዩም አሽ ሙር ያልተደሰተ መሆኑን ፊቱን ቅጭም አድርጐ እያሳየ ።

"እንደዚሁ እንደኛው ፥ በአንድ ዕድር የደረሰውን ታሪክ ሰምተሃል ?" አሉት ሥዩም ፥ ከቅሬታው ሊመልሱት መፈለ ጋቸውን በሚገልጽ አኳኋን ።

"መቼም እርስዎ ሊፈልግዎት ጨዋታ ያውቃሉ ፥ ምን ነበር ? እልሰማሁም" አለ ሽዋዬ ፥ ፊቱን ፈካ አድርጐ ።

"እንደዚሁ እንደኛው " ብለው ፥ ሁለቱን ዳኞችና ዘይኑን ተመለከቱና ፥ ሁሉም ለጨዋታቸው መጓጓታቸውን ሲገልጹላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቸው ንግግራቸውን ቀጠሉ ፤ "እንደዚሁ እንደኛው ዕድርተኛ አልሰበሰብላቸው ብሎ የተቸገሩ ዳኛ ከአንዲት ዕድርተኛቸው ጋር ተስማምተው ሴትዮዋን "ሞቱ" ብለው ቱልቱላ ያስነፉና ፥ የሬሳ ሳጥንም አስገዝተው ሴትዮዋን አስገቡ ። ዕድርተኛው መቼም ግድ ነውና ለቀብር ተሰበሰበ ። ወዳጅ ዘመድ መላቀስ ጀመረ ። የዕድሩ ዳኛም በዚያ ምክንያት አድርገው ዕድርተኛው የወር ክፍያውን እንዲያጠናቅቅ ፥ በሠፈሩ ውስጥ ሊሠራ ለታቀደው ልማት ዕርዳታ እንዲያደርግ ፥ እንዲያው በዕድሩ ላይ የደረሰውን ችግር ሁሉ ማስረዳት ሲጀምሩ ፥ እኒያ "ሙተዋል" የተባሉ ሴት ለካ ሆዳቸው ባብቶ ኑሮ ፥ ከሳጥኑ ውስጥ እንደሆኑ ማልቀስ ይጀ ምራሉ ። በዚህ ጊዜ እኒያ የዕድር ዳኛ ከሬሳው ሳጥን አጠገብ ነበሩና ፥ መግጠሚያውን ከፈት አድርገው ፥

"ዝም በይ አንቺ ! መሞት እንጂ ማልቀስ የለብሽም እሱ ይባላል " ሲሉ ሥዩም ፥

ሽዋዬ ቀበል አደረገና ፥ "ታዲያ ዛሬም አቶ ሥዩም ሙት ዋልና ለቀብር ውጡ እያልን እንለፍፍ ?" ብሎ ሲያሽካካ ፥

አቶ ሥዩምም ቀበል አድርገው ፥ "እይ ! ዕድርተኛው በብ ዛት የሚወጣው 'ወይዘሮ ላቀች ሞተዋል' ቢሉት ነው" ሲሉት ፥ ፊቱ ጥላሸት ለበሰ ።

"እሂሂ ! እባክዎ ክፉ አይናገሩ" ሲሉ መምሩ ፥

"እርስዎ ደግሞ ነገር አይጠብቁም !" አሉ ዘይኑ ።

የሆነውን ያህል ዕድርተኛ እንደ ተስበሰበ ፥ አቶ ሽዋዬ ከመካከል ቁሞ ሕዝቡ አቶ ፍጡርን እንዲመርጥ ላንቃው እስቲ ነቃ ሲጮህ ቆይቶ ፥ "አሁን ወደ ሌሎቹ ዕድሮች ስለምሔድ ፥ ስለዕድሩ ጉዳይ ተነጋገሩበት" ብሎ ፥ የወይዘሮ ላቀች ሽፍሮሌት ስለ መጣለት ተጋብቶ ተፈተለከ ።

አቶ ይጥናም ፥ ከዕድርተኛው መካከል ቁመው ስለ አቶ ፍጡር ምንነት ሲለፈልፉ ቆዩና ፥ "እንዲያው ባጭሩ ፥ እርሳ ቸውን ብንመርጥ ለሠፈራችን ፥ ለወረዳችን ቀርቶ ፥ ለታላቋ ከተ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማችንም ታላቅ ኩራት ነው" ብለው ሲቀመጡ ፥ ዕድርተኛው ሁሉ እርስ በርሱ መጐሻሸም ጀመረ ።

"ለመሆኑስ ሌሎቹ ተወዳዳሪዎች እነማን መሆናቸው ነው ?" አሉና ሥዩም አጉረመረሙ ።

"ስለ ሌሎቹ ምንም የሚያገባን ነገር የለም ፤ ምረጡ የተባልነው ፍጡርን ብቻ ነው" አሉና መለሱላቸው ዘይኑ ።

"እንግዲህ የምንመርጠው ማንን እንደሆነ ካወቅነው፥ አሁን የወር መዋጮአችንን እንከፍላለን ። ይብተር ያልያዛችሁ እየሔዳችሁ አምጡ ። ደግሞ ልታውቁት የሚገባ ነገር አለ ። ካርኔ ያልያዛችሁ የመፈለጊያ ሐያ አምስት ፥ ሐያ አምስት ሳንቲም ትከፍላላችሁ ። መቀጮውም ሐያ አምስት ፥ ሐያ አምስት ሳንቲም ሆኗልና ፥ ይህንኑ አውቃችሁ እንድትከፍሉ" ብለው አቶ ይጥና ያሻሻሉትን የገቢ ምንጭ ሲያስተዋውቁ ፥

አንዲት ዕድርተኛ ተነሡና ፥ "በየቀኑ የቤት ኪራይ መጨመር አልበቃችሁ አለና ፥ ደግሞ ብላችሁ ብላችሁ የዕድር ክፍያ ትጨምሩ ጀመር ?" ሲሉ ፥ ድንገተኛ ጭብጨባ አጀባቸው ።

አቶ ይጥና ተቆጡና በከተማው ውስጥ ባሉት ዕድሮች ሁሉ የሚሠራበት ደንብ ነው ። እኛ ብቻ የደነገግነው አይደለም ። ደግሞ ጭብጨባውስ አበጀሽ ለማለት ነው ?" ብለው ሲደነፉ ጸጥታ ሆነና ከጉርምርምታ ጋር ከፍያው ቀጠለ ።

"ለመሆኑ ፥ ከአቶ ፍጡር ጋር ለፓርላማው ምርጫ የሚወዳደሩትን ሰዎች ማንነት በሚገባ ያውቃሉ ?" ብለው አቶ ሥዩም ፥ አቶ ይጥናን ጠየቁ ።

"ምነው የእነርሱ ነገር ከነከነዎት ? ምን ያደርግልዎታል ?" ብለው ዘይኑ አፈጠጡባቸው ።

"እንዴ ! ምን ማለትዎ ነው ? የምንመርጣቸውን ሰዎች ኮ ማወቅ ይገባል" አሉ ሥዩም ።

"እውነት ብለዋል" አሉ አቶ ይጥና ፥ "ተገቢ ጥያቄ ነው ። የሚወክሉንን ሰዎች አጣርቶ ማወቅ ይገባል ። ግን ከአቶ ፍጡር

t.me/OLDBOOKSPDF

በቀር የቀሩት የሚረቡ አይደሉም ። እንደምንሰማው አንዳንድ እክል አለባቸው ። ለምሳሌ ያህል 'አንደኛው ተወዳዳሪ የአንድ ዕድር ገንዘብ ያዥ ሆኖ ፣ ያንኑ የዕድር ገንዘብ በልቶ እንደገና ከዕድርተኛው ተመጽውቶ የከፈለ ነው ። ወደዚህ ከመምጣቱ በፊት የአንድ አውራጃ ግምጃ ቤት ገንዘብ ያዥ ሆኖ ፣ ከፍ ያለ ገንዘብ አጉድሎ ፣ እንደዚሁ ከሕዝብ ተመጽውቶ ከፍሏል' ሲሉ ሰምቻለሁ ።''

''ዛሬም ፓርላማ የሚገባው በዚሁ ሙያው ነው ይበሉኛ?'' አሉ ሥዩም ።

''ይቆዩኝ ልጨርስልዎ ። ከኛ ቀጥሎ ካለው ወረዳ ከሚ ወዳደሩት መካከል ደግሞ ፣ አንዱ ተወዳዳሪ ከዚህ በፊት የሦ ስት ዕቁብ ዳኛና ገንዘብ ያዥ ሆኖ ፣ በአንድ ቀን የሦስቱም ዕቁ ቦች ዕጣ የወጣለት ባለዕድል ነው'' አሉና አቶ ይጥና ፣ የለበጣ ሣቅ እየሣቁ አቶ ሥዩምንና አቶ ዘይኑን ተመለከቷቸው ።

''እንዴት እንዴት ሆኖ ሦስት ዕጣ ባንድ ቀን ይወጣለታል? ታዲያ ፓርላማ የሚገባውም ለዚሁ ነው ? የዕቁብ ዳኛቸው ሊሆን ?'' አሉ ሥዩም ።

''እረ ይህስ የሁላችንንም የዕቁብ ዕጣ ባወጣልን !'' አሉ ዘይኑ ።

''ይኸማ የምርጫውን ዕጣ በሙሉ መውሰዱ ነው'' አሉ ሥዩምም ።

''ነገሩ እንዴት መሰላችሁ ?'' አሉና አቶ ይጥና ታሪኩን ቀጠሉ ፣ ''ሰውዬው ለካ ለሦስቱም ዕጣ ሦስት ጣሳዎች ያዘጋ ጅና ፣ የዕቁብተኛውን ዕጣ ከዚያ ያስገባና ፣ ዕጣውን ያስጥላል ። እንዲሁ እንዲህ እያለ ዕቁብተኛውን ሁሉ ካላመጡ በኋላ ፣ ከዕ ለታት አንድ ቀን የራሱ ስም ብቻ የተጻፈባቸው ወረቀቶች እዘ ጋጅቶ ፣ ሦስት ተመሳሳይ ጣሳዎች ያሰናዳና ፣ በዚያው ውስጥ አስ ገብቶ 'ዕጣ አውጡ' ይላል ። ልብ በሉ ፣ በሦስቱም ጣሳዎች የተሞሉት የእርሱ ስም የተጻፈባቸው ዕጣዎች ስለነበሩ ፡ ሲመ ዘዙ ቢውሉ በሙሉ የሚወጡት የእርሱ ዕጣዎች ናቸውና ፣ በዚህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዘዴው ሦስቱንም ዕጣዎቹን በአንድ ቀን አስወጥቶ ፣ በአንድ ቀን ሠላሳ ሺህ ብር ወሰደ ።''

''ታዲያ አልታወቀበትም ?'' አሉ ሥዩም ።

''በኋላማ ተንኮሉ ተደርሶበታል ።''

''ታዲያ አልተከሰሰበትም ?''

''ቢከሰስ ምን ይደረጋል ?''

''ይኸ ሥራው እየታወቀ ታዲያ እንዴት ሲፖርላማ ምረጡት ተብሎ ይቀርባል ?''

''አሄሄ ! ይች ምንድን ነች ና ! 'ስንት ገመና ያለባቸው ሰዎች ምረጡኝ' እያሉ ገብተዋል መሰለዎ ! ከዘንድሮዎቹ ተወዳዳሪዎች አንዳንዶቹን እቶ ሸዋዬ ያውቃቸዋል ። ሥዩም እርሱማ ሲያወራው ይደነዝዛሉ ። ጉድ ነው ፤ በመሬት ላይ ተሰምቶ አይታወቅም'' አሉ እቶ ይጥና ፣ የፍጡርን ገመና የሚያስንቁ ገመነኞች መኖራቸውንና ከፓርላማው ውድድርም እንዳላስከለከላቸው ለእቶ ሥዩም ብቻ ሳይሆን ፣ ለሁሉም ዕድርተኞች ለማሰማት ጮክ ብለው ንግግራቸውን በመቀጠል ፣ ''የኛ ፓርላማ ከሠፈራችን የበለጠ የጉድ ማፍለቂያና ማጐሪያ ነው ። የታወቁ የዕድርና የዕቁብ ገንዘብ ወለድ አበዳሪዎች ፣ ከሁሉም የባሱት ደግሞ ፣ የጣሊያን ታማኞች ሆነው አገራቸውን የወጉ ባንዳዎች ፣ ፍርድ በገንዘብ ሲሸጡ የኖሩ ዳኞች ፣ እናት አባታቸውን አንጠርም ብለው በየፍርድ ቤቱ የሚገኙቱ ሰዎች ፣ ከገረዳቸው ወልደው የልጅ ማሳደጊያ አንከፍልም በማለት በየፍርድ ቤቱ የሚገኙቱ ፣ ስንትና ስንት የመንግሥት ገንዘብ ያጐደሉ ፣ ስንትና ስንት ሹማምንት ድሃውን ገበሬ ከመሬቱ እየነቀሉ በማባረር ርስቱን የነጠቁ ፣ ለትምህርት ቤት ማሠሪያ ሕዝብ ያዋጣውን ገንዘብ የበሉ ባለሥልጣኖች ፣ ምን ስንቱ ተዘርዝሮ ያልቃል ብላችሁ ነው ? እንደዚህ የመሳሰሉ እንዳንድ የፓርላማ አባል የነበሩና ዛሬም ለውድድር የቀረቡ አሉ'' እያሉ ይጥና ፣ የሚያውቁትንና የሰሙትን ያህል በመዘክዘክ ላይ እንዳሉ ፣ አንድ ዕድርተኛ ከገንዘብ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተቀባዩ ጋር ሲጨቃጨቅ እዩትና ፣ የፓርላማውን አባላት ስንክሳር ቆም አድርገው ተጨቃጫቂውን በእጅ ጥቅሻ ጠርተው ፣

"ምን ፣ ፍጠሩ ነው የምትለው ?" ብለው ጠየቁት ።

"በቀብርና በስብሰባ አልተገኘህምና መቀጫ ሦስት ብር ከፈል ብለውኝ ነው" አላቸው ።

"የስንት ጊዜ ቅሪት ነህ?" አሉት ፣ ሆዱ አበጥ ማለት መጀመሩን ተመልክተው ።

"ምን አሉ ?" አለ ደንግጦ ፣

"ስንት ጊዜ ከቀብር ቀርተሃል ?"

"እምስት ቀን አልተገኘህም ነው እሚሉኝ ።"

"ታዲያ አትከፍልም ?"

"እምቢ አላልኩምኮ ። ግን እኔ እምለው ፣ ከቀብር ስንቀር የምንቀጣው ገንዘብ ለምን በዕለቱ ለሞተው ሰው ቢተሰብ በዕርዳታ መልክ አይሰጥም ? ለዕድሩ ዳኞች ማበልጸጊያ ለምን ይሆናል ነው የምለው" አላቸው ።

ከእግር እስከ ራሱ ገላመጡትና ፣

"ፍርድ ቤቶች የሚያስከፍሉት መቀጫ ለባለጉዳዮች ተሰጥቶ ያውቃል ? በል እስቲ ንገረኝ ?" ብለው ጠየቁት ።

"ያማ ለመንግሥት ነው ገቢ የሚሆነው ።"

"ይህም እንደዚያው ነው ፣ ለዕድሩ ነው ገቢ እሚሆነው ።"

"ለዕድሩ ገቢ ሆኖ ለዕርዳታ ወይም ለልማት ሲውል አይ ተንም ሰምተንም አናውቅማ" አላቸው ።

ይጥና ከተቀመጡበት ቱር ብለው ተነሡና ፣ "ታዲያ የት ዋለ ? ማን በላው ልትል ነው ?" ብለው ጠጋ ሲሉት ፣ መምሬና ዘይኑ ተነሥተው ገላግለው አስቀመጡዋቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምነው ቢዋጣላቸው ኑሮ?" ብለው አቶ ሥዩም፣ ለአቶ ዘይኑ ሹክ ሲሉዋቸው፣

"እርስዎ ደግሞ ያበዙታል!" አሉ ዘይኑም ቀስ ብለው።

አቶ ይጥና፣ ከድንገተኛ ንዴታቸው በረድ አሉና ወደ ቀናው ጨዋታቸው ተመልሰው፣ "እረ ስንትና ስንት ወንጀል ሲሠሩና ሲያሠሩ የኖሩ ናቸው፣ የፓርላማ አባል የነበሩና አሁንም ወደዚያው ለመግባት የሚታገሉ። ሌላው ቀርቶ የቢተ ክርስቲያን ንብረትና ሀብት የዘረፉና ያስዘረፉ ቄሶችስ ምረጡን ብለው ተሠልፈው አልነበረም?" ብለው፣ በሰዓት የጀመሩትን አፈ-ታሪክና ተጋፊው ዕድርተኛ የፈጠሩባቸውን ንዴት ተንፍሰው አስወጡት።

"እንዴ ሌላውስ ይሁን። የወሳለቱ ቂስ ሲገቡስ እንዴት ዝም ይባላል?" ብለው ዘይኑ መምሬን በአሽሙራዊ አስተያየት ሲመለከቱዋቸው፣

"አሄሄ!" አሉ መምሬ። "መቸስ ምድራቱ የሰው ልጅ እንጂ የመላእክት መኖሪያ አይደለችም። ከሰው ደግሞ ስሕተትና በደል አይጠፋምና፣ የሆነ ያልሆነ ጥፋት እየለቀሙ ምክር ቤቱ ባዶውን አያቀር። ካልተመከረበትስ እንዲያው ባዶውን ቢጉዞር ምን ያደርጋል?"

"እንዴ፣ ከዚህ ቀደም ተማሪዎቹ ጽፈው እንደ ለጠፉበት ይከራያሳ!" ብለው መለሱላቸው አቶ ሥዩም።

ስለ መቀጫ ገንዘብ አከፋፈል ሲከራከር የነበረው ዕድርተኛ እንደገና ከሌሎች የዕድር አባላት ጋር ሲከራከር አቶ ይጥና የጉሪጥ ሲመለከቱት ኑሮ፣ እንደ ገና ጠቀሱትና፣

"ደግሞ ምን ፍጠሩ ነው የምትለው? አልበረደልህም?" ብለው አፈጠጡበት።

"ከፍያለሁኮ" አላቸው።

"ታዲያ እዚያ የምታሰማው ዲስኩር ምንድን ነው?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"አይ እኔማ እምለው፣ አንድ ሰው ለመቅበር የሠፈሩ ሕዝብ የሚግተለተለው ለምንድን ነው ?" ብሎ ጉና ተናግሮ ሳያበቃ፣

እቶ ይጥና እንደገና ቁጣቸው ገነፈለባቸውና፣

"እንዴ፣ ከየት የመጣ ነው ባካችሁ ? አንድ ሰው ብቻውን ሬሳ ወስዶ ይቅበር ነው እምትለው ?" ሲሉት፣ ከአካባቢያቸው የነበሩት ሁሉ የዕለቱ ፀሐይ ያገኑተራቸውንና፣ የሰዓቱ የቡናና የብርጭቆ ናፍቆት ያደበናቸውን ዐይኖቻቸውን ጉለጉሉበት።

"ይቆይኝማ፣ ቁጣ አይቅደም፤ ሐሳቤን ላስረዳ። እኔ ያሰብኩት አንድ ሰው ለመቅበር ቢበዛ ቢበዛ፣ ሐያና ሠላሳ ሰዎች ቢያስፈልጉ ነው። አጅቦ የሚግተለተለው ሕዝብ የሚሠራው አንድም ነገር የለውም። መንገድና ቤተ ክርስቲያን ማጣበብ፣ ሥራ መፍታት፣ ለነጻጅ፣ ለታክሲና ለአውቶብስ ገንዘብ ማውጣት ወይም በፀሐይ መቃጠልና በዝናብ መበሰበስ ነው ትርፉ። ይህ ሁሉ ለሟች ወይም ለቤተሰቡ የሚያስገኘው ቅንጣት ታክል ትርፍ የለም። ይህንም ስል የሟቹን ቤተሰብ ማጽናናት አያስፈልግም ማለቴ እንዳልሆነ ተረዱልኝ። ዕድርተኛም ሆነ ሠፈርተኛ ጎዘን የያረሰበትን ቤተሰብ ማጽናናት ይገባዋል። ይህም ደግሞ፣ ከቤት በመሔድ ማጽናናት ሲቻል፣ ቤተ ክርስቲያን ድረስ ተነድቶ ሔዶ፣ ከዚያ መልስ መጥፋት የሚያስገኘው ጥቅም የለም።

"ከዚህ ሌላ ደግሞ፣ማንኛውም ለቅሶ ደራሽ የችሎታውን ያህል የሚቸርበት ሙዳየ ምፅዋት ወይም ሳጥን፣ ያለዚያም ጉን ዘብ ተቃባይ አዘጋጅቶ ዕርዳታ መሰብሰብና ጎዘን የደረሰበትን ቤተሰብ መርዳት ቢጀመር ምን አለበት ? ሟች ባለ ብዙ ቤተሰብ ይሆናል ፤ እርሱን ሲያጡ ቤተሰቦቹ ቀኑ ይጨልምባቸዋል ማለት ነው። ጎዘንተኛው የሟችን ነፍስ ለማስማር የሰባት፣ የዐሥራ ሁለት፣ የዐርባ፣ የሙት ዓመት መደገስ፣ መታሰቢያ ማሠራት ስላለበት፣ ለዚህ ሁሉ የሚያውለው ዕርዳታ ማድረግ ነው፣ ማጽናናት ማለት እንጂ፣ በቱልቱላ ወጥቶ ወይም ለይሉኝታ ብሎ ቤተክርስቲያን ተንጋግቶ ሔዶ፣ የዕድርተኛነት ስም ተጠርቶ መመለስ ምንድነው ጥቅሙ ? ምን ፋይዳ አለው ?" እያለ ሲደሰኩር፣ የዕድሩ ኃላፊዎች፣ ሽማግሌዎችና ዕድርተኞች ሁሉ ሲያዳምጡት ቆዩና፣ በመጨረሻ

t.me/OLDBOOKSPDF

አቶ ይጥና ፣ "ሐሳብህ አይከፋም ነበር ። ግን በሌሎች ዕድሮች ያልተሞከረ ነገር እንዴት አድርገን እኛ እንሠራበታለን ብለህ ነው?" አሉት ።

"እናንተ በነገሩ ካመናችሁበት ለምን በኛ ዕድር አይጀመርም ? ራሱ ዕድርስ ቢሆን የተጀመረው ባንድ ጐሳ ፣ ባንድ አውራጃ ብቻ አይደለም ? ይኸው ዛሬ መላው የአዲስ አበባ ነዋሪ ይተዳደርበት የለም ? ባንዱ የተጀመረውኮ ነው ፣ ወደ ሌላው የሚሸጋገረው" አለ ያ ዕድርተኛ ።

"ለመሆኑ መቼ ነው ከዚህ ዕድር የገባኸው ? ነባር ነህ እንግዳ ?" ብለው አቶ ሥዩም ጠየቁት ።

"እኔስ እንግዳ ነኝ ፤ ከመጣሁ ቅርብ ጊዜዬ ነው ፤ ከዕድሩም ከገባሁ ገና መንፈቅ አልሞላኝም ።"

"ሥራህስ ምንድነው ?" አሉ ይጥና ።

"ጋዜጠኛ ።"

"ሕዝቡ እርስ በርሱ እንዲረዳዳ ሃይማኖቱንና ንጉሠ ነገሥቱን እንዲያፈቅር ፣ አገሩን እንዲጠብቅ ፣ እንዲተባበር ምክሩ ፣ አስተምሩ ብትባሉ እንዲህ ያለ ያረመኔነት ምክር ታስማናለህ ?" አሉት መምሩ ተቆጥተው ። "ዳሩ እናንተ ምን የማትሉት ነገር አለና ? ሌላው ቀርቶ ቁልቢ ገብርኤልስ ለምን ይከበራል ? ሕዝቡ ለምን ስለት ይወስዳል ? እያላችሁስ ጽፋችሁ የለም ? እንደ እናንተማ ሐሳብ ቢሆንላችሁ ኑሮ ሃይማኖት ተረስቶ ፣ አገር ጠፍቶ ላችሁ ነበር ። እሱ ባለቤቱ በምሕረቱ ጠብቆን ነው እንጂ ። ዳሩ እናንተ ምን ታደርጉ መረን ስትለቀቁ ? በእውነቱ ይህ ሰው ከዕድሩ ቀርቶ ከሠፈሩ ፣ እንዲያውም ከወረዳው ፣ ኧረ እንዲያውም ካገሩ መልቀቅ ይገባዋል አሉ!"

"እንዴ ፣ ይህን ያህል የሚያስቆጣዎ ምን ከፋ ቃል ተናግሬዎ ታለሁ ? ስለ ቁልቢም ቢሆን የጻፍነው የሚቀርበው ስዕለት በሥርዓትና በዐቅም ይሁን ነው ያልነውና" ብሎ ተናግሮ ሳያበቃ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሠረሠራችሁን ያውጣውና ፣ ከሥርዓት የወጣ ምን ነገር ሲፈጸም አይታችኋል?" አሉት ፣ በጭራቸው እጅታ ግንባር ግን ባሩን ሊጠበጥቡት እየጐመጁ ።

"በቁልቢ የሚፈጸመውን ስሕተት ስንቱን ተናግረነው? እንኳን በቃል ባገራቱ ጋዜጣ ሁሉ ቢጻፍስ ተነግሮ ያበቃልና ነው? በዚያ በተከበረ ታላቅና ቅዱስ ሥፍራ 'ስዕለት አለብኝ' እየተባለ ኮረዳና ጉረምሳ አብረው አልተኙም? በገብርኤል ማግ ሥት በጾም ቀን እዚያው ቦታ ላይ ሙክትና ሠንጋ እየታረደ ፣ ሥጋ አልተበላም? ስዕለት ነው ተብሎ ዐይጥ አልፋረበም? ኧረ ስንቱ ተዘርዝሮ?! እኛ ተቃውመን የጻፍነው ይህን የመሳ ሰለውን ዐያፍ አድራጐት ነው እንጂ ፣ እርስዎ እንደሚያወሩት አያያለምና እንዲያው—"

"የማ,ያወሩት? እኔ ወሬኛ ነኝ? የወሬ ምንጭ ፣ የወሬ ፋብ ሪካ ያቋቋማችሁት እናንተ!" ብለው መምሬ ብድግ ሲሉ ፣ በገ ላ,ጋይ ብርታት ተመልሰው ተቀመጡ ።

አቶ ሥዩም ቀጠል አድርገው ፣

"በዕለተ ስቅለት አንድ የዚህ የወንድሜ ብጤ ከቁሱ ዘንድ ተረብ ሲል ፣ 'በሕማማቱ ሰሞን ምን ሠርተሃል?' ብለው ሲጠይ ቁት ፣ 'የኔታ ፣ ሰይጣን አስቶኝ ከባለቤትዎ ጋር ከአልጋ ላይ ወድ ቁያለሁ' ቢሏቸው ፣ የወይራውን ቅጠል ወርውረው በጭራቸው እጅታ በብረቱ ግንባር ግንባሩን ሲሉት ፣ እርሱም 'ምነው የኔታ፣ ምነው በብረቱ?' ቢላቸው ፣ 'ዝምበል! ሰው የማ,ጠበጠበው እንደ ኃጢአቱ ነው' አሉት ይባላል ። አሁን ደግሞ " ብለው እርሳቸውም ተናግረው ሳይጨርሱ መምሩ ይብስ ጠፉና ፣

"ኤዲያ! እባክዎ በቃዎት! 'የዕብድ ቀን አይመሽም' የሚባለው ለካ በከንቱ አይደለም ። እርስዎስ ከእርሱ በምን ይሻላሉ" አሉ ፦

አቶ ይጥና ሁሉንም ለማምነው አስታግሡና ወደ ጋዜጠኛው ዘወር ብለው ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሰማህ ወዳጄ ! ሆድ 'ጠጠር መብላት እፈልጋለሁ' ቢል 'ጥርስ ከማን ጋር ተማክረህ ነው ?' አለው ይባላል ። አሁንም አንተ ፣ የምትናገረውንም ሆነ የምትጽፈውን እየመከርክ አድርገው ። ያለዚያ ይህች ምላስህ ካንተ ጋር መክረሟን እንጃ !" ብለው ተግሣጽና ምክር ሰጥተው አሰናበቱት ።

በዚያ ሁኔታ ላይ በመነጋገር ላይ እንዳሉ ደግሞ እንድ ችግረኛ ቀረበና ፣

"ጌቶቼ ፣ ተቸግሬያለሁ ። ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ እርዱኝ ። የአምስት ልጆች አባት ፣አሮጊት እናት ጧሪ ነኝ ።ስሠራበት የነበረው ፈረንጅ ካገር ስለ ጠፋ ፣ የነበረኝን ጥሪት እስከ ዛሬ በልቼ ጨረስኩ ። አሁን ልጆቼን የማኮርሰው የማልሰው አጥቼ ፣ ተቸገርኩ ። ልጆቼ ዐይኔ እያዩ በረሃብ አለንጋ ከሚገረፉ ፣ ገደል ወይም ባሕር መግባት መርጫለሁ ። ያለዚያ ከዕድሩ ገንዘብ ላይ አበድሩኝ ፣ ሠርቼ እከፍላለሁ ። ሰሞት ለባለቤቴ የምትሰጪትን ገንዘብ ዛሬ ስጡኝና ለቤተሰቦቼ የዕለት ምግብ ገዝቼላቸው ልሙት ። 'አያያዟገውም ፣ እይጨክንም' ብላችሁ አታስቡ ፤ ቆርጫለሁ ። ሰሞኑን ከመኪናው መንገድ ላይ መድቄ ጃንሆይ በመኪናቸው እንዲድኑኝ ብሞክር ሳላገኛቸው ቀረሁ ። አሁን ግን ያለዕድሩ ምንም ረዳት እንደሌለኝ ተገንዝቤ መጣሁ" እያለ ሲማፀን አቶ ይጥና አቋረጡትና ፣

"ገደሉም ባሕሩም በቅርብ ይገኛል ። ዙረህ ዙረህ መሞትክ የማይቀር ከሆነ ፣ እኛ ላንተ ሰጥተንህ ከምትጠጣበት ፣ ከሞትህ በኋላ ለቤተሰብህ ብንሰጥ ይሻላል ። ዘመር በልልን ፣ ሥራ አህ ሰናክል" ሲሉት ፣ እየተንሰቀሰቀ በሩጫ ሔደ ።

"እህ! ይኸ ሰው ያደረገው እንደሆነስ ?" አሉ ሥዩም ።

"ምኑን ?" አሉ ይጥና ።

"መሞቱን ።"

"እባክም ይተዉኝ ጃል ፣ የሚሞተውስ ገንዘቡን ሰጥተነው ቢሆን ነበር" አሉ ይጥና ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ገንዘብ ካገኘማ ለምን ይሞት ነበር?"

"ጠላው፡ ካቲካላው፡ ጠጁን፡ ቢናውን፡ አረቄውን ተግቶ ተግቶ ነዘረ ድርቅ የሚለው" አሉ ይጥና።

"እህ! እንደሱ የሚያደርግ ቢሆን ኑሮኮ ገና ድሮ ይሞት ነበር" አሉ ሥዩም።

"ድሮማ ያመጠዙን የምትተበለው ሚስቱ ስለ ነበረች ነበር በሕይወት የሰነበተው" አሉ ይጥና።

"የለም እያሆንም፡ ዛሬ ለመሞት የቆረጠ ይመስላል" አሉ ዘይኑም፡ ሠግተው።

"ምናለ ታዲያ፡ ወንድ ከመጣው፡ ገንዘቡን ለሚስቱ መስጠት ነው እንጂ፡ ምድረ ሰነፈም 'ልሞት ነኝ' ባለን ቁጥር ገንዘብ ስጥን ያዘለቃል?" አሉ ይጥና።

የዕለቱ ስብሰባ አብቅቶ ወደየቤታቸው ሲያመሩ፡ አቶ ይጥናና መምሬ በሰውተቱ፡ አቶ ሥዩምና አቶ ዘይኑ ጐን ለጐን፡ ሌሎችም እንደዚው ሲሔዱ፡ ከዕድርተኞቹ አንዱ ወደ አቶ ሥዩም ጠጋ ብሎ አስቆማቸውና፡

"ብርቱ ጉዳይ አጋጥሞኝ፡ ለዛሬ፡ ያለዚያ ለነገ ሰኞ ልክ ፍል ከአቶ ይጥና ገንዘብ ተበድሬ ነበር። ትላንትና ቅዳሜ የሚወጣ ዕቁብ ስለ ነበረኝ፡ ከዚያ ላይ በማሽሞ ሆነ በብድር አገኛለሁ ብዬ ነበር። ግን ዳኛው ስላልተገኙ ዕቁቡ ሳይጣል ቀረ። ውትቢዎ በሚያውቀው፡ ትላንትና ዕንቅልፍ የሚሉ በዓይኔ ሳይዞር፡ እንዲሁ ስገላበጥ ኑጋ። ዛሬም——"ብሎ ሳይጨርስ፡

"ዛሬም ዕንቅልፍ እንዳታጣ፡ አሁኑን ጠጋ በልና 'ያነን ገንዘብ ለዛሬ ላገኝልዎ አልቻልኩም' በላቸውና፡ እርሳቸው ደግሞ በተራቸው ሲገላበጡ ይንጋላቸው። ሌላ የማደርግልህ ነገር የለኝም" ብለውት ሔዱ።

በዚያ ቀንና በቀጠሉት ሳምንታት በዕድር ዳኞች አማካይነት በተደረገው የተሟሟቀ ስብከትና ግብግ፡ አቶ ፍጠር የወረዳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውን ሕዝብ ወክለው የሕግ መምሪያ አባል ሆነው ተመረጡ። እርሳቸውም ከዕድር አስተባባሪነታቸው ላይ የምክር ቤቱም የኮሚቴዎች አስተባባሪ ስለሆኑ፣ ለቤተመንግሥቱ ያቀብሉ የነበረውን "የጃንሆይ ልደት" ስጦታ ስለ ቀጠሉበት፣ ቤተ መንግሥቱ ከወይዘሮ ላቀች ቤት ይልቅ እጅግ የቀረበ ሆነላቸውና፣ ከአራት ዓመት በኋላ ከደጃዝማችነት ማዕረግ ጋር የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ሲሆኑ፣ አቶ ሽዋንግዛውም ከፊታውራሪነት ጋር የጠቅላይ ግዛት እንደራሴ፣ አቶ ሽዋዬ ደግሞ በትምህርት ሚኒስቴር ረዳት ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ። ወይዘሮ ላቀችም የወረዳው ሕዝብ ወኪል ሆነዋል ተብሎ በአቶ ፍጡር ምትክ በሕግ መምሪያው ውስጥ ከነበሩት ወንበሮች በአንዱ ላይ ጉብ አሉበትና፣ እንኮይ ከመሰለው ቅላታቸው ላይ ጥቁር ካባ ደረቡበት።

ከዚያ በኋላ፣ የሀገሪቱ ታላላቅ ሹመትና ስጦታ ሁሉ የደጃዝማች ፍጡርን ቅድሚያ ትኩረት የሚጠይቅ እየሆነ መጣ። ለሹመት የሚታጨውን ሰውዬ ጠቅላላ ሁኔታ የሚያቀርቡ እርሳቸው በመሆናቸው፣ በዕድር ዳኞች አማካይነት በየዕድሩ ባስቀመጡዋቸው ሰዎቻቸው ተከታታይነት ማንኛውንም የሹመት እጩዎች ማበጠር፣ "ተጋፊዎችና ተቀናቃኞች" የሚባሉትንም መከታተል ዋናው ተግባራቸው ሆነ።

ያን ታላቅ አጋጣሚ፣ ወይዘሮ ላቀችም ሆኑ ፊታውራሪ ሽዋንግዛው በቀላሉ የሚያልፉት ወይም በብቸኝነት የሚጋተሩት ስላልነበረ፣ ቡድናቸውን ለማጠናከር ዘመድ አዝማድ እየፈለጉ በሹመትና በጉርሻ አጥለቀለቁት። ከደጃዝማች ፍጡር ጋር በጥቅም ከተሣሠሩ አንዳንድ የዕድር ዳኞችም በዚያው ዕድልና አጋጣሚ ከዕድር ዳኝነታቸው ላይ የምራቂ ሹመትና ችሮታ ባለቤቶች ሊሆኑ ችለዋል።

እየዋለ እያደረ ወይዘሮ ላቀችም ቤተመንግሥቱ ቤታቸው እየሆነ ሔደ። ከዚህ በኋላ፣ እንኳንስ በዕድራቸው፣ በወረዳው ውስጥም በነበሩት ዕድሮች ላይ ሠለጠኑባቸው የፈለጉትን ያህል ገንዘብ በፈለጉበት ሰዓት በ 'ይመለሳል' ስም መውሰድ የሚችሉ ሆኑ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀደም ብሎ የተጀመረው ከፊታውራሪ ሽዋንግዛው ጋር የነበራቸው የግንኙነት ሙቀት በይበልጥ እየቀዘቀዘ የሔደውም፣ ፊታውራሪ ወደ ጠቅላይ ግዛት ተዛውረው ከሔዱና እርሳቸውም ወደ ቤተመንግሥት መመላለስ ከጀመሩ በኋላ ነው። አቶ ሽዋዬ ግን ፣ ጥዋት ማታ አይለያቸውም ነበር።

አቶ ይጥና፣ የከተማው ዕድሮች አጠቃላይ አባል በመሆናቸው የወረዳው ጠቅላላ ጉዳይ የሚመለከታቸው ፣ የነበራቸው ተሰሚነትና ተከባሪነትም የዚያኑ ያህል እያደገ ሔደ። በወረዳው ውስጥ የሚገኙትን የዕድር ዳኞችና ዕውቅ ሰዎች እያስተባበሩም ለነወይዘሮ ላቀች ፣ ለነደጃዝማች ፍጡር ፣ ለነፊታውራሪ ሽዋንግዛውና ለነአቶ ሽዋዬ ሹመት ማስመረቂያ ዲል እያደረጉ በመደገስ ይበልጥ ታዋቂና ባለሟል ለመሆን በመቻላቸው ፣ በተራቸው ደግሞ የማዘጋጀ ቤት አማካሪ ለመሆን በቁ። ወይዘሮ ላቀች የሚፈልጉትን ገንዘብ ከየዕድር ዳኞችና ገንዘብ ያዥዎች የሚሰበስቡ እርሳቸው ስለነበሩ ፣ እየቦጨቁ በሚያስቀሩት ገንዘብ በየሠፈሩ እየሠሩ የሚያከራዩዋቸው ቤቶች እየበዙ ሔዱ። ከወይዘሮ ላቀችና ከፊታውራሪ ሽዋንግዛው በቀርም ሌሎቹ በዕድገታቸው መጠን ተስማሚ የሚሆኑ ቤቶችና ዕቃዎች ለዋውጠዋል።

ደጃዝማች ፍጡርም ፣ ለአዲሱ ማዕረጋቸው ተስማሚ የሚሆኑ እዲስ ሚስትም ማፈላለግ ጀምረዋል። የፍለጋው ግንባር ቀደም እስተባባሪዎችም ወይዘሮ ላቀችና አቶ ሽዋዬ ስለሆኑ ፣ እሳቸው በየሠርጉ ፣ በየለቅሶው በየዘመዱ ቤት የሚሰበሰቡትን ሴቶች ሲቃኙ ፣ እርሱ ደግሞ በመሥሪያ ቤትና በትምህርት ቤቶች አካባቢ ያጨነቁር ነበር። ምንም እንኳን ፊታውራሪ ሽዋንግዛው ቀደም ብለው ከአንድ ዘመዳቸው ቤት አስገብተው ሽዋዬን በቀለበት ቢያስተበትቡትም ቅሉ፣ ከወይዘሮ ላቀች ጋር የጀመረው መቀራረብና ግንኙነት እያመዘነበት ስለ ሔደ ፣ ባለቀለበቲቱን ከነመፈጠሩዋም እየረሳት ሔደ።

ልጅ አድባሩ ፣ ግዛትነቱ ወይም ሹመትነቱ ባልለየለት ዘዴ ወደ ጠረፍ ግዛት ተሸቀንጥረው ፣ በዚያው የጉልተኞች ልጆች እያለዋወጡ ፣ በዲቃላ ላይ ዲቃላ እያነባበሩ ፣ የግብርናና የንግድ ሥራቸውን በሰፊው ቀጠሉ። አቶ አርጋውንም ወደዚያው መስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደው ፣ በእንደራሴነቱ ሥልጣን ላይ አስቀምጠው ፣ በተንደላቀቀ ኑሮ ላይ የነበሩት ልጅ አድባሩ በርስታቸው ላይ በጀመሩት ዕድር የተተከ ለምች ፣ በዕድሩ መሰላልነት ወደ ቤተ መንግሥቱ ዋልታ ወጥተው መደላደልና መንሰራፋት ከጀመሩ በኋላ ፣ ደግሞ እርስ በርሳቸው መሠራረቅ በመጀመራቸው ፣ በመካከላቸው የነበረውም የጥቅም ቋጠሮ እየተፈታ መሔድ ጀመረ ።

ወይዘሮ ላቀች ፣ የቋመጡለትን ኃብቻ ሽዋንግዛው ችላ ስላሉት ፣ እንዲያውም ቅምጥነቱም በዛ ብለው ሌላ በመደረባቸው ፣ በመተከዣነት የተጠጋው ሽዋዬ የወይዘሮ ላቀችን ልበ ⁻ልበና እስከ መቁጣጠር ደረሰና ምስጢራቸው ይፋ እየሆነ ሔደ ።

ፊታውራሪ ሽዋንግዛው ፣ ከግዛታቸው እያስመረጡ በሚልኩት ማለፊያ ጤፍ ፣ ቅቤና ማር ሽዋዬ እየተቀለበበት በወይዘሮ ላቀች ልብ የተካቸው መሆኑን ሽዋንግዛው አረጋገጡ ። እርሳቸውም ፣ የዘመኑ ሥልጣኔ የገባቸው ነበሩና ፣ ልዋጭ እየያዙ በከተማው ውስጥ በግልጽ መታዬት ጀመሩ ። ላቁም ለሽዋዬ አዲስ ፊያት ገዙለትና ፣ ከጮኑ እየተጮበሩ ሽዋንግዛውን ለማስቀናት ጥረት ማድረግን ከፓርላማው ሥራቸው ቅድሚያ የሰጡት ተግባር ሆነ ። ሽዋንግዛውም ዐልፎ ዐልፎ ፣ በተለይም እኩለ ሌሊት ላይ ፣ ስልክ እየደወሉ ወይዘሮ ላቀችን መላ ደብና ማስፈራራት ስለያዙ ፣ ወይዘሮ ላቀች ደግሞ በይበልጥ ለማስቀናት ብለው ለሽዋዬ ማለፊያ ቤት በሠፈራቸው ውስጥ እንዲከራይ አድርገው እዚያው እየሔዱ ማደር ጀመሩ ።

* * *

"ቱቱቱ! ቱቱቱ! እዛሮ ላቀች ቂበሩ ይላሉ! እዘሮ ላቀች ቂበሩ ይላሉ! ቱቱቱ!" እያለ በዳሶ በጥዋት ተነሥቶ ሠፈሩን አተራመሰው ። እዘቦት ቀን ነው ፣ ካፊያ ቢጤም ያቸፈችፋል ። ወደየሥራቸው ሊገሠግሡ በጥድፊያ ላይ የነበሩትን ሁሉ የሰዓቱ ቡታ ዕንቅፋትነት አናደቸዋል ። በዚያ ነገናዛ ጥዋት ፣ በዚያ ሠፈር ጭቃ ድንኳን መትከል ፣ ወንበሮች መደርደር ፣ ስሐኖች

t.me/OLDBOOKSPDF

ብርጭቆዎችና ፍንጃሎች ማጠብ ፣ ዕንጨት መፍለጥ ፣ ጢስ ማጣጢያስ ፣ ንፍሮ መቀቀል—እዱ የዕለቱ ሞምልቅልቅና ምስ ቅልቅል!

አቶ ዘይኑ ፣ የበዳሶን ዐዋጅ እንደ ሰሙ ፣ ወደ ወይዘሮ ላቀች ቤት ለመሔድ እግረ መንገዳቸውን ወደ አቶ ሥዩም ቤት ጐራ አሉ ። ሥዩም ወደ ዕለቱ ሥራቸው ሊሔዱ በዝግጅት ላይ ነበሩ ። ገና አፋቸው እህል አላማሸም ። ዘመናዊ ስለሆኑ ጢም መላ ጨቱ ፣ ልብስ መለዋወጡ ሁሉ የቁርሳቸውን ሰዓት እየተሻማ ባቸው ከመኝታ ቤት ወደ መታጠቢያ ቤት ፣ ከዚያም ወደቁም ሳጥን በሚንጐዳጐዱበት ወቅት ደግሞ ሰላኩ "ድረሱልኝ" ብሏቸው እርሱን ሸንግለው እንዳበቁ ፣ አቶ ዘይኑ ከበራፉ ላይ ሆነው ቆረቆሩ ። ራሳቸው ከፈቱላቸውና የደንቡን ሰላምታ አድርሰው ሲያበቁ ፣

"ምነው በጥዋት ምን ተገኘ ? ይቀመጡ" አሉ ሥዩም ፣ የዕድሩን ጥሩንባ ያልሰሙ መስለው ።

"አልሰሙም እንዴ ? ዕድርኮ ተነፍቷል" አሉ ዘይኑ ፣ ከሶፋው ላይ ቁጢጥ ብለው እየተቀመጡ ።

"ምንድነው ያለው ? አልተሰማኝምኮ ?"

"እንዴ ! ወይዘሮ ላቀች ምነ ሆነው ኑሩዋል ?" አሉ ዘይኑ ።

"የሕግ መወሰኛ አባል ፣ የሸዋንግዛውና የሸዋዬ ቅምጥ ነበሩዋ !"

"ኤዲያ ፣ እርስዎ ደግሞ ! ሁልጊዜ ቀልድ ምንድነው ? ሙተዋልኮ ነው የሚለው በዳሶ ።"

"ታዲያ በዳሶ ነው ቅበሩ እሚለው ፣ ወይስ ዕድሩ ነው ?" አሉ ሥዩም ።

"እንዴ ምን ማለትዎ ነው ? በዳሶን ምን አግብቶት ቅበሩ ይላል ? ዕድሩ ነው እንጂ ።"

"ዕድሩስ ምን አግብቶት ቅበሩ ይላል ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴ ፣ ምን ማለትም ነው ! ዕድርተኛነታቸውን አጥ ትና ነው ?"

"የት ይተዋወቁና ?"

"ማንና ማን ?"

"ላቀችና ዕድሩ ።"

"ሆ! ሆይ ! እርስዎ ይቀልዳሉ ። ይልቁንስ ይለባብሱና እን ሒድ ።"

"ሥራ አለብኝ ጊታዬ ! ሥራ ፈታን ፣ ሥራ ፈቶች ተሰብስ ባችሁ ቅበሩ" አሉና ሥዩም ፣ ከተቀመጡበት ተነሡ ። አቶ ዘይኑ የመላእክቱንና የሰማዕታቱን ስም እየጠሩ ለምነው ፣ ተማፅነው የማይሆንላቸው ሲሆን ጊዜ ብቻቸውን ሔዱ ። አቶ ሥዩም ቁር ሳቸውን በልተው ፣ መከናቸውን ጐራጉረው ሊወጡ ሲዘጋጁ ፣ ዘይኑ ተመልሰው መጡና ፣

"በዳሶኮ ታሰረ " አሏቸው ።

"ዕድሩ ነው ያሰረው ? ደግ አደረገ ! ይህን ጊዜ ሳይታዘዝ ነፍቶ ይሆናል " አሉ ሥዩም ።

"መች እንደርሱ ሆነ ?"

"ታዲያ ቸኩሎ ነፍቶ ይሆን ?"

"አይደለም ።"

"ደጋግሞ ባለመነፋቱ ነው ፣ በማርፈዱ ?"
"አልደረሱበትም ።"

"ታዲያ አይነግሩኝም ?"

"የሞተችው የወይዘሮ ላቀች ሠራተኛ ናት!"

"አሄሄ እርስዎ ደግሞ ሌላ መርዶ አመጡ ! ታዲያ ብትሆንስ ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"የዕድሩ ዳሞችስ ፣ 'እንግዲህ በዳሶ አውጆታልና የዛሬን እርስዎ ይሙቱልን እባክዎ' ብለው ቢገንዙዋቸው ምን ነበረበት ?" አሉ ሥዩም እየሣቁ ።

"ያ ልቡን ውሃ የበላው ፣ ለካ ሲጋት አድሮ ኑሮ ከወደቀበት ቀስቅሰው ፣ ወይዘሮ ላቀች 'ዘመድ ስለ ሞተብኝ አቃብሩኝ' ይላሉ ብለህ ልፈፍ ቢባል ፣ እርሱ 'ላቀች ሙተዋልና ቅበሩ' እያለ ሲያሟርት አርፍዶ ፣ ሕዝቡም ተደናግጦ "

"የሕዝቡ ድንጋጤ ከምን የመጣ ይመስልዎታል ?"

"እህ ! ላቀችን ያህል ሰው ሲሞት እንዴት አያደናገጥም ? ትላንት አብረውን ቆይተው ፣ ዛሬ ሲሞቱ መደናገጥና ማዘን ይቀራል ?"

"ትላንትም አብረው የቆዩት ከሸዋዬ ጋር ፣ ለደነግጥ የሚገባውም ሸዋዬ ። ሕዝቡማ ደስ ብሎት ነበር ። ደስታው ፈን ቅሎት ነበር የተደናገጠው ። ደስታስ ያስደነግጥ የለ ?"

"እባክዎ ርስዎ ያግሙ ፣ ከሰው ጋር እንዲኖሩ ይሁኑ ። ምን ያደርጋል እጉል ነገር ?"

"ለላቀችና ለወዳጅቿ ካልሰገድኩ መኖር አልችልም ማለት ነው ?" አሉና ሸኙዋቸው ።

ከሾፌራቸው አርግዛ ምጥ ሲይዛት ወደ ሐኪም ቤት የሚወስዳት አጥታ የሞተችውን የወይዘሮ ላቀችን ሠራተኛ ለመቅበር የወረዳው ሕዝብ ፣ የፓርላማው አባላት ፣ የፊታውራሪ ሸዋንግዛውና የአቶ ሸዋዬ ዘመዶችና ጓደኞች ፣ ወዳጅ ዘመድ በነቂስ ተሰብስቧል ። ወይዘሮ ላቀችም የፓርላማውን ጥቁር ካባ አውልቀው የክቱን ጥቁቁር ልብስ ለብሰው የሥራ ጓደኞቻቸው በሆኑት አማካሪዎች ግራና ቀኝ ተደግፈው የይምሰል ውዝዋዜ ያሳያሉ ። ሸዋንግዛውና ሸዋዬም እርስ በርስ እየተገራመሙ ወዲያና ወዲህ ይላሉ ። ታዲያ ለጎዘኑ እንዲመች ተብሎ ፣ "የእጎታቸው ልጅ ፣ ያሳደጉዋትና የሚያስተምሯት ፣ ለታላቅ ሰው ልጅ የታጨች ነበረች" ተብሎ እንዲወራ የዕድሩ ባለሥልጣኖች ወስነዋል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በግቢያቸው ሁለት ምርጥ ምርጥ ድንኳኖች ተተክለዋል። ምርጥ ምርጥ ወንበሮችና ዕቃዎች ቀርበዋል። ምርጥ ምርጥ አስ ተናባሪዎች ተሠልፈዋል። ለጎዘንተኛዋና ለአጃቢዎቻቸው መቀ መጫ የሀገር ፍትርን ቲያትር ቤት የሚያስንቅ መድረክ ተሠ ርቷል። ከፍራሽ ላይ ፍራሽ ከምንጣፍ ላይ ምንጣፍ— የንግ ሥት ዘውዲቱን ዙፋን የመሰለ ሰገነት ተዘርግቷል። ከወረዳው ወልፎ በከተማው ከታወቁት አድባራት የታወቁ ካህናት ተጠ ርተው የሚችቷን ነፍስ መንግሥተ—ሰማያት ለማስገባት ጸሎተ ፍታት ያዘዋል። አስለቃሽ ከመካከል ቁማ ታስረግዳለች፤ ከማዘ ጋጃ ቤት ሻል ያለው የሬሳ መኪና ተመስጂል። ከመርካቶ የተገዛው ተራ የሬሳ ሳጥን በምርጥ አልባሳት ተሸፍኗል። በጉዞ ፍታት ሲያዘግም የዋለው አስክሬን ቤተ ክርስቲያን እስኪደርስ ቀድሞ የሔደው አቃባሪ ሁሉ፣ በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ኮልኩሎ የተሟሟቀ ጭውውትና ሣቅ ሰላቅ ተይዟል።

እቶ ዘይኑም ፣ በሠፈሩ በታወቁት ሽማግሌዎች አማላጅ የነት አቶ ሥዩምን አስገድደው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ለቀብር ወስደዋል። አብዛኛው የሰዓቱ ጨዋታ ስለ ሟችቷ ታሪክ ነበር።

"ከሕግንነቷ ጀምረው ያሳደጓት ፣ በትምህርቷ የተመሰገ ነች ፣ ዩኒቨርስቲ ልትጨርስ የተቃረበች ፣ ለትልቅ ሰው ልጅ የታጨች ነበረች" ሲል አንዱ ፣

ሌላው ደግሞ ፣ "እጮኛዋ ለትምህርት ወደ ሔደበት ወደ አሜሪካ ሊያስወስዳት ፡ ሁሉ ነገር አልቆላት ነበር አሉ" ይላል።

"እዩ የዛሬ ልጆች! ምን አስቸኳላቸው? ሊዳሩ ድግሱ ተጀምሮ ነበር አሉ። ታዲያ ተሳስተው ፅንስ ስለ ያዘች መድኃኒት ወስዳ ነው አሉ" ሲሉ አንዱዋ የምክር ቤት አማካሪት ፣

"እንዲያው ቢፈርድባት ነው እንጂ ፣ ስንቶቹ እያረገዙ እየ ተጋቡ በሁለተኛው ፣ በስድስተኛው ወር ይወልዱ የለም ?" ይላሉ አንደኛዋ።

"ምን ታድርግ? እጅሪትን ፈርታ ነዋ! ጥብቅ ናቸውኮ! በእርሳቸው ዘንድ ውስልት የለ። ይኸው ባላቸው ከሞቱ ስንትና

t.me/OLDBOOKSPDF

ስንት ዓመት ሆናቸው ። 'ከእንግዲህ ወዲህ ወንድ ለምኔ!' ብለው ብቻቸውን ይኖሩ የለም ? እሳቸው አሳድገዋት ምን ታድርግ ?'' ይላሉ ሌላዋ !

''እርሱኛዋ ቀንቶ ነው አሉ ያስረገዛት ። 'ጠርጥሬሻለሁ ፣ ከእንድ ሰው ጋር ሆቴል ቤት ስትገቢና ስትወጪ አይቼሻለሁ ፣ ክብሪናሽ መኖሩንና ያለመኖሩን ማረጋገጥ አለብኝ ፣ ያለዚያ ቀለ በቴን መመለሴ ነው ' ብሎ አስገድዷት ነው አሉ ያስረገዛት ።''

እንደዚህ እየተባለ በዚያች በምስኪን ሬሳ ላይ ወሬው ይሰ ለቅበት ነበር ።

ከዚያ ቀጥሎ የተሰበሰበው ቀባሪ ስለየራሱና በአካባቢው ስለ ሰማው ነገር ሁሉ ያጨዋወት ነበር ። ከአቶ ሥዩም ጋር የነበሩት የሰድር ዳኞች ፣ ነጋዘብ ያሻዎች ፣ ጸሐፊዎችና በሌላም የመንግሥትና የግል ሥራ የተሠማሩ ነበሩ ።

''በዚያ ሰሞን ትኩስ ሬሳ እያወጡ እየጣሉ ፣ ሣጥኑን ቀለም ቀባብተው እንደገና እየሸጡ ፣ የመቃብር አጥር ብረት ነቅለው እየሸጡ ያስቸግሩ ከነበሩት ሌቦች 'ሁለቱ በደፈጣ ተገደሉ' አሉ! ሰምታችኋል ? እንደዚህ ያሉ አረመኔዎች ተፈጠሩ ። ደግሞ የሚገርመው ቢተሰቦቻቸው የዕድር ገንዘብ መጠየቃቸው ነው'' ብሎ አንዱ ወሬ ሲጀምር ፣

ሌላው ደግሞ ፣ ''በኛ ሠፈር የደረሰውን ልንገራችሁ'' ብሎ የአዳማጮቹን ዐይነ ልቦና ከማረከ በኋላ ፣ አካባቢውን ተመለ ካከቶ ጨዋታውን ይቀጥላል ። ''አንድ ብልጣ ብልጥ ጋዜጠኛ ነው አሉ ፣ ከአንዱዋ ከናጠጡ ባላቸውን ከፈቱ አሮጊት ዘንድ ጠጋ ብሎ ልባቸውን ያጠፋቸዋል ። ከሰነባበቱ በኋላ አዲስ ፔጀ ገዝተው ይሰጡታል ። ሰነባብቶ በዚያ መኪና ቆናጽጅት መለዋወጥ ይጀምርና ፣አንዱዋን የሀብታም ነጋዴ ልጅ ያስረግዛል ። አባት በፍርድ ቤት ሊከሱ ጠበቃ ሲያማርጡ ፣ ሽማግሌ ልኮ ጠቅልሎ ያገባና ፣ በዚያ በፔጀው እዩኝ እዩኝ ማለት ሲጀምር እኒያ አሮጊት ደግሞ በተራቸው ' መኪናው በስሜ ነው ፤ ሊብሬው በጄ ነውና ፣ መኪናዬን መልስ ፣ ያለዚያ ያችን ቶፋ ፊት ኩታ ራህን ፍታ ። እንዴት በመኪናዬ ትዳርበት' ብለው ምርጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠበቃ ይዘው ይነሣሉ ። እርሱም ቤቱን ጠብ ርግፍ አድርጉ ይተወውና ከእርሳቸው ጋር ይጣበቃል ። በመጨረሻ ያች ሚስት ፣ 'ቤት ያለባል ምን ያደርጋል?' ብላ ፣ ጓዙዋን ጠቅልላ ፣ እንደ ገባች የወለደችውን ልጅ አንጠልጥላ ወጣችለት !''

''ወይዘሮ ላቀችና አቶ ሽዋዬም እንደዚሁ ሳይሆኑ አይቀሩም ፣ ምን አለ ትሉኛላችሁ'' ሲሉ ሥዩም ፣

''እባክዎ አጉል ነገር አይናገሩ'' አሉና ዘይኑ አገረመረሙ።

በዚህ ሲሣሣቁ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ከሚገቡት ሴቶች መካከል አንዱዋ ሽጋ ወጣት ነጠል ብላ ፣ ወደ እነአቶ ሥዩም ጠጋ ብላ ፣ ለእንደኛው ዕድር ጸሐፊ ሰላምታ ሰጠችውና አነጋግራው ስታልፍ ፣

''ማለፊያ ናት ፣ ምንም አትል ። ምስጢረኛ ዕድርተኛ ናት?'' ብለው አንዱ ቀንጣጭ አዛውንት ሲአሽሟጥጡት ፣ ሌሎቹም በጥያቄያዊ አስተያየት ሲያተኩሩበት ፣

''የባለቤቴ የጡት ልጅ ናት ።''

''እንኳን ወንድ ያልሆነ'' አሉት አንዱ አዛውንት ።

ወደ ቤተክርስቲያኑ ከሚገቡት አቃባሪዎች አንድ ባለሥልጣን በመንግሥት መርሰዲስ ዐለፉ ። ጥቂት ቆይቶ አንዲት ሴት በመንግሥት ፔጀ ሲያልፉ ተመለከቱዋቸውና አቶ ሥዩም ፣

''እያችኋቸው ክቡር አቶ...እና ባለቤታቸውን?'' ብለው ጨዋታ ሲጀምሩ ፣ ሁሉም አምን ታቸውን ሲያረጋግጡላቸው ፣ አቶ ሥዩም ጨዋታቸውን ቀጠሉበትና ፣''እስቲ እንግዲህ እግዜር ያሳያቹሁ ! ሚስቲቱ የመንግሥት መኪና መያዟ ምን ይባላል? ደግሞስ የምን አዩልኝ ነው ፣ ሁለቱም ለየብቻ በመንግሥት መኪና መምጣታቸው?'' ሲሉ ፣

''በዚህ ነው የሚገረሙት ? ከባልና ሚስት ዐልፎ ለልጆቻቸውስ የመንግሥት መኪና የሰጡ ባለሥልጣኖች ሞልተው

t.me/OLDBOOKSPDF

የለ ! ይኸ የጃንሆይ መንግሥትኮ በተአምር የሚንፏቀቅ ነው'' ብለው አንዱ ተቹ ።

''አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ ። ቆማጣ ሚስት አግብቶ ቆንጆ ልጅ ያስወልዳል ። ጐረቤቶች ተሰብስበው ግንፎ በልተው ስም ሲያወጡ አንዱዋ 'አስቱር' አንዱዋ 'አልማዝ' አንዱዋ 'ዝናሽ' አንዱዋ 'ፀሐይ' እያሉ የተሰበሰቡት ሴቶች ሁሉ አንዳንድ ስም ሲቸሩላት ፣ አባት ዝም ብሎ ሲያዳምጥ ቆየና ፣''እባካችሁ ጣጣሽ ገና በዓት'' አለ ይባላል ። ''ውላ አድራ እንደኔው ትቆመጣለች ማለቱ ነው ። ያዜም መንግሥት እንደዚሁ ነው ፣ ተማሪ እንኳ ባቅሙ ፣ 'መሬት ላራሹ' እያለ ሲነሣበት ምን ትላላችሁ ?'' አሉና ራሳቸውን ወዲያና ወዲህ ሲወራውሩት ፣ ሁሉቹም አንገቶቻቸውን እስክስታ እያወረዱ አጀቡዋቸው ።

አቶ ሺበሺ የተባሉ የወይዘሮ ላቀች ዕድርተኛ ፣ ጠጋ ብለው ከአቶ ሥዩም አጠገብ ቆም እንዳሉ ፣

''ምነው ሰሞኑን አልተያየንም ? እሑድ ለትም ቤተ ክርስቲያን አልመጡም ?'' ብለው ሲጠይቋቸው ፣

''ምንኮ የአዲስ አበባ ኑሮ ፣ ያውቁት የለም ?'' አሉ አቶ ሺበሺ ። ''አንድ ሰሞን መኪናዬቱ ፣ አንድ ሰሞን ባልተቤቲቱ ፣ አንድ ሰሞን አንዱ ልጅ ፣ አንድ ሰሞን አንደኛዋ ልጅ ፣ አንድ ሰሞን ከቤቱ ዕቃዎች አንዱ ፣ ሲብስም ተደራርበው ይታመማሉ። ታዲያ እነርሱን በየመጠጋገኛው ቤት ይገፍ ስንከራተት ነዋ!'' አሉዋቸው ።

''አዎ ! ብዙ ቤተሰብ ያለው ብዙ ደስታና ብዙ ችግር ይፈራረቁበታል ። እንደ እሜቴ ላቀች ማለት ነው ። ይኸው እላቸው ብዙ ቤተሰብ ስላላቸው አይደል ለገረዳቸው ጎዘን አገር ምድሩ የተሰበሰበላቸው ?'' ሲሉ ሥዩም ፣

''እባክዎ ይህን አጉል ነገር አይናገሩ'' አሉዋቸው አቶ ዘይኑ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለመሆኑ ሚችቲ ሐኪም ቤት አልገባችም ኑሩዋል ? እንደ ሰማሁት በወሊድ ምክንያት ነው የሞተችው አሉ" ብለው ሺበሺ ሲጠይቁ ፣ ሬሳው ሴቱን አስቀድሞ ፣ ወንዱን አስከትሎ በመኪና ተጭኖ ብቅ አለ ።

"የባልዮው ቀብርም ይሆን ያህል አልደመቀ" አሉ ሥዩም ።

"እባክዎ እንዲያው ዝም ይበሉ ። ሰው አይሰማም" አሉ ዘይኑ ።

"እህ ሰው እንዲሰማኮ ነው የምናገረው" አሉና ሥዩም አፈጠጡ ።

"ምን ጥቅም ያገኙበታል ? አሳቸውስ ቢሰሙ ?" አሉ ዘይኑ ።
"ማን ቢሰሙ ?"

"ወይዘሮ ላቀች !"

"እና ምን እሆናለሁ ?"

"ሆሆይ ! 'ጊዜ ያነሣው ቅል ድንጋይ ይሰብራል' ይባላል እኔ መቶ አለቃ ከበደ፣ እኔ አቶ እንደሻውስ እንደዚሁ አጉል ድፍረት እየተዳፈሩ አይደለም እንደዚያ ሆነው የቀሩት ? አይሆንም አይዳፈሩ ፣ ይቅርብዎ" አሉና ዘይኑ ፣ እንደ መጨረሻቸው አድርገው ምክራቸውን ለገሡ ።

"እንዲያው ለመሆኑላ የዕድሩ ገንዘብ ለማንኛቸው ሊከፈል ነው ? መቼም ሚች ያስረገዛትም ፣ እመቤትም አሉዋት ። ሁለቱም በይገባኛል ሳይነታረኩ ይቀራሉ ?" አሉ ሥዩም ፣ ጮክ ብለው ።

"ሁለቱም ዕድርተኞች ከሆኑ ፣ ለሁለቱም መክፈል ነዋ ! ሌ ምን ይደረጋል ?" አለ ያ የተጐራባች ዕድር ጸሐፊ ። "እንደዚህ የመሰለ ሁኔታኮ በአንድ ዕድር ደርሷል ። እንዲት ሴትዮ ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ባንድ ቤት ይኖራሉ ። ሟቷም በሥ ፈራቸው ዕድር ገብተዋል ። በመካከሉ እናት ሲሞቱ ፣ ሁለት ልጆች ፣ ድርሻ ድርሻችንን ክፈሉን ። የእናታችን ለብቻ ፣ ለኛም ለሁለታችን እንደዚሁ ለብቻ ለብቻ ሊከፈለን ይገባል" ብለው

t.me/OLDBOOKSPDF

የዕድሩን ዳኛ ይጠይቃሉ። ዳኛውም 'ይህማ እንዴት ይሆናል! ካንድ ቤት ለወጣ ሬሣ ሦስት ክፍያ እንዴት ይደረጋል! ብለው ሲተቹ፣ ሴቶቹ ደግሞ፣ደንቡ ለሦስታችንም ይፈቅድልናል' ብለው እጥብቀው ስለ ተከራከሩ፣ ለሦስታቸውም ድርሻ ድርሻቸው ተከ ፈለ'' አሉ።

አቶ ሥዩም ለጠቅ አደረጉና፣ ''እንዲህማ ከተፈረደ፣ ይህ ችም ሟች ድርሻ ስለሌላት ያስረገዛት ሰው አያገኝም። ባለመ ብቷ ወይዘሮ ላቀች ብቻ በመሆናቸው እመቤቷ ጉልበቷን ሲግጡ ኑረው፣ ሬሳዋ ከቤታቸው ስለወጣ ደግሞ የዕድሩን ገንዘብ ሊበሉ ነው።''

''እባክዎ ሁሉን አይናገሩ'' አሉ ዘይኑ እየተሣቀቁ።

ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ የነበረው አልቃሽ በቡድን በቡድን እየሆነ ሁሉም እንደየዝንባሌውና እንደየተግባቢነቱ ሲጨዋወት፣ በምድረ ሾፍሮሌት፣ መርሰዲስ፣ ሲትሮይን፣ ፔጆ፣ ኦፔል፣ ፊያትና ቮልስዋገን አውቶሞቢሎች የታጀበው ሬሣ ሲደርስ፣ ሁሉም ከየነበረበት እየተሰበሰበ ሬሣውን አጀብ አጀብ፣ ከብብ ከብብ ማድረግ ጀመረ። ላቀች ከነደጋፊዎቻቸው በወዳጃቸው መርሰዲስ፣ ፊታውራሪ ሸዋንግዛው ካንድ ወዳ ጃቸው ጋር፣ ሸዋዬም ከጓደኛው ጋር በየኦቶሞቢሎቻቸው ተከ ታትለዋል። ከጥዋት ጀምሮ ሲቆፈር ያረፈደው መቃብር በሚች እውነተኛ ደረጃ ነበር። እኩለ ቀን ካለፈ በኋላ ግን፣ ''ለእኅት ልጅነቷ'' ተስማሚ የሆነ መቃብር እንዲቆፈር እነአቶ ይጥና ስለ ወሰኑና መሬቱም የሚችለውን እውነተኛ ማንነት ዐውቆ፣ ''ደረጃዋ ወደሚፈቅድላት ውሰዱ'' ብሎ የለገመ ይመስል፣ አፉን ዘግቶ፣ ደረቱን ነፍቶ አልነካም በማለቱ፣ ከምርጥ ምርጥ ቆሩ ሪዎች ጋር ተጋጠሙና ለመቸናነፍ ጊዜ ፈጀ። ታዲያ ጉድጓድ እስቲቆፈር ድረስ ቀሳውስቱም፣ አስለቃሹም አጃቢዎቹን ያጨዋ ውቱ ነበር። በተለይ አስለቃሹዋ፣

''ተምራ ተምራ ዕውቀት ቢዘልቃት
መጠቀች አረገች፣ የላቀች ወጣት
የመኳንንቱ ልጅ፣ የባላባቱ ልጅ፣ ሲራኮትባት

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲያደባ ቆይቶ ሞት ሠርቶ እገባት
ጓደኞችሽ መጡ፣ እየተላቀሱ
መምህሮችሽ መጡ፣ ዕንባ እያፈሰሱ
የሕዝብ ዐዘን ይግባሽ፣ ተመለሺ ካሡ
መኳንንት ወይዛዝርት ተሠልፈው መጡ
በዕንባ ታጠቡልሽ፣ ድንገት እንችን ቢያጡ
ውበትና ትምህርት እሚልቶ ሰጥቷት
ፈጣሪ ወሰዳት፣ ለራሱ አሰቧት ።''

ግባተመሬት ከሆነ በኋላ፣ የወይዘሮ ላቀች ነፍስ አባት የነበሩት መምሬ ገብረ ወልድ ከሕዝቡ መካከል ቁመው ሲያሳርጉ፣

''ሐዋርያው ዮሐንስ፣ 'ሞትም እንግዲህ አይሆንም፣ ልቅሶም፣ የቀደመው ሐዲስልና' እንዳለው፣ እነሆ ይህች ወጣት ቀድማለችና በመቤቴም ቤት እንግዲህ ለቅሶ አይሆንም'' እያሉ ሲሰብኩ፣

''እህ! ምን ማለታቸው ነው እኚህ ቄስ? 'የሠራተኛዋ መቅደም ማስጠንቀቂያ ነውና ንስሐ ይግቡ፤ ያለዚያ በፍጥነት ይከተላሉ' እይሉዋቸውም?'' ሲሉ አቶ ሥዩም፣

''እረ እባክዎ፣ ሰው እንዳይሰማዎ'' አሉ ዘይኑ ።

ቄሱ አሳርገው እንዳበቁ፣ ለቀብሩ የሔደው ሕዝብ ወይዘሮ ላቀችን እየተሰናበተ ሲመለስ፣

''ሾፌራቸውስ የት ነው የሚያሰናብተው?'' ሲሉ ሥዩም፣

''እርሱን የሚሰናበቱት ከቤት ነው ። እዚህ ደግሞ እኩል ሊቆም ኑሩዋል'' አሉ ዘይኑ ።

ወይዘሮ ላቀች፣ አስተዛዛኛቸውን አሰናብተው በሥራ ጓደኞቻቸው ተደግፈው በቀረበላቸው መርሰዲስ ተጋብተው ሲሔዱ፣ የዕድራቸው ጸሐፊ ደግሞ፣ የዕድርተኞች ስም መጥሪያ በሆነው ሥፍራ ላይ ቆሞ የዕድርተኞችን ስም መጥራት ሲጀምር፣

''ይቆዩኝ፤ ሁለታችንም መምጣታችንን ነግሬው ልምጣ'' ብለው ዘይኑ ሮጥ ሲሉ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"እይሒዱ ። የዕድርተኛ ስም የሚጠራው ዋናው ዕድር ተኛ የሞተ እንደሆነ ነው እንጂ ፣ ለተቀጥላው ሁሉ አይደለም ። በደንባችንም ውስጥ የለም ። ወደ ቤታችን እንሒድ" አሉ ሥዩም።

"እንዴ ፣ ይቅጡናልኮ" አሉ ዘይኑ ፣ ለመሮጥ እያገረገሩ ።

"እነርሱም ስም መጥራት የጀመሩት ለቅጣት እንዲያመቻቸው ነው ። እስቲ ሁለት ጉድጓድ እስቲያስቆፍሩ ጦሙን ያዋሉትን ሕዝብ ከተበታተነ በኋላ ፣ እንደገና ስም እንጠራለን ማለት ምን ፍለጋ ነው ፣ ማንቲም ለመለቃቀም አይደለም ፣ መቼም በዘፈቀደ በስመ ዕድር የሚደናበር ሠፈር ነው ። የሚጥሉብንን እንከፍላለን ። የስሙኒ መቀጫ ፈርተው እዚያ ሔደው አይጋፉ" አሉና ሥዩም ፣ ወደ ቤታቸው ማዝገም ሲጀምሩ ፣ አቶ ዘይኑም የሚጣልባቸውን መቀጫ ለመክፈል ዝግጁ ሆነው አብረዋቸው ማዝገም ጀመሩ ።

እልፍ እንዳሉ ፣ ለወይዘሮ ላቀች ገረድ ቀብር ከከተተው ሕዝብ ሩቡን እንኳን የማያህል እታባሪ ያጀበው ሬሣ በባለሸራ ላንድሮቨር ላይ ተጭኖ ደረሰ ።

"መቼም በዚህ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ቀን እንድሰው ብቻ ቀብሮ መገላገል ቀርቷል ። ሬሣ ተራምደን እንሒድ ፣ እንመለስ እንጂ ምን ይደረጋል ?" አሉ ሥዩም ፣ አብረዋቸው የነበሩትም በነገሩ ተስማሙና ወደ ኋላቸው ተመልሰው ከቤተ ክርስቲያኑ ጥግ ቁመው ሲጠባበቁ ፣

"ብዙም የሚታወቅ ሰው አይመስልም ። አጀቡ መለስተኛ ነው" አሉ ዘይኑ ።

"ከሞቱም በኋላ መታደል ነው እንጂ ፣ የላቀችን ገረድ ግን የሚያውቃት ሆኖ ነው ፣ የሀገሪቱ መኳንንትና ወይዛዝርት በነቂስ ወጥተው የቀበሯት ?" አሉ ሥዩም ።

ቀዳሚው የሴት ሠራዊት ወልፎ ሬሳውን የጫነው ላንድሮቨር ወደ ቤተክርስቲያኑ እንደገባ ፣ ከኋላው ከነበሩት መንዶች አንዱ ወደ እነ አቶ ሥዩም ጠጋ ብሎ ከአቶ ዘይኑ ጋር ሰላምታ እንደ ተለዋወጠ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"የሞተው ማነው ?" ብለው ዘይኑ ጠየቁት ።

"ያውቋቸው ይሆናል ፣ ሻለቃ ደሳለኝ የሚባሉ ናቸው ። ዱሮ ወሎ ውስጥ ያውራኝ ገዥ ነበሩ ።"

"አዎ አዎ ፣ ዐውቃቸዋለሁ እንጂ ! አዬ ብዙ ጊዜያቸው ነበር ፤ ከታመሙ ቆይተው ነበር ። አዬ ጉድ! የብዙ ልጆች አባት ነበሩ" አሉ ዘይኑ ።

"ምን ያደርጋል ታዲያ ቤት ሙሉ ቢወለድ? እንደዚያ ታመው ሲቸገሩ አንድም ልጅ አልረዳቸውም ። እንደ እርሳቸው ከሆነስ ያለመውለድ ይመረጣል" አለ ወሬ ነጋሪው ።

"እንዴ! ደኅና ደኅና ሥራና ትዳር የያዙ ብዙ ልጆቸኮ አሉ ዋቸው ። እንዴት አልረዱዋቸውም ትላለህ?" አሉ ዘይኑ ።

"እናውቃቸዋለን ፣ አንዳቸውም አንድም ነገር አላደረጉላ ቸውም" አለና ወሬ ነጋሪው ወደ ፊት ሲያመራ ፣ እነአቶ ዘይኑም አብረውት ሲያዘግሙ ፣

"ስሙ ፣ አቶ ዘይኑ!" ብለው ሥዩም ፣ ንግግራቸውን እንዲ ሰሙላቸው ቆም አሉና ፣ "ፈረንጆች ሲመስሉ ፣ 'አንድ አባት ዐሥር ልጆች ያሳድጋል ። ዐሥር ልጆች ግን አንድ አባት መጦር አይችሉም' ይላሉ ። እውነታቸውን ነው ። ልጅኮ የወላጅን ያህል እንጀት የለውም ፤ እርሱ የሚያዝነውና የሚያንሰፈሰፈው ለሚ ወልደው ፣ ከአብራኩ ለሚከፈለው እንጂ ፣ ለወላጅ አይደለም" አሉዋቸው ።

የሻለቃ ደሳለኝ ፣ የቀብር ሥነ ሥርዓት ያለብዙ ጣጣ ተፈ ጽሞ ወደ ማሳረጊያው መልስ ሲሆን ፣ መቶ የማይሞሉ ቀባሪ ዎች ያጀቡት ሬሣ ብቅ ሲል አቶ ሥዩም ተመለሱና ፣

"እንግዲህ በስተጀርባ በኩል እንወጣ እንደሆነ እንጂ ፣ በፊት ለፊት መውጣት አልተቻለም" አሉ ።

አዲስ ደራሹን አስከሬን ካጀቡት ኅዘንተኞች መካከል ፣ በሁለት ጠብደል ጠብደል ሴቶች ግራና ቀኝ ተፈጥሮቃ የተያ ዘች ወፈርፈር ያለች ልጅ እግር ሴት ነበረች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"የናቴ ልጅ ፣ በብስጭት እንደ ተቃጠልክ ፣ በጥቃት እንደ ተለበለብክ ፣ ፍርድ ሰጭኝ እንዳልክ ፣ ዘመናይ ባለሥልጣን እንዳ ባረረህ ፣ እልህህን ቁጭትህን ሳትወጣ ዐፈር ልትግባ ነወይ? ወይ ወንድም ማጣት! ወይ ዳኛ ማጣት ! ወይ ፍርድ ማጣት! የሰሚ ያለህ! የዳኛ ያለህ! የፍርድ ያለህ !" የማትለው አልነበራትም ። የባጥ የቆጡን እያነሣች ትጮኻለች ።

አቶ ሥዩምን ደግሞ ፣ እንደዚያ የመሳሰለው ነገር ይጉተጉ ታቸዋልና ፣ ጠጋ ጠጋ ማለት ጀመሩ ። ታዲያ ፣ "ለሆዳም በሬ ጭድ ያዝለታል" እንዲሉ ፣ እንዲሁ የሩቅ ዕውቂያ እንጂ ብዙም ንግግር ያልነበራቸው ሰው አዩና ወደ እርሱው ቀረብ ብለው ፣ ሰላምታ ሰጡና ፣

"ሚች ማን ይባል ኑሯል? ምን ሆኖስ ነው የሞተ ?" ብለው እንዱን ጠየቁ ።

"አይ ፣ የሚያውቁት እንኳ አይመስለኝም ፤ አሟሟቱ ግን ያሳዝናል ። በግፍ ሞተ" ብሏቸው ራመድ ሲል ፣ ክንዱን ይዘው፣ "የግፍ ፍርድ ተበይኖበት ተሰቅሎ ነው ?" ብለው ጠየቁት ።

"በገንዘቡ ገዝቶ ሲያለማ የኖረውን መሬቱንና ፣ አስተምሮ ሥራ አስይዞ ያገባትን ሚስቱን ባለሥልጣን ነጥቆት ፣ በዚህየተ ነሣ ተበሳጭቶ ፣ 'የፍርድ ያለህ!' እንዳለ እንደ ጮኸ ፣ ጀንሆይ በሚሔዱበት ሁሉ እየዞረ ከመኪናው መንገድ እንደ ወደቀ የሚ ያቀርበው አጥቶ እንዳለቀሰ ፣ ደም ተፍቶ ሞተ "አላቸውና ሲሔድ ፣ እርሳቸውም ወደ አቶ ዘይኑ ዘወር አሉና ፣

"ይበሉ ፣ ወደ ቤታችን እንሒድ" አሉዋቸው ።

"እንዴትኮ? ሬሣ ተራምደን ?" አሉ ዘይኑ ።

"እንኳን እኔ ቆሜ ልቀብረው ፣ በቤተክርስቲያንም በመቀ በሩ አዝናለሁ" ብለው ሥዩም እየተቆናጠሩ ጉዞአቸውን ሲጀ ምሩ ፣

"ለምን ?"አሉ ዘይኑ ፣ ደንገጥ ብለው እየተከተሉ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴ! ርስቱንና ሚስቱን ባለሥልጣን ሲቀማው እያለቀሰ ከሚሞት ፥ የቀማውን ገልብጦት አይሞትም ኑሩዋል ?እንሒድ እባክዎ" ብለው ራመድ ራመድ ሲሉ ፥ ዘይኑም ተከተሉዋቸው ።

በዚያን ዕለት ማታ ፥ አቶ ዘይኑና ሌሎች የሰድሩ ሽማግሌዎች ሥዩምን አባብለውና ለምነው ፥ ወደ መይዘሮ ላቀች ቤት መለሱዋቸው ። ሁለቱ ድንኳኖች በመኳንንትና በወይዛዝርት ካፍ እስከ ገደፉቸው ግጥም ብለዋል ። ፊታውራሪ ሽዋንግዛውና አቶ ሽዋዬም ለየብቻ ሆነው ከየጓደኞቻቸው ጋር ይጨዋወታሉ ። ሁለቱም ዐይኖቻቸውን ከመይዘሮ ላቀች ላይ እያሳረፉ ይመልሳሉ ። ሁለቱም እርስ በርሳቸው ይገለማመጣሉ ።

ሥዩምና ዘይኑም ፥ አስተናባሪው ያሳያቸውን ቦታ ትተው ራሳቸው በመረጡት ሥፍራ ተቀመጡ ። ወዲያው ሥዩም በእጠ ገባቸው ከነበሩ ባለሥልጣን ጋር ሰላምታ ተለዋወጡ ። ባለሥልጣኑ ወንዝ የሚያሻግር ሹመት የነበራቸው ነበሩ ። ነገር ግን ሥዩምን ዘንግተዋቸው ኑሮ ፥ እጅግም ለሰላምታው አልተቸገሩበትም ነበር ። ሥዩም ግን ስላልዘነጉዋቸው ፥ "ከአሁን አሁን ያነጋግሩኝ ይሆናል" እያሉ ዐይን ዐይናቸውን ሲመለከቱዋቸው ነበር ።

"አዬዬ! መይዘሮ ላቀች እንዴት ተጐዱ! ሚችቷ የተማረች ነበረች አሉ" በማለት ባለሥልጣኑ የጀመሩትን ጨዋታ ፥

"አወይ ወዲያ!"አሉና ሥዩም እንገታቸውን ጠምዝዘው አንጠራጠሱባቸው ። የለነዘሩት ንግግር ተቀባይነት ያለማግኘቱን የተረዱት ባለሥልጣን በለሙት ወሬ ተጠራጠሩና ጨዋታቸውን መለወጥ እንደሚሻል በመረዳት ፥

"ከጌታዬ ጋር የምንተዋወቅ ይመስለኛል ። ከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኛ ነበሩ ፥ አይደል?" ብለው አቶ ሥዩምን ጠየቁዋቸው ።

"ዳኛስ አልነበርኩም ። ለነገሩ ግን ድሮ በአገር ግዛት ስሠራ ነበር የተዋወቅነው ። በኋላ ከባለሥልጣን ጋር መስማማቱ ችግር

t.me/OLDBOOKSPDF

ሆነና ወደ ንግድ ሚኒስቴር ተዛውሬ ጥቂት ዓመታት ካገለገልኩ በኋላ ፣ አሁንም የመስማማቱ ነገር ችግር ሆነና ጥየው ወጣሁ" ብለው ሲመለከቱዋቸው ፣

"ዛሬስ በጡረታ ላይ ነዎት?" አሉ ባለሥልጣኑ ።

"ዛሬማ ራሴ ፣ የራሴ አሽከርና ጌታ ሆኜ ፣ ራሴ ለራሴ ሥራ ፈጥሬ ፣ በንግድ ሥራ እተዳደራለሁ ። እርግጥ ጊዜው ረዘም ብሏል እንጂ ፣ ከዚህ ቀደም የተያየነውና የተጨዋወትነው በአይሮፕላን ውስጥ ነበር ። "

"ባገር ውስጥ ነው በውጭ አገር በረራ?" አሉ ባለሥልጣኑ ፣ የአቶ ሥዩምን የነጋዴነት ደረጃ ለማወቅና እርሳቸውም ዓለምን የዞሩዋት መሆናቸውን ለማሳወቅ ብለው ።

"በሁለቱም በረራ ነበር ። አንድ ጊዜ አሥመራ ድረስ ጐን ለጐን ተቀምጠን ፣ አብረን እየተጨዋወትን ሔደናል ። አንድ ጊዜ ደግሞ ከሮም አብረን እየበረርን መጥተናል ። ያውም እንኳ ትዝ ይልዎት እንደሁ ፣ አንድ መጽሔት ስለ አንድ የዓሣ ነጋዴና ስለ አንድ ገበያተኛ የጻፈውን አንብቤልዎ ፣ እርስዎም ሚስቶቻቸውን ስለ ተነጣጠቁ አውራጃ ገዥና ገበሬ አጫውተውኝ ነበር አሉዋቸው ። "

"አዎ! ትዝ አለኝ ። እንዲያውም ያን ታሪክ ለብዙ ሰዎች ሳጫውታቸው ኑሬያለሁ" አሉና ባለሥልጣኑም እንደገና ሲጨባበጡ ፣ አቶ ሥዩምም "እኔም እንጂ ያንጊዜ የነገሩኝን ነገር ለብዙ ሰዎች አጫውቻለሁ" አሉዋቸው ።

ባለሥልጣኑ ቀጠል አድርገው ፣ "ይቅርታ ፣ እስቲ ያን ታሪክ ለእኒህ ወዳጄ ይንገሩዋቸው ። በእውነት በኃላፊነት ላይ የምንገኝ ሁሉ ልንሰማውና ልብ ልናደርገው የሚገባ ይመስለኛል" ሲሉ ፣

"ምን ኑሩዋል ከሆነማ እንሰማው እንጂ!" አሉ አብረዋቸው የነበሩት ጓደኛቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"መቼም ፈረንጆች ማንኛውንም ነገር በምሳሌ ማቅረብና ማስተማር ይሆንላቸዋል ። በተለይ ጣሊያኖች በቀልድ አጻጻፍ የሚወዳደራቸው የለም" ብለው አቶ ሥዩም ለታሪካቸው ማስ ታወቂያ እንደ ሰነዘሩ ፣ ፈታውራሪ ሽዋንግዛው ከጓደኞቻቸው ጋር ሲወጡ ሁሉም ተመለካከቱዋቸውና ፣ ሥዩም ጨዋታቸውን ቀጠሉ ።

ባለሥልጣናቹን ተራ በተራ ሲመለከቱዋቸው ፣ እነርሱም ታሪኩ እየኮረኮራቸው ሣቅ እየተቀባበሉ ሲያስተናግዱ ፣ ከወይ ዘሮ ላቀች አጥር ግቢ ቀጥሎ ባለው ግቢ የተደበላለቀ ኡኡታ ሲያ ስተጋባ ፣ አቶ ይጥናም ፈጥኖ ደራሽ ሠራዊታቸውን እየመሩ ፣ ተሠማሩ ።

"እዩ ጣጣ! በከፉ ቀን የመጡ ሰዎች ሠፈሩን አስቸገሩ" ሲሉ ዘይኑ ፣ ከአጠገባቸው ከነበሩት ባለሥልጣኖች አንዱ ፣

"ስካራሞች ናቸው?" ብለው ጠየቁዋቸው ።

"ኧረ አይደሉም ። ባልና ሚስት ሆነው የሚኖሩ ሰዎች ናቸው" አሉ ።

"ተለያይተው ኑረው ፣ እንደገና ታርቀው ፣ ደግሞ እንደገና መጣላታቸው ነው?" አሉ ባለሥልጣኑ ።

"አይደለም ፣ ሴትዮዋ ባልዮውን ያናደዱ መስሏቸው ወደ ዘመዶቻቸው ሔደው ከርመው ሲመለሱ ቆብ ጭነው መጡ ። ከዚያ በኋላ በግቢያቸው ውስጥ ካሉት ቤቶች ባንደኛዋ ሲኖሩ ፣ ባልዮው ደግሞ በዚያው በድሮው ቤታቸው እንደሆኑ ሴት ማመ ላለስ ይጀምራሉ ። መነኩሴዋ ደግሞ ፣ 'እንዴት በቤቴ ውስጥ ፣ በአልጋዬ ላይ ሴት ይዘህ ትተኛለህ?' እያሉ መነታረክ ይጀም ራሉ ። ታዲያ ፣ ከቤት ውስጥ እየገቡ ፣ ከሚመጡት ሴቶች ጋር መደባደብ አመጡ ። የአሁኑም ኡኡታ ይኸው ነው ፤ ሌላ አይደ ለም" ሲሉ ፣ ከጎዘኑ ቤት እየተሯሯጡ የሔዱት እነ አቶ ይጥና ኡኡታውን አበረዱት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በሁለቱ ድንኳኖች የተጠቀጠቀው ሕዝብ ፣ በተጋጋሉ ጭውውት ላይ እንዳለ ራት ሲቀርብ ፣ አንዳንዱ ብድግ ብድግ ሲል ራሳቸው ደጃዝማች ፍጡር ተነሡና ፣

"ምነው ጃል ? እንዴት ገበታ ረግጣችሁ ትወጣላችሁ ? ነውርኮ ነው" ብለው ሲቆጡ ፣ የተነሣው ሁሉ ተቀመጠ ። በመጀመሪያ ከቤተ መንግሥት ከነአሳላፊዎቹ የተላከው ፣ ቀጥሎ ከታወቁ ባለሥልጣኖች ፣ ከዚያም ከምርጥ ምርጥ ወዳጆች የተላከው ምግብ በያይነቱ ፣ ጠላና ጠጅ በየመልኩ ቀረበ ። ደጃዝማች ፍጡር ፣ አቶ ይጥናና አቶ ሽዋዬ ሥራውን ተከፋፍለው አዛዥነቱን ወሰደዋል ። ጮማው ፣ ጥብሱ ቅቅሉ ፣ አረቄው ዊስኪው ፣ ኮኛኩ ፣ በያይነቱ ተንዶለዶለ ።

ምግቡ ተግ ብሎ ፣ ዕቃ ተነሣሥቶ ፣ መጠጡ ተደጋግሞ ፣ ጨዋታው ተሟሙቆ ፣ የድንኳኖችን ጣራ ቀዶ ሊወጣ እንደተቃረበ ፣ የወይዘሮ ላቀች ሠራተኛ ጠጋ ብላ ሹክ ስትላቸው ፣

"ከውጭ ስልክ ፈልጎኝ ነው ፣ መጣሁ" ብለው ለከበቡዋቸው ሴቶች ነግረው ሲነሡ ፣ ሁለት አስተዛዘኞች በግራና ቀኝ ደጋግፈው አብረዋቸው ሳሎን እንደገቡ ፣ "ስልኩ የት ነው?" ብለው ላቁ ሠራተኛቸውን ሲጠይቁ ፣

"መኝታ ቤት" ስትላቸው ፣ እርሳቸው ወደ መኝታ ክፍላቸው ሲያመሩ ፣ ሁለቱ ደጋፊዎች ሳሎን ቀሩ ።

"ስልክ የፈለጋቸው ምናልባት ከፈረንጅ አገር ይሆናል" ሲሉ አንደኛዋ ከድንኳኑ ከቀሩት ሴቶች ፣

"ምናልባት አሜሪካን አገር ያለው የሚችቷ እጮኛ ይሆናል" ብለው መለሱ ሌላዋ ።

ወይዘሮ ላቀች ፣ ከመኝታ ክፍላቸው እንደገቡ ፣ ሽዋዬ ኩቴንና ሽሚዙን አውልቆ ከአልጋው ጫፍ ቁጭ ብሎ የጫማውን ከር ሲፈታ አገኙት ።

"ወይ ፣ እረ በስማም በል! አንተ ደግሞ ታበዛዋለህ ። ይህ ሁሉ መኳንንትና ወይዘሮ በሁለት ድንኳን ሞልቶ እኛ ሌላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገር ልንሠራ! እሪ እባክህ ነውር ነው" በኋላ የት እሔድብሃ ለሁ?" አሉት፤

"በኋላማ ፍራሽ ደራርባችሁ ሳሎን ትረፈረፋላችሁ። አለና ዘሎ እንቅ አድርጎ ካልጋው ላይ ሊከምራቸው ሲል፣

"በል ቆዬኝ፣ መታጠቢያ ቤት ደርሼ ልምጣ" ብለው፣ ካፖርታቸውን አውልቀው ሲወጡ፣ ሽዋዬም ጫማና ሱሪውን አወላልቆ፣ ካልጋው ላይ ወጥቶ፣ ጋቢ ደርቦ፣ ተንጋሎ መጠባበቅ ጀመረ።

በድንኳኖቹ የሞላው አስተዛዛኝ መጠጡን እየተራጨ ሳለ፣ ፊታውራሪ ሽዋንግዛው ተመልሰው ገቡና እንደ ተቀመጡ፣ ዐይኖቻቸውን ላቀች ወደ ነበሩበት ቢወረውሩ የሉም። ቀጥሎም ሽዋዬን ፈለጉት፤ የለም። ወዲያው ብድግ ብለው ወጡና ከበራቱ ጥግ ከነበረው መኪናቸው ውስጥ ሽጉጣቸውን ይዘው፣ በቁጥታ ወደ ወይዘሮ ላቀች መኝታ ቤት ሔደው፣ በጥድፊያና በዝንጋታ ከውስጥ ሳይቆለፍ የነበረውን በር በርግደው ሲገቡ፣

"ከዚህ ሳላዳፍንብህ ተነሥ" አሉ ፊታውራሪ።

"የዛሬን ጌታዬ! የዛሬን። በድሮው ፍቅራችን! ባንዱ ልጅዎ ይገዎታለሁ የዛሬን!".....

ወይዘሮ ላቀችም ለባብሰው ወደ ድንኳናቸው ተመለሱና፣ ከአስተዛዛኞቻቸው መካከል ገቡ.....

t.me/OLDBOOKSPDF

ነሐሴ 19 ቀን 1966

በሀገሪቱ ዳር ድንበር የለውጥ ቋያ ከተቀጣጠለ ሰባት ወራት ሆኖታል። ነባርና አዲስ ሥርዓት ግብ ግብ ገጥመው ሕዝቡ ፣ "ለውጥ! ለውጥ!" ይላል። ባለሥልጣናች ግማሾቹ እጃቸውን ሰጥተው ፣ ግማሾቹ ተደናግጠው ተበታትነዋል። የሀገሪቱ ተወላጅና ዜጋ ቀርቶ የመላው ዓለም ዐይን ሕሊናም በሀገሪቱ ላይ አትኩሩዋል። ጋዜጦች ፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን በከፍተኛ ስሜትና ጉጉት የሚጠብቁ ሆነዋል። በየጊዜው ሲወጡ የነበሩት መግለጫዎች ፣ ማስጠንቀቂያዎችና ዐዋጆች የዕለት ተዕለት መወያያ ሆነዋል።

በየካቲት ወር የጀመረው ሕዝባዊው ንቅናቄ እየገፋ ከትርም ሰነት ወደ ሥርዓታዊ ዐመፅ ለመሸጋገር በዝግጅት ላይ መታየት ጀምሮዋል።

አቶ ሥዩምና ጓደኞቻቸውም ከየካቲት ወር ጀምረው እጃቻቸው ከጋዜጦች ፣ ጆሮዎቻቸው ከሬዲዮ ፣ ዐይኖቻቸው ከቴሌቪዥን የማይለዩ ሆነዋል። በየዕለቱ የሚተላለፉትን ዜናዎች እየተቀበሉ መልሶ መተቸትም የአቶ ሥዩም ኪነታዊ ሙያ ወደ መሆኑ ተረማምደዋል።

አቶ ሥዩም ፣ ከጋዜጣ ላይ በሚያዩት አርእስት ትችት የጀመሩት ፣ "የከፍተኛ ሥራ ኃላፊዎች አበል ለድርቅ ቀበሌ መርጃ እንዲውል ተወሰነ" በሚል አርእስት በወጣው ዜና ላይ ነበር።

"ምናለበት ከሌላው ሀብታቸውስ ቢሰጥ?" ብለው የሰነዘሩትን አስተያየታቸውን ወዳጆቻቸው ካደነቁላቸው በኋላማ እየገፉበት ሔዱ። ቀጥሎ ደግሞ ፣ "ሁለት ሴቶች በዘረፋ ተከሰሱ" የሚል አርእስት ከጋዜጣ ላይ እንደ ተመለከቱ ከልባቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

ከት ብለው ጣቁና ፣ ''የኛን ሠፈርስ እንዲት ሴት ይዘርፉት የለም ? ምን ያስደንቃል ?'' ብለው የሰነዘሩት ትችት ከወይዘሮ ላቀች ጆሮ ደረሰችና ፣ 'ይህች ቀን ትለፍና እኔና እርሱን ያገናኘን' ብለው ዝተዋል የምትል ወሬ አመጣችላቸው ።

ወይዘሮ ላቀችና አቶ ሥዩም ከነጓደኞቻቸው በዚያ ፍጭጫ ላይ በነበሩባቸው ቀናት ደግሞ ፣ ''የቀድሞ ሚኒስትሮች እንዲገለሉ ተደረገ'' የሚል ዜና ወጣ ። ለዚሁ አርእስትም ሥዩም ፈጥነው መልስ ሰጡ ።

''እንግዲህ የሠፈራችን ዕድር ባለሥልጣኖችም ተራ መከተሉ አይቀርም'' ብለው የሰነዘሩት አስተያየት በሠፈሩ ነዋሪዎች ዘንድ አስተጋባላቸው ። ምንም እንኳን ወይዘሮ ላቀች ከሸዋንግዛው ቢለያዩም ፣ የሸዋዬና የወይዘሮ ላቀች ቁርኝት እየጠበቀ በመሔድ ላይ ስለነበረ ፣ አቶ ሥዩምንና ሌሎችንም ተቀናቃኞቻቸውን እንደነመቱ አለቃ ከበደ አሽቀንጥረው ለማስወርወር በማንሰላሰል ላይ እንዳሉ ፣ ''የአገርን አንድነትና ዕድገት የሚቃረን ተግባር ፈጽመው ከተገኙት በስተቀር ለአገራቸው ዕድገትና መሻሻል ስለ እውነት በመነሣሣት ለአገር ፍቅር በመቆርቆር በፈጸሙት ተግባር ምክንያት በየጊዜው የታሰሩት እንዲፈቱ'' የሚል ጥያቄ ከጦር ኃይሎች ፣ ከፖሊስ ሠራዊትና ከብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ ቀረበ የሚል ዜና በሰኔ ወር መጨረሻ ላይ በመገለጹ ፣ የአቶ ሥዩምና የሠፈራቸው ዕድርተኞች ፈንጠዚያ ከሠፈሩ ዐልፎ ተርፎ ከተማውን አዳረሰ ።

ከዚህ በኋላ ፣ አቶ ሥዩም የዕድሩ ጥቂቶች አባላት በእንድነት ሆነው የሙቶ አለቃ ከበደና አቶ እንደሻው እንዲለቀቁ ላቸው ማመልከቻ ጽፈው ለሚመለከተው ክፍል አቀረቡ ። ቀጥለውም ወደ ፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ መምሪያ እየተመላለሱ ወይዘሮ ላቀች በሠፈሩ ዕድርተኞች ላይ በተለይም በሁለቱ አባሎቻቸው ላይ የፈጸሙትን ግፍና በደል እየዘረዘሩ ማስረዳት ቀጠሉ ።

የሙቶ አለቃ ከበደም ጓደኞች ቢሆኑ ፣ በጉዳዩ ላይ ማተኮር ጀመሩ ። በወቅቱ በየክፍላተ ሀገሩ ተቋቁመው በነበሩት ንውሳን ኮሚቴዎች አማካይነት ከበደና እንደሻው እንዲለቀቁ መላላክ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀጠሉ ። እነአቶ ሥዩም ፣ የወረዳቸው ገዥ የነበሩት የደረሱበት ከጠፉ በኋላ ፣ የወረዳው ዋና ጸሐፊ በእነከበደ ጉዳይ እንዲረዳ ቸው በጉናቸው ለማሠለፍ ጥረት በጀመሩበት ሰሞን ፣

"ስማህ ፣ ወዳጄ ነህ" አሉና ሥዩም ፣ ራሳቸውን እያወዛ ወዙ ሲያተኩሩበት ቆይተው ፣ ንግግራቸውን በመቀጠል ፣ "ስማህ ጌታዬ ነህ ! ምንም እንኳን የሠፈራችን ነዋሪም ባትሆን በዚህ ወረዳ ሲፈጸምበት የኖረውን ግፍና በደል አሳምረህ ታውቀዋ ለህ ። የወረዳው ገዥም ከባለባቶቹ ጋር በጥቅም ስለ ተሳሰረ ፣ እያየ እንዳላየ ፣ እየሰማ እንዳልሰማ ሆኖ መኖሩን አትስተውም ። እንተም ሳይቆጭህ እንዳልቀረ አላጣነውም ።

"በኛ ላይ ሲፈጽም የኖረው ግፍም አስበርግጐት ይሽውና የወረዳው ገዥ ከተሠወረ ውሎ አደረ ። ታዲያ ምን ትጠብቃ ለህ ? በግፍ የታሠሩትንና የተጋዙትን ሰዎቻችንን ያሉበት እያ ፈላለግን ነውና ፣ አንተም ደግሞ ላቀችና ኩባንያዋ እንዳይሠወሩ ብን በዐይን ቁራኛ አስጠብቅልን ። ግደለህም ወሮታህን የም ንዘነጋም አይደለንም" አሉት ።

"እኔማኮ የሚረዳኝ ፣ የሚያማክረኝ ፣ አብሮኝ የሚደክም ሰው ካገኘሁ የእነ ከበደን ጉዳይ ለመከታተል አላመነታም ። ግን የወይዘሮ ላቀች ሰዎች ደግሞ በቀላሉ የሚደፈሩ አይደሉምና ፣ በተቻለ መጠን——" ብሎ ተናግሮ ሳያበቃ ፣ አቶ ሥዩም አቋ ረጡትና ፣

"እርሱን ርሳው ። እንኳን ላቀች ያ ሁሉ ባለሥልጣን እንኩትኩቱ ወጥቷል ። እነማን ቀሩ መሰለህ ? አንድ ሥሩ የተበጣጠሰ ዛፍ ብቻ ነው ቁሞ ሲወዛወዝ የምታየው ። እርሱም ነገ መገንደሱ አይቀርም ። ስለዚህ አትጠራጠር ። ጊዜ ፊቱን መልሶልናልና ፣ በግፍ የታሰሩትን ሰዎቻችንን እናፈላልጋለን ። ላቀችን ከነቅምጧና ከነአራጋቢዎቿ አስጠብቅልን" በማለት የወ ረዳ ግዛቱን ዋና ጸሐፊ ረዳትነት ካገኙ በኋላ ፣ ላቀችንና ሰዎ ቻቸውንም መከታተል ጀመሩ ።

በዚያ ወቅት ደግሞ ወይዘሮ ላቀች ፣ ሽዋዬና ፍጡርም ቢሆኑ እንቅስቃሴውን በዝምታ የሚመለከቱ አልነበሩም ። በየ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሠፈሩ እየዞሩ ከየመስሎቻቸውና ብጤዎቻቸው ጋር ሲንሾካሾኩ መዋልና እንዳንድ ቀንም በዚያው ማደር አዘውትረው ነበር ።

እነመቶ አለቃ ከበደ ፣ ከአዲስ አበባ ከተሠወሩበት ቀን ጀምሮ ፣ በመጀመሪያ ከፋ ክፍለ ሀገር ከተወሰዱ በኋላ ፣እንደገና ደግሞ አቶ እንደሻው ወደ ጐሬ ተወስደው በግዞት ሲጠበቁ፣ ከበደም በሐረር ክፍለ ሀገር ኦጋዴን ውስጥ በዐይነ ቁራኛነት ፣ ቀጥሎም በእስረኛነት እንዲጠበቅ ተወስኖበት ኖሩ ።

በዚህ ምክንያት የነበሩበት ባለመታወቁ እስከ ሐምሌ ወር መጨረሻ ድረስ ሲፈለጉ ቆይተው ፣ በነሐሴ ወር አጋማሽ ላይ ከነበሩበት ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ቻሉ ።

ምንም እንኳን ሁለቱን የዕድሩን ተቆርቋሪዎች ከግዞትና ከእስር ለማውጣት ሳይቻል ቢቆይም ፣ ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት እነአቶ ሥዩም የተቻላቸውን ያህል ውስጥ ውስጡን ሲደግፏቸው ኑረዋል ።

ነሐሴ ፮ ቀን የመቶ አለቃ ከበደ ከቤቱ ሲገባ ፣ ነሐሴ ፲፬ ቀን ደግሞ አቶ እንደሻው እቤታቸው ገቡ ። ይሁን እንጂ ፣የሁለቱን መፈታት ላቀች ቶሎ እንዳይሰሙ በምስጢር እንዲጠበቅ ተሞክሮ ነበር ።

በዚያው ሰሞን ደግሞ ወይዘሮ ላቀች ፣ "አሞኛል" እያሉ ዙረቱን ተወት አድርገው ከቤት መዋል አዘውትረው ነበርና ፣ ዘመድና ወዳጅም እየተመላለሰ ይጠይቃቸው ነበር ። ይኸው አጋጣሚም ደግሞ እነሸዋዬ ፣ እነደጃዝማች ፍጡርና ሌሎችም ቤተሰቦች ማታ ማታ እየተሰበሰቡ ፣ የከተማውን ወሬ የሚሰልቁበት ምቹ ጊዜ ሆኖላቸው ነበር ።

እንድ ቀን ፣ በሚሎናቸው ተሰብስበው ጠጅና ወሬ በሚያወራርዱበት ሰዓት ፣ በሳሎኑ ፊት ለፊትና በስተጓሮው መሣሪያ የያዙ ሰዎች ገብተው እንዳይንቀሳቀሱ አስጠነቀቁዋቸው ። በየነበሩበት ደርቀው ቀሩ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"በሉ እንድ ባንድ እየተነሣችሁ ውጡ" የሚል ትእዛዝ ከተሰጣቸው በኋላ ፣ ተወስደው በወረዳው ግዛት ጽሕፈት ቤት በአንድ ክፍል ውስጥ ተዘጋባቸው ።

* * *

"ቱቱቱ! ቱቱቱ! ዛሬ በሦስት ሰዓት የዕድራችን ስብሰባ ስላለ ፣ ሁላችሁም እንዳትቀሩ ተብሏል" የሚል ድምፅ ቱል ቱላውን እያስቀደመ ነሐሴ ፲፱ ቀን ፭፯ እሑድ ከንጋቱ ፲፮ ሰዓት ጀምሮ በሠፈሩ ማስተጋባት ጀመረ ።

የዚያ ዕለት ለፈፋ እንኳን ለወይዘሮ ላቀች ዕድርተኞች ለአካባቢው ነዋሪዎችም ብርቅና ድንቅ ሆኖ ነበር ። ዕድሩ ሰብ ሳቢ አጥቶ ዕድርተኞቹም ያለፈ ሒሳብ ጭምር እየከፈሉ በየእ ቅራቢያቸው በሚገኙ ዕድሮች ገብተው ፣ "የዕላፊ የመመዝገቢያ" እየተባሉ ሲከፍሉት የነበረው ሒሳብ ያስቆጣቸው አቶ ሺበሺ የተባሉ የወይዘሮ ላቀች ዕድርተኛ ግን ፣ ለባለቤታቸው ዝክር ተጠርተው የነበሩ ጐረቤቶቻቸውን ስብስበው ፣ ዕድርተኛ እክል ሲደርስበት እንጀራና ወጥ ፣ እንዲሁም በወር ሃምሳ ሳን ቲም የሚያስከፍል ደንብ አውጥተው ሐያ የሚሆኑ አባላት መዝግበው ለማቋቋም ሞክረው ነበር ።

ይሁን እንጂ ፣ ያም ሙከራቸው እንደ ከባድ ጥፋት ተቆ ጥሮ እንደነመቶ አለቃ ከበደ የሚወረወሩበት ስልት ሲቀየስላ ቸው ፣ የለውጡ ግፊት ተገን ሆኖላቸው ለመትረፍ ቻሉ ።

ከብዙ ወራት በኋላ ፣ በወይዘሮ ላቀች ዕድር የተሰማው ቱልቱላ ብርቅና ድንቅ የሆነባቸው ዕድርተኞች ፣ የዕለት ፕሮግ ራማቸውን እየሰረዙ ወደ ግራሩዋ ሥር ማዝገም ጀመሩ ። "ምን ድነውኮ ምክንያቱ! ሰብሳቢው ማነው?" የሚለው ጥያቄ የሰንቱ መነጋገሪያ አርእስት ሆኖ አረፈደ ። የዕድሩ ወንበሮችና እግዳሚ ዎችም ወደዚያው ሲጋዙ አረፈዱ ። ምንም እንኳ የዕለቱዋ ፀሐይ ከደመና ጋር ትንቅንቅ ገጥማ ካፊያና ብርድ አካባቢውን ለመቈጣጠር ቢጣጣሩም ቅሉ ፣ የዕድሩ ቱልቱላ ያስተጋባው የምሥራች የሠፈሩን ነዋሪ ወደ ግራሩዋ ሥር እንዳይሔድ ሊከ ለክሉ አልቻሉም ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የወይዘሮ ላቀች ዕድርተኛ ብቻ ሳይሆን ፣ የሠፈሩም ነዋሪ ወንበሩን ከየቤቱ እየተሸከመ ወደ ግራሩዋ ሥር ማዝገም ጀምሩ ዋል ። ከዚያ በፊት ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ከሰማየ— ሰማያት የወረደ ፍጥረት ለማየት የተጠራ ይመስል ፣ ሴቱ ወጣቱ ፣ አዛውንቱ ፣ እንካሳው ፣ ዐይነ ሥውሩ ይንዛሉ ።

"ዓመቱ መቼም አዲስ ነገር የምንሰማበትና የምናይበት፣ ሆኗልና ፣ ዛሬ ደግሞ ምን አዲስ ነገር ያሳየንና ያሰማን ይሆን?" ሲል አንዱ ፣

"ወረዳው ወይዘሮ ላቀችን ሽረናልና ሌላ ዳኛ ምረጡ፣ ይለን ይሆን?" ይላል ሌላው ።

"እኔ ደግሞ አዲስ ነው ፣ ዕጩ ድንቅ ነው የምለው ፣ ላቀች ከነአጃቢዎቿ ተያዘች ቢሉኝ ነበር" ሲል አንዱ ፣ አብሮት የነበረው ደግሞ ፣

"መያዟማ የት ይቀራል? ጊዜ ትፈጃለች እንጂ!" ይለዋል ።

አቶ ሥዩምና አቶ ዘይኑም እንደ ተለመደው ጐን ለጐን ተቀምጠው የተሰብሳቢዎቹን ጭውውት እያዳመጡ ፣ እርስ በር ሳቸው አንዳንድ ጨዋታ እየተለዋወጡ ፣ ሲታገሉበትና ሲደክ መበት የነበረው ጉዳይ የመጨረሻ አልባት የሚያገኝበትን ደቂቃ በጉጉት በሚጠባበቁበት ሰዓት ፣ አቶ ስለሺ ከአጠገባቸው ሲቀ መጡ ፣

"ይኸውልዎ ዛሬ አዲስ ነገር ልናይ ፣ አዲስ ነገር ልንሰማ ተቃርበናል" አሉዋቸው ሥዩም ፣ ከሰላምታ ቀጥለው ።

"ምንድነውክ ነገሩ? የሚሰማው ጭምጭምታ እውነት ነው?" ብለው ጠየቁ ስለሺ ።

"ምንድን ነው የሰሙት?" አሉ ዘይኑም እየተፍነከነኩ ።
"የእነ ከበደ ነገር የሚወራው እውነት ነው?" አሉ ስለሺ።

"ምን የማይሆን አለ ብለው? ብቻ ትዕግሥት ይስጠን እንጂ!" አሉ ሥዩም ፣ ከንፈራቸውን ነክሰው ራሳቸውን በዛቻ እየነቀነቁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በሴቶቹ አካባቢ ደግሞ ፣ "ሁለቱም ናቸው የመጡት ። አቤት ክሳታቸው ! አቤት ንጣታቸው ! አቤት ?" ይባባላሉ ። በአካባቢዋ የነበረው ሠፈርተኛ የግራሩዋ ሥር አልበቃ ብሎት እርስ በርሱ እና ላፍ ገጥሞ በመንሾካሾክ ላይ እንዳለ የወረዳውን ጸሐፊ አቶ ይጥናና ሌሎች ሰዎች እጅበውት ወደ ግራሩዋ ሲያ መሩ በቅርብ ርቀት ታዩና ፣ የተሰብሳቢው ሹክሹክታ ወደ ጉር ምርምታ ተለወጠ ።

አቶ ሥዩምና አቶ ዘይኑ ፣ እንደዚሁም ጉዳዩን ያወቁት ሌሎች ዕድርተኞች ፣ ከየመቀመጫቸው እየተነሡ ሞብጨባ ሲጀምሩ ፣ ተሰብሳቢውም ተቀበላቸው ። የሴቱ ዕልልታ ጀመረ፣ ሞብጨባው ከዳር እስከ ዳር ተቀጣጠለ ። የወረዳው ጸሐፊ አጀብ ወደ ግራሩዋ ሲቃረብ ደግሞ ፣ ተሰብሳቢው ደስታ እየፈነቀለ ያስ ነጣው ጀመር ። ወዲያው ከወረዳው ጸሐፊ ግራና ቀኝ የነበሩት ሁለት ሰዎችም በደስታ እየዘለሉ ከተሰብሳቢው መካከል ገቡ ። ዕንባና ሣቅ ተቀላቀሉ ።

ከደቂቃዎች ትርምስ በኋላ ፣ የወረዳው ጸሐፊ ጸጥታ ጠየ ቅና ሁሉም ሲቀመጥ ፣ የመቶ አለቃ ከበደና አቶ እንደሻው በግ ዞትና በእሥራት ያሳለፉትን ሥቃይ እየዘረዘረ ማስረዳት ሲጀምር፣ ወይዘሮ ላቀችን ፣ ሸዋዬንና ደጃዝማች ፍጡርን ደግሞ ፖሊሶች እየነዱ ብቅ አሉ ።

ቱማና ሲቃ ተቀላቀሉና የግራሩዋን ሥር አተራመሱት ። አንዳንዱ ከተቀመጠበት ሲነሣ ፣ አንዳንዱ እንደ ተቀመጠ ይፈጭሳል ፣ ሌላው ይሳደባል ፣ የባሰበት ይራገማል ።

የሰባት ወራት ድንጋጤና የሐሳብ ውዝዋዜ ያደረቃቸው ላቀችና እጀቢዎቻቸው ከግራሩዋ ሥር ሲደርሱ ፣ ፉጨትና ዕል ልታ ተቀበሉዋቸው ።

"እንኳን ለዚህ ያደረሳችሁ! እንኳን የወንድ እጅ ለመቅ መስ ያበቃችሁ! እንኳን የሕግን የበላይነት ለማወቅ ያበቃችሁ! ሸዋንግዛውስ የታለ ? እርሱንም እንፈልገዋለን" የሚሉ ቃላት አስታጋቡ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የወረዳው ጸሐፊ ፣ እንደገና የተሰብሳቢውን ጸጥታ ጠየቀና ባደረገው ንግግር ፣ "ከዛሬ ጀምሮ የዕድራችሁን ፣ ዳኛ ፣ ጸሐፊና ገንዘብ ያዥ ራሳችሁ ትመርጣላችሁ ። እስከ ዛሬ የከፈላችሁት ንም ገንዘብ ተሳስባችሁ ከእነዚሁ ሰዎች ትቀበላላችሁ" ብሎ ተቀመጠ ።

"ፊታውራሪ ሽዋንግዛውንና አቶ ይጥናንም እንፋረዳቸዋ ለን" ሲሉ እንዲት ሴት ፣ የወረዳው ጸሐፊ እንደገና ተነሥቶ ፣

"ፊታውራሪ ሽዋንግዛው ተይዘው ከሌሎች መሰሎቻቸው ጋር በእስር ላይ ናቸው ። በሌላ ጊዜ ይቀርቡላችኋል ። አቶ ይጥ ናም እዚሁ ከመካከላችሁ ይነሮሉ" ብሎ ተቀመጠ ።

ይጥና ከነበሩበት ተነሥተው ከተሰብሳቢው ፊት ቀረቡና፣ "እኔማ ተጐትቼ ከመምጣት ብዬ ይኸውና መጥቻለሁ" ብለው ይዘውት ከነበረው ማጎደር አንድ ወቀረት አወጡና ተመለካከ ተው ፣

"ዕድሩ ለድኻን መጣዣ ፣ ለልማት ሥራና ለወር ክፍያ ያዋጣውንና እርተዛሬ የተሰበሰበውን ፣ እንደዚሁም ከሌሎች የዕድር ገንዘብ ያጐች በብድር ስም የወሰድነውን በድምሩ ሐያ ሰባት ሺህ አራት መቶ ብር ከዜሮ አምስት ሳንቲም ለወይዘሮ ላቀች አስረክቢያለሁ ። ለዚሁም ደረሰኝ አለኝ—" ብለው ፣ ንግግራቸውን ሊቀጥሉ አፋቸውን ሲከፍቱ ዝንብ ገባችባቸውና፣ እርሷን ሊያስወጡ ፊታቸውን አዙረው ሲያንሩ ፣

"ዕድርተኛውም ሁሉ ገንዘቡን ያስመልስዎታል" አሉ ሥዩም ።

ወዲያው አንድ ዕድርተኛ ተነሡና ፣"የተበላውን ገንዘባች ንን በሌላ ጊዜ እንተሳሰባለን ። ለደረሰብንም ግፍ ፍርድ እንጠ ይቃለን ። ለእሁኑ ግን የዕድራችንን ኃላፊዎች እንምረጥ" ብለው ሲቀመጡ ፣ አቶ ሥዩም ፈጥነው ብድግ አሉና ፣

"ለማችሁ ፣ ዕድርተኞች ! ለዚህ ዕድር ክብርና ዕድገት እነ ዚህ ሁለት ሰዎች ያደረጉትን ጥረትና በመጨረሻም የደረሰባ ቸውን ግፍ ታውቁታላችሁ ። ለብዙ ዓመታት ተሠቃ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይተውለታል ። ቤተሰቦቻቸውንም በዚህ ሠፈር እንዳይታዩ እነ ዚህ ግፈኞች አባርረዋቸው ፣ ያው እንደምታውቁት የተቻለንን ያህል ውስጥ ለውስጥ እያዋጣን ስንረዳቸው ቆይተናል ። ዛሬ ለዚህ ካበቃን ደግሞ የዕድራችን ዳኛ የመቶ አለቃ ከበደ ፣ጸሐፊ አቶ እንደሻው ቢሆኑና ገንዘብ ያዥውን ደግሞ ሌላ ጊዜ ብንመ ርጥ ቅር ትሰኛላችሁ?" ሲሉ ፣ እንዲት ሴት ደግሞ ተነሡና ፣

"ለገንዘብ ያዥነቱም እርስዎን መርጠናል" አሉ ።

"ተስማምተናል" ከሚል ድምፅ ጋር ጭብጨባው አስተጋባ።

የመቶ አለቃ ከበደ ከተቀመጠበት ተነሣና ፣ ወደ አቶ አር ጋው ሔዱ ከማጎደራቸው ውስጥ አንድ ወረቀት ወሰደና ከተሰ ብሳቢው ፊት ቆሞ ፣

"እኅቶቼና ወንድሞቼ! እንኳን ዐይን ለዐይን ለመተያዬት ያበቃን ። በኛ ሠፈርና ዕድር ብቻ ሳይሆን ፣ በመላ ሀገሪቱ ላይ ሲፈጸም የኖረው ግፍና በደል ተጠራቅሞ የፈጠረው እንቅስ ቃሴ ፣ እኛን ብቻ ሳይሆን ብዙ ወገኖቻችንን ነጻ አውጥቷል ። እኛም መንግላታታችን ፣ ቤተሰቦቻችን መጉላላታቸው አይቆጨ ንም ። ለዚህ ዕለት በመድረሳችን ከልብ ተደስተናል ። ዋናውም ጉዳይ ይኸው ነው ። የጣላችሁብንን ኃላፊነት ተቀብለናል ። ከዛሬ ጀምሮ ግን ፣ ይህን ባለርስቶች ያወጡብንን ደንብ ቀደነዋል" አለና ያን ወረቀት ቀዳዶ ለወይዘሮ ላቀች ሲሰጣቸው ፣ ጭብጨ ባውና ሁካታው አስተጋባ ። መቶ አለቃ ከበደም እንደገና ወደ ዕድርተኛው መለስ ብሎ ፣ ከዛሬ ጀምሮ ዕድራችንን "ዕድገት ባንድነት' ብለነዋል" ሲል ፣ እንደገና ጭብጨባና ዕልልታ ነጐደ።

ወይዘሮ ላቀች ፣ ከነአሽቢዎቻቸው ከዕድርተኛው ፊት እንደ ቆሙ ፣ ዕንባ ተናንቋቸው በመሐረማቸው ዐይኖቻቸውን ሲያባ ብሱ ፣ ደጀዝማች ፍጡርም የዕንባ ዘለላዎቻቸውን ጠራረጉ ።

የወረዳው ጸሐፊ ደግሞ ተነሣና ፣ "እንግዲህ ዕድራችሁ ነጻ ወጥቷል ፤ እነዚህንም በዳዮቻችሁን በእስር ቤት እናቆይላ ችኋለንና ፣ ሒሳባችሁን ትተሳሰባላችሁ ። ለዛሬ ስብሰባው አብ ቅቷል!" አለ.....

ተፈጸመ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF